
የዳንኤል እይታዎች Daniel Kibret's views
ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባሕል፣ እምነት፣ ፖለቲካ እና
ትውፊት ምልከታዎች ይቀርቡበታል
This blog will reflect my views on Ethiopia's culture, politics,
religion and tradition.

1. ይምርሃነ ክርስቶስ- የተሠወረ ሥልጣኔያችን 4
2. ለምጣዱ ሲባል 7
3. ቶም እና ጄሪ 10
4. መመረሽ፣መፈረሽ፣መደንበሽ 14
5. ገድለ ዜና ማርቆስ የያዛቸው መረጃዎችና ሁነቶች 18
5.1. መግቢያ 18
5.2. የመጽሐፉ ጸሐፍት 18
6. ጲላጦስ 27
7. የኔ ጀግና :- ይድረስ ለ CNN ቴሌቭዥን ጣቢያ 31
8. አሜሪካን ያገኙት ማነው? 34
9. ባሕር ዛፍ 42
10. ለዘብተኛነት/ሊበራሊዝም/፡የክርስትና ዘመናዊው ጠላት 45
11. መንፈሳዊ ወይስ መንፈሳይ? 54
12. የመቅደላው ጌታ 57
13. ባልን ማን ፈጠረው? 60
14. ገንዳ : (በተለይ ሻማ ሆነው በጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ) 63
15. ፊደል እያለው የማያነብ ማነው? 66
16. ኦርቶዶክሳዊ መምህር፣ ዕውቀቱ እና ክሂሎቱ :- ማስተማር ምንድን ነው? 71
17. ትልቅ ሰው : -እንዲህም ሆነ 80
18. ስማችሁ የለም 84
19. ሥጋ በል ዕጽዋት 87
20. ቅዱስ ያሬድ ማነው? 92
20.1. ያሬድ ክብር አነሰው 92
21. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ 97
22. አለቃ ተክሌ 105
23. ሀገር እንወዳለን 111
24. ፕሮፌሰር ሳቤክ 115
25. አለቃ ገብረ ሐና ተረት ናቸው እውነት 118
26. ተሳቢ 126
27. ዝምታ ወርቅ አይደለም 129
28. የዓለም ዋንጫ በኢትዮጵያ 132
29. ወንበሩ ነው እንዴ? 138
30. 171ኛው ሆስፒታል 141

31. ኤልዛቤል ከታሪክ አንድ ገጽ : 144
32. ጤፍ እና እንጀራ 146
33. በሰይጣን እጅ የወደቀ ቅርስ 149
34. በአንድ ሱቅ ታዛ ሥር 150
35. ሰው በቁሙ ሐውልት ለምን ያሠራል? 159
36. የአንድ አባት ምክር 162
37. ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው 163
38. የብርጭቆው ወይስ የምንጩ ውኃ 166
39. ቅኝ አልተገዛንም? 192

1. ይምርሃነ ክርስቶስ- የተሠወረ ሥልጣኔያችን

ከአዲስ አበባ በባሕርዳር፣ ጎንደር፣ ላሊበላ በኩል ወደ አኩስም የሚወስደውን የተለመደውን የቱሪስቶች የጉዞ መሥመር ተከትለን ነበር የተጓዝነው፡፡ እኛ ላሊበላ ላይ ወርደን ጉዟችንን ወደ ይምርሃነ ክርስቶስ አደረግን፡፡

ወደ ይምርሃነ ክርስቶስ ለመድረስ ከላሊበላ ወደ ሰቆጣ የሚወ ስደውን መንገድ ይዘን ለ30 ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ ብል ብላ ከተባለችው ከተማ ደረስን፡፡ ከዚያም ዋናውን መንገድ ትተን ወደ ምሥራቅ ተገነጠልን፡፡ መንገዱ ወደ ይምርሃነ ክር ስቶስ ቱሪስቶችን ለማጓጓዝ እንዲረዳ በአካባቢው መስተዳድር የተጠረገ መንገድ ነው፡፡ ከብልብላ በኋላ 7 ኪሎ ሜትር እንደ ነዳን ጥንታዊውን የንጉሥ ይምርሃነ ክርስቶስ ከተማ ዛዚያን በሩቁ አየናት፡፡ አሁን ለምልክት ከሚታየው እና የኢያቄም ወሐና ማኅበር በብረት ፍርግርግ ለማስታወሻ ካሠራው አነሥተኛ ጎጆ እና በዙርያው ካለው ዐጸድ በስተቀር ሌላ ምልክት አይታይበትም፡፡ቀሪውን ስድስት ኪሎ ሜትር ስናጠናቅቅ ከፊታችን ጥቅጥቅ ያለው ደን ገጭ አለ፡፡ 1526 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው እና በተራራው ላይ የተዘረጋው ጥንታዊ ደን በሀገር በቀል ጽድ እና ወይራ የተሞላ ነው፡፡መነኮሳቱ ደኑን የተከለው ንጉሥ ይምርሃነ ክርስቶስ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ከመኪና ወርደን ባሕል እና ቱሪዝም ባሠራው የእግረኞች መንገድ በኩል ተራራውን መውጣት ጀመርን፡፡ጸጥ ባለው አካባቢ የአእ ዋፍን ድምጽ ብቻ ነው የምትሰሙት፡፡1ኪሎ ሜትር ያህል እየተጠማዘዛችሁ ተራራውን ትወጣላችሁ፡፡

የእግር መንገዱን አጠናቅቃችሁ ከተራራው ወገብ ስትደርሱ «ውግረ ስሂን» የሚባለውን ዋሻ ከሩቁ ታዩታላ ችሁ፡፡ የወለል ስፋቱ 50 ሜትር በ38.75 ሜትር የሆነው ይህ ሰፊ የተፈጥሮ ዋሻ ዙርያው በቋጥኝ የታ ጠረ ነው፡፡በስተ ምዕራብ በኩል የዋሻው ከፍታ እስከ 7.7 ሜትር ይደርሳል፡፡በስተ ምሥራቅ በኩል ዋሻውን ውስጥ ለውስጥ እስከ አቡነ ዮሴፍ ተራራ የሚያገናኝ የውስጥ ለውስጥ መንገድ እንዳለው መነኮሳቱ ይናገራሉ፡፡ የገዳሙ ዲያቆናት ችቦ አብርተው የዋሻውን መጨረሻ ለማግኘት ገብተው ነበር፡፡ውስጥ ለውስጥ አራት ሰዓት ተኩል ያህል ከተጓዙ በኋላ ችቦው እያለቀባቸው ሲመጣ ጊዜ መመለሳቸውን የአካባቢው ሰዎች ይተርካሉ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የውስጥ ለውስጥ መንገዱ መግቢያ በደለል እየተደፈነ ይገኛል፡፡በአስቸኳይ ጥናት ማድረግ ካልቻልን እንደተሠወረ የሚቀር ብዙ ታሪክ አለ፡፡

ዋሻው የታጠረበትን የ1979ዓም የብሎኬት አጥር አልፋችሁ ስትገቡ ዓይናችሁ ሊነቀልበት የማይችለውን የ12ኛው መክዘ ሥልጣኔያችንን ታያ ላችሁ፡፡

የቤተ መቅደሱ ድንቅ ጥበብ በውኃ ላይ ከመሠራቱ ይጀምራል፡፡ ዋሻው ውስጥ ተዘርግቶ የነበረው ሐይቅ በላዩ ላይ በእንጨት እና በድንጋይ ተረብርቦ ነው ቤተ መቅደሱ የተሠራው፡፡ የኋላ ዘመን ትውልድ አያምነንም ብለው አስበው ይመስለኛል ከሥሩ የሚገኘውን የውኃ አካል ለማየት እንዲቻል ስትገቡ በስተ ግራ በኩል በእንጨት በር የሚዘጋ ጉድጓድ ትተውልናል፡፡ የአካባቢው ሰዎች እንደሚሉት እና በመጠ ኑም ማየት እንደሚቻለው በባሕሩ ላይ እንጨት፣ በእንጨቱም ላይ ሣር፣ በሣሩ ላይ ጭቃ፣ በጭቃውም ላይ ደረቅ አፈር፣ በአፈሩ ላይ ንጣፍ ድንጋይ ተደል ድሎ ነው የተሠራው፡፡ ወደ መቅደሱ ገብታችሁ በባዶ እግራችሁ ከቆማችሁ ቅዝቃዜው ይሰማችኋል፡፡

በባሕሩ ላይ የተረበረበው እንጨት በምን መሠረት ላይ ቆመ በእውነትም እንጨት ከሆነ ለአንድ ሺ ዓመታት እንዴት ቆየ? ተመራማ ሪዎችን የሚፈልጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የይምርሃነ ክርስቶስ ቤተ መቅደስ ውቅር አይደለም፡፡ጥንታዊው የኢትዮጵያውያን የሥነ ሕንፃ ጥበብ የተንፀባረቀበት ግንባታ ነው፡፡ ውጫዊ ስፋቱ 12.22 በ9.54 ሲሆን ከወለሉ እስከ ጣራው ያለው ከፍታ ደግሞ 5.88 ሜትር ያህላል፡ ፡ ከዕጽዋት፣ ከወጥ ድንጋዮች እና ከኖራ መሰል ነገር የተሠሩ 26 መስኮቶች ዙርያውን አስውበውታል፡፡ እነርሱም በሰሜን 8፣ በምሥራቅ 6፣ በደቡብ 7፣ በምዕራብ 5 ናቸው፡፡ ጠቢቡ አምስት ስድስት፣ ሰባት እና ስምንት ቁጥሮችን በቅደም ተከተ ላቸው የመረጠበት ምክንያት ምን ይሆን? ከ26ቱ መስኮቶች መካከል 22ቱ ሲከፈቱ አራቱ ግን አይከፈቱም፡፡ የአንዱ መስኮት ዲዛይን ከሌላው መስኮት ዲዛይን ስለሚለያይ ለሃያ ሁለቱ መስኮቶች ሃያ ሁለት ዓይነት ዲዛይን ነው የምናየው፡፡ የዘመኑ ጠቢባን ጥበባቸውን ለማሳየት ምን እንደተጠበቡ ያመላክታል፡፡

ቤተ መቅደሱ ደቃቅ፣ መጠናቸው የተመጣጠኑ ጥቋቁር ድንጋዮች በጭቃ እየተጣበቁ ነው የተገነባው፡፡ እንዴት ይሆን ጭቃ እና ድንጋዩን አቡክተው ያጣበቋቸው? የጭቃው ግንባታ ለ25 ሳሜትር ያህል ወደ ላይ ከተጓዘ በኋላ በአራት መዓዝን የተጠረበ ወጥ እንጨት ይገባበታል፡፡ እንዲህ እያለ ድንጋይ፣ ጭቃ እና እንጨት በጥበብ ተስማምተው ይምርሃነ ክርስ ቶስን ለሺ ዓመት ያህል አቁመውታል፡፡ እኔን የገረመኝ ነገር ቢኖር ዛሬ ዛሬ በስሚንቶ እና በድንጋይ የተሠሩት ሕንፃዎቻችን ዓመት ሳይሞላቸው ሲሰነጠቁ ጭቃውን ከድንጋይ እና እንጨት ጋር አዛምደው ይህንን ያህል ዘመን ያቆዩበት ጥበብ ምን ይሆን? የሚለው ነው፡፡ እንዲህ እየተያ ያዘ የተገነባው ግድግዳ ኖራ በሚ መ ስል ነጭ ነገር ከውጭ እና ከውስጥ ተለስኗል፡፡ የልስኑ ንጣት እና የእንጨቱ ወርቃማ ቀለም ለቤተ መቅደሱ ውጫ ዊ ገጽታ ዓይን እንዳይነቀል የሚያደርግ ውበት ሰጥቶታል፡፡

በምዕራብ እና በምሥራቅ ሁለት ሁለት ፎቆችን ያዘለው ሕንፃ ወለሉ እጅግ ለስላሳ በሆኑ ድንጋዮች ንጣፍ የተሠራ ነው፡፡ እጅግ የሚያስደንቀውን ሌላ ጥበብ የሚያዩት ደግሞ ወደ በሩ ስትዞሩ ነው፡፡ ከአንድ ወጥ እንጨት የተሠራው በር፣ ከግድግዳው ጋር አንድ ሺ ዘመን በሆናቸው ብሎኖች እየታሠረ በታጣፊ ብረት ተያይዟል፡፡በዚያ ዘመን እንጨት ሠርስረው የሚገቡ ብሎኖችን የመሥራት ጥበብ ነበረን ማለት ነው? በሩን ለመዝጋት ከእንጨት የሠሩት ጥንታዊ ቁልፍ እጅግ አስደናቂ ነው፡፡ የቁልፉ መግቢያ ቀዳዳ እንደ ዘመ ናዊው ቁልፍ የተገለበጠ ቅል ቅርጽ አለው፡፡ በዚያ ዘመን የነበረውን የቁልፍ ቴክኖሎጂ የታሪክ ምሥክር ሆኖ ያሳየናል፡፡

የቤተ መቅደሱን ውስጣዊ ጥበብ ለማየት ከአንድ ወር በላይ ይፈጃል ባይ ነኝ፡፡ የዘመኑ ጠቢባን ያለ ጥበብ ያለፉት አንድም ክፍት ቦታ አይገኝም፡፡ጣራው፣ ግድግዳው፣ ወለሉ፣ ዓምዶቹ በሮቹ እና መስኮቶቹ ሁሉ አንዱ ከሌላው የማይገናኝ ጥበብ ፈስሶበታል፡፡ የመቅደሱ መካከለኛ ቦታ ከተጠረበ እና ለስላሳ ከሆነ እንጨት የተገጣጠመ ሲሆን ክብ ሆኖ የታነፀ ነው፡፡ ውስጡ በመንፈሳዊ ሥዕሎች ያጌጠ ሲሆን የሚዘጋው በመጋረጃ ነው፡፡

የቤተ መቅደሱን ጣራ የተሸከሙት ዓምዶች በባለሞያ ከተጠረቡ ለስላሳ፣ ጠንካራ፣ ሰፋፊ እና ከባድ ከሆኑ የከበሩ ድንጋዮች የታነጹ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ዓምድ ልዩ በሆነ ሐረግ እና ሥዕል የተጌጠ ነው፡፡ የአንዱ ዓምድ ዲዛይን በምንም መልኩ ከሌላው ጋር አይያያዝም፡፡ የቅድስቱ ጣራ በስምንት ክፍል የተከፈለ እ ያንዳንዱ ጣራ የራሱ የሆነ ልዩ ዲዛይን እና ሥዕል አለው፡፡ አሁን አሁን ከአቧራ እና ከክብካቤ እጦት የጣራው ላይ ድንቅ ሥዕሎች እና ቅርጾች እየደበዘዙ ናቸው፡፡

በጣራው ውስጣዊ ገጽታ ከጣራው ጋር ተያየዘው ወደ ታች በወረዱ አራት መዓዝን በሆኑ ሁለት የእንጨት ገመዶች የተን ጠለጠሉ ዕንቁዎች አሉ፡፡ ከሁለቱ በአንደኛው ገመድ ላይ የተንጠለጠሉትን ዕንቁዎች በ1986 አካባቢ ሌቦች የወሰዷቸው ሲሆን እንዳይታወቅ ተመሳሳይ ነገር ተከተውበት ነበር፡፡

ውሳጣዊውን ክፍል ስታዩ በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ዘጠና፣ አርባ አምስት እና አንድ መቶ ሰማንያ ዲግሪዎችን ጠብቀው የጣራውን ከበብ፣ የዓምዶቹን መዓዝን እና የመስኮ ቶችን ቅርጽ ለመሥራት የተጠቀሙበት የጂ አሜትሪ ጥበብ ምን ይሆን? ምናለ ሕንፃውን እን ዳገኘነው ሁሉ ጥበቡንም አብረን ባገኘው? ያሰኛ ችኋል፡፡ ለመሆኑ ይህንን ሕንፃ ከማነፃቸው በፊት ዲዛይኑን በምን ሠሩት? ጣራውን ሲያንፁ የተጠቀሙበት የመደገፊያ እና የኮንክሪት ጥበብስ ምን ይሆን?

ቤተ መቅደሱ ውስጥ ሁለት ጥንታውያን የእንጨት ሳጥኖች ይገኛሉ፡፡ ዛሬ ዛሬ ለዕቃ ማስቀመጫነት በሚጠቀሙባቸው እነዚህ ሳጥኖች ላይ የሚታየው ቅርጻ ቅርጽ እና በሕንፃው ጣራ ላይ የሚታየው ቅርጻ ቅርጽ ተመሳሳይነት አለው፡፡ እንደ እኔ ግምት ከሆነ እነዚህ ሳጥኖች የሕንፃው ንድፍ የተቀመጠባቸው ሳጥኖች ይመስሉኛል፡፡ ጠቢቡ ሕንፃውን ሲያንፀው ምናልባት በእንጨቱ ላይ የሠራውን ዲዛይን እየተከተለ ይሆናል፡፡

ከቤተ መቅደሱ ጎን ያለው፣ዛሬ በዕቃ ቤትነት የሚያገለግለው እና ይምርሃነ ክርስቶስ በቤተ መንግሥትነት ይጠቀምበት ነበር የሚባለው ሕንፃ ግን እጅግ ተጎድቷል፡፡ ሌላው ቀርቶ አቧራውን እንኳን በዘመናዊው የአቧራ መጥረጊያ ማሽን በአንድ ቀን ማስለቀቅ በተቻለ ነበር፡፡ በዚሁ ከቀጠለ ከአሥር ዓመታት በኋላ የምና ገኘው አይመስለኝም፡፡

ይምርሃነ ክርስቶስ በ939 ዓም አካባቢ ተወልዶ በ1036ዓም አካባቢ ያረፈ የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ንጉሥ ነው፡፡ የነገሠው በ996 ዓም አካባቢ ሲሆን ቤተ መቅደሱን ያነፀው በ1018 ዓም አካባቢ መሆኑ ይነ ገራል፡፡ የላሊበላ አብያተ መቅደስ ተጠናቀቁበት ከሚባ ለው ዘመን 1193 ዓም ጋር ስናስተያየው ቢያንስ የሰባ ዐመት ቅድሚያ አለው ማለት ይቻላል፡፡

ይምርሃነ ክርስቶስን የሥነ ሕንፃ፣ የአርክቴክቸር እና የአርኬዎሎጂ ባለሞያዎች ሊጎበኙት ለዛሬው ሥራችን የሚጠቅምም ሀገራዊ ጥበብ ሊሸምቱበት ይገባል ባይ ነኝ፡፡ የባለ ሞያዎችን ጥናት እና ምላሽ የሚፈልጉ አያሌ ጥበቦች የፈሰሱበት ሕንፃ ነው፡፡ በተለይም ቦታው ዋሻ ውስጥ በመሆኑ እና ከተራራ ግርጌም በመደበቁ ከብዙዎቹ የእርስ በርስ ጦርነቶች ተርፎ ታሪኩን እንደያዘ ይገኛል፡፡በመሆኑም ከአካባቢው የተሻሉ መረጃ ዎችን ይሰጣል ባይ ነኝ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለአካባቢው ታሪክ እና ቅርስ ትኩረት በመስጠት መንገዱን ለማ ሠራት፣ አካባቢውን ለመጠበቅ፣ ለማስተዋወቅ እና ለመከባከብ የክልሉ ባሕል እና ቱሪ ዝም የሰጠው ትኩረት የሚደነቅ ነው፡፡

2. ለምጣዱ ሲባል

በትግራይ የሚነገር አንድ ብሂል አለ፡፡ አንድ ባል እና ሚስት አንዲት ትንሽ አይጥ አስቸገረቻቸው፡፡ አንድ ቀን ባል እና ሚስቱ ዱላ ዱላቸውን አንስተው የቤቱን ዕቃ ሁሉ ገልብጠው አይጧን ማሳደድ ጀመሩ፡፡ በዚህ ሲሏት በዚያ፣ በዚያ ሲሏት በዚህ ብዙ እያለች በጣም አደከመቻቸው፡፡ በመካከሉ ሚስቲቱ አይጧን ስታባርር አይጧ ዘልላ ምጣዱ ላይ ወጥታ ቁጭ አለች፡፡ ሚስቲቱም የሠነዘረችውን ዱላ ወደ ኋላ መልሳ፣ አይጧን በአግራሞት ማየት ጀመረች፡፡ ባልዋም የሚስቱን ሁኔታ ተመልከቶ «ምነው ትቆሚያለሽ አትያትም ወይ?» አላት፡፡ ብልኋ ሚስትም «መምታቱ አቅቶኝ አልነበረም ነገር ግን «**ምእንቲ ዛ ምንጎ እታ አንጭዋ ትሕልፍ**» አለችው ይባላል፡፡ «***ሰለ ምጣዱ ሲባል ኣይጧ ትለፍ ብዬ ነው***» ማለቷ ነው፡፡

ለዚያች እናት ምጣዱ የትዳሯ ትልቁ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ እንዲህ እንደ ዛሬ እንጀራ ተገዝቶ መበላት ሳይ ጀምር በፊት ያልጋገረ ሰው እንጀራን አያገኘውም፡፡ ከዚያውም በላይ ደኅነኛ ምጣድ ከገበያ እንደ ልብ አይገኝም፡፡ ቢገኝም ማሚሾቱ ብዙ ሞያ እና ድካምን ይጠይቃል፡፡ እናቶቻችን ወዝ የለመደ ምጣድ የሚሉት አላቸው፡፡ የጋጋሪዋን ወዝ የለመደ፣ ጋጋሪዋም ጠባዩን የለመደችው ምጣድ ማለት ነው፡፡ እንዲያውም እንዲህ ያለው ምጣድ የትም ስለማይገኝ ለድግስ ሥራ ሲጠሩ የራሳቸውን ምጣድ ይዘው ሄደው የእነርሱን ድርሻ በለመዱት ምጣድ የሚጋግሩ እናቶች ነበሩ፡፡ አሉም፡፡ ለዚህ ነው ያቺ እናት «ምእንቲ ዛ ምንጎ እታ አንጭዋ ትሕልፍ» ያለችው፡፡

ገበሬ እንኳን እርሻውን ሲያርም ሁሉንም ነገር አያርመውም፡፡ አንዳንዱን አረም ተስማሚውን ጊዜ በመፈለግ ያልፈዋል፡፡ አንዳንዱ እንደ እንክርዳድ ያለው አረም ከእህሉ ጋር ሥር ለሥር ይያያዝና ለእርማት ያስቸግራል፡፡ አንዳንዱም በጣም ጥቃቅን አረም ከመሆኑ የተነሣ ያንን አረም በማረም የሚፈጀው ጊዜ አረሙ ቢታረም ከሚያስገኘው ጥቅም ስለሚበልጥበት ይተወዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ዋና ዋናውን አረም ያርምና ያንን ያልፈዋል፡፡ የማሳ እና የሰው ንጹሕ የለውም ነውና የገበሬው ብሂል፡፡ እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውንም አብራችሁ እንዳትነቅሉት እንደተባለው፡፡ እንዲህ ያለውን አረም ከእህሉ የሚያስወግደው በመከር ጊዜ እያበራየ ነው፡፡

በትዳር ውስጥ ያሉ ባል እና ሚስት ትዳራቸውን አጽንተው ለመኖር ከፈለጉ ከሌሎች ብዙ ነገሮች ጋር ሊከተሉት የሚገባው ነገር አንዱ «ምእንቲ ዛ ምንጎ እታ አንጭዋ ትሕልፍ» የሚለው ነው፡፡ የተጋቡት ሰዎች ፍጹማን እና እንከን የለሾች አይደሉም፡፡ በእያንዳንዷ ስሕተት እና ጉድለት ላይ በመነታረክ፣ እያንዳንዷን ጥፋት እየቆጠሩ ነጥብ በማስቆጠር፤ ትዳርን አጽንቶ ማኖር ከባድ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለምጣዱ ሲባል አይጧን ማሳለፍ የሚገባበት ጊዜ አለ፡ ፡ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚሠራው ይሳሳታል፡፡ ዐውቆ የሠራውን በተግሳጽ ሳያውቅ የሠራውን ግን አሳልፎ በመነጋገር መፍታቱ የተሻለ ነው፡፡

በተለይም ሰው በተሳሳተበት ጊዜ ቢነግሩት የማይሰማቸውን ጉዳዮች አውለው አሳድረው ፣ነገር አብርደው እና ዘና አድርገው ቢነግሩት ነጠብጣብ እንደ ወረደበት መሬት በሚገባ ይቀበለዋል፡፡ እሳትን በእሳት ማጥፋት፤ ውኃንም በውኃ ማቆም አይቻልምና፡፡ ትዳርን ያህል ትልቁን ምጣድ ላለመስበር ሲባል ሊያልፉ የሚችሉትን ትናንሽ አይጦች ማሳለፍ ይገባል፡፡ ምክር የሚፈታው ችግር አለ፡፡ ተግሣጽ የሚፈታው ችግር አለ፣ ማሳለፍ የሚፈታውም ችግር አለ፡፡ አይጧን የሚያመጣውን ጉዳይ ሳንፈታ ወደ ቤት የሚመጡትም አይጦች በመግደል ብቻ አይጦችን ማጥፋት አይቻልም፡፡

እንኳንስ ዐዋቂዎቹ ባል እና ሚስት ቀርተው ሕፃናትን እንኳን በየአንዳንዱ በሚያጠፉት ጥፋት የምንናገራቸው ከሆነ ይደንዛሉ እንጂ አይሰሉም፡፡ በየደቂቃው የምትጠጣ ነጠብጣብ ውኃ ጥም እንደ ትቆርጠው ሁሉ በየደቂቃው ተው፣

እረፍ፣ እንዲህ አድርግ፣ እንዲያ አታድርግ፣ እያሉ መናገር ልጅን አያርመውም። አባቴ ልማዱ ነው፣ እናቴም ልማዷ ነው እያለ ሰምቶ እንዳልሰማ ያልፈዋል እንጂ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ደብረ ታቦር ላይ ቆመው እያሉ አንድ ገበሬ ሰክሮ በአጠገባቸው ያልፋል። ያም ገበሬ ወደ ንጉሡ ጠጋ ይልና «በቅሎው ይሸጣል» ይላቸዋል። የዐፄ ቴዎድሮስ ጋሻ ጃግሬዎች እነ ገብርዬ ሰይፍ መዝዘው «እንዴት ንጉሡን በድፍረት ይናገራል፤ እንበለው» አሏቸው። ንጉሡም ትእግሥት አድርገው «ተውት፣ ይሂድ። ነገር ግን የሚገባበትን ቤት ተከታትላችሁ ተመልከቱት አሏቸውና ተከታትለው ተመለከቱት።

በማግሥቱ ያንን ሰው ንጉሡ አስጠሩት። እየፈራ እየተንቀጠቀጠ መጣ። «ትናንትና እነዚህ ሁሉ ሰዎች ባሉበት በቅሎዬን ለመግዛት ጠይቀህ ነበርና እንድንስማማ ነው ያስጠራሁህ» አሉት። ሰውዬው ግን ማመን አልቻለም። የንጉሥ በቅሎ፣ ያውም ታጠቅ የተባለውን የዐፄ ቴዎድሮስን በቅሎ ለመግዛት የምጠይቅ እኔ ማነኝ ብሎ ደነገጠ። «የለም ንጉሥ ሆይ እኔ ብቻዬን ሆኜ እንዲህ ያለውን ሃሳብ አላሰበውም። ይህንን ጥያቄ ያቀረብነው ከጓደኞቼ ጋር አብረን ሆነን ነውና ከእነርሱ ጋር ተማከሬ መልስ ልስጥ» ብሎ ጠየቀ።

ንጉሡም «ትናንትና ስናይህ ብቻህን ነበርክ። ሌላ ጓደኛ አልነበረህም። ከየት አምጥተህ ነው የምትማከረው?» ሲሉ ገርሟቸው ጠየቁት። ያም ገበሬ «ንጉሥ ሆይ አላዩዋቸውም እንጂ አብረውኝ እነ ብቅል፣ ጌሾ፣ እነ ደረቆት፣ እነ ጠጅ፣ እነ ጠላ፣ እነ አረቄ ነበሩ። እነርሱ በሌሉበት ይህንን ነገር ብቻዬን አልናገረውም» ብሎ አሳቃቸው። ንጉሡም በአነጋገሩ ተገርመው ምሕረት አደረጉለት ይባላል። ለዚህ ነው ለምጣዱ ሲባል አይጧን ማሳለፍ የሚጠቅመው። ያንን ድፍረት የደፈረው ገበሬው ብቻውን አይደለም። እነ አረቄ፣ ጠላ፣እና እነ ጠጅ ናቸው። ስለዚህም አይጧን ከምጣዱ ለይቶ መምታቱ መልካም ነው።

ሰዎች በማኅበርም ሆነ በድርጅት፣ በኮሚኒቲም ሆነ በፓርቲ ለአንድ ዓላማ፣ በተወሰኑ መሠረታውያን ነገሮች ላይ ትስማምተው አብረው ይሠራሉ። ሰዎች አብረው ለመሥራት በሁሉም ነገር ላይ የግድ መስማማት የለባቸውም። ሌላው ቀርቶ በአንድ ቤት፣ አንድ አካል ሆነው የሚኖሩት ባል እና ሚስት እንኳን በመሠረታውያን ነገሮች ላይ እንጂ በሁሉም ነገሮች ላይ መስማማት አይችሉም። ሁለት ከመሆን የተነሣ የሚመጡ ልዩነቶች አሉና። ቢያንስ በምግብ ምርጫ ሊለያዩ ይችላሉ።

እነዚህ ማኅበራት፣ ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ፓርቲዎች አንዳንድ ጊዜ ለምጣዱ ሲባል አይጧን ማሳለፍ አለባቸው። በትንሽ በትልቁ በመጨቃጨቅ እና ባለመስማማት፣ በሆነው ባልሆነው በመለያየት እና እንደ አሜባ በመከፋፈል ምጣዱን የሚሰብሩት ከሆነ በውኑ ይህች ሀገር ተስፋዋ ምንድን ነው? ሰዎች ሲሠሩ ይሳሳታሉ። ከዕውቀት ማነስ ይሳሳታሉ፣ ከመቸኮል ይሳሳታሉ፣ ትክክለኛ ነገር የሠሩ መስሏቸውም ይሳሳታሉ። ማናቸውንም ዓይነት የሰዎችን ስሕተት ለመታገሥ የማንችል ከሆነ ሰዎችን የሚያሰባስቡ ተቋማትን መመሥረት የለብንም ማለት ነው። እናም መጀመርያ እኔ በእነርሱ ቦታ ብሆን ኖሮ ምን አደርግ ነበር? ብሎ ራስን መጠየቅ ቀጥሎም፣ ልናልፈው የሚገባንን ነገር ልንናገርበት እና ልንከራከርበት ከሚገባን ነገር ለመየት አለብን።

አካሄዳችን እና እርማታችን ዋናው ዓላማው ያቋቋምነውን ድርጅት፣ ማኅበር፣ ፓርቲ፣ ተቋም ማነጽ፣ ማጠናከር፣ እና የተሻለ ማድረግ ከሆነ ማናቸውም ነገራችን ምጣዱን የማይሰብር መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። ያለበለዚያ ግን አንዳንድ

ጥቃቅን የስሕተት አይጦችን እናጠፋለን ብለን የደከምንበትን፣ ስንት ወዝ እና ልፋት የፈሰሰበትን፣ ስንቶች እንደ እሳት ነድደው ያሟሹትን፣ የስንቶች ድካም እና ሞያ የፈሰሰበትን፣ምጣድ መስበር ይመጣል።።

ዛሬ በታላላቅ ቤተ እምነቶች የምናየው ጠባይ ለአይጧ ሲባል ምጣዱ ይሠበር የሚል የሞኝ አሠራር እየሆነ ነው።። አይጧን ከምጣዱ ለይተው መምታት አቅቷቸው ለብዙ ሺ ዓመታት የተደከመባቸው ትልልቆቹ ምጣዶች እየተሠበሩ ነው።። ያች ገበሬ እናት ትእግሥትን ገንዘብ አድርጋ፣ ለትልቁ ምጣድ ሲባል እስኪ ለጊዜው አይጧን ላሳልፋት ያለችው አይጧ ታስፈልጋለች፣ችግር አትፈጥርም፣እያደረገችው ያለው ነገር ትክክል ነው፣ ቤቱን ማውደሟ፣ ያልለፋችበትን ነገር መብላቷ፣ ቀበኛ መሆንዋ ተገቢ ነው፤ በዚህ ሁኔታም መኖር አለባት ብላ አይደለም።። ምጧጁን አትርፋ አይጧን ብቻ የምትመታበትን ተስማሚ ጊዜ ለማግኘት እንጂ።። በአንድ ጊዜ ሁለት ጥፋት ላለማጥፋት።።

የሃይማኖት አባቶች የዚህችን እናት ጥበብ እና ብልሃት ዛሬ ከወዴት ባገኙት?

የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት አንግበው የተነሡ ኃይላትም ኢትዮጵያን ያህል ብዙ ትውልድ ደክሞ ያሟሻትን ምጣድ፣ ስንቶች እንደ እሳት የተማገዱባትን ምጣድ፣ ስንት የማንነት፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የቅርስ፣ የእምነት እና የወግ እንጀራ ሲጋገርባት የኖረችውን ምጣድ፤ እናጠፋቸዋለን ብለው ለሚያስቧቸው አይጦች ሲባል እንዳይሰብሯት መጠንቀቅ ያስፈልጋል።። ሀገር ከፖለቲካ አመለካከት፣ ከርእዮተ ዓለም፣ ከፍላጎት፣ ከአስተሳሰብ እና ከምኞት ሁሉ ትበልጣለች።።

የችግር፣ የኋላ ቀርነት፣ የግፍ፣ የጭቆና፣ የመብት ረገጣ፣ የፍትሕ ማጣት፣ የእኩልነት ማጣት፣ የሰብአዊ መብት ማጣት የምንላቸው አይጦች መጥፋት አለባቸው።። እነዚህ ነገሮች ለዕድገታችን ዕንቅፋቶች፣ለኋላ ቀርነታችን ምንጮች መሆናቸውን የሚክድ የለም።። መጥፋት የለባቸውም ብሎ የሚከራከርም የለም።። ነገር ግን ምጣዱ ሳይሰበር መሆን አለበት።። እነዚህን አይጦች እናጠፋለን ብለን ዛሬ ከአንዳንድ ኃይሎች ጋር የምንመሠርተው ግንኙነት፣ የምንፈጥረው ጎበረት እና የምንዋዋለው ቃል ኪዳን አብሮ ምጣዱን የሚሰብር እንዳይሆን ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ ያስፈልጋል።።

በታሪካችን ውስጥ ያለፍንባቸው ብዙ አሳዛኝ እና ከፉ ነገሮች አሉን።። እነዚህን ዛሬ ሁላችንም የምንጸየፋቸውን እና እንዳይደገሙ የምንታገላቸውን የትናንት ጠባሳዎች ለማረም የምናደርገው ሂደታችን አይጧን በማጥፋት ሰበብ ምጣዱን የሚሰብር እንዳይሆን ጥንቃቄ ያስፈልገናል።። ሰው ጠባሳውን አጠፋለሁ ብሎ ቆዳውን አይልጥም።። የሀገሪቱን አንድነት፣ የሕዝቦችን በተዋሕዶ እና በተገናዝቦ መኖር፣ የነገን አዲስ ራእይ እና የትውልዱን የወደፊት ጉዞ የምንጋግርባትን ኢትዮጵያ የምትባለውን የተሟሸች ምጣድ፣ እዚህም እዚያም የሚያስቸግሩንን እና አንዳንድ ጊዜም ልናልፋቸው የሚገቡንን አይጦች በማጥፋት ሰበብ መስበሩ ለጫማ ሲባል እግርን እንደመቁረጥ ያለ ነው።።

እናም እስኪ አንዳንድ ጊዜ «ምእንቲ ዛ ምንን እታ አንጭዋ ትሕልፍ ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ» እንበል።።

3. ቶም እና ጄሪ



«ቶም እና ጄሪ» ፊልም ዊልያም ሐና እና ዮሴፍ ባርባራ በተባሉ ባለሞያዎች ለሜትሮ ጎልድዊን ካምፓኒ የተሠራ ተከታታይ የካርቱን ፊልም ነው። የቤት ውስጥ ድመት በሆነው በቶም እና በተንኮለኛዋ አይጥ በጄሪ መካከል በማያቋርጥ ቅንቃኔ እና ጠላትነት እየተቀጣጠለ የሚሄደው ይሄ ፊልም፣ አስገራሚም አስቂኝም ነው። በ1940 እኤአ የተጀመረው ቶም እና ጄሪ፣የአኒሜሽኑ ኩባንያ እስከ ተዘጋበት እስከ 1957 እኤአ ብቻ 114 ያህል ተከታታይ ፊልሞችን በሐና እና በባርባራ ደራሲነት እና አዘጋጅነት አቅርቧል።

በ1960 እኤአ በአዲስ መልክ ፊልሙ እንደ ገና መዘጋጀት እና መታየት ጀመረ። ዛሬ በታይም ዋርነር ካምፓኒ ባለቤትነት እና በዋርነር ብሮስ አከፋፋይነት የተያዘው የቶም እና ጄሪ የካርቱን ፊልም 162 ተከታታይ ፊልሞችን ያጠቃልላል።

ቶም እና ጄሪ አብረው በአንድ ሰው ቤት ውስጥ የሚኖሩ ነገር ግን መቼም ቢሆን ተስማምተው የማያውቁ ፍጡራን ናቸው። አልፎ አልፎ በጥቅም ምክንያት ሲስማሙ እንኳን በአከፋፈሉ ምክንያት ለመጣላት ጊዜ አይወስድባቸውም። ሁለቱንም የሚቃረን ነገር ከመጣ ግንባር የሚፈጥሩት ቶም እና ጄሪ፣ የጋራ ጠላታቸውን ለየራሳቸው ምክንያት ሲሉ ካጠቁ በኋላ እንደገና እርስ በርሳቸው መጣላት ይቀጥላሉ።

ይህ፣ መቼም የማያባራ የቶም እና የጄሪ የቅንቃኔ እና የጠላትነት ፊልም፣ በባለቤቶቹ ዘንድ የታወቁ 162 ተከታታይ ፊልሞች አሉት ቢባልም ጠቅላላ የፊልሞቹ ብዛት ግን ከዚህ ሳይበልጥ አይቀርም። ለምሳሌ 163ኛው ፊልም የሚዘጋጀውም፣ የሚሠራውም፣ የሚቀርበውም እኛው ሀገር ነው። ፊልሙን የደረሱትም፣ የሚያዘጋጁትም፣ የሚተውኑትም የ1960ዎቹ የኢትዮጵያ ትውልዶች ናቸው።

ቶም እና ጄሪ በአንድ ሰው ቤት የሚኖሩ ባላንጣዎች ናቸው። የ1960ዎቹ የሀገራችን ትውልዶችም በአንድ ወቅት የተነሡ የአንዲት ሀገር ልጆች ናቸው። የተነሡበት ዓላማም ተመሳሳይ ነው። እነርሱ በሚያስቡት መንገድ ብቻ ሀገሪቱን ማሳደግ። የርእዮተ ዓላማቸውም ቤቱ ተመሳሳይ ነው። ያም የብዕር ስሙ ይለያይ እንጂ ከኮሚኒስታዊ አስተሳሰብ አይዘልም። ፀር፣ትግል እና ግንባር ይወዳሉ።

ዛሬ በሀገሪቱ የወዲህም ሆነ የወዲያ ጎራ፣በድጋፍም ሆነ በተቃውሞ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በዲያስፖራ የሚገኙ፤ የፖለቲካው እና የቤተ እምነቱን መዘውር የሚዘውሩ አካላት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከ1960 እስከ 1970 ዓም ባለው ጊዜ ውስጥ የተነሡ፤ በዚያ ዘመን በነበሩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች የተማረኩ፣ የዚያን ዘመን የፖለቲካ አመለካከቶችን ሲያቀነቅኑ የነበሩ ናቸው፡፡

ወይ ኢሕአፓ፣ወይ ኢዲዩ፣ወይ መኢሶን፣ወይ ኢሠፓ፣ወይ ኢጭአት፣ወይ የተማሪዎች ንቅናቄ፣ ወይ የሠራተኞች ንቅናቄ፣የላብ አደር ፓርቲ፣ኢማሌድኅ፣ሰደድ ወዘተ ውስጥ ገብተው ሲቆራቆሱ እና ሲተረማመሱ፤ አንዱ ሌላኛውን ለማጥቃት ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር ሲያካሂዱ፣ አብዮታዊ ርምጃ ሲወስዱ እና ተቀናቃኞቻቸውን አብዮታዊ ምት ሲመቱ የነበሩ ናቸው፡፡

በውይይት ከበብ፣ በማሌ ጥናት፣በስብሰባ አካሄድ፣በፓርቲ አመሠራረት፣ጭቁኑን ሕዝብ በማታገል መርሕ አልስማማ ብለው ወይ ተጣልተዋል፣ ወይ ተኳርፈዋል፣ ወይ ተለያይ ተዋል፣ወይ ተፈላልገዋል፣ወይ ቂም ተያይዘዋል፣ ወይ ጥርስ ተነካክሰዋል፡፡ ስለዚህም እንደ ቶም እና ጄሪ አንዱ ሌላውን በጠላትነት እያየ ከመቀናቀን የተሻለ ሌላ ፊልም ለመሥራት ያዳግታቸዋል፡፡

«የምጠላው ወይም የምቃወመው አታሳጣኝ» ብለው የተሳሉ ይመስል ያለ ጠላት መኖር አይችሉም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቶም፣ ድሮ ጄሪ ያደረገችበትን ተንኮል ፊልሙን መልሶ እያየ ይበሳጫል፡፡ ከመበሳጨትም አልፎ ለመበቀል እርሷን ፍለጋ ይሄዳል፡፡ እነዚህም ከስድሳ ስድስት እስከ ሰባ ዓም የተቀረጸውን የደም መፋሰስ ፊልም ደጋግመው እያዩ አንዱ ሌላውን በኋላ ታሪኩ ምክንያት ለማጥቃት ይፈላለጋሉ፡፡

162 ፊልሞች ሲሠሩ ቶምም ሆነ ጄሪ አሁንም የፊልሙ ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው፡፡ አልተ ቀየሩም፡፡ ከ1940 እስከ 2009 ፊልሙን የሚሠሩት ቶም እና ጄሪ ናቸው፡፡ አልተለወጡም፡፡ በ1960ዎቹ የነበሩት ልጆች ያዩት የቶም እና ጄሪ ፊልም ዛሬም በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያሉ ልጆችም ያዩታል፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክም ፊልሙ እንደ ቶም እና ጄሪ አልተቀየረም፡፡ ያው ነው፡፡ በ1960ዎቹ የነበሩት የሀገራችን የፖለቲካ ቶም እና ጄሪዎች ዛሬም አሉ፡፡ የፖለቲካው ፊልም ዋነኛ ተዋናዮች እነርሱው ናቸው፡፡ አሁንም ሀገሪቱ ከ1960ው ትውልድ ተጽዕኖ መላቀቅ አልቻለችም፡፡ መቼ ይሆን ከስድሳዎቹ ወጥተን ወደ ሰባዎቹ፣ ወደ ሰማንያዎቹ፣ ወደ ዘጠናዎቹ እና ወደ ሁለተኛው ሺ የምንገባው? አሁንምኮ በየፖለቲካው መድረክ የምናያቸው ትክለ ሰብእናዎች የዛሬ ሠላሳ ዓመት የነበሩትን ነው፡፡

አዲሱ ትውልድም የቶም እና ጄሪ ፊልምን ስለለመደ በተመሠረቱት ነገሮች ሁሉ እነዚህን አካላት ካላካተተ፤ ወይንም እነዚህ አካላት ቡራኬ ካልሰጡት በቀር ይሳካል ብሎ ማመን ያቆመ ይመስለኛል፡፡

ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ
መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ
ተብሎ በተዘፈነባት ሀገር፣ዛሬ ዛሬ ገበየሁም አይሞት ባልቻም አይተካ፡፡

ቶም እና ጄሪ ቦታ ይቀያየራሉ እንጂ ስልትም መንገድም አይቀይሩም፡፡ ውጭ የነበረው ቶም ቤት ሲገባ ጄሪ ከቤት ትባረራለች፣ያለበለዚያም ጄሪ ቤት ገብታ ቶም ይባረራል፡፡ ዛሬ የአንድ ፓርቲ ሊቀመንበር የነበረው ነገ የሌላ ይሆናል፤ የአንድ ፓርቲ ልሳን ሲያዘጋጅ የነበረው ምንም ዓይነት የአመለካከት ለውጥ ሳያደርግ ሌላው ጋር ይቀላቀላል፡፡ ደንበኛ

ጥናት አድርገን ብንፈትሽ ዛሬ የቆሙለትን ዓላማ ደግመው ደጋግመው ሲቃወሙት የነበሩ አስገራሚ ቶም እና ጄሪዎችን በሀገራችን ታሪክ እናገኝ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች የፖለቲካ አመለካከታቸው የሚወሰነው እንደሚያምኑበት ነገር ሳይሆን እንደ ሚገቡበት ድርጅት እና እንደሚሠጣቸው ሥልጣን ነው፡፡

ቶም እና ጄሪን የሚያስማሟቸው ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ የመጀመርያው ጥቅም ሲሆን ሁለተኛው የጠላት መኖር ነው፡፡ በኛም የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ይሄው ፊልም እንደ ቀጠለ ነው፡፡ ቶሞች እና ጄሪዎች አንድ የሚሆኑት ጥቅም እስከተገኘ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ጥቅም ከተገኘ በርእዮተ ዓለሞቻቸው ላይ እንኳን የረባ ውይይት ሳያደርጉ፤ የቱጋ የአቋም ለውጥ እንዳደረጉ በሚገባ ሳይረዱም ሳያስረዱም በቅጽበት ይቀናጃሉ፣ ይተባበራሉ፤ ይዋሐዳሉ፣ግንባር ይመሠርታሉ፡፡ አከፋፈል ላይ ሲለያዩ ደግሞ የተባበሩ ቀርቶ የተጎራበቱ መሆናቸውን እስከንጠራጠር ድረስ ይናከሳሉ፡፡

ቶም እና ጄሪ ጠላት መጣብን ብለው ሲያስቡ አንድ ሆነው ያባርሩትና ከጠላታቸው በባሰ መልኩ እርስ በርሳቸው ይባላሉ፡፡ የሀገራችን ቶሞች እና ጄሪዎችም ሊያጠፋን ነው ብለው የሚያስቡት ጠላት ሲያጋጥማቸው አብረው ይሰበሰባሉ፣ይወስናሉ፣መግለጫ ያወጣሉ፣ ይሰለፋሉ፡፡ በኋላ ግን ጠላት ነው ብለው ከሚያስቡት አካል በባሰ ሁኔታ እርስ በርሳቸው መበላላት ይቀጥላሉ፡፡

ለቶም እንደ ጄሪ፣ለጄሪም እንደ ቶም የሚቀርባቸው የለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለቶም እንደ ጄሪ፣ ለጄሪም እንደ ቶም የሚጎዳቸው የለም፡፡ የኛም ፖለቲከኞች ይህንኑ ፊልም በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ 163ኛውን ክፍል፡፡

ባለፈው ጊዜ የዘመን አቆጣጠራችንን ብቻ ተመልክተን ሁለተኛውን ሺ አከበርነው እንጂ የፖለቲካ አቆጣጠራችን ብናየው ኖሮ ወደ ሁለተኛው ሺ ለመግባት ቢያንስ ገና ሠላሳ ያህል ዓመታት በቀሩን ነበር፡፡ አሁንም ተቃውሞ እና ጠላትነትን አልለየንም፣ አሁንም ገና ደጋፊነትን እና ምእመንነትን አልለየንም፡፡ ተቃዋሚያችን ምንም ዓይነት በጎ ነገር ቢያስብ ከመቃወም አንመለስም፤ ጠላትነት እንጂ ተቃውሞ አናውቅማ፡፡ የምንደግፈው አካልም ምንም ዓይነት ጥፋት ቢያጠፋ ከማመስገን ወደ ኋላ አንልም፤ ምእመንነት እንጂ ድጋፍ አናውቅማ፡፡ አይቶም እና ጄሪ፡፡

ሰሞኑን እዚህ ኔዘርላንድ በአንዳች ምክንያት የተጣሉ ሁለት ኢትዮጵያውያን ጎራዎችን ለማስታረቅ የተሰየሙ የሀገሬ ሽማግሌ ያሉኝን እዚህ ላይ ብጠቅሰው እንዴት ጥሩ ነው፡፡ አንደኛው ወገን ከሌላው ወገን ጋር ለመታረቅ በቅድመ ሁኔታነት አሥራ አምስት ነጥቦችን ያስቀምጣል፡፡ ሽማግሌዎቹም ይህንኑ ይዘው ወደዚያኛው ጎራ ይሄዱና ጉዳዩን ያቀርባሉ፡፡ እነዚህኞቹም ቡድኖች ከተወያዩ በኋላ አሥራ አምሱንም ነጥቦች በሙሉ እንቀ በላለን ብለው መልስ ይሰጣሉ፡፡ ሽማግሌዎቹም ድካማቸው ፍሬ በማፍራቱ ተደስተው ወደነዚያኞቹ ይሄዱና «እነዚያኞቹ በሃሳባችሁ ሙሉ በሙሉ ተስማምተዋል» ይሏቸዋል፡፡ ሰዎቹ አላመኑም «አሥራ አምስቱንም ነገር ተቀበሉት?» ይላሉ፡፡ «አዎ ሁሉንም ተቀብለዋል»፡፡ «እንዴት አንድ ሁለቱን እንኳን አልተቃወሙም፤ አንዳች ነገር ቢያስቡ ነውና እንዲያውም አንታረቅም» ብለው መልሱን አሉኝ፡፡

እውነታቸውን ነው፡፡ ቶም እና ጄሪአይደሉ፤ አንዳች የሚያጣላ፣ የሚያቆራቁስ፣ ለፓል ቶክ፣ ለዌብ ሳይት እና ለወሬ የሚሆን የጠብ መነሻማ ያስፈልጋቸዋልኮ፡፡ ተስማምተው ከሠሩ ምን ሊውጣቸው ነው? በኋላ በምን ተለያየን ሊሉ ነው፡፡ አይ ቶም እና ጄሪ፡፡

ኢትዮጵያዊውን የቶም እና ጄሪ ፊልም ከቁጥር አንድ ጀምራችሁ የምትተውኑ የፖለቲካ ቶም እና ጄሪዎች ጠቅላይ ሚኒስትራችን እንዳሉት በቃን ብትሉ ምናለ? ቢያንስ ለአፋችሁ ያህል፡፡ ሀገሪቱ 1960ዎቹን ለቅቃ ወደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ትገባ ዘንድ ብትረዷት ምናለ፤ በአንድ ወቅት በአንድም በሌላም መልኩ የቶም እና ጄሪን ፊልም የጀመራችሁ ተዋንያን፣ እባካችሁ ሌላ ፊልም እንይበት፡፡ የመነካከስ እና የመበላላት፣ የማያቋርጥ ቅንቃኔ እና ጠላትነት ተከታታይ ፊልም ሰልችቶናል፡፡

ሮተርዳም፣ኔዘር ላንድ

6/30/2009

4. መመረሽ፣መፈረሽ፣መደንበሽ

መጀመርያ ወደ ሱዳን ኤምባሲ ሄዳችሁ ሱዳን የመግቢያ ቪዛ ታወጣላችሁ፡፡ ከዚያ በጎንደር በመተማ በኩል ወደ ሱዳን ትገሠግሣላችሁ፡፡ ‘የሱዳን ሕዝብ ጥሩ ነው፣ለስደተኞች ይራራል‘ ይላሉ ጣልያን የገቡት ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች፡፡ እዚያ የታወቁ ሁለት አሸጋጋሪዎች አሉ፡፡ በአካል አታገኟቸውም፡፡ ስልካቸውን ከሀገር ሳትወጡ ይዛችሁ መሄድ አለባችሁ፡፡ አለበለዚያም ጣልያን የገባ ሰው ሊነግራችሁ ይገባል፡፡

አንዳች ሰዋራ ሥፍራ ተደብቃችሁ በስልክ ታገኟቸውና የጉዞ ዋጋ እና ቀን ትነጋገራላችሁ፡፡ እነርሱም ገንዘቡን ይዛችሁ የምትመጡበትን ቦታ እና ቀን ይነግሯችኋል፡፡ በተባላችሁት ሌሊት እቦታው ስትደርሱ እንደ እናንተ በቀጠሮ የመጡ ሌሎች ስደተኞችን ጨምረው በጭነት መኪና ወደ ሊቢያ ድንበር ትወሰዳላችሁ፡፡ ጉዞው ሌሊት ሌሊት፣ ያውም አብዛኛው በእግር፣ ጥቂቱ ደግሞ በመኪና ስለሆነ ከሃያ ቀን እስከ አንድ ወር ይፈጃል፡፡

ሊቢያ ድንበር ስትደርሱ የሱዳን አሸጋጋሪዎች ለሊቢያ አሸጋጋሪዎች ያስረክቧችኋል፡፡ ዋጋ ተነጋግራችሁ አሁንም ጉዞ ትጀምራላችሁ፡፡ ግማሹን በእግር ግማሹን በፒክ አፕ መኪና፡፡ ደረቅ ዳቦ እና ውኃ ይሰጣችኋል፡፡ መንገድ ላይ የሚሞቱ ልጆች ይኖራሉ፡፡ አሸዋውን ማስ ማስ አድርጎ በመቅበር ጉዞ መቀጠል ነው፡፡

«በእግር ወይንም በመኪና ስትጓዝ በእንጨት የመስቀል ምልክት የተሠራበት ነገር ካየህ እዚያ ቦታ አንድ አበሻ ስደተኛ ተቀብሯል ማለት ነው፡፡» ብሎኛል ጣልያን ያገኘሁት ልጅ፡፡ «ሰው ከታመመ እንደ በሽታው ነው፡፡ መጠነኛ ከሆነ በድጋፍ ይሄዳል፡፡ ከባድ ከሆነ ግን ቁርጥ ወገን ያስፈልገዋል፡፡ ከቡድኑ ከተቆረጥክ ችግር ስለሚያጋጠምህ አንዳንዱ ትቶህ ይሄዳል፡፡ ብዙ ጊዜ ግን የቂርቆስ ልጆች ይተዛዘናሉ፡፡ እንዲያውም

ከቂርቆስ ልጅ ጋራ አብረው ቢሰደዱ
ቢያገኝም ያበላል ቢያጣም ያዝናል ሆዱ

ተብሎ ተዘፍኖላቸዋል፡፡» አለኝ ሮም ያገኘሁት የአዲስ አበባው የቂርቆስ ልጅ፡፡ አዲስ አበባ ስለ ቂርቆስ ሠፈር ልጆች አያሌ አስገራሚ እና አስቂኝ ነገሮች እሰማ ነበር፡፡ እዚህ ጣልያን ደግሞ አገር ጉድ የሚያሰኝ ገድላቸውን መስማት ጀምሬያለሁ፡፡

ሊቢያ ስትገቡ የተቀበሏችሁ አሸጋጋሪዎች ከትሪፖሊ አጠገብ የገጠር መንደር ውስጥ በተሠራ አዳራሽ አስገብተዋችሁ ይጠፋሉ፡፡ ከዚያ ሌሎች አሸጋጋሪዎች ደግሞ ይመጡና «ትሪፖሊ ሩቅ ስለሆነ እንድንወስዳችሁ መቶ መቶ ዶላር ክፈሉ» ይሏችኋል፡፡ ታድያ የቂርቆስ ልጆች ምን አደረጉ መሰላችሁ፡፡ የተወሰኑት ልጆች ሌሊት ተደብቀው ይወጡና እግራቸው ወዳመራቸው ሲጓዙ ለካስ ትሪፖሊ ቅርብ ነው፡፡ ተመልሰው ይመጡና ሌሎችን ልጆች ነጻ ያወጧቸዋል፡፡ ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት ስደተኞች ደግሞ ግድግዳው ላይ በአማርኛ እንዲህ ብለው ይጽፋሉ «እንዳት ሸወዱ፣ ትሪፖሊ ቅርብ ነው፡፡ ብር ስጡን ቢሏችሁ አትስጡ፡፡ በዚህ እና በዚያ አድርጋችሁ ጥፉ» ይሄ ማስታወቂያ አያሌ ስደተኞችን ታድጓቸዋል፡፡ አይ የቂርቆስ ልጆች፡፡ ነፍስ ናቸውኮ፡፡

ትሪፖሊ ገብታችሁ የመርከብ ወረፋ መጠበቅ ነው፡፡ ክፉ ፖሊሶች ካገኟችሁ በመኪና ጭነው እንደ ገና ወደ ሱዳን ድንበር ወስደው ያሥሯችኋል፡፡ እዚያ እሥር ቤቱ በጣም አሰቃቂ ነው፡፡ እዚያም ቢሆን የቂርቆስ ልጆች ካሉ መከራው ይቀልላል፡፡ ከእሥር ቤቱ ለመውጣት የገንዘብ ጉቦ ያስፈልጋል፡፡ ያንን ደግሞ ለማግኘት ወይ አስቸጋሪ ሥራ መሥራት ያለበለዚያም ደውሎ ከዘመድ ማስመጣት ያስፈልጋል፡፡

እዚያ እሥር ቤት ብዙ ልጆችን ያስፈታ አንድ የቂርቆስ ልጅ ነበር፡፡ ሥራ ይወዳል፡፡ ሲጋራ፣ ብስኩት እና ሳሙና እየሸጠ ይኖር ነበር፡፡ በዚያ እሥር ቤት ብዙ ጊዜ የቆየው ሌሎችን ሲያስ ፈታ ገንዘቡ እያለቀበት ነው ይባላል፡፡ ሌሎች ደግሞ በሌላ ነገር ይተርቡታል፡፡ ከእሥር ቤቱ ሊወጣ በር ላይ ሲደርስ «አንድ ሲጋራ አለህ» የሚል ገሸር ሲመጣ ለርሱ ሊሸጥ እየተመለሰ ነው፡፡ እንዲያውም አንድ ጊዜ በአጥር ዘለሎ ሊያመጥ ሁሉም ነገር ተስተካክሎለት ነበር፡፡ ሊዘልል አንድ እግሩን እንዳሣ «አንድ ሲጋራ አለህ» የሚለውን ሲሰማ ተመልሶ መጣ ይባላል፡፡

በቤንጋዚ ወደብ አሻጋሪዎች እና ተሻጋሪዎች አይገናኙም፡፡ ሃያ እና ሰላሣ ሰው እስኪሞላ የሚመዘግቡ ሰዎች አሉ፡፡ የቡድኑ አባላት ሲሟሉ ገንዘብ ይከፍሉና ወደሚሻገሩበት ወደብ ይወሰዳሉ፡፡ የመሻገሪያዋ ጀልባ ብዙ ጊዜ ከቆርቆሮ እና ከእንጨት የምትሠራ ናት፡፡ ለአንዱ ስደተኛ አሻጋሪዎቹ የመርከቧን አነዳድ ያሳዩታል፡፡ ትምህርቱ ቢበዛ ከአንድ ቀን በላይ አይሰጥም፡፡

ለዚያ መከረኛ «ካፒቴን» የጀልባዋን ኮምፓስ አሥረው ካርታውን ያስረክቡታል፡፡ ምግብ እና መጠጥ ይጫናል፡፡ እንደ ጀልባዋ ስፋት ከሃያ እስከ ሠላሳ ስደተኛ ይሳፈራል፡፡ በሌሊት የጣልያንን መብራት በሩቁ እያዩ ጉዞ ይጀመራል፡፡ አሻጋሪዎቹ ጀልባዋ ስትነሣ ይመለሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ዕዳው የስደተኞቹ ነው፡፡

ጉዞው እስከ አስራ ሰባት ሰዓት ይፈጃል፡፡ የአንዱ እግር ከሌላው ጀርባ ጋር ተሰናስሎ ተኮራምቶ መጓዝ ብቻ ነው፡፡ ሙቀቱ እና ተስፋ መቁረጡ አንዳንዶችን ራሳቸውን ወደ ባሕሩ እንዲጥሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በተለይም መርከቡ መንገድ ከሳተ፡፡

የሚያስነበኘኝን የቂርቆስ ልጅ «ለምንድን ነው ጣልያን ውስጥ የቂርቆስ ሠፈር ልጆች የሚበዙት፡፡ እንዲያውም ሮም ውስጥ የቂርቆስ ልጆች ብቻ ያሉበት አንድ ሕንፃ አሳይተውኛል፤» አልኩና ጠየቅኩት፡፡ «ምናልባት የሱዳን ኤምባሲ ሠፈራችን ውስጥ ስለሆነ ይሆናል በሱዳን በኩል እያቋረጥን የመጣነው» አለና ቀለደብኝ፡፡ «ቆይ ግን ለመንገዱ ብዙ ዶላር ያስፈልጋል ሲባል ነበር የምሰማው፤ እንዴት ነው ጉዳዩ» አልኩት፡፡ «ቂርቆስ የድኻ ሠፈር ነው ብለው ስማችንን ያጠፉትኮ የቦሌ ልጆች ናቸው፤ እነርሱ አውሮፕላን ሲያዩ ስለሚውሉ የገዙ እየመሰላቸው ነው፤ እንዲያውምኮ መንግሥት ሀብታም ገበሬዎችን ብቻ ሳይሆን እኛንም መሸለም ነበረበት፤ የመረጃ እጥረት ነው» አለኝ፡፡

«እንዴት?» አልኩት፡፡ «እስኪ ተመልከት እኛ የቂርቆስ ልጆች የመንግሥትን እጅ ሳንጠብቅ፤ አነስተኛ ፣ጥቃቅን ሳንል፤ ራሳችንን በራሳችን ረድተን እዚህ መድረሳችን አያሸልመንም» አለና ሳቀ፡፡ «ሀብታም ገበሬዎች ራሳቸውን ቻሉ እንጂ የሕዝብ ቁጥር አልቀነሱም፤ እኛ ግን ራሳችን ንም ቻልን፣ከሀገር በመውጣታችን ደግሞ የሕዝብ ቁጥር ቀነስን፡፡ ከዚህ በላይ ምን የሚያሸልም ነገር አለ፡፡ አየህ እኛ እንደ ቦሌ ልጆች ጆግራፊን በቲቪ ሳይሆን በተግባር ነው የምንማረው»

«ደግሞምኮ የአባቶቻችንን ደም የመለስን እኛ ነን» አለኝ እየሳቀ፡፡ «እንዴት?»

«ጣልያን ባሕር አቋርጦ ሀገራችንን ወረረ፡፡ እኛ ደግሞ የአባቶቻችንን ደም ለመበቀል ባሕር አቋርጠን ሀገሩን ወረርነዋ፤ አንተ ቂርቆስኮ የጀግና ሠፈር ነው» አለና ሳቀ፡፡

«እውነት ግን ለምንድን ነው የቂርቆስ ልጆች እዚህ የበዛችሁት?» «ምን መሰለህ ይህንን በረሃ ለማቋረጥ ከሁለት እስከ ሦስት ወር ይፈጃል፡፡ የገንዘብ፣ የምግብ፣ የውኃ ችግር አለ፡፡ ካልተዛዘንክ በቀር ይህንን በረሃ ልታልፈው አትችልም፡፡ እኛ ደግሞ ከልጅነታችን ተዛዝነን መኖር ለምደናል፡፡ ስለዚህ እየተደጋገፈክ መጓዝ ነው፡፡ ያው እንግዲህ ባሕር ኃይልም አየር ኃይልም እየመጣ ይቀጥላል»

«የቀድሞ ወታደሮችም ይመጣሉ ማለት ነው» «አይ እነርሱ አይደሉም፡፡ በአውሮፕላን ጣልያን የገባው ስደተኛ አየር ኃይል ይባላል፡፡ በባሕር የገባው ደግሞ ባሕር ኃይል ይባላል፡፡ ታድያ አየር ኃይሉ ባሕር ኃይሉን ይንቀዋል፡፡»

«ለምን?» «ያው መከፋፈል ለምዶብን ነዋ፤ አታይም መንገድ ላይ እንኳን ጉስቁል ያለ አበሻ ካዩ ሰላም አይሉንም፡፡ ጣልያኖች እንደሆኑ አየር ኃይልም ሆንክ ባሕር ኃይል ሚኒስትር አያደርጉህም፤ ሁሉም ያው ሲኞራ ቤት ነው የሚሠራው፡፡

«ሲኞራ ቤት ደግሞ ምንድን ነው?» «ሰው ቤት ተቀጥሮ መሥራት ማለት ነው፡፡ እዚህ ብዙው አበሻ እንደዚያ ነው የሚሠራው፡፡ ያውም ለሴቶች እንጂ ለወንዶች ሥራ አይገኝም፡፡ ድድ ስታሰጣ መዋል ነው፡፡»

«ግን ምን ላይ እየኖርክ ድድ ታሰጣለህ» አልኩት፡፡ «እዚህ አበሻ ከድንኳን ሰባሪነት ወደ ሕንፃ ሰባሪነት ተሸጋግሯል» «እንዴት እንዴት ሆኖ» «ያንን ሁሉ በረሃ አቋርጠህ፤ ባሕር ሰንጥቀህ ጣልያን ስትገባ ምንም ነገር አታገኝም፡፡ ከምግብ በቀር ቤት እንኳን የሚሰጥህ የለም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ መጠለያ ውስጥ ያስገቡህና በኋላ ሠርተህ ብላ ብለው ያሰናብቱሃል፡ ፡ ያን ጊዜ ችግር ውስጥ ትወድቃለህ፡፡ አበሻ ታድያ ይሰባሰብና በልዩ ልዩ ምክንያት የተዘጋ ሕንፃ ያስሳል፡፡ የተወሰነ ጊዜ ሁኔታውን ታይና ሃያ ሠላሳ ሆነህ በሩን ሰብረህ ትገባለህ፡፡ ከዚያ ክፍሎቹን መከፋፈል ነው፡፡»

«ባለቤቶቹስ» «ባለቤቶቹ ኡኡ ይላሉ፡፡ ፖሊስ ይመጣል፤ ግርግር ይፈጠራል፡፡ የሰው ልጅ ሜዳ ላይ ወድቆ እንዴት ሕንፃ ተዘግቶ ይኖራል ብለህ ትከራከራለህ፡፡ መቼም የሰው መብት በመጠኑም ቢሆን የሚከበርበት ሀገር ነውና የሰው መብት ተከራካሪድር ጅቶችም አብረውህ ይጮኻሉ፡፡ በመጨረሻ ታሸንፍና ትኖርበታለህ፡፡»

«መብራት እና ውኃ አይቆርጡባችሁም» ?«ብዙ ጊዜ መብራቱን እንጂ ውኃውን መቁረጥ ያስቸግራቸዋል፡፡ የሮም ሕንፃዎች የድሮ ሕንፃዎች ናቸው፡፡ የውኃ መሥመሩ በቀላሉ አይገኝም፡፡ መብራቱን ግን ቢቆርጡትም እንቀጥለዋለን፡፡ አንድ ልጅ እንዲያውም በዚያ ምክንያት ሥራ አግኝቷል፡፡»

«መብራት በመቀጠል?» «አዎ፤ የቤቱን መብራት ሲቆርጡት በመንገድ ከሚያልፈው መብራት ሌሊት ቀጠለው፡፡ ፖሊሶቹ ሲመጡ ይበራል፡፡ ሄደው ከዋናው ማጥፊያ ቢያለያዩትም ይበራል፡፡ አይተው ስለማያውቁ ግራ ገባቸው፡፡ በኋላ ከመንገዱ መብራት መቀጠሉን ሲያዩ እንዴት ሊቀጠል እንደቻለ ማመን አልቻሉም፡፡ እና ትተውት ሄዱ፡፡ ይሄው ፏ ብሎልሃል፡፡ ልጁም ታድያ ኤሌክትሪክ ሠራተኛ ሆኖ ቀረ»

«ሴቶች ሲኞራ ቤት ይሠራሉ አልከኝ፤ ወንዶችስ ምን ይሠራሉ?» «ወንድ ከሆንክ አልፎ አልፎ ነው ሥራ የምታገኘው፡፡ ችግር አለ፡፡ አንዱ አበሻ ሲርበው ሴት ነኝ ብሎ ሲኞራ ቤት ተቀጥሮ ነበር አሉ፡፡» «እውነትክን ነው

ወይስ ቀልድ ነው» «እኔ ሲያወሩ ነው የሰማሁት፡፡» «እሺ ከዚያስ» «ልጁ ጢም የለውም፤ መልኩ የሴት ድምጽ ነው፡ ፡ እንዲያው ልጆች በሌላ ነገር ይጠረ ጥሩታል» «ምን ብለ» «ነገርዬው የለውም ይሉታል» «እሺ»

«እና ጉልበታም ነው፤ ሥራዋን ፉት፣ ጭጭ ነበር አሉ የሚያደርጋት፡፡ አንድ ቀን የሸንት ቤቱን በር ሳይዘጋው ረስቶት፣ ቆሞ ሸንቱን ሲሸና ሲኞራው በሩን ሲከፍት ፌንት ወጣ አሉ፡፡ ነፍሷ ደሞዟን ሳትቀበል ከቤት ወጥታ ጠፋች፡፡ በኋላ ግን እንደዚያ ያደረገው ሥራ ስላጣ መሆኑን ሲኞራው ሲሰማ አድንቆ ካምፓኒው ውስጥ ቀጠረው አሉ»

«ተው እባክህ፤ ይሄን የመሰለ ፊልም አይቻለሁ፤ ሲኮምኩ ይሆናል» «ኩምክና አይደለም፤ የሆነ ነው ብለውኛል»

«እሺ ይህንን ሁሉ ባሕር አቋርጦ የመጣ ሰው መጨረሻው ምንድን ነው?»

«ወይ ትመርሻለህ፣ ወይ ትፈርሻለህ፣ ወይ ትደነብሻለህ» «ምንድን ነው መመረሽ፣ ምንድን ነው መደንበሽ፣ ምንድን ነው መፈረሽ»

«ጣልያን ለመኖር የሚመጣ የለም፣ ስለዚህ ትንሽ ገንዘብ ነገር ቆጣጥረህ ወደ እንግሊዝ ትሻገራለህ፤ ይኼ መመረሽ ይባላል፡፡ ያለበለዚያ ደግሞ እዚሁ የመኖርያ ፈቃድ አወጥተህ የተሻለ ሥራ ካገኘህ ትኖራለህ፤ ይኼ ደግሞ መፈረሽ ይባላል፡፡ ሁለቱም ካልሆነልህ ደግሞ ትጀዝብና ደንብሽህ ትኖራለህ፡፡ **ሚላኖ፣ ጣልያን**

5. ገድለ ዜና ማርቆስ የያዛቸው መረጃዎችና ሁነቶች

5.1. መግቢያ

በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ከ200 በላይ ገድላትን እስከ አሁን ለማየት ዕድል ገጥሞኛል፡፡ የገድላቱ አጻጻፍ ተመሳሳይ የሆነ «ቅርጽ» /format/ እና ተመሳሳይ የሆነ «ፍሰት» /Flow/ የሚከተሉ ሆነው አግኝቻቸው ነበር፡፡ በዚህ ጽሑፍ «ቅርጽ» የምለው የገድሉ ባለቤት ታሪክ፣ ገድል፣ ቃል ኪዳን፣ ተአምር እና መልክዕ የሚጻፍበት መንገድ ማለቴ ነው፡፡ በአብዛኞቹ ገድሎች መጀመሪያ የሃይማኖት መሠረት የሚሆነው ምሥጢረ ሥላሴ እና ምሥጢረ ሥጋዌ በመግቢያነት ይቀርባል፡፡ ከዚያም የቅዱሱ ትውልድ ይገለጣል፤ ቀጥሎም ገድሉ ይከተላል፤ ከዚያም የተሰጠው ቃል ኪዳን ይጻፋል፤ በመጨረሻም ተአምሩ እና መልክዐ ይቀርባል፡፡

«ፍሰት» የምለው ደግሞ የታሪኩ ቅደም ተከተል የቀረበበትን መንገድ ነው፡፡ ታሪኩ ከየት ተነሥቶ፣ በየት በኩል አልፎ፣ የት ይደርሳል የሚለው ነው፡፡ በብዙዎቹ ገድሎቻችን ከቅዱሱ ወላጆች ይጀምርና አወላለዱን ከገለጠልን በኋላ የአካባቢያዊ እና የትምህርታዊ ዕድገቱን፤ ገዳማዊ ሕይወቱን፣ የተቀበለውን መከራ፤ ዕለተ ዕረፍቱን ነው የሚተርክልን፡ ፡

የገድለ ዜና ማርቆስ አቀራረብ ግን ከዚህ ከተለመደው መንገድ ወጣ ያለ በመሆኑ ስለ ገድላት ያለንን ዕውቀት የሚያሳድግ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ መረጃም የሚሰጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ገድሉን ለማንበብ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድል ያገኘሁት የዛሬ ስድስት ዓመት በደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም ከሚገኘው ዕቃ ቤት ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያ ጊዜ ለረዥም ሰዓታት ማንበብ እና ከሌሎች ነገሮች ጋር ለማዛመድ የቦታው ሁኔታ አላመቸኝም ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ማይክሮ ፊልም ማኑስክሪፕትስ ቤተ መጻሕፍት የሚገኘውን የማይክሮ ፊልም ቅጅ ለማንበብም በወቅቱ የማተሚያ መሣሪያው በመበላሸቱ በመብራት ረዥም ሰዓት ማጥናት አልተቻለም ፡፡ በዚህ መካከል ግን ገድለ ዜና ማርቆስን ገዳሙ አሳተመው፡፡ በመሆኑም ተረጋግቶ ለማጥናት ዕድል ተገኘ፡፡

ገድለ ዜና ማርቆስ ከብዙዎቹ ገድሎች የሚለይባቸው ነጥቦችን በዝርዝር ማየቱ ገድሉ በሃይማኖት፣ በታሪክ፣ በመረጃ እና በሥነ ጽሑፍ ዘርፎች ያለውን ቦታ ያመለ ክታል፡፡ የቤተ ክርስቲያናችንን ገድላት ያለ ጥልቅ ጥናት ከመተቸትና ታሪክ የማይሽረው ስሕተት ከመሥራትም ያድናል በማለት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

5.2. የመጽሐፉ ጸሐፍት

ገድለ ዜና ማርቆስ ስለገድሉ ጸሐፍት ከሌሎቹ ገድሎች በተሻለ ዝርዝር መረጃ ይለግሠናል፡፡ በብዙዎቹ ገድሎች ጸሐፊው አንድ ሰው ነው፡፡ ለምሳሌ በገድለ ክርስቶስ ሥምራ «ለዛቲ መጽሐፍ ጸሐፍከዋ አነ ፊልጶስ ወልዱ ለተክለ ሃይማኖት ዘብሔረ ሸዋ በመዋዕለ ንጉሥነ ዳዊት ዳግማዊ፡፡ ጸሐፍክዋ አነ እንዘ ትነግረኒ ለልይ ከመ ይትናገሩ ቅዱሳን ሶበ በጽሐ ጊዜ ዕረፍቶሙ» ይላል፡፡ በዚህም እጨጌ ፊልጶስ ዘደብረ ሊባኖስ ጊዜ ዕረፍቷ በደረሰ ጊዜ እየነገረችኝ ጻፍኩት ይለናል፡፡ በገድለ አባ ፊልጶስ ዘደብረ ቢዘን ደግሞ «አነሂ ጸሐፍኩ ለክሙ ዘሰማዕኩ በእዝንየ እምነ ደቂቁ ምእመናን ወቦ ዘርኢኩ በአዕይንትየ መንክራት ዘገብረ እስመ አነ ልህቁ ታኅተ እገሪሁ»፤ ሃይማኖተኛ የሆኑ ልጆቹ ሲናገሩ በጆሮዬ የሰማሁትን፤ እኔም ከእግሩ ሥር የያደግኩ ነኝና በዐይኔ ያየሁትን ድንቅ ሥራውን ጻፍኩላችሁ» ይላል፡ ፡ በገድለ ዜና ማርቆስ ግን የገድሉ ጸሐፍት ብዙ ናቸው፡፡

ሀ. የመጀመሪያዎቹ ጸሐፍት

በመቅድሙ አንቀጽ 1 ላይ እንደ ተገለጠው ገድሉን መጀመሪያ የጻፉት አባ አካለ ክርስቶስ፣ አባ ዮሴፍ እና አባ ገብረ መስቀል የተባሉ የአቡነ ዜና ማርቆስ ደቀ መዛሙርት ናቸው፡፡ ገድሉ የሚገልጥልን የጸሐፍቱን ስም ብቻ አይደለም፡፡ ከየት ከየት እንደ መጡም ይገልጥልናል፡፡ አባ ዮሴፍ ከየሐ ላሊበላ፣ አባ አካለ ክርስቶስ ከተከዜ በረሃ፣ አባ ገብረ መስቀል ደግሞ ከገዳመ ዘጌ /ገጽ 78/ የመጡ አበው ናቸው፡፡ እነዚህ አበው የአቡነ ዜና ማርቆስን ዝና ሰምተው በትሩፋታቸው ተማርከው የተከተሏቸው ደቀ መዛሙርት ናቸው፡፡

ለ. ሁለተኛው ጸሐፊ

የደብረ ብሥራት አበምኔት በነበረው በአባ ገብረ ክርስቶስ ዘመን ገድሉ እንደ ገና ተጽፏል፡፡ ያም የሆነው በገዳሙ ከሚገኘው የአቡነ ዜና ማርቆስ መቃብር አፈር ተቀብቶ የታወረ ዓይኑን ባዳነውና በኋላም ፈጣን ጸሐፊ በሆነው በጸሐፌ መንክራት ዮሐንስ አማካኝነት ነው፡፡ /ገጽ. 192/፡፡

ሐ. ሦስተኛው ጸሐፊ

ከአባ ገብረ ክርስቶስ ጋር በመሆን አባ ገብረ መርዓዊ የተባሉት አባት ከዕረፍቱ በኋላ በመቃብሩ ላይ የተደረገውን ጽፈዋል፡፡

መ. አራተኛው ጸሐፊ

በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት /1391-1460 ዓ.ም/ የአቡነ ዜና ማርቆስ ዐጽም ሲፈልስ የሆነውን ታሪክ ደግሞ አባ ዮሐንስ የተባለው አባት ጽፎ አስቀድሞ ከተጻፈው ከገድሉ መጽሐፍ እንዲካተት አድርጓል፡፡ /ገጽ. 144/፡፡

ሠ. አምስተኛው ጸሐፊ

በተለይ አቡነ ዜና ማርቆስ በሕይወት እያሉ ያደረጓቸውን ተአምራት አሰባስበው የጻፏቸው አባ ገብረ መስቀል፣ አባ እንድርያስ፣ አባ ገብረ ሚካኤል የተባሉ አበው መሆናቸውን ገድሉ ይተርክልናል /ገጽ. 272-273/፡፡

ረ. ስድስተኛው ጸሐፊ

በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ የገዳሙ አበምኔት የነበረው አባ ቃለ ዐዋዲ ገድሉን ለመጨረሻ ጊዜ ጽፎ አጠናቅቆታል፡፡ ይህም ከርሱ በፊት የነበሩትን ምንጮች በመጠቀምና እስከ እርሱ ዘመን የተፈጸሙትን ተአምራት በማጠቃለል ገድሉን እና ተአምራቱን ያጠናቀቀው ይመስላል፡፡ «ይህንን የድርሳንና የተአምር መጽሐፍ የጻፈው የደብረ ብሥራት አበ ምኔት አባ ቃለ ዐዋዲ ነው» ይላል ገድሉ /ገጽ. 377/፡፡ ይህም ገድሉ ከተጀመረበት እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ 200 ዓመታት ጊዜ የወሰደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህንን ሁኔታ ስንመለከተው ገድለ ዜና ማርቆስ የተጻፈው ታሪኩ ሲፈጸም በአካል በነበሩ፤ የዓይን ምስክር በሆኑ አበው እና እማት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ለዚህም ነው ገድሉ ይህንን ያህል ዘመን የፈጀው፡፡

የታሪኩ መገኛ

ገድለ ዜና ማርቆስ የአቡነ ዜና ማርቆስ ታሪክ እና ተአምር ከየት ሊገኝ እንደቻለ ይነግረናል፡፡ ታሪካቸውን በተመለከተ «ያን ጊዜ ወደ በረሐ ገብቶ ሱባኤ ይዞ በጽሙና ሰባት ዓመት በኖረበት ጊዜ ልጆቹ ያዩትን ተአምራቱን ጻፉ፤ ያላዩትንም እኅቱ ማርያም ክብራ ከልደቱ ጀምራ የሆነውን ሁሉ እየነገረቻቸው ጻፉ፡፡ /ገጽ.144/፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ምንጮችን እናገኛለን፡፡ የአቡነ ዜና ማርቆስ እኅት ማርያም ክብራ ከልጅነት ጀምሮ ያለውን ታሪክ የዓይን ምስክር ሆና ታውቃለች፡ ፡ ደቀ መዛሙርቱ ደግሞ በገዳ ማዊ ሕይወት የሆነውን ሁሉ ያዩትን ጽፈዋል፡፡

ሌላው የታሪክ ምንጭ ደግሞ «ከዕረፍቱ ጊዜ እና ከዕረፍቱ በኋላ የተደረገውን» የጻፉት አባ ገብረ ክርስቶስ /የገዳሙ አበምኔት የነበሩ/ እና አባ ገብረ መርዓዊ ናቸው፡፡ /ገጽ.144/ ዐጽሙ በሚፈልስ ጊዜ በአካል ተገኝቶ የነበረው አባ ዮሐንስም ያየውን ጽፎ በገድሉ ውስጥ አካትቷል /ገጽ.144/፡፡ አባ ቃለ ዐዋዲም በግራኝ ጊዜ ራሱ በአካል ተገኝቶ የተፈጸመውን ለማየት የበቃ ሰው ነው፡፡ /ገጽ. 146/፡፡ በመሆኑም ያየውን ጽፎ በገድሉ አካትቶታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ለተልእኮ ወጥተው ወደ ገዳማቸው ሲመለሱ የተልእኮዋቸውን ዜና ለደቀመዛሙርቶቻቸው ይተርኩላቸው እንደነበረ ገድሉ ይነግረናል፡፡ /ገጽ.101/፡፡

ከታሪኩ በተጨማሪም የተአምራቱን ምንጮች ጸሐፊዎቹ በሚገባ አስቀምጠውልናል፡፡ ለምሳሌ በገጽ 150 ሊቀ ጳጳሳቱ የነገራቸው መሆኑን፣ በገጽ 151 «ከእስክንድርያ የመጡ ሰዎች ነገሩን» ይላል፤ በገጽ 170 ዓይንዋ የተፈወሰላት ሴት የሰጠችው ምስክርነት፤ ልጇ የሞተባት ሴት የሰጠችው ምስክርነት /ገጽ. 27/ ያመነችው አረማዊት ሴት የሰጠችው ምስክርነት /ገጽ. 244/፣ የአከሱም መነኮሳት የሰጡት ምስክርነት /ገጽ. 310/ ለዚህ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ከትግራይ የመጣው መኮንን የሰጠው ምስክርነት/ገጽ 312/፤ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘው የነበሩ ወንድሞች የሰጡት ምስክርነት /ገጽ. 313/ የአቡነ አረጋዊ ገዳም መነኮሳት የሰጡት ምስክርነት /ገጽ. 318/፣ የግብጽ ሰዎች እና የሊቀ ጳጳሱ ረድእ የሰጡት ምሥክርነት /ገጽ. 327/፤ በዐፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ከአይሁድ እና ከተንባላት የመጡ 60 መልእክተኞች በሀገራቸው የተፈጸሙትን ተአምራት ወደ ገዳሙ ከስጦታ ጋር ይዘው መጥተው አስረክበው ነበር፡፡ «እኛም ጽፈን ከአባታችን ዜና ማርቆስ የገድሉ መጻሐፍ ጋር አኖርነው» ይላል ጸሐፊው /ገጽ. 369-370/፡፡

ተአምሩን የጻፉት አበው በመጽሐፈ ገድሉ ውስጥ ተአምሩን ከማካተታቸው በፊት የማረጋገጥ ሥራ ይሠሩ እንደነበረ መረጃ እናገኛለን፡፡ «እኛም ነገርዋን ሰምተን ከሀገርዋ ሰዎችም ጠይቀን፤ አረማዊ ንጉሥም እንዳመነና ወደ ንጉሣችን ወደ ዘርዐ ያዕቆብ መልእክተኞች እንደላከ ነገርዋ እውነት ሆነ» /ገጽ. 294/ ይሉናል ጸሐፊዎቹ፡፡

ይህ ሁኔታ ተአምራት የተፈጸመላቸው ሰዎች ስእለታቸውን ለመፈጸም ወይንም ደግሞ ተአምር የሠራላቸውን ቅዱስ ገዳም ለማየት ወደ ገዳሙ ሲመጡ አባቶች ታሪኩን አረጋግጠው በገድሉ ይመዘግቡት እንደነበር ያስረዳናል፡፡

የተአምራቱ አጻጻፍ እና ቁጥር

ገድለ ዜና ማርቆስን በመጨረሻ ያጠቃለለው አባ ቃለ ዐዋዲ ተአምራቱን በሁለት ከፍሏ ቸዋል፡፡ አቡነ ዜና ማርቆስ ከማረፋቸው በፊት የተፈጸሙ እና ካረፉ በኋላ የተፈጸሙ፡፡

አቡነ ዜና ማርቆስ ከተወለዱበት እስከ ዐረፉበት ጊዜ የተደረጉ 22 ተአምራት በገድሉ ተመዝግበዋል /ገጽ. 384/፡፡ ይህም ጽሑፍ የተጻፈው አቡነ ዜና ማርቆስ ባረፉ በ3ኛ ዓመት መሆኑን ገድሉ ይናገራል፡፡ /ገጽ 385/ ያረፉት በ1433 ዓ.ም በመሆኑ /እንደ ገድሉ ከሆነ፤ ሌሎች መረጃዎች ግን በ1402 ዓ.ም ነው ይላሉ፡፡/ የመጀመሪያዎቹ ተአምራት የተጻፉት በ1436 ወይም በ1405 ዓ..ም ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛዎቹ ተአምራት ቁጥራቸው 44 ሲሆን የተጻፉት በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት /1391- 1460 ዓ.ም/ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት አንድ ተአምር በአባ ቃለ ዐዋዲ አማካኝነት ተጨምሮአል፡፡ ይህ ሁኔታ የተአምራቱ ቁጥር 67 መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንደ እኔ እምነት ቅዱሳት መጻሕፍትን ሠፍሮ እና ቆጥሮ መመዝገብ እና በቀኖና መወሰን /በተለይ ተአምራትን/ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከ600 ዓመታት በላይ የቆየ ታሪክ ያለው መሆኑን ከሚያሳዩት ማሳያዎች አንዱ ይህ ይመስለኛል፡፡

በታተመው ገድል 'ሁለተኛ ክፍል' በሚል ርዕስ ከተቀመጡት ተአምራት መካከል ከ17ኛው ተአምር በቀር /በመጋቢት ወር ስለተፈጸመ በወቅቱ ለማንበብ እንዲመች ወደዚህ ክፍል የገባ ይመስላል/ የቀሩት 21 ተአምራት አቡነ ዜና ማርቆስ ባረፉበት ዓመት እና በቀጣዩ ዓመት የተፈጸሙ ይመስላሉ፡፡ ምክንያቱም በተአምራቱ መካከል የምናገኛቸው መረጃዎች ስለዚያ ዘመን የሚተርኩ ናቸውና፡፡

'ካልእ ተአምር' ተብለው ከተመዘገቡት 17 ተአምራት መካከል ሁሉም አቡነ ዜና ማርቆስ በሕይወት በነበሩ ጊዜ ያደረጓቸውን ተአምራት የሚነግሩን ናቸው፡፡ 'ሦስተኛው ተአምር' ተደርገው የተቀመጡት 22 ተአምራት ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ እስከ ዐፄ ናዖድ ዘመነ መንግ ሥት ባለው ዘመን ውስጥ ጻድቁ ካረፉ በኋላ ያደረጉትን ተአምራት የሚገልጡ ናቸው፡፡

በጠቅላላው በሁለተኛ ክፍል መጀመሪያ የተጻፉት 25፣ በሁለተኛ ክፍል የተቀመጡት 17፤ በሦስተኛ ክፍል ያሉት 22 ተአምራት ሲደመሩ 64 ተአምራት ይሆናሉ፡፡ ይህም በገድሉ ገጽ. 384 ከተጠቀሰው ድምር ቁጥር ከ67 በሦስት ያንሳል፡፡ በመሆኑም አንድም ከታሪክ ጋር ተቀላቅሏል፡፡ ያለበለዚያም ከዋናው ገድል ተገልብጦ ሳይደርሰን ቀርቷል ማለት ነው፡፡

የገድሉ ጸሐፊዎች ታሪኩን በታሪክ፣ ተአምሩን በተአምር መድበው በየፈርጁ ለማስቀመጥ የተቻላቸውን ሁሉ ማድረጋቸውን ሥራቸው ይመሠክራል፡፡ በታሪኩ ላይ የማይገኝና በተአምሩ የሚገኝ ነገር ሲኖር «በኋላ በአባታችን የተአምር መጽሐፍ እንነግራችኋለን፤ በተአምር መጻሐፉ ተጽፏልና» ይሉናል /ገጽ.89/፤ በሌላ ቦታም ታሪኩን ከዘረዘሩ በኋላ «የቀረውን ግን በተአምሩ መጽሐፍ እንነግራችኋለን፣ በተአምሩ ለኃጥአን የሚጠቅም ታላቅ ነገር የንስሐ ዜና አድርጎ የሠራላቸው አለና፡፡ አሁን ግን ወደ መጀመሪያው የገድሉን ነገር ወደ መናገር በእግዚአብሔር ሰላም እንመለስ» ይሉናል /ገጽ.97-98/፡፡ በገጽ. 99 ላይ ደግሞ «ግራኝ ለማጥፋት በተነሣ ጊዜ የዚህች የደብረ ብሥራት ገዳም

አበምኔት የነበረ አባ ቃለ ዐዋዲ የጻፈውን፣ አባታችን ዜና ማርቆስ ስለ ልጆቹ ያደረገውን ተአምራቱን በተአምር መጽሐፉ ኋላ እንነግራችኋለን» ይላል፡፡ ይህም ነገሮችን በየመልካቸው ለመመዝገብ ያደረጉትን ጥረት ያሳያል፡፡

ጊዜን ለማመልከት ያደረጉት ጥረት

የገድሉ ጸሐፊዎች ነገሮቹ የተፈጸሙበትን ጊዜ በትክክል ለመግለጥ ልዩ ልዩ መንገ ዶችን ተጠቅመዋል፡፡ በዚህም አብዛኞቹ ገድሎች ከሚጠቀሙበትና ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተወረሰ ከሚታመነው ድርጊቱን ብቻ ከመግለጥ ነባር ባህል ወጣ ብለዋል፡፡

ለምሳሌ ግርማ አስፈሪ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት አቡነ ዜና ማርቆስ 40 ዓመታቸው ነበረ ይሉናል፡፡ /ገጽ.88/ የግርማ አስፈሪ ጠቅላላ የንግሥና ዘመኑ 25 ዐመት መሆኑንም ገድሉ ያሳያል /ገጽ. 88/፡፡

እንደ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከሆነ ግርማ አስፈሪ የንዋየ ማርያም ስመ መንግሥት ሲሆን በሌላ ስሙ ውድም አስፈሪ ይባላል፡፡ የነገሠውም ከሰይፈ አርዕድ ቀጥሎ ከዐፄ ዳዊት 1ኛ በፊት ከ1371-1380 ዓ.ም ድረስ ነው፡፡ በመሆኑም ግርማ አስፈሪ የነገሠው በ1374 ዓ.ም ከሆነ እና በዚያ ጊዜ አቡነ ዜና ማርቆስ ዕድሜያቸው 40 ዓመት ከሆነ የተወለዱት /ከ3372 ሲቀነስ 40/ በ1331 ዓ.ም አካባቢ ነው ማለት ነው፡፡ በርግጥ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የንግሥና ዘመኑን 9 ዓመት ብቻ ነው የሚያደርጉት፡፡ የአቡነ ዜና ማርቆስ ዕድሜ በጠቅላላው 140 ዓመት ነው፡፡ በመሆኑም ያረፉት በ1471 ዓ.ም አካባቢ ነው ማለት ነው፡፡ ገድሉ ያረፉበትን ዓመት በዐፄ እንድርያስ ዘመን መሆኑን ያመለክታል ንጉሥ እንድርያስ በ1429 ዓ.ም አካባቢ ነው የነገሠው፡፡ በመሆኑም ዘመኑ ተቀራራቢ ነው፡፡

ሊቃነ ጳጳሳት

ገደለ ዜና ማርቆስ ስለ ልዩ ልዩ ሊቃነ ጳጳሳት መረጃዎች ይሰጣል፡፡ ከግብጽ ተሹመው የመጡ አባ ጌርሎስ፣ አባ በርተሎሜዎስ፣ አባ ዮሐንስ፣ አባ ማቴዎስ ስለሚባሉ ሊቃነ ጳጳሳት በመጠኑም ቢሆን ይነግረናል፡፡ ከአራቱ መካከል አቡነ ጌርሎስ እና አቡነ በርተሎ ሜዎስ ሰፋ ያለ ቦታ ይዘዋል፡፡ አባ ጌርሎስ ያረፉት አቡነ ዜና ማርቆስ በዐጸደ ሥጋ እያሉ በምሁር ገዳም ሲሆን በንጉሥ ከተማ በደብረ የረር ሊቀብሯቸው ሳለ አባታችን አገኟቸው፡፡ /ገጽ. 66/ /ምናልባት ከአዲስ አበባ ምሥራቅ በሚገኘው የረር ተራራ ይሆን/

ከዚያም ደመና ነጥቆ ሥጋቸውን ወደ ደብረ ደይ የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን ወሰደው በዚያም ተቀበሩ፡፡ ደይ ከዜና ማርቆስ ገዳም አጠገብ የሚገኝ ተራራ ነው፡፡ በተራራው ላይ ሕዝብ ናኝ /እንድርያስ/ ያሠራው ቤተ ክርስቲያን ፍራሽ ይገኛል፡፡

በገድለ ዜና ማርቆስ የእስክንድርያ ሊቃn ጳጳሳትን በተመለከተም መረጃ እናገኛለን፡፡

ፓትርያርክ ዮሐንስ

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ባረፉ ጊዜ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር፡፡ በዚያ ወቅት አንድ የሚያስገርም ነገር በገድሉ ላይ ተጽፏል፡፡ ሌሎች በዕለተ ቀብሩ የተገኙት ሁሉ እንጀራ ሲመገቡ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በድንገት በመገኘታቸው የሚመገቡት ነገር አልተዘጋጀም ነበር፡፡ የሚመገቡት የስንዴ እንጀራ መሆኑን ገድሉ ይናገራል፡፡ ይህም ከግብጻውያን ባህል ጋር የተስማማ ነው፡፡ በኋላም የስንዴ እንጀራ ተፈልጎ እንደቀረበላቸው ይገልጥልናል /ገጽ. 152/፡፡

በግብጻውያን የሊቃነ ጳጳሳት ዝርዝር መሠረት በዚህ ወቅት የነበሩት አቡነ ዮሐንስ 12ኛ /1480-83 እ.ኤ.አ/ ወይም ደግሞ አቡነ ዮሐንስ 13ኛ /1484- 1524 እ.ኤ.አ/ ናቸው፡፡ በአቡነ ዜና ማርቆስ ዕረፍት ጊዜ የተገኙት ከሁለቱ አንዱ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡

ፓትርያርክ አባ ማቴዎስ

ከደብረ ብሥራት የተነሡ 12 ደቀ መዛሙርት በግብጽ አድርገው ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ ያገኟቸው ሊቀጳጳስ የእስክንድርያው 88ኛ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ መሆናቸውን ገድሉ ይገልጥልናል /ገጽ. 324/ ፡፡እርሳቸው በመንበረ ማርቆስ በነበሩ ጊዜ በኢትዮጵያ የነበሩት ሊቀ ጳጳስ 92ኛው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ መሆናቸውን ይገልጣል፡፡ እዚህ ላይ በጣም የሚያስገርመው ነገር የመረጃ አሰጣጡ ነው፡፡ በአንድ በኩል የሊቃነ ጳጳሳቱን ስም ከነ ተራቸው /ስንተኛ እንደሆኑ መግለጡ፤/ በሌላ በኩል ደግሞ ለበለጠ ማስረጃ በእስክን ድርያ የነበሩትን ፓትርያርክ ከኢትዮጵያው ጳጳስ ጋር አጣምሮ መጥራቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ሜንያድረስ የተባለው የታሪክ ምሁር በጻፈው /The two thousand years Coptic Christianity/ በተባለው መጽሐፍ እንደ ምናገኘው አባ ማቴዎስ ሰማንያ ስምንተኛ ሳይሆን 87ኛ ፓትርያርክ ናቸው /1378-1408/፡፡ ምናልባት ኢትዮጵያውያን አበው የሚቆጥሩበትና ግብጻውያን የሚቆጥሩበት ተለያይቶ ይሆናል፤ ያለበለዚያም ደግሞ በኋላ ዘመን የተፈጠረ የገልባጭ ስሕተት ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ የጳጳሳት ዝርዝር መሠረት አቡነ ማርቆስ በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግ ሥት የነበሩትና በ1513 ወሎ የነበረው መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱ ሲከበር የባረኩት አባት ናቸው፡፡ አቡነ ማርቆስ ቤተክርስቲያኑን ሲባርኩ ዕድሜያቸው ከመቶ ዓመት በላይ ሆኖ ነበር፡፡

በዘመኑ የነበሩ አበው

ገደለ ዜና ማርቆስ ስለ አቡነ ዜና ማርቆስ ብቻ ሳይሆን ስለሌሎች በዘመኑ የተነሡ አበውም መረጃዎችን ይለግሠናል፡፡ ስለ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አባ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ፣ አባ ሕፃን ሞዓ፣ አባ አኖርዮስ ታላቁ፣ አባ ማትያስ ዘፈጠጋር፣ አባ ቀውስጦስ ዘመሐ ግል፣ በመጽሐፉ ውስጥ ታሪካቸው ይገኛል፡፡ በተለይም በገጽ.4 ላይ ከተጉለት የተነሡ ቅዱሳንን የዘር ሐረግ በዝርዝር ነው የሚያሳየን፡፡

በዘመኑ የነበሩ ነገሥታት

በዚያ ዘመን አካባቢ የተነሡ ነገሥታት ታሪክም በገድለ ዜና ማርቆስ ተመዝግቧል፡፡ የዐፄ ይኩኖ አምላክ /ገጽ. 7፣ 51-52/፡፡ ዐፄ ዓምደ ጽዮን በዘመኑ ከነበሩት አበው ጋር ከተጣሉ በኋላ እንዴት ወደ ሰላም መንገድ እንደተመለሱ /ገጽ. 248- 254/፤ ስለ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ /ገጽ. 275-279/፤ በገድሉ ውስጥ እናገኛለን፡፡

ሌሎች ታሪካዊ መረጃዎች

ገድለ ዜና ማርቆስ ለቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት እጅግ የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ታሪካዊ መረጃዎችን ይዞልናል፡፡ ስለ ጥንቱ የጉራጌ ሀገረ ስብከት /ገጽ. 31/፤ መጀመሪያ ሸዋ ውስጥ ስለተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት /ገጽ. 65/፤ የመስቀል በዓል አከባበር በዚያ ዘመን ምን ይመስል እንደነበር /ገጽ. 67/፤ በዘመኑ የነበረው የክርስቲያን - እስላም ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር /ገጽ.54፣ 118፣173፣183፣234፣285/፤ በዚያ ዘመን ስለነበረው የአርጎባ ሕዝቦች ሁኔታ /ገጽ. 290/፤ በሸዋ አካባቢ ስለነበሩ ቤተ እስራኤል /ገጽ. 67/ ስለማኅሌተ ጽጌ አጀማመር /ገጽ. 67-75/ ፤በዐፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት የሰንበት ክርክር እንዴት እንደተጀመረ /ገጽ.89፣275-279/፤ በእናርያ ይገኝ ስለ ነበረው ቀይ ወርቅ፣ /ገጽ.183/፤ ስለ በልበሊት ገዳም እና ስለ አባ ፊቅጦር /ገጽ.186 -187/፤ ጸሐፌ መንክራት ዮሐንስ ተአምረ ማርያምን በጻፈ ጊዜ እመቤታችን ያደረገችለትን ነገር /ገጽ.192/፡፡ ተአምረ ማርያም ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በፊት እንደ ነበረ መረጃ ይሰጣል፡፡ የግራኝ ሠራዊት የሸዋን አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት አድርጎ እንዳቃጠላቸው /ገጽ.378/፤ ስለ እጨጌ ዕንባቆም /ገጽ.333/፤ ስለ ደቅ ደሴት /ገጽ.114 -117/ በዚያ ዘመን ስለ ነበረው ቅዳሴ ሁኔታ /ገጽ.129-133/፡፡

የአቡነ ዜና ማርቆስ ትምህርት

ገድለ ዜና ማርቆስን ከሌሎች ገድሎች ከሚለዩት ነገሮች ሌላው ደግሞ የአቡነ ዜና ማርቆስን ትምህርት ብቻ ሳይሆን የትምህርታቸውን ቢጋር ጭምር መያዙ ነው፡፡

የአቡነ ዜና ማርቆስ የትምህርታቸው ቢጋር /ገጽ. 94-95/ በዚያ ዘመን የነበሩ አበው ምንን እንዴት ያስተምሩ እንደ ነበር የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም በላይ አባታችን ለእስላሞች ትምህርት የሰጡት መልስ /ገጽ.180/፤ ስለ ሰንበት ያስተማሩት ትምህርት /ገጽ. 256 - 267/ በገድሉ ላይ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህም በላይ አባታችን ከማረፋቸው በፊት ያደረጉት የመሰናበቻ ንግግር /ገጽ. 134-139/ በዝርዝር በገድሉ ላይ ይገኛል፡፡

በዚያ ዘመን የነበረው የተሳላሚዎች ጉዞ

በዚያ ዘመን የሸዋ ገዳማውያን ከትግራይ፣ ኤርትራ እና ግብጽ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እና የመንገዳቸውን አቅጣጫ በገድሉ ላይ ተመዝግቧል፡፡ ዐሥራ ሁለት የሚሆኑ የገዳመ ዜና ማርቆስ መነኮሳት ከሸዋ እስከ ኢየሩ ሳሌም ያደረጉት ጉዞ፣ የጉዞው አቅጣጫ፣ ያረፉበት ቦታ እና ያጋጠማቸው ነገር በዘመኑ ይደረግ የነበረው ሃይማኖታዊ ጉዞ እንዴት እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡ ከዜና ማርቆስ ገዳም ተነሥተው በወርዕ ወንዝ በኩል ወደ ደብረ አቁያጽ፤ ከዚያም ወደ አባ አሌፍ - ደብረ ሃሌ ሉያ /ደብረዳሞ/- በሱዳን በኩል በዓባይ ወንዝ በጀልባ

አድርገው ወደ ግብጽ ነበር የገቡት፡፡ በእያንዳንዱ ገዳም ይደረግላቸው የነበረውን አቀባበል ስናይ በሰሜን እና በደቡብ ገዳማት መካከል ከዘረኝነት የጸዳ ፍቅር እና መከባበር እንደነበር እናያለን፡፡

ተጓጉቹ ገዳማቱን እየተሳለሙ በግብጽ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት ሁለት ዓመት ያህል ፈጅቶባቸዋል/ገጽ. 370/፡፡

አስደናቂው የኢየሩሳሌም ክርክር

ከገዳመ ዜና ማርቆስ የተነሡት ዐሥራ ሁለቱ መነኮሳት በግብጽ በኩል ኢየሩሳሌም ገብተው አርባውን ጾም ጾመው የትንሣኤን በዓል አከበሩ፡፡ አብሮአቸው ወደ ኢየሩሳሌም የገባው የግብጹ ሊቀ ጳጳስ በምእመናን ተጋብዞ ወደ ግብጥ ሲገባ እነዚያ መነኮሳት የሚጋብዛቸው አጥተው በውጭ ቀሩ፡፡

አንድ ዮሐንስ የሚባል ሮማዊ መምህር /ምናልባት ካቶሊክ ሳይሆን አይቀርም/ በውጭ በበዓል ቀን መቀመጣቸው አሳዝኖት ወደ ቤቱ ወሰዳቸው፡፡ ለእነርሱ ምግብ ካቀረበ በኋላ ሌሎች መነኮሳት አምጥቶ አብረዋችሁ ይብሉ ብሎ ቀላቀላቸው፡፡ እኒያ የገዳመ ዜና ማርቆስ መነኮሳት በሃይማኖት ስለምንለያይ አብረን አንበላም አሉ፡፡ በዚህ የተናደደው ዮሐንስ ደብድቦ በጨለማ ቤት አሠራቸው፡፡ በኋላም በሰው ጥቆማ ዮሐንስ ተይዞ መነኮሳቱ ከገቡበት የጨለማ ቤት እንዲወጡ ተደረገ፡፡

የሀገሩ ገዥ በዮሐንስ ግፍ ተናድዶ ይሙት በቃ ፈረደበት፡፡ ከመነኮሳቱ መካከል አባ በኃይለ ማርያም የሚባል መምህር እኛ ነፍስ አንገድልም፤ ነገር ግን ስለሃይማኖቱ እንከራከርዋለን ብሎ ጠየቀ፡፡ ከዚያም ዕብራይስጥ እና የዐረብ ቋንቋ መቻሉን ሀገረ ገዥው ጠየቀው፡፡ አባ በኃይለ ማርያም የዕብራይስጥ እና የዐረብ ቋንቋን ከደብረ ሊባኖሱ መምህር ከእጨጌ ዕንባቆም መማሩን ተናገረ፡፡ ዕንባቆም በ15ኛው መክዘ መጨረሻ ወደ ክርስትና የገባ እና ከዚያም የደብረ ሊባኖስ እጨጌ እስከ መሆን የደረሰ፣ አንቀጸ አሚን የተሰኙ ሁለት መጻሕፍትንም የጻፈ የመናዊ ሰው ነው፡፡

ጉባኤው ተዘጋጀ፡፡ አባ ዳንኤል ዘገዳመ እንጦንስ፤ አባ ማርቆስ ዘገዳመ ቁስቋም፤ አባ ዮሐንስ የአትሪብ ሊቀጳጳስ፤ አባ ኤፍሬም የሀገረ መሊጣ ሊቀጳጳስ፤ አባ ሚካኤል የመርያ ኤጲስ ቆጶስ፤ አባ ሚካኤል እና አባ ማርቆስ የሚባሉ መምህራን ከግብጽ፣ ከሶርያና ዮርዳኖስ አብያተ ክርስቲያናት ተገኝተዋል፡፡ አባ ስምዖን የተባለ የመዓልቃ ገዳም አባትም በጉባኤው ተካፍሏል፡፡ የግብጹ ሊቀ ጳጳስ አባ ማቴዎስ ዳኛ ሆኖ ተገኘ፡፡ የአይሁድ እና የዐረብ አለቆች ተጋበዙ፡፡

የአርማንያ ኤጲስ ቆጶስ- አባ ባስልዮስ፤ የቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስ አባ ቴዎድሮስ፤ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ፤ የሶርያ ኤጲስ ቆጶስ አባ ዘካርያስ በጉባኤው ተሰየሙ፡፡ አባ ዮሴፍ የተባለ ሰውም የአባ በኃይለ ማርያምን እና የሮማዊው ዮሐንስን ቃል ወደ ሶርያ ቋንቋ እንዲተረጉም ተመደበ፡፡

በዚህ ሁሉ ጉባኤ ፊት ነው ክርክሩ የተካኼደው፡፡ ይህ ክርክር በጠቅላላው የገድሉን 33 ገጾች የሸፈነ ነው፡፡ አባ በኃይለ ማርያም የሚያነሣው ሐሳብ፣ የሚጠቅሰው ጥቅስ፣ የሚያቀርበው ማስረጃ በዚያ ዘመን የነበሩ ሊቃውንትን የዕውቀት አድማስ የሚያሳይ፣ ዕውቀታቸው እንደ ማር ከየአቅጣጫው የተቀመመ መሆኑን የሚመሰክር ነው፡፡ በዐረብኛ፣ በዕብራይስጥ እና በግእዝ መናገር እና ማሳመን የሚችል በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ዕውቀቱን ያስመሰከረ ሊቅ ነው አባ በኃይለ ማርያም፡፡

አባ ቃለ ዐዋዲ

የገድለ ዜና ማርቆስ ጸሐፊ አባ ቃለ ዐዋዲ ኢብን ኢብራሂም አሕመድ አልጋዚ ከምሥራቅ ወደ መካከለኛው ሸዋ እየገፋ ሲመጣ የደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም አበ ምኔት ነበር፡፡ አባ ቃለ ዐዋዲ ገድሉን እንዴት እንደ ጻፈው፤ በገዳሙ የነበሩ መጻሕፍትን እንዴት ከጥፋት እንዳዳነ ይተርክልናል፡፡ 200 መጻሕፍትን እና 16 ታቦታትን በደብረ ብሥራት ደበቃቸው፡፡ 200 መጻሕፍትን እና 7 ታቦታትን በሸር ካቢ ዋሻ /የት እንደሆነ አላወቅኩም/ ደበቀ፡፡ ካዘጋጃቸው የአባ ዜና ማርቆስ ገድል ቅጂዎች አምስቱን በጉራጌ ይገኝ በነበረው በምሁር ገዳም፤ ሁለት የገድለ ዜና ማርቆስ ቅጂዎችን እና 300 መጻሕፍትን በጋይ ዋሻ /ከዜና ማርቆስ ገዳም አጠገብ የሚገኝ/፤ 400 መጻሕፍትን ወተጌ በምትባል ሀገር ባለች ዋሻ፤ አንድ ገድለ ዜና ማርቆስ እና 100 መጻሕፍትን በእንቡ ልቡልና ዞረት ገደል በሚገኝ ዋሻ /ቀወት ውስጥ/ አስቀመጠ፡፡

ከዚህ በኋላ 400 መጻሕፍትን እና 2 ታቦታትን ይዞ፤ 1200 ደቀ መዛሙርት አስከትሎ፤ 14 ታቦታት የያዙ 547 መነኮሳት አጅበውት ወደ በጌምድር ተጓዘ፡፡ /ገጽ. 379/ ከላይ የተጠቀሱ መጻሕፍትን ስንደምራቸው 1608 መጻሕፍት በገዳሙ ውስጥ እንደነበሩ ያስረዳናል፡፡ ለእኔ እጅግ በጣም የሚደንቅ መረጃ ነው፡፡ አባ በኃይለ ማርያም ያለ ምክንያት በሙሉ ልብ በኢየሩሳሌም አደባባይ ስለ ሃይማኖቱ ልከራከር አላለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ መጻሕፍት የተከበበ ሊቅ ራሱ መጽሐፍ ማለት ነውና፡፡

በገዳሙ ውስጥ ከ1200 በላይ ደቀ መዛሙርት /ተማሪዎች/ እና ከ547 በላይ መነኮሳት እንደ ነበሩ ስናነብ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ በዚያ ጊዜ የሊቃውንት መፍለቂያ የገዳማውያን መናኸርያ እንደ ነበር ያሳየናል፡፡ አባ ቃለ ዐዋዲ የደበቃቸው እነዚያ መጻሕፍት ከጦርነቱ በኋላ ይውጡ፣ ይቅሩ መረጃው የለኝም፡፡

በዚያ ጊዜ ገዳሙ ለሌሎች የገጠር አብያተ ክርስቲያናት መጋቢ አስተዳዳሪ ሆኖ ስለሚያገለግል፤ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እና መናኝ ካህናት ታቦታትን ከገዳም ስለሚያገኙ በገዳማት ውስጥ ብዙ ታቦታት ይገኙ ነበር፡፡ በገድለ ዜና ማርቆስ ተመዝግቦ እንዳገኘነው በገዳሙ ውስጥ 57 ታቦታት ነበሩ፡፡

ገድለ ዜና ማርቆስ በተደጋጋሚ ሊነበብ፤ ከልዩ ልዩ ነገሮች አንፃር ሊተነተን የሚገባው ገድል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገድላት እንዴት ተጻፉ፣ ምንጫቸው ምን ነበር? ማን ጻፋቸው? እንዴት ሊጠበቁ ቻሉ? ከታሪክ ጋር ያላቸው ተዛምዶ? ወዘተን ለመሳሰሉ የዘመኑ ጥያቄዎች መልስ ከሚሰጡት ገድላት አንዱ ነው፡፡

ገድለ ዜና ማርቆስ አንዳንድ ወገኖች ገድልን በተመለከተ ያላቸውን ደከም ያለ አስተሳሰብ ሊያርምላቸው የሚችልና ጥናታቸውን ከንቀት ሳይሆን ከአክብሮት እንዲጀምሩ የሚያደርግ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

የጻድቁ በረከት ይደርብን፡፡

6. ጲላጦስ

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በኢትዮዽያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር ET 603 ከዱባይ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ላይ ነበርኩ፡፡ ሻርጅያ በተባለው ከተማ አንድ ኢትዮ ጵያዊ የጠየቀኝን ጥያቄ አወጣለሁ፣ አወርዳለሁ፡፡ ወቅቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ዘንድ ‹ሰሙነ ሕማማት› የሚባለው ነው፡፡ ሚያዝያ 17 ቀን ስቅለት ከሁለት ቀናት በኋላ ደግሞ የትንሣኤ በዓል ይከበራል፡፡

ያ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ፡- ‹‹መስፍኑ ጲላጦስ ክርስቶስን ለምን አሳልፎ ሰጠው?›› የሚል ጥያቄ ነበር ያነሣልኝ፡፡ ለጊዜው ይኾናል ያልኹትን ማብራሪያ ሰጠኹት፡፡ በኋላ ግን እኔው ራሴ በነገሩ ማሰላሰሌን ቀጠልኹ፡፡

ጴንጤናዊው ጲላጦስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ (በ34 ዓ.ም) በኢየሩሳሌም የሮምን ንጉሥ በመወከል የይሁዳ መስፍን ነበር፡፡ ክርስቶስ በፊቱ ተከስሶ የቀረበውም ከዚህ ሥልጣኑ የተነሣ ነበር፡፡ በዘመኑ ይደረግ እንደ ነበረው ተከሳሹን አስቀርቦ ጠየቀ፡፡ እር ሱን ያስረዳሉ የተባሉ የከሣሽ ምስክሮችንም ጠየቀ፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ‹‹ወንጀለኛ›› ሊያስደርግ የሚችል ምንም ነገር ዐጣ፡፡ ሚስቱም በሕልሟ ያየችውን ነገር በመግለጥ በርቱዕ መንገድ ብቻ ፍርድ እንዲሰጥ ነገረችው፡፡

እነዚህ ሁሉ ተደማምረው መስፍኑ ጲላጦስ ክርስቶስን፡- ‹‹ለሞት የሚያበቃው ቀርቶ የሚያሳስረው ጥፋት አላገኘሁበትም›› ሲል ደመደመ፡፡ አይሁድ ይህን ሲሰሙ ‹‹ይህን ካደረግኽ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም›› የሚል ፖለቲካዊ ተቃውሞ በከረረ ሁኔታ መሰንዘር ጀመሩ፡፡ ጲላጦስ ነገሩን ለማብረድ በማሰብ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስን ገርፌ ልስቀልላችሁ›› የሚል አማራጭ ሐሳብ አቀረበ፡፡ ከሳሾቹ አይሁድ ግን ‹‹ሞቶ ካላየነው አንተ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም›› ብለው ነገሩን አጠነከሩት፡፡ በመጨረሻም መስፍኑ ጲላጦስ ተሸነፈ እና ይሙት በቃ ፈረደ፡፡

የተከሰሰው እና በፍርድ አደባባይ የቆመው ክርስቶስ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ዳኛው ዐውቋል፡፡ ማወቅ ብቻም ሳይኾን በአንደበቱ መስክሯል፡፡ ሕጉም ንጹሕ የኾነ ሰው ከተከሰሰበት ነገር ነጻ እንዲኾን እና እንዲሰናበት ያዝዛል፡፡ ታዲያ ጲላጦስ ይህን ሁሉ እያወቀ ለምን የተዛባ ፍርድ ፈረደ?

አንድን ነገር ማወቅ፣ በጉዳዩም ማመን እና ላመኑበት እውነት እስከ መጨረሻው በጽንዐት መቆም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ጲላጦስ የዕውቀት ችግር አልነበረበትም፡፡ በዘ መኑ በነበረው የፍርድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዐት መሠረት የከሳሾቹን ምስክሮችም ኾነ ተከሳሹን በፊቱ አቁሞ ጠይቋል፡፡ በዚህም ክርስቶስ ምንም ወንጀል የሌለበት መኾኑን ዐውቋል፡፡ ነጻ መኾን እንዳለበትም አምኗል፡፡ ይህን ዕውቀቱን እና እምነቱን በተግባር እንዳያውል ግን አንድ ነገር ከለከለው - የሚያጣው ጥቅም፡፡

ክርስቶስ የተከሰሰበት አንዱ ወንጀል ‹‹ራሱን ከቄሣር ጋር በማስተካከል ‹ንጉሥ ነኝ› ይላል›› የሚለው ነው፡፡ በመኾኑም ክርስቶስን ነጻ ቢለቀው ‹‹ከቄሣር ሌላ ንጉሥ አለ ብሎ ያምናል›› ተብሎ ሊወነጀል፣ በኋላም ሥልጣኑን ሊያጣ ነው፡፡ ጲላጣስ እውነ ትን ተቀብሎ፣ ለእውነት መሥዋዕትነት ከፍሎ ሥልጣኑን ከሚያጣ እውነትን ሠውቶ በሥልጣን መቆየትን መረጠ፡፡ ያመነው ነገር፣ የተናገረው ነገር እና የፈረደው ፍርድ ተለያየ፡፡

አንዳንድ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚያምኑበት፣ በየመድረኩ የሚደሰኩሩት፣ አጠናን ብለው የሚተነትኑት፣ ከልብ ጓደኞቻቸው ጋር ሲያወጉ የሚዘረዝሩት፣ ‹‹ቢኾን መልካም ነው›› የሚሉት እና በቦታው ላይ ኾነው የሚፈጽሙት የሚለያየው ለእውነት መቆም የሚያስከፍለው ዋጋ ስላለ ነው፡፡

አንድ ዳኛ የሚተቸው፣ የሚተነትነው፣ በኅሊናው የሚያምንበት እና በልቡ የሚያመላልሰው ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ከተጋጨ፣ አንድ ባለሥልጣን እውነት ነው ብሎ የተቀበለው እና ትክክል ነው ብሎ የወሰነው ከተለያየ፣ አንድ ባለሞያ የጥናቱ ውጤት እና እርሱ ለአለቃው ያቀረበው ውጤት ከተቃረነ እንዳያጡት የሚፈሩት ጥቅም አለ ማለት ነው፡፡

በስብሰባ ተቀምጠው አለቆቻቸውን ወይም የሚመጣውን መከራ ፈርተው አንዳች ነገር የሚወስኑ ነገር ግን በልቡናቸው የተቀበሉት እውነት ከወሰኑት ጋር የሚጋጭባቸው ሰዎች ይህን በሽታ የሚያሥታግሱት ‹‹ምን ይደረግ ብለህ ነው፤ በግድ፣ ሳናም ንበት፣ አስፈራርተው፣ ሐሳባችንን ሳይቀበሉ ቀርተው . . .የማይኾን ነገር ወሰኑ›› እያሉ ለሚቀርባቸው ሰው በማውራት ነው፡፡ የውስጡን ግጭት በወሬ ነው የሚያስተነፍሱት፡፡

ከወዳጆቻቸው ጋር ሲቀመጡ የተቹትን፣ የነቀፉትን እና የተቃወሙትን ነገር በቦታው ሲኾኑ ግን ‹‹የጠሉት ይወርሳል. . . ›› የተባለው ደርሶባቸው እነርሱ የባሱ ኾነው ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሚያምኑት ነገር እና በሚሰጡት መግለጫ መካከል ቅራኔ ሲያጋጥማቸው በረዥም ዐረፍተ ነገሮች፣ ኧ. . .ኧ. . .ኧ በሚል የሚታክት የነገር ጉተታ ወይም ደግሞ ‹‹አበረታች ነው፤ አስደናቂ ነው፤ ልዩ ነው፤ ብሩህ ነው›› በሚሉ የማይለኩ ነገሮች ሊያሥታግሱት ይሞክራሉ፡፡

ሁለት እና ሁለት አራት መኾኑን እያወቁ፣ ጠረጴዛቸው ላይ በሚገኘው ወረቀት ይኽንኑ ሳያስቡት እየሞነጫጨሩ፣ 2 እና 2 ‹‹አምስት ነው›› ብለው ለማሳመን ሲሉ የማርስ እና የጁፒተርን ልምድ የሚጠቅሱት ኅሊናቸው እና ንግግራቸው ሲጋጭባቸው ነው፡፡

‹‹የእንጀራ ጉዳይ ነው፤ ልጆቼን ላሳድግ ብዬ ነው፤ ‹ከሰው ጋር ሲኖሩ ሞኝ ኾኖ አህያ ሲጭኑ ሦስት ኾኖ› ስለሚባል ነው፤ ክፉ ቀንን እና ቅዝምዝምን ጎንበስ ብሎ ማሳ ለፍ ስለሚገባ ነው፤ ብቻዬን ለውጥ ላመጣ ስለማልችል ነው . . .›› የሚባሉት ማብራሪያዎች ሁሉ ከነመሰሎቻቸው የዚሁ ጲላጦሳዊ ችግር መገለጫዎች ናቸው፡፡

ሰው በመኖር ብቻ ሳይኾን በመሞትም ያሸንፋል፡፡ ሰዎችን ከእንስሳት ከሚለዩ አቸው ነገሮች አንዱ ሰዎች በሞት ሊገታ የማይችል አሸናፊነት ሊኖራቸው ስለሚችል ነው፡፡ እነ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እነ ማኅተመ ጋንዲ፣ እነ አብዲሳ አጋ ተገድለዋል፤ ነገር ግን አሸንፈዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለሰማዕትነት እንዲበቁ ያደረጋቸው የሚሠሩት ሥራ ከሚያምኑበት ነገር ጋር እንዲቃረን ባለመፍቀዳቸው ነው፡፡

የተማረው እና የሚያምንበት ሌላ ኾኖ ጥቅም ብቻ በሚያስገኝለት ክሊኒክ የሚሠራ፣ ጥቅም ብቻ ባለበት ትምህርት ቤት የሚያስተምር፣ ጥቅም ብቻ ባለበት የፋይናንስ ሥራ ላይ የተሠማራ፣ ጥቅም ብቻ በሚገኝበት የጋዜጠኝነት መስክ የሚኳትን ስንቱ ነው !! ውሎ አበል፣ የተሻለ ክፍያ፣ የውጭ ዕድል፣ ሥልጣን፣ የወንበር አበል፣ መኪና፣ የሪሴፕሽን ግብዣ፣ ያማረ ቢሮ እና የተደላደለ ቤት ይቀርብኛል ብሎ የማያምንበትን የሚሠራ ስንቱ !!

ጲላጦስ ውሳኔውን ወስኖ ክርስቶስ ከተሰቀለ በኋላ በሥራው ሥራ መጸጸት ጀመረ፡፡ የውስጡ እምነት እየገፋ፣ ኅሊናውንም ዕረፍት እየነሳው መጣ፡፡ ያ ሰዓት ግን ምንም ሊያደርግ የማይችልበት ሰዓት ነበር፡፡ የእርሱ ፍርድ ተፈጻሚ ኾኖ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሏል፡፡ በታሪክ እንደሚነገረው ጲላጦስ እስከ ዕድሜው ፍጻሜ በዚያ በሥራው ሥራ እንደ ተጸጸተ፣ ኅሊናውም ሰላም ሳያገኝ ነው የኖረው፡፡

ነገር ካለቀ በኋላ ከመጸጸት እና የኅሊና ሰላም ከማጣት ከሚያምኑት እውነት ጋር መቆም እጅግ የተመረጠ ነው፡፡ ጦርነቱ ሲያበቃ፣ ፖለቲካው ሲቀየር፣ አስቸጋሪው ዘመን ሲያልፍ፣ የችግሩ ጊዜ ሲጠናቀቅ ‹‹እንዲህ ብዬ ነበር፣ እንዲህ ማድረግ አልነበረብኝም፤ ያደረግኹት ተገድጄ ነው፤ ተጽዕኖ ነበረብኝ፤ ለታሪክ ምስክርነት ለመትረፍ ብዬ ነው፤ በሠራሁት ሥራ አዝናለሁ፤ ተሰምቶኛል፤ ወዘተ ወዘተ›› ለችግሩ መፍትሔ አይሆኑም፡፡

የሞተው አይነሣም፤ የደኸየው ሀብት አያገኝም፤ የተነጠቀው አይመለስም፣ ትዳሩን የፈታው አያገባም፤ ያለቀ ዕድሜ አይተካም፤ ያመለጠ ዕድል አይገኝም፡፡ እናም ውስጣዊ ሰላም ይጠፋል፤ ጸጸት እንደ እግር እሳት ይበላል፡፡

በስታድዬሙ ዙሪያ ተሰብስቦ መተቸት፣ ሐሳብ መስጠት፣ ‹‹ለምን አልገባም›› ብሎ መውቀስ፣ ጎል ሲገባም መጨፈር፣ አሠልጣኝ እና ተጨዋችን መሳደብ እጅግ በጣም ቀላል ነው፡፡ ከዐሥራ አንዱ ተጨዋቾች እንደ አንዱ ኾኖ ውጤት የሚያመጣ ጨዋታ መጫወት ግን ከባድ ነው፡፡

የጨዋታ ጊዜው ሲጠናቀቅ ‹‹ይህ ቢደረግ እንዲህ ይኾን ነበር፤ ያ እንዲህ ቢያደረግ ይገባ ነበር፤ እገሌ ይህን l!ሠራ አይገባም ነበር፤›› እየተባለ ይተነተናል፡፡ እንዲህ ያለው ነገር ለወደፊቱ ጠቃሚ ልምድ ይገኝበት ይኾናል፡፡ ያን ጨዋታ ግን አይቀይረውም፤ የገባው ገብቷል፤ የተሳተው ተስቷልና፡፡

እናም ነገር ካለቀ በኋላ እንዲህ የኾነው እንዲያ ስላልኾነ ነው ከማለት በወቅቱ ማድረግ ያለብንን ነገር ማድረግ ነው፡፡ ‹‹አገራችን በባዕድ መያዝ የለባትም›› ብለው ያመኑበትን እምነት በተግባር ለመግለጥ በዐድዋ ዘመቻ መሥዋዕትነት የከፈሉት ጀግኖ ቻችን ኢትዮጵያን በነጻነት ለማቆየት ችለዋል፡፡ ነገር ግን ‹‹ከጣሊያን የምናገኘው ጥቅም ይበልጥብናል›› ብለው ባይዘምቱ ኖሮ ታሪክ በተቀየረ ነበር፡፡ ታዲያ ዛሬ እነዚያ ዘማቾች ያልዘመቱበትን ምክንያት ቢያስረዱን እንኳን የዐድዋን ድል ሊተካው አይችልም፡፡ በክፉ ቀን በጦርነት ሜዳ የተወለዱት ጀግኖች አባቶቻችን ግን መሥዋዕት ኾነው በሞታቸው ወራሪን አሸነፉ፡፡

ከስብሰባ ሲመጡ፣ ነገር ሲያልቅ፣ ጨዋታው ሲያበቃ፣ መከራው ገሸሽ ሲል ሺሕ ጊዜ ከማውራት ‹‹ጀግና የሚወለደው በጦር ሜዳ ነው›› ብሎ እዚያው ላይ ላመኑበት መሟገት ነው ሞያ ማለት፡፡

ስለ የሌሊት ወፍ ‹አፈጣጠር› የሰማሁትን እዚህ ላይ ባነሣው መልካም ነው፡፡ በጥንት ጊዜ የሌሊት ወፍ የሚባል ነገር አልነበረም አሉ፡፡ አንድ ጊዜ ግን ወፎች ተሰብስበው የሚወዳድቀውን ጥራጥሬ አይጦች እየበሉ ጦማቸንን ስላሳደሩን አይጦችን የሚከ ታተል፣ መልኩ አይጥ የሚመስል የወፍ ዘበኛ እንቅጠር ብለው ማስታወቂያ አወጡ፡፡ በዚህ ጊዜ ጉድጓድ ውስጥ መኖር የመረራት አይጥ ክንፍ አሰፍታ ‹‹ወፍ ነኝ›› ብላ ቀረበች፡፡ ምንም እንኳን ዘመዶቿ ‹‹አይጦች ጥራጥሬ መብላት የለባቸውም›› የሚሉትን ብትቃወምም ለመኖር ስትል ግን ለዘበኝነቱ ተስማማች፡፡ ጥርሷን አይተው እንዳያባርሯትም በድንጋይ ሰብራ አረገፈችው፡፡ ለብዙ ዘመን በዘበኝነቱ ጸንታ የገዛ ዘመዶቿ የሆኑትን ወፎች

ስታስበረግግ ኖረች፡፡ እየቆየች ግን ጥርሷ እያደገ፣ ፀጉርዋም እየታወቀ ሄደ፡፡ ለመደበቅ ብትሞክርም አልቻለችም፡፡ ወደ ድሮው ኑሮዋ እንዳትመለስ አይጥነቱን ረስታዋለች፡፡ ያደረገችው ነገር እየጸጸታት ስለ መጣ ከሁሉም ለመራቅ ስትል በሌሊት ብቻ መንቀሳቀስ ጀመረች ይባላል፡፡ የሌሊት ወፍ አይጥም ወፍም ኾና የኖረችው በዚህ ጠባይዋ ነው ይባላል፡፡

ትናንት የሠሩት ነገር ‹ጥርሱ እየበቀለ፣ ፀጉሩም ብቅ እያለ› እያስቸገራቸው ስን ቶች ወገኖቼ መከራ እያዩ ነው፡፡ ውስጣቸው አይጥ ኾኖ ላያቸው ወፍ እየኾነ፡፡ እንደ አይጥ እያሰቡ፣ እንደ ወፍ ሊሠሩ እየሞከሩ፣ መጨረሻቸው በጸጸት ጨለማ ውስጥ መሰወር ይኾናል፡፡

የእስክንድርን ታሪክ የጻፈው የግብጹ ንጉሥ በጥሊሞስ እንዲህ ይተርክልናል፡፡ በአንድ ትንሽ ጦርነት የእስክንድር ጦር ብዙ ጉዳት ደርሶበት አሸነፈ፡፡ የዚህ ጦርነት ጉዳት ያንገበገበው አንድ ወታደር ‹‹የአመራር ድክመት ባይኖር ኖሮ ይህን ጦርነት ለማ ሸነፍ ይህን ሁሉ መሥዋዕትነት መክፈል አያስፈልግም ነበር›› ብሎ በመተቸቱ ተከስሶ እስክንድር ዘንድ ቀረበ፡፡ ‹‹ይህ ዓይነቱ ሐሳብ ጦሩን ያዳክማል፤ ጠላትን ያስደስታል፤ መደፋፈር ያመጣል፤ ለሌሎች ክፉ አርአያ ይኾናልና ወታደሩም ይቀጣ፣ ሐሳቡም ስሕ ተት መኾኑ ይነገር›› ብለው የጦር ጀኔራሎቹ እስክንድርን ወጥረው ያዙት፡ ፡

ታላቁ እስክንድርም ‹‹እንደ ንጉሥነቴ ይህ ሰው ጥፋተኛ ነው፤ የሰነዘረውም አስተ ያየት ስሕተት ነው፤ እንደ እውነቱ ከኾነ ደግሞ ይህ ሰው ትክክል ነው፤ እኛ ጥፋተኞች ነን፡፡ እኔ ደግሞ እንደ ንጉሥነቴ ሳይኾን እንደ እውነቱ ፈርጃለሁ›› ብሎ ተናገረ፡፡

እኛስ?

7. የኔ ጀግና :- ይድረስ ለ CNN ቴሌቭዥን ጣቢያ

በቀደም ዕለት ፕሮግራማችሁን ስከታተል የዓመቱን የCNN ጀግኖች ምረጡ የሚል ማስታወቂያ በተደጋጋሚ አየሁ፡፡ ነገር ግን ምርጫው ካቀረባችኋቸው ዕጩዎች መካከል ሆነብኝና ተቸገርኩ፡፡ ምክንያቱም እኔ ልመርጣት የምችላት የኔዋ ጀግና አልተካተተችምና፡፡ እናንተ ካቀረባችኋቸው ዕጩዎች የተለየች፣ ምናልባትም ሥራዋን ባለማወቅ የተነሣ ማንም በዕጩነት ሊያቀርባት የማይችል አንዲት ጀግና አለች፡፡ የእኔ ጀግና እርሷ ነች፡፡

በ1960ዎቹ መጨረሻ የዚህች ሀገር ልጆች ጎራ ለይተው ቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር ብለው ተጨፋጨፉ፡፡ ከሁለቱም ወገን እልፍ አእላፋት ልጆች ደማቸው እንደ ጨው ተዘርቶ ቀረ፡፡ አባታችን ከቤት እንደወጣ የቀረው ያኔ ነበር፡፡

በኋላ በኋላ እንዳወቅኩት አባቴ ቀይ ሽብር ተፋፍሞበት መንገድ ላይ ተጥሎ ኖሯል፡፡ ለእናቴ ከጎዘኑ በላይ የጎዳት አስከሬኑን ለማንሣት በየቢሮው ደጃፍ፣ በየባለሥልጣናቱ ግቢ ያየችው መከራ፣ የከፈለችው ጉቦ ነው፡፡ እንዲህ ላለው ነገር እንግዳ በመሆኗ ሰዎች ይሆናል ያሏትን ሁሉ ታደርግ ነበር እንጂ ለውጤቱ ርግጠኛ አልነበረችም፡፡

ቀብሩ በዘመድ አዝማድም፣በጉቦም ተፈጸመ፡፡ ቀጣዩ ኑሮ ግን በዘመድ እና በጉቦ የሚዘለቅ አልሆነም፡፡ የቤት እመቤቷ እናታችን እናትም አባትም ሆነች፡፡ ቤቱ የሚተዳደረው በአባታችን ደመወዝ እና በእናታችን ጉልበት ነበር፡፡ አሁን የመተዳደርያውን ገንዘብ ማምጣቱም ሆነ የቤቱን ሥራ መሥራቱም የርሷ ኃላፊነት ነበር፡፡ እኛ ልጆቿ ደግሞ እንዳናግዛት ለሥራ ያልደረስን ለመብል ያላነስን ሕፃናት ነበርን፡፡ ለእናታችን የአባትነት ኃላፊነቱ እንጂ ወጉ እና መዓርጉ አልተረፋትም፡፡

እናታችን የመጀመርያውን ብርቱ ትግል ያደረገችው ሕልውናዋን ለማስጠበቅ ነው፡፡ አጋጣሚውን ለመጠቀም ያሰቡ ሰዎች የተከራየነውን ቤት መውሰድ ፈለጉና ቀበሌ ተጠራች፡፡ «አሁን ባለቤትሽ ስላረፈና አንቺም ገቢሽ አነስተኛ ስለሆነ ይህንን ሰፊ የቀበሌ ቤት ለቅቀሽ በዐቅምሽ ሌላ አነስ ያለ ቤት ውሰጅ» ተባለች፡፡ መከፈል እንደምትችል፤ ስትቸገር ያን ጊዜ ጉዳዩን እንደምታመለክት ለማን ታስረዳው፡፡ ለመናገር እንጂ ለመስማት ዝግጁ የሆነ ባለሥልጣን ማግኘቱ ነበር ከባዱ፡፡ ያውምኮ የቤቱ ኪራይ ሃያ አምስት ብር ነበር፡፡ መቼም አንዳንድ ደግ ሰው በየዘመኑ አይጠፋም፡ ፡ ከአመራሮቹ መካከል በደረሰባት ነገር ያዘኑ ሰዎች ረድተዋት በስንት መከራ ቤታችንን ከመልቀቅ ተረፍን፡፡

በርግጥ ለእናታችን ያችን ሃያ አምስት ብር ማግኘቱም ቢሆን ከባድ ነበር፡፡ ሥራ ለመቀጠር ስትሄድ ያ የቀይ ሽብር ታሪክ ቀድሟት ይደርስና ምክንያቱንም ውጤቱንም በማታውቀው ነገር፣ የርሷ ፍላጎት እና ተሳትፎ ይኑርበት አይኑርበት ባልተጣራ ነገር አዝና ትመለሳለች፡፡ ከሁሉም የሚከብዳት ግን ባሏ የሞተባት ሴት ሁሉ ለሥጋዊ ነገር ትንበረከካለች ብለው በሚያስቡ ወንዶች የሚመጣባት ፈተና ነው፡፡ አንዳንዶቹ የሥራ ፈተናው ቤታቸው ይሰጥ ይመስል ቤታቸው ይቀጥሯታል፡፡ ሌሎቹ የመሥሪያ ቤቱ ቢሮ ጠባቸው ሆቴል የተከራዩ ይመስል ሆቴል ይቀጥሯታል፡ ፡

እንጂራ ነውና መቅረት እየከበዳት፣ ችግሩን ታውቃለችና መሄዱም እየዘገነናት ለኛ ስትል አንድ ሁለት ጊዜ ሞከረችው፡ ፡ ነገር ግን የተፈለገው ዕውቀቷ እና ጉልበቷ ሳይ ሆን ሴትነቷ መሆኑን ስታውቅ እንደ አራስ ነበር ተቆጥታባቸው፣ እንደ አንበሳ አግሥ ታባቸው ትመጣና ቤት ገብታ ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች፡፡ ጸጋዬ ገብረ መድኅን «ወንድ ልጅ ብቻውን ነው የሚያለቅሰው» ብሎ ነበር፡፡ ወንድ ልጅ ብቻ አይደለም ብቻውን የሚያለቅሰው፡፡ አባትም እናትም ሆና ልጆቿን

የምታሳድግ ጀግና እናትም ብቻዋን ነው የምታለቅሰው፡፡ ልጆቿ እንዳይረበሹባት ልጆቿ ፊት አታለቅስም፡፡ መጠቃቷ እንዳይታ ወቅበት በአደባባይ አታለቅስም፡፡ ብቻዋን ነው የምታለቅሰው፡፡

ወርቆቿን ሸጠች፣ጥሩ ጥሩ ልብሶቿን ሸጠች፣ የቤት ዕቃዎቿን ሸጠች፣ በደኅና ጊዜ የገዛ ቻቸውን ጫማዎቿን ሳይቀር መሸጧን ከቤታችን ሲጠፉ ነበር የምናውቀው፡፡ በኋላም እኛን ሁሉ ያሳደገችውን አንዲት አነስተኛ ሱቅ ከፈተች፡፡ እኛ ትምህርታችን እና ኑሯ ችን አልተቋረጠም፡፡ የእርሷ ሰውነት ግን እየተለወጠ ሲሄድ ይታወቀናል፡፡ እርሷ ከኑሮ ጋር ብቻ አይደለም የታገለችው ከበሽታ ጋር ጭምር ነው፡፡ ሕመሟ እንዳይታወቅባት በውስጧ ትቋቋመው ነበር፡፡ ብተተኛ ብትተኛ እንኳን ከሁለት ቀን በላይ አትተኛም፡፡ በኋላ በኋላ ግን በሽታውንም አሸነፈችው መሰል አያማትም ነበር፡፡

ዛሬ ዛሬ ሳስበው የሚገርመኝ ነገር አለ፡፡ ግዥልን ያልናትን ሁሉ ትገዛለች፡፡ አድርጊልን ያልናትን ሁሉ ታደርጋለች፡፡ አንድም ቀን አትማረርም፡፡ ከየት እንደምታመጣው አላውቅም፡፡ እኛ ፊት እንደ ድሮው ትጫወታለች፡፡ ለትምህርታችን የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ አልተጓደለም፡፡ ከየት ነበር የምታመጣው? የሚለውን ሳስበው ይገርመኛል፡፡ እንደ ጧፍ አብርታ፣ እንደ ሻማ ቀልጣ ድህነትን አሸንፋ ልጆቿን አስተምራ ለሀገር ያበረከተች ይህች የጀግኖች ጀግና አይደለችም?

ዛሬ ዛሬ «ሃርድ ቶክ» ላይ ቀርበው ከባድ ከባድ ጥያቄዎችን በድፍረት የሚመልሱ ተጠያቂዎች ሲያደነቁ እሰማለሁ፡፡ ባታውቋት ነው እንጂ የኔ እናት ስንት «የሃርድ ቶክ» ጥያቄ በድፍረት መልሳለች መሰላችሁ፡፡ ያውም በቴሌቭዥን ሳይሆን በሕይወት፡፡ አባታ ችን የት ሄደ? ለሚለው የኛ የልጆቿ ጥያቄ ሁልጊዜ መልስ መስጠት አለባት፤ ለምን ሌላ ባል አታገቢም ? ለሚለው የዘመዶቿ ጥያቄ መልስ መስጠት አለባት፤ እንዴት እርሱ የለም ብለሽ እንዲህ እና እንዲያ ታደርጊያለሽ? ለሚለው የአባታችን ዘመዶች ጥያቄ መልስ መስጠት አለባት፤ በብቸኝነቷ ሊጠቀሙ ለሚፈልጉ ዘለሌዎች መልስ መስጠት አለባት፤ እንዲህ ለምን አታደርጊም እንዲያ ለምን አታደርጊም እያሉ ያለ ፍላጎቷ ሊያስኬዷት ለሚፈልጉ ጎረቤቶቿ እና ወዳጆቿ መልስ መስጠት አለባት፡፡ እና ይህች ጀግና አይደለችም ትላላችሁ፡፡ «ሀርድ ቶክ»ን ሳይሆን «ሀርድ ላይፍ»ን የተቋቋመች፡

እንዲያ ብቻዋን እየታገለች፡፡ አገር በሙሉ ድንኳን ተክሎ ለአባቴ ልቅሶ መቀመጡን እያወቀው፣ ጀግንነቷን ግን የሚያደንቅላት አልነበረም፡፡ ከፍ እያልኩ ስሄድ የሚያናድደኝ አንድ ነገር ነበር፡፡ ሠርግ እና ተዝካር ስትጠራ በመጥሪያ ወረቀቱ ወይንም ካርዱ ላይ የአባቴ ስም ይጻፋል እንጂ የርሷ ስም አይጻፍም፡፡ እድር የምንከፍለው፣ የቤት ኪራይ የምንከፍለው፣ መብራት እና ውኃ የምንከፍለው በአባቴ ስም ነው፡፡ ለምን? እርሷኮ አባትም እናትም ሆና እየኖረች ነው፡፡

በሠፈራችን የአባቴ እና የእናቴ እድር የተለያየ ነው፡፡ የወንድ እድር እና የሴት እድር፡፡ አባቴ በሕይወት እያለ እርሷ ወደ ሴት እድር እርሱ ደግሞ ወደ ወንድ እድር ነበር የሚሄዱት፡፡ አሁን ግን አባትም እናትም ሆናለችና በሁለቱም እድር መገኘት ያለባት፤ መከፈል ያለባት እርሷው ናት፡፡ የሴት እድር በጓዳ ሥራ መጠመዱ የተለመደ ስለሆነ እዚያ ስትሄድ እርሷም ጓዳ ገብታ ትሠራለች፡፡ የሚገርመኝ ግን የወንድ እድርተኞች የመጀመርያ ቀን ድንኳን ተክለው ድንኳን ውስጥ ከብበው ካርታ ከመጫወት ውጭ አንዳችም ሥራ የላቸውም፡፡ እርሷ የወንድ እድር ከፍያዋን ብትከፍልም እንደ ወንድ እድርተኞች ድንኳን ውስጥ እንድትቀመጥ የሚፈቅድላት ግን የለም፡፡ ለከፍያው እና ለጥሪው ወንድ፣ ለሥራው ግን ሴት ናት፡፡

ማኅበረሰቡ ለጀግንነቷ ዕውቅና ላለመስጠት ያላደረገው ጥረት አልነበረም፡፡ በሴትነቷ የሚደርስባትን ጥቃት ሁሉ ችላ፤ አባትም እናትም ሆና ባሳደገቸ ልጆቿን «የሴት ልጅ» እያለ ይሳደባል፡፡ ለመሆኑ ግን የሴት ልጅ ያልሆነ ማን አለ፡፡ «የሴት ልጅ» ማለት ስድብ ነውን? ኢየሱስ ክርስቶስስ ቢሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ቁርአኑም እንደሚሉት ያለ አባት ከእናት አይደለም እንዴ የተወለደው? «የሴት ልጅ» ማለት እንዴት ስድብ ይሆናል፡፡ ለመሆኑ የፈጣሪን ሥራ ተካፍላ የምትሠራ ሴት አይደለችም ወይ? ልጅን አርሞ እና ቀጥቶ ማሳደግ የሚችለው ወንድ ብቻ ነው ያለው ማነው?

እንዲያውም አንድ ጊዜ ታናሽ ወንድሜ ነገሩ ሁሉ አበሳጨውና «ያለ አባት ይህንን ሁሉ ለፍተሽ አሳድገሽ ለምንድን ነው በአንቺ ስም የማልጠራው? ይሄው ሰው ሁሉ የሠራውን ሕንፃ በስሙ እየሰየመ አይደለም? ታድያ አንቺ በአካልም፣ በዕውቀትም፣ በምግ ባርም አንፀሽ ያሳደግሺውን ልጅ በስምሽ ብትጠሪ ምን ነውር አለው? እንዲያውም ከዛሬ ጀምሮ የአባቴን ስም አስቀይራለሁ» ብሎ አስደንግጧት ነበር፡፡ የርሱን ሃሳብ ለማስ ቀየር በትጉት ሰብእና እንዴት እንደ ደከመች ትዝ ይለኛል፡፡ እርሷ ልፋቱን እና ውጤቱን እንጂ ስሙን እና ሽልማቱን መች ትፈልገዋለች፡፡

እኛን ለማሳደግ ለፋች፡፡ ቆይቶ ደግሞ ማደጋችንም ፈተና ሆነባት፡፡ ከሦስቱ ልጆቿ ሁለታችን ወንዶች ስለነበርን ብሔራዊ ውትድርናውን ትፈራው ነበር፡፡ «ምነው ሴት ብቻ በወለድኩ» ትላለች፡፡ በሴት ልጆች ላይ እንዲህ እና እንዲያ ዓይነት ጥቃት ደረሰ ስትባል ደግሞ፣ «እንኳንም ወንዶች ወለድኩ» ትላለች፡፡ አንዳንድ ጊዜ አምጣ እንደ ወለደችን አምጣ መልሳ ብትውጠን ትወድድ ነበር፡፡ «ምናለ አምጬ እንደ ወለድኳችሁ አምጬ መዋጥ ብችል፤ ደኅና ዘመን ሲመጣ መልሼ እወልዳችሁ ነበር» ትለናለች፡፡

እኅቴ ሁልጊዜ አንድ ነገር ይቆጫታል፡፡ ሰው በእናቱ ማኅፀን የኖረበት ጊዜ ለምን ከእድ ሜው ጋር እንደማይቆጠር፡፡ እንደ እናት ማኅፀን ምቹ እና ሰላማዊ፣ ያለ ሃሳብ እና ያለ ሰቀቀን የተኖረበት የት አለ? ምርጫ፣ ቅርጫ፣ ክፍያ፣መዋጮ፣ ተቆራጭ፣ ፖለቲካ፣ ፓርቲ፣ ፍርድ ቤት፣ፖሊስ ጣቢያ፣የሌለበት ልዩ ዓለም የታለ? ታድያ እንዲህ ያለው ሕይወት ከእድሜ ካልተቆጠረ ምኑ ሊቆጠር ነው ትል ነበር፡፡

ወርቋን ሽጣ ለልጆቿ ወርቅ የሆነ ሕይወት ከለገሰች እናት በተሻለ ጀግና ሆኖ ማን ወርቅ ይሸለማል? ወርቅንማ እንደ ወርቅ በእሳት ለተፈተነ ነው መስጠት፤ ምሳሌው ከአማናዊው ጋር ሲሠምር ደስ ያሰኛልኮ፡፡

ስለዚህም እርሷን ሸልሙልኝ፤ የእኔ ጀግና እርሷ ናት፡፡ ያለምንም በጀት፣ያለ ማንም ኢጋር ፣ ያለማንም አማካሪ፣ ያለ ምክር ቤት እና ካቢኔ፣ያለ ውጭ ርዳታ፣ ግብር ሳትሰበስብ ለሠለሳ ዓመታት ያህል ቤተሰቦቿን አባትም እናትም ሆና የመራች፤ ችግርን ተቋ ቁማ ታሪክ ያደረገች እናት፣ ፓርላማ ባለበት፣ካቢኔ በሚመክርበት፣ግብር ተሰብስቦ በጀት በሚመደብበት፣የውጭ ርዳታ በሚጨመርበት፣ አማካሪ በበዛበት ሥፍራ መምራት አትችልም የሚላት ማነው!! የኔ ጀግና እርሷ ናት እርሷን ሸልሙልኝ፡፡

ባሎቻቸውን በልዩ ልዩ ምክንያት አጥተው በብቸኛነት እና በጀግንነት ችግርን አሸንፈው፣ ልጆቻቸውን በማሳደግ ለወግ ለመዓርግ ላደረሱ እናቶች መታሰቢያ፡፡

8. አሜሪካን ያገኛት ማነው?

«በተለምዶ በሚታወቀው የዓለም ታሪክ «አዲሱ ዓለም» እየተባለ የሚጠራውን አሜሪካን ያገኘው ክርስቶፈር ኮሎምበስ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ሁለት ነጥቦችን እንድናነሣ ያደርገናል DISCOVERY የሚለው ቃል ያልታወቀን ነገር ማሳወቅን፣ ያልተገኘን ነገር ማግኘትን የሚ ያመለክት ቃል ከሆነ፣ ኮሎምበስ አሜሪካን አገኘ ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም ያች ቦታ ለአውሮፓውያን እንግዳ ትሁን እንጂ በውስጧ ግን ከጥንት ጀምረው ይኖሩባት የነበሩ ሕዝቦች ነበሩባትና፡፡ አውሮፓ ተገኘች እንደማትባለው ሁሉ አሜሪካም እንደ አዲስ ልትገኝ አትችልም፡፡

በሌላም በኩል ቃሉ «መጀመርያ በቦታው መድረስን የሚያመለክት ከሆነም ኮሎምበስ ወደ አሜሪካ ከማቅናቱ ብዙ ሺ ዓመታት በፊት ወደ ቦታው ያቀኑ ሌሎች ሕዝቦች አሉና ኮሎምበስ አሜሪካን አገኛት ማለት አይቻልም» ይላሉ ሳፉ ኪቤራ የተሰኙ ጸሐፊ NEW AFRICA በተሰኘ መጽሔት yJANUARY 2001 እትም ላይ They came before Columbus በሚል ርእስ ባወጡት ጽሑፋቸው ::

ኮሎምበስ ከመወለዱ ብዙ ሺ ዓመታት ቀድመው ወደ አሜሪካ የተጓዙት አፍሪካውያን ሲሆኑ፣ ባሕላቸውን በዚያው ይኖሩ ከነበሩት ቀያይ ሕንዶች ጋር አዋሕደውታል፡፡ የቀያይ ሕንዶችን አማልክት ተቀብለዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ የኑቢያ - ኬምት ሕዝቦች የአሜ ሪካ ቀያይ ሕንዶችን አማልክት ወደ ሀገራቸው አምጥተው ሲያመልኳቸው ከመኖራቸውም በላይ እነዚህኑ ቀያይ ሕንዶች «የቤተ አማልክቱ ጠባቂዎች እና የዚያ ምድር መንፈሳውያን መጓርጋትን የያዙ ናቸው» ብለው ያምኑ ነበር፡፡

የአፍሪካውያን በአሜሪካ ምድር መገኘት ከአሜሪካውያን ቅድመ ታሪክ /pre-historic America/ የቀደመ ዘመንን /40¸000¬ – 6¸000 ቅልክ/ አስቆጥሯል፡፡

የኑቢያ– ኬሚት ሕዝቦች ወደ አሜሪካ ምድር የገቡት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1200 ዓመት አስቀድመው ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ዘግየት ብለውም ቢሆን፣ ከክርስቶፎር ኮሎም በስ በፊት በምዕራብ አፍሪካ የሚገኙት የማንዲጋ ሕዝቦች ደግሞ በ1307 ዓም ወደዚ ያው ማምራታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በአፍሪካ አሜሪካውያን ጉዳይ ላይ ጥልቅ ምርምር ባደረጉት በዶ/ር ኢቫን ቫን ሰርቲማ እና በመሳሰሉት ምሁራን እየተጠናከሩ የመጡት መረጃዎች የአፍሪካውያንን በአሜሪካ ምድር ከኮሎምበስ በፊት መገኘት እያመለከቱ ይገኛሉ፡፡ ዶ/ር ኢቫን በ1977 ዓም ባሳተ ሙት They came before Columbus በተሰኘው መጽሐፋቸው ከኮሎምበስ በፊት አፍሪ ካውያን በአሜሪካ ምድር ይገኙ እንደነበሩ የአርኬዎሎጂ እና የሥነ ልሳን መረጃዎችን ያቀርባሉ፡፡

በአፍሪካ ካሪቢያን ጉዳዮች ላይ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በማበርከት የታወቀው ጸሐፊ ሪቻ ርድ ቢ ሙር The significance of African History በተሰኘ መጽሐፉ ላይ እንደሚለው «የአፍሪካ ታሪክ /በዓለም ላይ/ያለው ተጽዕኖ አፍሪካ እና ሕዝቦቿ ያላቸውን ታሪክ ለመ ካድ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ይታያል፡፡ ለረዥም ዓመታት ይህ ሁሉ የአፍሪካን ታሪክ ለማበላሸት ጥረት የተደረገው አፍሪካውያን ጥቂት ወይንም ምንም ዓይነት ዋጋ እንዳልነ በራቸው ለማሳየት መሆኑ ግልጽ ነው»፡፡

የማንዲጋ ጉዞ

የአርኬዎሎጂ ውጤቶች እና የታሪክ መዛግብት ከኮሎምበስ በፊት ከ1307- 1312 ዓም እኤአ ወደ አሜሪካን ምድር የተደረጉትን የአፍሪካውያንን ጉዞዎች በመግለጥ ላይ ናቸው፡፡ የ14ኛው መክዘ ሙስሊም የታሪክ ጸሐፊ የሆነው የአል ኡማርስ መረጃ ከእነዚህ መካከል አንዱ ነው፡፡ አል ኡማርስ የማንሳ ካንካን ሙሳ 1ኛን ትረካ መዝግቦ አቆይቶል ናል፡፡ ማንሳ ካንካን ሙሳ 1ኛ በወቅቱ የታወቀ የማንዲጋ /ማሊ/ ንጉሥ ሲሆን ወደ መካ ለመሳለም ሲጓዝ በ1324 እኤአ ግብጽ ካይሮ ውስጥ ነበር ከአል ኡማርስ ጋር የተገናኙት፡፡

ማንሳ ለአል ኡማርስ እንደ ተረከለት ማንዲጋውያን የአትላንቲክን ውቅያኖስን መጨረሻ ለማወቅ በነበራቸው ምኞት ወደ ምዕራብ ተደጋጋሚ ጉዞ አድርገው ነበር፡፡ ይህ ጉዞ ከማንሳ ቀደም ብሎ ማንዲጋን ያስተዳድር በነበረው ንጉሥ የተሰጠ ተልዕኮ ነበር፡፡ ከማንሳ የመካ ጉብኝት ጥቂት ዘግየት ብሎ የታሪክ መጽሐፉን ያዘጋጀው አል ኡማርስ እንደ ሚነግረን « (ማንሳን) የንጉሥነት ሥልጣኑ እንዴት ወደ እርሱ ዘንድ ሊደርስ እንደቻለ ጠየቅኩት፡፡ እርሱም እኛ ሥልጣንን በትውፊት የሚያወርስ ቤተሰብ አባል ነን፡፡ ከእኔ በፊት የነበረው ንጉሥ የዚህን ውቅያኖስ ዳርቻ ማወቅ የማይቻል ነገር ነው የሚለውን ሃሳብ አይቀበልም ነበር፡፡ 200 መርከቦችን በወርቅ፣ በምግብ እና በውኃ እንዲሁም በሌሎች በሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሞልቶ ከመርከበኞች ጋር መጀመርያ ላከ፡፡ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን መርከቦች እና መርከበኞችንም በሌላው ጊዜ እንዲሁ ላከ፡፡

«መርከበኞቹን ይመሩ ለነበሩት ካፒቴኖች ንጉሡ እንዲህ ብሏቸው ነበር፡፡ «መመለስ ያለባችሁ የውቅያኖሱን ዳርቻ ካገኛችሁ ወይንም የጫናችሁት ምግብና ውኃ ካለቀባችሁ ብቻ ነው፡፡» እናም ለብዙ ጊዜ ሳይመለሱ ቀሩ፡፡ በመጨረሻ አንድ መርከብ ብቅ አለ፡፡ የመርከቡን መሪም ምን እንዳጋጠማቸው ጠየቅነው፡፡ «ልዑል ሆይ» አለ ካፒቴኑ፡፡ «ለረዥም ጊዜ ያህል በውቅያኖሱ ላይ ከተጓዝን በኋላ በውቅያኖሱ መካከል አንዳች እንደ ወንዝ የሚፈስስ ውኃ አገኘን፡፡ መልኩም ሐምራዊ ይመስል ነበር፡፡ የኔ መርከብ ወደዚያ ለመድረስ የመጨረሻው ነበር፡፡ ከኔ በፊት የቀደሙት ሁሉም መርከቦች ወደዚህ ቦታ ደርሰዋል፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም አልተመለሱም፡፡ እኔ ግን ወደ ነበርኩበት ስለተ መለስኩ በዚያ ሐምራዊ ነገር ውስጥ ሰምጬ አልቀረሁም፡፡»

ነገር ግን ንጉሡ ሊያምነው አልቻለም፡፡ ስለዚህም 2000 ጀልባዎችን/Vessels / አዘጋጅቶ፣ መርከበኞችን እና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሞልቶ መልሶ ላካቸው፣ ያን ጊዜ ንጉሡ መንበሩን ለእኔ አስረከቦኝ ነበር፡፡ ያንን የመርከብ ካፒቴን እና ሌሎችን መርከበኞችም ከዚያ በኋላ ደግሜ አላየኋቸውም፡፡ እኔም የማይደፈረውን ሥልጣን እንደተረከብኩ ይሄው አለሁ፡፡»

ከማንሳ ሙሳ በፊት በማንዲጋ የነገሠው እና 2000 መርከቦችን ወደ ምዕራብ ለአሰሳ የላከው አቡበከሪ 2ኛ የተባለው የማንዲጋ ንጉሥ ነው፡፡ የአሰሳው ዳርቻ አቲሊስ ወይንም የሜክሲኮ ባሕረ ሰላጤ ወይንም የካሪቢያን መሬቶች ላይ ሳይሆን አይቀርም፡፡

እንደ አልጀርያው ምሁር እንደ ማሕሙድ ሐሚዱላህ አገላለጥ «የመርከቡ ካፒቴን ወደ ኋላ ለመመለስ በወሰነበት ጊዜ የአቡከሪ 2ኛ አሳሽ ኃይል የካሪቢያን ድንበር ላይ ደርሶ ነበር፡፡»

መርከቦችን የመሥራት ጥበብ በአፍሪካ ውስጥ ከኑቢያ እስከ ኬምት ድረስ የተስፋፋ እና የበለጸገ ነበር። **አል ካቲ** የተሰኘው የቲምቡክቱ የታሪክ ጸሐፊ የምዕራብ አፍሪካዋ የሶን ግሐይ የመጨረሻው ንጉሥ የሆነው አስክያ ኢሻቅ /1591 ዓም እኤአ/ ከሞሮኮ ጦር ወረራ ለመሸሽ 200 መርከቦችን በኒጀር ወንዝ ላይ ተጠቅሞ እንደነበር ይነግረናል። አል ካቲ እንደሚለው «የአስኪያ ንብረት የሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ መርከቦች በዚያው መንገድ ላይ ደርሰው ነበር። እንደ ምገምተው ቁጥራቸው ስድስት ወይንም ሰባት መቶ ሳይሆን አይቀርም።»

ማንሳ ሙሳ መካን ከነበኝ ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ ነበር ክሪስቶፈር ኮሎምበስ ወደ አሜሪካ ጉዞ የጀመረው። ኮሎምበስም ቢሆን ይህንን ለረዥም ዓመታት ሲካሄድ የኖረ ውን የማንዲጋዎች የምዕራብ አሰሳ አረጋግጧል። «ከምዕራብ አፍሪካ የሚነሡ የነጋዴ መርከቦች በየጊዜው ከጊኒ ወደብ እየተነሡ ወርቅ እና ሌሎች ሸቀጦችን ጭነው ወደ መካከለኛው አሜሪካ እየተጓዙ ይነግዱ ነበር። ወርቅን ከልዩ ልዩ ነገሮች ጋር በመቀ ላቀል የሚሠራ ልብስን ጥበብ ለመካከለኛው አሜሪካ ያስተማሩትም እነዚሁ አፍሪካ ውያን ናቸው።

«የአሜሪካ ሕንዶች የጥጥ ፈትል ጥበብን በሽመና አሠራር ቀለም እያስገቡ ልክ ከጊኒ፣ ከሴራልዮን ወንዞች ዳርቻ እንደሚመጣው ምርት አድርገው ያዘጋጁ ነበር። በሁለቱ ምርቶች መካከልም አንዳችም ልዩነት አይታይም ነበር።» በማለት ኮሎምበስ ጽፎ ነበር።

ማንዲጋዎች ከአሜሪካ ሕንዶች ጋር ወርቅን እና «አልማይዛር» የተሰኘውን የጥጥ ልብስ ይነግዱ ነበር። ኮሎምበስ የእነዚህን ልብሶች መነሻ ቦታ ያወቅ ነበር። ለዚህም ነው ስለ ጉዞው በጻፈው የጉዞ ማስታወሻ ላይ «የአሜሪካ ቀይ ሕንዶች /የሚጠቀሙበት/ አልማይዘር የተሰኘው ልብስ ከጊኒ እና ከሴራልዮን ወንዞች ዳርቻ የሚመጣውን ይመስላል» ያለው።

ደቡብ አውሮፓን ይቆጣጠሩ የነበሩት ሙር የተባሉት የሰሜን አፍሪካ ሕዝቦች ከማን ዲጋ ግዛት ጋር በንግድ ይገናኙ ነበር። አልማይዘር የተሰኘውን ምርት ለስፔናውያን ያስተዋወቁትም እነርሱ ናቸው። ኮሎምበስ ልብሱን ሊያውቀው የቻለው በዚህ ምክንያት ነው።

African presence in Early America በተሰኘው መጽሐፉ ዶ/ር ቫን ሴርቲማ «ቀያይ ሕን ዶች፣ በዌስት ኢንዲስ የደረሱ ኮሎምበስን እና ሌሎች የአውሮፓ አሳሾችን ከ1492 እኤአ በኋላ ጥቂት ዘግየት ብሎ እነርሱ ጥቋቁር ጊኒያውያን ብለው የጠሯቸው ጥቁር ሕዝቦች ወርቅን ወደ ደሴቶቹ ማምጣታቸውን ነግረዋቸዋል። በዚህም ምክንያት አንቲ ሊያውያን ወርቅን የሚጠሩባቸው ቃላት ከማንዲጋ ቃላት ሊወረሱ ችለዋል» ብሏል። «ጉአና፣ ካአና፣ጉአኒ፣ ጉአኒን» የሚሉት የአንቲሊያ ቃላት «ጋና፣ካኔ፣ካኒ፣ካኒኔ፣ጋኒን» ከሚሉት የማንዲጋ ቃላት የተወረሱ ናቸው።

አል ባክሪ የተባለው የሙስሊም የታሪክ ጸሐፊ በ1067 ዓም እኤአ «የንጉሡን እምነት የሚከተሉት የጥንቷ ጋና ሕዝቦች የጥጥ፣ የሐር እና በዝምዝም ወርቅ የተጠለፉ ልብ ሶችን ይለብሱ ነበር» ሲል ይገልጣቸዋል። ከአል ባክሪ አንድ መቶ ዓመታትን ዘግይቶ የጻፈው አል ኢድሪስ በምዕራብ አፍሪካ የነበሩት ሲላ፣ታኩር ፣ጋና እና ጋኦ የተባሉት ሕዝቦች አልማይዘር የተባለውን ልብስ ያዘወትሩ እንደነበር ጽፏል።

ሙንጎ ፓርክ የተባለው የስኮትላንድ አሳሽ በ1795 እኤአ በኒጀር ወንዝ አጠገብ የነበረችውን «ሳንሳንዲንግ»ን ሲጎበኝ ያጋጠመውን እንዲህ ብሎ ዘግቧል «ይህ ቦታ በሙሮች የተሞላ ነው፡፡ እነርሱም ጨውን ከቤሮ /ዋላታ/፣ ዶቃ እና ዛጎል ከሜዲትራንያን እያስ መጡ በወርቅ እና በጥጥ ልብስ ይለውጡ ነበር፡፡ ይህ በውድ ዋጋ የሚሸጡት ልብስ በሙሮች እና በቤሮ ሕዝቦች ዘንድ እጅግ ተፈላጊነት ነበረው፡፡ እዚያ በዝናብ እጥረት ምክንያት ጥጥ አይመረትም ነበርና» ብሏል፡፡

የጥጥ ልብስ ጥበብ አውሮፓውያን ወደ ምዕራብ አፍሪካ ከመምጣታቻው እጅግ ቀደም ብሎ የተስፋፋ ጥበብ ነው፡፡ አካንስ የተባሉት የጋና ሕዝቦች እና የኮትዲቮራውያን ኬኔቴ /KENTE/ ከአውሮፓውያን ወይንም ከዐረቦች የተወረሰ አይደለም፡፡ ይህ አለባበስ የአካባቢውን ሕዝቦች ባሕል፣ እምነት እና ወግ የሚያንጸባርቅ፣ ከሃያ በላይ የተቀደሱ ምልክቶችን የያዘ፣ በአብዛኛውም ከጥንቶቹ የግብጽ ሕዝቦች ከኬምታውያን የተወረሰ ነው፡፡

በደቡብ አሜሪካ በሆንዱራስ የሚገኙት የማንዲጋ ጎሳዎች፣ ጀራዎች፣ እና ጉአባዎች ራሳቸውን «አልማሚዎች» ብለው ይጠራሉ፡፡ ይህም በዓረብኛ «አል ኢማሙ» የሚለው ቃል ውርስ ነው፡፡ ትርጉሙም «መሪ» ማለት ነው የሚል ግምት በአንዳንድ የታሪክ እና የሥነ ልሳን ሊቃውንት ዘንድ ተሰጥቷል፡፡ አውሮፓውያን ለመጀመርያ ጊዜ የቅዱስ ቬንሰንት ደሴትን ሲረግጡ በዚያች ምድር ሁለት ዓይነት ሕዝቦች ነበር ያገኙት፡፡ ጥቁር እና ቢጫ መልክ የነበራቸው፡፡ ጥቁሮቹ ሕዝቦች ራሳቸውን «ክላይፉርናምስ» ብለው ነበር የሚጠሩት፡፡ ይህም «ካልፋቱ -ን-ናቢ» የሚለው የዓረብኛው ስያሜ ውርስ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የተፈጸመው እንግዲህ ከባርያ ንግድ መጀመር በፊት ነው፡፡

አስቀድመው በቅዱስ ቬንሰንት ደሴት የሠፈሩትና የደሴቲቱን መውጫ መግቢያ በሚ ገባ የሚያውቁት ማንዲጋዎች በ15ኛው መክዘ ከባርያ ንግድ እያመለጡ ለሚመጡት አፍሪካውያን ወገኖቻቸው በአካባቢያቸው የመደበቂያ ሥፍራ ይሰጡ የነበሩት በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፡፡

የኑቢያውያን - ኬምቶች ጉዞ፣ 1300 ቅልክ

ከአፍሪካውያን መካከል በአሜሪካ ምድር አስቀድመው የተገኙት የኑቢያ እና የኬምት ሕዝቦች ናቸው፡፡ ይህ ቅድምናቸውም በ1858 ዓም እኤአ በተገኘው የአርኬዎሎጂ መረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ስምንት ጫማ ርዝመት እና 18 ጫማ ክበብ ያለው የኑቢያውያንን መልክ የያዘ የድንጋይ ላይ ቅርጽ፣ ከ800 እስከ 600 ቅልክ ባለው ዘመን የተሠራ መሆኑ ተመስክሮለታል፡፡ በሜክሲኮ፣ ትሬስ ዛፖቴስ በተሰኘች መንደር የተገኘው የሰው ራስ ቅል ቅርጽ ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ በመላዋ ደቡብ አሜሪካ 17 ተመሳሳይ ቅርጾች ተገኝተዋል፡፡

በ1869 ዓም እኤአ፣ ጆዜ ሜግላር የተባለው የሜክሲኮ ምሁር ስለዚሁ የሰው ራስ ቅል ቅርጽ «Mexican society of geography and statistic bulletin ´ በተሰኘው መጽሔት ላይ ሲገልጥ «በ1862 እኤአ ሳን አንድሬ ቱክስትላ በተባለው ቦታ ነበርኩ፡፡ በሸርሸር ላይ እያለሁ የሰው ራስ ቅል መልክ ያለው የድንጋይ ቅርጽ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከመ ሬት ወጥቶ መታየት እንደ ጀመረ ሰማሁ»

«እኔም ወደ ቦታው እንዲወስዱኝ ጠየቅኩ፡፡ እዚያ ቦታ ስደርስም በአግራሞት ፈዘዝኩ፡፡ ያለምንም ማጋነን ይህ የኪነ ጥበብ ውጤት የሆነ ትልቅ የራስ ቅል ቅርጽ ነው፡፡ ያስደ ነቀኝ ነገር ቢኖር መልኩ ኢትዮጵያዊ መምሰሉ ነው፡፡ በዚህች ሀገር ውስጥ ጥንት ቀደም ብለው ጥቁር ሕዝቦች ይኖሩ እንደ ነበር ያመላክታል፡፡ ይህም በዓለም መጀመ ርያ አካባቢ መሆን አለበት» ብሎ ጽፎ ነበር፡፡

ይህንን እና ይህን የመሰለው የአፍሪካውያንን በአሜሪካ ምድር ቀድሞ መድረስ የሚያስረዱ ጽሑፎች እና መረጃዎች በአውሮ- አሜሪካውያን ምሁራን ዘንድ ሆን ተብለው እንዲዘነጉ እና እንዲድበሰበሱ ሳይደረጉ እንዳልቀሩ ይገመታል፡፡ ይህ የአፍሪካውያንን ታሪክ በአሜሪካ ምድር በደመቀ ሁኔታ የመግለጡ ነውር በ1939 ዓም ተገፈፈና አሜሪካዊው ሊቅ ማቲው ስቲርሊንግ፣ በስሚዘንያን ኢንስቲቲዩት እና በናሺናል ጂኦግራፊ ስፖንሰር የተደረገ አንድ የአርኬዎሎጂ ቡድን በመምራት ወደ አካባው ተጓዘ፡፡ ሜልጋር ከ 77 ዓመታት በፊት የገለጠውን የሰው ራስ ቅል ቅርጽ ለማጥናትም በሜክሲኮ ትሬስ ዛፖቴስ መንደር ተገኘ፡፡

በሚገባ ለስልሶ የተቀረጸው የራስ ቅል ቅርጽ ስተርሊንግን «አስደናቂ የሆነ ስሜትን ይፈጥራል፤ ምንም እንኳን ግዙፍ ቅርጽ ቢሆንም የኪነ ጥበብ ሥራው ያማረ እና ጥራት ያለው ነው፡፡ ምጣኔውም በሚገባ የተለካ፣የተመጣጠነ እና ፍጹም ነው፡፡ እውነታውን ለመግለጥ ከተፈለገ ይህ ቅርጽ የፈሰሰበትን ጥበብ ያሳያል፡፡ ገጽታዎቹ በሚገባ የሚለዩና መልኩም የጥቁር/ አፍሪካውያን/ መልክ ነው» እንዲል አድርጎት ነበር፡፡

ከዚህ ምስል በተጨማሪ የአፍሪካውያንን የብዙ አሥር ሺ ዓመታት የአሜሪካ ቆይታ የሚያሳዩ እና ከ1500 ቅልክ እስከ 1500 ዓም የተሠሩ አያሌ ቅርጾችም ቴራ ኮስታ በተባለው የሜክሲኮ አካባቢ ተገኝተዋል፡፡ በመስከረም 1974 እኤአ፣ በአሜሪካ ጥናት 41ኛው የሜክሲኮ ጉባኤ ላይ፣ ዶ/ክ አንድርዜይ ዊርሲንስኪ የአፍሪካውያን የራስ ቅሎች ሜክሲኮ ውስጥ በቼሮ ዲ ላስ ሜሳ፣ በሞንቴ አልባና እና በታላቲልኮ መገኘታቸውን ገልጠው ነበር፡፡

የኪነ ጥበብን ታሪክ የሚያጠኑት ትውልደ ጀርመናዊ የሆኑት ፕሮፌሰር አሌክሳንደር ቮን ዉቴናው «Unexplained Faces In Ancient America» በተሰኘው መጽሐፋቸው ከአሜሪካ የተለመደው ታሪክ ቅድሚያ ያላቸውን የአፍሪካውያንን ገጽታዎች የሚያሳዩ የጎሳ መሪዎች፣ የካህናት፣ የዘፋኞች፣ እና የከበሮ መቺዎችን ምስሎች አሰባስበዋል፡

ሳፉ ኪቤራ በቁጭት እንደሚገልጡት «ይህ የአፍሪካውያን በአሜሪካ ምድር በቀደም ተነት የመገኘት ታሪክ ትኩረት አግኝቶ በሚገባ ያልተነገረለት በዘረኛነት እና የአፍሪካ ውያንን አስተዋጽዖ አኮስሶ የማየት ጠባይ በተላበሰው ምዕራብ ቀየድ አሠራር ምክንያት ነው፡፡ ሮም እና ስፔይንን በሚገባ ያስተዳደሩት የአምስቱ የኑቢያ /ኢትዮጵያ/ ነገሥታት ታሪክስ ቢሆን መች በሚገባ ይነገራል፡፡ ፍላቪየስ ሆኖርየስ /395 ዓም/፣ እንዲሁም የአኒባልን ምስል በሮም ከተማ ያሳነፀው እና በ200 ዓም ኬምትን የነበኘው ንጉሥ ሴፕቲ ሚየስ ሴቨረስ /193 ዓም/ የኑቢያ/ ኢትዮጵያ/ ልጆች ነበሩኮ፡፡

የኦለሚ ሥልጣኔ /1200 ቅልክ- 400 ዓም/

ኦለሚ የሚለው ቃል ከአዝቴክ ቋንቋ የተገኘ ነው፡፡ አዝቴካውያን ከ15ኛው መክዘ በፊት በሜክሲኮ እጅግ ታላቅ የሆነ መንግሥት የነበራቸው እና በኋላ ወደ ደቡብ አሜሪካ የገቡ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ዋና ከተማቸው ላ ቬንታ የተሰኘችው የሜክሲኮ ከተማ ነበረች፡፡ «ኦለሚ» የሚለው ቃል «ኦሊን» ከሚለው የእነርሱ ቃል የተወሰደ ሲሆን «ግንዲላ» ማለት ነው፡፡ ይህም «ግንዲላ ከሚመረትበት አካባቢ የመጡ ሕዝቦች» ለማለት ነው፡፡ በሀገራችን ቆለኛ ደገኛ እንደሚባለው ያለ ነው፡፡

«በደቡብ አሜሪካ አስቀድመው መኖር በጀመሩት በኦለማውያን የተዘጋጁ የጽሑፍ ማስረጃዎች አውሮፓውያን አካባቢውን ሲይዙ ወድመዋል፡፡ ስፔይን ውስጥ የነበረውን የአፍሪካውያን ሙሮችን ቤተ መጻሕፍት ያወደሙት አውሮፓውያን በደቡብ አሜሪካም ይህንን ጥፋት ደግመውታል፡፡» ይላሉ ሳፉ ኪቤራ፡፡

ዲጎ ዴ ላ አንዳ የተባሉት የስፔይን ጳጳስ «እነዚህ ሕዝቦች የተለዩ የፊደል መልኮችን በመጠቀም መጽሐፋቸውን፣ ጥንታዊ ወጋቸውን እና ሳይንሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ እኛም እጅግ ብዛት ያላቸውን መጽሐፎቻቸውን አግኝተን ነበር፡፡ የጥንቆላን ነገር የያዙ በመሆናቸው ሁሉንም አቃጠልናቸው፡፡ እነርሱ ግን እጅግ ተፀፀቱ፣ አብዝተውም አዘኑ» ብለዋል፡ ፡

አንቶኒዮ ዲ ኩይዳድ የተባለው የስፔይን የታሪክ ጸሐፊ በ1588 እኤአ «/ስፔይናውያን/ የጥንታውያን ዩካታውያንን ብዙ መጽሐፎች አቃጥለዋል፡፡ እነዚያ መጻሕፍት የዩካታው ያንን አመጣጥ እና ታሪክ የሚናገሩ ነበሩ» ሲል ጽፏል፡፡

በአሜሪካ ታሪክ ቀድመው የሠፈሩት ሠፋሪዎች ከ3000 እስከ 2000 ቅልክ ባለው ጊዜ የገቡ ናቸው፡፡ የኦለማውያን ሥልጣኔ ግን ከሁሉም የላቀ ነበር፡፡ ይህ ሥልጣኔ በምዕራብ እስከ ጓቲማላ እና ሆንዱራስ፤ በመካከል እስከ ሜክሲኮ ጠረፎች፣ ኮስታሪካ እና ፓናማ ደርሶ ነበር፡፡

የኦሊማውያንን ሥልጣኔ ከፍ እንዲል ያደረጉት የኑቢያውያን (ኬምት ሕዝቦች ወደ አካባቢው መምጣት ነው፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ባሕላቸውን፣ ቋንቋቸውን እና አማልክቶቻቸውን ለአካባቢው ኦሊማውያን አውርሰዋል፤ እነርሱም ከኦሊማውያን ወርሰዋል፡፡ በ ላ ቬንታ የሚገኘው እና የግብፃውያንን የሚመስለው የኦሊማውያን ፒራሚድ እና የምስል ወካይ/ሄሮግላፊክስ/ ፊደላቸው ለዚህ የኑቢያውያን - ኬምቶች ተጽዕኖ አንዱ መገለጫ ነው፡፡

አሁን አሁን በአሜሪካውያን ምሁራን ዘንድ አፍሪካውያን ከአውሮፓውያን እጅግ እጅግ ቀድመው ወደ አሜሪካ ምደር መድረሳቸው የመከራከርያ ርእስ መሆኑ ቀርቷል፡፡ በአሁኑ ዘመን ዋና አከራካሪው ነገር «የመጀመርያዎቹ አፍሪካውያን ከየትኛው የአፍሪካ ክፍል መጡ?» የሚለው ነው፡፡

ከኑቢያ- ኬምት ሥልጣኔ የቀደመ ታሪክ ባለው በ ታ - ሴቲ ሥልጣኔ /3800 ቅልክ/ በውቅያኖስ ላይ የሚንሳፈፉ መርከቦች ሥዕል መገኘቱ የመርከብ ሥልጣኔ እና ውቅያኖስን የማቋረጥ ሃሳብ በአፍሪካውያን ዘንድ ያለውን ቀዳሚ ታሪክ ያሳየናል፡፡ ኒኮ 2ኛ የተባለው የኬምት ንጉሥ በ600 ቅልክ ባሕር ኃይሎቹን የአፍሪካን አህጉር በሙሉ ዞረው

እንዲመጡ ማዘዙን እና ባሕር ኃይሉም ዞሮ መምጣቱን፤ ንጉሡም የሞቀ አቀባበል እንዳደረገላቸው መዛግብቱ ያስረዳሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሚገኙት መረጃዎች መሠረት ለመጀመርያ ጊዜ ወደ አሜሪካ ምድር ያቀኑት አፍሪካውያን የኑቢያ-ኬምት ሕዝቦች መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ይህንን ቀደምትነታ ቸውን የሚያሳየው በአሜሪካ ምድር የተገነባው የመጀመረያው ፒራሚድ ነው፡፡ ይህ ፒራሚድ የቆመው እጅግ አስገራሚ በሆነ አቀማመጥ ነው፡፡ ዶ/ር ኢቫን ቫን ሰርቲማ African presence in Early America በሚለው መጽሐፋቸው ላይ «ፒራሚዱ የቆመው እንደ ሌሎቹ የግብጽ ፒራሚዶች ሁሉ በሰሜን ደቡብ አክሲስ ላይ ነው፤ ይህኛውም ፒራሚድ እንደ ግብጽ ፒራሚዶች ሁሉ ለቤተ መቅደስ እና ለመቃብርነት መንታ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ በሜክሲኮ ቲዮቲዩካን በተባለው ቦታ የቆመው ባለ 225 ስኩዌር ሜትሩ ትልቁ ፒራሚድ መሠረቱ ልክ ከግብጽ ፒራሚድ ጋር ተመሳሳይ መጠን ያለው እና ትልቁን የግብጽ ፒራሚድን /226.5 ስኩዌር ሜትር/ የሚተካከል ነው» ብለዋል፡፡

በሁለቱ ፒራሚዶች መካከል ያለው ተመሳሳይነት በኬምት የነበሩት አስትሮሎጂስቶች እና የሂሳብ ሰዎች ናቸው ወደ አሜሪካ ተጉዘው ይህንን ፒራሚድ በተመጣጣኝ ስሌት እና መጠን የሠሩት የሚለውን ግምት እጅግ ያጠናክረዋል፡፡ ዶ/ር ኢቫን ከዚህም በተጨ ማሪ «የኦሊማውያን ሥልጣኔ በነበሩባቸው ቦታዎች በተደረጉ ጥናቶች የተገኙት የራስ ቁሮች ምስል የኑቢያ (ኬምት ወታደሮች ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጨረሻው ሚሊኒየም የንጉሥ ራምሴ ወታደሮች ይለብሱት የነበረውን የሚመስል ነው፡፡ እነዚያ የራስ ቅላቸውን እና ማጅራታቸውን ይሸፍኑ ነበር፡፡ በራስ ቁራቸው ላይ የሚያደርጉት ጉትዬ ተንጠልጣይ ገመድ በሁለት ጆሮዎቻቸው ፊት እንዲወርዱ ያደርጉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡

የኬምታውያን እና የኦሊማውያን ሥልጣኔ በሌሎች ብዙ ገጽታዎችም ይመሳሰላል፡፡ በሜክሲኮ በ ቼሮ ዲ ላ ፔድሬ በሚገኘው የአማውያን መቅደስ የቆመው የተከበረ ሰው ምስል ድርብ ዘውድ የደፋ፣ የኬምታውያንን ምልክቶች ያሉበት ነገር እንደሚሠዋ የሚ ያሳይ አፍሪካዊ መልክ ነው፡፡ የኬምታውያን የተቀደሰ ጀልባ በኦሊማውያን ሥዕሎች ላይ በተመሳሳይ መልክ እና ስያሜ ተሥሎ ተገኝቷል፡፡ የሥልጣን ምልክት የሆነው የኬምታውያን የልዑላውያን መውቂያም በሜክሲኮ በ ኦአቶቲትላ በተመሳሳይ መልኩ በተሳለው በኦሊማዊው ንጉሥ እጅ ይታያል፡፡

የግብፃውያን የሕይወት ምልክት የሆነው አንክህ በተመሳሳይ ስያሜ እና ምልክት በኦሊማውያን ዘንድ ተገኝቷል፡፡ ኦሊማውያን ይህንን ምልክት የሕይወት ዛፍ To-naca-qua-hui-tl ብለው ነበር የሚጠሩት፡፡ የምልክቱ መጠን፣ ቅርጽ እና ቀለምም ከኬምታውያን ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡

በኬምታውያን የሥነ ፍጥረት መጽሐፍ የተጠቀሱት ዘጠኙ አማልክት በኦሊማውያን ዘንድ ነበሩ፡፡ በሜክሲኮ በሚገኘው ፒራሚድ ላይም «ዘጠኙ የጨለማ ልዑላን´ ተብለው ተጠርተዋል፡፡

እንግዲህ እነዚህን ነገሮች ይዞ ተጨማሪ መረጃዎችን በወዲህም ሆነ በወዲያ ማፈላለግ ያስፈልጋል፡፡ ሁልጊዜ የምዕራባውያንን ድምፅ ብቻ እየሰሙ እና እርሱንም እንደ ዶግማ የማይቀየር እውነት አድርገው እየያዙ መጓዝ ሊያከትም ይገባዋል፡፡ አፍሪካውያን ምሁራን የትናንት ታሪካቸውን በመመርመር፤ ለዛሬውም ትውልድ የሥነ ልቡና ስንቅ በመሰነቅ በእልህ እና በቁጭት ለዕድገት እና ለልዕልና የሚነሣ ትውልድ መፍጠር አለባቸው፡፡ ለብዙ ዓመታት

ሲከማች በነበረው የአፍሪካውያን የበታችነት ተረታ ተረት ምክ ንያት የወደቀውን የትውልድ ሞራል ከፍ አድርጎ በዚያው ላይ ወደ ላቀ ታሪክ የመሸጋገርያ ጊዜው አሁን ነው።።

ምዕራብ አፍሪካውያኑ አካኖች ሰንኮፋ ብለው የሚጠሩትን ፍልስፍና (ወደ ኋላ ተመልሶ ካለፉት ነገሮች ለአሁን ሥልጣኔ የሚጠቅሙትን ማምጣት) መጠቀም የሚያስፈልግበት ጊዜ ዛሬ ነው።። የጥቁር አፍሪካውያን ታሪክ ገና ብዙ ይቀረዋልና።።

9. ባሕር ዛፍ

አሜሪካ፣ ሜሪ ላንድ ግዛት፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ከተማ ውስጥ፣ ስታር ባክስ የተሰኘ አንድ ቡና መሸጫ ቤት ተቀምጠን ሰው እንጠብቃለን፡፡ ዕድሜያቸው ከዓርባዎቹ በላይ የሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን ከኛ አጠገብ ከሚገኘው ጠረጴዛ ዙርያ ተቀምጠው የሞቀ ክርክር ይዘዋል፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አልደረስንም፡፡ ከንግግራቸው ግን የክርክሩ መነሻ ጉዳይ ይታወቃል፡፡

በተለይም አንደኛው ሰውዬ በአካባቢው ሰው መኖሩን እስኪረሳው ድረስ እጁን እያወና ጨፈና እየጮኸ «የለም የለም በዛ፤ ዲቪ፣ አሳይለም፣ ስኮላርሺፕ ምናምን እያሉ ማንንም እየሰበሰቡ ኑሮውን አበላሹት፣ ስንት ነገር ነው የቀረው፡፡ ድሮኮ አበሻ ብርቅ ነበረ፤ ዛሬማ እንደ ጠጠር ረክሶ፡፡ ያለነውን በሚገባ ሳይይዙ መጨመር ምን ዋጋ አለው» ይላል፡፡

ጓደኛው ደግሞ «አሜሪካ የእኩል ዕድል ሀገር ናት፡፡ እድሉ ይሰጥሃል፤ አጠቃቀሙ የራስህ ነው፡፡ በመብዛት በማነስ አይደለም፡፡» እያለ ቻይናዎችን እና ላቲኖችን እየጠቀሰ ይከራከረዋል፡፡ ያኛው ግን እየደጋገመ «በጭራሽ በጭራሽ ስደተኛ አበሻ በዝቷል» እያለ እጁን ያወናጭፋል፡፡

እኔ በኋላ መገረም ጀመርኩ «ይኼ ሰው እንኳንም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊ አልሆነ፡፡ እርሱ ራሱ በሰው ሀገር መጥቶ እየኖረ ሌላውን መምጣት የለበትም፣ መብዛት የለበትም እያለ እንዴት ነው የሚከራከረው?»ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ «የሰው ኃይሏን ለምታጣው ኢትዮጵያ ተቆርቁሮ ነው እንዳልል የሚያንገበግበው ሰው ከሀገሩ መውጣቱ ሳይሆን እርሱ በሚኖርበት ሀገር መብዛቱ ነው፡፡ ለስደተኛው አዝኖ ነው እንዳልል ተንቀባርረን እንዳንኖር አበሻ እንደ ጠጠር በዝቶ እድሉ ሁሉ ተበላሸ ነው የሚለው፡፡ ታድያ የዚህ ሰው ችግሩ ምንድን?ነው»

መልሱን የሰጠኝ አንድ ወዳጄ ነው፡፡ ባሕር ዛፍነት ነው ችግሩ አለኝ፡፡

መነሻው አውስትራልያ ሆኖ እስያን፣ አፍሪካን፣ አውሮፓን፣ ሰሜን አሜሪካን እና ደቡብ አሜሪካን ያጥለቀለቀው ባሕር ዛፍ የድኾችን ጉሮሮ በመዝጋት እና የማገዶን ፍጆታ በመቻል ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ ቢኖረውም ጠባዩ ግን አስቸጋሪ ነው፡፡

ባሕር ዛፍ ብዙ ውኃ ይፈልጋል፡፡ ከተተከለበት አካባቢ ይነሣና በዙርያው ያለውን ውኃ ሥሩ እስከደረሰበት ድረስ ሙጥጥ አድርጎ ነው የሚሰበስበው፡፡ ሌሎቹ ዛፎች በአካባቢው ቢኖሩም ባይኖሩም እርሱ ግን ለራሱ ብቻ የሚሆን ውኃ ወደ ታች እና ወደ ጎን ሥሮቹን እየላከ መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ሌሎቹ ዛፎች ያላቸው አማራጭ ሁለት ነው፡፡ ነቅሎ ሌላ ቦታ የሚተክላቸው ካገኙ አካባቢውን መልቀቅ ያለ በለዚያም መድረቅ፡፡

አንዳንዱ ሰው ጠባዩ እንደ ባሕር ዛፍ ነው፡፡ ሥልጣንንም፣ገንዘብንም፣ ትምህርትንም፣ ዕድልንም፣ ሀብትንም የሚችልበት ቦታ ድረስ ሥሩን እየሰደደ ብቻውን መሰብሰብና ብቻውን ማደግ ይወዳል፡፡ ስለ ሀገር፣ ስለ ትውልድ፣ ስለ ወገን፣ ስለ ሌላ የሰው ዘር ግድ የለውም፡፡ ብቻ የሚገኘውን ነገር ሁሉ እርሱ ራሱ ብቻ አግኝቶ ማደግ ነው ሃሳቡ፡፡

እነርሱ ውጭ ሀገር ሄደው በርዳታ በተገኘ ገንዘብ ተምረው፣የቤት ዕቃ እና መኪና ገዝተው፣ በመጠኑም ቢሆን ገንዘብ ሰብስበው የሚመጡ ሰዎች አሉ፡፡ የሄዱበትን መንገድ፣ ያገኙትን ጥቅም ያውቁታል፡፡ ያ መንገድ ሌሎች ብዙ ወገኖቻቸውን ሊጠቅም እነርሱ የበሉትን ዓይነት እንጀራ እንዲያገኙ ሊያደርግ እንደሚችል ያውቃሉ፡፡

ወደ ሀገራቸው ተመልሰው የሥልጣኑን ቦታ ሲይዙት ግን የባሕር ዛፍን ጠባይ ይዘው ቁጭ ይላሉ፡፡ የሚረዱት የውጭ መንግሥታት መረረን ሳይሉ፡፡ የሚልከው የኢትዮጵያ መንግሥት አትላኩ ሳይል፡፡ የሚቀበሉት የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ሞላን ሳይሉ የሀገራችን ባሕር ዛፎች ግን ዕድሉን ብቻቸውን ተጠቅመው ለሌላው በሩን ዘግተው ቁጭ ይላሉ፡፡ ሥራቸው እንደ ባሕር ዛፍ ብዙ ነውና በቢሮክራሲ እና በቀጠሮ ብዛት፣ አልፎ አልፎም ደግሞ ለሰው ከባድ የሆኑ መመርያዎችን በማውጣት ዕድሉን ሁሉ ይዘጉታል፡፡

«በኛ ጊዜ ማስተርስና ፒኤች ዲ በስንት መከራ ነበር የሚገኘው፡፡ ሰው ተመርጦ ነበር የሚሄደው፡፡ ዛሬማ ማንንም እየላኩ አበላሹት፡ ክብሩን አሳጡት» ይላሉ፡፡ እንዲህ የሚሉት ግን ለማዕረጉ ክብር ተጨንቀውለት ሳይሆን የባሕር ዛፍ ጠባያቸው ሁሉን እኔ ብቻ ስለሚያሰኛቸው ነው፡፡

በምዕራቡ ዓለም ያሉ ድርጅቶች ሰውን በማስታወቂያ ከመቅጠር ይልቅ እዚያው ድርጅት የሚሠራ ሰው በሚያቀርበው በጎ አስተያየት /ሪኮመንዴሽን/ መቅጠር ይወዳሉ፡፡ ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ብለው ነው መሰል፡፡ ታድያ በዚህ መንገድ ሕንዶች፣ ቻይናዎችን እና ላቲኖችን ያህል የተጠቀመበት የለም፡፡

በአሜሪካ ምድር ስዘዋወር የምሰማው የኛ ታሪክ ግን ለየት ያለ ነው፡፡ በአንድ ድርጅት አንድ አበሻ ከተቀጠረ ማንንም ሪኮመንድ ማድረግ አይፈልግም፡፡ ከአፍሪካ ተወስዶ የእንስሳት ማቆያ ውስጥ እንደ ተቀመጠ ቺፓንዚ ብቻውን እየተጎበኘ ቢኖር ደስ ይለዋል፡፡ ቀጣሪዎቹ እና የሥራ ባልደረቦቹ ሌላ የርሱን ወገን ባለማየታቸው «ይህ አበሻ የሚባል ዘር እየጠፋ ያለ ዘር ነው እንዴ» እስኪሉ ድረስ ቢገረሙም፤ ቢሞት ሌላ ወገኑ እዚያ እንዲመጣ አይፈልግም፡፡

መሬት ለሁሉ ትበቃለች፡፡ የአማዞንን እና የኮንጎን ጫካዎች በአንድ አካባቢ አስተናግዳ የምትኖር ናት፡፡ መሬት፡፡ ባሕር ዛፍ ግን ሁሉንም ውኃ አሟጥጦ ካልጠጣ አይደሰትም፡፡ ይህም ሰው እንዲህ ነው፡፡ የድርጅቱ ሀብት ከርሱ ሌላ ሺዎችን ሊያስተናግድ ቢችልም ሥሩን ሰድዶ ብቻውን ካላሟጠጠ የኖረ አይመስለውም፡፡

በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶችኮ በየስብሰባው፤ በየዐውደ ጥናቱ፤ገንዘብ ሊያስገኝ በሚችል ጉዞ፤ በውጭ ሀገር ተልዕኮ ተመሳሳይ ዓይነት ሰዎች ነው የምናየው፡፡ ሌላ ባለሞያ፤ ሌላ የተማረ፣ ሌላ ዐቅም ያለው ሰው የሌለ ይመስል ለሂሳብም ጉዳይ፣ ለኤች አይ ቪ/ ኤድስም ጉዳይ፣ ለአካባቢ ጥበቃም ጉዳይ፣ ለሴቶችም ጉዳይ፣ ለሕፃናትም ጉዳይ፣ ለመዝገብ አያያዝም ጉዳይ፣ ለድርጅቱ ጥበቃም ጉዳይ እነዚያው ተመሳይ ሰዎች ናቸው የሚሄዱት፡፡

እነዚህ ሰዎች ሁለገብ የሆነ ዕውቀት እንዲኖራቸው ተፈልጎ፣ ወይንም በመሥሪያ ቤቱ የሚላክ ሰው ጠፍቶ፣ ያለበለዚያም ሞያው የሚመለከተው ሰው አልሄድም ብሎ አይደለም፡፡ እንደ ባሕር ዛፍ ሥርን ዘርግቶ ሁሉን የመሰብሰብ አባዜ ነው እንጂ፡፡ ባሕር ዛፍ የአካባውን ውኃ ሁሉ መልጭ አድርጎ እንደሚጠቀማት ሁሉ እነዚህም በመሥሪያ ቤቱ የተገኘን ዕድል ሁሉ ብቻቸውን ሙልጭ አድርገው ነው የሚጠቀሙት፡፡

በሀገራችንኮ ሌሎች ነጋዴዎች ሊደርሱባቸው የማይችሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚጠቀሙባቸው ስንት የንግድ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህ ዕድለኛ ነጋዴዎች ሥራቸውን በሚገባ ይሰድዱና በአካባቢያቸው ላለው ለሌላው ነጋዴ ሳያዝኑ ውኃውን ሁሉ ሙልጭ አድርገው ወደ ራሳቸው ይሰበስቡታል፡፡ እነርሱ ያድጋሉ ሌላው ይቀጭጫል፡፡ ያንጊዜ ሌላው ነጋዴ ያለው አማራጭ ሁለት ነው፡፡ ዐቅም ካለው ወደ ሌላ ሥራ ወይንም ቦታ ይሄዳል፡፡ ዐቅም ከሌለው ግን ሥራውን በኪሳራ ይዘጋል፡፡

ባሕር ዛፍ የአካባቢውን ውኃ ሙልጭ አድርጎ ለራሱ ብቻ በመውሰድ ሌላ ዓይነት ዛፍ እንዳይበቅል ማድረጉ ብቻ አይደለም፡፡ በአካባቢው ሌላ ዛፍ የሚበቅልም ከሆነ ያው እንደ እርሱ ዓይነት ባሕር ዛፍ መሆን አለበት፡፡ እንደ እርሱ የሚሻማ፡፡ ለሌላ ግድ የሌለው፡፡ ሥሩን የቻለውን ያህል ሰድዶ ውኃውን የሚሰበስብ ሌላ ተመሳይ ባሕር ዛፍ፡፡ ባሕር ዛፎች ለአካባቢያቸው አያዝኑለትም፡፡ የአካባው ሥነ ምዕዳር ቢበላሽም፡፡ መሬቱን በማድረቅ ወንዞች እንዲነጥፉ ቢደረግም፡፡ ሌሎች ዛፎች በመድረቃቸው ምክንያት የአካባቢው የአየር ሁኔታ ቢዛባም ለባሕር ዛፎች ምንም አይሰማቸውም፡፡ ብቻ እነርሱ ያግኙ፤ እነርሱ ይደጉ፡፡

የባሕር ዛፍ ጠባይ ያላቸውም ሰዎች እንደዚሁ ናቸው፡፡ እነርሱ በሚገኙበት ቦታ ሊገኝ የሚችለው እንደ እነርሱ ባሕር ዛፍ የሆነ ብቻ ነው፡፡ ሲበሉ የሚበላ፤ ሲሰርቁ የሚሰርቅ፤ ሕግ ሲጥሱ የሚጥስ፤ ሲጨክኑ የሚጨክን፤ ሀገር ሲጎዱ አብሮ አገር የሚጎዳ የነርሱው ቢጤ፡፡ ስለ ሀገር ጥቅም፡፡ ስለ ትውልድ አያስቡም፡፡ ብቻ እነርሱ ይጠቀሙ፡፡

አሜሪካ ውስጥ ፓርኪንግን በመሳሰሉ በአንዳንድ ሥራዎች የሚቀጠሩ ሰዎች የስርቆት ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡ እዚያ ቦታ ላይ የማይሰርቅ ሰው መቀመጥ አይችልም፡፡ ሌሎችን ያጋልጣላ፡፡ እነዚያ ሥራቸውን ሰድደው የሰው ገንዘብ መሰብሰብ የለመዱ ባሕር ዛፎች ከእነርሱ ውጭ ሌላ ዓይነት ዛፍ እንዲመጣ ስለማይፈልጉ ነገር ዓለሙን ሁሉ ዘጋግተው ሰውዬው አካባቢውን ጥሎ እንዲሄድ ያለበለዚያም እንደ እነርሱ ባሕር ዛፍ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡

ባሕር ዛፍ ከተስማማም ከሌላ ባሕር ዛፍ ጋር ነው፡፡ ባሕር ዛፍ የሆኑ ሰዎችም ከተስማሙም በዘር እና በትውልድ ቦታ ከሚመስላቸው ጋር ብቻ ነው፡፡ «የወንዛቸውን» ሰው ካልሰበሰቡ በቀር ሌላ ዐይነት ዛፍ አይታያቸውም፡፡ ሌላው ቀርቶ «ከትናንት ወዲያ»/አዲስ አበባ/ እና «ሠለስትና»/ጎጃም/፣ከትናንት በስቲያ/ጎንደር/ የሚሉ ሦስት ዓይነት ዛፎችን እንኳን ለማስተናገድ ፈቃደኞች ያልሆኑ ባሕር ዛፎች አሉ፡፡

ለዚህም ነው አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን፣ አንዳንድ መሥሪያ ቤት፣ አንዳንድ ደርጅት፣ አንዳንድ አካባቢ፣ አንዳንድ የሥራ መስክ ውስጥ ተመሳሳይ የዘር ሐረግ ወይንም የትውልድ ቦታ ወይንም ቀየ ያላቸውን ሰዎች ብቻ የምናየው፡፡ በባሕር ዛፍነት ጠባይ ምክንያት፡፡

10. ለዘብተኛነት/ሊበራሊዝም/፡የክርስትና ዘመናዊው ጠላት

ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን ዕወቅ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል።። 2ኛጢሞ. 3÷5

ለዘብተኛነት/ሊበራሊዝም/ በ18ኛው መክዘ መጨረሻ እና በ19ኛው መክዘ መጀመርያ ብቅ ያለ አስተሳሰብ ነው።። ይህ አስተሳሰብ በፖለቲካው መስክ ግራ ዘመም አስተሳሰብ በመባል ይታወቃል።። በደምሳሳው ልቅ በሆነ ሙበት እና ነጻነት የሚያምን፤ ነባር ባሕሎችን፣ ልምዶችን እና እምነቶችን በየጊዜው በመናድ ሰዎች ራሳቸውን አማልክት አድርገው እንዲያስቡ የሚያበረታታ አመለካከት ወይም ርእዮተ ዓለም ነው።።

ዛሬ በፖለቲካው መስክ ያለው ለዘብተኛነት ርእሰ ጉዳያችን አይደለም።። የምንወያየው ስለ ለዘብተኛ/ሊበራል/ ክርስትና ነው።።

ሊበራል ክርስትና የግራ ዘመምን አስተሳሰብ በመያዝ በዚያው በ18ኛው መክዘ መጨረሻ እና በ19ኛው መክዘ መጀመርያ ብቅ ያለ አስተምህሮ ነው።። ይህ አስተምሮ ፕሮቴስታንቲዝምን ሳይቀር አክራሪ /conservative/ ነው ብሎ የሚያምን እና በሃይማኖት ለሰው ልጅ ልቅ የሆነ ሙበት እና ነጻነት ሊሰጠው ይገባል በሚል የተነሣ ነው።። በአሜሪካ እና በአውሮፓ አብዛኞቹ ፕሮቴስታንቶች እና ፓስተሮቻቸው በዚህ አመለካከት የሚመሩ ናቸው።።

ይህ አመለካከት የፕሮቴስታንቱን ዓለም ሃይማኖት አልባ ማድረጉ ሳያንሰው የካቶሊካውያንን እና የምሥራቅ እና የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናትን በር በማንኳኳት ላይ ይገኛል።። በመገናኛ ብዙኃን እና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው በየጊዜው ስለሚለፈፍ፣ ታላላቅ የሚባሉ ፖለቲከኞች እና የተከበሩ ሰዎች በየአጋጣሚው ስለሚያነሡት የሊበራል ክርስትና አስተሳሰብ እንደ ተስቦ በየሰው እየሠረፀ ነው ማለት ይቻላል።። ሊበራል ክርስትናን እንዲህ እና እንዲያ ነው ብሎ ከመበየን መገለጫዎቹን ማቅረቡ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል።።

የሊበራል ክርስትና አመለካከት ዋና ዋና መገለጫዎቹ የሚከተሉት ናቸው።።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ይላሉ

ሊበራል ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ወቅት የነበሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ምን እንደሚያምኑ የገለጡበት መጽሐፍ እንጂ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም ብለው ያምናሉ።። በመሆኑም ሊተች፣ ሊስተካከል፣ ሊታረም እና ሊቀየር የሚችል ጽሑፍ ነው ይላሉ።። በዚህ አስተሳሰባቸው ምክንያትም ዛሬ ዛሬ ብዙዎቹ የፕሮቴስታንት አስተማሪዎች በትምህርታቸው ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ማለት አልነበረበትም እያሉ ይተቻሉ።። ወይም አንድ ሰው እንዳለው they want to re-write the bible።። ሃይማኖታቸውም የግድ መጽሐፋዊ መሆን እንደሌለበት እና መጽሐፍ ቅዱስ የሃሳብ መነሻ ብቻ መሆን እንደሚችል ያስተምራሉ።። በመሆኑም በየጊዜው አዳዲስ እና የተሻሻሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅዎች እንዲታተሙ ያበረታታሉ።።

መጽሐፍ ቅዱስ ወጥ ትርጓሜ አያስፈልገውም ይላሉ

ሊበራሎች መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ሰው እንደተመቸው እና እንደገባው መተርጎም ይችላል፡፡ አንድ ወጥ የሆነ እና «ትክክል ነው» ተብሎ ሊመሰከርለት የሚችል ትርጓሜ የለም ይላሉ፡፡ ይህም በሃይማኖት እና በአስተሳሰብ የተለያዩ ሚሊዮን ዓይነት የክርስትና ክፍልፋዮች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡ ዶግማ እና ቀኖና የሚባል ነገር ስለሌላቸው ስለሚያመልኩት አምላክ እንኳንስ ሁሉም፣ በአንድ ጉባኤ የተገኙት እንኳን ተመሳሳይ እምነት የላቸውም፡፡ በማናቸውም ትምህርታቸውም ቢሆን የቀደሙ አበውን ትምህርት፣ ትርጓሜ እና ሐተታ አያካትቱም፡፡ ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሱ ካልሆነ በቀር፡፡ የቅዱሳንን ሕይወትም አስረጂ አድርገው አይቆጥሩትም፡፡

በሃይማኖት ጉዞ ውስጥ አንድ ሊቋረጥ የማይገባው አንድነት «አሐተኔ» አለ፡፡ ይኸውም በአንድ ዘመን በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል፣በአንድ ዘመን በሚኖሩ ወይንም በነበሩ ክርስቲያኖች እና ከእነርሱ በፊት በነበሩ ክርስቲያኖች መካከል፣እንዲሁም በአንድ ዘመን በሚኖሩ ወይንም በነበሩ ክርስቲያኖች እና ከእነርሱ በኋላ በሚመጡ ክርስቲያኖች መካከል የሃይማኖት አንድነት መኖሩ ነው፡፡ እኛ ከቀደሙ ክርስቲያኖች እና ወደፊት ከሚመጡ ክርስቲያኖች ጋር የሃይማኖት አንድነት ከሌለን «አንዲት ሃይማኖት፣ አንዲት ቤተ ክርስቲያን» ብለን መጥራት አንችልም፡፡

ሊበራሊዝም መጽሐፍ ቅዱስን እያንዳንዱ ሰው በራሱ መንገድ እንደፈለገ እንዲተረጉመው በመፍቀዱ የተነሣ በአንድ ዘመን በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል የሃይማኖት አንድነት የለም፡፡ በአንድ ዘመን በሚኖሩ ክርስቲያኖች እና ከእነርሱ በፊት በነበሩ፣በኋላም በሚመጡ መካከል ያለውም አንድነት ፈርሷል፡፡

ትክክለኛም ሆነ የተሳሳተ ሃይማኖት የለም ይላሉ

ሊበራሎች «አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ እስካመነበት ድረስ ማንኛውም እምነት ትክክል ነው» ብለው ያስተምራሉ፡፡ ከኤፌሶን ምዕራፍ ሁለት «አንዲት እምነት» ከሚለው ትምህርት በተቃራኒ «የተሳሳተ ሃይማኖት የለም፤ ሁሉም ሃይማኖት እኩል እና ትክክል ነው፡፡ ልዩነቱ የሰዎች አስተሳሰብ ነው» ብለው ያስተምራሉ፡፡ በመሆኑም ልዩ ልዩ አመለካከት ያላቸው አማኞች በአንድ ጊዜ፣ በአንድ ቦታ ፣በጋራ ማምለክ ይችላሉ ብለው ያስባሉ፡፡

ይህ አስተሳሰባቸውም ሰዎች የራሳቸውን ፍልስፍና እንደ ሃይማኖት ትምህርት እየቆጠሩ በየጊዜው እንዲበታተኑ አድርጓቸዋል፡፡ ወደ ትክክለኛዋ መንገድ ከመመለስ ይልቅ ሁላችንም ትክክል ነን በሚል ፍልስፍና በስሕተቱ ጎዳና እንዲበረቱበት ረድቷቸዋል፡፡

የሚያስፈልገው ማኅበራዊ ወንጌል ብቻ ነው ይላሉ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማኅበራዊ ኑሮ፣ ለፍትሕ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰብአዊ መብት እና ለእኩልነት መዳበር ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር እንጂ በመሠረተ እምነት/ዶግማ/ ላይ ማተኮሩን ይቃወማሉ፡፡ ለሰብኩቱ ማራኪነት፣ አስደሳችነት እና ሳቢነት እንጂ ለትምህርቱ ትክክለኛነት አይጨነቁም፡፡ የነገረ ሃይማኖት ጉዳዮችን ማንሣት ሊለያየን ስለሚችል «ከዚህም ከዚያም ያልሆነ አቀራረብ» /neutral approach/ መጠቀም ያስፈልጋል ባዮች ናቸው፡፡ ትምህርታቸው መንፈሳዊ ሳይሆን ሥነ ልቦናዊ፣ ለማዳን ሳይሆን ለማስደሰት፣ እውነቱን ለመመስከር ሳይሆን ሰው እውነት የመሰለውን እንዲመርጥ ለማድረግ የታሰበ ነው፡፡ የዶግማ እና የቀኖና ትምህርት አይሰጡም፡፡

ዛሬ ዛሬ ይህ በሽታ እኛም ውስጥ ገብቶ ነው መሰለኝ ሰባክያን የተባልን ሰዎች ከዶግማ ትምህርት እየወጣን በስብከት ላይ ብቻ ወደማተኮር እየቃጣን ነው፡፡ በትምህርታችን ውስጥ እንኳን መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርትን በተገቢው መንገድ አናቀርብም፡፡ ምእመናንም ይህንኑ ለምደው መሠረታዊ ትምህርት ሲሰጥ እንደ ባከነ ጊዜ ይቆጥሩታል፡፡ በትምህርት አሰጣጣችንም ውስጥ የአበው ትምህርት፣ ትርጓሜ እና ሐተታ እየተረሳ፣ የቅዱሳንም ሕይወት በአስረጅነት መጠቀሱ እየቀረ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን አልባ ክርስትናን ያስፋፋሉ

ሊበራል ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ለድኅነት የግድ አስፈላጊ አይደለችም፡፡ ያለ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያን መሆን ይቻላል፤ ብለው ያምናሉ፡፡ አንድ ሰው ካመነ ክርስቲያን ለመሆን በቂው ነው፡፡ ስለዚህም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ መጠመቅ፣ መቁ ረብ፣ መማር፣ መዘመር ወዘተ የግድ አያስፈልገውም ብለው ያስተምራሉ፡፡ ፕሮቴስታንቲዝም ሲጀመር «ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ከተራ ቤት እኩል ነው» ብሎ ተነሣ፣ ቀጥሎ ደግሞ ሊበራሎቹ «ያም ቢሆን አያስፈልግም» ብለው ደመደሙት፡፡ ውሻ በቀደደው አይደል ድሮስ ጅብ የሚገባው፡፡

በዚህ የተነሣም ብዙ ፕሮቴስታንቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም፣ አይሳተፉምም፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ ሀገር 10% የሚሆኑ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው ቤተ ክርስቲያን እሑድ እሑድ የሚሄዱ፡፡ በስካንዴኒቪያን ሀገሮች ደግሞ ከ2 እስከ 3% ብቻ ይሄዳል፡፡ በአሜሪካ 60% ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም፡፡ ከሚሄዱት ከ40% ብዙዎቹ ማኅበራዊ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የሚሄዱ ናቸው፡፡ እንዲያውም በአሁኑ ዘመን ደግሞ «የኮምፒውተር ቤተ ክርስቲያን» online church የሚባል እየተከፈተ ነው፡፡ ስለዚህም በዳታ ቤዙ ላይ የኃጢአት ዝርዝር አለ፤ የሠሩትን ኃጢአት ከዳታ ቤዙ ውስጥ ገብተው ክሊክ ሲያደርጉ ቅጣቱን ይነግርዎታል፡፡

መዋቅር አልባ እምነትን ያስፋፋሉ

ሊበራሊዝም ማንኛውም ክርስቲያን በፈቀደው መንገድ እንዲያምን ስለሚያስተምር ማናቸውንም ዓይነት የሃይማኖት መዋቅሮች አይቀበልም፡፡ ሃይማኖታዊ መዋቅሮች ይኑሩ ከተባለም በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሚመረጡ የቦርድ አባላት የሚመሩ እና ለብዙኃኑ ድምጽ ተገዥ የሆኑ መሆን አለባቸው ይላል፡፡ በዚህም የተነሣ የክህነትንም ሆነ የአስተዳደር እርከኖችን አይቀበልም፡፡ ጳጳሳት በካህናት ላይ፣ ካህናት በምእመናን ላይ ያላቸውን ሃይማኖታዊ ሥልጣን፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖታዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳይ በመወሰን ረገድ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለውን ሥልጣን አይቀበልም፡ :

በአሜሪካን ሀገር በ1960 እኤአ መሥመራውያን አብያተ ክርስቲያናት /main line protestants/ ከጠቅላላ ክርስቲያኑ 40% ይሸፍኑ ነበር፡፡ በ40 ዓመታት ውስጥ ግን በሊበራሎች ተነጥቀው ዛሬ 12% ብቻ ናቸው፡፡

ኑፋቄ የሚባል ነገር የለም ይላሉ

ሊበራሎች «የሁሉም ሰው ሃይማኖታዊ አመለካከት ትክክል ነው» ብለው ስለሚያምኑ ኑፋቄ የሚባል ነገር የለም ይላሉ፡፡ እንዲያውም ጥንት የተወገዙ መናፍቃን መብታቸው ተነክቷል ብለውም ያስባሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት የተለዩ የግኖስቲኮች መጻሕፍትን እንደ ገና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባትም ይጥራሉ፡፡ መናፍቃንን በተመለከተ

ምናልባት በዚያ ጊዜ የነበሩ አባቶች ተሳስተው ከሆነ ነገሩን እንደ ገና ማየት አለብን የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ የበርናባስ ወንጌል፣ የይሁዳ ወንጌል፣ የማርያም መግደላዊት ወንጌል ወዘተ የተባሉና በግኖስቲኮች የተጻፉ የክህደት መጻሕፍት ዛሬ ዛሬ እንደ አዲስ ግኝት በመቸብቸብ ላይ ናቸው፡፡

መናፍቃንን መናፍቃን ማለተ ሰውን ማራቅ ነው፡፡ ስለ መናፍቃን ማውራት መለያየትን ማባባስ ነው፡፡ ስለ ራሳችን ብቻ እንናገር እንጂ ስለሌሎች አናንሣ፡፡ የሚሉት አመለካከቶች የልዩነቱን ድንበር አፍርሰው ክርስቲያኖች ስንዴውን እና እንክርዳዱን መለየት እንዳይችሉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ለአዳዲስ አስተሳሰቦች ክፍት በር ይከፍታሉ

ሊበራሎች ለአዳዲስ አስተሳሰቦች በራችን ክፍት መሆን አለበት፣ አንድ ነገር አሳማኝ እስከሆነ ድረስ ልንቀበለው ይገባል ይላሉ፡፡ ዋናው ነገራቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት ሳይሆን ምን ያህል ሕዝቡ ይቀበለዋል? በሚለው መሠረት ነው፡፡ በዚህ የተነሣም የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን፣ የሴቶችን ክህነት፣ የእንስሳትን አባልነት ወዘተ በመቀበል ላይ ናቸው፡፡ የሊበራሎች አንዱ መሠረታዊ አስተሳሰብ ዘመኑን በቅዱሳት መጻሕፍት መዋጀት ሳይሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለዘመኑ ማመቻቸት ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እና በአባቶች ትምህርት ሳይመረመሩ አዳዲስ አስተሳሰቦች እንዲሁ የሚገቡባት ቤት መሆን አለባት ይላሉ፡፡

ግዴለሽነትን ያስፋፋሉ

ሊበራሎች ለጾም፣ ለጸሎት፣ ለሥነ ምግባር እና ለባሕል ግዴለሾች ናቸው፡፡ ሥርዓታዊ እምነት አይመቻቸውም፡፡ አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆን ከማመን እና ከማወቅ በላይ አያስፈልገውም ስለሚሉ ሌላ ዓይነት ሥርዓተ አምልኮን እንዲፈጽም አይገደድም፡፡ ጋብቻን ማክበር፣ ከሱስ ነጻ መሆን፣ ንጽሕናን መጠበቅ፣ ድንግልናን ማክበር፣ ወዘተ የሰው በነ ፈቃድ እንጂ የሃይማኖት ትምህርት ናቸው ብለው አይወስዷቸውም፡፡ ስለዚህም አማኞች ትክክለኛ ኑሮ እና የተሳሳተ ኑሮ፣ሥነ ምግባራዊ እና ኢሥነ ምግባራዊ የሚባለውን ለይተው እንዲያውቁ እና እንዲኖሩ አይነገራቸውም፡፡

ሊበራል ክርስትና ምን አመጣ?

ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይፈሩ አደረገ

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር የተባለው ተዘንግቶ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ የሚያሾፉ ፊልሞችን እንዲሠሩ፣ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣን እንኳን የማይለውን የዳቪንቺን ኮድን የመሰሉ አስተሳሰቦችን እንዲያራምዱ፣ በስቅለት ቅርጽ የፋሲካ ካንዲ እንዲሠሩ፣ ወዘተ አደረጋቸው፡፡ በየዘፈኖቻቸው ስመ እግዚአብሔርን እያነሡ እንዲቀልዱ አበረታታቸው፡፡ የጌታችን የስቅለት ሥዕል ከየቦታው እንዲነሣ ፣ አሠርቱ ትእዛዛት ከአሜሪካ ፍርድ ቤት በር እንዲነሣ አስደረጉ፡፡

ዛሬ ዛሬ ቅዱሳንን፣ ቤተ ክርስቲያንን እና የቤተ ክርስቲያን አካላትን እያነሡ መቀለድ እና ማቃለል በሀገራችን እየተለመደ ነው፡፡ ምሁራን፣ባለ ሥልጣናት፣ጋዜጠኞች እና ሌሎችም በይፋ በቤተ ክርስቲያን ነገሮች ላይ መቀለድ ልማድ አድርገውታል፡፡ የሚገርመው ነገር እነርሱም አይሰቀቁ፣እኛም ለምደነው እንስቃለን፤ አናዝንም፡፡ ለሌሎች

አርአያ ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ አገልጋዮች፣የእምነት አባቶች እና ገዳማውያን ሳይቀሩ በሥነ ምግባር ብልሹነት እና በሙስና እስከ መዘፈቅ ደርሰዋል፡፡

ለአክራሪ እስልምና ኢጋለጠን

አክራሪ እስልምና እጅግ በጣም ወግ አጥባቂ እምነት ነው፡፡ ይህ እምነት ወደ ምዕራቡ ዓለም ሲዘምት በሊበራሊዝም የተቦረቦረ ኅብረተሰብ ነው ያገኘው፡፡ ይህ የራሱ ማንነት የሌለው እና ሁሉም ትክክል ነው ብሎ የሚያምን ኅብረተሰብ ደግሞ በፍጥነት እና በፍላጎት ለሚሠራው አክራሪ እስልምና የተመቸ ሁኔታ ፈጠረለት፡፡ ፓትሪክ ሱኬዶ የተባሉ «የእስልምና እና ክርስትና ጥናት ተቋም ዳይሬክተር» እንደ ተናገሩት 200 ከፍተኛ የአሜሪካ ኩባንያዎች የሽሪያ ሕግን አጣጥመው ይሠሩበታል፡፡ ሳዑዲ ዐረቢያም ለዋና ዋና የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የገንዘብ ርዳታ በመስጠት የትምህርት ሥርዓቱ ከተቻለ ለእስልምና አመቺ ካልተቻለም ለዘብተኛ እንዲሆን ታደርጋለች ብለዋል፡፡

እጅግ ታዋቂ የሆኑ አሜሪካውያን ክርስትናው አላረካቸው ብሎ እስልምናን ሊቀበሉ የቻሉት፣ መጀመርያውኑ ርግጠኛውን ክርስትና ባለማግኘታቸው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ አንዳንድ የምዕራብ ዜጎች ከነ አልቃይዳ ጎን ተሰልፈው የገዛ ሀገራቸውን እና ወገናቸውን እስከማጥፋት የደረሱት ያሳደጋቸው ለዘብተኛ ክርስትና ሊያረካቸው ባለመቻሉ ነው፡ ፡

የሞራል መላሸቅን አስከተለ

ክፉ እና ደጉን ለይቶ የማያውቅ፣ ማንንም የማይፈራ፣ ለሱስ፣ ለመገዳደል፣ ለመጠጥ፣ ለሐሺሽ፣ ለዝሙት፣ ለጭፈራ፣ የተጋለጠ ለማኅበረሰባዊ እሴቶች ግድ የሌለው፣ ሀገሩን እና ወገኑን ለመርዳት የማያስብ፣ ከትምህርት ይልቅ መዝናናትን የሚመርጥ ትውልድ እንዲያፈሩ አደረገ፡፡ ዛሬ አሜሪካን ውስጥ ድራግ የማይቀምስ ወጣት የለም፡፡ በድንግልና መቆየት ነውር ሆኗል፡፡ ሌላው ቀርቶ አሜሪካውያን ለሂሳብ፣ ለፊዚክስ እና ለኢንጂነሪንግ ፍቅር የሌላቸው በሙዚቃ ግን የተለከፉ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ይሄ ነው፡፡ ቅዱሳንን ንቀው ታላላቅ ሰዎችን የሚያመልኩ፣ የፈለግኩትን ባደርግ ምን አለበት? በሚል ስሜት ለወንጀል የሚዳረጉ እንዲሆኑ አደረጋቸው፡፡

ቅድመ ጋብቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ኃጢአት ሳይሆን እንደ ሙበት በመታየቱ ዛሬ ወጣቶቻቸው እምብዛም አይጨነቁበትም፡፡ በአሜሪካ ውስጥ በተደረገ ጥናት ዕድሜያቸው 20 ዓመት ከሞላቸው ወጣቶች መካከል ቢያንስ 75% ቅድመ ጋብቻ የጸታ ግንኙነት ፈጽመዋል፡፡ በነገራችን ላይ የዛሬ 2 ዓመት በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በተደረገ ጥናትም ከ50% በላይ ተማሪዎች 18 ዓመት ሳይሞላቸው ጸታዊ ግንኙነት ማድረጋቸውን አመልክቷል፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎች መካከል የሚኖር ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን መሆኑ እየቀረ በተፈለገ ጊዜ ሊቀር የሚችል መሆኑ ስለተሰበከ ፍቺ በርክቷል፡፡ ጋብቻ በአንደ ወቅት የሚፈጸም ሥነ ሥርዓት እንጂ የቅድስና ምንጭ መሆኑ እየተረሳ ነው፡ ፡ በዚህም ምክንያት ሳይጋቡ በደባልነት መኖር እንደ ጋብቻ ኑሮ እየተቆጠረ መጥቷል፡፡

በአሜሪካ አብያተ ክርስቲያናቱ የጽንስ ማስወረድ ደጋፊዎች እና ተቃዋሚዎች ተብለው እስከ መለየት ደርሰዋል፡፡

አገልግሎትን እንደ ሞያ ማየት

በሊበራሊዝም አስተሳሰብ መንፈሳዊ አገልግሎቶች እንደ አንደ ሞያ ብቻ ይታያሉ፡፡ ጵጵስና፣ ካህንነት፣ ዘማሪነት፣ወዘተ ሞያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የሃይማኖት ሥነ ምግባርን እና አርአያ ክህነትን አይጠይቁም፡፡ አገልግሎት እንደሞያ ከታየ ፈሪሃ እግዚአ ብሔር ጠፍቶ ድፍረት ቦታውን ይይዛል፡፡ የሚያስተምሩትን ራሳቸው የማይፈጽሙ፣ለክብር ፣ ለዝና እና ለገንዘብ ብቻ ሲሉ የሚያገለግሉ፣ በመንፈሳዊነት ስም ኃጢአትን የሚፈጽሙ አገልጋዮች እየበዙ ይሄዳሉ፡፡ ባለፉት ዓመታት በአሜሪካ እና በአውስ ትራሊያ በካቶሊክ መነኮሳት ላይ የታየው የሞራል ዝቅጠት በሽታው የደረሰበትን ደረጃ ያመለክተናል፡፡

በሀገራችንም ቢሆን ዛሬ ዛሬ ምንኩስናን ለፍጹምነት መብቂያ መንገድ ሳይሆን የድብር አስተዳዳሪ ለመሆን፣ውጭ ሀገር ለመሄድ፣ የተሻለ ደመወዝ ለማግኘት የሚያስችል መንገድ አድርገው የሚቆጥሩት እየበዙ መጥተዋል፡፡ ሰባኪነት እና ዘማሪነትም ቢሆን ተሰጥኦ እና ትምህርት፣ሃይማኖት እና ምግባር የሚጠይቅ መሆኑ እየተዘነጋ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ ቀላል እና ክፍት የሥራ ቦታም ይመስላል፡፡

የማይጾም፣ የማይጸልይ፣ የማያስቀድስ፣ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የራቀ፣ የሌለበትን ሕይወት የሚያስተምር እና የሚዘምር አገልጋይ እየመጣ ነው፡፡ እንደ ባለሞያ ለእንጀራው ሲል ብቻ የማያምንበትን የሚያስተምር አገልጋይ እየመጣ ነው፡፡ ሰዓታት መቆም፣መቀደስ፣መመንኮስ፣ኪዳን ማድረስ፣ ጠዋት ተገብቶ ማታ የሚወጣበት ሥራ እየሆነ መጥቷል፡፡

የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የማያውቃቸው ምእመናንን እና ካህናትን አፈራ

ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው የማያስቀድሱ፣ የንስሐ አባታቸውን አግኝተው የማያውቁ፣ በአዳራሽ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ለመሰብሰብ የማይፈልጉ፤ አንድም ቤተ ክርስቲያን የማያውቃቸው ካህናት፣ ገዳም የማያውቃቸው መነኮሳት እየበዙ መጥተዋል፡፡

ከዚህም ብሶ ከአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የተነጠሉ አብያተ ክርስቲያናት እና ጳጳሳት ቁጥራቸው እየጨመረ ነው፡፡ «እኔን ከመሰለኝ» የሚለውን የሊበራል አስተሳሰብ በመከተል በአንድ በኩል ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር እየተሰበሰቡ በሌላ በኩል ደግሞ የግላቸው ቤተ ክርስቲያን መሥርተው የሚንቀሳቀሱ ጳጳሳት ተፈጥረዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች እና የጤና ተቋማት የግል እና የመንግሥት ተብለው እንደ ሚከፈሉት ሁሉ አገልጋዮችም የግል አገልጋዮች እና የቤተ ክህነት አገልጋዮች ተብለን እስከ መከፈል ደርሰናል፡፡

የሊበራሊዝም ግርፍ የሆኑ አንዳንዶች ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሊያድን እንጂ ሃይማኖት ሊመሠርት አልመጣም የሚል ፍስፍና ያስፋፋሉ፡፡ ለመሆኑ ሃይማኖት ምንድን ነው? ሃይማኖት ማለትኮ በቀላሉ ሲተረጎም እግዚአብሔርን የማምለኪያ መንገድ ማለት ነው፡፡ ታድያ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን መንገድ አልዘረጋም? ሐዋርያው ይሁዳስ «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ የተሰጠች ሃይማኖት» በማለት የገለጠው ምንድን ነው?/ይሁዳ 1÷3/ ቅዱስ ጳውሎስስ በኤፌሶን መልእክቱ «አንድ ሃይማኖት አለ» ያለው/ኤፌ 4÷5¼ ተሳስቷልን? ልጁ ቲቶን «ስለዚህም ምክንያት የቀረውን

እንድታደራጅ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝሁህ» ቲቶ 1÷5 በማለት የገለጠው ክርስትና የራሱ አደረጃጀት ስላለው አይደለምን?

ምን ይደረግ ?

ሊበራል ክርስትና ዛሬ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን እየተፈታተኑ ካሉት የዘመኑ ፈተናዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ፈተና በሁለት መልኩ ይገባል፡፡

የመጀመርያው አስተሳሰቡን በማራመድ ሆን ብሎ በሚደረግ ወረራ ነው፡፡ በሀገራችን ፕሮቴስታንቶች እና ተሐድሶዎች ሞክረውት የነበረው ይሄንን መንገድ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን አንዳንድ ፖለቲከኞች፣ ፓስተሮች እና ተሐድሶዎች ይህንኑ አስተሳሰብ ያራምዱታል፡፡ የሁለት ሺ ዓመት መሠረትን በማጥፋት ቤተ ክርስቲያንን ያልተጣሩ አስተሳሰቦች መናኸርያ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ ባለፉት ሁለት ሺ ዓመታት ወንጌል የገባው ሕዝብ አልተፈጠረም፣ ክርስቲያኑ ክርስቶስን አያውቅም ነበር ብሎ ማሰብ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በቋንቋው ተርጉሞ እና ከዮዲት እና ግራኝ ጠብቆ ያቆየን ሕዝብ መጽሐፍ ቅዱስን አታውቅም ነበር ብሎ በድፍረት ማስተማር መሠረትን ለማናጋት እንጂ እውነቱ ጠፍቶ አይደለም፡፡ አንድ ምሁር እንዳለው ይህ «ክርስቲያንን መልሶ ክርስቲያን ማድረግ re christianization of the Christians » ማለት ነው፡፡

በተለይም አሜሪካ የዚህ ወረራ ዋነኛ ቦታ ሆናለች፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት፣ትውፊት እና ባሕል እያቃለሉ ማስተማር፣ወይንም ደግሞ በጭራሽ ርእሰ ጉዳይ አድርጎ አለማስተማር እና ማስረሳት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ባለፉት ዘመናት ከ30 በላይ ገድላትን እና ድርሳናትን የሚሳደቡ ጽሑፎች በተሐድሶአውያን ታትመው በነጻ እየተሠራጩ ይገኛሉ፡፡ አክራሪ እስልምናን በተመለከተ ግን ትንፍሽ ብለው አያውቁም፡፡

ሁለተኛው ደግሞ አስተሳሰቡ ሳይታወቅ ይገባና ውስጥ ለውስጥ ይሸረሽራል፡፡ ከዚያም በሃይማኖት ለዘብተኛ ያደርጋል፡፡

ቅዱሳንን እና ክብራቸውን ማቃለል፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስሕተት ለመፈለግ መኳተን፣ የጸሎት መጻሕፍትን አለመጠቀም፣ በሰበብ በአስባቡ ከጾም መሸሽ፣ በየምክንያቱ ከቤተ ክርስቲያን መራቅ፣ ለንዋያተ ቅድሳት ያለን አክብሮት መቀነስ፣ ምን አለበት በሚል ምክንያት ነገሮችን በፈለግነው መንገድ ማድረግ፣ ጳጳሳትን፣ ካህናትን እና አገልጋዮችን መናቅ፣ እና በድፍረት መናገር፤ ቤተ ክርስቲያን ባልሄድም በልቤ መልካም ሰው ከሆንኩ ይበቃኛል እያሉ መጽናናት፣ በሃይማኖት ጉዳዮች ሳቅ እና ቀልድ ማብዛት፣ በሃይማኖት ማፈር፣ አንዲት እምነት ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወጥቶ፣ ለሌሎቹ ያዘኑ በመምሰል፣ ሁሉም ልክ ነው የሚል አዝማሚያ መያዝ ከበሽታው ምልክቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በሽታው ሌላም ምልክቶች አሉት፡፡ የሊበራል ክርስትና «እኔ እኔ» አስተሳሰብ ወደ መዝሙሩም፣ ወደ ትምህርቱም ይገባና ሁሉም በዚሁ ይቃኛል፡፡ እግዚአብሔርንም የኔ ማለት ይጀመራል፡፡ በትምህርታችን ውስጥ እኔ እንዲህ ሆኜ፣ ይህንን አድርጌ፣ እንዲህ ያለ ነገር ታይቶኝ፣ ወዘተ እያሉ ራስን ከፍ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮችን መጨማመር፣ በመዝሙሮቻችንም ራስን መስበክ ይመጣል፡፡ በምሥራቃውያን ትውፊት ሰው ስለ ራሱ ይናገር የነበረው ታናሽነቱን፣

ትጎትናውን ወይንም በደለኛነቱን ለመግለጥ ነበር፡፡ ሊበራሊዝም ዘልቆ ሲገባ ግን የራስን ታላቅነት እና ክብር መናገርም ይጀመራል፡፡

ሊበራሎች ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ነው ብለው አያምኑም፡፡ ከዚያ ይልቅ ለሰዎች ሕይወት «ሞዴል ነው» ይላሉ፡፡ ስለዚህም እንደ አንድ ፍቅረኛ፣ ጓደኛ፣ አርአያ ያዩታል እንጂ በአምላክነቱ አይቀበሉትም፡፡ በመሆኑም ናፈቀኝ፣ እወደዋለሁ፣ ጓዴ ነው፣ አብሮ አደጌ ወዘተ ብሎ መጥራት ያዘወትራሉ፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው ገብቶብን እንደሆነም አላውቅም «ስትናፍቀን እንዘምራለን» የሚል መዝሙር በሰንበት ት/ቤቶች ሲዘመር የሰማሁ ይመስለኛል፡፡

ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ከሁለት አቅጣጫ በሚመጣ ፈተና ተወጥራለች፡፡ ከምሥራቅ ወግ አጥባቂው እና በከፍተኛ ሁኔታ ኃይልን፣ ገንዘብን እና ነውጥን በሚጠቀመው አክራሪ እስልምና፣ ከምዕራብ በኩል ደግሞ ለሃይማኖት ግድየለሽ፣ በፈጣሪ በሚቀልደው እና ጠንካራ እና ጽኑዕ እምነትን ለመሸርሸር በተነሳው ሊበራል ክርስትና፡፡ አንዱ በኃይል ሌላው በፍልስፍና - ኦርቶዶክሳዊነትን ለማጥፋት ዘምተዋል፡፡

ይህንን ከሁለት ወገን የመጣ እና ሳንዱዊች ሊያደርገን የተዘጋጀ ፈተና **«መንፈሳውያን ሃይማኖታውያን»** በመሆን ብቻ ነው ድል የምንነሣው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በመዋቅር የተበታተነች፤ በአሠራርዋ የተዳከመች ከሆነች፤ ልጆቿ በመንፈስ የዛሉ፣ በሃይማኖት ዕውቀት ያልበረቱ ከሆኑ ፈተናውን መቋቋም አይችሉም፡፡

«በክርስትና እና በሳይንስ መካከል ያለው ዐቢይ ልዩነት፣ በሳይንስ የቅርቡ በጣም የተሻለ ሲሆን፣በክርስትና ግን የጥንቱ በጣም የተሻለ መሆኑ ነው in science the latest is the best, but in Christianity the oldest is the best» በማለት ይስሐቅ አል ባራኪ የተባሉ ሶርያዊ ሊቅ እና ሳይንቲስት ተናግረዋል፡፡ ክርስቲያን የሆንነው እኛ አባቶቻችንን ለመምሰል እንጂ አባቶቻችን እኛን እንዲመስሉን አይደለም፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያንም የመጣነው እኛ በቤተ ክርስቲያንዊ ትምህርት እና ሕግ ልንመራ እንጂ ቤተ ክርስቲያን በኛ ትምህርት እና ሕግ ለመምራት አይደለም፡፡

በመሆኑም ትክክለኛውን ክርስትና ለመኖር እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያንም ወደ እኛ መግባት አለባት፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ክርስትና በሦስት መልኩ መገለጥ አለበት ትምህርታዊ፣ ሊተርጂያዊ፣ እና ትውፊታዊ፡፡ ትምህርታዊ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን አባቶቻችን በተረዱበት መንገድ እና መሠረት መረዳት፣ መመስከር እና መኖር ማለት ነው፡ ፡ በክርስትና አዳዲስ ማብራርያዎች እንጂ አዳዲስ መሠረተ ሃሳቦች ሊኖሩ አይችሉም፡፡

ሊተርጂያዊ ማለት ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚገኙትን ጾም ፣ጸሎት፣ ቅዳሴ፣ የምሥጢራት ተሳትፎ፣ ዝማሬ፣ ወዘተ ገንዘብ ማድረግ እና የእነዚህ ፍሬዎች የሆኑትን የምግባር ፍሬዎች ማሳየት ማለት ነው፡፡ ትውፊታዊ ማለትም በቤተ ክርስቲያን ያገኘናቸውን የቀደሙ አበው የሕይወት መንገዶች፣ትሩፋቶች፣ጸጋዎች፣ ቅርሶች በመያዝ፣በመጠበቅ እና በመጠቀም መኖር ነው፡፡

ዋናን ከውኃ ውጭ መዋኘት እንደማይቻለው ሁሉ ክርስትናንም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ መኖር አይቻልም፡፡ በመርከቧ ሲጓዙ ማዕበል በተነሣባቸው ጊዜ በዚያው መርከብ ውስጥ ሆነው አድነን ነበር ያሉት ሐዋርያት፡፡ እኛም በየምክንያቱ ከቤተ ክርስቲያን መውጣታችንን ትተን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመኖር ችግሮችን መጋደል እና መቋቋም ያስፈልጋል፡ ፡

በረከታቸው ይደርብንና ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ «ሽረሪት አትሁኑ» ይሉ ነበር፡፡ ሽረሪት ድር አድርታ የኖረችበት ቤት ሲቃጠል ውኃ አምጥታ ከማጥፋት ይልቅ ቤቱን ለቅቃ ሌላ ቦታ በመሄድ ድር ታደራለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ፈተና በገጠማት ቁጥር እየሸሹ የራስን ጎሊናዊም ቁሳዊም ጎጆ መቀለስ ሽረሪትነት ነው፡፡

ሃይማኖት የትርፍ ጊዜ ሥራ መሆን የለበትም፡፡ መንፈሳዊነትም ባሕል እና ልማድ ብቻ ሆኖ ያለ ልቡና እንዲሁ የሚኖርበት መሆን የለበትም፡፡ በመሆኑም ቀጥ ብሎ ራስን መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ እንደዋዛ የምንናገራቸው እና የምናደርጋቸው ነገሮች ቤተ ክርስቲያንን ሸርሽረው ሸርሽረው በምእመናን ላይ የማይጠገን ቁስል ከመጣላቸው በፊት በቀደሙት አበው ትምህርት እና ኑሮ መነጽርነት መንገድን እና ልብንም መመርመሩ የተሻለ ነው፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

11. መንፈሳዊ ወይስ መንፈሳይ?

ከአራት ዓመት በላይ አብረን ስናገለግል ፀጉርዋን ተገልጦ አንድ ቀን አይቼው አላውቅም፡፡ ሁልጊዜ በሻሽ እና በነጠላ እንደ ተሸፈነ ነው፡፡ ቀሚሷ መሬት ወርዶ አፈር ይጠርግ ነበር፡፡ አንገቷ ቀና ብሎ የሚሄድ አይመስለኝም፡፡ አብረዋት በሚዘምሩት የመዝሙር ክፍል አባላት ጠባይ፣ ምግባር፣ አለባበስ ሁልጊዜ እንደ ተናደደች፡፡ እንደ ተቆጣች፡፡ እንደ ገሠጸች ትኖር ነበር፡፡ በተለይም ሱሪ የለበሰች ዘማሪት እርሷ ፊት ከታየች አለቀላት፡፡ የነነዌ ሰዎች በይቅርታ የታለፉትን እሳት ልታወርድባት ትደርስ ነበር፡፡ እንኳን ቀለማ ቀለም ቀርቶ ቅባት መቀባት በእርሷ ዘንድ ለገሃነም የሚያደርስ ኃጢአት ነው፡፡ ፀጉር መሠራትና ንጽሕናን መጠበቅማ አይታሰብም፡፡

ይህችን እኅት የማውቃት በአንድ ማኅበር አብረን ስናገለግል ስብሰባ እና የጋራ አገልግሎት እያገናኘን ነው፡፡ የእርሷን ተግሣጽ እና ቁጣ ፈርተው ብዙ እኅቶች የአገልግሎት ክፍሉን ለቅቀዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ለሽምግልና እኛ ጋር መጥተው በስንት ልመና መልሰናቸዋል፡፡ ሌሎቹም የመጣው ይምጣ ብለው ችለዋት አገልግለዋል፡፡

በመካከል ልጅቷ በድንገት ከአልግሎት ክፍሉ ጠፋች፡፡ እኛም ቤቷ ድረስ ሰው ልከን ነበር፡፡ ነገ ዛሬ እያለች አልተመለሰችም፡፡

አንድ ቀን ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዓይነ ሥውራን ማኅበር በኩል ወደ የካቲት ሆስፒታል በሚወስደው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በኩል ስጓዝ መልኳን የማውቃት የምትመስል አንዲት ልጅ አየሁ፡፡ አለባበሷ ለየት ያለ ነበር፡ ፡ የአጭር አጭር ሱሪ ለብሳለች፡፡ ከደረቷ በላይ ያለው አካሏ ልብስ የሚባል አልነበረውም፡፡ ከንፈሯ ቦግ ያለ ቀለም ተቀብቷል፡፡ የጥፍሯ ቀለምም ከሩቁ ይታያል፡፡ የጆሮዋ ጌጥ ባለ ሦስት አንገት አስደርጓታል፡፡

ዓይኔን ማመን አቃተው፡፡ ‹በሕልሜ ነው፣ በእውኔ፣ ወይስ በቴሌቭዥን› አለ ሰውዬው፡፡ ያች ዘማሪውን ሁሉ ሱሪ ለበሳችሁ ብላ ያባረረች፤ ቅባት ተቀባችሁ ብላ አትዘምሩም ያለች፤ ቀሚሳችሁ አጠረ ብላ ልብስ ያስቀየረች፡፡ ጥፍራችሁ ረዘመ፣ ፀጉራችሁ ተተኮሰ ስትል የነበረች ልጅ እንደዚህ ሆነች? ማረጋገጥ ፈለግኩና ከምሄድበት መኪና ወርጄ ከሰው ጋር ቆማ ወደምታወራበት ቦታ ተሻገርኩ፡፡ ሰላምም አልኳት፡፡ መቼም ባታየኝ በወደደች፡፡

ለመሆኑ መንፈሳዊነት ምንድን ነው፡፡ ረዥም ቀሚስ መልበስ ነው? ፀጉርን በአሮጌ ሻሽ መሸፈን ነው? ገላን ያለመታጠብ ነው? አንገትን መድፋት ብቻ ነው? ቀስ ብሎ መናገር ነው? ኋላ ቀርነት ነው? አይመስለኝም፡፡ ቴሌቭዥን አለማየት፣ኢሜይል አለመጠቀም ነው? ከጸሎት መጻሕፍት በቀር ሌላ ነገር አለማንበብ ነው?

መንፈሳዊነትኮ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ነው፡፡ ራስን ማሸነፍ ነው፡፡ አእምሮን እና ልቡናን ቀና እና ሰላማዊ ማድረግ ነው፡፡ ለመሆኑ የውስጡ መንፈሳዊነት አይደለም እንዴ ወደላይ መገለጥ ያለበት፡፡ ስለ ሐዋርያት ስንናገርኮ የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው፣ የሥጋቸው ቅድስና ለልብሳቸው፣ የልብሳቸው ቅድስና ደግሞ ለጥላቸው ተረፈ ነው የምንለው፡፡ መንፈሳዊነቱ ከውስጥ ወደ ውጭ እንጂ ከውጭ ወደ ውስጥ አልነበረም፡፡

አንዳንድ ጊዜ «መንፈሳዊነት» ከ «መንፈሳይነት» ጋር እየተመሳሰለ የምንቸገር ይመስለኛል፡፡ ዲያቆን ኤፍሬም እሸቴ ነው ይህችን ቃል ያመጣት፡፡ ከሁለት ቃላት «መንፈሳዊ» እና «መሳይ» ከሚሉ ቃላት ቆራርጦ «መንፈሳይ» የሚል ቃል ፈጠረ፡፡ ትርጉሙም «መንፈሳዊ መሳይ» ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች መንፈሳውያን ይመስላሉ እንጂ አይደሉም፡፡

አባ ኤፍሬም ሶርያዊ ባስልዮስን ለማየት በሄደ ጊዜ ስለ ክብረ ወንጌል ሲል ከላዩ የወርቅ ልብስ ለብሶ ፣ የወርቅ ወንበር ዘርግቶ፣ የወርቅ ጫማ ተጫምቶ በጉባኤው ላይ ባየው ጊዜ «ደገኛ መምህር የተባለው ባስልዮስ ይኼ ነውን?» ብሎ ነበር፡፡ በኋላ ግን ተአምራቱን አይቶ አድንቆታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የውጭ ገጽታ ውስጥን ሊገልጥም ላይገልጥም ይችላልና፡፡

ልክ ነው ክርስቲያናዊ አነጋገር፣ አለባበስ፣ አረማመድ፣ ገጽታ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማለት መንፈሳዊነት ጅልነት፣ ከርፋፋነት፣ ኋላ ቀርነት ወይንም ደግሞ፣ ንጽሕናን አለመጠበቅ ማለት ግን አይደለም፡፡ በመንፈሳዊነታቸው የሚደነቁት የቤተ ክርስቲያን ከዋክብት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ባስልዮስ ዘቂሳርያ በዘመኑ በነበረው የግሪክ ፍልስፍና እና ዕውቀት የበለጸጉ ነገር ግን ዕውቀታቸውን እና ሥልጣኔያቸውን በወንጌል የቃኙ ነበሩ፡፡

ብዙዎቻችን ከውስጥ ለሚመነጨ ትእግሥትን፣ ደግነትን፣ ታዛዥነትን፣ ትኅትናን፣ አርቆ ማሰብን፣ ኀዘኔታን፣ ፍቅርን፣ ትጋትን ለመሰሉ ነገሮች ትኩረት አንሰጥም፡፡ ከዚያ ይልቅ ተዋንያን ሊያደርጉት የሚችሉትን የውጭ ገጽታን ብቻ በማየት መመዘን እንመርጣለን፡፡

እውነተኛው መንፈሳዊነት ግን ከመንፈሳይነት መለየት አለበት፡፡ መንፈሳይ ሰዎች የራሳቸው መለያ ባሕርያት አሏቸው፡ ፡

እነዚህ ሰዎች ከውስጣዊ መንፈሳዊነት ይልቅ ለውጫዊ ነገሮች ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ውስጣዊ ማንነታቸውን ለመሸፈን ሲሉ ሕግ ከሚፈቅደው በላይ ለውጫዊ ገጽታ ይጨነቃሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ስለ የፀጉር አያያዝ የራስዋ ባህል አላት፡፡ እነርሱ ግን ፀጉር መታጠብን ኃጢአት ያደርጉታል፡፡ ክርስቲያኖች የሚለብሱት ልብስ ራሳቸውን የማያጋልጥ እንዲሆን ትመክራለች፡፡ እነርሱ ግን ልብስ ሁሉ መሬት ካልጠረገ ይላሉ፡፡ ያደፈ በመልበስ፣ የአእምሮ ችግር ያለባቸው ይመስል እጅግ ቀሰስ ብለው በመናገር፣ ሰው መሆናቸውን ረስተው ምንም ነገር እንደማይበሉ እና እንደማይጠጡ በማሳመን፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ በመልበስ፣ ሰንሰለት በመታጠቅ፣ ትልልቅ መቁጠርያ እጃቸው ላይ በመጠቅለል፡፡ ይበልጥ መንፈሳዊ ሆነው መታየት ይፈልጋሉ፡፡

ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው በዱርዬ እና በሴተኛ አዳሪዎች ዘንድ ያለውን ያህል ፈሪሃ እግዚአብሔር በአገልጋዮች ዘንድ የለም ይል ነበር፡፡ አንዳንዶች በአገልግሎት እየበረቱ ሲሄዱ ከመንፈሳዊነት ወደ መንፈሳይነት ስለሚለወጡ፡፡

ጋሽ ግርማ ከበደ ከሚያስተምረው ነገር የማልረሳው ቃል አለ፡፡ «ሰው የሚጠላውን ኃጢ አት ደጋግሞ ይሠራዋል» ይላል፡፡ ለምንድን ነው ደጋግሞ ይሠራዋል ያለው? እኔ እንደ ተረዳሁት መጀመርያውኑ ይህ ሰው ውስጡ ያላመነበትን እና ሊያደርገው የማይፈ ልገውን ነገር ነው ለማስመሰል ሲል እያወራ ያለው፡፡ ስለዚህም በውስጡ ያንን የጠላውን ነገር ላለማድረግ መንፈሳዊ ተጋድሎ ስለማያደርግ ደጋግሞ ሲሠራው ይገኛል፡፡

እንዲያውም አንዳንዶች መንፈሳያን ስለ አንድ ሰው መንፈሳዊነት ደጋግመው በጥላቻ ወይንም በንቀት፣ ወይንም ደግሞ በመመጻደቅ የሚያወሩ ከሆነ ያንጊዜ አንዳች ነገር ተረዱ፡፡ ሳያስቡት እየተናገሩ ያሉት ስለ ራሳቸው ነው፡፡ መንፈሳውያን ሰዎች ስለሌሎች ውድቀት ሲያነሡ ከርኅራኄ እና ከኀዘኔታ ጋር ነው፡፡ የደስታ ስሜት አይሰማቸውም፡፡

እንደ ጀብዱም አይቆጥሩትም፡፡ ለዚህም ነው በቅዳሴ አትናቴዎስ ሊቁ ስለ አዳምና ሔዋን አንሥቶ «እኛስ እናንተን ልንወቅሳችሁ አንችልም» በማለት የተናገረው፡፡

መንፈሳውያን ይነበባሉ፤መንፈሳያን ግን ይታያሉ፡፡ መንፈሳውያን ይቀመሳሉ፣ መንፈሳያን ግን ይላሳሉ፡፡ መንፈሳውያን ያዳምጣሉ፤ መንፈሳያን ግን ይለፈልፋሉ፡፡ መንፈሳውያን ያስተውላሉ፤ መንፈሳያን ግን ይቸኩላሉ፤ መንፈሳውያን ያጠግባሉ፣ መንፈሳያን ግን ያቁለጨልጫሉ፡፡ መንፈሳውያን ይመዝናሉ፤ መንፈሳያን ግን ያፍሳሉ፡፡ መንፈሳውያን ያርማሉ፤ መንፈሳያን ግን ይተቻሉ፡፡

መንፈሳውያን ጠላቶቻቸውን ወዳጆቻቸው ለማድረግ አንድ ሺ ዕድል ይሰጣሉ፤ መንፈሳያን ግን ወዳጆቻቸውን ጠላቶቻቸው ለማድረግ አንድ ሺ በር ይከፍታሉ፡፡ መንፈሳውያን ይጾማሉ፣ መንፈሳያን ይራባሉ፤ መንፈሳውያን ይጸልያሉ፣ መንፈሳያን ግን ይናገራሉ/ያነባሉ፡፡ መንፈሳውያን ሱባኤ ይይዛሉ፣ መንፈሳያን ግን ስለ ሱባኤያቸው ያወራሉ፡፡ መንፈሳውያን ይሰጣሉ፣ መንፈሳያን ግን ሲሰጡ ያሳያሉ፡፡ መንፈሳውያን ቃለ እግዚአብሔርን ያስተምራሉ፣ መንፈሳያን ግን በራሳቸው ቃላት ይጠበባሉ፤ መንፈሳውያን ወደ ውስጥ፣ መንፈሳያን ወደ ውጭ ያያሉ፡፡ መንፈሳውያን የነገን፣ መንፈሳያን የዛሬን ያያሉ፡፡ መንፈሳውያን ምክንያቱን፣ መንፈሳያን ድርጊቱን ያያሉ፡፡ መንፈሳውያን ራሳቸውን፣ መንፈሳያን ሌላውን ያያሉ፡፡

መንፈሳውያን ከመፍረዳቸው በፊት ይመክራሉ፤ መንፈሳያን ከፈረዱ በኋላ ይመክራሉ፡፡ መንፈሳውያን ዘጠኝ ጊዜ ለክተው አንድ ጊዜ ይሰፋሉ፣ መንፈሳያን ግን ዘጠኝ ጊዜ ሰፍተው አንድ ጊዜ ይለካሉ፡፡ መንፈሳውያን ከመናገራቸው በፊት ያስባሉ፣ መንፈሳያን ከተናገሩ በኋላ ያስባሉ፡፡ መንፈሳውያን ይወስናሉ፣ መንፈሳያን አስተያየት ያበዛሉ፡፡ መንፈሳውያን ሰው እንዳይሞት በቸግሩ ጊዜ ይረዳሉ፣ መንፈሳያን ግን ሰው ሲሞት የልቅሶ ትርኢት ያሳያሉ፡፡ መንፈሳውያን ስለ ሌሎች በጎ መናገርን ያዘወትራሉ፣ መንፈሳያን ስለ ራሳቸው በጎ መናገርን ይፈልጋሉ፡፡ መንፈሳያን ነጭ እና ጥቁር ብቻ ያያሉ፣ መንፈሳውያን ግን ግራጫንም ጨምረው ይመለከታሉ፡፡

መንፈሳዊ ሰው አንድ ሰው ነው፡፡ መንፈሳይ ሰው ግን ሁለት ሰው ነው፡፡ ውጩ ሌላ ውስጡ ደግሞ ሌላ ነው፡፡ ገና ያልተሸነፈ፣ እንዲያውም እየገነገነ እና እየገነተረ የሚሄድ ክፉ ጠባይ አለባቸው፡፡ አይጋደሉትም፡፡ አይጸየፉትም፡፡ ሊያሸንፉት አይፈልጉም፡፡ አይቃወሙትም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጥሩ ተዋናይ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአረማመድ፣ በመቅለስለስ፣ በመሸፋፈን እና ለሰው መስለው በመታየት ሊገልጡት የሚፈልጉት ሌላ ማንነት ደግሞ አላቸው፡፡ ይህ የውስጥ ማንነት አንድ ቀን ያሸንፍና እንደ ዴማስ ያስኮበልላቸዋል፡፡ ያን ጊዜ በሰው ይፈርዱ የነበሩትን ነገር ሁሉ አብዝተው ያደርጉታል፡፡ ወጣ ወጣ እና እንደ ሽንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ የተባለው ይደርስባቸዋል፡፡

አንዳንዴ መንፈሳይነት ሕይወት ሳይሆን በሽታ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ያውም የአእምሮ መዛባት/ mental disorder/፡፡ በሁለት ማንነቶች መካከል እየተምታቱ መኖር፡፡ መንፈሳዊ ሰው ኃጢአት ቢሠራ እንኳን ንስሐ ይገባበታል፡፡ ያርመዋል፡፡ ይጋደልበታል፡፡ ኃጢአቱን በመሸፈን እና በማስመሰል ሳይሆን በመጋደል እና በማስወገድ ያምናል፡፡ መንፈሳይ ሰው ግን ሌሎች እንዳያዩት እንጂ እግዚአብሔር እንዳያየው አይጨነቅም፡፡

አሁን እኛ እስኪ ራሳችንን እንየው

መንፈሳዊ ነን ወይስ መንፈሳይ?

12. የመቅደላው ጊታ

ልዩ መርሐ ግብር ፡ ***ዐፄ ቴዎድሮስ አስደናቂውን ገድል ከፈጸሙ 142 ዓመታት ሆኗቸው። ባለፈው ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓም። መቅደላ ላይ ራሳቸውን የሠውት ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም ነው። ባለፈው ሳምንት መታሰቢያ ሊደረግላቸው ይገባ ነበር። ከአንዳንድ FM ሬድዮኖች በቀር ያስታወሳቸውም የለ። እስኪ በአዲሰ ነገር አውጥቼው የነበረውን ጽሑፍ ለመታሰቢያነት መልሰን እንየው። መልካም ንባብ።***

እነሆ በዊንድዘር ቤተ መንግሥት እንገኛለን። ይህ ቤተ መንግሥት በዓለም ላይ በስፋቱ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት አገልግሎት ሰጭ ቤተ መንግሥት ነው። «ዊልያም ወራሪው» እየታባለ በሚጠራው የእንግሊዝ ንጉሥ/ 1066-1087/ የተገነባው ይህ ቤተ መንግሥት 10.5 ሄክታር ስፋት አለው። በውስጡ 951 ክፍሎች ሲኖሩት ከእነዚህም ውስጥ 225ቱ የመኝታ ክፍሎች ናቸው። ቤተ መንግሥቱ ለእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤጥ በዓመት ሁለት ጊዜ /በሰሞነ ትንሣኤ እና በሰኔ ወር/ ለማረፊያነት ያገለግላል።

ወደዚህ ቤተ መንግሥት የሄድኩት ልቅሶ ልደርስ ነው። በሃገራችን ባሕል አንድ ሰው በሞተበት ጊዜ ተገኝቶ ያልቀበረና ልቅሶ ያልደረሰ ሰው ዘግይቶ ሲመጣ ወደ መቃብር ሄዶ የሟችን መቃብር አይቶ እርሙን ያወጣል። እኔም ወደዚህ ቤተ መንግሥት የሄድኩት በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስን መቃብር ለማየት ነበር።

በመቅደላ ጦርነት ጊዜ በጀኔራል ናፒየሪ አማካኝነት ከእናቱ ጋር ወደ እንግሊዝ ተጓዘ። መንገድ ላይ እናቱ ዐርፋ ብቸኛ የሆነው ዓለማየሁ የንግሥት ቪክቶርያ ክብካቤ ሳይለየው በእንግሊዝ የንጉሣውያን ቤተሰቦች ዘንድ አደገ። ነገር ግን እንደ ሀገሩ እንደ ሕዝቡ የሚሆንለት አላገኘም። በ18 ዓመት ዕድሜው ታምሞ ሞተ። በሀገሩ ቢሆን ኖሮ ሙሽ ወርዶለት፣ ፍትሐት ደርሶለት፣ የውሎ ልቅሶ ተዘጋጅቶለት፣ ግጥም እና ዜማው እየወረደ ነበር የሚቀበረው። ይህንን ክብር በባዕድ ሀገር ያግኘው ያግኘው አላወቅኩም።

ትኬት ለመቁረጥ ወደ እንግዳ መቀበያው ስንገባ ረዥም ሰልፍ ነበር። እንዳይሰለቸን ስለ ቤተ መንግሥቱ የሚያብራራ የምናነበው ብሮሸር ሰጡን። የምንጎበኘው የዐፄ የፋሲልን ቤተ መንግሥት አይደለምና። መቼም እንግሊዞች ቱሪስትን በመሳብ፣ በመከባከብ እና በሥርዓቱ በማስጎብኘት የሚመሰገን ባሕል አላቸው። በዓመት ከ12 ቢሊዮን ፓውንድ በላይ እንደሚያገኙበት መረጃዎች ያመለክታሉ።

እዚያ ቦታ ቆሜ የፋሲልን ቤተ መንግሥት የጎበኘሁበትን ጊዜ አሰብኩት። አልፎ አልፎ ከተጻፈው ነገር በቀር በሥዕል፣ በቅርጽ፣ በዓይነት፣ በጽሑፍ፣ በቪዲዮ ታሪኩን ለመግለጥ የተደረገ ጥረት አልነበረም። ሌላው ቀርቶ የቤተ መንግሥቱን ታሪክ አስጎብኝዎቹ ደስ እንዳላቸው ይተርኩታል እንጂ ከነካርታው የተዘጋጀ መጽሐፍ እንኳን አላገኘሁም ነበር። «እዚህ ቦታ ይተኙበት ነበር» ብሎ ከመግለጥ ባለፈ በዚያ ዘመን የነበረውን አልጋ አፈላልጎ ወይንም አስመስሎ ሠርቶ ለማሳየት አይሞክርም።

ዊንድዘር ቤተ መንግሥትን ስትጎበኙ ግን ያን ጊዜ የነበረው ሳሎን፣አልጋ፣ ማዕድ ቤት ከነቁሳቁሱ ትጎበኙታላችሁ፤ ዶሮዎች እና በጎች እንዴት ይታረዱ እንደነበር በላስቲክ በተሠራ ቅርጽ ታዩታላችሁ። ይጠቀሙበት የነበረው መሣርያ፣ ቢላዋው፣ ሰሐኑ አልቀራቸውም። ታድያ እነ ዐፄ ፋሲል ቢያንስ ሞሰብ አልነበራቸውም፣ ይቀመጡበት የነበረውን ወንበር፣ ይጫወቱበት የነበረውን ገበጣ፣ ድስቱን እና መክተፊያውን፣ የዘመኑ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበረውን መሣርያ፣ ልብሳቸውን እና ምንጣፋቸውን በየገዳማቱ ከሚገኙት ቅሪቶች ገልብጦ በመሥራት ማሳየት አቅቶን ነው?

በጥንታዊው የአሳሳል ዘይቤ የጥንቱን ሁኔታ ስለን በየግድግዳው ብናስቀምጠው፤ ፎቶ አንሥተን ለቱሪስቱ ብንሸጠው፣ ፖስት ካርድ ብናደርገው ሀገር ስለሚያሳድግ ከመጀመርያው መታሰብ የለበትምi

የሃያኛዋን ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ የሚያሳየው የአዲስ አበባው ቤተ መንግሥትስ ቢጎበኝ ምን ይለዋል? ነፍሳቸውን ይማርና የቤተ መንግሥቱ ኃላፊ የነበሩት ብርጋድዬር ጀኔራል ፍሬ ሰንበት ዓምዴ አያሌ ቅርሶችን አሰባስበዋል።

የዊንድዘርን ቤተ መንግሥት በየክፍሎቹ እያየን፣ በኛም ስንፍና እየተናደድን ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገባን፡ ከመግቢያው በር አጠገብ የቤተ መንግሥት አስጎብኝዎችን ልብስ የለበሱ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰው አገኘን። ጠጋ አልንና «የዓለማየሁ ቴዎድሮስን መቃብር ለማየት ነበር» አልናቸው። «ኢትዮጵያውያን ናቸሁ?» ሲሉ ጠየቁን። እኛም በአዎንታ ራሳችንን ነቀነቅን። «ብዙ ጊዜ ነጮች እና ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ጥቁሮች ናቸው የሚጠይቁን» ሲሉ በመገረም ተናገሩ። ከዚያም እየመሩ ይዘውን ሄዱ። በበሩ ገብታችሁ ወደ ግራ ትታጠፉና ግድግዳውን ጨርሳችሁ ወደ ቀኝ ልትዞሩ ስትሉ ማዕዘኑ ላይ የዓለማየሁን መቃብር ታገኙታላችሁ።

ከላይ የመዖር መስቀል፣ ዝቅ ብሎ ደግሞ የአንበሳ ሥዕል ይታያል። ከአንበሳው ሥር በእንግሊዝኛ Near this spot lies buried Alemayehu /ከዚህ ቦታ አጠገብ ዓለማየሁ ተቀብሯል/ ይልና መልሶ በአማርኛ «ዓለማየሁ ቴዎድሮስ» ይላል። ቀጥሎም The Son of Theodor king of Abyssinia, Born 23 April 1861 Died 14 Nov. 1879. This tablet is placed here to his memory by Queen Victoria. /የአቢሲኒያ ንጉሥ የቴዎድሮስ ልጅ፤ አፕሪል 23 1861 ተወለደ፣ ኖቬምበር 14 ቀን 1879 ዐረፈ። ይህ ጽሑፍ ለእርሱ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በንግሥት ቪክቶርያ ተቀመጠለት/ ይላል። በመጨረሻም ልብን የሚነካ ጥቅስ ሠፍሯል I was stranger and ye took me in. ከጥቅሱ ሥርም የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕል ይገኛል።

ዝም ብዬ ፈዝዤ አየው ነበር። በማያውቀው ሀገር፣ አባቱ እና እናቱ ሞተውበት፣ በልጅነት እድሜው እንዴት ይሆን ያሳለፈው? ምን ይሆን የተሰማው? እርሱ ትናንት ያለ ፍላጎቱ ወደ መጣባት ሀገር ዛሬ የርሱ ወገኖች በፍላጎታቸው በረሃ እና ባሕር እያቋረጡ እንደሚመጡ ያውቅ ይሆን?

እነዚህ ሁሉ በጎሊናዬ ሲያልፉ አስጎብኛችን «የእርሱ አባት ከጦርነቱ በፊት ራሳቸውን መግደላቸውን ዐውቃለሁ፣ የት ነው የተቀበሩት?» አሉና ጠየቁኝ። «መቅደላ በሚባል ተራራ ላይ ነው» አልኩና መለስኩላቸው። «ምናልባት እዚያ ቢሆን ኖሮ በሀገሩ ባሕል የተሻለ ክብር ያገኝ ይሆናል» አሉና አንድ አስደንጋጭ ጥያቄ አመጡብኝ «እንዴት ነው መቅደላ) መቼም መቃብሩን በሚገባ እንደ ያዛችሁት ተስፋ አደርጋለሁ፣ እዚህ ድረስ ዓለማየሁን ለማየት ከመጣችሁ

እዚያ ያለውንማ በጣም ታከብሩታላችሁ ማለት ነው፡፡ እዚህ የሚመጡ አንዳንድ ጎብኝዎች ይጠይቁናል፤ እስኪ ስለ መቅደላ ንገሩኝ?»

ነገር መጣ፡፡

ምን ብዬ ልንገራቸው፡፡ መቅደላ የቱሪስት መዳረሻ አይደለም ልበላቸው? የልጃቸው መቃብር በባዕድ ሀገር ያገኘውን ክብር አባቱ በሀገሩ አላገኘውም ልበላቸው? መቅደላ ላይ ሙዝየም የለም፣ የሚጎበኝ ነገር የለንም፣ የአባቱም መቃብር እንደ እንግዳ መቃብር ያለ ነው ልበላቸው? ሴፓስቶፖል የመቅደላ አፈር ተሸከመው እንጂ በሥነ ሥርዓት አልተቀመጠም ልበላቸው? ዓለማየሁንስ መቃብሩን ሰው ይጎበኘዋል መቅደላ የአባቱ መቃብር ግን ተረስቷል ልበላቸው? በቴዎድሮስ መቃብር ላይ የተጻፈ ታሪክ፣ የተሠራ ሙዝየም፣ የተሰበሰበ ቅርስ የለም ልበላቸው? ጦርነት ካልመጣብን ቴዎድሮስ ትዝ አይለንም ልበላቸው? ራሳቸውን በጀግንነት መሠዋታቸውን እንጂ ሀገር ለማሳደግ፣ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም፣ ራስን ለመቻል፣ ከጥገኛነት ለመውጣት፣ ሀገርን ለማደራጀት የሠሩት ሥራ ትዝ ብሎን አያውቅም ልበላቸው? ከልማታቸውመ ከጥፋቸውመ ገና ትምህርት አልወሰድንም ልበላቸው? አዲሱ ትውልድ ከእርሳቸው የወረሰው ቁንዳላቸውን ብቻ ነው ልበላቸው?

ቴዎድሮስ የተዋጉት ከእንግሊዞች ጋር ነው፡፡ የተዋጓቸው እንግሊዞች ልጃቸውን በሥርዓት ይዘው፣ ሲሞት በሥርዓት ቀበሩት፣ ንግሥት ቪክቶርያም መታሰቢያ አደረገችለት፤ ዐፄ ቴዎድሮስ የሞቱላት፣ የተዋጉላት፣ ኢትዮጵያ ግን ረስታቸዋለች ልበላቸው? መልሱን አልነገርኳቸውም፤ ዝም አልኳቸው፡፡

«በል ከዚህ እንደወጣህ ወደ ኩዊንስ ጌት እና ኬሲንግተን ጎዳን ሂድና ከንጉሣችሁ ጋር የተዋጋውን ሰው ታገኘዋለህ» አሉኝ፡፡ እንዳሉኝም ከኢንተርኔት ላይ አድራሻውን አውጥተን ወደዚያው በረርን፡፡

ቦታው ላይ ስንደርስ በፊረስ ላይ እንደሚጋልብ ሆኖ የታነፀ ሐውልት አገኘን፡፡ ከሐውልቱ ሥር የተጻፈውን ጽሑፍ ለማየት ዝቅ ስል በእንግሊዝኛ «ጀኔራል ናፒዬሪ፣ የመቅደላው ጌታ Lord of Magdala´ ይላል፡፡ ይህ መዓርግ የናፒየሪ የልጅ ልጆች ሁሉ የሚጠሩበት መዓርግ ሆኗል፡፡ ልቤ በጎዘን ተመታ፡፡ «የመቅደላው ጌታ» መቅደላ ላይ ተኝቷል፡፡ መቅደላን የመረጣት፣ ያከበራት እና ታሪክ የሠራባት የመቅደላው ጌታ እንደ ተራ ሰው መቅደላ ላይ ተኝቷል፡ ፡ እንግሊዞች ግን ሌላ የመቅደላ ጌታ ሰይመው እርሱንም አከብረው፤ ለልጅ ልጆቹም መጠርያውን ሰጥተው ሐውልቱን መሐል ለንደን ላይ አቁመውለታል፡፡ አዲስ አበባ ግን የመቅደላው ጌታ ሐውልቱ የላትም፡፡

13. ባልን ማን ፈጠረው?

«ባል ሚስቱን በሥራ ቢረዳት ፣በቤት ውስጥ ቢተጋገዙ፣ የባል ትምክህት ቀርቶ የሚስት ተጨቋኝነት ተወግዶ በእኩልነት ቢኖሩ፣ ባሎች በልጆች አስተዳደግ፣ በማዕድ ቤት አስተዳደር፣ የቤት ቀለብ በመግዛት ቢሳተፉ» እየተባለ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሃሳቦች ይሰነዘራሉ፣ ትምህርቶች ይሰጣሉ፣ ቅስቀሳዎች ይደረጋሉ፡፡ ሃሳቦቹ መልካሞች ቢሆኑም እጅግ ግን የዘገዩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሃሳቦች የሚነሡትና እንዲተገበሩም የሚፈለጉት አብዛኞቹን ሊለወጡበት በማይችሉበት፣ ያለበለዚያም ጥቂት ለውጦችን ብቻ በሚያመጡበት ደረጃ ላይ ከደረሱ በኋላ ነውና፡፡

ባልነት ማኅበረሰቡ ሲሠራው የሦስት ነገሮች ድምር ውጤት አድርጎ ነው፡፡ የወንዴነት፣ የወንድነት እና የአባ ወራነት፡፡ «ወንዴነት» በተፈጥሮ የሚገኝ ጸታ ነው፡፡ ወንድነት እና አባ ወራነት ግን ማኅበረሰቡ የሚፈጥራቸው ናቸው፡፡ ለዚህም ነው «ወንዴን ፈጣሪ ባልን ግን ማኅበረሰቡ ይፈጥረዋል» የሚባለው፡፡ በኛ ማኅበረሰብ ዘንድ «ወንድነት» የተፈጥሮ ጸታን ብቻ አያመለክትም፡፡ ወንድነት ጀግንነትን፣ አሸናፊነትን እና ታላቅነትን የሚያመለክትም ነገር ነው፡፡

ወግድልኝ ድኻ ወግድልኝ ቅኔ

ወንዶች ከዋሉበት እውላለሁ እኔ - በሚለው የአርበኛነት ግጥምም «ወንዶች» ብሎ የጠራቸው «ጀግኖች»ን ነው፡፡

«ወንድ» የሚለው ስያሜ ለሴቶችም ሊሰጥ የሚችል ቅጽል ነው «እርሷ እኮ ወንድ ናት» እንዲሉ፡፡ እንዲያም ቢሆን እንኳን ማኅበረሰባችን ይህንን ስያሜ ለሁለቱ ጸታዎች የሚሰጥበት መንገድ ይለያያል፡፡ ማኅበረሰባችን «ወንድነት» ከወንዴነት ጋር የተያያዘ እንዲሆን ይፈልጋል፣ ይጠብቃል፡፡ ወንድነትን ከሴቴነት ጋር አብሮ እንዲኖር ግን አይጠብቅም፡፡ ለዚህ ነው «ወንዱ ልጅ እንደ ሴት አለቀሰ» በማለት ማልቀስ ከወንድ የማይጠበቅ፣ ሴት ብታደርገው ግን የማያስገርም ነገር አድርጎ የሚገልጠው፡፡ በሌላም በኩል በሴቷ ዘንድ የጀግንነት ሥራ የታየባት እንደሆነ በዚያው በሴትነትዋ እንደማድነቅ

ጉድ በል ጃን አሞራ ተደነቅ ስሜን

ሴቷ ልጅ እንደ ወንድ ኑዳቸው ነጩጌ በማለት በጣልያን ጦርነት ጊዜ የገጠመው ለዚህ ነው፡፡ ይህም ከወንዶቹ የሚጠበቀውን ሴቷ ልጅ መሥራቷን ለማመልከት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ «ሴቴነት» እና «ሴትነትም» እንዲሁ ይለያያሉ፡፡ «ሴቴነት» ጸታ ነው፡፡ «ሴትነት» ግን ማኅበረሰቡ የሚፈጥረው ገጸ ባሕርይ ነው፡፡ ሴትነትን ከሴቴ ጸታ ጋር ብቻ ሳይሆን «ከመሸነፍ፣ ከማልቀስ፣ ከመፍራት እና ጠባየ ስስ ከመሆን» ጋር ማኅበረሰቡ አያይ ዞታል፡፡ ይህንኑ በባሰ ሁኔታ ለመግለጥም «ሴታ ሴት» የሚል ቃል ጨምሮለታል፡፡ ሴቶቹ እንኳን ራሳቸው ከወንዶቹ ጋር ሲጣሉ ድፍረት በተሞላው ልብ «ቀሚስ ብለብስ ሴት እንዳል መስልህ» እያሉ ይናገራሉ፡፡ «ፊሪ እንዳልመስልህ» ማለታቸው ነው፡፡ ችግሩ ግን «ሴትነት» ከሴቴዎች የሚጠበቅ፣ ቢከሰት የማይገርም ነገር ተደርጎ ሲወሰድ፣ በተቃራኒው ከወንዴዎች የማይጠበቅ እና የሚያሳፍር ነገር ተደርጎ መወሰዱ ነው፡፡

ሴትነት እና ወንድነት ማኅበረሰባችን ለሁለቱ ጾታዎች ያለውን አመለካከት፣ ደረጃ እና ከሁለቱ ጾታዎች የሚጠበቀውን ነገር የሚያመለክቱ ራሱ ማኅበረሰባችን የፈጠራቸው ነገሮች ናቸው። በዚህም የተነሣ አብዛኛውን ጊዜ «ባልነት» የሦስት ነገሮች ድምር ውጤት እንዲሆን አድርጎ ማኅበረሰቡ ቀምሮ ሠርቶታል። ወንዴነት፣ወንድነት እና አባ ወራነት።

ማኅበረሰቡ «ወንድ» የተባለውን ገጸ ባሕርይ ሲቀርጸው አደባባይ ከመዋል ጋር፣ ገድሎ ከመፎከር ጋር፣ ኃይልን ከመጠቀም ጋር፣ ከአሸናፊነት ጋር ነው። «ሴትነት»ን ደግሞ ቤት ውስጥ ከመዋል፣ ከተሸናፊነት፣ ከማጀት እና ከጭምትነት ጋር አያይዞታል። በዚህም ምክንያት ማኅበረሰባችን ለወንዶች ይሰጠው የነበረውን ቦታ ያህል ለሴቶች ሊሰጥ አልቻለም። ሴት ስትወለድ አንድ ጊዜ ወንድ ሲወለድ ሦስት ጊዜ እልል የሚለው ወንዴነትን ከጀግንነት ጋር ስለሚያያይዘው ነው።

ለብዙ ዘመናት ወንድ ነገሥታት ከሚስቶቻቸው ጋር ሲነግሡ እንዳልኖሩ ሁሉ እቴጌ ዘውዲቱ በነገሡ ጊዜ ባላቸው አብረው እንዳይነግሡ የተደረገው ከዚሁ የማኅበረሰቡ አመለካከት የተነሣ ነው። ባላቸው ከነገሡ መንግሥቱን ይቀናቀናሉ፣ በኋላም የፈለግነውን ለማስደረግ እምቢ ብለው ከንዳቸውን ያሳያሉ ተብሎ ተፈርቶ። ማኅበረሰቡ እንዲህ አድርጎ የቀረጻቸውን «ወንድ» እና «ሴት» የሚባሉ ሁለት ገጸ ባሕርያትን ማኅበረሰባዊ ሚና በተመለከተ በተረቶቹ፣ በግጥሞቹ፣ በአባባሎቹ፣ በስያሜዎቹ፣ በንግግሮቹ ሁሉ ይበልጥ ያጠነክራቸዋል። አሁን እንኳን ሠለጠነ በሚባለው ዘመን ትንንሽ ዕቃዎችን «አንቺ» ብለን ስንጠራ ትልልቅ ዕቃዎችን ግን «አንተ» ብለን የምንጠራቸው ይሄው በየተረቱ እና በየአፈ ታሪኩ፣ በየሠርጉ እና ልቅሶው እየሰማን ስንቀረጸው የኖርነው ነገር አልለቀን ብሎ ነው። ስለ ሴቶች መብት የተቋቋሙ ብዙዎቹ ማኅበራት እና ድርጅቶች እንኳን ድርጅታቸውን «አንተ» ብለው እንጂ «አንቺ» ብለው የማይጠሯት ይሄው የማኅበረሰቡ ትርጓሜ ውስጣቸው በማያነቃንቁት መሠረት ላይ ስለተገነባ ነው።

ባልን መጀመርያ የሚፈጥሩት ራሳቸው እናቶች ናቸው። «ወንድ ነህ» እያሉ ከሚሰጡት ማሞካሻ ጀምሮ ወደ ማጀታቸው የተጠጋውን ልጅ «ሴታ ሴት፣ እዚህ ጓዳ ውስጥ ምን ያርመጠምጥሃል» እያሉ እስከማባረር ድረስ የባልነቱን ተግባር ከልጅነቱ ያስለምዱታል። ሴቶች ልጆቻቸውን የቤት ሞያ ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት ያህል ለወንዶች ልጆቻቸው ያንን ለማድረግ አያስቡም። ሲያስቡ እንኳን «አንተ ወጡን ሠርተህ ሚስትህ ምን ልትሠራ ነው?» እያሉ ከመገረም ጋር ነው። አንዳንድ ጊዜ ማኅበረሰቡም ቢሆን የአንዳንድ እናቶችን ተግባር ይቃወመዋል። «ልጁን የቤት ሠራተኛ አድርጋ አስቀረችው፤ እንግዲህ ይሄ ልጅ ሚስት ነው ባል የሚያገባው» ይላቸዋል። ብዙዎቻችን የምናውቀው

ይወለድ እና እነከፍ እንከፉ

ጋን ይሸከማል ከነድፍድፉ የሚለው ሥነ ቃል እኮ ጀግንነትን የሚያበረታታ ይመስላል እንጂ መልእክቱ ሌላ ነው። እንከፍ እንከፉ ከተወለደ ጋንን ከነድፍድፉ ይሸከማል ነው የሚለው። ጋንን ከነ ድፍድፉ የሚሸከም «እንከፍ» ለምን ይሆናል። ጀግናውስ ለምን አይሸከምም? ይህንን ነገር ሴቶቹ ሲያደርጉት የሚተች የለም። ወንዶቹ ሲያደርጉት ግን እንደ እንከፍነት ይወሰዳል። ይህንን እየሰማ ያደገ ልጅ ታድያ «እህትህን ውኃ አሸክማት» ቢባል እንዴት እሺ ይላል።

በአንድ ወቅት ሁለት ባል እና ሚስቶች ተጣሉና ሽምግልና ተቀመጥን። ከኔ ጋር ሽማግሌ ሆነው የተቀመጡት ሰዎች በእድሜ የእኔን እጥፍ እና ከዚያ በላይ የሚሆኑ ነበሩ። እኔ ወደ ሽምግልናው የገባሁት ቤተሰቡን በሌላ ሁኔታ

ስለማውቅ ነበር፡፡ የጠቡ መነሻ ባልየው ከሚስታቸው ውጭ ሌሎች ልጆች እንዳሏቸው መታወቁ ነበር፡፡ ሚስት በዚህ ዓይነት ልጉተማ መን አንችልም፡፡ መጀመርያ ነገር ትዳሬን አፍርሷል፣ ሁለተኛም ዋሽቶኛል ብለው ለሽማግ ሌዎቹ አቀረቡ፡፡ ወደ ሰባ ዓመት የተጠጉት አንደኛው ሽማግሌ የተናገሩት ነገር ምንጊዜም አይረሳኝም፡፡ «ወንድ ልጅ ሌላ ቦታ አይሂድ ማለት'ኮ ወንድ ልጅ አይሸና ማለት ነው» የሚል ምሳሌ አመጡ፡፡ ከሁለት ሰዎች በቀር ሌሎቹ አምስት ሽማግሌዎች ይህንኑ ሃሳብ አጠናከሩት፡፡ ማኅበረሰቡ ለወንዶች እዚህ ድረስ መብት ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ይህንን እየሰማ ያደገ ልጅ ነገ ምን ዓይነት ባል ሊሆን ይችላል?

ጥሩ ወንድ በሌለበት ጥሩ ባል፣ጥሩ ሴት በሌለበትም ጥሩ ሚስት መመኘት የዋሕነት ነው፡፡ ጥሩ ሴት ማለትኮ መልካም ሥነ ምግባር ያላት፣ ክብሯን የጠበቀች፣ሞያ የምትችል እና መልከ ቀና የሆነች ማለት ብቻ አይደለም፡፡ የሴትነት ሚናን በሚገባ የምታወቅ መሆንም አለባት፡፡ እርሷ ራስዋ ማኅበረሰቡ የቀረጸውን የተሳሳተ ገጸ ባሕርይ የተሸከመች እና ችግሩም የማይገባት ከሆነች «ጥሩ ሴት» አፈራን ማለት አንችልም፡፡ ጥሩ ወንድም እንዲሁ፡፡ መልከና ቁመና፣ጠባይ እና አመል ብቻ ጥሩ አያሰኝም፡፡ ወንድነትን ማኅበረሰቡ ስለ ወንዶች ከፈጠራቸው የተሳሳቱ አመለካከቶች ጋር ደባልቆ የሚቀበል፣የችግሩ ፈጣሪ ባይሆን እንኳን የችግሩ ሰለባ ከሆነ «መልካም ወንድ» ፈጠርን ማለት አይቻልም

ባልነት በወንድነት ውስጥ ያድግና በጋብቻ ጊዜ ይገለጣል እንጂ ባልነት በጋብቻ ቀን አይጀ መርም፡፡ ከተበላሸ ወተት የተስተካከለ እርጎ አይገኝም፡፡ እርጎውኮ በወተቱ ውስጥ ነበረ፡፡ እርጎው እርጎ ተብሎ ከመጠራቱ በፊት ወተት ነበር፡፡ እርጎነት የሚጀመረው ወተትነት ሲጀመር ነው፡፡ እርጎው ጥሩ እንዲሆን የፈለገ ሰው መጀመሪያ መከባከብ ያለበት ወተቱን ነው፡፡ በእኩልነት የሚያምኑ፣ የሥራ ልዩነት የማይፈጥሩ፣ ሳሎኑንም ጓዳውንም የሚያውቁ፣ ሚስቶቻ ቸውን በሁለመናቸው የሚራዱ ባሎችን ከጎረምሶች መካከል መፈለጉ እምብዛም የሚያዋጣ አይመስልም፡፡

ምዕራባውያን ባሎች ከኢትዮጵያውያን በተሻለ የጓዳውን ሥራ ይሠሩታል፡፡ ጓደኞቻቸው ይህንን ቢያውቁ ምንም አይመስላቸውም፡፡ እነርሱም ያንኑ ያደርጉታልና፡፡ ቤት በመዋላቸው ወይንም ጓዳ ጓዳውን በመዋላቸው «ሴታ ሴት» ብሎ የሚሰድባቸው የለም፡፡ ለምን? እነርሱም በጾታ ወንዴዎች ናቸው፡፡ በእኛ ሀገር ካሉት ወንዴዎች ጋር የጾታ ልዩነት የለባቸውም፡፡ ልዩነቱ ማኅበረሰቡ አንድ ዓይነት ሆነው የተፈጠሩትን ወንዴዎች ሁለት ዓይነት አድርጎ እንደገና መፍጠሩ ነው፡፡ ያኛው ማኅበረሰብ «ወንድ» ለሚለው ገጸ ባሕርይ የሰጠው ትርጓሜ ጓዳውንም እንዲጨምር መሆኑ፣ እና የኛ ማኅበረሰብ ጓዳ ጓዳውን መከልከሉ ነው ልዩነቱ፡፡ ለዚህም ነው ባልን ማኅበረሰቡ ይፈጥረዋል የሚባለው፡፡

እዚህም በየጎረቤቶቻችን ቀድሞ የነቃ ቤተሰብ አግኝተው እና የማኅበረሰቡንም ትችት ችለው ባልነትን ለወንድነት ከተሰጠው ትርጉም በተጨማሪ አስፍተው የተቀረጹ ወንዴዎች አሉ፡፡ የሴቶችን ማኅበረሰባዊ ሚና መጋራት የባልነት አንዱ ተግባር አድርገው እንዲወስዱት ሆነው በመቀረጻቸው በጾታ ከሌሎቹ ወንዴዎች አንዱ ቢሆኑም እንኳን ባልነቱ ላይ ግን ሌላ ሆነው መልሰው ተወልደዋል፡፡ ባልን ማኅበረሰብ ይፈጥረዋል ማለት ይህ ነው፡፡

እነዚህን ባሎች ማግኘት የሚቻለው ከዛሬ ሕፃናት ውስጥ ነው፡፡ እነዚህን ባሎች የመፍጠር ሥልጣንም በዛሬው ማኅበረሰብ ጫንቃ ላይ ነው፡፡ ልጆቻችን በሕፃንነታቸው ያልተማሩትን ሥራ በኋላ ከየት ያመጡታል? በልጅነታቸው ያላወቁትን ጓዳ በኋላ የት ያውቁታል? በልጅነታቸው ያልተረከቡትን ኃላፊነት በኋላ ከማን ይቀበሉታል?

14. ገንዳ : (በተለይ ሻማ ሆነው በጨለማ ውስጥ ለሚኖሩ)

አንድ መምህሬ ነበሩ፡፡ ስለ አንድ ጉዳይ ጠይቀናቸው ያብራሩልንና ዘወትር የማት ለወጥ ምክር አለቻቸው፡፡ «ገንዳ እንዳትሆኑ» ይሉናል፡፡ ብዙ ጊዜ እሰማታለሁ እንጂ ለምን ብዬ ጠይቄ አላውቅም ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ምን ማለታቸው እንደሆነ ለማወቅ ፈለግኩና ጠየቅኳቸው፡ «አያችሁ፣ ገንዳ ለከብቱ ሁሉ ያጠጣል እንጂ ለራሱ አይጠጣም፡፡ እንዲያውም ባጠጣ ቁጥር እየጎደለ ሄዶ ጭራሹኑ ይደርቃል፡፡ እናንተም እንደዚያ እንዳትሆኑ» አሉን፡፡ ለብዙዎች ምክር የሚሰጡ ለራሳቸው መካሪ ካጡ፤ ለብዙዎች የደስታ ምንጭ የሆኑ እነርሱ በጎዘን ከሰመጡ፤ ብዙዎችን የሚያዝናኑ እነርሱ ግን ከተደበሩ፤ ለብዙዎች የሀብት ምንጭ የሆኑ እነርሱ ግን በድኅነት ከተቆራመዱ፤ ብዙዎችን ያስተማሩ እነርሱ ዕውቀት ከጎደላቸው፣ብዙዎችን ያስታረቁ እነርሱ ዕርቅ ካጡ፣ ብዙዎችን የመሩ እነርሱ መንገድ ከጠፋባቸው፣ ብዙዎችን ያዳኑ እነርሱ መድኃኒት ካጡገንዳነት ማለት ይሄ አይደል እንዴ፡፡

በካባ ውስጥ ያለን ድንቁርና እና በቡቱቶ ውስጥ ያለን ዕውቀት ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው ይባላል፡፡ መድረክ ላይ ወጥተው፣ ዓይን የሚስበውን እና ልብ የሚማርከውን ልብስ ለብሰው፣ ሕይወትን በቀልድ ቀምመው እኛን በሳቅ የሚያፈነዱን ሰዎች በእውነት የእነርሱ ሕይወት ትስቃለች? በኪናዊ ሥራዎቻቸው እኛ የገዛ ሕይወታችንን መለስ ብለን እንድናያት ያደረጉን እነዚህ ሰዎች ሕይወታቸውን መለስ ብለው የሚያዩበት መነጽር አላቸው?

የትዳርን መልካምነት ፤የፍቅርን ጣፋጭነት ፣የቤተሰብን ደስታ፣ የማኅበራዊ ኑሮን ርካታ በዜማዎቻቸው ከሸነው ያቀነቀኑልን ወገኖች ትዳራቸውን እና የፍቅር ሕይወታቸውን፣ ቤተሰባቸውን እና ማኅበራዊ ኑሯቸውን ሲገመግሙት ያቀነቀኑለትን ያህል ሆኖ ያገኙታል? ወይስ ለዜማው ስኬት፣ ለገበያው ሥምረት፣ ለአድማጩ ሐሴት ሲሉ ብቻ ነው ያቀነቀኑት? በፊልሞቻቸውም ይሁን በመድረክ ትወናቸው ኅብረተሰባችን ምቀኝነትን እና ክፋትን፣ ቅናትን እና ስግብግብነትን፣ ቂምን እና በቀልን፣ መሠሪነትን እና ተንኮለኛነትን እንዲያርቅ የሚያስተምሩን እና የሚያሳዩን ወገኖቻችን መልእክቱ ለተመልካቹ ብቻ ነው ወይንስ እነርሱንም ይመለ ከታል? መልእክቱ ለመድረክ ብቻ ነው ወይስ ወደ ቤታቸውም ይሄዳል? ጉዳዩ የኅብረተሰቡ ብቻ ነው ወይንስ እነርሱንም ይዳስሳል? ለመሆኑ እርስ በርሳቸው ደኅና ናቸው?

«ተማር ልጄ» ብለው እያዜሙ እነርሱ ግን «ትምህርት እስከ ስድስት፣ ዘመድ እስከ አክስት» የሚሉ ከሆነ፤ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስለ አንድነት እየሰበኩ እነርሱ ግን ግላዊነት የሚያጠቃቸው ከሆነ፤ ስለ ፍቅር እያቀነቀኑ እነርሱ ግን የትዳራቸውን ነገር ውኃ ውኃ የሚያደርጉት ከሆነ፤ አንድ ሰው ለአንድ ነው ካሉን በኋላ አንድ ለአሥር የሚመሩ ከሆነ፤ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ እያስተማሩ፣ በዚህ እና በዚያ መንገድ ትያዛላችሁ ብለው እየሰበኩ፣ እነርሱ ግን «አንቺው ታመጭው ፣አንቺው ትሮጭው» እንደ ሚባለው ምክሩን ለራሳቸው የማይጠቀሙበት ከሆነ ከዚህ በላይ ገንዳነት ምን አለ? ሌሎች ሰዎች ሀብታቸውን ለሀገር ልማት እንዲያውሉት መንገር ብቻ ነው እንዴ፣ እኛስ ሀብታችንን የትም ከምንረጨው ለምን መሥመር አናስይዘውም፤ ሌሎች አንዳች ነገር ሲያስመርቁ ተገኝተን ምረቃውን እንደምናሞቀው ሁሉ የራሳችንን ነገርስ ለምን አናስመርቅም፤ ነው ወይስ ከምሽት ክበብ እና ከክትፎ ቤት በላይ ማቋቋም አንችልም? የሕግ አማካሪ፣ የቢዝነስ አማካሪ፣ የሂሳብ ባለሞያ፣ የሞያ አማካሪ እንዳይኖረን ያገደው የትኛው ሕግ ነው?

«አይሆንም እንጂ ቢሆንማ፣ ሽርሽር ወደ ጅማ» የሚል አንድ ሠርግ ላይ ሰምቻለሁ፡፡ አይሆንም እንጂ ቢሆንማ እኛም ሞያችንን በዕወቀት ብንደግፈው፣ ለሞያችን እና ለዕድገታችን የሚሆኑ ትምህርቶችን ከፍለን ተምረን ራሳችንም መሥመራችንን ብናው ቀው ጥሩ ነበር፡፡ ዲፕሎማ እና ዲግሪኮ ለመቀጠር ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ የተማሩትን ቀጥረን በዘመናዊ መንገድ ሕይወታችንን ብንመራ መልካም ነበር፡፡ «አይሆ ንም እንጂ ቢሆንማ» አሉ፡፡ ከልጆቻችን ጋር ስለ ትምህርታቸው ለመወያየት፣ ትምህርት ቤትም ሄዶ የልጆችን ነገር ለመጠየቅ፣ ወደ ውጭ ወጣ ሲሉ በጣት ከማውራት ለመዳን፣ እኛም ዐውቀናል ጉድጓድ ምሰናልም ለማለት፤ መማርን የመሰለ ነገር የለም፡፡ ብዙ ሰዎች ሊያደንቁን ይችላሉ፣ ሊወደን የሚችል ግን አንድ ሰው ወይንም አንዲት ሴት ብቻ ናት፤ በብዙ ቦታዎች ልንጋበዝ እንችላለን፣ ሊኖረን የሚችለው ትዳር ግን አንድ ብቻ ነው፤ ፊርማችንን ብዙዎች ይፈልጉት ይሆናል፤ እውነተኛ ፍቅራችንን እና እኛነታችንን የሚፈልጉት ግን ጥቂቶች ናቸው፤ ከኛ አንዳች ነገር መስማት የሚፈልጉ አያሌዎች ናቸው፤ ለኛ ጥቂት ነገር ሊነግሩን የሚችሉ ግን በጣት ይቆጠራሉ፤

ከኛ የሚፈልጉ አሉ፤ እኛን የሚፈልጉ መኖራቸው ግን ያጠራጥራል፤ በኛ የሚጠቀሙ ሞልተዋል፣ እነዚያ ሁሉ ግን እኛን ይጠቅማሉ ማለት አይደለም፤ ዝና ለተወሰነ ጊዜ ነው፣ ሕይወት ግን እስከ ሞት ድረስ ናት፤ መድረክ ላይ የሚያጨበጭቡልን እልፍ አእላፋት ናቸው፣ ከመድረክ ስንጠፋ የሚፈልጉን ግን እጅግ በጣም ጥቂት፤ ስንስቅ የሚስቁ አናጣም፤ ስናለቅስ ዕንባችንን የሚያብሱ ማግኘት ግን ይቸግራል? ሞያችንን የምናካፍለው ቁጥሩ ብዙ ነው፣ ችግራችንን የምናካፍለው ግን የት ይገኛል?
አውሮፕላን አገልግሎቱን በሚገባ ለመስጠት ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉታል፡፡ ሊነሣበት እና ሊያርፍበት የሚችል አውሮፕላን ማረፊያ እና ሊበርበት የሚችል አየር፡፡ በቴክኖሎጂው ምጥቀት የተነሣ በሰዓት የፈለገውን ያህል ኪሎ ሜትር ቢበርም፤ ምቾቱ የተጠበቀ፣ ደረጃው የላቀ ቢሆንም፤ የቱንም ያህል ወደ ላይ እንደ ንሥር ቢነጠቅም፤ መነሻ እና ማረፊያ ከሌለው ግን ሄዶ፣ ሄዶ ነዳጁ ሲያልቅ መከስከሱ አይቀርም፡፡ በዜማቸው፣ በኪነ ጥበብ ውጤቶቻቸው፣ በትወናቸው፣ በሀብታቸው፣ በፖለቲካ ተሳትፏቸው፣ በሊቅነታቸው ወዘተ ታዋቂ የሆኑ እና አያሌዎችን ከኋላቸው ወይንም በዙሪያቸው ለማሰለፍ የበቁ ሰዎች፣ የቱንም ያህል ወደ ላይ እና ወደ ጎን በክብር እና በዝና፣ በአድናቆት እና በምስጋና፣ በሀብት እና በንብረት ቢመጥቁም፤ የቱንም ያህል በሕዝቡ ተወዳጅ እና ተፈቃጅ ቢሆኑም፤ እንደ አውሮፕላኑ ማረፊያ እና መነሻ ከሌላቸው ግን አንድ ቀን እነርሱም መከስከሳቸው የማይቀር ነው፡፡

ብዙ ሺዎች ሲያደንቁህ ከነበረበት መድረክ ወርደህ ቤትህ ስትገባ ምን ይጠብቅሃል፤ ቤትህ እንደ መድረኩ ይሞቃል? ብዙዎችን ካዝናናህበት የሳቅ ባሕር ወጥተህ ብቻህን ስትሆን ነፍስህ ምን ትልሃለች፤ አያሌዎች የተጠቀሙበትን ጉዳይ አቅርበህ ራስክን ስታየው ምንድን ነህ ይልሃል? ይህ ነው ከባዱ ጥያቄ፡፡
አንዳንድ ጊዜ ለዚህች ሀገር ባለውለታ የሆኑ የሥነ ጥበብ እና የኪነ ጥበብ ሰዎች ታመው መታከሚያ፤ ተቸግረው መኖርያ፤ ዐርፈው መቀበርያ እያጡ ሲለመንላቸው ሳይ እኒያ መምህር የተናገሩት ነገር ትዝ ይለኛል፡፡ አነሰም በዛም በወቅቱ ጥቂት ነገር አግኝተው ይሆናል፤ በወቅቱ መሬት ለማግኘት፣ ቤት ለመሥራት፣ ጥሪት ለመቋጠር ምቹ የነበሩ ሁኔታዎች እነርሱንም የሚመለከቱ ነበሩ፤ በወቅቱ አያሌ አድናቂዎች እና እነርሱ ካልመጡ ሞተን እንገኛለን የሚሉ ተመልካቾች ነበሯቸው፡፡ ታድያ ለምን እዚህ ደረጃ ላይ ወደቁ?
እኔ እንደሚመስለኝ የእኛ እንጂ የራሳቸው እንዲሆኑ ስላልረዳናቸው ነው፡፡ አጨበጨብንላቸው፣ አቋጨንላቸው፣ አቆላመጥናቸው፣ ጋበዝናቸው፣ እፍ እፍ አልንላቸው፣ አበድን ላቸው፤ ራሳቸውን ሆነው ማረፊያ ኖሯቸው እንዲኖሩ ግን አላደረግናቸውም፡፡

በየመንደራችን ጉልት ቸርችረው፣ ጠላ ጠምቀው፣ እንጨት ሰብረው፣ የዕለት ሥራ ተቀጥረው ሕይወትን ይገፉ የነበሩ ወገኖች፣ ቢያንስ የቀበሌ ቤት ለመከራየት፣ ዕድር እና ዕቁብ ለመግባት፣ ልጆቻቸውን አስተምረው የተሻለ ቦታ ለማድረስ፣ የሚያከራዩት ሰርቢስ ቤት ለመሥራት ሞክረዋል፤ «የሕዝብ ልጆች» እየተባሉ የኖሩ የኪነ ጥበብ እና የሥነ ጥበብ ሰዎች ግን፣ የሕዝብ ብቻ ሆነው የራሳቸው ሳይሆኑ ቀሩ፡፡ «የሁሉም የሆነ የማንም አይሆንም» ይባል የለ፡፡ እንደ አውሮፕላኑ መነሻ እና ማረፊያ እንዲኖራቸው ማድረግ ነበረብን፡፡ መምከር ነበረብን፡፡ ማስጨነቅ ነበረብን፡፡ እነርሱም ማሰብ ነበረባቸው፡፡ አርቲስት ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ታዋቂ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ደራሲ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ጋዜጠኛ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ፖለቲከኛ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፤ ነጋዴ ከመሆናችሁ በፊት ሰው ናችሁ፡፡ ሰው ባትሆኑ ኖሮ እነዚህን ነገሮች ሁሉ መሆን አትችሉም ነበር፡፡ ሰው መሆናችሁ ሲያቆም ደግሞ እነዚህ ሁሉ ነገሮች አብረው ያቆማሉ፡፡ ስለዚህም ዝናን እና ታዋቂነትን፣ ክብርን እና ሽልማትን፣ ገንዘብን እና ሀብትን፣አድናቆትን እና ተወዳጅነትን ስላገኛችሁበት ነገር ብቻ ሳይሆን ሰው ስለሆናችሁበትም ነገር ማሰብ አለባችሁ፡፡

አገር መውደድ ቤተሰብን እና ትዳርን ከመውደድ፣ ሕዝብን ማስተማር ራስን ከማስተማር፣ ሌላውን ማዝናናት የትዳር ጓደኛን ከማዝናናት፣ ተወዳጅነት በገዛ ልጆቻችን ከመወደድ፣ መደነቅ በትዳር አጋር ከመደነቅ፣ መከበር በመንደራችን ከመከበር፣ ደስተ ኛነት በግል ሕይወት ከሚገኝ ርካታ መጀመር አለበት፡፡ አውሮፕላን ማረፊያውን ለቅቀን አየር ላይ ብቻ የምንንሳፈፍ ከሆነ መከስከሳችን አይቀሬ ነው፡፡

ጊዜ ስለሌለን፤ ኪነ ጥበብ የሕዝብ ስለሆነች፣ ሕዝቡን በየአጋጣሚው ማገልገል ስላለብን፣ ሥራችን ሌሊትም ቀንም ስለሆነ፣ ሞያችን አንዳንድ ጊዜ ለብቻ መሆንን ስለሚፈልግ፣ ወደ ውጭ ሀገር በብዛት ስለምንወጣ፣ እዚህም እዚያም ስለምንፈለግ፣ እያልን የምንተወው ቤተሰብ፣ የምናሳዝናቸው የትዳር አጋሮቻችን እና ልጆቻችን በኋላ ዋጋ ያስከፍሉናል፡፡ ጊዜ ላይኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሰው ነንና ለቤተሰብ ጊዜ መስጠት የግድ ያስፈልገናል፡፡ ቤተሰብ የመነሻ እና የማረፊያ ሜዳችን ነው፡፡ አውሮፕላኑ ቢበላሽ ወርዶ የሚሠራው ማረፊያው ላይ ነው፡፡ ማረፊያው ከተበላሸ ምን መሆን ይችላል? «ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡታል፣ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡታል» ይባል የለ! ሕዝብ አይጨበጥም፡፡ ሕዝብ የሚባል መዋቅርም የለም፡፡ ሕዝብ ተቆጥሮ በትክክል አይታወቅም፡፡ ስለ ሕዝብም አፍን ሞልቶ ትክክለኛውን ስሜት መናገር አይቻልም፡፡ ሕዝብ የሚባል ተቋምም በሕግ ዘንድ የለም፡፡ ቤተሰብ ግን ይጨበጣል፡፡ ይቆጠራል፡፡ አፍን ሞልቶ ሊናገሩለትም ይቻላል፡፡ በሕግም የታወቀ ትርጉም እና ጥበቃ አለው፡፡ እናም የማይጨበጠው የሕዝብ ከመሆናችን በፊት፣ የሚጨበጠው የቤተሰባችን እንሁን፡፡

የጂአግራፊ መምህራችን ምድር ሁለት ዓይነት ዙረት አላት ብለውናል፡፡ በፀሐይ ዙርያ እና በራስዋ ዛቢያ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ተጠባብቀው ይኖራሉ፡፡ እኛም በፀሐይ ዙርያ ብቻ ሳይሆን እንደ ምድር በራሳችንም ዙርያ እንዙር፡፡ እነዚህ ሁለቱ ተጠባብቀው ይኑሩ፡፡

ለምንድነው ቢሉ፤ ገንዳ እንዳንሆን፡፡

15. ፊደል እያለው የማያነብ ማነው?

አንድ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የዶክትሬት ዲግሪዋን ጥናት ከምትሠራ አንዲት የውጭ ሀገር ተማሪ ጋር ተገናኘን፡፡ ጥናትዋን የምትሠራው በጎንደር ዘመን በተሳሉ የቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች ላይ ነበር፡፡ ለመገናኘታችን ምክንያት የሆነውም በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ መረጃዎችን እንድሰጣት ፈልጋ ነው፡፡

ወደ እኔ የጠቆሟት ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን እንደምጽፍ ነግረዋት ነበር፡፡ ምን ያህል መጻሕፍት እና መጣጥፎች እንደ ጻፍኩ ጠይቃኝ ነገርኳት፡፡ ካዳመጠችኝ በኋላ ገርሟት የተናገረቸውን ግን እስከ መቼውም አልረሳውም፡፡ «እነዚህን ሁሉ ጽፈህ ግን የሚያነብብ ታገኛለህ?» አለችኝ፡፡ የግራም የቀኝም መመለስ ቸግሮኝ ዝም አልኩ፡፡ «ይቅርታ ወደዚህ ሀገር ስመጣ ጥሩ ያልሆነ ነገር ስለሰማሁ ነው» ብላ አስተያየቴን በሚጠብቅ መልኩ አየችኝ፡፡ «ምን ሰማሽ?» አልኩ ድከም ባለ ድምፅ፡፡ በውስጤ ግን «ምን ሰማሽ ደግሞ» ነበር ያልኳት፡፡ «ኢትዮጵያውያን ከንባቡ ይልቅ ወደ ንግግሩ ታደላላችሁ ይባላል፡፡ እንዲያውም አንድ ጓደኛዬ ገንዘብሽ እንዳይሰረቅ ከፈለግሽ መጽሐፍ ውስጥ አስቀምጭው ብላኛለች» ብላ ፈገግ አለች፡፡ እኔም ፈገግ አልኩ፡፡ የርሷ የለበጣ የእኔ ግን የማሽላ ፈገግታ ነበር፡፡ «ለምንድን ነው መጽሐፍ ውስጥ ደብቂው ያሉሽ?» አልኳት፤ ከእርሷ መስማት ፈልጌ፡፡ «ማንበብ ስለማይወዱ ገልጠው አያገኙትም ብለው ነዋ»

ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሰማንያ ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ አለ፡፡ ቢያንስ ከዚህ ውስጥ አሥር ሚሊዮኑ ማንበብ ቢችል፡ ፡ አራት ሚሊዮኑ ደግሞ የሚነበብ ነገር የመግዛት ዐቅም ቢኖረው ብለን እስኪ እንነሣ፡፡ በሳምንት የሚታተሙት ጋዜጦች ሁሉም ተደምረው መቶ ሺ አይሞሉም፡፡ ከመማርያ መጻሕፍት ውጭ የሚታተሙ መጻሕፍት ቢበዛ በአማካይ አሥር ሺ ኮፒ ናቸው፡፡ በሳምንት ውስጥ የሚታተሙት መጽሔቶች ቁጥር ተደምሮ ሠላሳ ሺ አይሞላም፡፡ ለምንድን ነው? ለመሆኑ በሳምንት ውስጥ ለሻሂ፣ ለቡና እና ለማኪያቶ ከምናወጣውና ለመጻሕፍት፣ ለመጽሔቶች ወይንም ለጋዜጦች መግዣ ከምናወጣው የቱ ይበልጣል?

አንድ ሰው ሠላሳ ዓመት እስኪሞላው ድረስ ሠላሳ መጻሕፍትን እንኳን አንብቦ ይሆን? በቤታችን ውስጥ ከብርጭቆው፣ ከስኒው እና ከመጻሕፍቱ ቁጥር የትኛው ይበልጥ ይሆን? ስንቶቻችንስ ከተማርንባቸው መጻሕፍት ውጭ አንብበናል፡፡ ለሞባይል ካርድ እና ለመጻሕፍት መግዣ የምናወጣውን ስናመዛዝነው የቱ ይበልጣል? ለወሬ እና ለንባብ ከምናውጣው ጊዜስ የቱ ያመዝናል? ሰማሁ ብሎ ከሚናገረውና አነበብኩ ብሎ ከሚናገረው የቱ ይበዛል? ለምንስ የመጻሕፍት መሸጫዎች የጫት ቤቶችን ሩብ ያህል እንኳን በየሠፈራችን መከፈት አልቻሉም? የጫት መቃሚያ ቤቶች ቁጥርስ ከአብያተ መጻሕፍት ቁጥር መቶ እጥፍ ለምን ሆነ?

አንዲት የበረራ አስተናጋጅ የነገረችኝን እዚህ ላይ ማንሣት አለብኝ፡፡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ከተሳፈሩ ጋዜጣ ስጡን የሚለው መንገደኛ ቁጥር ትንሽ ነው፡፡ በአብዛኛው ሌሎች ዜጎች ከሆኑ ግን ያለውን ማዳረሱ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ከአፍሪካ ሀገሮች ኬንያን፣ ዑጋንዳን፣ ደቡብ አፍሪካን፣ ሌሴቶን አይቻለሁ፡፡ በማለዳ ዓይናችሁ ውስጥ ከሚገባው አሥር ሰው ቢያንስ አራቱ ጋዜጣ ሲያነብብ ታያላችሁ፡፡ ኬንያ ውስጥ በጠዋት በአውቶቡስ ከሚጓዘው ተሳፋሪ እጅ

የሚነበብ ነገር አታጡም፡፡ ጉልት ሻጮቹ እንኳን ከድንቹ እና ከሽንኩርቱ ጎን አንድ የተጣጠፈ ጋዜጣ አያጡም፡፡

ምዕራባውያኑንማ አታንሡ፡፡ አውሮፓ ውስጥ አንድ አውቶቡስ እና ባቡር ሙሉ ሰው ተሳፍሮ ድምፅ አትሰሙም፡፡ አብዛኛው ሰው ዓይኑን በሚነበብ ነገር ላይ ተክሎ ነው የምታገኙት፡፡ እንዲያውም የሚያወራ ሰው ካገኛችሁ ምናልባት አበሻ ሳይሳፈር እንደ ማይቀር መጠርጠር ትችላላችሁ፡፡

ኢትዮጵያ ከዓለም መጀመርያ ፊደልን ከቀረፁ ሀገሮች ተርታ የምትደመር ናት፡፡ ከወረቀት በፊት በብራና፣ ከብራናም በፊት በድንጋይ ላይ ሀሳባቸውን በጽሑፍ ከገለጡ ሕዝቦች አንደኛዎቹ ኢትዮያውያን ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሀገራቸው ቋንቋ አስቀድመው ከተረጎሙ ጥቂት ሕዝቦች መካከል ናቸው ኢትዮጵያውያን፡፡ በብራና የተጻፉ ተራራ ተራራ የሚያክሉ መጻሕፍት አሉን፡፡ «የጻፈ፣ ያጻፈ፣ ያነበበ፣ የተረጎመ» የሚሉ ብዙ ቃል ኪዳኖችን ስንሰማ ኖረናል፡፡ ታድያ ምነው የንባብ ባህላችን የታሪካችንን ያህል አልሆን አለ?

አንደኛው ምክንያት ባህላችን የቃል ባህል Falk lore culture ስለሆነ ይመስለኛል፡፡ «አሉ፣ ተባለ፣ ሰማሁ፣ ይባላል፣ ተወራ» የሚሉት ነገሮች «አየሁ፣ አነበብኩ፣ አረጋገጥኩ» ከሚሉት ነገሮች ይበልጥ ሥር ሰድደዋል፡፡ የቃል ተረት ሲነገረን እንጂ መጽሐፍ ሲነበብልን አላደግንም፡፡ ወላጆቻችንም ሴቶቹ ቡና ላይ፣ ወንዶቹም መጠጥ እና ልቅሶ ላይ ቁጭ ብለው ሲያወጉ እንጂ ሲያነቡ አይተን አናውቅም፡፡ ለልጅ ከረሜላ፣ ማስቲካ እና ጀላቲ እንጂ መጽሐፍ ተገዝቶ ሲሰጥ አላየንም፡፡

ትውፊታዊው የትምህርት ሥርዓታችንም በቃል መያዝን እንጂ መጻፍን እምብዛም አያበረታታም፡፡ በቃል የመያዙ ችሎታ እጅግ የሚበረታታ እና የሚደነቅ ቢሆንም የመጻፍ እና የማንበብ ባህልን ባለማዳበሩ ግን ብዙ ሰማዕያንን እንጂ ብዙ አንባቢያንን አላፈራልንም፡፡ ብዙ ተናጋሪዎች እንጂ ብዙ ደራሲያን አላገኘንም፡፡ እስካሁን ድረስ የቃል ትምህRት ከመጻፍ ጋር ተዛምዶ ያለው በድኅ ትምህርት ቤት ይመስለኛል፡፡

አንዳንድ ጊዜም መጻፍ ከድግምት፣ ከጥንቆላ እና ከሥራይ ጋር መያያዙ አንባብያንን እና ጸሐፍያንን አላበረታታቸውም፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሺ የሚቆጠሩ ሊቃውንትን እየጠራን በጣት የሚቆጠሩ ደራስያንን ብቻ ያገኘነው፡፡

በርግጥ የብዙ አፍሪካውያን ሕዝቦች ባህል የቃል ባህል ነው፡፡ እነርሱ ግን ከዚህ ባህላቸው ጎን ለጎን፣ ያውም የራሳቸው ባልሆነ ፊደል እና ቋንቋ ተምረው የንባብ ባህልን አዳብረዋል፡፡

የንባብ ባህልን በተመለከተ ከ15ኛው መክዘ በፊት እና በኋላ የባህል ልዩነት ያለ መጻሕፍትን ዝርዝር፣ በገድለ ዜና ማርቆስ በገዳሙ ስለመኖራቸው የተነገረላቸውን በሺ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ዝርዝር፣ደብረ ሊባኖስ በግራኝ ስትቃጠል በውስጧ የነበሩ መጻሕፍት ብዛት፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የጻፋቸውን ወደ አርባ የሚጠጉ መጻሕፍት፣ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የጻፋቸወን ሰባት መጻሕፍት፤ ሌላው ቀርቶ የዐፄ ልብነ ድንግል እናት ንግሥት እሌኒ የጻፈቻቸውን ሁለት መጻሕፍት ስናይ የንባብ እና የጽሕፈት ባህል መዳበርን ያሳየናል፡፡

በመካከለኛው ዘመን ከዐረብኛ እና ከቅብጥ የተተረጎሙትን መጻሕፍት ቁጥር ስናጤን እነዚህን መጻሕፍት በተጻፉበት ቋንቋ ያነበቡ፣ ተረድተውም መተርጎም ይችሉ የነበሩ ሊቃውንት መኖራቸው ያስደንቀናል። የአብዛኞቹ ቅዱሳን ገድላት በዚህ ዘመን መጻፋቸውም ኢትዮጵያውያን በቃል የነበሩ ሀብቶችን በጽሑፍ ለማስፈር ያደረጉትን ጥረት ያሳያል።

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ካወጃቸው ዐዋጆች አንዱ ንባብን እና ጽሕፈትን የሚያበረታታ ነበር። ራሱ እየጻፈ ጻሐፊዎችንም ይሸልም ነበር። በየአጥቢያው ቤተ መፍትጻት እንዲከፈቱ አደረገ። ቅዳሜ እና እሑድ ሌላ ሥራ ቀርቶ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የቻሉ እንዲያነብቡ ያልቻሉ ደግሞ ሲነበብ እንዲሰሙ አደረገ።

ከግራኝ አህመድ ጦርነት በኋላ አረማዊነት ከክርስትና ጋር እየተቀላቀለ፣ የጥንቆላ እና የመተት፣ የሥራይ እና የድግምት ሥራዎች እየገነገኑ ሲሄዱ ጽሕፈት ጥንቆላ፣ ንባብም ድግምት እየሆነ መጣ። ተማሪዎችና ሊቃውንትም ስማቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከንባብ እና ጽሕፈት ይልቅ ወደ ቃል ጥናት ብቻ እያተኮሩ መጡ። እንዲያውም አንዳንድ ምሁራን ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ የመጽሐፍ ትምህርቶች እየተዳከሙ የዜማ እና የአቋቋም ትምህርቶች ይበልጥ ቦታ እንዲያገኙ ያደረጋቸው ይኼው አመለካከት ነው ይላሉ። አንድ ሊቅ እንዳሉት ኢትዮጵያውያን ከክርስትና ስማቸው ይልቅ ወደ ዓለማዊ ስም እንዲያዘነብሉ ያደረጋቸው አንዱ ምክንያት ጽሕፈት እና ንባብ ከድግምት እና ጥንቆላ ጋር መያያዙ ነው። ድግምት የሚደገመውና እና መተት የሚመተተው በክርስትና ስም ነው በመባሉ ኢትዮጵያውያን የክርስትና ስማቸውን መደበቅ ግድ ሆነባቸው።

ሌላው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ደግሞ በዚመናዊው ሥርዓተ ትምህርታችን የገጠመን ችግር ነው። ዘመናዊው ትምህርት ሲወጠን፣ሥርዓተ ትምህርቱም፣ መጻሕፍቱም፣ መምህራኑም ከውጭ ነበር የመጡት። ነባሩ መሠረት ተረስቶ አዲስ መሠረት ተመሠረተ። ሽምድዶ እና አጥንቶ ማለፍ እንደ ባህል ተወሰደ። የመማርያ መጻሕፍቱም ሆኑ የማጣቀሻ መጻሕፍቱ ከውጭ የሚመጡ በመሆናቸው እንደልብ ሊገኙ አልቻሉም። ያለው አማራጭ የተገኘውን ሽምድዶ መያዝ ነው። ዛሬም ድረስ በታላላቅ የሀገሪቱ የትምህርት ተቋማት የማጣቀሻ መጻሕፍት እና የመማርያ መጻሕፍት ሳይቀሩ ከውጭ የሚገቡበት ሁኔታ አለ። ተማሪውም ንባብን የሕይወቱ አካል ሳይሆን የአንድ ወቅት ችግሩ መፍቻ ብቻ አድርጎ አየው። ለዚህም ነው በታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች በፈተና ጊዜ የተጣበቡ አብያተ መጻሕፍት ፈተና ሲያልቅ እንደ መቃብር ሥፍራ ጭር የሚሉት። አንብቦ እና ተረድቶ መተንተን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ እንኳን ከባድ እየሆነ «የጥናት ወረቀት እንሥራለን» የሚሉ ማስታወቂያዎች ያለ ሀፍረት ተለጥፈው እናያለን።

ሀብታም በሚባሉት ዜጎች ግቢ ውስጥ ጃኩዚ፣ ሳውና፣ የመዋኛ ገንዳ፣ የልጆች መጫወቻ ከፍል፣ የመጠጥ መጠጫ ኮሪደር ከነ ባንኮኒው፣ የዲ ኤስ ቲቪ መመልከቻ ክፍል ከነ ስክሪኑ ስንት ወጭ ወጥቶባቸው ይዘጋጃሉ። የመጻሕፍት ማንበቢያ ክፍሎች ግን አይዘጋጁም። ትንሽ ሻል ያሉትም ቢሆኑ «ቀላል አይደለንም» ለማለት ያህል የተዋቡ መደርደርያዎች ውስጥ ዳጎስ ዳጎስ ያሉ መጻሕፍትን ይደረድራሉ፡ ነገር ግን ለጌጥነት ካልሆነ በቀር ለንባብ አይውሉም፡ ፡ የንባብ እና የጽሕፈት መነሻ እና ባለቤት የነበሩት አብያተ ክርስቲያናትም ትልልቅ ሕንፃ ገንብተው ሱቅ እና የመቃብር ፉካ እንጂ ቤተ መጻሕፍት መክፈትን አላሰቡበትም። ሌላው ቀርቶ በየቤተ ክርስቲያኑ ተከማችተው ብል እና አይጥ የሚጫወትባቸው መጻሕፍት ወጥተው ብናነብባቸው ምን ነበረበት?

አንዳንድ ጊዜ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች እና በመጻሕፍት ላይ አንዳች ነገር ወጥቶ ያነበቡ ሰዎች ላላነበቡት ይናገራሉ።

እነዚያ ያላነበቡት ሰዎች ርግጡን አንብበን እናጣራ ከማለት ይልቅ የሰሙትን እንዳዩት አድርገው ያወራሉ። «ኣይተሃል?» ሲባሉም በድፍረት «ያየ ሰው ነግሮኛል» ይላሉ። ሌላው ቀርቶ ይህንን ነገር አንብበው እንዲህ እና እንዲያ ያለ ነገር አለው ብላችሁ ስትጋብዟቸው ይቀበሏችሁና «ምንድን ነው የሚለው ግን» የሚሏችሁ አሉ። ጨክናችሁ «አንብቡት» ስትሏቸው «አንተ አንብበህው የለ፤ ለምን አትነግረኝም» ይሏችኋል። አትፍረዱባቸው አስተዳደጋቸው ነው።

«ድንጋይ ውኃ ውስጥ ሺ ዘመን ቢቀመጥም ሊበቅል አይችልም» እንደሚባለው ንባብ ባህል በሆነባቸው አውሮፓ እና አሜሪካ የሚኖሩ ወገኖቻችን እንኳን በሞባይል ስልክ፣ በ«ፓል ቶክ» እና በ«ስካይ ፒ» ለወሬ የሚሯሯጡትን ያህል ለንባብ ብዙ ጊዜ የላቸውም። በተለይ በሰሜን አሜሪካ ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት በኋላ የስልክ ዋጋ ነጻ ስለሆነ አበሻ እየተደዋወለ «ምን አዲስ ወሬ አለ» ማለት ልማዱ ሆኗል። በውጩ ዓለም የሐበሻ መጠጥ ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፣ ጠላ እና ጠጅ ቤቶች፣ ቁርጥ ቤቶች፣ የባህል ዕቃ መሸጫ ቤቶች፣ ተከፍተዋል። የሐበሻ ቤተ መጻሕፍት ግን እንጃ። ብዙው የዲያስጶራ ሰውም ሽሮ እና በርበሬ ከሀገር ቤት ያስመጣል እንጂ መጻሕፍት ላኩልኝ ወይም አምጡልኝ ኣይልም። እንዲያውም ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በአንድ የመንግሥት ቢሮ የሚሠራ ወዳጄ አንደን ጥናት ጠቅሶ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን literally illiterate ከሚባሉት ወገን ናቸው ብሎኛል። ይህም መመሪያዎችን፣ ማኑዋሎችን፣ መረጃዎችን፣ ብሮሸሮችን፣ መግለጫ ዎችን፣ ማስታወቂያዎችን አንብበው፣ተገንዝበው ከመመራት ይልቅ በራሳቸው ልማድና ሊሆን ይችላል በሚሉት የሚመሩ ማለት ነው። ፊደል ቆጥረዋል፣የትምህርት ደረጃ አላቸው ግን ከተጻፈው ይልቅ የተባለውን፣ ከሕጉ ይልቅ ይሆናል ብለው የሚያስቡትን ያምናሉ። አንድን መረጃ ሲፈልጉ ስለ ጉዳዩ የተጻፈ ነገር ፈልገው ከማንበብ ይልቅ ዐዋቂ ሰው ያፈላልጋሉ። «ኣቁም» የሚለውን ምልክት ኣይተው ከማቆም YLቅ «እገሌኮ አቁም ሲባል ሄዶ ምንም አልሆነም » የሚለውን ይቀበላሉ።
ለዚህ ባህል አስተዋጽያ ያደርጋሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው ምሁራንም የቸግሩ መፍትሔ ከመሆን ይልቅ የቸግሩ ሰለባ ሆነዋል። በአንድ በኩል ሽምደዳን በማበረ ታታት፤ በሌላም በኩል እነርሱ ካወጡት ማስታወሻ «ኖት» ውጭ ተማሪዎቹ ሌላ ዕውቀት ያለ እንዳይመስላቸው በማድረግ፤ የባሰባቸው ደግሞ ከሌላ ምንጭ አዲስ ነገር ይዘው የሚመጡ ተማሪዎቻቸውን «ኣሁን ማንበብህ ነው፣ ማወቅህ ነው፣ አንባቢ ነኝ ለማለት ነው» እያሉ ሞራል በመንካት ንባብን ኣፈር ድሜ አስጋጡት።
እስኪ ከምሁራኖቻችን መካከል የጥንቶቹ ካልሆኑ በቀር ዕውቀታቸውን ለሕዝብ በሚገባ ቋንቋ የጻፉ እነማን ናቸው? ስንት ፕሮፌሰሮች በሀገሪቱ ቋንቋ ሕዝብ የሚያስተምር ነገር ጽፈዋል? ሌላ ቀርቶ የ ፒ ኤች ዲ ወረቀታቸውን መች ወደ ሀገራችን ቋንቋ ተረጎሙት? አንዳንዶቹማ መጽሐፌ ኢትዮጵያ ኣይግባ ብለው ኣይደለም እንዴ የተናዘዙት። እስኪ ስለ አካውንቲንግ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ምሕንድስና፣ ጤና፣ ወዘተ የሚገልጡ ስንት የአማርኛ መጻሕፍት አሉን። ከተከለ ጻድቅ መኩርያ በቀር ታሪካችንን እንኳ የኛው ምሁራን በእንግሊዝኛ ኣይደል የጻፉት? ዕውቀቱን በሀገሩ ቋንቋ ማስረዳት የሚችል ስንት ምሁር አለን?
ቻይናዎች እና ጃፓኖች አንድ ባህል አላቸው። አንድ ነገር በውጭ ቋንቋ በተጻፈ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ሀገራቸው ቋንቋ ተተርጉሞ ይቀርባል። ሕዝቡ በሚገባውና በሚያውቀው ቋንቋ ዕውቀትን ያገኛል። የዕውቀት ሽግግር ማለት ይህ ነው። እኛ ሀገር ግን ከማይታወቅ መጽሐፍ ጠቅሶ «መጽሐፉን እንኳን አታገኙትም» ማለት የዐዋቂነት መለኪያ ሆኗል።

ሌላም ችግር አለ በሀገራችን፡፡ መጽሐፍ ከመጻፍ እና ከማሳተም ይልቅ ያልተፈቀደ ቅጅ ካሴት እያባዙ መሸጥ ያዋጣል፡ ፡ ከመጻፉ ማሳተሙ፣ ከማሳተሙ ማሠራጨቱ ከባድ ነው፡፡ አንድ ደራሲ አስደናቂ መጽሐፍ ጽፎ ከሚያገኘው ይልቅ አንድ ሰው አንድ ሺ ቢራ አከፋፍሎ የሚያገኘው ይበልጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜም የወረቀት ቀረጥ ከአልኮል ቀረጥ ይልቅ የሚወደድበት ጊዜ ነበረ፡፡ የወረቀት ዋጋም እንደ ጤፍ ዋጋ በየጊዜው ይጨምራል፡፡ እንግዲህ እነዚህ እና ሌሎችም ተጨማምረው አበሻን ሰሚ እንጂ አንባቢ አላደረጉትም፡፡ የወሬ እንጂ የንባብ ባህልንም አላደበሩለትም፡፡

ታድያ ምን ይደረግ ትላላችሁ? እስኪ እኔ የመፍትሔ ሃሳብ ከመሰንዘሬ በፊት እናንተ ተወያዩበት? «ፊደል እያለው፣ የማያነብብ ማነው?» ለሚለው የዕንቆቅልሽ ጥያቄ «አበሻ» የሚል መልስ እንዳይሰጠው ምን እናድርግ?

16. አርቶዶክሳዊ መምህር፣ ዕውቀቱ እና ክሂሎቱ :- ማስተማር ምንድን ነው?

ጌታችን ሐዋርያትን ሲልካቸው የሰጣቸው የመጨረሻው መመርያ ለመምህራን ሁሉ መሠረት ነው፡፡ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያ፣ እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» /የሐዋ 1÷8/ ይህ ቃል የአንድ ሐዋርያ ተግባር ፍጻሜ እንደሌለው ያስረዳናል፡፡ ሊቃውንቱ ይህንን መመርያ በሁለት መንገድ ተርጉመውታል፡፡ (Arch bishop Anthonios Marqos, The Theology of mission and missionary.)

1/ **ከቅርብ እስከ ሩቅ**፡- የአንድ ሐዋርያ ተግባር አጠገቡ ካለው ማኅበረሰብ ጀምሮ አይቶት እና ሰምቶት እስከማያውቀው ሕዝብ ሊደርስ እንደሚችል

2/ **ከቀላል ወደ ከባድ**፡- ለአገልግሎቱ ቀላል ከሆነው አንሥቶ ውስብስብ እና አስቸጋሪ ወደሆነው አገልግሎት፤ መሥዋዕትነት ከማይጠይቀው አገልግሎት መሥዋዕትነት እስከ ሚጠይቀው አገልግሎት እንደሚደርስ ያስረዳል፡፡

በዚህ ተግባሩ የሚፈጽማቸው አገልግሎቶች በሁለት ዋና ዋና ተልዕኮዎች እና በአምስት ዝርዝር ተልዕኮዎች ይጠቃለላሉ፡፡

ዋና ዋና ተልዕኮዎች

1. **ያመኑትን ማጽናት**፡- በወንጌል አምነው፣ በቤተ ክርስቲያን በረት ውስጥ ያሉ ምእመናን በመናፍቃን፣ በከሃድያን እና በኢአማንያን እንዳይነጠቁ መጠበቅ

2. **ያላመኑትን ማሳመን**፡- ወደ ወንጌል ማዕድ ያልቀረቡ የአዳም ልጆችን ወደ ወንጌል ማዕድ ቀርበው የመዳንን መንገድ ዐውቀው እንዲጓዙ ማድረግ

ዝርዝር ተልዕኮዎች

መመስከር፡- ወንጌልን ማስተማር
መምራት፡- ሕዝቡን በሕይወት፣ በዕውቀት እና በአሠራር አርአያ መሆን
ማሠልጠን፡- ቤተ ክርስቲያንን ሊመሩ፣ ሊያስተዳድሩ፣ ጉባኤያትን ሊያስተምሩ፣ ለሕዝቡ አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ መሪዎችን ማሠልጠን
ማደራጀት፡- ጉባኤያትን፣ ማኅበራትን፣ ሰንበት ት/ቤቶችን፣ አጥቢያዎችን፣ ማደራጀት
መትከል፡- አጥቢያዎችን፣ ገዳማትን፣ ማሠልጠኛዎችን፣ የአብነት ት/ቤቶችን ወዘተ መትከል

እነዚህ ነገሮች የመምህራን ሥራ መድረክ ላይ ወጥቶ ከማስተማር በላይ መሆኑን ያስረዱናል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ላይ የአበው ሐዋርያትን ተግባር ብንመለከት እነዚህን አምስት ተግባራት በጉዞዎቻቸው ውስጥ እናገኛለን፡፡

አንዳንድ ሊቃውንት አንድ የወንጌል መምህር ሦስት ነገሮች ሊኖሩት ይገባል ይላሉ፡፡ እነዚህም

የማስተማር ቀደምት አበው ጉባኤ ዘርግተው፣ተዘዋውረው አስተምረዋል፡፡ ትምህርቶቻቸው በዘመኑ የግሪክ ፍልስፍና የሚዋጅ፤ እንደ ዲዮናስዮስ ያሉ የአርዮስፋሳስ ሊቃውንትን የማረከ ነበር፡፡ ኢየሱስ ከናዝሬት ወደ ገሊላ ሄደ የሚል ሳይሆን አዳዲስ ዕው ቀት በየዕለቱ የሚገኝበት ነበር፡፡

ለምሳሌ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በቁስጥንጥንያ ሐጊያ ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ የሠርክ ጉባኤ ነበረው፡፡ ትምህርቶቹን ተከታትለው ይጽፉ የነበሩ ደቀ መዛሙርትም ነበሩት፡፡ እርሱም ትምህርቶቹን አስቀድሞ ይጽፋቸው ነበር፡፡ ባስልዮስ ዘቂሳርያም በቂሳርያ ከተማ በመሠረተው ገዳም ኢያሌ ሕዝብ ያስተምር ነበር፡፡ በተለይም ዓምደኞች እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ መምህራን ሕዝቡን ሌሊትና ቀን ያስተምሩት ነበር፡፡ ስምዖን ዘዓምድ ከቆመበት ዓምድ ሳይወርድ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ይመጡ የነበሩትን ሁሉ አስተምሯል፡፡

የመጻፍ በሐዋርያውያን አበው እና ከእነርሱ በኋላ በተነሡ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ዘንድ እነዚህን ሦስቱን ነገሮች እናገኛለን፡፡ ዛሬ በየድርሳኖቻቸው እና በሃይማኖተ አበው የምናገኛቸውን ጽሑፎች እና መጻሕፍት ጽፈዋል፡፡ ትርጓሜያትን አዘጋጅተዋል፡፡ እንዲያውም በሃይማኖተ አበው ላይ የምናገኛቸውን ድርሰቶቻቸውን ስናይ አበው እርስ በርሳቸው በመልእክት ትምህርት ይለዋወጡ እንደ ነበር፣ጥያቄ ይጠያየቁ እንደነበር እንረዳለን፡፡

ከትምህርት መጻሕፍት በተጨማሪ እስከ ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጡ የጸሎት፣ቅዳሴ፣የመዝሙር፣ የሥርዓት መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል፡፡ ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ባስልዮስ፣ ዲዮስቆሮስ፣ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እና ሌሎች ቅዳሴ አዘጋጅተዋል፡፡ እነ አባ ሄሮኒመስ እና ዮሐንስ አፈወርቅ ትርጓሜ ጽፈዋል፡፡ እነ ሄሬኔዎስ እና አቡሊዲስ ዘሮም ለዘመኑ መናፍቃን ምላሽ ጽፈዋል፡፡ እነ ባስልዮስ እና አባ ኤፍሬም የጸሎት መጻሕፍት ደርሰዋል፡፡ እነ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ፣ ሶቅራጥስ እና ሩፊኖስ ታሪክን አደራጅተዋል፡፡ እነ አውግስጢኖስ የሕይወት ታሪካቸውን ጽፈዋል፡፡ እነ ቅዱስ አትናቴዎስ የነገረ ሃይማኖት መጻሕፍትን እና የአበውን ታሪክ ጽፈዋል፡፡

የመመራመር ተሰጥኦ ቀደምት አበው ዘመናቸውን ለመዋጀት ይችሉ ዘንድ የግሪክን እና የሮምን ፍልስፍናዎች፣ የብሉይ ኪዳንን ትምህርቶች እና ባህሎች፣ የዘመን አቆጣጠር እና የመልክዐ ምድራዊ ሥራዎች መርምረዋል፡፡ አቡሊዲስ ዘሮም ለብሉይ ኪዳን እንደ ዋና መክፈቻ ቁልፍ የሚነገረውን የዘመን አቆጣጠር ትንተና አቅርቧል፡፡ ኤጲፋንዮስ ስለ ሥነ ፍጥረት አክሲማሮስ የተሰኘ መጽሐፍ አቅርቦልናል፡፡ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ የመጽሐፍ ቅዱስን መልክዐ ምድር አጥንቷል፡፡

የዕውቀት ምንጮች

አንድ መምህር ሊያስተምራቸው የሚችሉ ነገሮችን የሚያገኝባቸው ምንጮች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህም መሠረታውያን እና ተጨማሪዎች ይባላሉ

የዕውቀት *መሠረታውያን*

የዕውቀት መሠረታውያን የምንላቸው የምእመናንን ሕይወት እና እምነት፣ የቤተ ክርስቲያንን አካሄድ እና አሠራር የሚወስኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ምንጮች የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመመስከር እና ለማረጋገጥ የምናውላቸው ናቸው፡፡

የጌታችን ትምህርቶች ወደ ኋላ ሄደን ብሉይን ፣ወደፊት ተጉዘን ሐዲስን የምንተረጉመው የቤተ ክርስቲያን መሠረቷ የሆነው ጌታችን በሰጠን መሠረት ላይ ሆነን ነው፡፡

የሐዋርያት ትምህርቶች፡ በወንጌል ተጽፎ የምናገኘው የጌታችን ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን መሠረቷ ነው፡፡ጌታችን ከዋለበት ውለው ካደረበት አድረው፣ ትምህርት ተአምራት ሳይከፈልባቸው የተማሩ፣ የመጀመርያዋን ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ፣ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ በልዩ ሁኔታ የተጠሩ ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያን ያስቀመ ጧቸው ትምህሮች፣ ሥርዓቶች እና አሠራሮች የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እና አካሄድ ይወስናሉ፡

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርቶች፡ ከሐዋርያት የተቀበሉትን ትምህርት፣ሕይወት እና ሥርዓት ለቤተ ክርስቲያን አደራጅተው እና አብራርተው፣ያስረከቡ አበው ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት እና ጉዞ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ አንድን አባት የቤተ ክርስቲያን አባት የሚያደርገው አራት ነገሮችን ሲያሟላ ነው፡፡

1. ርቱዕ የሆነውን ኦርቶዶክሳዊ እምነት አምኖ ሲያስተምር
2. ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ የሚረዳ መጽሐፍ ሲጽፍ እና
3. ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም ሲችል
4. ለሌሎች አርአያ የሚሆን የቅድስና ሕይወትን ሲኖር (H.G. Bishop Moussa, The Characteristics of Orthodox Teaching. P ,85)

አንድ ኦርቶዶክሳዊ መምህር የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በተመለከተ ሊከተላቸው የሚገቡት መርሖች አሉ፡

1 **የአባቶችን ሕይወት ማጥናት**

የአባቶችን ሕይወት ማጥናት ለተሻለ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያበረታ፣ የሚያተጋ እና የሚያበረታታ ነገር ይገኝበታል፡፡

መንፈሳዊ ልምዳችንን ይጨምርልናል፡፡ ለተለያዩ ችግሮች እና ሁኔታዎች ምን ማድረግ እንዳለብን ተግባራዊ ልምድ እናገኛለን፡፡

የተለያዩ እሴቶችን እንማርበታለን፡፡ የተለያዩ አበው ልዩ ልዩ ጸጋ፣ ተሰጥኦ እና ደረጃ አላቸው፡፡ የልዩ ልዩ አበውን ሕይወት ስናጠና እነዚህን ነገሮች እናገኛለን፡፡ ከአትናቴዎስ ለሃይማኖት መጽናትን፣ ከእንጦንስ ራስን መግዛትን፣ ከአርሳንዮስ ትኅትናን፣ ከዲዮስቆሮስ ሃይማኖትን በድፍረት እና በእውነት መመስከርን፣ ከአባ ቢሾይ ጸሎት እና ፍቅርን፣ እንማራለን፡፡

በአማላጅነታቸው እንድንጠቀም ያደርገናል፡፡

2 **የአባቶችን ትምህርት እና አባባል ማጥናት**

አንዳንዶች ያለፈውን መጥቀስ እና ካለፈው መነሳት ትውፊታዊነት ወይንም ያለፈውን ብቻ የማድነቅ አባዜ ያደርጉታል፡፡ ግን አይደለም፡፡ ክርስትና በኛ አልተጀመረም፤ እኛ ለክርስትና ተቀባዮች እንጂ ጀማሪዎች አይደለንም፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚነግሩን ደግሞ ዘመናት በጨመሩ ቁጥር የቅድስና ሕይወት እየደከመ እንጂ እየበረታ አይሄድም፡፡ ስለዚህም በእምነት ረገድ ያለፉት ከኛ ይሻላሉ፡፡

በመሆኑም አንድ ኦርቶዶክሳዊ መምህር የአባቶችን ትምህርት አጥንቶ ትምህርቱን በእነርሱ መሥመር ማድረግና በትምህርቱም እነርሱን መጥቀስ ይኖርበታል፡፡

3 **ሕይወቱን እና ትምህርቱን በአባቶች ሕይወት እና ትምህርት መሠረት ማድረግ** (Ibid, p. 78)

እኛ አባቶች ፈጽመው አይሳሳቱም infallible ብለን አናምንም፡፡ ሰው የመሆን ስሕተቶችን ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የዶግማ እና የሥነ ምግባር ጥፋቶችን አይሠሩም፡፡ በትንታኔያቸው አና በትርጓሜያቸው አንዱ ከሌላው ሊለዩ ይችላሉ፤ ነገር ግን በኦርቶዶክሳዊ እምነታቸው እና ሕይወታቸው አንድ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሊቅነታቸው የምናደንቃቸው ቢሆንም እነዚያን አራት ነገሮች ካላሟሉ ግን «የቤተ ክርስቲያን አባት» አንላቸውም፡፡ ለምሳሌ አርጌንስ በኑሮው እና በድርሰቱ የሚደነቅ ቢሆንም ክርስትናን ከግሪክ ፍልስፍና በመቀላቀሉ «የቤተ ክርስቲያን አባት» አይባልም፡፡

እንዴት እናንባቸው?

አበውን በአጠቃላይ ማንበብ አለብን፡፡ ምክንያቱም አንዱ በሌላው ይሟላሉና፡፡ ሃሳባቸውን፣ የተነሡበትን ምክንያትና ሌሎች ነገሮችን ተተን አንድን ሃሳብ ብቻ ለራሳችን መደገፊያ መጠቀም የለብንም፡፡ በርግጥ እንደ ተሰጥኦዋቸው ልዩነት ቢኖርም የሁሉም አንድ ማዕከላዊ ነገር ግን ኦርቶዶክሳዊ እምነት እና ሕይወት ነው፡፡

የነበሩበትን ዘመን፣ ሁኔታ እና ለነማን እንደ ጻፉት መረዳት አለብን፡፡ መጀመርያ የተጻፈበትን ቋንቋ፤ በዘመናቸው የነበረውን የሃይማኖት እና የሥነ ምግባር ችግር ማጤን አለብን፡፡

የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ ይህ አከፋፈል በአብዛኞቹ ሊቃውንት ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ እንደ መከፈያ ዘመን የሚጠቀሙትም የመጀመርያውን ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የሆነውን ኒቂያን ነው፡፡

ቅድመ ኒቂያውያን /pre Nicene /

እነዚህ አባቶች በአብዛኛው ከፈላስፎች እና ከግኖስቲኮች ጋር የተከራከሩ፤ የመጀመርያዎቹ አበው ናቸው፡፡ ጽሑፎቻቸውም በአብዛኛው አልተገኙም፡፡ ዮስጢኖስ ሰማዕት፣ ሄሬኔዎስ፣ ሄርማን፣ ታትያን፣ አቴናጎራስ፣ ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ ፓፒያን፣ዲዮናስዮስ፣አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ወዘተ

ድኅረ ኒቂያውያን /post Nicene/ እነዚህኞቹ አበው ከመናፍቃን ጋር የተከራከሩ ናቸው፡፡ በተለይም አርዮሳውያንን፣ ንስጥሮሳውያንን፣ አቡሊናርዮሳውያንን ተከራክረዋል፡፡ በአብዛኛው ካለፉት በተሻለ ጽሑፎቻቸውን እናገኛለን፡፡ አውግስጢኖስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አትናቴዎስ፣ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ባስልዮስ፣ ቄርሎስ፣ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ዲዮስቆሮስ፣ ወዘተ ናቸው፡፡

ከዘመናቸውም በተጨማሪ በጻፉበት እና ባስተማሩበት ቋንቋ ምክንያትም በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነዚህም

በግሪክ ቋንቋ የጻፉ፡ በአብዛኛው በግብጽ፣ ቁስጥንጥንያ፣ ሶርያ፣ አርመንያ፣ አንጾኪያ የነበሩ

በላቲን ቋንቋ የጻፉ፡ በአብዛኛው በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አፍሪካ የነበሩ፡፡

በሌላም በኩል ባስተማሩበት ሀገርም ይከፈላሉ፡

ሮማውያን፡ በሮም እና የሮም ሀገረ ስብከት በነበሩት ቦታዎች ያስተማሩና የጻፉ፡፡ እነ አውግስጢኖስ፣ ዲዮናስዮስ፣ ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ ሄሮኒመስ፣ ወዘተ

ግብፃውያን፡ በግብጽ እና በሀገረ ስብከቷ የጻፉ፣ ያስተማሩ፡፡ ለምሳሌ አትናቴዎስ፣ ዲዮናስዮስ፣ ዲዮስቆሮስ፣ ቄርሎስ፣ ወዘተ

አንጾኪያውያን/ቀጰዶቅያውያን/፡ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ ባስልዮስ፣ ወዘተ

አርመናውያን፡ ለምሳሌ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ

ሶርያውያን፡ ለምሳሌ ኤፍሬም ሶርያዊ

ኢትዮጵያውያን፡ ቅዱስ ያሬድ፣አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ ርቱዐ ሃይማኖት፣ ወዘተ

የአበውን ትምህርቶች ለማጥናት እንድንችል ጽሑፎቻቸውን በይዘታቸው መከፋፈልም ይቻላል፡

- ***ትርጓሜያት /Exegetics/*** ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጎም የተጻፉ
- ***የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት መጠበቅ /Apologetics/*** የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለማስረዳትና ከብረዛ ለመጠበቅ የተጻፉ
- ***ትምህርቶች /Sermons and Essays/*** ስለ ሕይወት፣ስለ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፣ስለ ሥነ ምግባር፣ስለ ልዩ ልዩ በዓላት፣ወዘተ የሚያብራሩ ጽሑፎች
- ***መልእክታት/Epistles/*** ወደ ልዩ ልዩ ቦታዎች የተላኩ መልእክታት
- ***ቅዳሴያት/liturgies/***
- ***መዝሙራት እና ጸሎቶች/ Poetry and Hymns of Praise/***
- ***ክርክሮች /Dialogues/*** በልዩ ልዩ ጊዜ ስለ ሃይማት ጉዳዮች የተደረጉ ክርክሮች
- ***ምናኔያውያን / Ascetics/*** ስለ ምንኩስና፣ብሕትውና እና የምናኔ ሕይወት የተጻፉ፡፡ ***ሕግጋት እና ሥርዓታት/Church Law/*** ቤተ ክርስቲያን የምትመራባቸውን ልዩ ልዩ ሥርዓቶች እና አሠራሮች የደነገጉባቸው ጽሑፎች***የታሪክ መጻሕፍት/Ecclesiastical history/*** የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በተመለከተ የተጻፉ (Fr.Tadros Yacoub Malaty. An Introduction of Patrology.)

ኢትዮጵያውያን አባቶች

ለቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት፣ የመዝሙር፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ እና የሥርዓተ መጻሕፍትን የጻፉ ኢትዮጵያውያን አበው «ኢትዮጵያውያን አበው» ይባላሉ፡፡

እነዚህ አባቶች በሦስት ይከፈላሉ፡፡

የቤተ ክርስቲያን አባቶች፡ የምንላቸው ከፍ ብለን ያየናቸውን አራቱን መመዘኛዎች ያሟሉትን ነው፡፡እነዚህ አበው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ገብተው ቅዱሳን ተብለዋል፡፡ እነርሱም ቅዱስ ያሬድ፣ ርቱዐ ሃይማኖት፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣እነ አባ ጽጌ ድንግል፣እጨጌ ዕንባቆም፣ ወዘተ ናቸው

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፡ የምንላቸው በሁሉም ነገር ተሟልቶላቸው ቅዱሳን ለመባል ግን የቤተ ክርስቲያንን ውሳኔ ያላገኙትን ነው፡፡ ከጥንቶቹ የመልከዐ ሥላሴን ደራሲ መምህር ስብሐት ለአብን፣ እነ መምህር ኤስድሮስን፤ እነ መምህር አካለ ወልድን፣ ወዘተ፣ ከአሁኖቹ እነ መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬን ያካትታል፡፡

የቤተ ክርስቲያን መምህራን በየቤተ ክርስቲያን መምህራን የምንላቸው በማስተማር እና በድርሰት በርትተው በሕይወታቸው ምክንያት የቅድስና ማዕረግ ያላገኙትን ነው፡፡ እነ ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ፣ እነ ንግሥት ዕሌኒ፣ እነ ዐፄ ናዖድ፣ ፡በትምህርት፣በድርሰት አና በልዩ ልዩ አገልግሎት ቢበረቱም በኑሮ ዐንቅፋት ገጥሟቸዋል፡፡፡

የቤተ ክርስቲያን ትውፊት፡ ሁሉም ነገር በመጽሐፍ አልተጻፈም፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በጸሎቱ፣ በማኅሌቱ፣ በቅዳሴው፣ወዘተ የምናገኛቸው ትምህርቶች እና ሥርዓቶች ለቤተ ክርስቲያን ርቱዐዊ ጉዞ አስፈላጊ ናቸው፡ ፡ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት ውሳኔዎች በየዘመናቱ የተነሡ መናፍቃንን፣ በየጊዜው የተፈጠሩ ችግሮችን፣ በየሁኔታው የገጠሙ ፈተናዎችን ለመፍታት በጉባኤያት ተሰብስበው አበው የደነገጓቸው ድንጋጌዎች ቤተ ክርስቲያን ከማዕበል ወጥታ ወደ ጸጥታ ወደብ እንድታመራ ያደረጉ፤ የቤተ ክርስቲያንንም አንድነት ያጸኑ ዋልታዎች ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁለት ዓይነት ጉባኤያት ተደርገዋል፡፡
ዓለም ዐቀፍ ጉባኤያት፡ እነዚህ ጉባኤያት በወቅቱ የነበሩ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የተሳተፉባቸው፣ የቤተ ክርስቲያንንም ጉዞ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው ጉባኤያት ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በ325 ዓም የተደረገውን ጉባኤ ኒቂያ፣ በ381 ዓም የተደረገውን ጉባኤ ቁስጥንጥንያ እና በ431 የተደረገውን ጉባኤ ኤፌሶን ትቀበላለች፡፡ ለሌሎቹ ግን ርቱዓን ናቸው ብላ ዕውቅና አትሰጥም፡፡
አካባቢያዊ ጉባኤያት እነዚህ ጉባኤያት በአንድ አካባቢ የተነሡ ችግሮችን ለመፍታት በአካባቢው የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት የሠሯቸው ጉባኤያት ናቸው፡፡ የእስክንድርያ፣ የጋንግራ፣ የዕንቆራ፣ የካርታጎ ወዘተ እየተባሉ የሚጠሩ ጉባኤያት ናቸው፡ ፡ በሀገራችንም በ14ኛው መክዘ የተደረገውን የደብረ ምጥማቅ ጉባኤ መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንድ የቤተ ክርስቲያን መምህር በእነዚህ በሁለቱ ዓይነት ጉባኤያት የተወሰኑ ውሳኔዎችን ማወቅ አለበት፡፡

ተጨማሪ ዕውቀቶች፡- አንድ አስተማሪ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስላወቀ ብቻ ሊያስተምር አይችልም፡፡ ዘመኑንም ማወቅ አለበት፡፡ ዘመኑን ማወቅ ማለት ደግሞ፡

- የዘመኑን አስተሳሰብ ማወቅ
- የዘመኑን ችግሮች ማወቅ
- የዘመኑን ጥያቄዎች ማወቅ
- የዘመኑን የአኗኗር ሁኔታ ማወቅ
- የዘመኑን ሥርዓተ ማኅበር ማወቅ ማለት ነው፡፡

እነዚህን ነገሮች ለማወቅ ደግሞ ሚዲያዎችን መከታተል፣ የዘመኑን ወሳኝ መጻሕፍት ማንበብ እና አካባቢን ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ሃብታም እና ድኻ፣ ጋብቻ፣ ወዘተ መጻሕፍቱን ስናነብ ሊቁ ዘመኑን እንዴት እንደተረዳው እናውቃለን፡፡ የግሪክን ፈላስፎች፣ የዘመኑን ዜናዎች፣ የወቅቱን የአኗኗር ባህል በውስጡ ይተነትናቸዋል፡፡ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ የጻፈውን የሙሴ ሕይወት ስናነብ የግሪክ ፈላስፎችን አመለካከት እንዴት እንዳፈረሰ እናያለን፡፡ አንድ አስተማሪ ከላይ ያሉትን ምንጮች መጠቀም የሚያስችሉት ሦስት መሣርያዎች አሉ፡፡ እነርሱም

- የማንበብ ልምድ
- መረጃ የማሰባሰብ ልምድ እና
- የቋንቋ ችሎታ ናቸው፡፡

የማንበብ ልምድ፡ የማያነብ ሰባኪ ባያስተምር ይመረጣል፡፡ ከሚደርቅ ምንጭ የሚያረካ ውኃ አይገኝምና፡፡ ማንበብ ደግሞ ከመጻሕፍት ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ተንቀሳቃሽ መጻሕፍት ከሆኑት ሊቃውንት መማርም ነው፡፡ ከቀደሙት አበውም ሆነ ከማንደርስበት የዕውቀት ምንጭ መማር የምንችለው በማንበብ ነው፡፡ ስለዚህም ሰባኪው የማነበብ እና የማጣጣም ልምድ ሊያዳብር ይገባዋል፡፡ ወስኖ፣ ጊዜ እና ገንዘብ መድቦ ማንበብ ልምድ መሆን አለበት፡፡ የምናነባቸው መጻሕፍት እንደ በያይነቱ ምግብ ከሁሉም አቅጣጫ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ የሕክምና ሰዎች ልዩ ልዩ ዓይነት ምግብ የሚመገብ ሰው የተለያዩ ቫይታሚኖች፣ ማዕድኖች እና ገንቢ ነገሮች የማግኘት ዕድሉ ይሰፋል እንደሚሉት ሁሉ ልዩ ልዩ ዓይነት መጻሕፍትን ማንበብም እንደዚሁ ነው፡፡

የማሰባሰብ ልምድ፡ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት በቀላሉ አይገኙም፡፡ በየገዳማቱ እና በየሊቃውንቱ፤ በየቤተ መጻሕፍቱ እና በየሙዝየሙ ተበትነዋል፡፡ እነዚህን ለማገኘት ትእግሥት እና ጥረት ያስፈልጋል፡፡ መረጃዎችን በኮፒ፣ በድምጽ፣ በማስታወሻ፣ በላካል እና በአእምሮ የማሰባሰብ ልምድ ያስፈልጋል፡፡

የቋንቋ ችሎታ፡ ግእዝን፣ ዐረብኛን፣ ዕብራይስጥን እና ግሪክን የመሳሰሉ ቋንቋዎች የጥንት ጽሑፎችን ለመመርመር፤ እንግሊዝኛ ደግሞ በዘመኑ የተጻፉትንም ሆነ የተተረጎሙትን ለማግኘት አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ዐቅማችን የፈቀደውን ያህል ብናውቃቸው በሩ ወለል ብሎ ይከፈትልናል፡፡

የማስተማር ዓላማ

ኦርቶዶክሳዊ የማስተማር ዐላማው ማስደነቅ፣ ማስደመም፣ ማዝናናት፣ ማሳወቅ፣ ማስጨብጨብ፣ ወዘተ አይደለም፡፡ ማዳን ነው፡፡ (Tadros The Syrian, Orthodox Teaching. P 35) ሰዎች እግዚአብሔርን ዐውቀው፣ በክርስትና ሕይወት ኖረው፣ መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ ማድረግ ነው፡፡ ሐዋርያዊው ሄሬኔዎስ በጻፈው «መድፍነ መናፍቃን» በተሰኘው መጽሐፉ መግቢያ ላይ ማርቅያኖስ የተባለውን ልጁን ሲመክረው «ይህንን የምጽፍልህ ከጥቂቱ ነገር ብዙ ዐውቀህ፣ የእውነትንም ልዩ ልዩ ክፍሎች ተረድተህ፣ የእግዚአብሔር የሆኑትን ነገሮችም ተገንዝበህ፣ የመዳንን ፍሬ እንድታፈራ ነው» ብሏል፡፡ ለዚህ ደግሞ ማሳመን፣ ማሳተፍ እና ማስቀጠል ወሳኞቹ ናቸው፡ ፡ (Irnaeus, On The apostolic preaching. P 29)

ማሳመን፡ ማለት አንድን ሰው በበቂ ኦርቶዶክሳዊ ዕውቀት ማስታጠቅ ነው፡፡ እንዳይናወጽ እና እንዳይወድቅ አድርጎ መትከል ነው፡፡ ነገ መምህሩ እንኳን ባይኖር ተማሪው በራሱ ሊኖር እንዲችል አድርጎ መገንባት ነው፡፡

ማሳተፍ ደግሞ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ነው።

ማስቀጠል ደግሞ እየጾመ፣ እየጸለየ፣ አሥራት እያወጣ፣ ሰንበቴ እየጠጣ፣ እየተማረ፣ እያስተማረ፣ እየጻፈ፣ እየቀደሰ፣ እያስቀደሰ፣ ወዘተ በአገልግሎት እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

በዚህ ጉዞ ውስጥ ሰባኪው ምእመናን በሦስት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ጽናት መለካት አለበት

በዕውቀት የታነጹ እንዲሆኑ፡ ኦርቶዶክሳዊውን ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊት፣ ሕግ፣ የአበው ታሪክ፣ ወዘተ በሚገባ ማወቃቸውንና ለመመስከር በሚያበቃ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ማረጋጥ

በክርስቲያናዊ ኑሮ የታነጹ እንዲሆኑ፡ ክርስቲያኖች በሦስቱ መሠረታውያን እሴቶች ማለትም በጾም ፣ጸሎት እና ምጽዋት፤ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሳተፉ እንዲሆኑ፤ በጎ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው እና ከነቀፋ የጸዱ እንዲሆኑ መከታተል

በልዩ ልዩ ግንኙነቶች ርቱዓን እንዲሆኑ፡ ከማኅበረሰቡ፣ ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከቤተሰባቸው፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው፣ ከንግድ አጋሮቻቸው ወዘተ ጋር በእምነት የተቃኘ፣ በሥነ ምግባር የተኀበኘ አቀራረብ እና አኗኗር እንዲኖራቸው።

በአሁን ዘመን ያሉ ሰባኪያን የሚያስፈልጓቸው አምስት ነገሮች

1/ **የውይይት እና የዕውቀት መገበያያ መርሐ ግብሮች**
ሰባኪያን ያገኟቸውን ዕውቀቶች፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮች እና ያቀዷቸውን ሃሳቦች የሚመካከሩባቸው የዕውቀት ጉባኤያት ያስፈልጋሉ። እነዚህ ጉባኤያት ጥናቶችን፣ ትምህርቶችን፣ ውይይቶችን እና የልምድ ልውውጦችን ማካተት አለባቸው። ይህን የመሰሉ መድረኮች በሀገር አቀፍም ሆነ በአካባቢ ደረጃ ሊመሠረቱ ይችላሉ።

2/ **ተተኪዎችን ማፍራት**
ፍላጎት እና ተነሣሽነት ያላቸውን ማሳወቅ እንጂ የሚያውቁትን ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ ከባድ ነው። በመሆኑም ጥረት፣ ትጋት እና ፍላጎት ያላቸውን መርጦ በግል፣ በቡድን እና በማኅበር በማሠልጠን ማሠማራት ያስፈልጋል። አሁን እንደምናደርገው ሲንቀሳቀሱ የማይታዩትን ለማንቀሳቀስ ከመሞከር፤ የሚንቀሳቀሱትን የሰሉ የበቁ እንዲሆኑ ማድረግ ይሻላል።

3/ **ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም**
ቪዲዮ፣ መቅረጸ ድምፅ፣ ኮምፒውተር ወዘተ የመሳሰሉትን መሣርያዎችን በበቂ ሁኔታ መጠቀም ያስፈልጋል። በተለየም ሰባኪያን የኢንተርኔትን አጠቃቀም አውቀው ብሎ ጎችን በመክፈት፣ ዌብሳይቶችን በማዘጋጀት፣ የኢሜይል ትምህርቶችን በመላክ ወዘተ እንዲሳተፉ መደረግ አለበት።

4/ **መንፈሳዊ ድፍረት እና ንቃት**

ዛሬ ዛሬ መድረኮቻችን ዕውቀት እና ሕይወት በሌላቸው ሰባኪያን እየተሞሉ ይመስላል፡፡ እነዚህ ሰባኪያን ያላቸው አንድ ነገር ቢኖር ድቅድቅ ድፍረት ነው፡፡ ሌሎች በትጎትና ዝም ሲሉ እነርሱ በድፍረት ያልሆኑትን ነን ብለው ወጡ፡፡ ስለዚህም ያልተማሩትንም፣ የማያምኑበትንም ያስተምራሉ፡፡ አሁን ከእውነተኞቹ መምህራን መንፈሳዊ ድፍረት እና አካላዊ እና ሥነ ልቡናዊ ንቃት ያስፈልጋል፡፡ ራሳችሁን በዕውቀት እና በአተያይ አዘምኑ፡፡ የምታውቁትን ሁሉ «እናውቃለን፤ ግን አይጠቅምም ብለን ተውነው» ለማለት ማቻል አለባችሁ፡፡

የትምህርት ደረጃዎቻችንንም እናሻሽል፡፡ ወደፊት ከአብነት ትምህርት ቤት የሚመጡት እያነሡ፤ ከዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የሚመጡት እየበዙ ነው የሚሄዱት፡፡ ስለሆነም አብረናቸው ማደግ ይኖርብናል፡፡ ካልሆነም በማንበብ እና በመከታተል ራሳችንን ማብቃት አለብን፡፡

5/ **በመዋቅር መሥራት ነገር ግን ያለ መዋቅር ማሰብ**

ሥራን በአደረጃጀት፣ በመዋቅር እና በተቋማዊ መንገድ መሥራት መልካም ነው፡፡ ሃሳብን ግን በመዋቅር ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ መዋቅሮች ይረዱናል፤ ያግዙናል እንጂ አይተኩንም፡፡ ስለሆነም ለማንበብም፣ ለመጻፍም፣ ለማስተማርም፣ ለመማርም፣ ለማደግም፣ ለመሻሻልም፣ ወንጌልን ለማስፋፋትም፣ ለማሠልጠንም መዋቅርን እና መዋቅርን ብቻ መጠበቅ የለብንም፡፡ አንዳንዶቻችን በኮሚቴ፣ በማኅበር፣ በቡድን፣ በጽዋ ካልተሰበሰብን ሥራ መሥራት የምንችል አይመስለንም፡፡ እነዚህ ሁሉ ለሥራ መልካም ሊሆኑ ይችላሉ ለማሰብ ግን መሰብሰብ አያስፈልግም፤ መጸለይ እና መጨነቅ እንጂ፡፡ ከመዋቀራችን በፊት ሰው ነበርን፡፡ ስለሆነም መጀመርያ የሰውነታችንን ሥራ እንሥራ፡፡ በጀት ፈልገን፣ ሰው አስተባብረን ለመሥራት እንሞክር እንጂ ሁሉን በዕቅድ እና በበጀት፣ በመመርያ እና በስብሰባ አናድርገው፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

17. ትልቅ ሰው : -እንዲህም ሆነ



ስድስት ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ወጣቶች ወንዶች፡፡ ደግሞ የሚገርመው ሁሉም ቀጠን እና ረዘም ይላሉ፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ሊያገባ ይነሣል፡፡ አምስቱ ጓደኞቹ ደግሞ ሚዜ ብቻ ሳይሆን ሽማግሌም ሊሆኑት ይነሣሉ፡፡ የሽምግልናውን ባህል ጠይቀው፣ አጥንተው እና ተዘጋጅተው የልጅቱ ወላጆች በተቀጠሩበት ቀን ወደ ልጅቱ ቤተሰቦች ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ «ግቡ ግቡ» ይባሉና ገቡ፡፡ «ተቀመጡ» ሲባሉ «አንቀመጥም ጉዳይ አለን» ይላሉ እንደ ባህሉ፡፡ ወላጆች እና ዘመዶችም ገላግለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

እናትም ወደ ጓዳ፣ አባትም ወደ መኝታ ቤት ገቡ፡፡ የቀረው ቤተ ዘመድም የደራ ወሬ ጀመረ፡፡ ጥቂት ጊዜ ጠብቀው ትንሽ ከቤተ ዘመዱ ጋር የሚተዋወቀውን አንዱን ጓደኛቸውን ወደ ጓዳ ላኩት፡፡ እናቲቱን አገኛቸው፡፡ «እማማ ቁጭ በሉ ብላችሁን ጥላችሁን ጠፋችሁኮ» አለ በቀልድ «እስኪመጡ አንዳንድ ነገር ላድርግ ብዬ ነው» አሉት እናቲቱ፡፡ «የምትጠብቁት ሰው አለ እንዴ?» አለ ልጁ፡፡ «ምን ሽማግሌዎቹኮ ቀሩ፤ መጀመርያ የናንተን እንጨርስ መሰል» ይላሉ እናት፡፡

ልጁ ግራ ገባው፤ እንደ ማፈርም አለ፡፡ አሁን ምን ይባላል፡፡ ተመለሰና ለጓደኞቹ ነገራቸው፡፡ ተያዩ እና ተደነጋገጡ፡፡ ከዚያም እንደገና ሁለት ሆነው ወጡ፡፡ «እማማ እኛኮ ነን ሽማግሌዎቹ፤ ሌላ ማን ይጠበቃል?» አሉ እንደ ቀልድ አድርገው፡፡ «እናንተማ ሚዜ ናችሁ፣ ሌላ ሌላ ነገር አለን የምንነጋገረው፤ አሁን አትቸኩሉ ትንሽ ቆዩ» ይላሉ እናትም፡፡ ወጣቶቹ ምን ብለው ያስረዱ፡፡

ቢጨንቃቸው ቀልዱን ተውትና ትንሽ ኮስተር ብለው የመጡበትን ምክንያት አስረዷቸው፡፡ «እንግዲህ እኛ የወጣት ሽማግሌ አይተን አናውቅ፤ ምን ይደረግ ብላችሁ ነው፡፡ እንዲያውም አመጣጣችሁ ግራ ገብቶን ስለ ሠርጉ ልታወሩን መስሎን ነበርኮ፤ ለካ ሽማግሌዎቹ እናንተ ናችሁ ? እኛኮ «ትልልቅ ሰዎች» ነበር የምንጠብቀው» እያሉ ሳቁ፡ አባትዬውም «ትልልቅ ሰው ጠፋና እናንተ መጣችሁ» እያሉ እየተኮሳተሩም፣ እየሳቁም ወጡ፡፡ ሌሎቹም እንዲሁ፡፡

«የልጅ ሽማግሌ ከተገኘ እንግዲህ መልካም ነው» አሉና አጎትዬው ነገሩን አደላደሉት፡፡ አንድ ሁለት ቤተ ዘመዶችም ነገር የሚያስተካክል ወግ ጨማመሩ፡፡

እነዚህ «ሽማግሌዎች» ሁሉም መሐንዲሶች ናቸው፡፡ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሠርተዋል፡፡ በትንሹ አሥር ዓመት በሥራ ዓለም አሳልፈዋል፡፡ የከተማዋን ታላላቅ ሕንፃዎች በማርቀቅ እና በመገንባት አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡ በየቢሮአቸው የሥራ ኃላፊዎች፣ የኩባንያ ባለቤቶች እና ብዙ ሠራተኞችን የሚያስተዳድሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን «ትልቅ ሰው» ተብለው ሊቆጠሩ አልቻሉም፡፡ ለምን?

ደግሞም እንዲህ ሆኗል፡፡

አንዲት ትዳር ከመሠረተች ሰባት ዓመታትን ያስቆጠረች፣ የሁለት ልጆች እናት፣ ከአሥራ ሁለት ዓመታት በላይ በሥራ ያሳለፈች፣ የሁለተኛ ዲግሪዋን የያዘች ፤ በባንክ፣ በማስተማር እና መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት የሠራች ሴት ለኤክስፐርትነት ቦታ ልትወዳደር ሊቃለ መጠይቅ ከጠያቂዎቿ ፊት ተቀምጣለች፡፡ ለቦታው ደግሞ ከሚጠየቀው በላይ የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ አቅርባለች፡፡ በግራ በቀኝ ያሉት ይፈትኗታል ያሉትን ጥያቄዎች እያነሡ ጠየቋት፡፡ መለሰችላቸው፡፡ ወደ ኋላ ወደ ታሪኳ፣ ወደ ፊት ወደ ምኞቷ እየሄዱ ጠየቁ፡፡ ተመለሰላቸው፡፡

በዚህ ጊዜ ከጠያቂዎቹ አንዱ እንዲህ አለ «ይህ ቦታ የትልልቅ ሰዎች ቦታ ነው፡፡ the great men position, specially grey haired men´ ታድያ ላንቺ አይከብድሽም?» አለ፡፡ እንግዲህ በእርሱ ኅሊና «ኤክስፐርት» ሲባል በእድሜ ጠና ያለ፣ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት፣ ኮት እና ሱሪ የለበሰ፣ ከረባት ያሠረ፣ መነጽር የሰካ ትከሻው ሰፊ ያውም ወንድ ነው የሚታየው ማለት ነው፡፡ ትልቅ ሰው ማለቱ ይኽ ነው፡፡

እነዚህ ታሪኮች አንድ ጥያቄ እንድናነሣ ያደርጉናል፡፡ «ትልቅ ሰው» ማነው? የሚል፡፡ በትምህርት፣ በሥራ ልምድ፣ በዕውቀት፣ በአስተሳሰብ ችሎታ፣ በብቃት «ትልቅ ሰው» መሆንና፤ በማኅበረሰቡ ዘንድ «ትልቅ ሰው» ተብሎ ተቀባይነት ማግኘት ይለያያሉ፡፡ ይኼ ልዩነት ደግሞ ዕድሜን፤ መልክን፣ የሰውነት ሁኔታን፣ አለባበስን፣ አንዳንድ ጊዜም ዘርን፣ ሥልጣንን፣ ወዘተ መሠረት ሊያደርግ ይችላል፡፡

አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ ክፍል የተማራችሁባቸውን መጻሕፍት ስታስታውሱ በመማርያ መጻሕፍቱ ላይ ዶክተሩ፣ ሳይንቲስቱ፣ ዳኛው፣ ንጉሡ፣ አርበኛው፣ ነጋዴው፣ቄሱ፣ሼኹ፣ አባት፣ እናት፣መምህር፣ የተሳሉበትን ሥዕል እስኪ በዓይነ ኅሊናችሁ ቃኟቸው፡፡ ረዘም ብለው ትከሻቸው ደልደል ያለ፤ በዕድሜ ጠና ያሉ፤ ፀጉራቸው ወደ ውስጥ ገባ ገባ ያለ፤ ጉንጯቸው ትንሽ ሞላ ያለ፤ ዓይነት ሰዎች ናቸው፡፡ በቁመታቸው አጠር፣ በሰውነታቸው ቀጠን፣ ፀጉራቸው ሞላ፣ በእድሜያቸው ወጣት፣ ልጅ እግር ሰዎች የሚሳሉት ኳስ ሲጫወቱ፤ ዳቦ በወተት ሲበሉ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ አትክልት ሲያጠጡ፣ ሐኪም ቤት ገብተው ሲታከሙ፣ የመኪና መንገድ ሲሻገሩ፣ ዛፍ ሲቆርጡ ወዘተ ነው፡ ፡

እንግዲህ የማኅበረሰባችን «የትልቅ ሰው አመለካከት» ከዚህ ይጀምራል ማለት ነው፡፡ አንድ ጓደኛዬ ከልጁ ጋር ትምህርት ቤት ሄዶ ዳይሬክተሯን ሲያነጋግራት አልተግባቡም፡፡ «ለነገሩ እኛ ወላጅ እንዲያመጣ ነው የነገርነው፤ ስለዚህ ከወላጆቹ ጋር እንነጋገራለን» ብላው እርፍ፡፡ ያንን ሲያዩት ልጅ የሚመስል ቀጭን እና ለግላጋ ወጣት ማን ከወላጅ ይቁጠረው፡፡ የልጁ ታላቅ ወንድም ነበር የመሰላት፡፡

ይህ አመለካከት በአንድ በኩል ሰዎችን በማንነታቸው ሳይሆን በውጫዊ ቁመናቸው ብቻ ቦታ እንድንሰጥ አድርጎናል በሌላ በኩል ደግሞ ተገቢ ሰዎች በተገቢ ቦታ እንዳይቀመጡ አግዶብናል፡፡

የክልሎች የአዳጊ ወጣቶች ሻምፒዮና ይባልና ውድድር ይደረጋል፡፡ ውድድሩ ለአዳጊ ወጣቶች ነው፡፡ ተተኪዎችን ለማፍራት ተብሎ፡፡ አወዳዳሪዎቹ ግን ያለ «ትልልቅ ሰዎች» በሌሎቹ አያምኑም፡፡ ስለዚህ እድሜ እያስቀነሱ «ትልልቆቹን» ተጫዋቾች በአዳጊዎቹ ምትክ ይዘዋቸው ይመጣሉ፡፡ በአዳጊዎቹ አይተማመኑም፡፡ በዚህ ምክንያት አዳጊዎቹም ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ፤ በራሳቸው እንዳይተማመኑ ሆነው ተቀርፀዋልና፡፡ አገሪቱም ያለ ተተኪ ትቀራለች፡፡

በሩጫው ዓለምም ቢሆን በዚህ እና በዚያ ውድድር ተገኝቶ «ሚኒማ» ያላሟላ ለዓለም ዐቀፍ ውድድር አይቀርብም ይባላል፡፡ «ትልልቆቹ» በእነዚህ ገንዘብ አልባ በሆኑ የሀገር ውስጥ ውድድሮች ተገኝተው ላብ አይጨርሱም፡፡ ገና ለታዋቂነት ያልበቁ አዳዲስ ሯጮች በእነዚህ ቦታዎች ተገኝተው «ሚኒማ» ማሟላት ብቻ ሳይሆን ሌላ «ሚኒማ»ም ይፈጥራሉ፡፡ ዓለም አቀፍ ውድድሩ ሲመጣ ግን እነዚያ አዳዲስ ጀግኖች እንዲቀሩ ይደረጉና «ታላላቆቹ» ይላካሉ፡፡ ያለ «ታላላቆች» ውጤት ይመጣል ብሎ የሚጠብቅ የለምና፡፡

ሌላው ቀርቶ በሀገራችን የፖለቲካ ሂደት ውስጥ አንዱ ችግራችን ይኸ «ትልቅ ሰው» ለምንለው ነገር ያለን አመለካከት ነው፡፡ እስኪ አስተውሉ፡፡ በፖለቲካው መድረክ ከስድሳ ስድስት ጀምሮ ያሉት ተዋንያን ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አዘውትረን ተመሳይ ፊት ነው የምናየው፡፡ ከአንዳንዶቹ በቀር ወጣት መሪ አናይም፡፡ እነዚያው ሰዎች ደግሞ ወይ በሀብት የገነኑ፣ በእድሜ የሸመገሉ፣ አንዳች የትምህርት ወይንም የውትድርና መሳርግ ያላቸው እንዲሆኑ እንፈልጋለን፡፡ ለብስለታቸው፤ ለዕውቀታቸው፣ ለአመራር ችሎታቸው እና ለጀግንነታቸው ከምንሰጠው ቦታ ይልቅ ለአካላዊ፣ እድሜያዋ እና መሳርጋዊ ሁኔታዎች የምንሰጠው ቦታ ይበልጣል፡፡ ስለዚህም ፊልሙ ሲቀያየር እንኳን እነዚያኑ ተዋንያን ብቻ ነው የምናየው፡፡

ቴሌቭዥናችሁን ከፍታችሁ የአክሲዮን ገበያውን እስኪ ተመልከቱ፡፡ «እንዲህ ያለ ኩባንያ ተመሠረተ፤ አክሲዮን እየሸጠ ነው፤ መሥራች ሁኑ» እየተባለ ይተዋወቃል፡፡ ሃሳቡን ያመነጩት፣ አስተባባሪዎች እና መሥራቾች በጠረጴዛ ዙርያ ተደርድረው ፈገግ እያሉ ይታያሉ፡፡ «ትልልቅ ሰዎች»፡፡ በእድሜ ጠና ያሉ፤ ትከሻቸው ለኮት የሚያመች፤ መነጽር ያደረጉ፣ ሰውነታቸው ሞላ ሞላ ያለ፣ ሲፈርሙ እጃቸው ወዝ የጠገበ «ትልልቅ ሰዎች»፡፡ መጀመርያ ነገር ወጣቶቹ ቢሰባሰቡ የሚያምናቸው የለም፤ ወጣቶቹ ቢቀላቀሉም የሚቀበል አይገኝም፡፡ ሀብትም ከ«ትልልቅ ሰዎች» ውጭ ይገኛል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ኧረ ምን ወጣቶቹን ብቻ ሴቶቹስ የአክሲዮን መሥራች እንዳይሆኑ ማን ነው ያገዳቸው? የግድ ለሴቶች ተብሎ ብቻ መቋቋም አለበት ?

አንድ በሚሊዮኖች የሚያንቀሳቅስ ኩባንያ ባለቤት የሆነ ጓደኛዬ ለአንድ ጉዳይ ማመልከቻውን ይዞ አንድ ቢሮ ይሄዳል፡፡ ጸሐፊዋ ደብዳቤውን ትቀበልና ካነበበችው በኋላ «ለዚህ ጉዳይ ራሳቸው የድርጅቱ ባለቤት ቢመጡ ነው የሚሻለው» ትለዋለች፡፡ እርሱ ቀልደኛ ነገር ነበርና እሺ ብሏት ይወጣና ተመልሶ ወዲያው ይመጣል፡፡ «ምነው የረሳኸው ነገር አለ» ትለዋለች፡፡ «ባለቤቱ ይምጡ ስለተባለ ነው» ይላታል፡፡ ግራ ገብቷት አየችው፡፡ «ታድያ ለምን አትነግራቸውም» አለች ጸሐፊዋ፡፡ «ሰምቼ ነው የመጣሁት» አላት፡፡ ይበልጥ ግራ ስትጋባ እየሳቀ «ባለቤቱኮ እኔ ነኝ» ብሎ አረዳት፡፡ ምን ታድርግ እርሷ «ትልቅ ሰው» ነዋ የጠበቀችው፡፡

ሌላው ቀርቶ አንዳንድ ማኅበረሰብ «ትልቅ ሰው» ለሚለው መዓርግ የሰጠው አለባበስ አለ፡፡ ጉዳይ ለማስፈጸም ወደ አንድ ቢሮ ስትሄዱ ኮት፣ ሱሪ እና ከረባት ሽክ አድርጋችሁ፣ የመኪና ቁልፍ እያሽከረከራችሁ፣ ሞባይል ጆሯችሁ ላይ ገጥማችሁ፣ መነጽራችሁን አናታችሁ ላይ ሰክታችሁ፣ ድምፃችሁን ጎርነን እያደረጋችሁ ካልሄዳችሁ፤ ያለበለዚያም የእድሜያችሁን ልክ የሰውነታችሁ ገጽታ ካላንፀባረቀባችሁ፤ ከ«ትልቅ ሰው» የሚቆጥራችሁ አታገኙም፡፡ ሴት ከሆናችሁም ሙሉ ቀሚስ፣ ወይንም ኮት እና ቀሚስ፣ ያለበለዚያም የአበሻ ቀሚስ ካላደረጋችሁ፤ «የኔ ልጅ» እያላችሁ ካልተናገራችሁ፣ ነጠላ ቢጤ ደረብ ካላደረጋችሁ፣ ስትሄዱ ዘገም ካላላችሁ ማን ከ«ትልቅ ሰው» ይቆጥራችኋል፡፡

አንዳንድ ሱቅ ገብታችሁ ወደድ ያለ ልብስ እና ጫማ ስትጠይቁኮ ቁመናችሁን እና አለባበሳችሁን፣ እድሜያችሁን እና ነገር ዓለማችሁን ተመልክተው «ይወደድብሃል/ይወደድብሻል» ይሏችኋልኮ፡፡ በእነርሱ ቤት እናንተ ያንን ዕቃ ለመግዛት የሚበቃ ገንዘብ ልትይዙ አትችሉም፡፡ የእነርሱን የ«ትልቅ ሰው» መመዘኛ አታሚሉማ፡፡ ቤት እና መኪና ስትገዙማ ሁኔታችሁን በማየት ብቻ ደላላ ናቸው ወይንም ሊያደክሙን ነው ብለው የሚገምቷችሁ ብዙ ናቸው፡፡ እናም አንዳንድ ጊዜ «የለም፣ አይሸጥም፣ ባለቤቶቹ የሉም፣ተሸጧል» ሲሏችሁ የ«ትልቅ ሰው» መመዘኛ ስለማታሚሉ ልትገዙት አትችሉም ማለታቸው መሆኑንም ተረዱ፡፡

የእድር ስብሰባ ላይኮ ዘመናዊውን ትውልድ ያጣነው መክፈል አቅቶት አይደለም፡፡ ነገር ግን እርሱን ቁም ነገረኛ ብሎ የሚቆጥረው ስለማይኖር፤ እድሩም የ«ትልልቅ ሰዎች» እድር ስለሆነ ነው፡፡ በየሠፈሩ ያሉ እድሮች በዚህ «የትልቅ ሰው» አሠራራቸው ከቀጠሉ ወራሽ ማግኘታቸውን እጠራጠራለሁ፡፡

እናም እስኪ «ትልቅ ሰው»ነትን ለዕውቀት፣ ለችሎታ፣ ለብቃት ሰጥተን ትርጉሙን እንቀይረው፡፡ ልጆቻችንንም በዚሁ መልኩ እንቅረፃቸው፡፡ እኛም «ሰው ፊትን ያያል» የሚባለውን ትተን ሊታዩ የማይችሉትን የምናይበትን መንገድ እንፈልግ፡፡ ያለበለዚያ the big man theory ሀገርንም ትውልድንም ይገድላል፡፡

18. ስማችሁ የለም

በሰማያዊው ዙፋን ዘንድ አንድ ውሳኔ ተላለፈ፡፡ «እነዚህ የኢትዮጵያ ሰዎች ሃይማኖተኞች ናቸው፡፡ ስለዚህም ዓለም ከማለፉ በፊት አስቀድመው ተጠርተው ዋጋቸውን ሊቀበሉ ይገባል» የሚል፡፡ አንድ ሊቀ መልአክ እልፍ አእላፍ መላእክትን አስከትሎ ከሰማይ ሲወርድ ታየ፡፡ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሰዎችንም ሁሉ ለሰማያዊ ፍርድ ሰበሰባቸው፡፡ ወዲያውኑ በመንግሥተ ሰማያት በር ላይ ሁለት ዓይነት ሰልፎች ታዩ፡፡ አንደኛው ሰልፍ ረዥም፤ ሌላኛው ሰልፍ ግን አጭር ነበር፡፡ ረዥሙ ሰልፍ ባለበት ቦታ ገበሬዎች፣ ወዛደሮች፣ የዕለት ሥራ ሠራተኞች፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ሕፃናት፣ ሊስትሮዎች፣ የቤት ሠራተኞች፣ ሾፌሮች፣ መሐንዲሶች፣ ሐኪሞች፣ አስተማሪዎች፤ ማን ያልተሰለፈ አለ፡፡ ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ መንግሥተ ሰማያት የመግቢያ ካርድ ማግኘት ቻሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ ሲመለከቱ በአጭሩ ሰልፍ በኩል የተሰለፉት የልብ ልብ ተሰማቸው፡፡ መጀመርያውኑ ለብቻቸው ሰልፍ የሠሩት ከሕዝብ ጋር ላለመደባለቅ እና ላለመምታታት ብለው ነበር፡፡ እንዴት ሲያስተምሩት፣ ሲያስመልኩት፣ ሲያስሰግዱት፣ ሲያሳልሙት፣ ከኖሩት ሕዝብ ጋር አብረው ይሰለፋሉ? መጀመርያ ነገር እነርሱ ያስተማሩት ሕዝብ መንግሥተ ሰማያት ከገባ እነርሱ የማይገቡበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ወደፊትም ቢሆን በመንግሥተ ሰማያት ለየት ያለ የከብር ቦታ ሊጠብቃቸው ስለሚችል ለየት ብለው መሰለፋቸው ተገቢ ነው፡፡ ይህንን እያሰቡ እና እያወሩ እያለ አንድ መልአክ ወደ እነርሱ ሰልፍ መጣ፡፡ ተሰላፊዎቹ በኩራት ገልመጥ ገልመጥ አሉ፡፡ እንዲያውም «ከመካከላችን ማን ይሆን ቀድሞ የሚገባው» የሚለው ነገር ሊያጨቃጭቃቸው ነበር፡፡ አንዳንዶች በተከታዮቻቸው ብዛት፣ አንዳንዶች በነበራቸው መንፈሳዊ ሥልጣን፣ አንዳንዶች ባገኙት የካሴት እና የመጽሐፍ ገቢ፣ ሌሎችም በሕዝቡ ዘንድ በነበራቸው ተደናቂነት፣ የቀሩትም ደግሞ በንግግር እና በድምጽ ችሎታቸው እየተማመኑ እኔ እበልጣለሁ እኔ እቀድማለሁ ሲባባሉ መልአኩ «እናንተ እነማን ናችሁ?» የሚል ያልተጠበቀ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡ ሁሉም መልአክነቱን ተጠራጠሩት፡፡ አገር ያከበራቸውን፣ሕዝብ ያረገደላቸውን፣እነርሱን ለማየት እና ለመንካት አዳሜ የተንጋጋላቸውን፣ በየፖስተሩ፣ በየካሴቱ፣ በየመጽሐፉ፣ በየመጽሔቱ «ታዋቂው» እየተባሉ ሲቀርቡ የኖሩትን፤ ሰይጣን ያወጣሉ፣ መንፈስ ይሞላሉ፣ ጠበል ያፈልቃሉ፣ እየተባሉ ሲያርዱ ሲያንቀጠቅጡ የኖሩትን፤ ሲዘምሩና ሲያስተምሩ ወፍ ያወርዳሉ የተባሉትን፤ ገንዘብ ከፍሎ መንፈሳዊ ቦታ ተሳልሞ ለመምጣት ሕዝብ ቢሮአቸውን ደጅ ሲጠናቸው የኖሩትን እነዚህን ጉምቱ ጉምቱ ሰዎች የማያውቅ መልአክ እንዴት ሊኖር ቻለ? ተጠራጠሩ፡፡

«ለምንድን ነው ለብቻ ሰልፍ የሠራችሁት? ለምን ከሕዝቡ ጋር አልተሰለፋችሁም?» መልአኩ ይበልጥ የሚገርም ጥያቄ አመጣ፡፡ ተሰላፊዎቹ እርስ በርሳቸው ተያዩ፡፡ ከመካከል አንድ በነገሩ የተበሳጨ ሰባኪ «እንዴት እንደዚህ ያለ ጥያቄ በዚህ በመንግሥተ ሰማያት በር ላይ እንጠየቃለን፤ እስካሁንም ተሰልፈን መቆየት አልነበረብንም፡፡ እኛን ለመሆኑ የማያውቅ አለ? ስንት ሕዝብ ያስከተልን ሰባኪያን፤ ስንት ሕዝብ የፈወስን አጥማቂዎች፣ ስንት ሕዝብ ያስመለክን አስመላኪዎች፣ ስንቱን ያስረገድን ዘማሪዎች፤ ስንቱን የታደግን ፈዋሾች፣ ስንቱን የመራን የእምነት መሪዎች፤ ስንቱን በባዶ እግሩ ያስኬድን ባሕታውያን፤ ስንቱን ለገዳም ያበቃን መነኮሳት፤ ሕዝብ ተሰብስቦ የሾመን «ሐዋርያት»፤ እንዴት እነማን ናችሁ ተብለን እንጠየቃለን?» ሁሉም በጭብጨባ ደገፉት፡፡

መልአኩ «መልካም፤ የስም ዝርዝሩን ላምጣውና ስማችሁ እዚያ ውስጥ ካለ ትገባላችሁ» ብሎ አንድ ትልቅ ሰማያዊ

መዝገብ ይዞ መጣ፡፡ «እኛ ካልተጻፍን እና የኛ ስም ከሌለ ታድያ የማን ስም በዚህ መዝገብ ውስጥ ሊኖር ነው፡፡ ይኼው እኛ የማናውቀው ሰው ሁሉ እየገባ አይደለም እንዴ?» አለ አንድ አስመላኪ በንዴት፡፡ «ልክ ነህ፤ እናንተ የማታውቁት፣ ፈጣሪ ግን የሚያውቀው፤ እናንተንም የማያውቅ ፈጣሪውን ግን የሚያውቅ ብዙ ሕዝብ አለ ወዳጄ» አለው መልአኩ መዝገቡን እየገለጠ፡፡

«የሁላችሁንም ስም ማስታወስ ስለምችል ሁላችሁም ስማችሁን ንገሩኝ» አላቸው፡፡ ከወዲህ ወዲያ እየተንጫጩ ስማቸውን ከነማዕረጋቸው ነገሩት፡፡ መልአኩ ከፊቱ ላይ የጎዘንም የመገረምም ገጽታ ይነበብበታል፡፡ ቀስ እያለ የስም ዝርዝሩን ያይና ገጹን ይገልጣል፤ ያይና ገጹን ይገልጣል፤ ያያል፣ ገጹን ደግሞ ይገልጣል፡፡ ብዙ ሺ ገጾችን ገለጠ፣ ገለጠ፣ ገለጠ፤ ማንንም ግን አልጠራም፡፡ ከዚያ ይባስ ብሎ የመጨረሻውን የመዝገቡን ሽፋን ከቀኝ ወደ ግራ መልሶ ከደነው፡፡ «ምንም ማድረግ አይቻልም፤ የማናችሁም ስም መዝገቡ ላይ የለም» ብሎ መልአኩ በጎዘን ሲናገር «ምን?» የሚል የድንጋጤ ጎበረ ድምጽ ተሰማ፡፡ «የማናችሁም ስም ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገቡት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የለም» አለ መልአኩ በድጋሜ፡፡

«ሊሆን አይችልም» «የተሳሳተ መዝገብ ይዘህ መጥተህ እንዳይሆን» «ወደ ሲዖል የሚገቡትን መዝገብ ይሆናል በስሕተት ያመጣህው» «እኛኮ አገልጋዮች ነን፤ የከበረ ስም እና ዝና ያለን፤ ስንኖርም፣ መድረክ ላይ ስንቀመጥም፣ ድሮም ልዩ ነን፤ የኛ መዝገብ ልዩ መሆን አለበት» «እስኪ ሌላ መልአክ ጥራ» ብቻ ሁሉም የመሰለውን በንዴት እና በድንጋጤ ይሰነዝር ጀመር፡፡ ሌሎች መላእክትም ሌሎች ዓይነት መዝገቦችን ይዘው መጥ ተው እያገላበጡ ፈለጉ፡፡ የነዚያ «የከበሩ አገልጋዮች» ስም ግን ሊገኝ አልቻለም፡፡
«እኛኮ የታወቅን ነን» አሉ አንድ አጥማቂ፡፡ «ሕዝብማ ያውቃችሁ ይሆናል መዝገብ ግን አያውቃችሁም» አላቸው መልአኩ፡፡ «እንዴት እኮ እንዴት? » አሉ በዋና ከተማዋ ታዋቂ የነበሩ ፓስተር፡፡ «ሊሆን አይችልም፤ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም» አሉ አንድ ሼሕ፡፡ «የዚህን ምክንያት ማወቅ ትፈልጋላችሁ? » አለ አንዱ መልአክ፡፡ «አዎ» የሚል ጎበረ ድምጽ ተሰማ፡፡
«ምክንያቱኮ ቀላል ነው፡፡ ሌሎችን መንፈሳዊ እንዲሆኑ ታስተምሩ ነበር እንጂ እናንተ መንፈሳውያን አልነበራችሁም፡፡ እናንተ ድራማ ስትሠሩ ነውኮ የኖራችሁት፡፡ መድረክ ላይ ወጥታችሁ መንፈሳዊ ድራማ ትሠሩ ነበር፡፡ ልብሳችሁ፣ ንግግራችሁ፣የእጅ አጣጣላ ችሁ፣ ጸሎታችሁ፣ የተዋናይ ነበርኮ፡፡ የማትሆኑትን ነበር ስታስተምሩ የነበራችሁት፡፡

ለመሆኑ ለሕዝቡ የምታስተምሩትና እናንተ የምትመሩበት የሃይማኖት መጽሐፍ አንድ ነው? ወይስ ይለያያል? እናንተ የምድር ቤታችሁን በብዙ ሺ ብሮች እየገነባችሁ ሰዎች ግን ቤታቸውን ረስተው የሰማዩን ቤት ብቻ እንዲያስቡ ታስተምሩ ነበር፤ ሕዝቡን ስጡ ስጡ እያላችሁ እናንተ ግን አምጡ አምጡ ትላላችሁ፡፡ ሕዝቡን በባዶ እግሩ እያስኬዳ ችሁ እናንተ የሚሊዮኖች መኪና ትነዱ ነበር፤ ሕዝቡን እያስጾማችሁ፣ እናንተ ግን ጮማ ትቆርጡ ነበር፤ ታስተምሩት የነበረውኮ ያጠናችሁትን ቃለ ተውኔት እንጂ የምታምኑ በትን እና የምትኖሩትን አይደለም፡፡ እናንተኮ ግብር የማትከፍሉ ነጋድያን ነበራችሁ፡፡ እናንተ ከገዳም ወደ ከተማ ትገባላችሁ፤ ሰውን ግን ከከተማ ወደ ገዳም ትወስዳላችሁ፡፡
እርስ በርሳችሁ እንደ ውሻ እየተናከሳችሁ ለማስተማር እና ለመዘመር ሲሆን፣ ለማስመ ለከና ለማሰገድ ሲሆን፣ የአዞ እንባ እያነባችሁ መድረክ ላይ ትወጣላችሁ፡፡ እርስ በርሳ ችሁ ከበርሊን ግንብ የጠነከረ የመለያያ ግንብ እየገነባችሁ

ሕዝቡን ግን አንድ ሁኑ፣ ተስ ማሙ፣ ታቻቻሉ እያላችሁ ታስተምራላችሁ፡፡ ለመሆኑ ይህ ሁሉ ፓስተር፣ሰባኪ፣ ዘማሪ፣ መነኩሴ፣ባሕታዊ፣ ዑላማ፣አሰጋጅ፣አስመላኪ፣ የእምነት አባት፣እያላት ነው ኢትዮጵያ እንዲህ ስሟ በድህነት እና በጦርነት የሚነሣው? ሙስና እና የዘመድ አሠራር፣ ጠባብ ነት እና ዘረኛነት፣ስግብግብነት እና ማጭበርበር፤ ከፋት እና ምቀኛነት የበዛው ይኼ ሁሉ አገልጋይ እያላት ነው? ለመሆኑ እናንተ ባትኖሩ ኖሮ ይህች ሀገር ከዚህስ የከፋስ ምን ትሆን ነበር?

ለመሆኑ ተከፋፍላችሁ፣ተከፋፍላችሁ፣ተከፋፍላችሁ መጨረሻችሁ ምንድን ነው? ለመሆኑ አንድ ባትሆኑ እንኳን ለመግባባት፤ ለመገነዛዘብ፤ ቢያንስ ላለመጠላላት፤ ቢያንስ በጠላትነት ላለመተያየት፤ ላለመወጋገዝ፤ ላለመነቃቀፍ አስባችሁበት ታውቃላችሁ? የሀገራ ችሁ ፖለቲከኞች እንኳን የሥነ ምግባር ደንብ ይኑረን ሲሉ እናንተ ለመሆኑ የሥነ ምግባር ደንብ አላችሁ? ሻማ ሲበራ ዋናው ጨለማ ከሻማው ሥር ነው የሚገኘው፡፡ ሌላውን ታበራና ሻማዋ ለራሷ ጨለማ ትሆናለች፡፡ እናንተስ? በየቤተ እምነታችሁ ያለውን ችግር መቼ ፈታችሁ ነው ሕዝብ እናስተምራለን የምትሉት? ለናንተ ሁልጊዜ ጠላታችሁ ሌላ እምነት የሚከተለው ብቻ ነው? ለራሳችሁ ግን ከራሳችሁ በላይ ጠላት የለውም፡፡ ሕዝቡኮ አንዳችሁ ሌላውን ስትተቹ፤ አንዳችሁ በሌላው ስትሳለቁ፤ አንዳችሁ በሌላው ላይ ነጥብ ስታስቆጥሩ፤ አንዳችሁ የሌላውን ኃጢአት ስትዘረዝሩ መስማት ሰልችቶት ነበር፡፡ «ታድያ እኛ ያስተማርነው ሕዝብ እንዴት ጸደቀ? » የሚል አንድ ድምጽ ተሰማ፡፡ «ሕዝቡማ ምን ያድርግ በምትናገሩት እናንተ አልተጠቀማችሁም እንጂ ሕዝቡማ ተጠቀ መበት፡፡ ሕዝቡማ በሁለት መንገድ ተጠቀመ፡፡ እናንተን እያየ «እንደነዚህ ከመሆን አድነን» በማለቱ ተጠቀመ፤ የምትሉትን እየመዘነ በማድረጉም ተጠቀመ፡፡ እንደ እናንተ ቢሆን ኖሮማ ማን ይተርፍ ነበር፤ አጫርሳችሁት ነበርኮ፡፡ የዚህ ሕዝብ ጉብዝናው ይሄ አይደል እንዴ፤ ሙዙን ልጦ መብላቱ፡፡ ሲገዛው ከነልጣጩ ነው፤ ሲበላው ግን ልጦ ነው፡፡ የእናንተንም ትምህርት የሰማው መላጥ ያለበትን ልጦ እየጣለ ነው፡፡

እናንተ ለዚህች ሀገር መድኃኒት ነበራችሁ፡፡ ነገር ግን ጊዜው እንዳለፈበት መድኃኒት በሽታዎቿ ሆናችሁ፡፡ የሚከተል እንጂ የሚድን፤ የሚያደንቅ እንጂ የሚለወጥ፤ የሚያወቅ እንጂ የሚሠራ፣ የሚመስል እንጂ የሚሆን መች አፈራችሁ? ሕዝቡን የናንተ ተከታይ አድርጋችሁት ቀራችሁ፡፡ ያንን ጠባያችሁን ይዛችሁ እዚህ ከገባችሁ ደግሞ የገባውን ታስወጡታላችሁ ተብሎ ይፈራል፡፡ የሚያለቅሱ ድምጾች እየበረከቱ መጡ፤ አንገታቸውን ያቀረቀሩት ብዙዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹን ፀፀቱ ያንገበግባቸው ነበር፡፡ ሌሎቹም ራሳቸውን ጠሉት፡፡ «አሁን ምንድን ነው የሚሻለን» አሉ አንድ ፓስተር፡፡ «የዚህን መልስ እኔ መስጠት አልችልም፤ ፈጣሪዬን ጠይቄ መምጣት አለብኝ» አለና መልአኩ ትቷቸው ሄደ፡፡ ከደቂቃዎች በኋላ ሲመለስ እንዲህ የሚል መልስ ይዞ ነበር፡፡ «አንድ እድል ይሰጣችሁ፡፡ ትስተካከሉ እንደሆነ አንድ እድል ይሰጣችሁ፡፡ ሕዝቡን ተውትና ራሳችሁን አስተካክሉት፤ ያኔ ሕዝቡ በራሱ ጊዜ ይስተካከላል»

ድንገት ሁሉም መሬት ላይ ተገኙ፡፡ እነሆ አሁን በየቤተ እምነቱ ያሉት በዚህ መንገድ የተመለሱት ናቸው፡፡

19. ሥጋ በል ዕጽዋት

ብዙዎቻችን ሥጋ በል እንስሳት መኖራቸውን እናውቃለንም ተምረናልም። እናም አይገርመንም። ሥጋ በል ዕጽዋት መኖራቸውን ግን ብዙ ጊዜ ሰምተንም ተምረንም ስለማናውቅ ከመገረም አልፎ «እንዴት ሊሆን ቻለ?» የሚል ጥያቄንም ይፈጥርብናል። ሥጋ በል እንስሳትስ በከርናቸው ደቁሰው፣ በጥርሳቸው ዘንጥለው ይበላሉ። ለመሆኑ እነዚህ ሥጋ በል ዕጽዋት እንዴት አድርገው ነው ሥጋ የሚበሉት? ደግሞስ በምን ሆዳቸው ይፈጨታል? እያለ ጥያቄው ይቀጥላል።

ሥጋ በል ዕጽዋት አፈጣጠራቸው እንደ ዕጽዋት አኗኗራቸው እንደ አራዊት ነው። ነፍሳቱ የሚያውቋቸው በተክልነታቸው አብበው ሲለመልሙ ነው። በውስጣቸው ግን የአውሬነት ጠባይ ስላለ የዋኾቹ ነፍሳት አትክልት ናቸው ብለው ሲጠጓቸው ረኾም ቅጠላቸውን ጥቅልል ያደርጉና ነፍሳቱን እምሽክ አድርገው ይበሏቸዋል።

ከእስስት እና ከእንሽላሊት ያመለጡ ነፍሳት እንኳን በእነዚህ ሥጋ በል ዕጽዋት በቀላሉ ይጠቃሉ። የንብ ጥበብ፣ የቢራቢሮ ውበት፣ የጢንዚዛ ጩኸት፣ የተርብ ኃይለኛነት፣ የትንኝ ተናዳፊነት፣ አይበግራቸውም።

ለምን?

እነዚህ ሥጋ በል ዕጽዋት መልካቸውም፣ ቁመናቸውም፣ አኳሃናቸውም፣ እንደ ዕጽዋት ነው። የሚኖሩትም ከዕጽዋት ጋር ከዕጽዋት መካከል ነው። እንደ ዕጽዋት አበባ አላቸው፤ ቅጠል አላቸው፤ ግንድ አላቸው፤ ሥር አላቸው፤ ልምላሜ አላቸው። እንደ ዕጽዋት ከመሬት ተነሥተው ወደ ላይ ያድጋሉ፤ አፈር እና አየር ይወስዳሉ፤ በሁለመናቸው ዕጽዋትን ይመስላሉ።

ነገር ግን የዋኾቹ ነፍሳት ሊያውቁት የማይችሉ አንድ ድብቅ ጠባይ አላቸው። እርሱም ለሌላ ያልተገለጠ የአውሬነት ጠባይ በውስጣቸው አለ። ይህንን ጠባይ እንኳንስ ነፍሳቱ ሰውም ያወቀው በቅርቡ ነው። በባህላዊው ዕውቀት ሥጋ የሚበላ አውሬ መኖሩን እንጂ ሥጋ የሚበላ ተክል መኖሩን የሚናገር ታሪክም፣ ተረትም፣ ወግም፣ አባባልም የለም።

ይህ ጠባያቸው ነው እንግዲህ ሳይደክሙ አድፍጠው ግዳያቸውን በእጃቸው ላይ እንዲጥሉ ያደረጋቸው። የዱር አራዊት አንድ ጊዜ አውሬ መሆናቸው በሁሉም ዘንድ ስለታወቀ፤ በአራዊት እንበላለን ብለው የሚሰጉ እንስሳት ብዙዎች ናቸው፤ እያንዳንዱ እንስሳም ከእነርሱ የሚያመልጥበትን የየራሱን ጥበብ በዘመናት ብዛት አከማችቷል። ያደፍጣል፣ ያመልጣል፣ ይሸውዳል፣ ይመሳሰላል፣ ቀለሙን ይቀይራል፣ ጊዜ ይመርጣል፤ ይናደፋል፤ ይቧጭራል፤ ከባሰበትም በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ይጋደላል እንጂ በቀላሉ እጁን አይሰጥም።

ይህንን የግዳዮቻቸውን ጠባይ ያወቁት አራዊትም ለመብላት የሚያስቧቸውን እንስሳት የሚያጠቁበት አያሌ ዘዴ ዘይደዋል። ኃይል፣ ጉልበት፣ ጥበብ ይጠቀማሉ። ጊዜ መርጠው አድብተው ያጠቃሉ። ግዳይ እንዲህ በቀላሉ አይጣልምና ብዙ ድካም እና ልፋት አለባቸው።

ሥጋ በል ዕጽዋት ግን ይህ ሁሉ የለባቸውም። ጠባያቸውን አሳምረው፣ ዕጽዋትን መስለው፤ እስከ ጊዜው ድረስ አውሬነታቸውን በልምላሜያቸው እና በአበባቸው ሠውረው ጸጥ ይላሉ። ነፍሳቱ እንደ ለመዱት አበባ ለመቅሰም እና ቅጠልን ለመብላት፣ ለእረፍት እና ለመዝናናት ወደ እነርሱ ሲጠጉ ግን ተክልነታቸው ያበቃና አውሬነታቸው ብቅ ይላል። የገባ አይወጣም። የተያዘ አያመልጥም።

አሁን አሁን ከሰዎች መካከል ማኅበረሰቡን እያስቸገሩ ያሉት ሥጋ በል ዕጽዋት ናቸው፡፡

እነዚህ ሥጋ በል ዕጽዋት በመልካቸው፣ በቁመናቸው፣ በንግግራቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በአቀራረባቸው ፍጹም ትኑታን፣ ደጋጎች፣ ቅኖች፣ ታዛጦች፣ አስተዋዮች፣ ታማኞች፣ የተማሩ፣ የተመራመሩ ይመስላሉ፡፡ ውስጣቸው ግን ተቃራኒ ነው፡፡

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ አንድ እንግሊዛዊ ነበረ፡፡ እንግሊዝ ጀርመንን መምታት አለባት እያለ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይናገራል፡፡ የእንግሊዝ መንግሥት የሚወስደውን ማንኛውንም ርምጃ ይደግፋል፡፡ መቼም የእንግሊዝኛ ንግግሩ ለጉድ ነው፡፡ ከቃላት፣ ከሰዋስው፣ ከአባባል አንዳች አያዛንፍም፡፡ አገሬው የሚሳሳታቸውን የተለመዱ ስሕተቶች እርሱ ጨርሶ አይሳሳ ታቸውም፡፡ ስለ እንግሊዝ እና ስለ እንግሊዛዊነት የርሱን ያህል ሰባኪ እና ተቆርቋሪ አልነበረም፡፡ አንዳንዴ መንግሥት ያመናቸውን ስሕተቶች እንኳን እርሱ ስሕተት አይደሉም ብሎ ይከራከራል፡፡

ታድያ የእንግሊዝ የስለላ ድርጅት ተጠራጠረው፡፡ ተጠራጠረውና ክትትሉን በጥብቅ ቀጠለ፡፡ ከብዙ ምርመራ በኋላ ታድያ የጀርመን ሰላይ ሆኖ አገኘው፡፡ አለምክንያት እንደዚያ ለምለም ተክል አልሆነም፡፡ ውስጡ ሥጋ በል ቢሆን ነው፡፡

እየደጋገመ ወደድኩሽ ይለኛል

ማርያምን ይሺ ሰው ልቡ ይጠላኛል

ያለችው የገጠር ዘፋኝ ይህንን የእንግሊዝ ሥጋ በል ዕጽ ጉዳይ ቀድማ ሳትደርስበት የቀረች አይመስለኝም፡፡

ስለ ነጻነት ይሰብካሉ፣ ስለ ሴቶች መብት ይከራከራሉ፣ ስለ ትዳር ይቆረቆራሉ፣ ስለ ሕፃናት ይራራሉ፤ ሃይማኖትን ያጠብቃሉ፤ ምግባርን ያከርራሉ፤ ገንዘብን ይጠላሉ፤ ክብርን ይንቃሉ፤ ዝናን ይጠየፋሉ፤ ሥልጣንን ይርቃሉ፡፡ ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት ግን አምነውበት፣ ወድደውት እና ውስጣቸው ከዚህ ተሠርቶ አይደለም፡፡ ጊዜ እስኪያገኙ ድረስ ብቻ ነው፡፡

«አንገት ደፊ፣ ሀገር አጥፊ» የሚለው አባባል ማኅበረሰባችን እነዚህን ሥጋ በል ዕጽዋት በመጠኑም ቢሆን እንደ ደረሰባቸው ያመለክታል። ሁሉም አንገት የደፉ ሰዎች አገር ያጠፉ ማለት አይደለም። ነገር ግን ተክል መስለው ለስልሰው ውስጣቸው አውሬ የሆኑ ሰዎች አውሬ መሆናቸውን በግልጥ ካሳዩ ሰዎች ይበልጥ ይጎዳሉ ማለት ይመስለኛል።

ፀጉሩን ቆጣጥሮ፣ ያረጀ እና የተቀዳደደ ልብስ ለብሶ፤ ፊቱ ኮስተር፤ ዓይኑ ደፍረስ፤ ጡንቻው ፈርጠም፣ ጣቱ ረዘም ያለ፤ ሎቲ አንጠልጥሎ ሠንሠለት ጠቅልሎ የሚመጣን ጎረምሳ ማን ያምነዋል? የቻለ ይሸሸዋል፤ ያልቻለ በዝምታ ያሳልፈዋል፤ ከባሰም ይተናኮለዋል። እርሱን የሚያምን፣ የሚቀበልና የሚያስተናግድ አይገኝም። አለባበሱን ሽከ አድርጎ፤ ፀጉሩን አሳምሮ፤ ልብሱን ቀያይሮ፤ ጫማውን ወልውሎ፤ የፊልም አክተር መስሎ ቢመጣ ግን «ኖር» ባዩ «ልተዋወቅህ» ባዩ ብዙ ነው። የሚጠራጠረው ቀርቶ «መጠርጠር» የሚለውን ቃል በእርሱ አጠገብ የሚያወራ አይገኝም።

ግን «በቆብ ውስጥ ያለን ኃጢአትና በኮት ላይ ያለን ጽድቅ» ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው። ይባላል። ይበልጥ መጠንቀቅም ገጽታው የሚያስፈራውን አይመስለኝም። እርሱማ ሁሉም ያፈጥጥበታል። ከባዱስ በለስላሳው የዕባብ ቆዳ ውስጥ ያለው መርዝ ነው።

እስኪ አስተውሉ። በሀገራችን አያሌ ሕፃናት የተደፈሩት በጠላቶቻቸው እና በሚፈሩት ሰው፣ አይደለም። በጣም በሚወዷቸው፣ በሚቀርቧቸው፣ በሚያምኗቸው ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች ለሕፃናቱ ከወላጆቻቸው በላይ ደግ እና ቅርብ ሆነው ነው ድርጊቱን የሚፈጽሙት። ድርጊቱን ፈጽመው ለመሠወር የሚያስችላቸውም ሥጋ በል ዕጽዋት በመሆናቸው ነው። ገጽታቸው፣ አለባበሳቸው፣ ንግግራቸው እና በማኅበረሰቡ የሚታወቁበት ጠባይ በውስጣቸው ከደበቁት ጠባይ በተቃራኒው እና እጅግ በደግነት የተሞላ ነው። እናም ይህንን አስነዋሪ ተግባር ይፈጽማሉ ብሎ ማንም አይጠረጥርም። አሁን ዕጽዋትን ሥጋ ይበላሉ ብሎ ማን ይጠረጥራል?

እንደ እባብ ብልህነትን ትተው እንደ ርግብ የዋሕ ብቻ ይሆኑ እጎቶቻችን ብዙ ጊዜ የሚደፈሩት በየሠፈራቸው በሚያስፈራሯቸው፣ በሚዝቱባቸው እና ይጎዱናል ብለው በሚያስቧቸው ጎረምሶች አይደለም። እንዲያውም እነዚህ ጎረምሶች ማኅበረሰቡ በክፉ ጠባያቸው ስለሚያውቃቸው ይጠነቀቃቸዋል፤ ሊያደርጉት ሲያስቡም ይነቃባቸዋል። ፖሊስም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በዓይነ ቁራኛ ይጠብቃቸዋል።

አደገኞቹስ ሥጋ በል ዕጽዋት ናቸው፡፡ ሰላምተኞች፤ ትኑቶች፤ ለእኅቶቻችን ተቆርቋሪዎች፤ ከአፋቸው የማር ወለላ ጠብ የሚል፤ ተናግረው አሳማኞች፤ አለባበሳቸው እና አካሄዳቸው በጨዋነት የተሞላ፤ ሲቀርቧቸው ክፉ ነገሮችን ሁሉ አውጋዦች፤ ኃጢአትን እና ወንጀልን እንኳን ሊፈጽሙ፣ ቃሉን ሰምተው የሚያውቁ የማይመስሉ እነዚህ ናቸው የእኅቶቻችን ጠላቶች፡፡

መቼም ደግን ነገር የሚጠላ የለም፡፡ ርግቦቹ እኅቶቻችን ለፍቅር የሚመች፤ ለኑሮ የሚደላ፤ ለትዳር የሚሆን ጨዋ የተማረ፤ እንኳንስ እኔን ሊያሰናክል ከመሰናከል የሚጠብቀኝ፤ ብረት መዝጊያ የሚሆን አገኘን ይሉና በቅጠሉ ሊያርፉ፤ ከአበባው ሊቀስሙ ጠጋ ይሏቸዋል፡፡ ያን ጊዜ ነው የዕጽዋቱ ሥጋ በልነት ብቅ የሚለው፡፡ «ሰው የሚጠላውን ኃጢአት ደጋግሞ ይሠራዋል» ይል ነበር ጋሽ ግርማ፡፡ በአፉ እየደጋገመ ያለ ቦታውና ያለ ጊዜው የሚያወግዝ ሰው፣ ያንን ነገር ይፈልገዋል ማለቱ ነው፡፡

እነዚያ የተጠቁ እኅቶች ለማን ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ሥጋ በል ዕጽዋት የሚታወቁት በተክልነታቸው እንጂ በሥጋ በልነታቸው አይደለማ፡፡ ማን ያምናል፡፡ እርሷ ከምትናገረው ይልቅ እርሱ የሚናገረው ይታመናል፡፡ ይህ ተክል ሥጋ በልቷል ብትል ማን ያምናታል?

ከጋብቻ በኋላ የቤት አልጋ የውጭ ቀጋ፤ የቤት እሾክ የውጭ መልአከ፤ የቤት ንፉግ የውጭ ደግ የሆኑ የትዳር አጋሮችኮ ከጋብቻ በፊት እንደዚያ አልነበሩም፡፡ ወንዱም ስትጠሪኝ አቤት ስትልኪኝ ወዴት እላለሁ፤ ከልጅሽ በታች ከሠራተኛሽ በላይ ሆኜ እታዘዝሻለሁ ሲል ነበር፡፡ ሴቷም ብትሆን እንደ ምንጣፍ ተነጥፌ፤ እንደ እናት ተንሰፍስፌ፤ እንደ ጉዝጓዝ ተጎዝጉዤ፣ እንደ ሎሌ ታዝዤ ብላ ነበር የገባችው፡፡ ዛሬ ዛሬ አንዳንዶቹ ከትዳር በፊት የኖሩትንና በትዳር ውስጥ ያሉበትን ሁኔታ ሲያስተያዩት ፊልም ያዩ እንጂ የነበሩበት አይመስላቸውም፡፡

«ትዳር ምን እዳ ነው ትዳር ምን እዳ ነው» ተብሎ ሲዘፈን እንዴት እንዲህ ይባላል? ይሉ የነበሩት ሰዎች ዛሬ ዛሬ እነርሱ ራሳቸው ግጥም እየጨማመሩ መዝፈን ጀምረዋል፡፡ ሥጋ በል ዕጽዋት ገጥመዋቸው፡፡

በአንዳንድ አስነዋሪ ተግባራት ውስጥኮ በሁለት እጅ የማይነሱ ታላላቅ ሰዎች፣ ባለ ሥልጣናት፣ የሃይማኖት መምህራን፣ ታዋቂ ሰዎች ሲገኙ ፖሊስ እና ኅብረተሰብ የሚደነግጠው ዕጽዋት ሥጋ ይበላሉ ብሎ ስለማያስብ ነው፡፡ በግብረ ሰዶማዊነት፤ በአደንዛዥ ዕጽ ንግድ፤ በሴተኛ አዳሪነት መስፋፋት፤ በሕፃናት ንግድ፤ በኮንትሮባንድ ሽያጭ፤ ጉቦ በመቀበል እና በማቀበል፤ በሕገ ወጥ መንገድ ሰዎችን ወደ ውጭ በመላክ ወንጀሎች ውስጥኮ ብዙ ሥጋ በል ዕጽዋት ይገኛሉ፡፡

ስፖርት እናሠራለን፤ ሙዚቃ አለማምደን ታዋቂ እናደርጋለን፤ ፊልም አሠርተን እናሸልማለን ብለው የዋሆችን እየቀረቡ የሚያታልሉትኮ ሥጋ በል ዕጽዋት ናቸው፡፡ ሲያዩት ቀጣሪ ነው፣ ሥራ አስኪያጅ ነው፣ የተከበረ ሰው ነው፡፡ ውስጡ ሥጋ በል ነው፡፡ ሲያዩት የፊልም ባለቤት፤ የፊልም ዳይሬክተር ነው ውስጡ የእጎቶቻችንን ሥጋ የሚበላ ሥጋ በል ዕጽ ነው፡፡ ሲያዩዋት እንደ እናት ርግብግብ፣ እንደ እኅት ቅሩብ ናት ነገር ግን ወንድሞቻችንን እና እኅቶቻችንን ለርካሽ ዓላማ የምታሰልፈው ሥጋ በል ዕጽ እርሷ ናት፡፡

ዛሬ ዛሬኮ የንግዱን ሚዛን ያዛቡትና ማጭበርበርን እና ሙስናን ባህል እንዲመስል ያደረጉት ብዙዎቻችን የምንጠራጠራቸው ዓይነት ነጋዴዎች አይደሉም፡፡ እነርሱማ መውጫ መግቢያቸው፣ መብያ መጠጫቸው የታወቀ ነው፡፡ የችግሩ ዋና ፈጣሪዎች «አያደርጉም፤ ደግሞ ምን ጎድሏቸው፤ ኧረ እነርሱ ይህንን አይሠሩም» እየተባለ የሚነገርላቸውና ሲያዩዋቸው እንደ ተክል አረንጓዴ፣ እንደ አበባ ውብ፣ ውስጣቸው ግን ሥጋ በል የሆኑት ናቸው፡፡

ቤተ እግዚአብሔርን የሚዳፈረው ምሥጢሩን የሚያውቀው ነው ይባላል፡፡ አንዳንድ ጊዜኮ የእምነት ሰዎች በሚባሉት ዘንድ የሚሠራውን ግፍ፣ በደል፣ ጭካኔ፣ ተንኮል፣ ኃጢአት ያህል በተራው ሕዝብ ሲሠራ አይታይም፡፡ ለቤተ መቅደስ ቅርብ ሆነው ከእግዚአብሔር የራቁ ሰዎች ሥጋ በል ዕጽዋት ናቸው፡፡ አለባበሳቸው፣ አዋዋላቸው፣ አነጋገራቸው፣ መዓርጋቸው፣ ሥልጣናቸው፣ እንደ አትክልት የለመለመ፣ አረንጓዴ፣ ሰላም እና ፍቅር የሞላበት፣ ፍትሕ እና ርትዕ የሰፈነበት ይመስላል፡፡ ወደ ውስጣቸው ሲገቡ፣ በጥላቸው ሥር ሲያርፉ፤ አበባቸውን ለመቅሰም ሲጠጉ ግን የሚያዩት ነገር እንደ ሎጥ ሚስት አድርቆ የሚያስቀር ነው፡፡

አሁን ችግሩ እነዚህን ሥጋ በል ዕጽዋት እንዴት እንለያቸው? የሚለው ነው፡፡ እኔ የዚህ ምሥጢር አልተገለጠልኝም፡፡ የተገለጠለት ካለ ግን ምናለ ቢገልጥልን፡፡

20. ቅዱስ ያሬድ ማነው?

20.1. ያሬድ ክብር አነሰው

ገና ጥንት ያኔ . . . . . .
ሰውም ሳይሰፍርባት አሜሪካ ታውቃ፣
ገና ጥንት ያኔ . . . . . .
እንዲህ ሳትሠለጥን አውሮፓም ተራቅቃ፣
ገና ጥንት ያኔ . . . . . .
ዓለም፣ ከእንቅልፏ ሳትነቃ፣

እነ ሞዛርት እና እነ ቤት ሆቨን፣
የዜማን ምልክት ገና ሳይነግሩን፣
ያሬድ አንተ ነበርክ
የዜማን ቅማሬ የሠራህልን፣
. . . . . .
መንኮራኩር ሠርተው
ጨረቃ ላይ ወጥተው፣
አፈር ስላመጡ ዓለም ተደነቀ፣
ወሬው ተሟሟቀ፣
ከምዕራብ ተነሥቶ ከምሥራቅ ዘለቀ፣
ከሺ ዓመት በፊት ግን
ያሬድ የተባለ አንደ ሊቅ ነበረ፣
ጨረቃንም አልፎ ጠፈር ተሻገረ፣
ሐሳስን ሰንጥቆ ሰማያት ውስጥ ገብቶ፣
አስደናቂ ዜማ ከመላእክት ሰምቶ፣
አኩስም ላይ አዜመው
ከጽናጽል እና ከመቋሚያ አስማምቶ፣

ግና ምን ያደርጋል . . . . . .
ከጨረቃ አፈር የሚበልጥ ነገር፣
ጨረቃም ላይ ካለው የሚበልጥ ምሥጢር፣
ያሬድ ይዞ መጥቶ፣
የሚናገር እና የሚያደንቅ ጠፍቶ፣
ዓለም አያውቀውም አልሰማውም ከቶ፣

ያሬድ ግን ቅዱስ ነው
ያሬድ ምሁር ሊቅ፣
ያሬድ መተርጉም ነው

ምሥጢር የሚያረቅቅ፣

ያሬድ ፈላስፋ ነው

ያሬድ ባለ ቅኔ፣

ያሬድ ባለ ዜማ

የዜማው መጣኔ፣

ያሬድ ሐጋጊ ነው

ሥርዓት የሠራ፣

ያሬድ መምህር ነው

ዕውቀትን ያበራ፣

ያሬድ ቀማሚ ነው

ብሉይ ከሐዲስ፣

ያሬድ ሰባኪ ነው

ነፍስ የሚመልስ፣

ያሬድ አመልካች ነው

ኖታን የፈጠረ፣

ያሬድ መናኒ ነው

በጸሎት የኖረ፣

እነ ቸርችል፣ ፑሽኪን እነ ካኒንግሃም

አደባባይ መንገድ ሲሰየምላቸው፣

ያሬድን ስላጡት አዘነ ልባቸው፣

ነቢይ በሀገሩ አይከብርም እንዲሉ፣

እኒህ ኢትዮጵያውያን እጅግ ይሞኛሉ፣

የእጃቸውን ንቀው ሌላ ያከብራሉ፣

ብለው አዘኑብን በፈጸምነው ግፍ፣

ያሬድን ረስተን ሌላውን ስናቅፍ፣

አይበቃም ወይ ታድያ የሞኝነት ኑሮ፣

መቅረት አለበት ወይ ታሪኩ ተቀብሮ፣

ይተረክ ታሪኩ ይነገር ዝናው፣

ይጠና ይመርመር ይታወቅ ሥራው፣

መወያያ ይሁን በየሚዲያው፣

መማማርያ ይሁን ትውልድ ያድንቀው፣

ያለበለዚያ ግን

ያለፉትን ንቀን ወደፊት ብንሄድ፣

እኛንም የሚንቅ ይመጣል ትውልድ።።

የቅዳስ ያሬድ አባቱ አብድዩ /ይስሐቅ/ እናቱ ክርስቲና /ታውክልያ/ ይባላሉ /በሌላም በኩል አባቱ እንበረም እናቱ ትውልያ ይባላሉ የሚል ታሪክም አለ፡፡/ የትውልድ ሥፍራው አክሱም ነው፡፡ የተወለደው በ505 ዓ.ም/ ሚያዝያ 5 ቀን የሚል አለ/ ሲሆን በተወለደ በ7 ዓመቱ ወላጅ አባቱ ስለሞተ እናቱ የአክሱም ጽዮን መምህር ለነበረው ለአጎቱ ለጌዴዎን እያስተማረ እንዲያሳድገው ሰጠችው፡፡ ከአባ ጌዴዎንም ዘንድ እየተማረ ለ25 ዓመት ተቀመጠ፡፡

ሆኖም ቃለ እግዚአብሔር የመቀበል ችሎታው ደካማ ስለሆነ በጣም ያዝን ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ከትምህርት ድክመቱ የተነሣ አጎቱ በጨንገር ቢገርፈው በዚህ ተበሳጭቶ ትምህርቱን ትቶ ሄደ፡፡ በመንገድም ሲጓዝ ውሎ በቀትር ደክሞት ከዛፍ ሥር ዐረፈ፡፡ በዚያ ጊዜ አንድ ትል ከዛፉ ላይ ያለውን ፍሬ ለመብላት ስድስት ጊዜ በመውደቅና በመነሣት ዛፉ ላይ ለመውጣት ሞክሮ በሰባተኛው ሰተት ብሎ ወጥቶ ሲበላ ተመለከተ፡፡ እርሱም በፈጸመው የብስጭት ተግባር በመጸጸት ተመልሶና አጎቱን ይቅርታ ጠይቆ ትምህርቱን ቀጠለ፡፡ አጎቱም ተደስቶ ዓይነ ልቡናውን ያበራለት ዘንድ እያለቀሰ ፈጣሪውን ለመነለት፡፡ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ለቅዱስ ያሬድ ዕውቀትን ገልጾለት መጻሕፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን ዐወቀ፡፡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይህን በተመለከተ

ሰላም ለያሬድ ስብሐተ መላእክት ለሕዋጼ
እንተ አዕረገ በልቡ ጎሊና መንፈስ ረዋጼ
ለትምህርተ መጽሐፍ ገብአ እምጎበ ኮነ ነፋጼ
በብዙኀ ፃማ ዘአልቦ ሐጻጼ
መልዕልተ ዕፅ /ኮሞ/ ነጸሮ እንዘ የዐርግ ዕጼ

የሚል ዐርኬ ደርሰውለታል፡፡ ይህን አርኬ የድጓ መምህራን ጠዋት ጉባኤ ሲዘረጉ ተማሪዎቻቸውን ያስደርሷቸዋል፡፡

ከዚያም በኋላ ወደ መምህሩ ተመልሶ ትምህርቱን ቀጠለና ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ አጠና፡፡ ሚመተ ዲቁናን ቀጥሎም ሚመተ ቅስናን ተቀበለ፡፡ ቅዱስ ያሬድ ግእዝ፣ እዝልና አራራይን ከሦስት ወፎች/መላእክት በወፎች ተመስለው/ መማሩን ሊቃውንት ይገልጣሉ፡፡ እነዚህ በወፍ የተመሰሉ መላእክት እየመሩት ወደ አርኣያም አርጎ የ24ቱን ካህናተ ሰማይ ዜማ ከተማረ በኋላ ጠዋት በ3 ሰዓት በአክሱም ቤተ ክርስቲያን «ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሣረረ ወበዳግመ አረአዮ ለሙሴ ዘከመ ይግበር ግብራ ለደብተራ» ብሎ አዜመ፡፡ ይህን ዜማ የደረሰበት ወሩ ታኅሳስ ቀኑም ዕለተ ሰኞ ነው ይባላል፡፡ የቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያ ዜማው «አርያም» በመባል ይታወቃል፡፡ ይህም ከመላእክት ወይም ከሰማይ የተገኘ መሆኑን ለማጠየቅ የተሰጠው ስም ነው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ይህንን ዜማ በተመስጦ ሲያዜም ንጉሡ፣ንግሥቲቱ፣ ጳጳሱ መኳንንቱና ካህናቱ ወደ አኩስም ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው መጥተው በአድናቆት ያዳምጡት ነበር፡፡ ምክንያቱም ገደለ ቅዱስ ያሬድ እንደሚገልጥልን ከዚያ በፊት በውርድ ንባብ ከሚደረግ ጸሎትና መንፈሳዊ አገልገሎት በቀር ይህን የመሰለ ዜማ አልነበረምና፡፡

የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ብሉይን ከሐዲስ ያስማማ፣የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ የያዘ፣ እንዲሁም ለልዑል እግዚአብሔር፣ለእመቤታችን፣ለቅዱሳን መላእክት፣ ለጻድቃንና ለሰማዕታት ተገቢ የሆነውን ምስጋና የያዘ ነው፡

፡ ከዚህም በላይ ለአራቱ የዓመቱ ወቅቶች እንዲስማማ አድርጎ ለበጋ፣ ለክረምት፣ ለመጸውና ለጸደይ እንደሚሆን አድርጎ ከፋፍሏቸዋል፡፡ ለየበዓላቱም ተስማሚ ድርሰት መድቦላቸዋል፡፡ ይህንን ድርሰቱን በግእዝ፣ በእዝልና በአራራይ ዜማ ያዘጋጀው ሲሆን ለነዚህም ስምንት የዜማ ምልክቶች ሠርቶላቸዋል፡፡

የቅዱስ ያሬድ ዜማ አንዴት ሁሉንም ይመስጥና ወደ አርያም በመንፈስ ይወስድ እንደ ነበር ለማስረዳት በገድሉም በሌሎችም መጻሕፍት የተመዘገቡ ታሪኮች አሉ፡፡ አንድ ቀን ንጉሥ ገብረ መስቀል፣ንግሥቲቱ፣ ጳጳሱ፣ ካህናቱና ምእመናኑ በተሰባሰቡበት ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ሲያዜም ንጉሡ በመመሰጡ የተነሣ በመሰቀል ተሰላጢኑ ጫፍ የቅዱስ ያሬድን እግር ወጋው፡፡ ነገር ግን ማንም አላወቀም ነበር፡፡ ቅዱስ ያሬድ መዝሙሩን ሲፈጽም ንጉሡ መስቀል ተሰላጢኑን ቢያነሳው የቅዱስ ያሬድ ደሙ ፈሰሰ፡፡ ንጉሡ በዚህ ደንግጦ ለዚህ ካሣ ይሆን ዘንድ የፈለግከውን ጠይቀኝ እሰጥሃለሁ ብሎ ቃል ገባለት፡፡ ቅዱስ ያሬድ ግን ከዚህ ዓለም ተለይቶ በምናኔ መኖርና መዝሙሩንም በሚገባ ማዘጋጀት እንደሚፈልግ ገለጠ፡፡ ምንም እንኳን አኩስምን ለቅቆ መውጣቱ ንጉሡን ቅር ቢያሰኘውም ቃሉን አንድ ጊዜ በመስጠቱ ምንም ሊያደርገው አልቻለም፡፡ ቅዱስ ያሬድም ከዚህ በኋላ አኩስምን ለቅቆ ወደ ስሜን ተራራ ጸለምት መጓዙ ይነገራል፡፡

በጐንደር ፎገራ በሚባል ሥፍራ ቅዱስ ያሬድ ጣዕም ያለው ዜማውን ሲዘምር ተጠምደው የሚያርሱ በሬዎች ድምፁን እየሰሙ ገበሬውን ሥራ ስለ አስፈቱት በዚህ ተናዶ ቅዱስ ያሬድን በጅራፍ እንደ ገረፈው ይነገራል፡፡ ቦታውም «ወርቀ ደም´ እየተባለ እስከ ዛሬ ይጠራል፡፡ ወርቃማና ንጹሕ ደሙ የፈሰሰበት ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ያዘጋጀበት ዘመን ከ540-560 ዓ.ም. ባለው ጊዜ መሆኑ ይነገራል፡፡ ዜማውን ካዘጋጀ በኋላ 11 ዓመት አስተምሯል፡፡ በእርሱ ዘመን ተሰዓቱ ቅዱሳን በሃይማኖት ችግር ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጥተው ስለ ነበር ቅዱስ ያሬድ ከአንዱ ከአባ ጳንጠሌዎን የውጭውን ሀገር ቤተ ክርስቲያን ባሕልና ሥርዓት ይጠይቅ ነበር፡፡ በጆሮ የሰማውንም በዓይን ለማየት ሁለት ጊዜ ሮም የተባለችውን የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ጐበኘሁ ይላል፡፡ «ወሪድየ ብሔረ ሮሜ ለቤተ ክርስቲያን ርዒከዋ» እንዲል፡፡ የታሪክ ምሁሩ ሥርግው ሀብለ ሥላሴ ለቁስጥንጥንያ ዜማ መነሻው ቅዱስ ያሬድ ነው ይላሉ፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚያደርጉት የቁስጥንጥንያን ዜማ የደረሰው ሊቅ ዜማውን አገኘው የሚባለው የቅድስት ሶፍያን ቤተ ክርስቲያን ሲዞር ከሰማው ዜማ ነው፡፡ ይህ ዘመን ደግሞ ቅዱስ ያሬድ ከተነሣበትና ወደ ሮሜ ሄድኩ ካለበት ዘመን ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እናም ምናልባት ያ ሰው ዜማውን የሰማው የቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያንን እየዞረ ሲዘምር ከነበረው ከቅዱስ ያሬድ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ፡፡ Ancient and medival Ethiopian History/

ቅዱስ ያሬድ ማትያስና ዮሴፍ በተባሉ የአቡነ አረጋዊ ደቀ መዛሙርት መሪነት ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ወጥቶ ከጻድቁ ጋር በመገናኘትና የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ እያደነቀ ዙሪያውን ከዞረ በኋላ «ያድክዋ ወርኢኩ ሥነ ሕንፃሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን» ሲል ዘመረ፡፡ በዚያም ለአንድ ሳምንት ሰንብቶ ሄዷል፡፡

ቅዱስ ያሬደ ከአቡነ አረጋዊ እና ከዐፄ ገብረ መስቀል ጋር በመሆን በወሎ፣ በጎንደር፣ በሸዋ እና እስከ ጋሞጎፋ ብርብር ማርያም ድረስ በመሄድ አስተምሯል፡፡ አንዳንድ መረጃዎች የዐርባ ምንጭን ታሪክ ከቅዱስ ያሬድ፣ ከአቡነ አረጋዊ እና ከዐፄ ገብረ መስቀል ታሪክ ጋር ያያይዙታል፡፡ ሦስቱም ብርብር ማርያምን ለማየት ሄደው በነበረ ጊዜ በዛሬው ዐርባ

ምንሥ አካባቢ ሠፍረው ነበር፡፡ በዚያ ቦታ ለወታደሩ የሚበቃ የሚጠጣ ውኃ በመጥፋቱ አቡነ አረጋዊ ጸልየው መሬቱን በመስቀል ቢመቱት ዐርባ ውኃዎች ፈለቁ ይባላል፡፡

ዐፄ ገብረ መስቀል የጣና ቂርቆስን ቤተ ክርስቲያንን በሚያሠራ ጊዜ በዚያ ቦታ ለሁለት ዓመት ተቀምጦ ድጓውን በማስተማሩ ምልክት የሌለው ድጓው እስከ ዛሬ በገዳሙ ይገኛል፡፡ ቀጥሎም የዙር አባን ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ወደ ጋይንት በተጓዙ ጊዜም በዚያ ሁለት ዓመት ዝማሬ መዋሥዕት የተባለ ድርሰቱን አስተምሯል፡፡ ይህ ቦታ እስከ ዛሬ የዚህ ትምህርት ማስመስከሪያ ነው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ከዚያ በኋላ ወደ አከሱም ተመልሶ በመደባይ ታብር በተባለ ቦታ ቅዳሴያትን በዜማ አዘጋጅቷል፡፡ ይህ ቦታ ከአከሱም 15 ኪ.ሜትር ርቆ ይገኛል፡፡ ከዚህ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ አኩስምን ተሰናብቶ ለመሄድ ወደ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ገባና «ቅድስት ውብጽዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን ማዕርገ ሕይወት» እያለ አንቀጸ ብርሃን የተባለውን ድርሰቱን ሰተት አድርጎ አዘጋጀው፡፡ ይህንን ድርሰት ሲያዜም አንድ ክንድ ያህል ከምድር ከፍ ብሎ ይታይ ነበር ይባላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ በሰሜንና ወገራ፣ አገውና በጌምድር እየተዘዋወረ አስተምሮ ከሰሜን ተራራዎች ውስጥ እየጸመና እየ[ለየ በብሕትውና ለብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ በሰሜናዊ ምሥራቅ በኩል ባለው በጸለምት ዋሻ ውስጥ በ571 ዓ.ም ግንቦት 11 ቀን ተሠውሯል፡፡ ይህ ቦታ በተለምዶ የሰሜን ተራሮች በሚባለው ወስጥ የሚገኝ ከፍተኛና ብርዳማ ቦታ ነው፡፡

ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ዜማን ከማበርከቱም ሌላ በትምህርት ሂደትም አስተዋጽዖ አድርጓል፡ ፡ የድጓን፣ የጸመ ድጓን የዝማሬ መዋሥዕትንና የቅዳሴን ትምህርት ከማስተማሩም በላይ ለቅኔ ትምህርትም መሠረት ጥሏል፡፡

መቼም ለኢትዮጵያ ሊቃውንት ትልቁ ጥፋታቸው ኢትዮጵያዊ መሆናቸው ነው፡፡ ይህን ጊዜ አውሮፓዊ ወይንም አሜሪካዊ ቢሆን ኖሮ በስሙ የማይጠራ ነገር ባልነበረ ነበር፡፡ መንገዱ፣ትምህርት ቤቱ፣ ኮሌጁ፣ አደባባዩ፣ ምኑ ቅጡ፡፡ እኛም የፈረንጅ ነገር ስለምንወድ በየመማርያ መጽሐፋችን በተማርነው ነበር፡፡ ኢትዮያዊ ሆነና ተጎዳ፡፡ የመጀመርያዋን ዜማ የዘመረባት ቦታ እንኳን እንደ ዋዛ በድንጋይ ታጥራ ምልክት እንኳን የላትም፡፡ ከያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት በቀር ሀገሪቱ በስሙ ምንም አልሰየመችለትም፡፡ ያሬድ ግን በዓለም ላይ የመጀመርው የዜማ ኖታ/ ምልክት/ ባለቤት ነው፡፡ አሁን ለኛ ከጵኽኪን እና ከያሬድ የቱ ይቀርበናል፡፡ ከቸርችል እና ከያሬድ የቱ ይጠቅመናል፤ ከደጎል አደባባይ እና ከያሬድ አደባባይ የቱ ያኮራናል፤ ከቤኒን መንገድ እና ከቅዱስ ያሬድ መንገድ የቱ ይሻለናል፡፡

በርግጥ አሁን አሁን ጅምሮች ይታያሉ፡፡ የቅዱስ ያሬድን ዩኒቨርሲቲ በአኩስም ከተማ ለመገንባት ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራ ተጀምሯል፡፡ የከተማው ምክር ቤትም ቦታ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኗል፡፡ ያድርሰን ብቻ፡፡

እስኪ አንድ ሃሳብ ላቅርብ፡፡ እናንተም ጨምሩበት፡፡ በ2005 ዓም የቅዱስ ያሬድን 1500ኛ ዓመት ለማክበር በያላችሁበት በበጎ ፈቃደኛነት ኮሚቴ አቋቁሙ፡፡ ሌላ ሰው እንዲመጣ እባካችሁ አትጠብቁ፡፡ ቄብ ሳይት ሥሩ፤ ፌስ ቡክ ግሩፕ ክፈቱ፡፡ በየቦታው የቅዱስ ያሬድ 1500ኛ ዓመት በዓል ኮሚቴ የሚል አደራጁና በዐውደ ጥናት፣ በአውደ ርእይ፣ በዝማሬ፣ እናክብረው፡፡ የዜማ ሊቃውንት ዝማሬ አዘጋጁ፤ ሰዓሊዎች የሥዕል ዐውደ ርእይ አዘጋጁ፡፡ የዜማ ባለሞያዎች ስለ ቅዱስ ያሬድ ዜማ ለዓለም የሚያስተዋወቅ መርሐ ግብር ዘርጉ፡፡ ነገ አይደለም ዛሬ እንጀምር፡፡ ከብረ

በዓሉ በ2004 ሚያዝያ 5 ቀን ይጀመርና በ2005 ግንቦት 11 ቀን ይፈጸም፡፡ እስኪ ሌላም ሃሳብ ጨምሩበትና አንዳች ታሪክ እንሥራ፡፡ እንዴው ግን ግንቦት 11 የዓመቱ የዜማ ቀን ቢሆን ምን ይመስላችኋል?

21. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ

ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ታላቅ ቦታ የያዘ ኢትዮጵያዊ ሊቅ፡፡ ዐፄ ዳዊት ደግሞ «ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ» ብለውታል፡፡ አባቱ ሕዝበ ጽዮን እናቱ አምኃ ጽዮን ይባላሉ፡፡ እንደ ድርሳነ ዑራኤል አባቱ በመጀመርያ የትግራይ በኋላ ደግሞ የሰግላ «ጋሥጫ» ገዥ ነበረ፡፡ እንደ ገድሉ ደግሞ ጠቢብና የመጻሕፍት ዐዋቂ፤ የእግዚአብሔር ወዳጅና በቤተ መንግሥት በነበረችው ድንኳን «ሥዕል ቤት» ከሚያገለግሉ ካህናት ወገን ነበር፡፡ የመካከለኛውን ዘመን ታሪክ የመረመርን እንደሆነ ሁለቱም ምንጮች ስለ አንድ ጉዳይ የተለያዩ መረጃዎች የሚሰጡ ሳይሆኑ አይቀርም፡፡

ለምሳሌ በንጉሥ ላሊበላ ዘመን የአራቱ የኢትዮጵያ ግዛቶች አስተዳዳሪዎች የታላላቅ አድባራት ገዥዎች ነበሩ፡፡ ከዚህም በላይ የአንዳንድ ገዳማት አበምኔቶችና በቤተ መንግሥት የሚያገለግሉ ካህናት አንድ አንድ አውራጃ ወይም ወረዳ ይሾሙ ነበር፡፡ በመሆኑም የአባ ጊዮርጊስ አባት ከህነትን ከገዥነት የደረበ ሳይሆን አይቀርም፡፡ የአባ ጊዮርጊስን እናት ገድሉ «ወእሙኒ እም ስዩማነ ወለቃ» ይላታል፡፡ ይህም በወለቃ /የዛሬው ደቡብ ወሎ፣ ቦረና / ከነበሩ መኳንንት ወገን መሆኗን ያመለክታል፡፡

አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በ1357 ዓ.ም ነው፡፡ /ገድሉ ያረፈበትን ዘመንና ያረፈው በተወለደ በ60 ዓመቱ መሆኑን ስለሚገልጥ ከዚያ በመነሣት የሚገኝ ነው፡፡/ ወላጆቹ ልጅ ስለሌላቸው ዘወትር እያዘኑ ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ የተወለደው በቅዱስ ዑራኤል አብሳሪነት መሆኑን ድርሳነ ዑራኤል ይተርክልናል፡፡

አባ ጊዮርጊስ የመጀመርያውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማረው ከአባቱ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምክንያቱም አባቱ የመጻሕፍት ሊቅ መሆኑን ስንመለከትና ገድሉም አባ ጊዮርጊስን በተመለከተ «ወሶበ ልሕቀ ሕቀ ወሰዶ ኀበ ጳጳስ ወሴሞ ዲያቆን» የሚለውን ስናጤነው አባቱ የመጀመርያውን ደረጃ ትምህርት ካስተማረው በኋላ ከጳጳሱ ዘንድ ወስዶ ዲቁና አሹሞታል ማለት ነው፡፡ ገድሉ ዲቁና የሰጡትን ጳጳስ ስም አይነግረንም፡፡ ነገር ግን በ1341 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የመጡትና እስከ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት መጀመርያ የነበሩት አቡነ ሰላማ መተርጉም ሳይሆኑ አይቀርም፡፡

ዲቁና ከተቀበለ በኋላ ለትምህርት ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ተላከ፡፡ ወደ ሐይቅ የገባው በዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት /1374-1306 ዓ.ም/ መሆኑን ገድሉ ይገልጣል፡፡ ሐይቅ እስጢፋኖስ የተለያዩ ሊቃውንት የሚገኙባት፣በብዙ መጻሕፍት የተሞላችና ዙሪያዋን በሐይቅ በመከበቧ የተማሪን ሃሳብ ለማሰባሰብ አመቺ የሆነች ቦታ ናት፡፡ አባ ጊዮርጊስ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርት አልገባው ብሎ ለሰባት ዓመታት ተቀምጦ ነበር፡፡ አብረውት የሚማሩት ተማሪዎች ይህ ትምህርት የማይገባው ስለ ምንድን ነው? በእርሱ ኃጢአት ነው ወይስ በወላጆቹ ? ይሉት ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ የሐይቁ መምህር የነበረው ዐቃቤ ሰዓት ሠረቀ ብርሃን ለአባቱ «ልጅህ ትምህርት አይገባውምና የቤተ

መንግሥት ነገር አስተምረው» ብሎ መለሰው፡፡አባቱ ሕዝበ ጽዮን ግን «አንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፤ እዚያው ገዳሙን ያገልግል » ብሎ እንደ ገና ላከው፡፡

አባ ጊዮርጊስ ዕውቀት ስለ ተሠወረው ሁልጊዜ በሥዕለ ማርያም ሥር እየተንበረከከ ይጸልይ ነበር፡፡ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምንም እህል በመፍጨት ያገለግል ነበር /በ1988 ዓ.ም የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳምን የጽሑፉ አዘጋጅ በነበኘበት ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ይፈጭበት የነበረውን የድንጋይ ወፍጮ ገዳማውያኑ አሳይተውታል/፡፡ አንድ ቀን እመቤታችን ተገለጠችለትና «ኣይዞህ ዕውቀት የተሠወረብህ ትምህርት ስለማይገባህ ሳይሆን የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንዲገለጥ ነውና ታገሥ» አለችው፡፡ ከዚያም ጽዋዕ ልቦና አጠጣችው፡፡

ከዚህ በኋላ በሐይቅ እስጢፋኖስ ትምህርቱን በሚገባ ተምሮ አጠናቀቀ፡፡ በዕውቀቱም ቀድሞ የሚያውቁት ሁሉ ይደነቁበት ነበር፡፡

አባ ጊዮርጊስ በዜማ /የያሬድን ዜማ ከአቡነ ሳሙኤል ዘጋርማ እንደተማረው ገድሉ ይነግረናል፡፡ /በዚያ ዘመን በዐፄ ዳዊት አማካይነት በሰሜን ኢትዮጵያ የያሬድ ድጓ ዋና ማዕከል በሆነው በደብረ ነጎድጓድ ተሾሞ ሳያስተምር አልቀረም፡፡ምክንያቱም በኢትዮያ የድጓ ሊቃውንት ዝርዝር ውስጥ አባ ጊዮርጊስ ይጠቀሳልና/፣ በትርጓሜ መጻሕፍትና በቅኔ የጠለቀ ዕውቀት እንዳለው ድርሰቶቹ ይመሰክራሉ፡፡

የማስተማር ሥራውን የጀመረው በዚያው በሐይቅ እስጢፋኖስ መሆኑን ገድሉ በሚከተለው መልኩ ይገልጠዋል «ወአብርሃ ለቤተ ክርስቲያን እንተ ተሐንጸት በሐይቅ ባሕር፣ ወእም አሜሃ አሐዙ ይስአሉ እም ኀቤሁ ኩሎሙ ሰብአ ሀገር ቃለ መጻሕፍት ወትርጓሜሆሙ፣ ወኩሉ ቃለ ማኅሌት፡፡»

ከሐይቅ በኋላ በዚያ ዘመን ሸግላ በመባል ትጠራ ወደ ነበረችው ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ጋሥጫ ተጓዘ፡፡ በዚያ ጊዜ የነገሥታቱ መቀመጫ በዚያ የነበረ ይመስላል፡፡ ለዚህ ሦስት ምልክቶች አሉ፡፡ የመጀመርያው በነገሥታቱ መቀመጫ አካባቢ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚበዙት ሁሉ /አኩስምን፣ ላስታን፣ ጎንደርን፣ አንኮበርንና አዲስ አበባን በምሳሌነት ማንሣት ይቻላል፡፡/ በጋሥጫም በዚያ ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በገድሉ ላይ አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸግላ በመጣ ጊዜ ወደ ቤተ መንግሥት እንዳስገቡት የሚገልጠው ነው፡፡ ሦስተኛው መረጃ ጋሥጫ የዐፄ ይስሐቅ የክረምት ጊዜ ማረፊያ እንደነበረች ገድሉ መግለጡ ነው፡፡

አባ ጊዮርጊስ ወደ ሸግላ ሲመጣ አባቱ በጣም አርጅቶና መንኩሶ ነበር፡፡ ስለዚህም በአባቱ እግር ተተክቶ በቤተ መንግሥቱ ያለችውን ሥዕል ቤት እንዲያገለግል ወደዚያው አስገቡት፡፡ በቤተ መንግሥቱም የንጉሡን ልጆች ከማስተማሩም በላይ በቤተ መንግሥቱ ዙርያ ከነበሩት ሊቃውንት መካከል አባ ጊዮርጊስ አንዱ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስ ሥላሴን አንድ ገጽ ብለው ያምናሉ ተብለው በተከሰሱ ጊዜ ነገሩን እንዲያጣሩ ከተመረጡት ከቄስ ሐፄ ተክሥተ ብርሃንና ከሐይቁ መምህር ከዐቃቤ ሰዓት ዮሴፍ ጋር አብሮ ተልኮ ነበር፡፡ እነዚህ ሦስት አበው ጳጳሱን ካነጋገሩ በኋላ ክሱ ውሸት መሆኑን በማረጋገጥ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ የሚገልጠውን የጳጳሱን እምነት በጽሑፍ ይዘው መጡ፡፡

በቤተ መንግሥቱ በነበረ ጊዜ የንጉሡን ልጆች ይስሐቅን፣ ቴዎድሮስን፣ እንድርያስን፣ ሀብተ ኢየሱስን፣ ሕዝቅያስን፣ ኢዮስያስን፣ ዘርዐ ያዕቆብንና ሴት ልጁን እሌኒን በምግባርና በሃይማኖት ቀርጿቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ዘርዐ ያዕቆብ በድርሰቱ ሲመስለው ቴዎድሮስ ደግሞ በሕይወት መስሎታል፡፡ ዐፄ ዳዊት የአባ ጊዮርጊስን ሊቅነትና መልካም ሥነ ምግባር በሚገባ ስላወቀ በጋብቻ ሊዛመደው ወዶ ስለነበር ልጁን እንዲያገባ ዘወትር ይጠይቀው ነበር፡ ፡ አባ ጊዮርጊስ ግን በድንግልና ጸንቶ ለመኖር እንደሚፈልግ ከመግለጽ አልተቆጠበም፡፡ የዐፄ ዳዊት ጥያቄ ስለበዛበት ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ሄዶ ቅስናን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው መነኮሰ፡፡ ገድሉ የት እንደ መነኮሰ አይገልጥልንም ነገር ግን አንድም በሐይቅ እስጢፋኖስ ያለበለዚያም በደብረ ጎል ሊሆን እንደሚችል ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ግምታቸውን አስቀምጠዋል፡፡

ከመነኮሰ በኋላ ወደ ሸግላ በመምጣት «ወእምድኅረዝ ኮነ አቡነ ጊዮርጊስ መምህር ለነገሥት ወለካህናት ዘደብተራ ወለኩሉ ዐበይተ ቤተ መንግሥት፣ ለንቡራነ እድ ወለመኳንንት፣ ለመሳፍንት ወለኩሉ ተዐይነ ቤተ መንግሥት- ከዚህ በኋላ ለነገሥታትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ካህናት እንዲሁም በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ታላላቆች፣ ለንቡራነ እድና ለመኳንንት፣ ለመሳፍንትና በቤተ መንግሥቱ ለነበሩ ባለሟሎች ሁሉ መምህር ሆነ፡፡»

አባ ጊዮርጊስ በሸግላ በነበረ ጊዜ በወባ በሽታ ታምሞ ሊሞት ደርሶ እንደ ነበር ገድሉ ይናገራል፡፡ ታምሞ በነበረ ጊዜ አንድ ሌሊት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ ተገልጠውለት ከእኛ ጋር ትኖር ዘንድ ልንወስድህ መጣን አሉት፡፡ እርሱም የድርሰት ሥራዬን ሳልሠራና እግዚአብሔርንም አብዝቼ ሳላመሰግነው አሁን አትውሰዱኝ ሲል ለመነ፡፡ እነርሱም ልመናውን ተቀብለውት ከሕመሙ ፈውሰውት ሄዱ፡፡ ለዚህም ይመስላል ከበሽታው እንደ ተፈወሰ ወድያው የድርሰት ሥራውን የጀመረው፡፡

የመጀመርያ መጽሐፉን ጽፎ እንደ ጨረሰ ጠፍቶበት እንደ ነበር ገድሉ ይተርካል፡፡ በቤቱ ውስጥ የነበሩትን መጻሕፍት ሁሉ እያገላበጠ ቢፈልገውም ሊያገኘው አልቻለም፡፡ አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ሌሊት በአገልግሎት ላይ እያለ እመቤታችን ተገልጣ «ለምን አስቀድመህ ሳትነግረኝ ጻፍክ?» ስትል ጠየቀችው፡፡ እርሱም «አንቺን ደስ ያሰኘሁ መሰሎኝ ነውና ይቅር በይኝ» ሲል መለሰላት፡፡ ከዚህ በኋላ የድርሰት ሥራውን ፈቅዳለት ተሠወረችው፡፡ «ወሶቤሃ በርሃ ልቡ ከመ ፀሐይ ወሐተወ ውስተ ኅሊናሁ ባሕረየ መለኮት፤ ወነጸረ ኩሎ ኀቡኣት - ከዚህ በኋላ ልቡ በራለት፣ ኅሊናውም ነገረ መለኮትን ዐወቀ፡፡ የተሠወረውንም ሁሉ ተመለከተ» ይላል ገደሉ፡፡

የመጀመርያው ድርሰቱ ***አርጋኖን*** የተሰኘውና በቅኔ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚያመሰግነው መጽሐፉ ነው፡፡ ስለ አርጋኖን ድርሰቱ ገድሉ በሚከተለው መንገድ ይገልጠዋል «ወሰመዮ በሠለስቱ አስማት ዘውእቶሙ አርጋኖነ ውዳሴ፣ ወመሰንቆ መዝሙር ወእንዚራ ስብሐት - በሦስት ስሞችም ሰየማቸው እነርሱም ***አርጋኖን ውዳሴ፣ መሰንቆ መዝሙርና እንዚራ ስብሐት*** ይባላሉ፡፡» ይህ አገላለጥ አንድ ነገር እንድናስተውል ያደርገናል፡፡ ይሄውም ስለ አርጋኖን መጽሐፍ ይዘት ነው፡፡ በገድሉ ላይ አርጋኖን መጽሐፍ አንድ ሆኖ ሦስት ክፍሎች ያሉት ይመስላል፡፡ እስካሁን የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አርጋኖንንና እንዚራ ስብሐትን ለየብቻ አግኝቷቸዋል፡፡ አርጋኖን ከሰኞ እስከ ዓርብ ላሉት ዕለታት ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን፣ እንዚራ ስብሐት ግን ከ«ሀ » እስከ «ፖ» ያሉትን ፊደላት በመከፈያነት በመጠቀም የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህም አርጋኖንን አባ ጊዮርጊስ ሲያዘጋጀው አንድ ሆኖ በኋላ ግን በየክፍሉ እየተጻፈ የተባዛ ይመስላል፡፡

እመቤታችን አርጋኖንን ስለ ወደደችለት ዚማት /ምናልባት ዝማ ይሆን?/ በሚባለው ሀገር በነበረ ጊዜ «ከድርሰቶችህ ሁሉ እንደ አርጋኖን የምወደው የለም» ብላዋለች፡፡ ዐፄ ዳዊትም ድርሰቱን በጣም ከመውደዱ የተነሣ በወርቅ ቀለም እንዳጻፈው ገድሉ ይገልጣል፡፡

ከዚህ በኋላ የደረሰው ደርሰት ውዳሴ መስቀል ይባላል፡፡ ቀጥሎም **መጽሐፈ ስብሐት ዘመዓልት ወዘሌሊት** የተባለውን /ወይም እርሱ ራሱ መጽሐፈ ብርሃን ብሎ የሰየመውን/ መጽሐፍ አዘጋጅቷል፡፡ ይህን መጽሐፍ «መጽሐፈ ብርሃን» ብሎ የሰየመበትን ምክንያት ገድሉ ሲያበራራ «አስመ ውእቱ ያበርህ ወያስተርኢ ፍናወ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ወፍናወ ስብሐቲሆሙ ለትጉኃን ወለኩሎሙ ማኅበረ ቅዱሳን ልዑላነ ብርሃን ወዓዲ ይነግር እንዘ ያስተሐውዝ ውዳሴሃ ለድንግል ንጽሕት— የእግዚአብሔርን የምስጋናውን መንገድ ያበራል /አብርቶ ያመለክታልና፣ ልዑላነ ብርሃን የሆኑትን የማኅበረ ቅዱሳንንና የትጉኃንን የምስጋናቸውን መንገድ ያመለክታልና፣ የእመቤታችንንም የምስጋናዋን ጣዕም ይገልጣልና/ ይላል፡፡»

በዚያ ጊዜ በነበረው ልማድ ካህናቱ ቁርባን በሚያቀብሉ ጊዜ ሕዝቡ ወደ ካህናቱ መጥተው ሲቀበሉ ንግሥቲቱ ግን ካለችበት ካህናቱ ሄደው ነበር የሚያቆርቧት፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን «ይህ ቁርባን ንጉሠ ነገሥት ነውና ንግሥቲቱ ወደዚህ መጥታ ልትቀበል ይገባታል እንጂ እኛ መሄድ የለብንም » ሲል ተቃወመ፡፡ ይህ ነገር ንግሥቲቱንና አባ ጊዮርጊስን ስላጋጫቸው ዐፄ ዳዊት ችግሩን ለመፍታት አባ ጊዮርጊስን ወደ ሀገረ ዳሞት ንቡረ እድነት ሾሞ ላከው፡፡

አባ ጊዮርጊስና አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ የተገናኙት አባ ጊዮርጊስ ወደ ዳሞት በሚጓዝ ጊዜ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ አለባበሱ እንደ ተርታ ሰው በመሆኑ አቡነ ሳሙኤል በመጀመርያ አላወቁትም ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ አባ ጊዮርጊስ ቅር ብሎት ወደ ዳሞት ተመለሰ፡፡ እንደ ሥርግው ሐበለ ሥላሴ ግምት ሁለቱን ያላግባባው ሥርዓተ ጸሎት ሳይሆን አይቀርም፡፡ በዚያ ጊዜ በዋልድባ ሥርዓተ ጸሎቱ ሰባት ጊዜ በቀን መጸለይን የሚያዝ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን በቀን ሰባት ጊዜ ብቻ መጸለዩ ለእግዚአብሔር ያንሰዋል ብሎ ያምን ነበር፡፡ ምናልባትም በዚያን ጊዜ 22 ሰዓት የሚፈጀውን ሰዓታት ሳያዘጋጅ አልቀረም፡፡

ከዚህ በኋላ የአባ ጊዮርጊስ ዋናው ትኩረቱ በድርሰቱ ላይ ሆነ፡፡ ወደ ጳጳሱ ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ዘንድ በመሄድ የቅዳሴ ድርሰት ለመድረስ እንዲፈቀድለት ከጠየቀ በኋላ የቅዳሴ ድርሰት ማዘጋጀቱን ገድሉ ይገልጣል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ቅዳሴያት ደራሲያቸው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ፍንጭ የሚሰጠን ይሆናል፡፡ ገድሉ እንደሚተርከው አንዳንድ ካህናት የአባ ጊዮርጊስን ቅዳሴ ተቃውመው ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አርዮስን በቀጣበት መንገድ ቀጥቷቸዋል፡፡

አባ ጊዮርጊስ ነገረ ሃይማኖትን ጠንቅቆ የተረዳና የሚያስረዳ ስለነበር በዘመኑ የተነሡ የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ እርሱ ከሌለ አይሳኩም ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ በሸዋ በይፋት ራሳቸውን ቤተ እስራኤል እያሉ የሚጠሩ አይሁድ ነበሩ፡፡ ከአቡነ ዜና ማርቆስ ጀምሮ ብዙ መምህራን ወደነዚህ ሕዝቦች እየተሠማሩ ወንጌልን አስተምረዋል፡፡ አቡነ ዜና ማርቆስ ወደ ክርስትና ለተመለሱት ቤተ እስራኤላውያን በእመቤታችን፣ በቅዱስ ሚካኤል፣ በአባ ኖብና በሰማዕቱ በጊጋር ስም አራት አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተው ነበር፡፡ ሁለቱ የመጀመሪያዎቹ አሁንም አሉ፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንም ቤተ እስራኤላውያኑ ሙሉ በሙሉ ወደ ክርስትና አልተመለሱም ነበር፡፡

ከእነዚህ አይሁድ መካከል አንዱ ከክርስቲያኖች ጋር በነገረ ሃይማኖት ለመከራከር ጥሪ አቀረበ፡፡ «ክርስቲያኖች ከረቱኝ ወደነርሱ ሃይማኖት እገባለሁ እኔ ከረታኋቸውም ወደኔ ሃይማኖት ይገባሉ» ሲል ነገሩን ጥብቅ አደረገው፡፡ ዐፄ ዳዊት ይህን ጉዳይ ሲሰማ በጣም ስለ ተናደደ ሊቃነ ካህናቱን፣ ንቡራነ እዱንና የመጻሕፍት ዐዋቂዎችን ሁሉ ከየሀገሩ እንዲሰባሰቡ አዘዘ፡፡ አይሁዳዊው በአንድ ወገን መምህራኑ በአንድ ወገን ሆነው ክርክሩን ጀመሩ፡፡ የመጀመርያው እድል የተሰጠው ለአይሁዳዊው በመሆኑ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ አቀረበ፡- «እናንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የምትሉት ይሄ ክርስቶስ እውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ፣ ወደ ቢታንያ በመጣ ጊዜ አልዓዛር የተቀበረበትን ቦታ ሳያውቅ ቀርቶ 'አልዓዛርን የት ቀበራችሁት?» ብሎ እንደ ጠየቀ በወንጌላችሁ ተጽፏል፡፡ ለዚህ መልስ ስጡኝ፣እኔንም ከመጽሐፉ አሪቴ ጠቅሳችሁ ጠይቁኝ? » ሲል የመከራከርያ ነጥቡን አቀረበ፡፡
በዚህ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ ታሞ አልጋ ላይ ነበር፡፡ ሊቃውንቱም እንዲህ ያለው ነገር ያለ እርሱ አይሆንምና አባ ጊዮርጊስ ይምጣ ሲሉ ለዐፄ ዳዊት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ አባ ጊዮርጊስም በአልጋ ላይ እያለ እንዲመጣ ተደረገ፡፡ በአልጋ ላይ ሆኖም በጉባኤው ላይ ተገኘ፡፡ ጉባኤተኞቹ የቀረበውን ጥያቄ ነገሩት፡፡ አባ ጊዮርጊስ የሰጠውን መልስ ገድሉ በሚከተለው መንገድ ይገልጥልናል «እኔ ግን በወንጌል ሳይሆን በኦሪት እከራከርሃለሁ፡፡ የምኩራብ መጻሕፍት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን የታወቁ ናቸውና፡፡ ምኩራብ ዘራች ቤተ ክርስቲያንም አጨደችው፤ ምኩራብ ፈተለችው ቤተ ክርስቲያን ለበሰችው፤ አዳምን በገነት ሳለ አዳም ሆይ ወዴት ነህ? ብሎ የጠየቀው ማነው? አብርሃምንስ ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? ብሎ የጠየቀው ማነው? እስቲ መልስልኝ? ሰይጣንንስ ከወዴት መጣህ? ብሎ የጠየቀው ማነው? እግዚአብሔር አብ አይደለምን?» በዚህ ጊዜ አይሁዳዊው መልስ አጥቶ ዝም አለ፡፡ ንጉሡ፣ ሊቃውንቱና መኳንንቱም እጅግ ተደሰቱ፡፡

አባ ጊዮርጊስ ሌላው ያጋጠመው ክርክር ቢቱ ከተባለው ሰው ጋር ያደረገው ክርክር ነበር፡፡ ቢቱ «በምጽአት ጊዜ የሚመጣው ወልድ ብቻውን እንጂ አብና መንፈስ ቅዱስ አይመጡም» የሚል ኑፋቄ ማስተማር ጀምሮ ነበር፡፡ ቢቱ ከዚህ ኑፋቄው በተጨማሪ የጥንቆላ ሥራም ይሠራ ነበር፡፡ ቢቱ በጥንቆላ ሥራው የተነፀ በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት የነበረው ሰው እንደ ነበረ ገድሉ ይናገራል፡፡ ይህን መሰሉን ተግባር አጥብቆ የተዋጋው ዘርዐ ያዕቆብ እስኪመጣ ድረስ ነገሥታቱ ምንም ክርስቲያኖች ቢሆኑ በዚህ መሰሉ ስንኩል ሕፀፅ ይዋጡ ነበር፡፡

ቢቱና አባ ጊዮርጊስ ወደ ንጉሥ ዳዊት ቀርበው በጉዳዩ ላይ መነጋገር እንደሚፈልጉ ገለጡ፡፡ ዐፄ ዳዊትም ጳጳሱና ሊቃውንቱ ባሉበት እንዲነጋገሩ ስለ ወሰነ ጳጳሱ እንዲመጡ አዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ ተንኮለኛው ቢቱ ከአባ ጊዮርጊስ ጋር ከተከራከረ እንደሚረታ ስላወቀ ንጉሡ የአባቶቻችንን ሃይማኖት ክዷልና አትምጣ የሚል ደብዳቤ በአባ ጊዮርጊስ ስም ጽፎ ጳጳሱን ሊጠሩ በሄዱት መልእክተኞች እጅ ላከ፡፡ ወድያውም ለዐፄ ዳዊት ይህንን ነገር አሳበቀ፡፡ ዐፄ ዳዊትም ፈጣን መልእክተኞች ልኮ የፊተኞቹ መልእክተኞች እንዲመለሱ አደረገና ደብዳቤው ተነበበ፡፡ የቢቱ ተንኮል ያልገባው ንጉሥ ዳዊት ይህን ደብዳቤ ሲመለከት አባ ጊዮርጊስን በደም አበላ እስኪነከር ድረስ እንዲደበደብ አድርጎ ወደ እስር ቤት አስገባው፡፡ ዐፄ ዳዊት እስኪሞትና ልጁ ቴዎድሮስ እስኪነግሥ ድረስም በዚያ ቆየ፡፡ ቢቱ ግን በመልአከ ተቀስፎ ሞተ፡፡

አባ ጊዮርጊስ በወኅኒ ቤት እያለ ጴጥሮስና ጳውሎስ እየመጡ ያጽናኑት ነበር፡፡ ***ውዳሴ ሐዋርያት*** የተሰኘውንና የሐዋርያትን ምስጋና የያዘውን መጽሐፍ ያዘጋጀው በወኅኒ በነበረ ጊዜ ነው፡፡ አብዛኞቹን ድርሰቶቹን በዚህ ጊዜ ሳያዘጋጃቸው እንደማይቀር ይገመታል፡፡ ዐፄ ዳዊት በሞተ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ እጅግ አድርጎ አዘነ፡፡ እንዲያውም

አንዳንዶች «በመሞቱ ደስ ልትሰኝ ይገባሃል እንጂ እንዴት ታለቅሳለህ?» ብለው ጠይቀውት ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን «ጥቂት ቢኖር እወዳለሁ፤ እመቤታችንን የሚወድ ሰው ነውና» ብሎ ነበር የመለሰው፡፡

ዐፄ ቴዎድሮስ አባ ጊዮርጊስን ከወጎኒ ቤት አውጥቶት በጥንቱ ቦታ አስቀመጠው፡፡ አባ ጊዮርጊስ ግን የቤተ መንግሥትን ነገር ለመሸሽ ስለ ፈለገ በጋሥጫ ከመቀመጥ ይልቅ ርቆ ጥንት ወደ ነበረበት ወደ ዳሞት በመሄድ ማስተማር ጀመረ፡፡ ወደ ዳሞት ሲሄድ እግረ መንገዱን ወደ ደብረ ሊባኖስ ገብቶ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን መቃብር ተሳልሟል፡፡ በዚያ ጊዜ የደብረ ሊባኖሱ አበ ምኔት እጨጌ ዮሐንስ ከማ /ሰባተኛው የደብረ ሊባኖስ እጨጌ/ እንደ ነበሩ ገድሉ ይናገራል፡፡

ነገር ግን በዕውቀቱ የሚቀኑበት፣ በችሎታው የሚመቀኙት ሰዎች ነገር ሠርተው ከንጉሥ ቴዎድሮስ ጋር ስላጣሉት እልም ካለ በረሃ እንዲጋዝ ተደረገ፡፡ አባ ጊዮርጊስ ከግዞት የወጣው ዐፄ ቴዎድሮስ ሲሞት ነበር፡፡

የአባ ጊዮርጊስ ሌላው ተማሪ የነበረው ዐፄ ይስሐቅ በ1399 ዓ.ም መንግሥቱን ሲይዝ አባ ጊዮርጊስን ከግዞት አውጥቶ ወደ ጋሥጫ መለሰው፡፡ በዚያ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ እድሜው 42 ዓመት ሲሆን በስደትና በጤንነት መታወክ የተነሣ ከባድ ጉዳት ደርሶበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜውን በጾም፣ በጸሎትና በድርሰት ያውለው ነበር፡፡

«ወበአሐቲ መዋዕል ተስዕሎ አሐዱ መስፍን ዘስሙ ቴዎድሮስ ዘይሰመይ ካዕበ ሊቀ ሐራ በእንተ ሃይማኖት ርትዕት ወደረሰ ሎቱ መጽሐፍ ዘይሰመይ ፍካሬ ሃይማኖት፡፡ ወሶበ ርእይዎ ወአንበብዎ ለውእቱ መጽሐፍ ንጉሥ ወኩሎሙ ካህናተ ምሥጢር ይቤሉ አማንኪ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፣ ወቄርሎስ አፈ በረከት ተንሥኡ በመዋዕሊነ፡፡ ኢትዮጵያ ተመሰለት በቁስጥንጥንያ፣ ወተአረየታ ላዕለ እስክንድርያ - አንድ ቀን ቴዎድሮስ የተባለ መስፍን፣ ዳግመኛም የጦሩ አዛዥ የሚሆን፣ አባ ጊዮርጊስን ስለ ርትዕት ሃይማኖት ጠየቀው፡፡ አባ ጊዮርጊስም ***ፍካሬ ሃይማኖት*** የተባለውን መጽሐፍ ደርሶ ሰጠው፡፡ ንጉሡና የምሥጢር ሊቃውንት የሆኑ ካህናት ይህንን በተመለከቱ ና ባነበቡ ጊዜ በእውነት ዮሐንስ አፈወርቅና አፈ በረከት የሆነው ቄርሎስ በዘመናችን ተነሥተዋል፡፡ ኢትዮጵያም ቁስጥንጥንያን መስላለች፣ ከእስክንድርያም በላይ ከፍ ከፍ ብላለች ብለው አደነቁ» ይላል ገድሉ፡፡ አባ ጊዮርጊስ ፍካሬ ሃይማኖት የተሰኘውንና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምታምነውንና የምታወግዘውን በግልጥና በዝርዝር የጻፈበትን መጽሐፍ እንዴት እንደ ደረሰው ሲገልጥ፡፡ ፍካሬ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን እምነት በግልጥና በዝርዝር በማስቀመጥ ረገድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመርያው ሥራ ነው የሚል እምነት የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አለው፡፡ የዘረዘራቸው የመናፍቃን ስሞችን እና ክህደታቸውን ስናይ በዘመኑ የነበሩ ሊቃውንት ስለ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያላቸውን ዕውቀት ያሳየናል፡፡

አባ ጊዮርጊስ መከራ ያልተለየው አባት ነበር፡፡ ገድሉ እንደሚተርከው በቤተ መንግሥቱ የነበሩ ሰዎች የርሱን መከበርና መወደድ አይፈልጉትም ነበር፡፡ በተለይም ***ፍካሬ ሃይማኖት*** የተሰኘውን መጽሐፍ በመጻፉ የተነሣ መከበሩ አልተዋጠላቸውም፡፡ ስለዚህም ነገር ሠርተው ከዐፄ ይስሐቅ ጋር አሁንም አጣሉት፡፡

ዐፄ ይስሐቅ አባ ጊዮርጊስን አሳስሮ ውኃ ወደማይገኝበት ዐለታማ ቦታ አጋዘው፡፡ በዚያም በመከራ ለብዙ ጊዜ ኖረ፡፡ በዚያ እያለ ዘወትር በጸሎት አብዝቶ ይተጋ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ዐፄ ይስሐቅ ወደ ልቡናው እንዲመለስ አደረገ፡፡ ንጉሡ በአባ ጊዮርጊስ ላይ የፈጸመው ነገር ሁሉ ፀፀተው፡፡ አገልጋዮቹንም ጠርቶ አባ ጊዮርጊስን እንዲያመጡት

አዘዘ፡፡ ነገር ግን እነዚያ ተንኮል ሠሪዎች የአባ ጊዮርጊስ መምጣት ተንኮላቸውን ስለሚያጋልጠው አባ ጊዮርጊስ ሞቷል ብለው አስወሩ፡፡ ይህንን ሲሰማ ዐፄ ይስሐቅ ፈጽሞ አዘነ፡፡

አባ ጊዮርጊስ ሞቷል እየተባለ መወራቱን ከደቀ መዝሙሩ ስለ ሰማ በሕይወት የመኖሩን ዜና ጽፎ ለዐፄ ይስሐቅ እንዲያደርስለት አውሎ ንፋስን ላከው፡፡ አውሎ ንፋሱ ደብዳቤውን ተሸክሞ በመሄድ ዐፄ ይስሐቅ በድንኳን ተቀምጦ በነበረ ጊዜ ጉልበቱ ላይ አስቀመጠው፡፡ ንጉሡ ምትሐት የተሠራበት ስለ መሰለው ደነገጠና መኳንንቱንና ሕዝቡን ሰብስቦ ጉዳዩን ገለጠ፡፡ ወዲያውም አሳት አስነድዶ ቢጥለው ሊቃጠል አልቻለም፡፡ ወደ ውኃም ቢጨምረው አልጠፋም፡፡ በዚህ ተደንቆ ወረቀቱን ከፍቶ አነበበው፡፡ ደብዳቤው ከአባ ጊዮርጊስ የተላከ መሆኑን ሲያውቅ ዐፄ ይስሐቅ ደነገጠ፡፡ እነዚያን መልእክተኞች ይዞ ወደ ወኅኒ ጨመራቸው፡፡ አባ ጊዮርጊስንም ከግዞት ያወጡት ዘንድ ላከ፡፡

አባ ጊዮርጊስ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመጣ ንጉሡ በደስታ ተቀበለው፡፡ ደብዳቤውን በማን እጅ እንደ ላከውም ጠየቀው፡፡ አባ ጊዮርጊስም ደብዳቤውን በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ በነፋስ እንደ ላከው አስረዳ፡፡

ከግዞት ከተመለሰ በኋላ እመቤታችን ተገልጣለት መከራው ሁሉ እንደ ሐዋርያት መሆኑን ገለጠችለት፡፡ አእምሮውን ብሩህ፣ ልቡናውን ትጉኅ የሚያደርግ እጅግ ብዙ ምሥጢር ነገረችው፡፡ ተሰናብታው ከሄደች በኋላ «እጅግ ብዙ መብራት አቅርቡ አምስት ፈጣን ጸሐፊዎችንም አምጡ » ብሎ አዘዘ፡፡ እርሱ እየነገራቸው እነርሱ እየጻፉ እረፍት ሳያደርጉ ሦስት ቀን ሙሉ አስጽፎ መጽሐፈ ምሥጢር የተሰኘውን መጽሐፍ ፈጸመ፡፡ አባ ጊዮርጊስ ይህንን ያደረገው ምናልባት በስደትና በመከራ ስለ ደከመ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አምስቱ ጸሐፍት የየድርሻቸውን አጠናቅቀው በአንድ አደረጉት፡፡ አባ ጊዮርጊስም ይህን ተመልክቶ በእጅጉ አደነቀ፡፡ «እኔ የዚህን መጽሐፍ ቃል አልተናገርኩም፤ መንፈስ ቅዱስ በእኔ አፍ ተናገረ እንጂ » ሲል በወቅቱ መመስከሩን ገድሉ ይናገራል፡፡

ይህንም መጽሐፍ ***መጽሐፈ ምሥጢር*** ሲል ሰየመው፡፡ የጻፈው በ1409 ዓ.ም እድሜው 52 በደረሰ ጊዜ ሲሆን የዚህ መጽሐፍ ቅጅ በነጋድያን እጅ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ በወቅቱ ሄዶ እንደ ነበር ገድሉ ያስረዳል፡፡

መጽሐፈ ምሥጢር የተጻፈበትን ዘመንና ምክንያት የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ከዚህ በተለየ ነው የሚያስቀምጠው፡፡ «በመዋዕሊሁ ለዝንቱ ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ኮነ ተቃሕዎ በእንተ ሃይማኖት ወተዋሥአ አባ ጊዮርጊስ ምስለ አሐዱ አፍርንጅ ወሞዓ እስከ ከሠተ ወጸሐፈ መጽሐፈ ምሥጢር - በዚህ በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ክርክር ሆነ፡፡ አባ ጊዮርጊስም ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራከሮ ረታው፡፡ መጽሐፈ ምሥጢር የተባለውን መጽሐፍም ደረሰ፡፡» ይላል፡፡ ይህ ግን የሚያስኬድ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ዐርፎ ነበርና፡፡

ዐፄ ይስሐቅ ለአባ ጊዮርጊስ ምድረ ሰዎን /ይህ ቦታና ጋሥጫ ቅርብ ይመስላሉ፡፡ እንደዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ግምት ከወለቃ ወንዝ ማዶ ያለው ሀገር ሰግላ፣ ወዲህ/ ወደ ሰሜን ሸዋ/ ያለው ሀገር ደግሞ ምድረ ሰዎን ተብሎ ሳይጠራ አልቀረም፡፡ ምክንያቱም ገድለ አባ ጊዮርጊስ ስለ ምድረ ሰዎን ሲናገር በዚያ የአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እንዳለ ይተርካል፡፡ የአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ያለው ከአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳም ሥር ነው፡፡ አባ ጊዮርጊስ በግዞት

በነበረ ጊዜ በራእይ እመቤታችን ተገልጣ ዕረፍቱ በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እንደሚሆን እንደ ነገረችው ገድሉ ይተርካል፡፡/

የተባለውን የጳጳሳት መቀመጫ የነበረውን ሀገር በርስትነት ሰጥቶት ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ በምድረ ሰወን ንጉሥ ይስሐቅ ከረምቱን ያሳልፍበት በነበረው ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠራ፡፡ በዚያም በማስተማርና በጾም በጸሎት ይተጋ ነበር፡፡ በጋሥጫ እያለ ዐፄ ይስሐቅ አስጠራው፡፡ በዚያ ጊዜ ንጉሡ የመናገሻ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ስለ ነበር እንዲባርክለት ፈልጎ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ምንም እንኳን በዚያ ጊዜ ታምሞ የተኛም ቢሆን ወደ ንጉሡ ተጓዘ፡፡ እዚያ ሲደርስ በጣም ተዳክሞ ነበር፡፡ ሥርዓቱን ለመፈጸምም ዐቅም አልነበረውም፡፡ ስለዚህም ንጉሥ ይስሐቅ በአልጋ ተሸክመውት እንዲዞሩና ቤተ ክርስቲያኗን እንዲባርካት አደረገ፡፡

ቡራኬውን ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዝሙሮቹን ሰብስቦ «ከሞትኩ አባቴ በጸሎተ ሚካኤል መከራ ወደ ተቀበለባትና እኔም ቤተ ክርስቲያን ወዳነፅኩባት ቦታ ወስዳችሁ ቅበሩኝ» ሲል አዘዛቸው፡፡ ለደቀ መዛሙርቱ የመጨረሻ የስንብት ትምህርቱን እያስተማራቸው እነርሱም በአልጋ ተሸክመውት ወደ ጋሥጫ እያመሩ ሳለ በመንገድ ላይ ሐምሌ ሰባት ቀን 1417 ዓ.ም በ60 ዓመቱ ዐረፈ፡፡ ከመናገሻ ወደ ጋሥጫ የሚወስደው መንገድ በአዲስ አበባ በኩል አድርጎ፣ በደብረ ጽጌ በኩል ወጥቶ፣ በመርሐ ቤቴና በጉንደ መስቀል በኩል በማለፍ በሚዳና በወረሞ በኩል ወደ ቦረና የሚሻገር ይመስላል፡፡

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በ1986 ዓ.ም በሰሜን ሸዋ ሚዳ ጉንደ መስቀል ቤተ ክርስቲያን በተገኘ ጊዜ አባ ጊዮርጊስ በመንገድ ላይ በማረፉ ለጊዜው ዐጽሙ ያረፈበትን ቦታ ካህናቱ በክብር ጠብቀው አሳይተውታል፡፡ በገድሉም ላይ በዘመዶቹና በደቀ መዝሙሮቹ መካከል የት ይቀበር? በሚለው ጉዳይ ላይ ክርክር መነሣቱንና ንጉሡ በገዳሙ እንዲቀበር መወሰኑን ይገልጣል፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ ክርክሩ አልቆ ዐጽሙ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እስኪገባ ድረስ በሌላ ቦታ ዐጽሙ ዐርፎ መቆየቱን ገድሉ ጨምሮ ይገልጣል፡፡ በመሆኑን ያረፈበት ቦታ ጉንደ መስቀል ሳይሆን አይቀርም፡፡

እስካሁን ድረስ ያሉን ምንጮች የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ቁጥራቸው ከዐርባ በላይ እንደሆኑ ይገልጣሉ፡፡ በስም የምናውቃቸው ግን የሚከተሉትን ብቻ ነው፡፡ ምናልባት ብዙ ጥናት ማድረግ ሳያስፈልገን አይቀርም፡፡

1. ሰዓታት ዘመዓልት ወዘሌሊት
2. ኖኅተ ብርሃን /ከመጽሐፈ አርጋኖን ጋር አብሮ ታትሟል/
3. ውዳሴ መስቀል
4. ቅዳሴ
5. ውዳሴ ሐዋርያት
6. አርጋኖነ ውዳሴ
7. ፍካሬ ሃይማኖት
8. መጽሐፈ ምሥጢር
9. ውዳሴ ስብሐት

10. እንዚራ ስብሐት
11. ሕይወተ ማርያም
12. ተአምኖ ቅዱሳን
13. መጽሐፈ ብርሃን
14. ጸሎት ዘቤት ቤት

አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስሙ እና ክብሩ የተዘነጋ ሊቅ ነው፡፡ አብዛኞቹ መጻሕፍቱም ለአንባብያን አልቀረቡም፡፡ በርግጥ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ መጽሐፈ ምሥጢር የተሰኘው መጽሐፉ በአማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡ ይህ መጽሐፍ በማኅበረ ቅዱሳን፣ በገዳሙ እና በቅርቡ ደግሞ በባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሦስት ጊዜ ለኅትመት ቀርቧል፡፡ ዘመኑ የአባ ጊዮርጊስ ነው ያሰኛል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳንም ገዳሙን ለመርዳት ከፍተኛ ፕሮጀክት ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

እኔ ገዳሙን ከአንድ ቀን የእግር ጉዞ በኋላ በቦታው አይቼዋለሁ፡፡ በደቡብ ወሎ ቦረና ውስጥ ይገኛል፡፡ ከደሴ እስከ ከላላ አንድ ቀን፤ ከከላላ እስከ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ አንድ ቀን ይወስዳል፡፡ ገዳሙ ዙርያውን በሙስሊም የተከበበ፤ በተራራ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ አብዛኞቹ መነኮሳት ዐቅመ ደካማ ናቸው፡፡ ቦታው አስቸጋሪ በመሆኑ ብዙ ወጣት መነኮሳት አይሄዱበትም፡፡ የሚገርመው ነገር የአካባቢው ሙስሊሞች ለገዳሙ ልዩ ከበሬታ አላቸው፡፡

እስኪ በተለይም በውጭ ሀገር የምትኖሩ እና ዐቅሙ ያላችሁ ምእመናን፣ ታሪክ ወዳጆች እና ሀገር ወዳዶች ይህ ታካዊ ቅርስ እንዳይጠፋ የምትችሉትን አድርጉ፡፡ ትልቁ ችግራቸው የዓመት ቀለብ ነው፡፡

በየአካባያችን ማኅበራትን እና ኮሚቴዎችን አቋቁመን መጻሕፍቱን ብናሰባስብ÷ በተለይ በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ ያሉትን፤ ስለ እርሱ ብንጽፍ፤ ገዳሙን ብንረዳ፤ ሰንበት ት/ቤቶቻችን በስሙ ቤተ መጻሕፍት እንዲያቋቁሙ ብናግዛቸው፡፡ በስሙ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ቤተ ክርስቲያን ብንተክል፡፡ በየዓመቱ ሐምሌ ሰባት ቀን የቅድስት ሥላሴ በዓልን የሚያነግሡ አድባራት የእርሱንም ታቦት አስገብተው በድርብ ቢያነግሡት፡፡ ቀኑ «የሊቃውንት ቀን» ተብሎ ቢከበርና እርሱንና ሌሎች ሊቃውንትን የምናስብበት ቀን ቢሆን፡፡ ዐውደ ጥናቶች፤ ሴሚናሮች፤ የቅኔ እና የዜማ ምሽቶችን በማዘጋጀት ብናስበው፡፡

22. አለቃ ተክሌ

አለቃ ተክሌ የታዋቂው ሊቅ የአለቃ ገብረ ሐና ልጅ ናቸው፡፡ ዝማሜው ከእርሳቸው የቀደመ ታሪክ ቢኖረውም ያሳወቁት እና ወንበር ዘርግተው ያስተማሩት እርሳቸው በመሆኑ «የተክሌ ዝማ» እየተባለ በስማቸው ይጠራል፡፡

የአለቃ ተክሌ እና የዝማሜው መገጣጠም ግን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በፍትሐ ነገሥት ዐዋቂነታቸው የዐፄ ቴዎድሮስ ፍርድ ቤት ዳኛ የነበሩት አለቃ ገብረ ሐና በቀልደኛነታቸው ምክንያት ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር ሊስማሙ አልቻሉም ነበር፡፡

በኋላ ደግሞ ካህናት በዐፄ ቴዎድሮስ ላይ ባመፁ ጊዜ በአድማው ካሉበት ካህናት መካከል አንዱ ገብረ ሐና መሆናቸው ስለታወቀ ዐፄ ቴዎድሮስ በአለቃ ገብረ ሐና ላይ አምርረው ሊቀጧቸው ዛቱ፡፡ አለቃም ሸሽተው ጣና ሐይቅ ሬማ መድኃኔዓለም ገዳም ገቡ፡፡ በዚያም ባሕታዊ ጸዐዳ ገብረ ሥላሴ የተባሉ የአቋቋም ሊቅ አገኙ፡፡ ሁለቱም ተወያይተው በጎንደር አቋቋም ስልት የመቋሚያውን የአካል እንቅስቃሴ ጨምረው ዝማሜውን አዘጋጁት፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት ለዝማሜው መነሻ ያደረጉት በጣና ዳር የበቀለውን ደንገል እየተባለ የሚጠራ ሸንበቆ መሰል ተክል እንቅስቃሴ ነው ይላሉ፡፡ ባሕታዊ ጸዐዳ «ከእንግዲህ እኔ ወደ ዓለም አልመለስም፤ አንተ ይህንን ስልት አስተምር» ብለው አለቃ ገብረ ሐናን አደራ አሏቸው፡፡

ይህንን በአፈ ታሪክ ሲነገር የነበረ ታሪክ ወደ ካቶሊክነት የተቀየረውና ከአንቶኒዮ ዲ አባዲ ጋር በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ስለ ሆነው ሁሉ ደብዳቤ ይለዋወጥ የነበረው፣ የዋድላው ሰው ደብተራ አሰጋኸኝ ጥር ስድስት ቀን 1858 ዓ.ም ለአንቶኒዮ ዲ አባዲ በጻፈው ደብዳቤ እንዲህ በማለት ፍንጭ ይሰጥበታል፡፡ «አለቃ ገብረ ሐናን ንጉሥ መቱዋቸው በሸመል፡፡ ወደ ትግሬ ወደ ላስታ ተሰደዱ፡፡ እጅግ ተዋረዱ፡፡ እኔም በዋድላ አገኘኋቸው ወደ ቆራጣ ሄዱ፡፡» (Sven Rubenson ed.Acta Aethiopica: Tewodros and His Contemporaries, p 259)

አለቃ ይህንን ዝማሜ በጎንደር በኣታ ማስተማር ጀምረው ነበር ይባላል፡፡ ነገር ግን ጎንደሬ ሚባለውን መቋሚያ ስልት ከጥንት ጀምረው የሚያውቁት የጎንደር ሊቃውንት ለቀበሏቸው አልቻለም፡፡ በተለይ ይህ የአለቃ ገብረ ሐና አቋቋም ለተመስጦ እንጂ ለፕሮቶኮል ስለማይመች ከጎንደር ሊቃውንት ጋር ነጋ ጠባ ክርክር ሆነ፡፡ አለቃ ገብረ ሐናም ይህንን አቋቋም እንዳያስተምሩ ተከለከሉ፡፡ አለቃ ቢጨንቃቸው ቤታቸውን ዘግተው ለልጃቸው ለተክሌ አስተማሩት፡፡ ተክሌ በአቋቋሙ መካኑን ሲያውቁ ከእስልምና ወደ ክርስትና ተመልሰው የቤተ ክርስቲያንን ሊቃውንት በመብራት እየፈለጉ ወደሚሾሙት ወደ ወሎው ራስ ሚካኤል ሀገር ላኩት፡፡
አለቃ ገብረ ሐና ደርቡሽ ጎንደርን ሲወርር ልጃቸውን ወደ ወሎ ልከው እርሳቸው ዘጌ ገዳም ገቡ፡፡ በኋላም ዐፄ ምኒልክ ደርቡሽን ለመውጋት ወደ ፎገራ መምጣታቸውን ሲሰሙ ከተደበቁበት ወጥተው ንጉሡን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ ምኒልክም እንደገና የራጉኤል አለቃ አደረገው ሾሟቸው፡፡ ልጃቸው ተክሌ ወሎ ንጉሥ ሚካኤል ዘንድ እያሉ የተንታ ሚካኤል በዓል ሲከበር ከአባታቸው የተማሩትን ዝማሜ በተመስጦ አቀረቡት፡፡ ንጉሥ ሚካኤልም በዚህ ተደንቀው በዚያው በተንታ እንዲያገለግሉ አደረጉ፡፡ የተክሌ ዝማሜ በይፋ የተጀመረው ያኔ ነው ይባላል፡፡ በኋላ ራስ ጉግሣ /1792 -1818/ ዝናውን ሰምተው ንጉሥ ሚካኤልን በማስፈቀድ ወደ ደብረ ታቦር አምጥተው ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ሾሟቸው፡፡

አለቃ ተክሌም በደብረ ታቦር ኢየሱስ ተቀምጠው ትምህርቱን አስፋፉት፡፡ በምስክርም አለቃ ብሬን፣ አለቃ መኮንንን፣ አለቃ ዓለሙንና አለቃ ይትባረክን መርቀዋል፡፡ አለቃ ተክሌ ያረፉት ራስ ጉግሣ ወሌ በሌሉበት በመሆኑ ራስ ጉግሣ መርዶውን ሲሰሙ «ምን ተክሌ ሞተ ትሉኛላችሁ፤ የደብረ ታቦር ኢየሱስ ፈረሰ በሉኝ እንጂ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ቢፈርስ አሁን ካለው በበለጠ አድርጌ ልሠራው እችላለሁ ተክሌን ግን ከወዴት አገኘዋለሁ?» በማለት ተናግረዋል ይባላል፡፡ አልቃሽም፡

«ተክሌ ገብረ ሐና ተቀበረ ጣቱ
መንክረ ክስተቱን የዘመመበቱ»- ብላ ገጥማለች፡፡

ታላቁ ራስ ጉግሣ ደብረ ታቦር ኢየሱስን በጣም ስለሚወዱ «ላቂያዬ» ብለው ይጠሩት ነበር ይባላል፡፡ የደብሩንም አገልጋዮች ብዛት ወደ 318 ከፍ እንዲል አድርገውት ነበር፡፡ በራስ ጉግሣ ወሌ ወደ 150 ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡ የታላቁ ራስ ጉግሣ፣ የራስ ዓሊ፣የራስ ይማም፣የራስ ዶሪ፣ የራስ ማርዬ፣ የራስ እንግዳ፣ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ባለቤት የወ/ሮ የሺ እመቤት ቀብር የተፈጸመው እዚህ ነው፡፡

በ15ኛው አለቃ ዘመን ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የደብሩ አለቃ «መልአከ ታቦር» ተብሎ እንዲጠራ ፈቀዱ፡፡ የተክሌ አቋቋም ትምህርት ቤት በጥር አምስት ቀን 1993 ዓ.ም የአካባቢው ምእመናን፣ የሀገሩ ተወላጆችና በጎ አድራጊዎች ባደረጉት አስተዋጽዖ በአዲስ መልክ ተሠርቶ ተመርቋል፡፡

የክልሉ መንግሥት ለአለቃ ተክሌ አንዳች መታሰቢያ ማድረግ አለበት፡፡ በተለይም ብዙ በደከሙበት በደብረ ታቦር መንገድም ይሁን ትምህርት ቤት፣ አደባባይም ይሁን ድልድይ በስማቸው መሰየም ይገባዋል፡፡

ሦስት ምሁራን ያቀረቡት ጥናት ተጠቃልሎ የታተመበትን ‹‹ያለ መቻቻል ፖለቲካ ሰማዕታት›› የተሰኘ መጽሐፍ ሳነብ ከ1969 - 1970 ዓ.ም የነበረውን የአገራችን ልዑላን እና ጎያላን ፍትጊያ በዐይነ ኅሊናዬ እየቃኘኹ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ካነበብኳቸው ዘመኑን ከተመለከቱ ጽሑፎች ጋር እያዛመድኩ አወጣሁ፤ አወረድኩ፡፡ ከዚያም ለምን እንደዚያ ‹‹ቀይ ሽብር›› እና ‹‹ነጭ ሽብር›› እየተባባልን መጨራረስ አስፈለገን? ያን ሁሉ ጭካኔ እና የእብድ ውሻ ሥራ ምን አመጣው? አብዮት ለማካኼድ የስንት ሰው ደም መፍሰስ አለበት? ውቃቤው እንዲረካ የስንት ሰው ?ሕይወት መቀጠፍ አለበት? ከማይም እስከ ምሁር፣ ከሲቪል እስከ ወታደር እንዲያ ሲጨፋጨፍ አደብ የሚገዛ እንዴት ጠፋ?

እንደ እኔ እምነት የችግሩ አንዱ መነሻ ‹‹መቶ በመቶ የማሸነፍ አባዜ›› ይመስለኛል፡፡ ኢሕአፓም፣ መኢሶንም፣ ደርግም ሌላውም መቶ በመቶ አሸንፎ፣ ሌላውን አካል ደምስሶ በጠላቱ መቃብር ላይ የአብዮት ሐውልት ለመሥራት ነበር የሚያስበው፡፡ ሁሉም ለማሸነፍ እንጂ ለመሸነፍ አልተዘጋጀም ነበር፡፡ ሲያሸንፍ ደግሞ ያኛውን ወገን ከምድረ ገጽ ጠራርጎ አጥፍቶ ብቸኛ አሸናፊ ለመኾን ነበር የሚያስበው፡፡ ስለዚህም ሰውን መግደል፣ ማረድ፣ መጨፍጨፍ ዶሮ የማረድ ያህል እና ከዚያም በታች ቀልሎ ታየ፡፡

ሁሉንም ነገሮች መቶ በመቶ ማሸነፍ አይቻልም፡፡ የተወሰነ የመሸነፊያ መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ብሸነፍስ ምንድን ነው የምኾነው፣ አሸናፊዬን በምን ዐይነት ሁኔታ ነው የማየው? ያሸነፈኝ ሁሉ ጠላቴ ነው ወይ? ሁለታችንስ አብረን ልናሸንፍ አንችልም ወይ? ወይም ደግሞ የአሸናፊነታችን መጠን ብቻ ሊለያይ አይችልም ወይ? ብሎ ማሰብም ያስፈልጋል፡፡

በምርጫ 97 የታየው አንዱ ችግር ይህ ይመስለኛል፡፡ ሁሉም ተቀናቃኝ አካላት መቶ በመቶ ወይም በዚያ ዘመን ቋንቋ ‹‹በዝረራ›› ለማሸነፍ ብቻ ነበር የተዘጋጁት፡፡ ገዥውም ፓርቲ ይኹን ተቃዋሚው መቶ በመቶ አሸንፈው አንዱ ሌላውን ድባቅ ለመምታት እንጂ አሸናፊነትን በተወሰነ እና መኾን በሚገባው መጠን ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም፡፡

አማራጫቸው ወይ ዜሮ አልያም መቶ ብቻ ነበር፡፡ በመካከል ምንም ነገር አልተገኘም፡፡ መቶውን ጠቅልሎ lመውሰድ እንጂ 99 ለማድረግ የተዘጋጀ እንኳን አልነበረም፡፡ ይህ ደግሞ ከአብዮቱ ዘመን ጀምሮ የለመድነው ጠባይ ኾኗል፡፡

ኔልሰን ማንዴላ ከተፈቱ በኋላ በተደረገው የመጀመሪያው የደቡብ አፍሪካ ምርጫ ፓርቲያቸው ብቻውን ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል የሚችልበትን የአሸናፊነት ድምፅ አላገኘም ነበር፡፡ ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ አገዛዝ ለማላቀቅ ግማሽ ምእት ዓመት ያህል የታገለው የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ያን የአሸናፊነት አክሊል ያለመቀዳጀቱን በተመለከተ ማንዴላ ተጠይቀው ሲመለሱ፡- ‹‹መቶ በመቶ ማሸነፍ አልነበረብንም፡፡ ያ ቢኾን ኖሮ ማንንም ሳናማክር ሕገ መንግሥቱን እንዳሻን እናደርገው ነበር፡፡ አሁን ግን የግድ ከሌሎች ጋር መወያየት፣ መግባባት እና መተማመን ያስፈልገናል፡፡ ታዲያ ከሌሎች ጋር አብረን እንድ ንሥራ ከሚያደርገን ድል በላይ ምን ድል አለ?›› ነበር ያሉት፡፡

በእኛም ቤት እንዲህ የሚል ጠፍቶ ነው ያ ሁሉ ትርምስ የተፈጠረው፤ ብዙዎችም ያገኙትን ዕድል እንደ ዋዛ ያጡት፡፡

ይህ መቶ በመቶ ካላሸነፍኩ የሚያሰኝ አባዜ በአንዳንዶች የጓደኝነት እና የትዳር ሕይወት ውስጥም እናየዋለን፡፡ አብረው ኖረው፣ ተዋደናል ብለው፣ ስንት ታሪክ ሠርተው የነበሩ ባል እና ሚስት ወይም ጓደኛሞች በመካከላቸው ጠብ የተፈጠረ ዕለት ይኸው በሽታ ያገረሸባቸዋል፡፡ ሁለቱም መቶ በመቶ ማሸነፍ ስለሚፈልጉ ያኛውን ወገን ለመጉዳትም ኾነ አፈር ድሜ ለማስጋጥ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም፡፡ ሁለቱም ወገኖች ያኛው ወገን ተዋርዶ፣ አንገቱን ደፍቶ፣ ደኽይቶ፣ አጥቶ ነጥቶ፣ ተንከራትቶ፣ ወድቆ ካላዩት በስተቀር አይረኩም፡፡

በመካከል ሽማግሌ ገብቶ ለማስታረቅ ሲሞክር እንኳን ይቅርታ ካልጠየቀኝ/ ካልጠየቀችኝ የሚል እንጂ ይቅርታ ልጠይቅ የሚል ወገን ማግኘት ከባድ ነው፡፡ ያኛውን አካል እግር ሥር አንበርክኮ፣ ጫማ ሲስም እና ሲማፀን ማየት ያስደስታቸዋል፡፡ ‹‹የ'ታባቱ/ የ'ታባቷ ተንበርክኮ /ተንበርክካ ለመነኝ/ለመነችኝ›› ብሎ መፎከር ጀግንነት ነው፡፡ በተወሰነ መልኩ እንኳን ለመሸነፍ የተዘጋጀ ስለማይኖር ማስታረቁ ከባድ ይኾናል፡፡

ብዙ ጊዜ እንዲያውም ዕርቅ አስቸጋሪ የሚኾነው ሁለቱ ታራቂ ወገኖች መቶ በመቶ አሸንፈው መውጣት ስለሚፈልጉ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ'ኮ ከዕርቁ ስምምነት በኋላ ሁለቱም ወገኖች የሚተርኩትን ስንሰማ በቦክስ መድረክ አንዱ ሌላውን ዘርሮት ቀበቶ ውን ተሸልሞ የመጣ እንጂ ተደራድሮ፣ ተስማምቶ፣ ሰጥቶ እና ተቀብሎ፣ የተወሰነ ተሸንፎ፣ የተወሰነ አሸንፎ የተስማማ አይመስልም፡፡

የአገራችንን የንግድ ሂደት ስናየው ‹‹መቶ በመቶ የማሸነፍ›› ጠባይ የተጠናወተው ነው፡፡ ተደብቆ ወደ አምራች አገር ሄዶ፣ ተደብቆ ዕቃ አምጥቶ፣ ጉቦ ሰጥቶ ከጉምሩክ አውጥቶ፣ የእርሱ ዕቃ ብቻ ገበያ ላይ እንዲውል አድርጎ፤ ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ 100% አትርፎ ሲገኝ ነው የሚረካው፡፡ ሸማቹም ቢኾን ያለ ዋጋው ዋጋ ሰጥቶ ካልገዛ በቀር አይረካም፡፡ 30 በመቶ፣ 40 በመቶ፣ 50 በመቶ የሚባል ትርፍ ከትርፍ አይቆጠርም፡፡ ማጭበርበርን እና ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ መሸጥን የሚያስከትለው ይህ ‹መቶ በመቶ ካላተረፍኩ› የሚያሰኝ አባዜ ነው፡፡

ተቋራጩም ቢኾን አውጥቶ አውርዶ፣ ደረጃ አሳንሶ፣ የዕቃ ጥራት ቀንሶ፣ ነካ ነካ አድርጎ ዛቅ ያለ ትርፍ ካላተረፈ የሥራ አይመስለውም፡፡ ትላንት የተመረቀ ሕንፃ ዛሬ ተሰንጥቆ፤ የምረቃው ዕለት ድልድዩ ሲጠገን፣ የርክክቡ ጊዜ መንገዱ ነቅቶ፣ አፉን ከፍቶ ኡኡ ሲል የምናየው ወይ ተቋራጩ መቶ በመቶ ለማትረፍ ሲል ከተገቢው ደረጃ በታች ሠርቶት ነው፤ አለበለዚያም ደግሞ አሠሪው መቶ በመቶ ለመብላት ሲል በዚህ መንገድ አሠርቶት ነው፡፡

አንድን አካል ፍጹም አድርጎ የማወደሱ አባዜ የመጣውም ከዚህ መቶ በመቶ ካላሸነፍ ከሚል ጠባይ ነው፡፡ ‹‹የእኛ የኾነው መልአከ ነው፡፡ ያኛው ደግሞ ሰይጣን ነው፡፡ በመካከል ምንም ነገር የለም፡፡ መልአኩን ስናወድስ ምንም ዐይነት እንከን አይታየንም ወይም ለማየት ፈቃደኛ አይደለንም፡፡ የማይሳሳት፣ ቅን አሳቢ፣ የልማት አርበኛ፣ ታጋሽ፣ ጀግና፣ ንጹሕ፣ ምንጊዜም በጎ ነገር ብቻ የሚሠራ አድርገን ነው የምንስለው፡፡ ይኽን እና ያንን ተሳስቷል ብለን ብንናገር ከ100% ስለሚቀንስብን ዐይኔን ግንባር ያድርገው ነው የምንለው፡፡ ያኛው ወገንም ቢኾን አንድ ቀን ተስቶ ስለ እርሱ ደካማ ጎን የተነገረ እንደ ኾነ tናጋሪውን እንደ ጠላት ነው የሚያየው፡፡

በተቃራኒው ደግሞ የሌላው ወገን ደግነት፣ ቅንነት፣ በጎነት፣ መልካም ሥራ፣ ንጽሕና የማይታየው አለ፡፡ እርሱ ስለ ተቃወመው እና ስለ ጠላው ብቻ ስንዴ ቢያመርት ‹‹እንክርዳድ ነው››፤ ጠላ ቢጠምቅ ‹‹አተላ ነው››፤ ጠጅ ቢጥል ‹‹አንቡላ ነው››፤ መን ገድ ቢሠራ ‹‹በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ጊዜ የታሰበ ነው››፤ ት/ቤት ሲገነባ ‹‹ጥራት የለውም››፤ ከማለት ውጭ አንዷንም ቅንጣት በጎ ሥራ ለማየት ፈቃደኛ አይኾንም፡፡ «ከጠላት በጎ ነገር አይገኝም´ የሚለው አባዜ ስላለ መቶ በመቶ መጥላት እንጂ ‹98 በመቶ ለመጥላት› እንኳን ፈቃደኛ አይኾንም፡፡ ተቃራኒውን ጠላት አድርጎ ስለሚያየው የሚ ረካው መቶ በመቶ ሲጠፋ እንጂ በግማሽ ሲሻሻል ለማየት እንኳን በጀ አይልም፡፡

በአገራችን የፊልም ኢንዱስትሪ በማደግ ላይ ነው፡፡ ይህ ኢንዱስትሪ ከገጠሙት ፈተናዎች አንዱ ግን ‹‹መቶ በመቶ የማሸነፍ አባዜ›› ነው፡፡ የፊልሙ ባለቤት መቶ በመቶ ማትረፍ ስለሚፈልግ ብዙ ከፍያ የማይጠይቁ ባለሞያዎችን ለማሰባሰብ ይተጋል፤ ‹‹ገንዘብ የለኝም፤ ለሞያው ፍቅር ብዬ ነው›› እያለ በመለመን ያሠራል፡፡ አንዳንዶቹን በርዳታ፣ ሌሎቹን በአነስተኛ ከፍያ ያሠራል፡፡ እንዲህ እያደረገ ለወግ ለማዓርግ ከደረሰ በኋላ ፊልሙ ሲመረቅ የደረቀ አበባ ከመስጠት ያለፈ ባለውለታዎቹ ትዝ አይሉትም፡፡ ‹‹እነ እገሌ ረድተውኛል›› ለማለት እንኳን ይኮራል፡፡

በገንዘቡ ብቻ ሳይኾን በአሠራሩ ላይም ‹‹መቶ በመቶ የማሸነፍ አባዜ›› አለ፡፡ ባለቤ ቱም፣ ዳይሬክተሩም፣ ተዋናዩም እኔ ያልኩት ብቻ ይኹን ይላሉ፡፡ ማንም ለማንም የማርያም መንገድ እንኳን ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም፡፡ ሁሉንም ሊያግባባ/ ግን የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ የሚችል መንገድ ከመፈለግ ይልቅ ሁሉም ለማሸነፍ ስለሚጥሩ እና በኋላ ፊልሙ ሲወጣ ‹‹እንደዚህ'ኮ ነበር፤ በኋላ'ኮ እኔ ነኝ እንደዚህ ያስደረግኹት›› ማለት ስለሚፈልጉ ፊልሙን ለመሥራት ከወሰደው ጊዜ በላይ የእነርሱ ገሃዳዊ እና ውስጣዊ ትግል ረጅም ጊዜን ይወስዳል፡፡

አሁን አሁን እየተለወጠ መጣ እንጂ'ኮ በመንግሥት ሚዲያ እና በግሉ ሚዲያ መካከል የነበረው ትግል «መቶ በመቶ ካላሸነፍኩ´ በሚለው አባዜ የተቃኘ ትግል ነበር፡፡ ለመንግሥት የብዙኀን መገናኛ የመንግሥት ስሕተት አይታየውም፤ ‹‹ቅዱስ መንግሥት›› ነውና፡፡ ለብዙዎቹ የግል ሚዲያዎች ደግሞ የመንግሥት ስሕተት እንጅ በጎ ጎኑ፣ መልካም ሥራው ፈጽሞ አይታያቸውም፤ ‹‹ርኩስ መንግሥት›› ነውና፡፡ ሁለቱም ‹‹መቶ በመቶ ማሸነፍ›› ስለሚፈልጉ ለመቀራረብ እና በተወሰነ መልኩ የጋራ ጠባይ ሊኖ ራቸው እንኳን አልቻለም፡፡ ድረ ገጾቻችንን እንኳን ስናይ ወይ ስለ ‹‹ቅዱስ መንግሥት›› አለበለዚያም ስለ ‹‹ርኩስ መንግሥት›› የሚተነትኑ እንጂ ለማጣጣም እና ሚዛናዊ ለመኾን የሚሞክሩ አይደለም፡፡ እንዲህ ያሉትን ገጸ ድሮች ለማግኘት ከባድ ነው፡፡

በቀን የሚሸነፍ ጨረቃ፣ በሌሊት የሚሸነፍ ፀሐይ በሌለበት ቦታ ጽንፈኝነት ሥር ይሰድዳል፡፡ ሰውዬው በአርባዎቹ መጨረሻ እና በጎምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር አሉ፡፡ ታዲያ ጣለበትና ሁለት ሚስቶችን አገባ፡፡ አንዷ ወጣት ሌላዋ

ባልቴት፡፡ ወጣትዋ ‹‹ባልሽ ሽማግሌ ነው›› መባል ስለማትፈልግ ወጣት ለማድረግ ቆርጣ ተነሣች፤ ባልቴ ቷም ‹‹ወጣት አግብታ ትመናቀራለች›› ላለመባል ባልዋን ሽማግሌ ለማድረግ ታጥቃ ተነሣች፡፡ ሁለቱም ሚስቶች ለዚህ ውሳኔያቸው የወሰዱት ርምጃ ወጣትዋ ሽበቱን መንቀል፣ ባልቴቷም ጥቁሩን ፀጉር መንቀል ነበር፡፡ ሁለቱም መቶ በመቶ ለማሸነፍ ስለ ፈለጉ የሚያግባባ መካከለኛ ነገር ለማግኘት እንኳን አልቻሉም፡፡ እናም አንዷም ነጩን ሌላውም ጥቁሩን ፀጉር ነቅለው ነቅለው በመጨረሻም መላጣ አደረጉት ይባላል፡፡ ቢያንስ ከጥቁሩም ተቀንሶ ከነጩም ተቀንሶ ሰውዬው ጎልማሳ የሚኾንበትን መንገድ እንኳን ቢያስቡ ምን ነበረበት ?!

ሁልጊዜም የሚገርመው ነገር ይህ ነው፡፡ በነጭ እና በጥቁር መካከል ግራጫ የሚባል ነገር የለንም፡፡ አማራጫችን ሁሉ ወይ ነጭ አለበለዚያም ጥቁር ብቻ ነው - ቀን ወይም ሌሊት፤ ቅዱስ ወይም ርኩስ፤ መልአክ ወይም ሰይጣን ብቻ ነው፡ ፡ ካለፈው ታሪ ካችን ለመማር እና በጎዎቹን ይዘን ስሕተቶችን አርመን ለመጓዝ ያልታደልነውም አዲስ የሚመጣ ሁሉ ያለፈውን መቶ በመቶ ካልቀየረ ወይም ካልተቃረነ በቀር የኖረ ስለማይ መስለው ነው፡፡ አዲስ አለቃ እንኳን በየመ/ቤቱ ሲመደብ ቢቻል ሌላ ቢሮ ቢቀመጥ፣ ካልተቻለም ወንበር እና ጠረጴዛውን ቀይሮ ቢቀመጥ የሚመርጠው መቶ በመቶ ለመለ የት እና ለማሸነፍ ነው፡፡ ደርግ የንጉሡን ውርስ ድራሹን አጠፋው፤ አሁን የመጣውም የደርግን ውርስ አጠፋ፤ ተቃዋሚ ኾነው ነገ መንግሥት መኾን የሚመኙትም የኢሕአዴግን ውርስ ካላጠፉ የነገሡ አይመስላቸውም፡፡ ተቻችሎ፣ ተወራርሶ፣ ተመቻምቾ (compromise) ለመጓዝ ፈቃደኝነቱ አይታይም፡፡

በሃይማኖቶች መካከልም ይኸው መቶ በመቶ የማሸነፍ አባዜ እየተንጸባረቀ ነው፡፡ የራሱን አጉልቶ የሌሎችን ተችቶ የሐሳብ ክርክር እና የአስተምህሮ ልዕልናን ከማሳየት ይልቅ የእርሱን መኖር ከሌሎች መጥፋት ጋር ያያይዘዋል፡፡ የእርሱ መኖር የሚረጋገ ጠው ሌሎች ሲጠፉ ብቻ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ፈጣሪ ለምን ሰይጣንን ጨርሶ ማጥፋት እንዳልፈለገ እንኳን ለመመርመር ፈቃደኛ አይደለም፡፡ እንደ እኔ እምነት ግን ተቃራኒን መቶ በመቶ ማጥፋትን ከእርሱ እንዳንማር ፈልጎ ይመስለኛል፡፡

አንዱ ሌላውን ይተች፤ እርሱም ሲተች፣ ሲነቀፍ ይቀበል፤ ሌላውን ጨርሶ ለማጥፋት መነሣትን ግን ምን አመጣው? ነጥብ ለማስቆጠር ብቻ ሳይኾን ነጥብን ለመቀ በልም ፈቃደኛ መኾን ያስፈልጋል፡፡

ርኅራኄ የሚባለው ነገር መቶ በመቶ ካላሸነፍኩ የሚል አባዜ ባለበት ቦታ አይገኝም፡፡ ሰውን ከገደሉ በኋላ መቆራረጥ፣ ከመ/ቤት ካባረሩ በኋላ ሌላ ቦታ እንዳይቀጠር ነገር ዓለሙን (ማኅደሩን) ማበላሸት፣ ከፊቱ ለፊቱ ተመሳሳይ ሱቅ መክፈቱ ሳያንሰው ንግድ ፈቃዱን ለማስነጠቅ መኳተን፣ አንድን ሰው እስከ መጨረሻው መበቀል፣ ርኅራኄ ሲጠፋ የሚከሠቱ ናቸው፡፡

ድሮ ልጅ ኾኜ ያነበብኹት አንድ የተረት መጽሐፍ እንዲህ የሚል ታሪክ ነበረው፤ የበግ *ሥጋ* መንገድ ላይ ወድቆ ያገኙ ሁለት ቀበሮዎች ለእኔ ይገባል ለእኔ ይገባል እየተ ባባሉ መጣላት ጀመሩ፡፡ *ሥጋ*ውን ለመካፈልም ኾነ ሸጠው ገንዘቡን ለመካፈል ፈቃደኞች አልኾኑም፡፡ መንገድ አላፊዎች ሁሉ የተለያዩ አማራጭ የዕርቅ ሐሳቦች ቢያመጡላቸውም ሁለቱም ‹‹*ሥጋ*ው ሳይነካካ መቶ በመቶ ካላገኘን ሞተን እንገኛለን፡፡›› አሉ፡፡ ተናከሰው ተናከሰው ተዳከሙ እና ሁለቱም ወደቁ፡፡ በዚህ መካከል አንዲት ቡችላ በዚያ መንገድ ስታልፍ ሁለት ቀበሮዎች ቆስለው ወድቀው አንድ ሙዳ *ሥጋ* መካከላቸው ተጋድሞ ታያለች፡፡ ወዲያው ግራ ቀኙን ተመልከታ *ሥጋ*ውን አፈፍ አደረገችና በረረች፡፡

ይህን ትዕይንት የተመለከተ መንገደኛ፡-

ቀበሮ ሲጣላ፣
ተስማምቶ እንዳይበላ፣
መንትፋቸው ሄደች፣
ዘዴኛ ቡችላ፤- ብሎ ገጠመ አሉ፡፡

ሥጋውን መቶ በመቶ እኔ ብቻ ነኝ የምበላው ማለት፣ ሥጋውን ለሁለቱም የማይበጅ ሦስተኛ አካል እንዲበላው አሳልፎ መስጠት ማለት ነው፡፡

23. ሀገር እንወዳለን

ሰውዬው የውጭ ሀገር ዜጋ ቢሆኑም ዐሥር ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ አስተምረዋል፡፡ ሚስተር ዣክ ይባላሉ፡፡ ሻሂ እየጠጡ ኢትዮጵያዊውን ጓደኛቸውን እየጠበቁ ነው፡፡ ሁለት ጊዜ ፉት እንዳሉት ጓደኛቸው ከች አለ፡፡ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የተጠለፈበት ቆብ አድርጓል፡፡ በለመዱት የኢትዮጵያውያን ባህል መሠረት ከመቀመጫቸው ተነሥተው ተቀበሉት፡፡ ወንበር ስቦ እንደ ተቀመጠ ያጠለቀውን ቆብ ጠረጴዛው ላይ አኖረው፡፡ ሚስተር ዣክ የተቀመጠውን በኢትዮጵያ ባንዴራ የተጠለፈ ቆብ አየት አደረጉና «እናንተ ኢትዮጵያውያን ለምንድን ነው በባንዴራችሁ ማጌጥ የምትወዱት?» አሉና ኢትዮጵያዊውን እንግዳቸውን ጠየቁት፡፡

«እኛ ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን እንወዳለን፡፡ በሀገራችን ለመጣ ርኅራኄ የለንም፡ ይህ የሀገር ፍቅር በደማችን ውስጥ አራተኛ ሴል ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ለዚህ ነው» አላቸው፡፡

«ቆይ ግን ሀገራችንን እንወዳለን ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው? ለመሆኑ ምኑን ነው የምትወዱት? ለእናንተ ሀገር ማለትስ ምን ማለት ነው? ወንዙ እና ተራራው ነው? ሜዳው እና ጫካው ነው? ምኑ ነው ሀገር?»

ኢትዮጵያዊው ትኩር ብሎ እያያቸው «ሁለመናው ነው፡፡ ሰው፣ እንስሳው፣ ሜዳው፣ ተራራው፣ ጫካው፣ ወንዙ፣ ሁሉም» አለና መለሰላቸው፡፡

«እኔ ግን አይመስለኝም» አሉት ሚስተር ዣክ፡፡

«እንዴት?» ተገርሞ ጠየቃቸው፡፡

«እናንተ ለሀገራችሁ የድመት ፍቅር ይመስለኛል ያላችሁ»

«የድመት ፍቅር ምን ዓይነት ነው» እንግዳው ተገርሞ እንደገና ጠየቀ፡፡

«ቤት ያከራዩኝ ሰውዬ ምን እንዳሉኝ ታውቃለህ፡፡ ድመት ልጆቿን የምትበላው ስለምትወዳቸው ነው፡፡ ፍቅሯን የምትገልጠው ልጆቿን በመብላት እና ለዘላለም ሆዷ ውስጥ በማድረግ ነው አሉኝ»

«እና»

«እናማ እናንተም ለሀገራችሁ ያላችሁን ፍቅር የምትገልጡት ሀገራችሁን በመብላት ይመስለኛል»

«ያንን ያህል እንደርሳለን ብለው ነው» አንገቱን ወዘወዘ እንግዳው፡፡

«ኧረ እንዲያውም ሳይብስ አይቀርም፡፡ አሁን ለምሳሌ እናንተ ኢትዮጵያውያን በቅኝ ገዥዎች ባለመገዛታችሁ ስትኮሩበት አያለሁ፡፡ ልክ ነው ለጀግኖች አባቶቻችሁ ምስጋና ይግባቸውና ለዚህ የታሪክ ዕድል አብቅተዋችኋል፡፡ የሦስት ሺ ዘመን የነጻነት ታሪክ አለን እያላችሁ በኛ በአፍሪካውያን ላይ ትኮሩብናላችሁ እንጂ በሦስት ሺ ዘመን ምን ሊሠራበት እንደሚችል አላሳያችሁንም፡፡ ነጻነትን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል አሳያችሁን እንጂ በነጻነት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አርአያ ልትሆኑን አልቻ ላችሁም፡፡ እርስ በርስ ስትዋጉ፣ አንዳችሁ የሠራችሁትን ሌላችሁ ስታጠፉ፣ መቶ ዓመት የለፋቸሁበትን በአንድ ቀን ደምስሳችሁ እንደገና ስትጀምሩ ነው የኖራችሁት፡፡ እስቲ ተመልከቱት የሦስት ሺ ዘመን ታሪክ አለን ነውኮ የምትሉት፡፡ ታድያ ሦስት ሺ ዘመን ተጉዛችሁ እዚህ መድረስ ብቻ ነው የቻላችሁት? አቆጣጠራችሁ ግን በምንድን ነው? አንድ ዓመትስ በእናንተ ዘንድ ስንት ቀን ነው?

«ለመሆኑ ሀገራችሁን ስለምትወዱ ነው እርስ በርስ ስትዋጉ የኖራችሁት? ሀገራችሁን ስለምትወዱ ነው የቀደመውን እያፈረሳችሁ እንደ አዲስ የምትጀምሩት? ወንዙን ሰው ሲነካባችሁ ዘራፍ ብላችሁ ትነሣላችሁ፤ እናንተ ግን ወንዙን አትጠቀሙበትም፡፡ መሬቱን ሰው ሊቆርስ ሲመጣ አራስ ነብር ሆናችሁ ትነሣላችሁ፤ እናንተ ግን መሬቱን አታለ ሙትም፡፡ ቅርሳችሁን ሰው ሊዘርፍ ሲመጣ የቻለ ይዘምታል ያልቻለ ያቅራራል፤ እናን ተም ግን ቅርሱን አትጠብቁትም፡፡ አሁን ይሄ ምቀኝነት ነው ወይስ ሀገር መውደድ ነው?»

ኢትዮጵያዊው እንግዳ ያልጠበቀው ነገር ስለመጣበት ትክዝ እንደማለት አለና «በርግጥ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ዋልጌዎች የሚሠሩት ሥራ ግን መላውን ሕዝብ መወከል የለበትም» አላቸው፡፡

«ልክ ነህ» አሉ ሚስተር ጣኪ «ልክ ነህ ጥቂቶች ሁሉንም አይወክሉም፡፡ የማየው ነገር ግን ይህንን አባባልህን እንዳልቀበለው ያስገድደኛል፡፡ ተመልከት ቅቤው ውስጥ ሙዝ እየጨመረ የሚሸጠውኮ የራሳችሁ ሰው ነው፡፡ ለውጭ ሀገር አይደለም የሚሸጠው ለገዛ ጎረቤቱ ነው፡፡ ሂድ እስኪ በየሱቁ ስንት ጊዜው ያለፈበት የታሸገ ምግብ ይሸጣልኮ፡፡ ገዥው የሌላ ሀገር ሰው አይደለም፡፡ የራሳችሁ ወገን ነው፡፡ ያደረ ኬክ፣ ያደረ ምግብ፣ የተበላሸ ሥጋ የምትሸጡትኮ ለጠላት ሀገር አይደለም ለራሳችሁ ሰው ነው፡፡ አሁን እነዚህ ሰዎች ሀገራችንን እንወድዳለን ብለው ግሥላ ሲሆኑ ባይ ይገርመኛል፡፡ ወገናቸውን እየገደሉ ምኑን ነው የሚወድዱት እላለሁ፡፡ አሥር ብር የገዛችሁትን ዕቃ አንዳች እሴት ሳትጨምሩበት በገዛ ወገናችሁ ላይ መቶ ብር አትርፋችሁ ያለ ርኅራኄ እየሸጣችሁ ሀገራችሁን ትወድዳላችሁ ማለት ነው?»

«መሬቱን ብቻ ነው እንዴ ሀገር የሚሉት? በአንድ መንደር ውስጥ የሚገኝ መሸታ ቤት መንደርተኛውን እየበጠበጠ ስላስቸገረ የቀበሌ ጥበቃዎች መጡና ድምጽ ቀንሱ አሏቸው፡፡ እነርሱም እሺ አሉና የሚገርም ዘፈን ከፈቱ አሉ፡፡»

«ምን የሚል?»

«እኛም አንተኛ ሰውም አናስተኛ የሚል»

«ሆሆይ! ይህቺን አገር አገላብጠው ነውኮ የሚያውቋት» አለ እንግዳው ተደንቆ፡፡

«ሂድና ሠራተኛውን እየው፡፡ ሌላ ትርፍ ሀገር ያለው፣ በቅኝ ገዥዎች ተገድዶ የሚሠራ ነውኮ የሚመስለው፡፡ አንዳንዱ ዘግይቶ ይገባል፣ አንዲት ነገር ሳይሠራ ለሻሂ ይወጣል፤ እጁን ወደ ኋላ አጣምሮ እየተዝናና ቢሮ ይመለሳል፣ አንዲት ነገር ሳይሠራ ለምሳ ይወጣል፡፡ አንድ ነገር ከጠየቅከው «ነገ፣ ነገ» ነው የሚለው፡፡ ነገ መቼ እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ግንባታዎቻችሁ ለጠላት ሀገር የሚሠሩ እንጂ እንወድዳታለን ለምትሏት ሀገር የሚሠሩ አይመስሉም፡፡ የሚጀመሩበትን እንጂ ግንባታው የሚያልቅበትን ጊዜ ማንም አያውቅም፡፡ ተሠርቶ ሳይመረቅ ይፈራርሳል፡፡ ከሚሠራበት ገንዘብ የሚበላው ይበልጣል፡፡ ሠራተኛው ምድጃ ከብቦም ተረት ያወራል፣ አካፋ ተደግፎም ሥራ ላይ ተረት ያወራል፡፡

«ለመሆኑ እነዚያ የዚህ ሁሉ ግንባታ ሠሪዎቹ፣ አሠሪዎቹ፣ ተቆጣጣሪዎቹ አሁን አንተ እንደ ምትለኝ ሀገራቸውን ይወዳሉ ማለት ነው? የትኛዋን ሀገር ነው የሚወድዱት? ወይስ እኛ የማናውቃት ሌላ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አለቻችሁ? ቻይናዎቹ ያሉትን ሰምተሃል?»

«ምን አሉ?»

«መንገድ ሲሠሩ፣ እነርሱ ቀን ቀን የሠሩትን እና የሰበሰቡትን የአካባቢው ሰው ሌሊት ሌሊት አፍርሶ እና አግዞ እየወሰደ አስቸገራቸው፡፡ በኋላ እንደ እኔው ሀገራችሁን ትወዳላችሁ ሲባል ሰምተው ስለነበር «ቆይ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ሌላ ሀገር አላቸው እንዴ? ከሀገራቸው ሰርቀው የት ነው የሚወስዱት?» አሉ ይባላል»

«አሁን አሁንኮ ትውልዱ ጉዳዩን እያስተዋለ እየተለወጠ ነው፡፡ ምናልባት ቀድሞ እንዲህ ያለ ነገር ሊኖር ይችላል» አለ ኢትዮጵያዊው እንግዳ፡፡

«የለም የለም እንዲያውም ብሷል፡፡ አዲሱ ትውልድ የምትለው የሚገኘውኮ እኔ በማስተምርበት ኮሌጅ ነው፡፡ አየሁትኮ፡፡ ቤተ መጻሕፍት ገብቶ በድኻ ሀገር በጀት የታተመ መጽሐፍ የሚሰርቅ፣ የሚቀዳድድ፣ እላዩ ላይ ትርኪ ምርኪ ነገር የሚጽፍ ይህ ነው ሀገር ወዳዱ ትውልድ? ከእርሱ ቀጥሎ እዚህ ትምህርት ቤት የሚማረው የራሱ ወንድም እና እኅት መሆኑን እንኳን የሚረሳው ነው ሀገር ወዳዱ? ከዕውቀት ክርክር ይልቅ በጎጠኛነት ተቧድኖ መደባደብ የሚቀናው ነው ሀገር ወዳዱ ትውልድ? ነገሩ ምን ያድርግ የሚያስተምሩትም ቢሆኑኮ የሀገራቸውን ሰው የሚያስተምሩ፣ እንወዳታለን ለሚሏት ሀገር ትውልድ ሊያፈሩ የሚያስተምሩ አይመስሉም፡፡ የዛሬ ሃያ ዓመት ባዘጋጁት ማስታወሻ እያስተማሩት፣ ከቤተ መጻሕፍት አውጥተው ቢሮአቸው የደበቁትን መጽሐፍ ማጣቀሻ እየሰጡ ጥናት

እያዘዙት ምን ያድርግ፡፡ በገጠሩ ሴት ልጅ በልጅነቷ ተጫውታ ሳትጨርስ ትዳርና በልጅነቷ ትወልዳለች፡፡ እርሷም ልጅ፣ የወለደችውም ልጅ ይሆንባትና አብረው እየተጫወቱ ያድጋሉ፡፡ አሁንም ኮሌጃችሁን እንደዚያው አደረጋችሁትኮ፡፡

«አሁን በየሕክምና ቦታው የሚሠራው የድሮው ትውልድ ነው ልትለኝ ነው? ለመሆኑ እርሱ ሀገር ወዳድ ነው? ጊዜ ባለፈበት መድኃኒት ወገኑን የሚያክመው፣ በመንግሥት በጀት የተገዛ መድኃኒት አውጥቶ የሚሸጠው፣ ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ የሌለ ምርመራ እያዘዘ ድኻው ተማርሮ ከሕክምና ይልቅ ወደ ዳማ ከሴ እንዲጓዝ ያደረገው ሀገሩን ስለሚወድድ ነው?

«እስቲ የመኪና ምርመራ እንዴት እንደሚደረግ ተመልከት፡፡ መኪናው ሳይታይ በስልክ እኮ ነው የሚመረመረው፡፡ ለመሆኑ መርማሪው ሰውዬ ይሄ መኪና እርሱን፣ ቤተሰቡን፣ ዘመዶቹን እንደማይገጭ ርግጠኛ ነው? ሀገሩን ስለሚወድ ነው ሕዝብ እንዲያልቅ ፈቅዶ የተበላሸ መኪና ጤነኛ ነው ብሎ የሚፈርመው?

«በአንድ ወቅት አዲስ አበባ መንገዶቿን ሰየመች ተብሎ በየቦታው ተለጠፈ፡፡ ሦስት ወር አልሞላውም ሲወድቅ እና ሲጠፋ፡፡ ማን ዘረፈው? ሀገር ወዳዱ፡፡ ተካዮቹስ ቢሆኑ ለምን ዘወር ብለው አላዩትም? ሀገር ወዳድ ስለሆኑ፡፡

«እኔ ሀገር የመውደድን ጉዳይ አሁን እርስዎ ባሰቡበት መንገድ አስቢው አላውቅም፡፡ ብቻ እኛ የሀገራችን ጉዳይ ሲነሣ ደመ ቁጡዎች፣ አትንኩን ባዮች እና ኮስታሮች መሆናችንን አውቃለሁ፡፡» አለ ኢትዮጵያዊው እንግዳ፡፡

«ልክ ነህ ይህንንማ ዓለም በሙሉ ይመሰክርላችኋልኮ፡፡ ይህች ሀገርኮ ዝም ብላ እንዲሁ በነጻነት አልኖረችም፡፡ አንዳች ልዩ ነገርማ አላችሁኮ፡፡ ሀገራቸውን ባይወድዱ ኖሮ አባቶቻችሁ ደማቸውን ባልገበሩ ነበር፡፡ አጥንታቸውን ከስክሰው ድንበር ባላጠሩ ነበር፡፡ ዘመናዊ መሣርያ የታጠቁትን በባህላዊ መሣርያ ባላሸነፉ ነበር፡፡ ግን ሀገር መውደድ ይሄ ብቻ ነወይ) ሌላ አይንካን እኛ ግን እንደፈለግን እንጫረስ፣ ሌላ አይዝረፈን እኛ ግን እንዘራረፍ፣ ሌላ አይጨቁነን እኛ ግን እንጨቋቆን፣ ቅኝ ገዥ መጥቶ ቀንበር የሆነ ሕግ አያውጣብን እኛ ግን እርስ በርሳችን ቀንበር እንጫጫን፣ ጠላት ወርሮ መብታችንን አይንካ፣ እኛ ግን መብታችንን እርስ በርስ እንገፋፈፍ ነው የምትሉት) ይሄኮ ነው ያልገባኝ ነገር፡፡ ሀገር ማለትኮ መልከዐ ምድሩ ብቻ አይደለም፤ ይሄ ባለጉዳይ ሆኖ ቢሮህ የመጣው፣ታምሞ ሊታከም አንተጋ የመጣው፣ ሊማር አንተ ጋ የመጣው፣ሊገዛ ሱቅህ ጋ የቆመው፣ በሞያህ እያገለገልከው ያለኸው፣በመኪናህ ላይ የተሳፈረው፣ እርሱኮ ነው ሀገር» አሉ ሚስተር ጣኪ፡፡

«እንዴ ሚስተር ጣኪ በዐሥረኛው ዓመት ሀገራችን መረረዎት መሰለኝ፡፡ እርስዎም እንደኛው ደመ ቁጡ ሊሆኑ ነው ማለት ነው፤ባለፈው ታምመው ተኝተው እያለ የኢትዮጵያዊ ደም ነበር እንዴ የተደረገልዎ» አለ ኢትዮጵያዊው ነገሩን ወደ ቀልድ ወስዶ ሀሳብ ለማስቀየር፡፡

«አየህ ይህች ሀገር ይበልጥ ስታውቃት ይበልጥ የምታሳዝን፣ ይበልጥ የምታስቆጭ፣ ይበልጥ የምታንገበግብ ናት፡፡ ቆይ ግን ይህንን ሁሉ የምታደርጉት ሀገራችሁን ስለምትወዱ ከሆነ ሀገራችሁን ባትወድዱ ኖሮስ ከዚህ የከፋ ምን ታደርጉ

ነበር?አንድ እዚህ ሀገር የሰማሁት ቀልድ ነገር አለ፡፡ አንድ ባል ሚስቱን ይደበድባታል፡፡ እርሷም ቤቷን ትታ ትወጣለች፡፡ በኋላ ሽማግሌ ገብቶ ታረቁ ይላቸዋል፡፡ ባልም እኔኮ ስለምወዳት ነው የመታኋት፣ የፍቅር ነው ይላል፡፡ ሚስቲቱም ስትወደኝ ከሆነ እንዲህ የምትመታኝ ስትጠላኝ ምን ልታደርግ ነው? አለችው አሉ፡፡ አሁንም እናንተ በሀገራችሁ ላይ ራሳችሁ ይህንን ሁሉ ግፍ የምትፈጽሙት ሀገር ወዳድ ስለሆናችሁ ከሆነ ብትጠሏት ኖሮ ምን ልታደርጉ ነበር?

24. ፕሮፌሰር ሳቤክ

አንድ መምህር ስለ source credibility ለተማሪዎቻቸው የሚከተለውን ገጠመኝ ተናገሩ፡፡ አንድ ጊዜ ከጓደኞቻችን ጋር ተሰብስበን በአንድ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ነበር፡፡ እኔም አንድን ሃሳብ አነሣሁና ሙግት ጀመርን፡፡ ያንን ሃሳቤን ለማስረዳት ያቀረብኳ ቸውን ማስረጃዎች እና መከራከርያዎች ወዳጆቼ ሊቀበሉኝ አልቻሉም፡፡ በኋላም አንድ ሃሳብ መጣልኝ፡፡ የኔውን ሃሳብ እንደገና አሣመርኩና «ባይገርማችሁ ፕሮፌሰር ሳቤክ የተባሉ የታወቀ የእንዲህ ያለ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ምሁር እንዲህ እና እንዲያ ብለዋል» እያልኩ ማስረዳት ጀመርኩ፡፡ ያን ጊዜ ሁሉም በአድናቆት ያዳምጡኝ፤ ራሳቸውንም ይነቀንቁ ጀመር፡፡ እኔም በፕሮፌሰር ሳቤክ ስም ሃሳቤን ሁሉ አስረድቼ ተቀባይነትም አግኝቼ ቤቴ ገባሁ፡፡

የሚገርማችሁ ግን ፕሮፌሰር ሳቤክ ማለት ፕሮፌሰር ሳ/SA/ ቤክ /BEK/ ማለት «ሳሙኤል በቀለ» ማለቴ ነበር፡፡ ነገር ግን የውጭ ሃገር ምሁር ስም አስመስዬ ስለተናገርኩት ተቀባይነት አገኘሁ፡፡ ያንኑ ሃሳብ ግን እኔ ራሴ አንሥቼ ስከራከርበት ማንም ሊቀበለው ፈቃደኛ አልነበረም፡፡

እንጀራ እንዴት ተቦክቶ እንዴት ይጋገራል? ጥጥ እንዴት ተለቅሞ፣ እንዴት ተባዝቶ፣ እንዴት ተፈትሎ፣ እንዴትስ ይሸመናል? በሬ እንዴት ይጠመዳል፣ እንዴትስ ይታረሳል? ቡና እንዴት ተቆልቶ፣ እንዴትስ ተወግጦ፣ እንዴትስ ይፈላል? ሽሮ እንዴት ወጥ ይሆናል? ለሚሉት ሃሳቦች ሁሉ የግድ የውጭ ሀገር መጽሐፍ እና የውጭ ሀገር ምሁራን፣ የውጭ ሀገር ድርጅቶች እና የውጭ ሀገር ጥናት መጥቀስ ፣በዚያም ላይ ተነሥቶ መከራከር የዐዋቂነት ማሳያ የሆነበት ክፉ ልማድ አለን፡፡

ይህ ልማድ ዛሬ የተፈጠረ ብቻ ሳይሆን ሥር የሰደደ መሠረት ያለው ይመስለኛል፡፡ በእምነት ታሪካችን ውስጥ እንኳን ኢትዮጵያውያን የደከሙባቸውን እና የዕውቀት እና የትጋት ውጤቶቻቸው የሆኑትን ጥበቦች እና ድርሰቶች፣ ቅርሶች እና ሀብቶች በጎበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና ከበሬታን እንዲያገኙ ሲባል ከኢየሩሳሌም የመጡ፣ ከግብጽ የተገኙ፣ ከመካ የወጡ እያልን የፕሮፌሰር ሳቤክን ማዕረግ ስንለግሳቸው ኖረናል፡፡

ብራና ዳምጠው፣ ቀለም በጥብጠው፣ ብርዕ ቀርፀው ታላላቅ ሥራ የሠሩ ቀደምቶቻችንም ኢትዮጵያዊ ስማቸውን ከገለጡ፣ «ነቢይ በሀገሩ አይከበርም» የተባለው ይደርስብናል ብለው በመፍራት የውጭ ሀገር መሠረት ያለው የብዕር ስም እንዲጠቀሙ ተገድደዋል፡፡ በኋላም በዚሁ የስም መኩሸኔነት የተነሣ የደከሙበት ሥራ የእነዚያ የውጭ ሀገር ሰዎች ሥራ እየተደረገ ተቆጥሮባቸዋል፡፡

ሌላው ቀርቶ ይህንን ጠባያችንን ጠንቅቀው ያወቁት የውጭ ሀገር ሰዎች እንኳን የሀገርን ስም የሚያስጠሩ እና የሐበሻን ታሪክ ከፍ አድርገው የሚዘክሩ ነገሮችን በዚያው በተለመደው ልማድ መሠረት ለውጭ ሀገር ሰዎች እየሰጡ እንዲጽፉ እና የስም ዝርፊያ እንዲያካሂዱ አድርገናቸዋል። የላሊበላ የሥነ ሕንፃ ጥበብ በአውሮፓውያን የተገነባ ነው እየተባለ ለብዙ ዘመናት የተነገረው፤ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዐ ያዕቆብና ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወት ኢትዮጵያውያን አይደሉም የተባሉት በዚሁ ልማድ መሠረት ነው።

የፕሮፌሰር ሳቤክ ጉዳይ የእምነት ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ፖለቲከኞቻችንንም የለከፈ በሽታ ነው። በስድሳቹ ኢጋማሽ እና መጨረሻ ለሀገሪቱ እናስባለን ብለው የተነሡት አብዮታውያን ምሁራን የሀገሪቱን ነባራዊ ችግር አጥንተው፤ የሀገሪቱን ነባር ፍልስፍናዎች እና መንገዶች ፈትሸው፤ ለኢትዮጵያዊው ችግር ኢትዮጵያዊ መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ ማርክስ እና ሌኒን ለዚህች ሀገር ከእነርሱ በላይ ያስቡ ይመስል፣ የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ውስጥ ማፈላለግ ነበር የያዙት።

ነገራቸው ሁሉ ሕዝቡ ምን ይላል? እኔ ራሴስ ምን አስባለሁ? ለሀገሬ የሚበጀው ሀገራዊ መንገድስ የቱ ነው? ከማለት ይልቅ ማርክስ እንዲህ ብሏል፣ ሌኒን እንዲህ ብሏል እያሉ እነ ማርክስ እንኳን የማያውቁትን ትርጓሜ እየሰጡ ነበር ሲተላለቁ የነበሩት። «የተሻለው ሀገራዊ ሃሳብ እና መፍትሔ የኔ ነው» ከሚለው ይልቅ የተሻልኩት ማርክሲስት፣ ሌኒኒስት እኔ ነኝ ነበር ክርክሩ።

ከጎጃም እና ጎንደር ይልቅ ሩሲያን እና ዩክሬንን፣ ከወለጋ እና ጋምቤላ ይልቅ ሀንጋሪን እና ቼኮዝሎቫኪያን፣ ከሐዲስ ዓለማየሁ ይልቅ ማክሲም ጎርኪን፣ ከጸጋዬ ገብረ መድኅን ይልቅ ፑሽኪንን፣ ከወንፈል እና ደቦ ይልቅ ወልባ እና ማልባን፣ ያጠኑት የዚህች ሀገር ልጆች ነበሩ መግባባት ያቃታቸው። ለሁሉም ነገር መነሻዎቻቸው እና መከራከርያዎቻቸው ፕሮፌሰር ቴቤክ ናቸው። አንዳንዶቹም የራሳቸውን ሃሳብ ማቅረብ መሸነፍ እና መናቅን ስለሚያስከትልባቸው ቢቻል ለማርክስ እና ሌኒን፣ ባይቻልም ለማዶ እና ለቼ ጉቬራ፣ ያም ካልተሳካ ለፊደል ካስትሮ እየሰጡ ያቀርቡ የነበሩት ይኼው ልክፍት አስገድዷቸው ነው።

የሀገሪቱ ባለ ሥልጣናት እና መሪዎች ለሀገራቸው ጋዜጠኞች ተናግረው፣ ነገ የእነርሱ ቃለ መጠይቅ ሲጠቀስ ትውልደ ኢትዮጵዮውያኑ አዲስ ዘመን እና የኢትዮጵያ ሬዲዮ፣ አዲስ አድማስ እና አዲስ ነገር፣ ሪፖርተር እና በሬሳ ተብሎ ከሚነገር ይልቅ ፋይናንሻል ታይምስ እና ኒውዮርክ ታይምስ፣ ቢቢሲ እና አልጀዚራ፣ ተብለው ፕሮፌሰር ሳቤክ ቢጠቀሱላቸው የሚመርጡ ይመስለኛል። ለዚህም ነው የራሳችንን ጉዳይ በእንግሊዝኛ እና በዐረብኛ ተጽፎ፣ መልሰን በአማርኛ እንድንሰማውና እንድናነበው የሚደረገው።

«የኛ ሙሽራ ኩሪባቸው

በእንግሊዝ አናግሪያቸው» እየተባለ ይዘፈን የነበረው የሠርግ ዘፈን እዚህም ይሠራል ማለት ነው።

የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶችን እና የውጭ ሀገር ታላቅ ድርጅቶችን ሠራተኞች እና ኃላፊዎች ለማሳመን እና ስለሀገሪቱ በእነርሱ አፍ እንዲነገር፣ ብሎም «የእገሌ ሀገር ባለ ሥልጣን የሀገሪቱን ዕድገት አደነቁ፤ እገሌ የተባሉት የዚህ መስሉ ዓለም ዐቀፍ ድርጅት ልዑክ ኢትዮጵያ በአስደናቂ ዕድገት ላይ ናት አሉ» እየተባለ ዜና እንዲሠራ የሚደረገው የፕሮፌሰር ሳቤክ ልክፍት ስለያዘን ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ከኢትዮጵያውያን የኑሮ ሁኔታ፣ ከሀገሪቱ

ነባራዊ ሁኔታ፣ በሀገሪቱ ላይ ከሚታዩት ተጨባጭ ለውጦች፣ በሕዝቡ ላይ ከሚታየው ገጽታ፣ ራሱ ተጠቃሚው ከሚናገረው ይልቅ ለምን የእነዚህ ሰዎች ምስክርነት አስፈለገ?

አንዳንድ ጊዜኮ ክርክራችን በራሱ አስገራሚ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አድጋለች ወይስ አላደገችም፤ በኢኮኖሚያችን ላይ ለውጥ መጥቷል ወይስ አልመጣም፣ የኑሮ ዋጋ ተወድዷል ወይስ ረክሷል፣ እያሉ ለመከራከር የዓለም ባንክ እና ዓለም ዐቀፉ የገንዘብ ድርጅት እንጂ እኛ ራሳችንን ከቁም ነገር አንቆጠርም፡፡ እነርሱ አድጋችኋል ካሉን ሕዝቡ የፈለገውን ቢል ችግር የለውም፤ አላደጋችሁም ካሉንም ሕዝቡ የፈለገውን ያህል ቢያድግ አንቀበለውም፡፡ የግድ ፕሮፌሰር ሳቤክ መመስከር አለባቸው፡፡

ብለነው ብለነው የተውነውን ነገር

ባሏ ትናንት ሰምቶ ታንቆ ሊሞት ነበር

እንደተባለው ሕዝቡ እና የሀገር ውስጥ ሚዲያው ሲያቦካው እና ሲጋግረው ለኖረው ነገር ማብራርያ ወይንም መልስ የሚሰጠው በውጭ ሀገር የሚኖሩት፣ የሚታተሙት፣ የሚሠሩት፣ የተደራጁት ፕሮፌሰር ሳቤክ አንድ ነገር ከተናገሩ ነው፡፡ አንዳንድጊዜማ ፕሮፌሰሩ ያሉት ሳይነገረን መልሱን እንሰማዋለን፡፡ ይህም ሕዝቡ በአማርኛ ከሚናገረው ይልቅ ፕሮፌሰር ቴቤክ በእንግሊዝኛ የሚናገሩት ይበልጥ ያስደነግጣል ማለት ነው፡፡

በምርጫ ጊዜ ከሚታዩት ገጽታዎቻችን አንዱ ይሄ ልክፍት ነዉ፡፡ ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ነው አይደለም? ተጭበርብሯል ወይስ አልተጭበረበረም? ደረጃውን የጠበቀ ነው ወይስ የወረደ? ለሚሉት መከራከርያዎች እገሌ ወይንም እገሊት የተባሉ ታዛቢ፣ እገሌ የተባለ የውጭ ሀገር ሰው፣ እነ እገሌ የተባሉ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች፣ ወይንም ደግሞ የእገሌ ሀገር መንግሥት ምን አለ? ነዉ ክርክሩ፡፡ ሕዝቡ ያለውን ማንም ሊሰማው ፈቃደኛ አልነበረም፡ ፡ በምርጫው መሳካት ተጠቃሚው፤ በመጭበርበሩም ተጎጅው ሕዝቡ ነው፡፡ ከእርሱ በላይ ሊሰማ የሚገባው አልነበረም፡፡ ግን «የሐምሌ ውኃ ጥሩ ነው የሚጠጣው የለም፣ የድኃ ምክር መልካም ነው የሚሰማው የለም» የተባለው ነው የተፈጸመው፡፡

ሕጎቻችን እና ሥርዓቶቻችን ሲረቀቁ እንኳን እንደ ትልቅ ነገር የሚነሣው «ከኢትዮጵያውያን ባህል እና ወግ፣ በኢትዮጵያ ካሉ ብሔረሰቦች ነባር ልምዶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች እና ምሁራን ይህ እና ያ ሃሳብ ተገኝቷል» የሚለው ሳይሆን «የእገሌ ሀገር ልምድ ተቀስሟል፤ በእነ እገሌ ሀገር እንዲህ እና እንዲያ ይደረጋል» የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ በነጥቡ ላይ ክርክር ሲነሣም እንደ ማስረጃ የሚቀርበው የዚያ ሀገር አሠራር እና ሕግ፣ ልምድ እና ባህል ነው፡፡

«መልክ ከፈጣሪ፣ ሞያ ከጎረቤት» ይባላልና መልካም መልካሙን መቅሰም የሚያስፈልግም የማይጠላም ነው፡፡ ነገር ግን ዋናው መመዘኛው ፕሮፌሰር ሳቤክ ምን አሉ? የሚለው ሳይሆን ለኢትዮጵያ ምን ይበጃታል?የሚለው መሆን አለበት፡፡

በዚያ ሀገር የሚበላው ሁሉ በኛ ሀገር አይበላም፣ በዚያ ሀገር ነውር የሆነው ሁሉ በኛም ነውር አይሆንም፣ በዚያ ሀገር የሚፈቀደው ሁሉ በኛ ሀገር አይፈቀድም፣ የዚያ ሀገር የኑሮ ፍልስፍና ከሀገራችን ሊለይ ይችላል፤ የነርሱ ደረጃ ከደረጃችን፣ ፍላጎታቸውም ከፍላጎታችን የሚለይበት ነገር ይኖረዋል፡፡ ደግሞም የዚያ ሀገር ሰዎች ያንን ሕግ እና

አሠራር ሲቀርጹ ለሀገራቸው እንዲጠቅም ብለው እንጂ ለኛ አርአያ ምሳሌ ለመሆን ብለው አይደለም፡፡ ስለዚህም ወሳኙ ጫማውን በእግር ልክ ማስተካከሉ እንጂ እግርን በጫማ ልክ መቁረጡ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያውያን እስካልበጀ ድረስ አሜሪካ የሠለጠነችበት፣ ቻይና የተመነደገችበት፣ ጀርመን የተመነጠቀችበት ቢሆንም እንኳን ሊቀር፣ ሊሻሻል እና ሊቀየር ይችላል፡፡

25. አለቃ ገብረ ሐና ተረት ናቸው እውነት

የአባታቸውን ስም አንዳንዶቹ ደስታ ተገኝ ነው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ገብረ ማርያም ነው ይላሉ፡፡ ምናልባት ግን አንዱ የዓለም ሌላው የክርስትና ስማቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የእናታቸው ስም ደግሞ መልካሜ ለማ መሆኑን የእንጦጦ ራጉኤል 125ኛ ዓመት መታሰቢያ መጽሔት ይገልጣል፡፡ ታኅሣሥ 10 ቀን 1978 ዓም የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግን የእናታቸውን ስም ሣህሊቱ ተክሌ ይለዋል፡፡ የተወለዱት በደቡብ ጎንደር ዞን፣ ፎገራ ወረዳ፣ ናቢጋ ጊዮርጊስ በተባለው ቦታ በ1814 ዓ.ም በጎዳር ወር ውስጥ ነው፡፡

የመጀመርያውን ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው ከቀሰሙ በኋላ ወደ ጎጃም ሄደው ቅኔ ተቀኙ፡፡ ከዚያም ጎንደር ከተማ ተመልሰው ከመምህር ወልደ አብ ወልደ ማርያም ጸዋትወ ዜማ፣ ከባሕታዊ ገብረ አምላክ አቋቋም፣ ከዐቃቤ ስብሐት ገብረ መድኅን ትርጓሜ መጻሕፍትን እንዲሁም ድጓን ተምረዋል፡፡

አለቃ ገብረ ሐና ቀልደኛነታቸው ገና ከትምህርት ቤት የጀመረ ይመስላል፡፡ እንዲያውም የቦሩ ሜዳው መምህር አካለ ወልድ እና የአለቃ ገብረ ሐና መምህር የሆኑት መምህር ወልደ አብ ወልደ ማርያም አለቃን «አንተ በቀልድህ ተጠራ» ሲሏቸው መምህር አካለ ወልድን ደግሞ «አንተ በዕወቀትህ ተጠራ» እንዳሏቸው ይነገራል፡፡

አለቃ ገብረ ሐና በዚህ የሰፋ ዕውቀታቸው የተነሣ በ26 ዓመታቸው ጎንደር ሊቀ ካህንነት ተሾመው ነበር፡፡ በዚህ ሹመትም ለሰባት ዓመታት ማገልገላቸው ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት በትርጓሜ መጻሕፍት ዕውቀታቸውና በስብከታቸው በጎንደር የታወቁ ነበሩ፡፡ በፍትሐ ነገሥት ሊቅነታቸውም በዳኝነት እየተሰየሙ አገልግለዋል፡፡ አለቃ ገብረ ሐና ቀልድ ዐዋቂነታቸው በሕዝብ ዘንድ በይፋ እየታወቀ የመጣው በዚህ ወቅት ነው፡፡

አለቃ ገብረ ሐና በቀልድ ዐዋቂነታቸው የተነሣ የትንሹ ራስ ዓሊ አጫዋች ሆኑ፡፡ ዐፄ ቴዎድሮስ ሥልጣኑን ሲይዙ አለቃን በቤተ መንግሥት ነበር ያገኟቸው፡፡ አለቃ የቤተ መንግሥቱን ሰዎች በቀልዳቸው ሸንቆጥ ስለሚያደርጉ ከኮስታራው ቴዎድሮስ ጋር መስማማት አልቻሉም ነበር፡፡ በመጀመሪያ ከዐፄ ቴዎድሮስ ጋር የተጋጩት ቴዎድሮስ ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ካህንን እና ሦስት ዲያቆን ይበቃል ያሉትን ሀሳብ አለቃ ባለመቀበላቸው ነው፡፡ የመሰላቸውን ሃሳብ ለዛ ባለው አነጋገር የሚገልጡት አለቃ ዐፄ ቴዎድሮስ የደብረ ታቦርን መድኃኔዓለም አሠርተው አስተያየት ቢጠይቋቸው የቤተ ክርስቲያኑን ጠባብነት ለመግለጥ «ለሁለት ቀሳውስት እና ለሦስት ዲያቆናት መቼ አነሰ» ብለው መናገራቸው ይወሳል፡፡ እንዲያውም ዐፄ ቴዎድሮስ «ገብረ ሐና ፍትሐ ነገሥቱን ጻፍ፣ ፍርድ ስጥ፣ ገንዘብም ያውልህ ፣ቀልድህን ግን ተወኝ» ሲሉ ተናግረዋቸው ነበር ይባላል፡፡ አለቃ ግን አላቆሙም፡፡

በተለይ ደግሞ በንጉሡ ባለሟል በብላታ አድጎ ላይ «አድግ» /በግእዝ አህያ ማለት ነው/ እያሉ በሚሰነዝሩት ትችት በተደጋጋሚ ተከስሰው ዐፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻ ቴዎድሮስ ክስ ሲሰለቻቸው ምላስ ቀርቶ ታገሉና ተሸናነፉ ብለው ፈረዱ፡፡ በዚህ ትግል አለቃ ተሸነፉ፡፡ ንጉሡም እንግዲህ ምን ይበጅህ? ሲሉ ቢጠይቋቸው « ድሮስ

ይሄ የአህያ ሥራ አይደል» ብለው በመመለሳቸው ከአካባቢያቸው ለማራቅ ሲሉ ንጉሡ ገብረ ሐናን ለትግራይ ጨለቆት ሥላሴ አለቃ አድርገው በመሾም ወደ ትግራይ ላኳቸው፡፡ ከአንቶኒዮ ዲ አባዲ ጋር በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ስለ ሆነው ሁሉ ደብዳቤ ይለዋወጥ የነበረው፣ የዋድላው ሰው ደብተራ አሰጋኸኝ ጥር ስድስት ቀን 1858 ዓ.ም ለአንቶኒዮ ዲ አባዲ በጻፈው ደብዳቤ እንዲህ በማለት ይህን ሁኔታ ገልጦት ነበር «አለቃ ገብረ ሐናን ንጉሥ መቱዋቸው፣ በሽመል፡፡ ወደ ትግሬ ወደ ላስታ ተሰደዱ፡፡ እጅግ ተዋረዱ፡፡ እኔም በዋድላ አገኘኋቸው፡፡ ወደ ቆራጣ ሄዱ፡፡»

ካህናት በዐፄ ቴዎድሮስ ላይ ባመፁ ጊዜ በአድማው ካሉበት ካህናት መካከል አንዱ ገብረ ሐና መሆናቸው ስለታወቀ ዐፄ ቴዎድሮስ በአለቃ ገብረ ሐና ላይ አምርረው ሊቀጧቸው ዛቱ፡፡ አለቃም ሸሽተው ጣና ሐይቅ ሬማ መድኃኔዓለም ገዳም ገቡ፡፡ በዚያም ባሕታዊ ጸዐዳ ገብረ ሥላሴ የተባሉ የአቋቋም ሊቅ አገኙ፡፡ ሁለቱም ተወያይተው በጎንደር አቋቋም ስልት የመቋሚያውን የአካል እንቅስቃሴ ጨምረው ዝማሜውን አዘጋጁት፡፡ ባሕታዊ ጸዐዳ «ከእንግዲህ እኔ ወደ ዓለም አልመለስም፤ አንተ ይህንን ስልት አስተምር » ብለው አለቃ ገብረ ሐናን አደራ አሏቸው፡፡ ከዐፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ በ1864 ዓ.ም ዐፄ ዮሐንስ ሲነግሡ ከገዳም ወጥተው ወደ ትግራይ አቀኑ፡፡

አለቃ ገብረ ሐና በዐፄ ዮሐንስ አደባባይ ፍትሐ ነገሥትን እየተረጎሙ ብዙ ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በአኩስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በሚገኙ አንዳንድ የብራና መጻሕፍት ላይ የአለቃ ገብረ ሐና ስም ሠፍሮ የሚገኘው በዚህ ምክንያት ነው የሚሉ አሉ፡፡ ዐፄ ዮሐንስ በመተማ ጦርነት ሕይወታቸው ሲሠዋ አለቃ ገብረ ሐና ወደ ናበጋ ጊዮርጊስ ተመለሱ፡፡

በመቀጠልም በቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት የሚያውቋቸው ምኒልክ በሸዋ መንገሣቸውን ተከትለው ወደ ሸዋ መጡ፡፡ አለቃ ገብረ ሐናን ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ያደረጉት ሊቅነታቸውን የሚያውቁት እነ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እና እነ አለቃ ገብረ ማርያም ናቸው፡፡

ዐፄ ምኒልክ በዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ሳሉ አለቃ ገብረ ሐናን ስለ ሚያውቋቸው በደቡብ ጎንደር የሚገኘውን የአቡነ ሐራን ገዳም ሾሟቸው፡፡ ይህንንም የታዋቂው ገጣሚ የመንግሥቱ ለማ አባት አለቃ ለማ ኃይሉ «አለቃ ገብረ ሐና÷ የጎንደር የከተማው ናቸው፤ ትምህርታቸውም እዚያው ነው፡፡ አቡነ ሐራ የሚባል ገዳም በበጌምድር ነው ወዲህ እሱን ተሾመው ነበር በአጤ ምኒሊክ፡፡ ኻጤ ዮሐንስ ጀምሮ በምኒሊክ ጊዜ እንደ አቡነ ሐራ የከበረ ገዳም አልነበረም» በማለት መስክረውታል፡፡ አለቃ ከደቡብ ጎንደር ወደ አዲስ አበባ የተዛወሩት የአቡነ ሐራን ገንዘብ ለገበሬዎች አከፋፈሉ ተብለው ተከስሰው ነበር፡፡ አለቃ ለማ ይህንን ጉዳይ ሲያስታውሱት ¬«የስእለቱን ገንዘብ አበላሹ፣ ገንዘቡን አጠፉ ብሎ ከሠሠ አገሩ፤ ተከሰው በኃጢአት መጡ፤ ኻጤ ምኒሊክ፡፡ አትሄድም ተባሉ ቀሩ፡፡ ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ፤ ሆሆይ ገብረ ሐና የማይታወቀበት ወዴት አለ፤ አልተሾሙም ራጉኤል ነበሩ፤ የወር ቀለብ አጤ ምኒሊክ እየሰጧቸው»

ንጉሥ ምኒልክ አለቃን የእንጦጦ ራጉኤል የአቋቋም መምህር አድርገው ሾሟቸው፡፡ ቤትም ተሰጣቸው፡፡ በኋላም የእንጦጦ ራጉኤል አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ፡፡ እርሳቸውም ትርጓሜ መጻሕፍትን እያስተማሩ እንጦጦ ተቀመጡ፡፡ ጥቂት ጊዜ በአዲስ አበባ እንደተቀመጡ እንደገና ወደ ጎንደር ሄደው ደራ ውስጥ ቁላላ ሚካኤል ተወልደው ያደጉትን ወይዘሮ ማዘንጊያን አገቡና ተክሌ/ አለቃ ተክሌን/፣ በፍታ/ጥሩነሽ/ እንዲሁም ሥኑ /አለቃ/ የተባሉ ልጆች ወለዱ፡፡ ተክሌ ለትምህርት ሲደርስ ከሌላው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር እርሳቸው ከባሕታዊ ጸዐዳ ገብረ ሥላሴ ጋር

ሆነው ያዘጋጁትን ዝማሜም አስተማሩት። ይህም ተክሌ ከሦስቱም ልጆቻቸው የመጀመርያ ሳይሆን እንዳልቀረ እንድንገምት ያደርገናል።

አለቃ ገብረ ሐና ደርቡሽ ጎንደርን ሲወርር/ /1880 ዓም/ ልጃቸውን ወደ ወሎ ልከው እርሳቸው ዘጌ ገዳም ገቡ። በኋላም ዐፄ ምኒልክ ደርቡሽን ለመውጋት ወደ ፎገራ መምጣታቸወን ሲሰሙ ከተደበቁበት ወጥተው ንጉሡን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ምኒልክም እንደገና የራጉኤል አለቃ አደረገው ሾሟቸው። ልጃቸው ተክሌ ወሎ ንጉሥ ሚካኤል ዘንድ እያሉ የተንታ ሚካኤል በዓል ሲከበር ከአባታቸው የተማሩትን ዝማሜ በተመስጦ አቀረቡት። ንጉሥ ሚካኤልም በዚህ ተደንቀው በዚያው በተንታ እንዲያገለግሉ አደረጉ። የተክሌ ዝማሜ በይፋ የተጀመረው ያኔ ነው ይባላል። በኋላ ራስ ጉግሣ ዝናውን ሰምተው ንጉሥ ሚካኤልን በማስፈቀድ ወደ ደብረ ታቦር አምጥተው ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ሾሟቸው።

አለቃ ገብረ ሐና ለአዳዲስ አስተሳሰብ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ አእምሮ ከነበራቸው ሊቃውንት ወገን ነበሩ። ፎቶ መነሣት የሰይጣን ሥራ ነው በተባለበት ዘመን የፍትሐ ነገሥቱ ሊቅ አለቃ ገብረ ሐና ከዐፄ ምኒልክ ጋር ፎቶ ተነሡ። እንዲያውም ጣልያን ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ቤት በርብሮ አቃጠለው እንጂ ዐፄ ምኒሊክ ከቤተ ክህነት ሰዎች ጋር ፎቶ የተነሡት መጀመሪያ ከአለቃ ጋር ከተነሡ በኋላ ነው ይባላል።

በአድዋው ዘመቻ ዋዜማ በኢትዮጵያ ላይ ተንኮል ይሸርቡ የነበሩትን አባ ማስያስን እና ዐሥራ ሁለቱን ሰላይ ፈረንጆች ተንኮላቸውን ቀድመው ተረድተው በተለመደው ደፍረታቸው በቅኔ እየሸነቆጡ ከቤተ መንግሥት እንዲባረሩ ያደረጓቸው አለቃ መሆናቸው ይወሳል።

አለቃ ከዚህም በላይ ፈጣሪን በቅኔ የተሟገቱ ሊቅም ነበሩ።

ኮንኖ ታጥኣን ኩሎሙ ኢይደልወከ ምንተ

አፍቅሩ ጸላእትከሙ እንዘ ትብል አንተ

ብለው የሙግት ቅኔ የተቀኙ ናቸው /ጠላቶቻችሁን አፍቅሩ የምትል አንተ ታጥኣንን ለምን በገሃነም ትቀጣለህ ታድያ።/

አለቃ በአዲስ አበባ እያሉ ከመኳንንቱና ከመሳፍንቱ ጋር ያላስማሟቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ። የመጀመርያው ትንባሆ ይጠጣሉ ተብሎ የተነገረው ሐሜት አንድ ቀን በቅኔ ማኅሌት ፒ¬ፓቸው ወድቆ በመጋለጣቸው ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአድዋ ጦርነት ታላቅ ጀብዱ ለፈጸሙት ለደጃዝማች ባልቻ ዐፄ ምኒልክ የሚወዷትን ጎራዴያ ቸውን ሲሸልሟቸው «ወይ ጎራዴ ወይ ጎራዴ፣ ከቤቷ ገባች» በማለት በሽሙጥ በመናገ ራቸው ባልቻ እገላለሁ ብለው ተነሡ። ይህም አልበቃ ብሏቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነገር ተኳረፉና መላ የቤተ መንግሥቱ ሰው አደመባቸው። ዐፄ ምኒልክ አለቃን ምን ቢወዷቸው በተለይ ከደጃች ባልቻና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር የፈጠሩትን ጠብ አልወደዱላቸውም።

በእዚህ ምክንያት አለቃ ገብረ ሐና ከአዲስ አበባ ለቅቀው እንዲወጡ ተወሰነ ባቸው። በጎንደርና በወሎ ጥቂት ጊዜ ከሰነበቱ በኋላ ልጃቸውን ገብረ ሐና ሞተ ብለህ ተናገር ብለው ወደ አዲስ አበባ ላኩት። አለቃ ተክሌ ይህንን መርዶ በቤተ መንግሥቱ ሲያረዱ ምንም እንኳን ገብረ ሐና ከብዙዎቹ ጋር ቢኳረፉ ታላቅ ኅዘን ሆነ። ከተወሰኑ ቀናት በኋላም አለቃ ራሳቸው አዲስ አበባ ገቡና ጉድ አሰኙ። ምኒልክ አስጠርተው ሞቱ ከተባለ በኋላ ከየት መጡ ቢባሉ «በሰማይ

ጣይቱ የለች፣ ምኒልክ የለ፣ጠጅ የለ፣ጮማ የለ፡፡ ባዶ ቤት ቢሆንብኝ ለጠባቂው ጉቦ ሰጥቼ መጣሁ» ብለው ሁሉንም አሳቋቸው፡፡ ጣይቱም መኳንንቱም ይቅር አሏቸው፡፡

አለቃ ገብረ ሐና እድሜያቸውም እየገፋ አደብም እየገዙ መጡ፡፡ አዲስ አበባ ተቀምጠውም ትርጓሜ መጻሕፍት ማስተማር ቀጠሉ፡፡ ዐፄ ምኒልክ የአብያተ ክርስቲያናቱን የግብዝና መሬት ለመኳንንቱ በመስጠታቸውና ካህናቱ ምንም ባለማግኘታቸው የተቆጡት አለቃ ገብረ ሐና ተቃውሟቸውን በቀልድ ለዐፄ ምኒልክ አቀረቡ፡፡ ይህም ከወይዛዝርቱና ከመኳንንቱ ጋር መልሶ አጋጫቸው፡፡

ከዚህ በኋላ አዲስ አበባ መቀመጥ ስላልቻሉ ለመጨረሻ ጊዜ በ1896 ዓም አካባቢ ወደ ደብረ ታቦር ተመለሱ፡፡ ያኔ ልጃቸው አለቃ ተክሌ ደብረ ታቦር ኢየሱስን እልቅና ተሾመው ነበር፡፡

ለጥቂት ቀናት ደብረ ታቦር ከልጃቸው ጋር ሰንብተው ወደ ትውልድ ቦታቸው ናበጋ ጊዮርጊስ መጡ፡፡

በዕድሜያቸው መጨረሻ ዝምተኛ ሆነው ነበር፡፡ ቀድሞ በሠሩት ሥራ እየተፀፀቱ አንደበታቸውን ከነገረ ዘርቅ ከለከሉ፡ ፡ ከጥሩ ምግብና ከጥሩ መጠጥም ተቆጠቡ፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍቱንም ሰብስበው «መሳቂያና መዘበቻ አደረግኳችሁ» እያሉ ይቅርታ ይጠይቋቸው ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሰነበቱ በኋላ በ84 ዓመታቸው፣ የካቲት 24 ቀን 1898 ዓ.ም ዐረፉ፡፡

ብዙዎቻችን ስለ አለቃ ገብረሐና ከልጅነታችን ጀምሮ ሰምተናል፡፡ አለቃ እንዲህ አሉ፣ይህንን መልስ ሰጡ፣እገሌን እንዲህ ብለው ቀለዱበት ወዘተ እየተባለ ተነግሮናል፡፡ታድያ ዘመኑ እየረዘመ ሲመጣ በብዙዎች ዘንድ አለቃ በተረት እንደነ ስንዝሮ የምናውቃቸው ሰው ናቸው ወይስ በዚህች ምድር አካል ነሥተው፣ነፍስ ዘርተው ተመላልሰዋል? የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ የዚህ ጥያቄ መነሻ ምክንያቱ ሁለት ይመስለኛል፡፡ አንዱ የታላላቅ ሰዎችን ሥራ በሚገባ መዝግቦ፣መታሰቢያቸውን አደራጅቶ፣ሥራቸው በተገቢው መንገድ ለትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ ልማዳችን እጅግም በመሆኑ አለቃ በቃል ብቻ በሚነገረው ሥራቸው እና ታሪካቸው የተነሣ ወደ ተረትነት በመቀየራቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በዘመናችን ከኮምፒውተር፣ ከስልክ፣ ከመኪና እና ከአውሮፕላን ጋር የተያያዙ ቀልዶች ሁሉ በስማቸው ሲነገሩ ጊዜ አለቃ ገብረ ሐና እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሰው ከመሆን ይልቅ በየዘመኑ የተነሣ ትውልድ ማለት የሚፈልገውን ሁሉ በስማቸው የሚልባቸው የተረት ገጸ ባሕርይ መስለው ታዩ፡፡

አለቃ ገብረ ሐና ግን በዚህች ምድር በኢትዮጵያ በደቡብ ጎንደር ዞን፣ፎገራ ወረዳ ፣ናበጋ ጊዮርጊስ አጥቢያ ተወልደው ያደጉ የተፈጥሮ ሰው ናቸው፡፡ይህንን በተመለከተ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያገኛቸውን ያህል ማስረጃዎች ቀጥሎ ያቀርባል፡፡

ነ. **ትውልዳዊ**

ከአለቃ ገብረ ሐና የተወለዱ፣ ዘራቸውንም ከእርሳቸው ጀምረው የሚቆጥሩ ትውልዶች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ይህንን ያደረጉት ለተለየ ጥቅም ነው እንዳንል በዚህ ምክንያት ያገኙት ጥቅም የለም፡፡ ይህን የሚሉት የትውልድ እና ቀደምትን አክብሮ የማንሣት ኢትዮጵያዊ ባሕል አስገድዷቸው ብቻ ነው፡፡ ናባጋ ሄደን ብንጠይቅ የአለቃ ገብረ ሐና ዘር በዝቶ ተባዝቶ እናገኘዋለን፡፡ አለቃ ገብረ ሐና አለቃ ሥኑን ወለዱ፣ አለቃ ሥኑ ደግሞ አለቃ ኃይሉን ወለዱ፣ አለቃ ኃይሉም ዛሬ ናባጋ የሚኖሩትን ቄስ አሰጌን ወለዱ፡፡ የልጃቸው የወይዘሮ ጥሩነሽ ትውልድም እዚያው ፎገራ

ይገኛል፡፡ እኔ አግኝቼ ለማናገር አልቻልኩም እንጂ፡፡ በእርግጥ የአቋቋሙ ሊቅ ተክሌ ልጅ እንዳልነበራቸው ከደብረ ታቦር ሊቃውንት እና ከተወላጆቻቸው ተነግሮኛል፡፡ ይህንን ትውልድ ስንመለከተው ከሦስቱ ልጆች እና የልጅ ልጆቻቸው መካከል ሁለቱ እንደ ገብረ ሐና «አለቃ» የሚለውን መዓርግ ደርሰውበት ነበር፡፡ቄስ አሰጌም ቢሆኑ የቤተ ክህነቱን ትምህርት ተምረውታል፡፡

ናቡጋ ወርጇ የአካባቢውን ሕዝብ ስጠይቅ የአለቃ ገብረ ሐና መንደር መሆኑን፣ ትውልዶቻቸው እነ ማን እንደሆኑ ነግረውኛል፡፡ የቄስ አሰጌ ልጆችም ዘራቸውን ሲቆጥሩት አለቃን ያነሷቸዋል፡፡

2.አካባቢያዊ

ናቡጋ ጊዮርጊስ አለቃ ገብረ ሐና ቤት ሠርተውበት የነበረው ቦታ ዛሬ ሸንበቆ እና ቡና በቅሎበት ይታያል፡፡ እኔ እንዲያውም ይህ ውኃ ተከትሎ የሚበቅል ሸምበቆ አለቃን አይለቃቸውም ወይ አሰኝቶኛል፡፡ያኔ ከዐፄ ቴዎድሮስ ሸሽተው ዘጌ ደሴት ሲገቡ ያገኙት እና እንቅስቃሴውን ተመልከተው የአቋቋሙን ሥርዓት የቀመሙበ ሸምበቆው ነበር፡፡ ዛሬም በቤታቸው በቅሎ ይታያል፡፡ በናባጋ ጊዮርጊስ ደብር አለቃ የሕይወታቸውን የመጨረሻ ዘመናት የጸለዩበት ቦታ፣ ያድሩበት የነበረው ጥንታዊው ዕቃ ቤት፣ የተቀበሩበት ቦታ ዛሬም ይታያል፡፡ በመቃብራቸው ላይ የአካባቢው ሰዎች አክብረው ቤተ ልሔም ሠርተውበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዐፄ ምኒሊክ ተሾመው ያገለገሉበት እንጦጦ ራጉኤል፣ ጎንደር በኣታ ለማርያም ደብር የአለቃ ገብረ ሐናን አገልግሎት እና ማንነት ይመሰክራሉ፡፡

3.ቅርሶች

ከአለቃ ገብረ ሐና ጋር የተያያዙ ቅርሶች ዛሬም ይገኛሉ፡፡ ይለብሱት የነበረው እና የፈትሉ እና የጥልፉ ውበት የዚያን ዘመን ጥበብ የሚያሳየው ቀሚሳቸው ቅዳጅ፣ የመጽሐፋቸው ማኅደር በናባጋ ጊዮርጊስ፤ያሠሩት ከበሮ በጎንደር በኣታ ለማርያም የአቋቋም ት/ቤት ዛሬም ይገኛል፡፡

4.የዘመነኞች ምስክርነት

አለቃ ገብረ ሐና ጋር በአንድ ዘመን የመኖር እድልን ያገኙ ሰዎች አለቃ ገብረ ሐናን በተመለከተ የገለጿቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ከጣልያናዊው አንቶንዮ ዲ አባዲ ጋር ደብዳቤ ይለዋወጥ የነበረው የዋድላው አሰጋኸኝ ጥር ስድስት ቀን 1858 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ «አለቃ ገብረ ሐናን ንጉሥ መቱ ዋቸው በሽመል፡፡ ወደ ትግሬ ወደ ላስታ ተሰደዱ፡ ፡ እጅግ ተዋረዱ፡፡ እኔም በዋድላ አገኘኋቸው ወደ ቆራጣ ሄዱ፡፡» በማለት መግለጡ በዘመኑ አለቃ ገብረ ሐና እንደነበሩ የሚያመላክት ነው፡፡ በአለቃ ገብረ ሐና ዘመን የነበሩት አለቃ ለማ ኃይሉም ስለ አለቃ ገብረ ሐና ልዩ ልዩ መረጃዎችን ይሰጡናል፡፡

5. የትምህርት ቤት የዘር ሐረግ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤት ትውፊት መሠረት የታላላቅ ትምህርቶች ምስክሮች የዘር ሐረግ አላቸው፡፡ የድጓ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የአቋቋም፣ የትርጓሜ ወዘተ...፡፡ አለቃ ገብረ ሐና በአቋቋም ትምህርት ቤት በጎንደር በኣታ የመምህራን የዘር ሐረግ ውስጥ ስማቸው ይወሳል፡፡

6. **ፎቶ**

አለቃ ገብረ ሐና ፎቶአቸው ለትውልድ ከተቀመጠላቸው ጥቂት የጥንት ሊቃውንት አንዱ ናቸው፡፡ በ1890 ዓም ሙሴ ሜንሮስ የተባለ ኢጣልያዊ ያነሣቸው ፎቶ ግራፍ እና አንድ እስካሁን ፎቶ አንሺውን ማወቅ ያልቻልኩት በኢንተርኔት የተለቀቀ ፎቶ ግራፍ አግኝቻለሁ፡፡

የአለቃ ቀልደኛነት ከየት መጣ?

የአለቃ ገብረ ሐና ቀልደኛነት ከየት መጣ? የሚለው ጉዳይ የብዙዎች ጥያቄ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን የተሟላ መልስ ለማግኘት ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን የተሻለ ግምት ለማቅረብ ብቻ እንሞክራለን፡፡ በአንድ በኩል የደብተራ ዘነብ፣ የአለቃ ገብረ ሐና፣ የዲማው ካሣ ጉዱ በአንድ ተመሳሳይ ዘመን መገኘት ያ ዘመን ሊቃውንቱ በአዲስ መሥመር /አፈንግጦሽ/ የተጓዙበት ዘመን ይሆን? ያስኘናል፡፡ ደብተራ ዘነብ ያዘጋጁት መጽሐፈ ጨዋታ ቅኔውን እንዴት አድርገው እያዋዛ ለሚያስረዳ አገላለጥ እንደተጠቀሙበት፣ አለቃ ለማ ኃይሉ ሕልውናውን የመሰከሩለት፣ በኋላም ታላቁ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፋቸው የኪነ ጥበብን መልክ ቀብተው ያቀረቡት ጉዱ ካሣ ቅኔውን ሥርዓቱን ለመተቸት እንዴት እንዳዋለው ስናጤን እነዚህ ሰዎች የጎጃምን ቅኔ ሲቀምሱ ማን? ምን? አቀመሳቸው እንድንል ያደርገናል፡፡ ምናልባትም አንድ ተመሳሳይ መምህር ገጥሟቸው ይሆን ያስኘናል፡

በሌላ በኩል ደግሞ ፎገራን የሚጎበኝ ሰው ስለ አለቃ የሰላ ቀልድ አንድ ነገር ይጭርበት ይሆናል፡፡ ፎገራ ከኦሮምያዋ ግንደ በረት ጋር የተያያዘው የባርያ ንግድ አንዷ መተላለፍያ ነበረች፡፡ ወደ ደብረ ታቦር መንገድ ወጣ ብላ የምናገኛት «ኢፋግ» የባርያ ንግድ ማረፊያ ነበረች፡፡ ወረታ ፣በጠቅላላውም ፎገራ በጥንቱ የሲራራ ንግድ ዋነኛ መናኸርያ ነበረች፡ ፡ ታድያ በዚህ ምክንያት ይመስለኛል በፎገራ የትግራይ፣የኦሮሞ እና የአማራ ሕዝቦች ተጽዕኖ ይታይ በታል፡፡ አለባበሱን፣ የፀጉር አቆራረጡን፣ ከወገብ በላይ ራቁት መሆንን ስትመለከቱ የእነዚህን ሕዝቦች አሻራ ታያላችሁ፡፡ በአካባቢውም በልዩ ልዩ ሕዝቦች የሚጠራ መንደርም አለ፡፡ለምሳሌ የትግሬ መንደር፡፡ ይህ ሁኔታ በአለቃ ገብረ ሐና ሕይወት ውስጥ ተጽዕኖ አሳድሮ ይሆን? አለቃ አማርኛም ኦሮምኛም ትግርኛም የተቀላቀለበት ቀልድ የሚቀልዱት በዚህ ምክናያት ይሆንን አሰኝቶኛል፡፡

ሌላም ነጥብ እናንሣ፡፡ የፎገራ ገበሬዎች ከዘመን የመፍጠን ጠባይ ይታይ ባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከኮርያ ባለሞያዎች የሩዝን ሁኔታ ተረድተው ለገበሬዎች ያስፋፉት አንድ የፎገራ ገበሬ ናቸው፡፡ ዛሬ የፎገራን መሬት ያለበሰው ሩዝ የኒህ ትጉ ገበሬ የአሠረጫጨት ዘዴ ውጤት ነው፡፡ የግብርና ባለሞያዎች በአዳዲስ ዘር አሠረጫጨት እና ገበሬውን ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር በማለማመድ ጉዳይ ከኒህ ገበሬ የሚቀስሙት ይኖር ይሆን? አስቲ እንጨምር፡፡ የፎገራ ገበሬ የሚያመርተው ሩዝ ዘለላው እሾህ ስላልነበረው ወፍ እየጠረጠረ ያስቸግረው ነበር አሉ፡፡ ታድያ ከዘመን የቀደሙ አንድ ገበሬ ዛላው እንደ ገብስ እሾሃማ የሆነ ዘር በምርምራቸው ማግኘታቸውን፣እንዲያውም በስማቸው ይህንን ዘር ለመሰየም እንቅስቃሴ መጀመሩን ከባለሞያዎች ሰምቻለሁ፡፡ ይህ ከዘመን አፈንግጦ መጓዝ የሀገሩ ልማድ ይሆን? ገና ብዙ የአንትሮፖሎጂ፣የግብርና እና የታሪክ ምርምር የማሻው በመሆኑ ከኔ ይልቅ በዚህ ሞያ ልሒቅ ለሆኑት እንዲቀጥሉበት አደራ እላለሁ፡፡

የአለቃ ገብረ ሐናን ቀልዶች ስንመለከት ቅኔያውያን ናቸው፡፡ በኋላ በዝር ዝር ለማስረዳት አንደምሞክረው የአለቃ ቀልዶች አመራማሪ፣ አስደናቂ፣ እንደ ጥቅስ ሁልጊዜ ሊነገሩ የሚችሉ፣ ፈጣን ናቸው፡፡ ይህ የአለቃ ቀልዶች ጠባይ ከምሁርነታቸው የመነጨ ይመስላል፡፡ አንድን ነገር ገልብጠው ማሰብ ይቸሉ ነበር፡፡ ጣና ሐይቅ ወስጥ የሸንበቆውን ንቅናቄ ተመልክተው ከዝማሜው ጋር ማዋሐዳቸው የአእምሮአቸውን ስለት ያስረዳናል፡፡ ከተሰጥኦዋቸው ጋር ቀልዳቸውን ያስዋበው የመላው ዕውቀታቸወ ነው፡፡

የአለቃ ገብረ ሐና ሰብእና እና አስተዋጽዖ

ሰብእና

ብዙዎቻችን በቀልዳቸው ብቻ የምናውቃቸው አለቃ ገብረ ሐና በብዙ ሞያዎች የተካኑ ነበሩ፡፡ ባለ ቅኔ፣ የአቡሻከር እና የመርሐ ዕውር ሊቅ፣ የድጓ ምሁር፣ የፍትሐ ነገሥት ሊቅ፣ የአቋቋም ዐዋቂ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህር ነበሩ፡ ፡ታደያ በሥራዎቻቸው እና በቀልዶቻቸው የእነዚህን ነፀብራቅ እናገኛለን፡፡ አለቃ ለማ ኃይሉ ስለ ሊቅነታቸው ሲመሰክሩ «የሞያ መጨረሻ እርሳቸው ሊይደሉም ወይ? የሐዲስ መምህር ናቸው፣ ፍታነገሥትን በርሳቸው ልክ የሚያውቀው የለም፤ ይኸ የቁጥሩን ÷መርሐ ዕውሩን፣ አቡሻከሩን የሚያውቅ ነው ባለሞያ፡፡ መቼም ለዚህ ለዝማሜ እሚባለው፤ ለመቋሚያ፤ እገሌ ይመስለዋል ሊይባልም፤ ከገብረ ሐና ፊት የሚዘም የለም» ይላሉ፡፡ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴም «አለቃ ገብረ ሐና እጅግ የተማሩ የጎንደር ሊቅ ነበሩ፡፡ በዚህም ላይ ደግሞ ኃይለ ቃልና ጨዋታ ያውቁ ነበር» በማለት ይገልጧቸዋል፡፡ በጎንደር አድባራት ሊቀ ካህንነት፣ በአዲስ አበባ እንጦጦ ራጉኤል እና በአቡነ ሐራ ገዳም ተሾመው ማገልገላቸውን ስናይ ይህንን ዕውቀታቸውን ያስረዳልናል፡፡ እንዲያወም በዚያ ዘመን ከከበሩት አድባራት አንዱ አቡነ ሐራ ደንግል ገዳም ስለነበር ለዚያ አለቃ ሆኖ መሾም የታላቅነት ምልክት መሆኑን አለቃ ለማ ገልጠዋል፡፡

ሀ.አለቃ ገብረ ሐና የድኾች ጠበቃ

አለቃ ገብረ ሐና ምንም ከመኳንንቱ እና ከመሳፍንቱ ጋር ቢውሉ፣ምንም እንኳን የእንጦጦ ራጉኤል ሰዎች እንደሚናገሩላቸው በዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት ከምኒሊክ እና ከእቴጌ ምንትዋብ ቀጥለው ግብር የሚቀመጡት ገብረ ሐና ቢሆኑም ድኾች ሲጨቆኑ እና ሲያዝኑ ግን ሊይወዱም ነበር፡፡ በአንድ ወቅት የአቡነ ሐራ ገዳም አካባቢ ርሃብ ገብቶ ገበሬው ሲቸገር ቢያዩ «እናንተ ባገኛቸሁ ጊዜ ለአቡነ ሐራ እንደሰጣችሁ ሁሉ እናንተ ሲቸግራችሁ ደግሞ አቡነ ሐራ ይሰጧችኋል» ብለው ከሥዕለት የተሰበሰበውን ገንዘብ አውጥተው ለገበሬዎች አከፋፈሉት፡፡ በዚህ ጉዳይ ተከስሰው ከፍርድ ሚኒስቴሩ ከአፈ ንጉሥ ነሲቡ ዘንድ ቀርበው ሊፈረድባቸው ነበር፡፡ በኋላ ግን ሊቀ መኳስ አባተ ቧ ያለው ዐፄ ምኒሊክ አለቃ ገብረ ሐናን ሲያደነቁ እንደሚሰሙ እና አፈንጉሥ ለሚሰጡት ፍርድ እንዲጠነቀቁ በማመልከታቸው ጉዳዩ ወደ ዙፋን ችሎት ተመራ፡፡ ዐፄ ምኒሊክም አለቃ ገብረ ሐናን የፍትሐ ነገሥቱ ሊቅ አንተ አይደለህም ወይ? እስቲ ምን ይላል ንገረን? አሏቸው፡፡ አለቃም «ፍትሐ ነገሥቱማ ሲሦውን ለካህናት፣ሲሦውን ለሠራያን ይገባል ይላል፡፡ እኔም ክፉ ቀን ስለሆነ ለሕዝቡ አካፍየዋለሁ፡፡ አቡነ ሐራ አባታቸውን አይጦሩበት፣ ልጃቸውን አይድሩበት» ሲሉ መለሱላቸው፡፡

አለቃ ገብረ ሐና ከምኒሊክ ባለሟሎች ጋር ተጣልተው ለመጨረሻ ጊዜ አዲስ አበባን ለመልቀቅ ያበቃቸውም መኳንንቱ እና መሳፍንቱ ግብዝናውን እየተሸሙ የድኻውን ካህን መሬት እየወሰዱ ካህኑን በቶፍነት ስም ጭሰኛ ማድረጋቸውን በመቃወማቸው ነበር። አለቃ ይህንን አሳዛኝ አሠራር ፊት ለፊት ተቃውመውታል። በዚህም ምክንያት ከአዲስ አበባ ይወጡ ተብለው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ በቅተዋል።

ለ. አለቃ ገብረ ሐና ንጉሥ የማይፈሩ

ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ በሚባልበት በዚያ ዘመን ነገሥታቱን እና መኳንንቱን በመገሠጽ አለቃን የሚወዳደር አልነበረም። ለአንድ ቤተ ክርስቲያን አምስት ልዑክ ይበቃል ብለው ዐፄ ቴዎድሮስ ያነሡትን ሃሳብ አለቃ ገብረ ሐና አልተቀበሉትም። ዐፄ ቴዎድሮስ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን ሲመረቅ አለቃ ተጋብዘው ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስም እንዴት ነው ቤተ ክርስቲያኑ ብለው ቢጠይቋቸው ማነሡን ለመግለጥ «ለሁለት ካህን እና ለሦስት ዲያቆን በቂ ነው» አሏቸው። በዚህም ከቴዎድሮስ ጋር ተኳረፉ።

አስተዋጽዖ

ነ.ዝማሜ

አለቃ ገብረ ሐና ለቤተ ክርስቲያን እና ለኢትዮጵያ ካበረከቱት ነገር አንዱ «የተክሌ ዝማሜ» የሚባለው ነው። አለቃ ገብረ ሐና ይህንን የመቋሚያ ስልት ያዘጋጁት ከዐፄ ቴዎድሮስ ሸሽተው ዘጌ በገቡ ጊዜ ነበር። በዚያ የነበረውን የሸንበቆ ውዝዋዜ ተመልክተው ከአቋቋሙ ስልት ጋር አዋሕደው ከባሕታዊ ጸዐዳ ገብረ ሥላሴ ጋር በመሆን ነበር። ባሕታዊ ጸዐዳ ገብረ ሥላሴ ወደ ዓለም ስላልተመለሱ አለቃ ገብረ ሐና ይህንን አዲስ ዝማሜ ይዘው ጎንደር ገቡ። ወዲያወም የአቋቋሙ መምህር አለቃ ገብረ ሐና ለተማሪዎቻቸው አዲሱን ዝማሜ ማስተማር ጀመሩ።ጎንደሮች ሲያገለግሉ ሸማቸውን ታጥቀው ስለነበር በሚያዘሙበት ጊዜ በተመስጦ ወዲያ እና ወዲህ ሲሉ ሸማቸውን እያስጣለ ቢያስቸግራቸው ካህናቱ ተመካክረው አለቃ ይህንን ዝማሜ እንዳያስተምሩ ወሰኑባቸው። በዚህ ጊዜ አለቃ ለልጃቸው ለተክሌ ደብቀው ማስተማር ጀመሩ።

ተክሌ የደርቡሽን ወረራ ሸሽቶ ወሎ ራስ ሚካኤል ዘንድ በሄደ ጊዜ ተንታ ሚካኤል ሲመረቅ ያንን ተደበቆ የኖረ ዝማሜ አወጣው መኳንንቱ እና መሳፍንቱ ፣ሕዝቡ እና ካህናቱ ተገርመው ያዳምጡት እና ያዩት ጀመር። ሲጨርስም ራስ ሚካኤል በተንታ ሚካኤል ይህንን ዝማሜ እንዲያስተምር አደረጉ። በኋላም የደብረ ታቦሩ ራስ ጉግሣ ራስ ሚካኤልን ለምነው ለደብረ ታቦር ኢየሱስ አለቃ አድርገው ተክሌን ወሰዱት እርሱም በዚያ ሲያስተምር ቆይቶ እዚያው ዐረፈ። ዝማሜውም በስሙ «ተክሌ» እየተባለ ተጠራ።

እንዲያውም ተክሌ በሞቱ ጊዜ

ተክሌ ገብረ ሐና ተከተተ ጣቱ
መንክሩን ከሥተቱን የዘመመበቱ

ብላ አልቃሽ ገጥማ ነበር። ራስ ጉግሣም «ምን ተክሌ ሞተ ትሉኛላቸሁ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ፈረሰ በሉኝ እንጂ፤ደብረ ታቦር ኢየሱስ ቢፈርስ ከዚህ አስበልጬ እሠራው ነበር ተክሌን ግን ከየት አገኘዋለሁ» ማለታቸው ይነገራል።

2. **ሰም እና ወርቅ ቀልድ**

ብዙዎቻችን አለቃን የምናውቃቸው በሰም እና ወርቅ ቀልዳቸው ነው። ሌቨን ዶናልድ የተባሉ ደራሲ «ሰም እና ወርቅ»» Wax and gold በተሰኘው መጽሐፋቸው አለቃ ገብረ ሐና በሰም እና ወርቅ ቅኔያቸው፣ በቀልዳቸው እና በፈጣን መልሳቸው እንዲሁም በሂሳቸው የታወቁ መሆናቸውን ገልጠዋል። የአለቃ ገብረ ሐና አብዛኞቹ ቀልዶች ሰም እና ወርቅ ቅኔ ናቸው። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን የግእዝ ቅኔ ስልት የተከተለ ነው።

ምንጭ ዐረፈ ዓይኔ ሐጎስ፣ አለቃ ገብረ ሐናና አስቂኝ ቀልዶቻቸው፣ አዲስ አበባ፣1979 ዓም፤ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ታኅሣሥ 10፣1978 ዓም(ምን ሠርተው ታወቁ) ዓምድ) መንግሥቱ ለማ፣ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ፣ አዲስ አበባ 1959 ዓም፣ገጽ 137-138፤ጎሩይ ወልደ ሥላሴ፣የሕይወት ታሪክ፣አዲስ አበባ፣1918 ዓም፣ገጽ 89፤ ኤልሳቤጥ ገሠሠ፣ በአለቃ ገብረ ሐና የሚነገሩ ቀልዶች፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አአዩ፣ 1974 ዓም፤ Sven Rubenson, ed. Acta Ethiopica: Tewodros and His Contemporaries 1855-1868, p259

26. ተሳቢ



በቀደም ዕለት ነው። በአንድ ትልቅ አውራ ጎዳና ላይ አንድ የጭነት መኪና ከነ ተሳቢው ይጓዛል። እየሄደ ቆየና ድንገት ቆም አለ። ሾፌሩም ከጋቢናው ወረደና ወደ ተሳቢው አመራ። ሆድ ዕቃውን እና ዳሌውን ፈታተሸው። ከሳቢው ጋር የተያያዘበትን ገመድም አየው። ጎማዎቹን መታ መታ አደረጋቸው። እኔ የሚያደርገውን እንጂ የሚያስበውን ለማየት አልታደልኩም።

ወደ ጋቢናው ተመለሰና መፍቻ ነገሮች ይዞ ወጣ። አንድ ሌላ ሰውም ዓይኖቹን እየደባበሰ አብሮት ወረደ። ምናልባት የደከመው ረዳት ይሆናል ብዬ ጠረጠርኩ። ለሁለት ተጋግዘው ብረቱን ፈቱና ሳቢውን ከተሳቢው ለዩት። የመሳቢያውን ብረት መሬት አስነኩሱና ተሳቢውን ወደፊት ሳብ አደረጉት። ከአካባቢው ብቅ ብቅ ያሉ ወጣቶች ልምድ ባለው አኳኋን ቀረቡና ለጥበቃ ሥራ በገንዘብ ተደራደሩ። ተስማሙ መሰለኝ። ሾፌሩ እና ረዳቱ ጋቢና ውስጥ ገብተው መኪናውን እያስጓሩ ወሰዱት። ምስኪኑ ተሳቢ ግን በቆመበት ቀረ።

አይ ተሳቢ፤ አልኩ በልቤ። የራሱ ጭንቅላት የለው፣ ራሱ መሪ የለው፣ የራሱ ፍሬን የለው፣ የራሱ ጌጅ የለው፣ የራሱ ነዳጅ መስጫ የለው። የራሱ ማርሽ የለው። በሳቢው ላይ ተማምኖ እና ሳቢውን ተከትሎ በሄደበት ይሄዳል፤ በቆመበት ይቆማል። ከወሰደው ይሄዳል፤ ከገተረው ይቆማል። እርሱ እቴ ወዴት እንደ ሚሄድ አይወስንም።

የሚወስንለት ሌላ ነው፡፡ እርሱ እቴ መንገዱን ኣይመርጥም፤ መንገድ የሚመርጥለት ሌላ ነው፡፡ እርሱ እቴ መነሻ እና መድረሻውን ኣያውቅም፡፡ ሌላው ካስነሣው ይነሣል፡፡ ካደረሰው ቦታ ይደርሳል፡፡

ኣይ ተሳቢ፡፡

እኔም ጠጋ ብዬ «ኣንተ ግን እስከ መቼ በሌላ መኪና ጭንቅላት ትመራለህ፡፡ ከምትሳብ ለምን ራስህን ኣትችልም?» ስል ጠየቅኩት፡፡

እኔስ መኪና ነኝ፤ ግን እንደ ሀገር ስንት ዘመን ተስበናል፡፡ ማርክስ እና ሌኒን ሳቢዎቻችን ሆነው ስንት ጊዜ ሳቡን፡፡ የኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ በማርክሲዝም እና በሌኒኒዝም ካልሆነ በራስዋ ኣንወስንም ብለን ስንሳብ፣ ስንሳብ፣ ስንሳብ ኖርን፡፡ ጎርቫቾብ የሚባል ኣንድ ሰው መጣና የኮሚኒዝምን መኪና የሆነ ቦታ ኣቆማት፡፡ እኛም ቆምን፡፡ ከዚያ እነርሱ መኪናቸውን ኣስነሥተው ጠፉን፡፡ እኛ ተሳቢዎቹ ወዴት እንሂድ፡፡ ቀድሞም ለመሳብ እንጂ ለመሄድ ኣልተነሣንምና፡፡

ኣሁንም ያው በሽታ ኣልለቀቀንም፡፡ ክርክራችን እና ኣመለካከታችን «ለኢትዮጵያ የትኛው ይስማማታል፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ ኣስተሳሰብ፣ ርእይ እና መንገድ፣ ነገር ግን የምንፈልገው ቦታ ራሳችንን በራሳችን መርተን የሚያደርሰን የቱ ነው?» በሚለው ላይ ኣይደለም፡፡ ኣንዱ ወደ ምዕራብ ወስዶን ኢትዮጵያን የኣሜሪካ መኪና ይሳባት ይላል፡፡ ሌላው ምሥራቅ ወስዶን ኢትዮጵያን የቻይና መኪና ይሳባት ይላል፡፡ ሳንሳብ ራሳችን መንዳት ኣንችልም ወይ?» ኣለና መለሰልኝ፡፡

«ይህ ችግር ግን የኣፍሪካውያን ሁሉ ኣይደለም ወይ?»

«ነው እንጂ፡፡ እምቢ ማለት የሚችሉ የኣፍሪካ ሀገሮችኮ በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ኣፍሪካ የኣዳዲስ ሀሳቦች መሞከርያ የሆነችው፡፡ በተለይም ቅኝ የተገዙ ሀገሮች የገዥ ዎቻቸው ተሳቢዎች ሆነው ቀርተዋል፡፡ የትምህርት ሥርዓታቸው፤ የኣኗኗር ጠባያቸው፤ የፖለቲካ መርሖኣቸው፣ የባንክ ሥርዓታቸው ሁሉ የሚወሰነው በሳቢዎቻቸው ነው፡፡ የራሳቸውን መንገድ እና ፖሊሲ ቀርፀው ከመጓዝ ይልቅ ሳቢዎቻቸው ወደሚወስዷቸው መጓዝን ይመርጣሉ፡፡ »

«ቆይ ግን ይህ ነገር ክስተት ነው ኣመለካከት ነው ? » ስል ጠየቅኩት፡፡ «እንደኔ ክስተት ሳይሆን ኣመለካከት ነው የሚመስለኝ፡፡ እስኪ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ብቅ በል፡፡ ኢትዮጵያን በተመለከተ የውጭ ሰዎች የሰጡትን ትንታኔ፣ ድምዳሜ እና ኣቋም ያለ ምንም ጥያቄ እንደ ወረደ ታገኘዋለህ፡፡ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያዊውን የቦታ፣ የሰው እና የዕቃ ስም ፈረንጆች በሚጠሩበት ኣጠራር ሲጠራ ታገኘዋለህ፡፡ እነዚያ የውጭ ሰዎች የሰጡት ትንታኔ እና መደምደሚያ እውነት ይሆን ? እኔ ከእነርሱ ይልቅ ለሀገሪቱ እቀርባለሁ ብሎ መልሶ የሚጠይቅ ኣታገኝም፡፡ የተሳቢነት በሽታ ስላለ ዝም ብሎ በእነዚያ ሰዎች ጭንቅላት ብቻ መመራት ነው፡፡ እነርሱ ቲዎሪያቸውን ሲቀይሩ ትቀይራለህ፣ እነርሱ ኣዲስ መጽሐፍ ሲጽፉ ያው እርሱን ጠቅሰህ እንደገና ታስተምራለህ፤ እነርሱ ተሳስተን ነበር ካሉ ኣንተም ተሳስቼ ነበር ትላለህ፡፡ እነርሱ መጻፍ ሲያቆሙም ያንተም የማስተማርያ ኖት እዚያው እንደ ቆመ ይቀራል፡፡»

«እንዲህ ካልከማ እዚህ እየኖረ አሜሪካ ላይ የሚታሰብለት ብዙ አይደል እንዴ?» አልኩት።

«በደንብ አይተኸዋል» አለኝ። «የሚለብሱትን፣ የሚበሉትን፣ የሚማሩትን፣ የሚጫሙትን ሁሉ የሚጠ ብቁት አሜሪካ እና አውሮፓ ከሚገኙ ዘመዶቻቸው ነው። እነርሱ ኢትዮጵያ ተቀምጠው ምንም አያስቡም። ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚዘንብ አሜሪካ ውስጥ ቢዘንብ ደስ ይላቸዋል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጠረ ችግር ይልቅ አሜሪካ ውስጥ የተፈጠረ ችግር ያሳስባቸዋል። ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ይልቅ ለአሜሪካ ኢኮኖሚ ይጸልያሉ። ከአራት ኪሎ ማርያም ይልቅ ለዲሲዋ ማርያም ይሳላሉ።

«በየቀኑ ከአሜሪካ እና ከአውሮፓ ስልክ እየተቀበሉ ስለየሀገራቱ መረጃ ይሰበስባሉ። ከዚያም እዚያ የኖሩ ያህል ከጓደኞቻቸው ጋር ሲሆኑ ይተነትናሉ። የመረጃ ምንጫቸው እዚያ ሀገር ያለው ጭንቅላታቸው ነው። እርሱ ካኮረፈ ያኮርፋሉ፤ ከታመመ ይታመማሉ፤ ጮቤ ከረገጠ ይረግጣሉ። ወደ ውጭ ስለመሄድ እንኳን ሲያስቡ አንድ ቀን ይህ ሰው ይወስደኛል ብለው በርግጠኛነት ያምናሉ።

«እነዚህ ሰዎች ናቸው ባለፈው ጊዜ የአሜሪካ ኢኮኖሚ ተናግቶ ጭንቅላቶቻቸው ቀጥ ሲሉ እነርሱም ቀጥ ያሉት። እየተንተቱ መሄድን ብቻ ስለሚያውቁ ወዴት ይሂዱ። ሥራ መፈለግ እና ሥራ መሥራት አልለመዱም። አንድ በዲግሪ የተመረቀ ሰው ከሚያገኘው በላይ በዶላር እየተላከላቸው ሲያገኙ የኖሩ ናቸው። ልብሳቸው እና ጫማቸው ከባሕር ማዶ ነው የኖረው። ታድያ አሁን መኪናው በድንገት ሲያቆም ምን ይዋጣቸው። ያው እንደኔ መንገድ ላይ መገተር ነው እንጂ» አለ ፈገግ ብሎ።

«አንተ እነርሱን ትላለህ። እዚህ ሀገር ሆነውስ ተሳቢዎች አሉ አይደለም እንዴ? አንድን ሀብታም፣ ወይንም ባለ ሥልጣን ተጠግተው፣ ሲስቅ እየሳቁ፤ ሲያለቀስ እያለቀሱ፤ ሲከሳ እየከሱ፤ ሲወፍር እየወፈሩ፤ የሚኖሩ ተሳቢዎች አሉኮ። የት እንደሚሄዱ ፍጻሜያቸውን አያውቁም። ስለ ራሳቸው በራሳቸው አያስቡም። የሚሄዱት ያ ሰው በሄደበት ነው። የሚያምኑት ያ ሰው የሚያምነውን ነው። የጠላውን ይጠላሉ፤ የወደደውን ይወድዳሉ። በትልቅ ዋርካ ሥር ያሉ ትንንሽ ዛፎችን ታውቃለህ? እንደዚያ ማለት ናቸው። ምግባቸውን የሚያገኙት ከዋርካው ነው። የሚጠለሉትም በዋርካው ነው።

«ታድያ ያ ሰው ቢከሥር፣ ከሥልጣን ቢወርድ፣ ወይንም ጊዜ ቢከዳው እነዚህ ተሳቢዎች ግራ ይገባቸዋል። የሆነ ቦታ ቆመው ይቀራሉና። ያላቸው አማራጭ አንድ ብቻ ነው። ሌላ የሚስባቸው መፈለግ።»

«ቲፎዞ ከመሆን በቀር የራሳቸው ሃሳብ የሌላቸው ሰዎችስ አታውቅም?» አለኝ።

«ልክ ነህ ዐውቃለሁ» አልኩት።

«እነርሱምኮ እንደ እኔ ተሳቢዎች ናቸው። እገሌ እንዲህ አለ ከማለት በቀር እነርሱ ራሳቸው የሚሉት ነገር የሌላቸው።

አንብበው፣ ተምረው፣ ወይንም መርምረው ከማግኘት ይልቅ ከሌላ ሰው ሰምተው ብቻ የሚወስኑ አሉልህ፡፡ እነርሱ ማሰብ አይፈልጉም፤ ማንበብም አይፈልጉም፤ ማየትም አይፈልጉም፡፡ ነገር ግን የሚስባቸው ሰው አላቸው፡፡ ምን ጊዜም የሌላ ሰው ቲፎዞ ይሆናሉ እንጂ በራሳቸው አይቆሙም፡፡»

«የአንድ ታዋቂ ዘፋኝ ወይንም የፊልም ተዋናይ ተሳቢዎች የሆኑስ አላየህም» አልኩት፡፡

«እነዚህ የለበሰውን ለመልበስ፣ እንደ አካሄዱ ለመሄድ፣ እንደ ድምፅ አወጣጡ ለማውጣት፣ እንደ አቆራረጡ ለመቆረጥ፣ እንደ አነጋገሩ ለመናገር፣ እንደ ማይክራፎን አያያዙ ለመያዝ፣ መከራ የሚያዩ ወገኖቻችን ያሳዝኑኛል፡፡ ለምን በራሳቸው ጭንቅላት አይመሩም፡፡ ከሌላውኮ ጥቂት ወስደህ አዳብረህ፣ ካንተ ጋር አስማምተህ አዲስ ማንነት ትፈጥራለህ እንጂ እንዴት የሌላው ፎቶ ኮፒ ትሆናለህ፡፡ ከሌላው መማር ነው እንጂ እንዴት ሌላውን እንዳለ ትቀዳለህ? እንደ እገሌ ጎበዝ ነው ሲባል እንጂ፣ እገሌን ይመስላል ሲባልኮ ጥሩ አይደለም፡፡ በራስ መመራት እንጂ መሳብኮ ደግ አይደለም፡፡»

እንዲህ እያወጋን አንድ ተሳቢ የሌለው የጭነት መኪና መጣ፡፡ ሾፌሩም ከመኪናው ወረደ፡፡ መንገድ ላይ ወደ ቀረው ተሳቢም ተጠጋ፡፡ ሆድ ዕቃውን ሲነካካው ቆየ፡፡ ከዚያም ከሳቢው ጋር የሚገናኝበትን ገመድ ፈታታው፡፡ የጭነት መኪናውን ወደ ተሳቢው አስጠጋና ገጠመው፡፡

«እንዴ ከሌላ መኪና ጋር ልትሄድ ነው እንዴ?» ብዬ ጠየቅኩት፡፡ የተሳቢ ነገር ይሄውኮ ነው፡፡ የራስህ ጭንቅላት ከሌለህ ያገኘህ ሁሉ ይስብሃል፡፡ ሳቢ ተሳቢውን እንጂ ተሳቢ ሳቢውን አይመርጥም ሲባል አልሰማህም፡፡» አለኝ፡፡

«ታድያ አሁን ወዴት ነው የምትሄደው»

«እንደምሄድ እንጂ ወዴት እንደምሄድ አላውቅም፡፡ ተሳቢ መሳቡን እንጂ መንገዱን አያውቅም፡፡» አለ፡፡

መኪናው አጓርቶ ተነሣ፡፡ ተሳቢውም ወደማያውቀው ቦታ ሄደ፡፡

27. ዝምታ ወርቅ አይደለም

ሰውዬው ከሚስቱ ሌላ አንዲት ሴት ወደደና እፍ ከንፍ አለ፡፡ ልጁን እና ሚስቱን እየተወ ከዚህችኛይቱ ጋር ማምሸት፣ ብሎም ማደር ጀመረ፡፡ በመጨረሻም አንድ ቀን ወደ ሚስቱ መጣና ድንገተኛ የሆነ ጥያቄ አቀረበ፡፡ «እኔ እና አንቺ እንድንፋታ እፈልጋለሁ፤ ለምን ብለሽ ምክንያቱን አትጠይቂኝ፡፡ መፋታት ብቻ እፈልጋለሁ፡፡ ደግሞም ሌላ ቀን አይደለም፣ ነገ እንዲሆን እፈልጋለሁ» አላት፡፡ ሚስቱ በሁለት ነገሮች ተጨነቀች፡፡ በአንድ በኩል ምንም ነገር አትጠይቂኝ ብሏታል፡፡ በሁለተኛ ነገር ልጇ ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ፈተና ልትቀመጥ ጥቂት ቀናት ቀርቷታል፡፡ «ባልፈልገውም፣ ባልስማማበትም፤ ካልክ የግድ እቀበለዋለሁ፡፡ ነገር ግን በኛ ምክንያት ልጃችን መጎዳት የለባትምና የአንድ ወር ጊዜ ያህል እንታገሥ፡፡» አለችው፡፡ እርሱም አሰበና «ጥሩ አንድ ወር መታገሥ አያቅተኝም፤ ነገር ግን በዚህ አንድ ወር ውስጥ ሽማግሌ መላክ፣ ምክንያቱን መጠየቅ የለም፤ ስለ ፍቺው ማናችንም ምንም ነገር ማንሣት የለብንም፤

በዚህ ቃል ግቢ» አላት፡፡ እርሷም «እስማማለሁ፤ ግን አንተም የምነግርህን ለመፈጸም ከተስማማህ ነው፤ ታድያ በዚህ አንድ ወር ጠዋት ጠዋት ከዕንቅልፌ ስነሣ፣ ማታ ማታም ወደ አልጋዬ ስሄድ ያኔ የሠርጋችን ዕለት አቅፈህ እንደ ወሰድከኝ አድርገህ አቅፈህ ትወስደኛለህ» ስትል ጠየቀችው፡፡ ነገሩ ያልጠበቀው እና ያልተለመደ ዓይነት ቢሆንበትም፣ ቀላል እና ሊያደርገው የሚችል ስለሆነ እሽ ብሎ ቃል ገባላት፡፡

አንዱ ወር ተጀመረ፡፡

ጠዋት ጠዋት ከዕንቅልፏ ስትነሣ አቅፎ፣ ከፍ አድርጎ፣ ወደ በረንዳ ካደረሳት በኋላ ወደ ሥራው ይሄዳል፡፡ ማታ ማታም እንዲሁ አቅፎ ወደ አልጋዋ ይወስዳታል፡፡ ስለ ፍቾው አይነጋገሩም፡፡ እየዋለ እያደረ ሲሄድ የሰውነቷ ጠረን፣ የምትለብሳቸው ልብሶቿ፣ የዓይኖቿ እና የፀጉሯ ሁኔታ፣ የገላዋ ልስላሴ እና የአካሏ ቅርጽ እየሳቡት መጡ፡፡ በየቀኑ እያቀፈ ሲያወጣት እና ሲያስገባት ሰውነቷ እየቀለለው፤ ለርሱም እርሷን አቅፎ መሸከሙ አንዳች እንግዳ የሆነ የደስታ ስሜት እየፈጠረለት መጣ፡፡ ከራሱም ጋር ሙግት ጀመረ፡፡ «ለምንድን ነው እንፋታ ያልኳት፤ አሁን የሚሰማኝን ስሜት ያህል ስሜት ከአዲሷ ወዳጄ ጋር ለምን አይሰማኝም? ለምንስ ነበር ይህንን ነገር እንዳደርገው ቃል ያስገባችኝ ? ይህን የመሰለውን ገላዋን፣ እንዲህ የሚማርከውን ጠረንዋን፣ እንዲህ የሚያስደስተውን ፈገግታዋን፣ እንዲህ የተዘናፈለውን ፀጉሯን፣ እንዲህ ልዩ የሆነውን አካሏን እንዴት እስከ ዛሬ አላስተዋልኩትም ?እርሷ ናት ከኔ ጋር የነበረችው ወይስ እኔም ከርሷ ጋር ነበርኩ?»

የወሩ መጨረሻ እየደረሰ መሆኑን ሲያውቅ ከእርሷ መለየቱ ጨነቀው፡፡ እንዲያውም ይህ ሁኔታ የፈጠረበትን እንግዳ ስሜት እየወደደው መጣ፡፡ ነግቶ እና መሸቶ እርሷን አቅፏት እስከሚወስዳት በጉጉት መጠበቅ ጀመረ፡፡ በሌላም በኩል ደግሞ በዚህ ድርጊቷ በውስጡ ያሳደረችበትን ስሜት እያሰበ ያደንቃትም ጀመር፡፡ ብልህነቷን፣ አስተዋይነቷን እና በቀላል ድርጊት ቀልቡን ልትገዛው መቻሏን ሲያስበው «ምን ዓይነት አስገራሚ ሴት ናት?» ይላል፡፡ ወሩ ሊያልቅ ሁለት ቀን ሲቀረው የመፋታቱን ሃሳብ በውስጡ መረመረው፡፡ ነገር ግን አላገኘውም፡፡ በዚህ ሁኔታ መፋታቱ ደግሞ ለሕይወቱ የማይፈታ ዕንቆቅልሽ እንደሚሆንበት እያሰበ ተጨነቀ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ አንድ ወር ውስጥ ፍቾን በተመለከተ ላለመነጋገር ቃል ተግባብተዋልና እንዴት አድርጎ ይናገር፡፡ ዛሬም በደስታ ስሜት አቅፎ ከአልጋዋ እንደወሰዳት ሁሉ ማታ ወደ አልጋዋ መለሳት፤ ከበፊቱ እጅግ በጣም ቀለለችው፤ አሳዘነችውም፡፡

በወሩ መጨረሻ:- ወደ አዲሲቱ ወዳጁ ዘንድ ሄደና «የፍቾውን ሃሳብ ሠርገፎዋለሁ፡፡ እኔና ባለቤቴ ፍቅር የሌለን መስሎኝ ነበር፡፡ እኛ ግን ለካስ ፍቅር አላጣንም፡፡ ያጣነው ሁለት ነገሮች ብቻ ነው፡፡ መነጋገር እና መቀራረብ፡፡ ለዚህ ያደረሰንም አለ መቀራረባችን እና አለመነጋገራችን ብቻ ነው፡፡ አሁን ግን መነጋገር ባንችል እንኳን መቀራረብ ግን ችለናል፡፡ ዛሬ ደግሞ መነጋገር እንችላለን፡፡ ስለዚህ ሌላ የሚሆንሽን ፈልጊ» አላት፡፡ ሴትዮዋ ተናደደችና በጥፊ መታችው፤ ከአጠገቧ የነበረውንም ውኃ ቸለሰችበት፤ «ይሄ ለብዙው ኃጢአቴ የተከፈለ ቅጣት ነው» እያለ ወጥቶ ሄደ፡ ፡ ከዚያም ወደ አበባ መሸጫ ሱቅ ውስጥ ገባ፡፡ ያኔ ሲጋቡ የገዛላትን ዓይነት አበባ ገዝቶ ወደ ቤቱ ከነፈ፡፡ «ጓደኛዬ ትዳር ማለት አግብተው የሚኖሩት ሳይሆን በየጊዜው የሚጋቡት ነው ያለው እውነቱን ነው፡፡ ትዳር እንደ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና አንድ ጊዜ አልፈውት ሰርተፊኬቱን የሚሰቅሉት አይደለም ያለው እውነቱን ነው፡፡ ትዳር እና ተክል ከብካቤ ይፈልጋሉ፡፡ እንዲሁ ቢያድጉ ይደጉ ተብለው የሚተው ነገሮች አይደሉም፡፡

«ልክ እዚህ ሀገር ችግኝ የመኮትኮት፣ የማጠጣት፣ የመከባከብ እና የማሳደግ እንጂ የመትከል ችግር እንደሌለብን ሁሉ፤ እኛም ጋር የመጋባት ችግር የለም፡፡ ፍቅር ግን ማግባትን ብቻ ሳይሆን ማጠጣትን፣ መኮትኮትን፣ ማረምን፣ ከብት እንዳያበላሸው አጥር ማጠርን፣ በየጊዜው ማዳበርያ መጨመርን ጭምር ይፈልጋል፡፡ በርግጥ በዕድሉ የሚበቅል ዛፍ እንዳለው ሁሉ በእድሉ የሚኖር ትዳርም ይኖር ይሆናል፡፡ ይህ ግን ሕይወትን ለራስ ጥረት ሳይሆን ለአጋጣሚዎች ብቻ አሳልፎ መስጠት ነው» ያለው እውነቱን ነው፡፡ እኔ አልሰማሁትም እንጂ እርሱስ ተናግሮ ነበር፡፡»

መኪናውን አቆመና ወደ ግቢው ውስጥ ገባ፡፡ በረንዳ ላይ ትጠብቀው የነበረችው ባለቤቱ የለችም፡፡ በሩንም አንኳኳ፡፡ የሚከፍት ግን አልነበረም፡፡ ደግሞ ሲያንኳኳ ገርበብ ብሎ የተዘጋው በር በራሱ ጊዜ ተከፈተ፡፡ ባለቤቱ ግን በዚህች በወሩ ሠላሳኛ ቀን ሳሎንም የለችም፡፡ እየተገረመም፣ ግራ እየተጋባም ወደ መኝታ ቤቱ ዘለቀ፡፡ አልጋው ላይ ፈገግ እንዳለች ጋደም ብላለች፡፡ አበባውን እንደያዘ ጠጋ አለና በእጁ ጉንጯን ነካው፡፡ ቀዝቅዟል፡፡ በቁልምጫ ጠራት፡፡ መልስ ግን አልነበረም፡፡ ግራ ተጋብቶ ዓይንዋን ገለጥ አደረ ገው፡፡ ሊገለጥለት ግን አልቻለም፤ በርከክ አለና ሰውነቷን ደባበሰው፤ ቀዝቅዟል፡፡

«የመጨረሻው ቀን ነው፤ ይህችን ቀን ማየት አልፈልግም፤ ለልጄ ስል እስከዛሬ ታግሻለሁ፤ በቃኝ» የሚል ጽሑፍ ራስጌዋ ላይ አገኘ፡፡

እርሷ ፍቾውን አትፈልገውም፤ ስለዚህም ሳትፋታ ሞተች፡፡ በርሱ ውስጥ የነበረውን የሃሳብ ለውጥ አላወቀችም፤ ምክንያቱም ላይነጋገሩ ቃል ተግባብተው ነበርና፡፡ እርሷ የዛሬዋን ቀን በስጋት እና በጭንቀት ነበር የጠበቀቻት፡፡ የመለያያቸው ቀን፤ የሕይወቷን ግማሽ የምታጣበት ቀን፡፡ የማትፈልገውን ነገር የምታደ ርግበት ቀን ናትና፡፡ እርሱ ግን የዛሬዋን ቀን በጉጉት ነበር የጠበቃት፡፡ የሚነጋገሩባት ቀን፤ ፍቾውን እንደተወው የሚነግርባት ቀን፤ ፍቅሩን የሚነግርባት ቀን፤ ይቅርታ የሚጠይቅባት ቀን፤ ለፍቅሩ ሲል ትን ሽም ብትሆን ቅጣት ከፍሎ የመጣባት ቀን፤ በእርሱ እና በባለቤቱ መካከል የመነጋገር እና የመቀራረብ እንጂ፣ የመዋደድ እና ስሜት ለስሜት የመስማማት ችግር እንደሌለ መረዳቱን የሚገልጥባት ቀን ናትና፡፡ ግን ምን ያደርጋል፤ ሁለቱም ይህንን በየልባቸው ያውቁታል እንጂ አልተነጋገሩም፤ ሃሳባቸውንም በሌላ መንገድ አልተለዋወጡም፡፡ በዚህ የተነሣም በችግሩ መፍቻ ቀን ዋናው ቸግር ተፈጠረ፡፡

ሁለት የትዳር ነቀርሳዎች፡- አለመቀራረብ እና አለመነጋገር፡፡ አብረው አንድ አልጋ ላይ እያደሩ፤ አብረው እየበሉ፤ አብረው እየኖሩ የማይቀራረቡ ባል እና ሚስት አሉ፡፡ አንድ አልጋ ላይ የሚተኙት አንድ አልጋ ላይ መተኛት ስላለባቸው ብቻ ነው፡ ከመጋባታቸው በፊት የነበራቸው ጉጉት እና ናፍቆት አሁን የለም፡፡ ሳይተኙ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል፡፡ አብረው ይበላሉ፤ በአንድ ማዕድ መሆኑ፣ አንድ ጠረጴዛ ላይ መሆኑ እንጂ ያኔ በፊት ለምሳ ሲገባበዙ የነበረው ናፍቆት እና ጉጉት የላቸውም፡፡ ዝም ብሎ መብላት ብቻ፡፡

እያንዳንዷን ቀን ልዩ፣ ደስታ የሚፈጠርባት እና ከትናንት የተለየች ለማድረግ አይጥሩም፡፡ ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ ነገም እንደ ዛሬ ነው፡፡

በስንት ልመና በስንት ጥየቃ፣
በስንት ደጅ ጥናት በስንት ጥበቃ፣
እንግዲህ ምን ቀረሽ አገባሁሽ በቃ፣

እንደተባለው ይሆንባቸዋል፡፡ አገባኋት በቃ፤ አገባሁት በቃ፤ ከንግዲህ ምን ቀረ? ብለው ያስባሉ፡፡ ሰው ተፈጥሮ አላለቀም፡፡ በየጊዜው ነው የሚፈጠረው፡፡ ፈጣሪም ሰውን እንደ ተወለደ እንዲያልቅ አላደረገውም፡፡ በየቀኑ፣ በየሰዓቱ፣ በየደቂቃው ላስተዋለው ሰው እንግዳ ፍጥረት ነው፤ አዳዲስ ነገር ይታይበታል፡፡ ይህ ግን መቀራረብን ይጠይቃል፡፡ ባል እና ሚስት ከተቀራረቡ ሳይፋቱ በየቀኑ ይጋባሉ፤ ጋብቻቸው እየታደሰ ይሄዳል፡፡ የትና ንቷ ሚስት ከዛሬዋ ትለያለች፤ የዛሬው ባልም ከትናንቱ የተለየ ነው፡፡ ለውጥ፣ ዕድገት፣ ብስለት፣ አለ፡፡ መልክም ተለውጧል፡፡ ግን ቀርቦ የሚያየው ያስፈልገዋል፡፡

የዚያ ባል ችግሩ ሚስቱን አግብቷት እንጂ ቀርቧት አያውቅም ነበር፡፡ አብሯት ይኖራል እንጂ ከርሷ ጋር አይኖርም ነበር፤ ምድር በፀሐይ ዙርያ ስለምትዞር ይመሻል ይነጋል እንጂ በእነርሱ የተለየ የሕይወት ጉዞ ምክንያት አይመሽም አይነጋም፡፡ በማከሰኞ እና በረቡዕ መካከል ከስሙ በቀር በሕይወታቸው ውስጥ ልዩነት የለውም፡፡ ሌላው ችግር ደግሞ ያለ መነጋገር ነው፡፡ መነጋገር ማለት በሚያውቁት ቋንቋ ማውራት ማለት አይደለም፡፡ እርሱንማ ከብትም ሲገናኝ እምቧ እምቧ ይባባላል፡፡ ይህ ግን መነጋገር አይደለም፡፡ በየጊዜው፣ በየሰዓቱ፣ ሁለመናን መለዋወጥ ማለት ነው፡፡ ካልተነጋገሩበት የምሥራች፣ የተነጋገሩበት መርዶ ይሻላል፡፡ ካልተነጋ ገሩበት ፍቅር የተነጋገሩበት ጠብ ይበልጣል፡፡ ካልተነጋገሩበት ስጦታ የተነጋገሩበት ንጥቂያ ይሻላል፡፡

ባል እና ሚስቱ ባለመነጋገራቸው ችግሩን በሁለት አቅጣጫ ፈቱት፡፡ የሁለቱም ፍላጎት ችግሩን ላንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት ነበር፡፡ የሁለቱም ፍላጎት ፍቺ የሚባለውን ነገር ላለማየት ነበር፡፡ የሁለቱም ፍላጎት ሠላሳኛዋን ቀን መገላገል ነበር፡፡ ነገር ግን ባለ መነጋገር ምክንያት በሁለት አቅጣጫ ሆነ፡፡ እርሷ ሞትን መረጠች፤ እርሱ ደግሞ ይቅርታን መረጠ፡፡ ችግሩ የመጣው በዚህ ጉዳይ ላለመነጋገር ሲወስኑ ነው፡፡ እርሷ በጉዳዩ ትጨነቃለች፤ ለምን ይሆን ከኔ መለየት የፈለገው? የሚለው ጥያቄ ያሳስባት ነበር፡፡ በሃሳብ ብዛትም እየከሳች ሄዳ ነበር፡፡ ለዚህም ነበር በየቀኑ ሲያቅፋት ትቀልለው የነበረው፡፡ እርሱ ግን መቅለሏን እንኳን ለመጠየቅ ፈራ፡፡ እርሱ ከራሱ ጋር እንጂ ከእርሷ ጋር አይነጋገርም ነበር፡፡

እናም አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ፤ በትዳር ውስጥ ግን ዝምታ ወርቅ አይደለም፡፡

28. የዓለም ዋንጫ በኢትዮጵያ

አሥራ ዘጠነኛው የዓለም ዋንጫ በአፍሪካ ምድር በመካሄድ ላይ ነው፡፡ ሀገራቸውን የወከሉ ቡድኖች ዋንጫ ለመሳም ይፋለማሉ፡፡ እኔ ግን «የኳስ ብቻ ነው እንዴ ዋንጫ ያለው? የሀገርስ ዋንጫ የለውም እንዴ?» ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ «ሀገር እንደ ቡድን ለዋንጫ አይጫወትም ወይ» እያልኩ አሰላስላለሁ፡፡ እናም ጎሊናዬ «ይጫወታል እንጂ» አለና የሚከተለውን ወግ አወጋኝ፡፡

ባታውቀው ይሆናል እንጂ ሀገርማ እንደ ቡድን ለዋንጫ ይጫወታል፡፡ ይሄው ኢትዮጵያ እንኳን ስንት ጊዜ ለዋንጫ ተጫውታለችኮ፡፡ ታድያ እንደ እግር ኳሱ አይደለም፡፡ በዚህኛው ግጥሚያ ዋንጫ የበላችበትም፣ ያጣችበትም ጊዜ አለ፡፡ በርግጥ በታሪክ መዝጋቢዎች ዘንድ አንድ ልዩነት ተከስቷል፡፡ አንዳንዶች ዋንጫ ካጣችበት ይልቅ የበላችበት ጊዜ ይበልጣል ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ዋንጫ ካገኘችበት ይልቅ ያጣችበት ጊዜ ይበልጣል ይላሉ፡፡

በታሪክ ሊቃውንቱ ዘንድ ያለው ልዩነት በኳስ ጠቢባኑም ዘንድ ተፈጥሯል፡፡ ጠቢባኑ «በእግር ኳስ ማጥቃት መከላከል ነው፤ መከላከል ግን ማጥቃት አይደለም» በሚለው ላይ ተስማምተዋል፡፡ «ለመሆኑ ኢትዮጵያ እንደ ቡድን የምትጫወትበት የጨዋታ ፍልስፍና በማጥቃት ላይ ነው ወይስ በመከላከል ላይ ነው የተመሠረተው?» በሚለው ላይ ነው ዋናው ልዩነታቸው፡፡ አንዳንዶቹ በመጀመርያዎቹ የሥልጣኔ ዘመናት በማጥቃት ላይ የተመሠረተ ጨዋታ ስንጫወት እንደ ነበር፤ በዚህም ምክንያት በሥልጣኔ ለመግፋት፣ በዓለም ላይ ኃያል ሀገር ሆኖ ለመቆጠር፣ የዓለምን ንግድ ከሚቆጣጠሩት ኃያላን አንዱ ለመሆን መቻላችንን ያትቱና ከተወሰኑ ዘመናት በኋላ ግን በመከላከል ላይ የተመሠረተ ጨዋታ መጫወት መጀመራችንን ይገልጣሉ፡፡ በዚህም ምክንያት አሸንፈናቸው የነበሩት ማይምነት፣ ረሃብ፣ ኋላ ቀርነት፣ ድህነትና ሌሎችም ቡድኖች ሲያሸንፉን መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡

ሀገሪቱ በእግር ኳሱ ለአፍሪካ ፋና ወጊ፣ለካፍ መሥረት ጣይ፣ ለመጀመርያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫዎች የአንበሳውን ደርሻ ወሳጅ እንዳልነበረች፣ ጭራሽ ወደ ኋላ ሄዳ እግር ኳስ በሀገሪቱ ያለ እስከማይመስል ድረስ ከአፍሪካ ዋንጫ ከራቅን ዘመናት መቆጠሩን በምሳሌነት የሚያነሡ ተንታኞች አሉ፡፡ ይህ ሂደት በብሔራዊ ቡድኑ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱም እንደ ሀገር ጥንት አጥቅታ በመጫወት ስመ ገናና ሆና የሥልጣኔን ዋንጫ እንዳልወሰደች ሁሉ፤ ወደ ኋላ ግን «ሥልጣኔ» የሚለው ቃል በመዝገበ ቃላታችን ውስጥ ያለ እስከማይመስል ድረስ ከውድድር ውጭ ሆነን መኖራችንን በቁጭት ያነሡታል፡፡

ደግሞ አንዳንዶቹ በዚህ አይስማሙም፡፡

እነዚህ የኳስ ተንታኞች ነገራቸውን በማስረዘም «የጣልያን፣ የብራዚል፣ የእንግሊዝ፣ የስፔን፣ የግብጽ፣ እግር ኳስ» እየተባለ የሚጠራ በየሀገሩ የበቀለ፣ በቅሎም ሀገራዊ መሠረት ይዞ ያደገ እግር ኳስ አላቸው፡፡ የአንዱ ፍልስፍና፣ ጠባይ፣ ስልት ከሌላው ይለያል፤ ግን ለመሆኑ የኢትየጵያ እግር ኳስ የሚባል አለ?» በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ታድያ አንዳንዶቹ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን መልስ ቢጤም ለመስጠት ሞክረዋል፡፡

«የኢትዮጵያ ሀገራዊ እግር ኳስ አንዱ ችግሩ ይኼ ነው» ይላሉ፡፡ አንዴ በእንግሊዝ፣ አንዴ በፈረንሳይ፣ አንዴ በአሜሪካ፣ አንዴ በሶቪየት ኅብረት፣ አንዴ በኩባ፣ አንዴ በቻይና የፍልስፍናና የርእዮተ ዓለም እግር ኳስ ስንሠለጥን ኖርን፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያዊ መሠረት ያለው፣ ከትውልዱ ጋር ተስማምቶ የመጣ፣ ለውጤት ልንበቃበት የምንችል ኢትየጵያዊ እግር ኳስ አጣን» ሲሉ ያመሠጥሩታል፡፡

ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን ሀገር ቡድን ሆና ስትጫወት ጨዋታው እንዴት ምርጥ መሰላችሁ ይላሉ ተንታኞቹ፡፡ ሕግ አለ፡፡ ሜዳ አለ፡፡ ዳኛ አለ፡፡ አጥቂ አለ፡፡ ተከላካይ አለ፡፡ አማካይ አለ፤ ግብ ጠባቂ አለ፤ አሠልጣኝ አለ፤ ተጠባባቂ ተጨዋች አለ፡፡ ምን የሌለ አለ፡፡

መቼም የእግር ኳስ ሕግጋት በዓለም ላይ ግልጽ ከሚባሉት መካከል ናቸው፡፡ ደግሞ የሚገርመው የእግር ኳስ ሕግጋት ለሁሉም እኩል የሚሠሩ መሆናቸው ነው፡፡ ታዋቂ ብትሆን ባትሆን፣ ኮከብ ብትሆን ባትሆን፤ ውድ ብትሆን ባትሆን፤ የዳኛው ሀገር ሰው ብትሆን ባትሆን ልዩነት የለውም፡፡ እስከ ተጫወትክ ድረስ፡፡ ታድያ ሀገር ስትጫወት እንደ እግር ኳስ ሕግጋት ግልጽ እና ለሁሉም በእኩልነት የሚሠራ ሕግ ያስፈልጋታል፡፡ በእግር ኳስ የቤት እና የእንጀራ ልጅ እንደ ሌለው ሁሉ ሀገር ከድኅነት፣ ከኋላ ቀርነት፣ ከረሃብ፣ ጋር ተጫውታ ዋንጫ ለመውሰድ

በምታደርገው ግጥሚያም የቤት እና የእንጀራ ልጅ የማይለይበት ሕግ ያስፈልጋታል የሚሉ የኳስ ባለሞያዎች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

አንዱ ያልታደለ ተጫዋች ቀይ ካርድ ያገኘበትን ጥፋት ሌላው እድለኛ ተጫዋች በቢጫ የሚታለፍ ከሆነ፤ አንዱ ምስኪን ባላደረገው ነገር ቢጫ እያየ፤ ተደጋጋሚ ጥፋት የሚያጠፋው ተጫዋች የዳኛ ዓይን እንኳን ሳይገረምመው የሚታለፍ ከሆነ ቡድኑ ይጎዳል። እንኳን ዋንጫ ማምጣት በስዕለት እንኳን ማጣርያውን አያልፍም የሚሉም አሉ።

እግር ኳስ ሕግ ብቻ ሳይሆን ሕጉን በሜዳ ውስጥ በብቃት የሚተገብሩ ዳኞችም ያስፈልጉታል። ከተጫዋቾቹ ወገንተኛነት የጸዱ፣ ለኅሊናቸው እና ለሕግ ብቻ ተገዥ የሆኑ፣ ሕጉን በማስፈጸም ብቃት ያላቸው፣ ለሚወስኑት ውሳኔ በቂ ምክንያት እና በራስ መተማመን ያላቸው፤ ይህንን ብወስን እንዲህ እሆናለሁ ብለው የማይፈሩ፣ እውነቱን ፈርደው ከመሸበት የሚያድሩ፣ ብቁ ዳኞችን ያገኘ ጨዋታ ባለሞያ ሴት እንደያዘችው ወጥ አርኪ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

መቼም ዳኛ ያጣን ጨዋታ እንደማየት እድሜ አሳጣሪ ነገር የለም። ስንቱን ድንቅ ጨዋታ ብቃት እና ቆራጥነት የሌላቸው ዳኞች አበላሽተውታል። አንዱን ቡድን በቀይ ሲያሸበርቁት ሌላኛውን ሞት የሚያስፈርድ ጥፋት እንኳን ቢያጠፋ በፈገግታ የሚያልፉ፤ ለአንዱ ፍጹም ቅጣት ምት ያለ አግባብ ሲሰጡ የአንዱን ቡድን አግባብ ያለው ቅጣት ምት የሚከለክሉ፤ ገንዘብ ተቀብለው ፍርድ የሚያዳሉ፣ ቡድን የሚበድሉ፤ በወገንተኛነት ፍርደ ገምድል ውሳኔ የሚሰጡ ስንት ዓይነት ዳኞችን በእግር ኳስ ታሪክ አይተናል።

አሁን ያ ቲየሪ አነሪ በእጁ እያባበለ ያገባትን ግብ ዳኛው ባለማየቱ አየርላንዶች እንዴት ነው አንጀታቸው ያረረው። የማያይ ዳኛ ችግሩ ይኼ ነው። አንዳንዱ በእግሩ አግብቶ ያልተቆጠረለትን ሌላው በእጁ አግብቶ ይቆጠርለታል። በተለይ ሀገር እንደ ቡድን ስትጫወት በእጃቸው የሚያገቡ ተጫዋቾች እንዳይበዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ይኼው ሁላችንም ይህችን ታሪካዊት ሀገር «ብልጽግና» በሚባለው የፊፋ የደረጃ ሰንጠረዥ ቢቻል እንደ አሜሪካ እና ቻይና ከመጀመርያዎቹ ተርታ ማሰለፍ፤ ካልቻልን ደግሞ የነብራዚልን እና የነ ሕንድን ያክል መካከለኛው ደረጃ ላይ ማድረስ አለብን ብለን ልምምድ ከጀመርን ቆየት ብለናል።

ታድያ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ምርጥ፣ ብቁ፣ የሀገር ነገር የሚበላቸው፣ ባንዴራ ለተባለው እና በአንጻዴ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ላሸበረቀው ማልያቸው ፍቅር ያላቸው፤ ለማሸነፍ እልክ የተሞሉ፤ የቴክኒክ እና የታክቲክ ክሂሎት የተላበሱ ተጨዋቾችን መምረጥ ያስፈልጋል። የተጨዋቾቹ አመራረጥ ብቃት፣ ችሎታ እና ዕውቀትን መሠረት ያደረገ እንጂ በዝምድና፣ በወገንተኛነት እና በጥቅማ ጥቅም እንዳይሆን የእግር ኳስ አምላክ አደራ ብሏል።

በአንዳንድ የእግር ኳስ ቡድኖች እንደሚታየው መመረጥ ያለባቸው ተጨዋቾች ይቀሩና እንኳን ለዓለም ዋንጫ ለሠፈር ግጥሚያ የማይሆኑ ተጨዋቾች ይመረጣሉ። ደጋፊ፣ ተመልካች፣ ሚዲያ፣ ባለሞያ እሪ ቢልም አሠልጣኞቹ «የመጣው ቢመጣ ምን ጦር ቢደረደር» ብለው በወሰኑት ብቻ ይጸናሉ። ታድያ በኋላ ውጤት የጠፋ እንደሆነ መከራ ነው።

አገርም ስትጫወት ታድያ እንዲህ ያለውን አሠራር ካላረምን አለቀልን፡፡ ተጨዋቾች መመረጥ ያለባቸው በችሎታቸው ብቻ መሆን አለበት፡፡ የዚህ ወይንም የዚያ ፖለቲካ አባል መሆን እና አለመሆን፤ ይህንን ወይንም ያንን አመለካከት መቀበል እና አለመቀበል፤ ሰሜን ወይንም ደቡብ መወለድ፣ ቅርበት እና ርቀት አይደሉም ወሳኞቹ፡፡ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሀገር ፍቅር፣ ቁርጠኛነት፣ታማኝነት፣ሥነ ምግባር፣ ለሕግ ተገዥነት፣ እነዚህ ናቸው ዋነኞቹ፡፡ ያለበለዚያ ግን ሀገራችን እንኳንስ የብልጽግናን ዋንጫ ልታመጣ፣ እንኳንስ ማጣርያውን ልታልፍ፣ ከጎረቤት ሀገሮች ተወዳድራ ለሴካፋን ዋንጫ ማጣርያ መቅረቧም ያጠራጥራል፡፡

እግር ኳስ የቡድን ጨዋታ ነው፡፡ አጥቂ፣ ተከላካይ፣ አማካይ፣ ግብ ጠባቂ፣ ሌላውም ሌላውም ተቀናጅቶ ለአንድ ውጤት ሊጫወት ያስፈልጋል፡፡ በርግጥ የኳስን ማርሽ የሚቀይሩ፤ በግላዊ ችሎታቸው ለቡድን ውጤት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ተጨዋቾች በየዘመናቱ ይኖራሉ፡፡ እንደነ ፔሌ፣ ማራዶና፣ ጋሪንቻ፣ ቤከን ባወር፣ አቢዲ ፔሌ፣ ሮማርዮ፣ ሮናልዲኒዮ፣ ካካ፣ ሜሲ፤ ዥረ ስንቶቹ፡፡ በሀገር ቡድንምኮ እንዲህ ያሉት ሞልተዋል፡፡ በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በጦር አመራር፣ በግብርና፣ በፍልስፍና፣ በንግድ፣ በስፖርት፣ የታሪክን ማርሽ የሚቀይሩ ምርጥ ተጫዋቾች አሉ፡፡

ታድያ እነዚህ ተጨዋቾች ዓይን ያለው አሠልጣኝ ይፈልጋሉ፡፡ ካሉበት በመብራት ፈልጎ፤ ተደራድሮ፣ አባብሎም ቢሆን፣ ያለ የሌለ ገንዘቡንም ቢሆን ከስክሶ ወደ ቡድኑ የሚያመጣቸው፡፡ ያደላቸውማ የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሰውንም ሀገር ተጫዋች ለዕውቀቱ እና ችሎታው ሲሉ በገንዘብ ገዝተው ያጫውታሉ፡፡ በሀገር ውስጥ ሲገኝማ ክብር ነው፡፡ ይኼው ብራዚሎች ለፔሌ፣ አርጀንቲናዎች ለማራዶና፣ ጀርመኖች ለቤከን ፓዎር፣ ፈረንሳዮች ለኡነሪ፣ እንግሊዞች ለቤካም፣ ጋናዎች ለአቢዲ ፔሌ፣ አይቮሪኮስቶች ለድሮግባ ያላቸው ፍቅር እና አክብሮት ከመሰማት አልፎ የሚታይ እኮ ነው፡፡
ታድያ እኛም ለእነዚህ በግል ችሎታቸው የታሪክን እና የጨዋታን ማርሽ ለሚቀይሩ ተጫዋቾች ልዩ ክብር ሊኖረን ይገባል፡፡ በእግር ኳስ ቡድናችንም ውስጥ በተገቢው እና በሚገባቸው ቦታ ብናሰልፋቸው ለብልጽግና ዋንጫ የምናደርገውን ጥረት እንዲመነደግ ያደርጉታል፡፡

ምንም እንኳን በግላቸው ተአምር የሚሠሩ ተጫዋቾች ቢኖሩም ብቻቸውን ግን ምንም ሊሠሩ አይችሉም፡፡ እግር ኳስ የቡድን ጨዋታ ነውና፡፡ አገር የብልጽግና ዋንጫ እንድታገኝ የሚደረገው ሰላማዊ ፍልሚያም የቡድን ጨዋታ መሆኑ እሙር ነው፡፡ ይህ የዋንጫ ፍልሚያ ምርጥ አሠልጣኝ ያስፈልጉታል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ሀገሮች ለዓለም ዋንጫ ያሰለፉትን ቡድን በውጭ ሀገር ሰው እስከ ማሠልጠን ይደርሳሉ፡፡ ሰውዬው ከዜግነቱ በላይ ዕውቀቱ ይፈለጋልና፡፡

ሀገርም ድኅነትን እና ኋላ ቀርነትን አሸንፋ የብልጽግና ዋንጫ ማግኘት ትችል ዘንድ ምርጥ አሠልጣኝ ያስፈልጋታል፡፡ ትዕግሥትን ከዕውቀት፣ ልበ ሰፊነትን ከችሎታ፣ አባታዊነትን ከብቃት አዛምዶ ገንዘብ ያደረገ አሠልጣኝ፡፡ ለወገኑ፣ ለሀገሩ ልጅ፣ ለአብሮ አደጉ፣ ያመነውን ለሚያምን፣ በሚሄድበት ለሚሄድ፣ የሚወድደውን ለሚወድ የማያዳላ፡፡ ተጨዋች የመምረጫ መመዘኛው ችሎታ እና ብቃት የሆነ አሠልጣኝ ያገኘች ሀገር ዋንጫ ባትሰም እንኳን ማጣርያውን አልፋ ቢያንስ ግማሽ ፍጻሜ መግባቷ አያጠራጥርም፡፡

ደግሞ እሳት የላሱ አጥቂዎችን ማስለፍ እንዳንረሳ፡፡ ጉልበት ከታክቲክ የያዙ፤ እልክ ከሞራል የተላበሱ አጥቂዎች በመብራት መፈለግ አለባቸው፡፡ ታድያ እነዚህ አጥቂዎች የሥነ ልቡና መረጋጋት እና የልቡና መሰብሰብ ያሻቸዋል፡፡ አታዩትም አንዳንዱን ጎል ሥር ደርሶ መረጋጋት ሲያቅተውና «አሞራው በሰማይ ሲያይሽ ዋለ» እያለ በእግሩ ሲዘፍን፡
፡

በተለይም ደግሞ የማጥቃት ብቃት ያላቸው ፖለቲከኞች፣ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራን፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ ጋዜጠኞች፣ አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች፣ የዲፕሎማሲ ባለሞያዎች፣ በቡድኑ ውስጥ መካተታቸውን አሠልጣኞች እና ረዳት አሠልጣኞች ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ እነዚህ ናቸው በድኅነት እና በኋላ ቀርነት ላይ እንደ ዶሮ ወጥ የሚጣፍጡ፣ እንደ ብርንዶ የሚያስንመጁ ግቦች ማስቆጠር የሚችሉት፡፡ ምን አጥቂ ብቻ፤ ተከላካይ የሌለው የእግር ኳስ ቡድን የጎል ናዳ ነው የሚወርድበት፡፡ ጨዋታውንም እግር ኳስ መሆኑ ቀርቶ ቅርጫት ኳስ ያደርገዋል፡፡ ከተቃራኒ ቡድኖች ከድኅነት፣ ከኋላ ቀርነት፣ ከጭቆና፣ ከአምባገንነት፣ የሚመቱ አደገኛ አደገኛ ጎሎች እንዳይገቡብን ከተፈለገ እንደ ጣልያን ካቴና ዘግተው የሚይዙ የፖሊስ፣ የፍትሕ፣ የሲቪል ማኅበራት፣ የፋይናንስ ሥርዓት፣ የኡዲት፣ የጤና፣ የመንፈሳዊ ተቋማት፣ የፀረ ሙስና፣ ተከላካዮች በደንብ ሠልጥነው መሰለፍ አለባቸው፡፡

በርግጥ አንዳንድ ጊዜ በመከላከል ላይ የተሠማሩ ተጫዋቾች ግብ እንዳይቆጠር በሚያደርጉት ግብግብ ሕግ እስከ መተላለፍ እና ከቢጫ አልፈው ለቀይ ካርድ እስከመዳረግ ይደርሳሉ፡፡ ብዙ ጊዜም የቢጫ እና የቀይ ካርድ ሰለባዎች የሚሆኑት ተከላካዮች ናቸው፡፡ እናም በሀገር ቡድን ውስጥም ያሉ ተከላካዮች ሕግን ያለ ሕግ እናስከብራለን ብለው፣ ሕግ በመተላለፍ እግር እየሰበሩ፣ ተቃራኒን እየጎተቱ፣ እየገፉና እየጣሉ ለቢጫ እና ቀይ ካርድ እንዳይዳረጉ ሥልጠናው ላይ አሠልጣኞች፤ ጨዋታውም ላይ ዳኞች ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ የአማካዩን ነገርስ እንዴት እንረሳዋለን፡፡ ከበረኛው እየተቀበለ፤ ከተከላካዩ እየወሰደ፤ ለአጥቂው እያቀበለ፤ ግቡ እንዲቆጠር ወሳኙ ተጨዋች አማካዩ እኮ ነው፡፡ እኔ ብቻ ላግባ ሳይል፣ ለአጥቂዎች ምርጥ ምርጥ ዕድሎችን እየፈጠረ፣ ግብ የሚሆን ኳስ እያመቻቸ የሚያቀርበው ያ ጀግና አማካይ ባይኖር የምን የጨዋታ ውበት፣ የምን የዋንጫ ሽልማት፡፡ እግር ኳስስ መች በቴሌቭዥን ይታይ ነበር፡፡

ለሀገርምኮ አማካዩ የውጤቷ መሠረት ነው፡፡ በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ያሉት አማካይ ተጫዋቾች እኔ ብቻ ላግባ ሳይሉ፣ ለአጥቂ ሳይንቲስቶች፣ ምሁራን፣ ገበሬዎች፣ ባለ ሀብቶች፣ አርቲስቶች፣ አትሌቶች ነጋዴዎች ኳስ የሚያቀብሉ ታታሪ፣ ጥበበኛ፣ የቡድን ሥራን ዋጋ የሚያውቁ አማካዮች እንዲሆኑ ነው ይህ ሁሉ ልፋት፡፡ አማካይ ሲቪል አገልጋዮች ኳሱን በጊዜ ለአጥቂዎቹ ማቀበላቸውን ትተው እዚያው መሐል ሜዳ ላይ በቢሮክራሲ ሲያንከባልሉት ከዋሉ፤ ሰዓቱም ያልቃል፣ውጤቱም ይጠፋል፡፡
ምን ምርጥ ምርጥ አጥቂ ብናሰልፍ የቢሮክራሲው አማካይ ካልተስተካከለ የአጥቂዎቹን አንጀት እየላጠ፣ ተስፋቸውን እያስቆረጠ፣ ሞራላቸውን እየገደለ፤ የሥራ ተነሣሽነ ታቸውን እየከሰከሰ ሀገሪቱን ውጤት አልባ ማድረጉ የታለመም፣ የተፈታም ነው፡፡ ይሄው በየሀገሩ ገንዘቡን፣ዕውቀቱን እና ልቡን ይዞ ለሀገሩ ቡድን ሊሰለፍ የተነሣውን አልሚ ሁሉ ተስፋ አስቆርጠው ከሀገር ያስወጡት እነዚህ መሐል ሜዳ ላይ ኳስ ማንከባለል የሚወድዱ ቢሮክራት አማካዮች አይደሉ እንዴ፡፡ ይድነቃቸው ይሙት፡፡ እንደ አሞራ የሚንሳፈፉ፣ እንደ ካንጋሮ የሚዘሉ፣ እንደ ዓሣ አንበሪ ኳስ የሚቀልቡ በረኞችንም ካሉበት ተፈልገው የቡድን ተሰላፊ መሆን ይገባቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፍጹም ቅጣት ምት እና የመለያ ምት የመጣ እንደሆነ ብቻቸውን ነውና የሚጋፈጡት፡፡ ኢትየጵያ እንዲህ በነጻነት ኮርታ እንድትኖር ያደረጓት በምንም መልኩ ግባቸውን የማያስደፍሩ ቆራጥ እና ጀግና አርበኛ በረኞች ስለነበሯት ነው፡፡ ዛሬም ታድያ

ለአጥቂውም፣ ለተከላካዩም ለአማካዩም የማያዳሉ፤ ገለልተኛ ሆነው ግባቸውን የሚጠብቁ በረኞች ከሌሉን የዋንጫውን ነገር እንርሳው፡፡ የመከላከያ ሠራዊታችን ይኼው በየድንበሩ ዘብ ቆሞ በሀገሪቱ ላይ አደገኛ ቡድኖች ግብ እንዳያስቆጥሩ እየጠበቀ አይደል እንዴ፡፡

መቼም ሀገራቸው አሠልጥና፣ ስንት እና ስንት ገንዘብ አፍስሳ፣ ውለታዬን ይከፍላሉ ብላ በእግር ኳስ ቡድን ውስጥ ስታሰልፋቸው ከተቃራኒ ቡድን ገንዘብ እየተቀበሉ ውጤት አሳልፈው የሚሰጡ ተጫዋቾች መኖራቸውን ሰምታችኋል፡፡ እነዚህ ማልያው የሀገራቸው፣ ልባቸው የገንዘባቸው የሆኑ ተጫዋቾች በሁለት መንገድ ቡድናቸውን ጎድተውታል፡፡ በአንድ በኩል የቡድኑን የቴክኒክ እና የታክቲክ፣ ብሎም የአሰላለፍ ምሥጢር ለተቃራኒ ቡድን በማሾለክ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሀገራቸው ቡድን ውስጥ ተሰልፈው ለተቃራኒው ቡድን በመጫወት ሀገር ይጎዳሉ፡፡ የሀገሬ ሰው «ባንዶች» የሚላቸው እነዚህን ነው፡፡
ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው
አስቀድሞ መምታት ባንዳ ባንዳውን ነው
ተብሎ የተዘፈነው ስለነእርሱ መሆኑን መቼም የኳስ ደጋፊዎች አትረሱትም፡፡
ደግሞም ሌላም የሚሰማ ነገር አለ፡፡ አንዳንድ የአፍሪካ እና የላቲን አሜሪካ ተጨዋቾች ለተሸጡበት ቡድን የሚጫወቱትን ያህል ለሀገራቸው ቡድን አይጫወቱም እየተባሉ ይታማሉ፡፡ ምክንያቱስ? ሲባል እግራቸውን አጥተው እድሜያቸውን ላለማሳጠር ነው እያሉ የሚተነትኑ ባለሞያዎች አሉ፡፡ በሀገራችን ቡድን ውስጥስ ይኖሩ ይሆን እንዴ፡፡ ከሀገራቸው ወጥተው በባዕድ ሀገር ደም ተፍተው፣ ዕውቀት ሠውተው፣ ጊዜ ከስክሰው እያገለገሉ፤ በየሚሠሩበት ሀገር ባለ ሀብት፣ ሳይንቲስት፣ ምሁር፣ ባለሞያ ሆነው እየሠሩ ለሀገራቸው ተሰልፈው መጫወት ግን የማይፈልጉ ይኖሩ ይሆን እንዴ፡፡

ርግጥ ነው አንድ የሰማሁት ነገር አለ፡፡ አንዳንድ ጥበበኛ እና በሳል ተጫዋቾች፣ አሠልጣኞች በሀገራቸው ክለብ እና ቡድን አላሰልፋቸው ሲሉ ሳይወዱ በግድ ለባዕድ ሀገር ይጫወታሉ ይባላል፡፡ በእነዚህ ላይ ለመፍረድ ይከብዳል፡፡ ታድያ ኢትዮጵያ ከድኅነት፣ ኋላ ቀርነት፣ ኢ ፍትሐዊነት፣ አምባገነንነት ጋር ለምታደርጋቸው ግጥሚያዎች መሰለፍ ሲችሉ የሚያሰልፋቸው ያጡ፤ በዚህም ምክንያት ሀገራቸውን ጥለው ለባዕድ ሀገር ሳይወዱ የተሰለፉ ተጫዋቾች ካሉ አሠልጣኞች እንደገና ጉዳዩን ማየት ሳያስፈልጋቸው አይቀርም፡፡ አንዳንድ ተጫዋቾች ደግሞ ለቡድን ተመርጦ ነገር ግን ዘወትር «ቤንች» ላይ መቀመጥ ይሰለቻል ብለውኛል፡፡ እውነታቸውን ነው፡፡ አልተመረጥንም እንዳይሉ ተመርጠው፤ ነገር ግን አንዳንዶች እንደ መስቀል ወፍ አልፎ አልፎ ብቻ ሲጫወቱ፣ አንዳንዶች ደግሞ ከናካቴው አንድም ቀን ኳስ ነክተው የማያውቁ ተጠባባቂዎች አሉ፡፡ አሁን እነዚህ የሚያጫውተን አጣን ብለው ለሌላ ቡድን ቢሰለፉ ይታዘንላቸዋል እንጂ ይታዘንባቸዋል?

ሞት ይርሳኝና የተመልካቹን ነገር ረሳሁት፡፡ መቼም ጨዋ እና የተማረ ተመልካች ማግኘት ምርጥ አጥቂ የማግኘት ያህል ነው ይባላል፡፡ ሙሉ ጨዋታ እያበረታታ፣ ተስፋ ሳይቆርጥ እየደገፈ፡፡ ውጤት ሲጠፋም ለቀጣዩ ግጥሚያ እየተዘጋጀ፤ ውጤት ሲገኝም እየረካ፤ በገንዘቡ እና በዕውቀቱ እየተሳተፈ፤ በሞራል እና በጭብጨባ መንፈስ የሚያድስን ተመልካች ያህል ጸጋ የት ይገኛል? ሲሠሩ እያመሰገነ፣ ሲያጠፉ በምክንያት እየተቸ፤ ጎበዞችን እየሸለመ፣ ያለ ብቃታቸው የተሠለፉትን እያረመ የሚጓዝ ተመልካች ለማግኘት ለየትኛው ታቦት እንሳል ይሆን፡፡

የኢትዮጵያ ቡድን የብልጽግናን ዋንጫ እንዲያመጣ ከተፈለገ እንዲህ ያለ ተመልካች ያስፈልጋል፡፡ የሚያማ፣ የሚሳደብ፣ የሚወራወር፣ ወገን ለይቶ የሚደባደብ፤ ወይንም ጨርሶ «እኔ የለሁበትም» ብሎ እጁን አጣጥፎ የሚቀመጥ ተመልካች ሳይሆን የሚያበ ረታታ፣ የሚሸልም፣ ለምርጥ ተጫዋቾች ዕውቅና የሚሰጥ፣ ሀገሩ የብልጽግና ዋንጫ እንድታመጣ የሚደረገውን ግጥሚያ በገንዘቡም፣ በዕውቀቱም ባለው ሁሉ ነገር የሚደግፍ ተመልካች ከሌለ ዮፍታሔ ንጉሤ «ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ፣ የእንቧይ ካብ» እንዳሉት ይሆናል፡፡
አንድ የመጨረሻ ነገር እናንሣ፤ ጨዋታው ሊጀመር ስለሆነ፤ የቡድኖቹ ብሔራዊ መዝሙር እየተዘመረ ነው፡፡ በዘመናዊው እግር ኳስ የሚዲያው ሚና ወሳኝ መሆኑን መቼም ታውቃላችሁ፡፡ ገለልተኛ የሆነ፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ፤ ክፉ እና ደጉን ሊያሳይ የሚችል፤ ከስሜታዊነት የጸዳ ሚዲያ ያስፈልገናል፡፡ የሆነውን ነገር በርግጡ የሚነግረን ሚዲያ፡፡ እየተጠቃ ያለውን ቡድን እያጠቃ ነው፣ እያሸነፈ ያለውን ቡድን ጎል እየገባበት ነው፤ ጥፋት እየሠራ ያለውን ተጫዋች እንከን የለበትም፤ ጥፋት የተሠራበትን ቡድን ጥፋተኛ ነው እያለ ጨዋታ የሚያበላሽ ሚዲያ ካለ እግር ኳስ ምኑን እግር ኳስ ይሆናል፡፡

አሁን ጨዋታው ተጀምሯል፡፡ የኢትየጵያ ቡድን ወደፊት መታ፤ ለጥቂት፣ ለጥቂት፣ አያያያያ፡፡

29. ወንበሩ ነው እንዴ?

የአመለካከት ለውጥ በሰዎች ጎሊና ውስጥ ካልመጣ አሠራሮች እና መመሪያዎች ብቻቸውን ምን ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ ጨለማን መተቸት ብርሃን፣ ክፉን መተቸት ደግነት፣ ኋላ ቀርነትን መተቸት ብቻውን ሥልጣኔ፣ ድንቁርናን መተቸት ብቻውን ዕውቀት አያመጣም፡፡ በሽታውን ተቃውመሃል ማለት መድኃኒቱን ይዘሃል ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ ረሃብን ታወገዛለህ ማለት ጥጋብን ታመጣለህ ማለት ነው የሚለውን ዋስትና አያሰጥም፡፡ አንዳንዴ በተቃራኒውስ ሊሆን ቢችል?

ጥቂት የገረሙኝን ነገሮች እስቲ መጀመርያ ላካፍላችሁ፡፡ ተራ ሰው እያለ ጨዋ፣ ሰው አከባሪ፣ እንኳን የሰው ገንዘብ ሊወስድ የራሱን አበድሮ የማያስመልስ፣ በሀገሩ ኋላ መቅረት የሚቆጭ፣ በሞሳኞች የሚናደድ፣ በቢሮክራሲ የሚማረር የነበረ ሰው ዕድሉን አግኝቶ ቦታውን ሲይዘው፣ ሲጠላው የነበረውን ነገር ለምንድን ነው በባሰ ሁኔታ ሲፈጽመው የሚገኘው ?

ተራ አገልጋዮች እያሉ ትጉኃን፣ ብቁዐን፣ ቅኑዐን፣ መንፈሳውያን የነበሩ ሰዎች እንዴት ነው የሥልጣኑን ቦታ ሲይዙት፣ ደግነታቸው እና ቅንነታቸው፣ መንፈሳዊነታቸውና ታማኝነታቸው ሁሉ ጠፍቶባቸው «ሥልጣን በቀረባቸው ኖሮ» እስከመባል የሚደርሱት?

እዚህ ሀገር ቤት እያለ ዋነኛ የመንግሥት ፖሊሲ ደጋፊ እና ተከራካሪ የነበረ ሰው ወደ ውጭ ወጥቶ መኖር ሲጀምር ለመለወጥ አፍታ እንኳን ሳይወስድበት እንዴት ነው ሲደግፈው የነበረውን ሁሉ በጭፍን መቃወም የሚጀምረው? ጭንቅላት እንደ ኮምፒውተር ሶፍትዌሩን በደቂቃ ይቀይራል እንዴ፡፡ መለወጥስ ተፈጥሯዊ ሂደት የለውም?

በተቃራኒውም እዚያ ውጭ ሀገር እያለ መንግሥት ምንም ዓይነት የጽድቅ ሥራ ቢሠራ አልጥምህ ብሎት ሲቃወም የኖረ ሰው ሀገር ቤት ሲገባ በምን ዓይነት ሁኔታ ሀሳቡን ሊቀይር እንደቻለ ሳይታወቅ እንዴት ነው መንግሥት

ተሳስቼያለሁ ያለበትን ነገር ሳይቀር «እንዴው ለትጎትና ነው የተናገረው እንጂ አልተሳሳተም» እያለ ጭፍን ደጋፊ ሊሆን የሚችለው?

አስቀድመው በተቋቋሙት ፓርቲዎች አለመተባበር፣ አለመሥራት፣ ግለኛነት፣ አለመጠናከር፣ የጠራ ፖሊሲ ማነስ ተናድዶ እና የተሻለ ነገር መሥራት አለብኝ ብሎ አዲስ ስም እና መተዳደርያ አውጥቶ አዲስ ፓርቲ ያደራጀ ሰው እንዴት ነው የተናደደባቸውን የሌሎች ፓርቲዎች ድክመቶች እና ስሕተቶችን በፎቶ ኮፒ የሚደግመው?

ምናልባት ከላይ ላነሣሁት ችግር መነሻው ወንበሩ ይሆንን?

ወንበሩ ግድግዳውን፣ ጣራውን፣ ጠረጴዛውን፣ መደርደርያውን ሁሉ ገንዘብ በገንዘብ አድርጎ ያሳያል እንዴ? ወንበሩ ዘመድ ዘመድ ቅጠር፣ ቢሮክራሲ አብዛ፣ ተሰብሰብ ተሰብሰብ፣ ያሰኛል እንዴ? ያለፈውን አሠራር ለማሻሻል ስንት ቢፒአር ያሠሩ ኃላፊዎች የበፊቶቹ ኃላፊዎች ከሠሩበት አሠራር በባሰ እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው ወንበሩ ይሆን? የለውጥ ሐዋርያት ተብለው፣ የየመሥሪያ ቤቱን ቢፒአር አጥንተው፣ያለፈውን ተችተው እና አዲስ አሠራር ቀርጸው፣ ለውጡን ያራምዳሉ ተብለው በቦታው ሲቀመጡ፣«የውኃ ውኃ ምናለኝ ቀሃ» የሚያሰኙን ከወንበሩ ይሆን?

ስብሰባ ላይ ስለ ሙስና፣ ስለ ብልሹ አሠራር፣ ስለ ሀገር ዕድገት፣ በምግብ ራስን ስለ መቻል፣ስለ ሰብአዊ መብት፣ስለ እኩልነት፣ስለ ፍትሕ፣ ተንትነው እና አሳምረው የሚናገሩ ሰዎችን ሳይ እና ስሰማ ሰዎቹ የሚያምኑበትን ነው የተናገሩት ወይስ ወንበሩ ነው ያናገራቸው? እላለሁ::

የመጀመርያ ዲግሪያቸውንም ሆነ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የመመረቂያ ጽሑፍ ሲያዘጋጁ የተቹትን፣ ቢታረም እና ቢስተካከል ብለው ሃሳብ ያቀረቡበትን ነገር እነርሱ ቦታውን ሲይዙት ግን እንዲያ የሚባል ሃሳብ መኖሩን እስኪረሱት ድረስ በተቹት አሠራር መልሰው እንዲሠሩ የሚያደርጋቸው ወንበሩ ይሆን እንዴ?

ናይሮቢ ከተማ ውስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች የሚኖርበት «ኪቢራ» የሚባል መንደር አለ:: የሀገራችን ሰው «ካሉት በታች ከሞቱት በላይ» የሚለው የኑሮ ዓይነት በዓይነ ሥጋ የሚታየው እዚያ ነው:: ከሚበሉበት የማይበሉበት ጊዜ የሚበልጥባቸው ድሆች በተጨናነቀ እና በቆሻሻ በተሞላ አካባቢ ይኖራሉ:: የዛሬው የኬንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ራይላ ኡዲንጋ ከፍተኛ ድጋፍ ያገኙት በኪቢራ መንደር ነበር፤ ምርጫው ተጭበረበረ ባሉ ጊዜም አያሌ መሥዋዕትነት የከፈሉላቸው የኪቢራ ድሆች ናቸው:: ኪቢራን ለማሻሻል፣ ቢያንስ መኖርያ፣መንገድ፣ ትምህርት ቤት እና የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ቃል ገብተው ነበርና::

ምርጫው ከነግርግሩ አልፎ ራይላ ኡዲንጋም ቦታውን ያዙ:: ኪቢራ ግን አሁንም ያንኑ የድህነት ጉዞዋን እንደ ቀጠለች ነው:: የተነገረ እንጂ የተሠራ ነገር ለማየት አልታደለችም:: እንዲያውም ኡዲንጋ ለቀጣዩ ምርጫ እየተዘጋጁ ነው:: ኡዲንጋ ከመመረ ጣቸው በፊት «ኬንያውያን ፍትሕ እና ማኅበራዊ ዋስትና አጥተዋል» እያሉ ለመተቸት በምሳሌነት የሚያነሷት ኪቢራን ነበር:: የኪቢራን የድህነት ጉዞ የኬንያን ኢፍትሐዊ አሠራር ማሳያ አድርገውት ነበር: : በቦታው ላይ ሲቀመጡ ግን እርሳቸውም እንደ ቀድሞዎቹ ሆኑና አረፉት:: እኔ ኪቢራን ከሁለት ሳምንት በፊት ስነበኝ ያገኘኋቸው ኬንያዊ ሽማግሌ «ወንበሩ ነው፣ ችግሩ ከወንበሩ ነው፤ እኛ አሁን በወንበሩ ላይ ማን ይቀመጥ ማለታችንን ትተን ሰዎቻችን በምን ዓይነት ወንበር ላይ ይቀመጡ ብለን ማሰብ አለብን» ነበር ያሉኝ::

አንድ ጊዜ እንስሳት ሁሉ በአንበሳ አገዛዝ ተማረሩ፡፡ በርሱ ያገዛዝ ዘመን በዙርያው ያለው ዛፉም ቅጠሉም፣ ሣሩም አፈሩም ሥጋ እየመሰለው ይህንን ቁረጥ ያንን ፍለጥ እያለ ሊጨርሳቸው ደርሶ ነበር፡፡ በዚህ ተማርረው እንስሳቱ ሁሉ ዐመጹና አንበሳን ከመንበሩ አወረዱት፡፡ ከዚያም ያለፈውን ስሕተት ሊደግም የማይችል ማን ነው? ብለው ተመካከሩ፡፡ በመጨረሻም በደግነቱ፣ በየዋሕነቱ በቅንነቱ ተማርከው፤ ሥጋ በል ባለመ ሆኑም ተደስተው በግ ንጉሥ እንዲሆናቸው መረጡት፡፡ እርሱም በደስታ ተቀበለው፡፡

የንግሥናውን በዓል አክብሮ በትረ መንግሥቱን ጨብጦ ወደ መንበረ መንግሥቱ ሄዶ ተቀመጠ፡፡ ወዲያውም አጠገቡ የቆመውን ጠባቂውን ጠራና «ያንን ሥጋ አምጣው» አለው፡፡ ጠባቂውም ግራ ገባውና «ጌታዬ እርስዎ ሥጋ የማይበሉ በግ ነዎት፣ ደግሞም በአካባቢው ቅጠል እንጂ ሥጋ የለምኮ» ብሎ መለሰለት፡፡ በጉም «ያ ሽንጥ እንዴት አይታይህም፤ ደግሞስ ሥጋ ካማረኝ መብላት መብቴ ነው፤ ንጉሥ አይደለሁም እንዴ» አለው፡፡

ግራ የገባው ጠባቂ ፈጠን ብሎ በአካባቢው ወደ ነበሩት ሽማግሌዎች ተጓዘና «ንጉሥ በግ» ያዘዘውን ነገራቸው፡፡ እነርሱም በተራቸው ግራ ተጋብተው ወደ ንጉሡ በግ መጡና «ጌታችን ምን ፈለጉ?» ብለው ጠየቁ፡፡ ንጉሥ በግም «እዚያ የተሰቀለውን ሽንጥ ሥጋ አምጡልኝ» አላቸው፡፡ ሽማግሌዎቹም «ጌታችን እርስዎ ከመቼ ጀምሮ ነው ሥጋ መብላት የጀመሩት፤ በግ እኮ ነዎት» አሉት በጉም «ዛሬ ብጀምርስ ማን ከልክሎኝ» አለና መለሰላቸው፡፡ «በግ እኮ ሣር በል ነው እየተባለ ነው የሚነገረው፣ በትምህርት ቤትም ልጆቻችን የሚማሩት እንደዚሁ ነው» አሉና ጠየቁት፡፡ «በሉ እንደዚያ ከሆነ የምታውቁት ዕውቀታችሁን አስተካክሉ፡፡ የመማርያ መጽሐፉንም አስተካክሉ» አለ ቆጣ ብሎ፡፡

ሽማግሌዎቹ ቢቸግራቸው «በአካባቢያችንኮ ቅጠል እንጂ ሥጋ የለም» አሉት በጉን፡፡ በጉም «ይሄው ይታየኛልኮ፤ በአስቸኳይ ሂዱና አምጡ» አላቸው፡፡ ሽማግሌዎቹም ተያዩና «ላይ የለም ችግሩ ከበጉ ወይንም ከአንበሳው አይደለም፡፡ ከወንበሩ ነው፡፡ እዚህ ወንበር ላይ ሲቀመጡ ቅጠሉን ሥጋ አድርጎ ያሳያል ማለት ነው» ተባባሉ፡፡ ከዚያም በጉን አባረሩት፡፡ በሁኔታው ግራ የተጋባው ኢጋዝንም «እስኪ ይሄ ነገር ምን እንደሆነ ልሞክር» ብሎ መንበሩ ላይ ሄዶ ተቀመጠ፡፡ ሽማግሌዎቹም «ደግሞ አንተ ምን ታየህ?» ብለው ጠየቁት፡፡ ኢጋዝኑም ፊት ለፊቱ ወዳለው ዛፍ ዞሮ ምራቁን እየዋጠ «ያ ሥጋ እንዴት ያሳሳል» አለ ይባላል፡፡

30. 171ኛው ሆስፒታል

በዓለም በደረጃው 171ኛ በሆነው ሆስፒታል ውስጥ ነው ከዚህ የሚከተለው ታሪክ የተፈ ጸመው፡፡ ይህ ሆስፒታል ዛሬ አንድ መቶ ሰባ አንደኛ ይሁን እንጂ እጅግ ገናና የሆነ ታሪክ እና ዝና የነበረው ነው፡፡ አያሌ ከባድ በሽታዎችን ድል እየመታ፣ ታላላቅ ሰዎችን እያፈራ፣ ለአንድም ቀን በበሽታ ሳይደፈር የኖረ ሆስፒታል ነው – 171ኛው ሆስፒታል፡፡

አንድ ቀን የሆስፒታሉ አምስት ሠራተኞች ሻሂ እየጠጡ የቆጥ የባጡን ይጨዋወቱ ነበር፡፡ በመካከል ላይ «እኛ ለብዙ ዓመታት በዚህ ሆስፒታል ውስጥ እየሠራን ነው፤ ሆስፒታላችን ግን እናውቃለን በሚሉ ጥቂት ዶክተሮች የተያዘ ነው፡፡ እነዚህ አምስት እና ስድስት ዶክተሮች ብቻ ናቸው ቀዶ ሕክምና እያደረጉ የሚያከሙት፡፡ በዚህ ምክንያትም ገንዘብ፣ ስም እና ዝና ያገኙት እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ ይህ የጥቂት ዶክተሮች አስ ተዳደር ማብቃት አለበት፡፡ ሁላችንም ይህ ዕድል ያለ አድልዎ ሊሰጠን ይገባል» የሚል ሃሳብ አነሡ፡፡ ይህ ሃሳብ እንደ ሰደድ እሳት በሆስፒታሉ ውስጥ በአንድ ጊዜ ተነዛ፡፡ የጥበቃ ሠራተኞች፣ ጸሐፊዎች፣ የጤና ረዳቶች፣ መዝገብ ቤቶች፣ አትክልተኞች፣ ምግብ ቤቶች፣ ፋርማሲስቶች፣ የጥገና ባለሞያዎች፣ ግዥ ክፍሎች፣ ሌሎችም ሃሳቡን በመደገፍ ተነሡ፡፡ «ካሁን በኋላ የጥቂት ዶክተሮች የአገዛዝ ዘመን ማብቃት አለበት» የሚለው መፈክር ይስተጋባ ጀመር፡፡

በዐሥረኛው ቀን ሠራተኞቹ ማኅበር አቋቋሙ፡፡ የማኅበሩ ሊቀመንበርም የሆስፒታሉን ባልደረቦች ለስብሰባ ጠራ፡፡ «ዛሬ የተሰበሰብነው ለለውጥ ነው፡፡ ይህ ሆስፒታል ከተቋቋመ አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ እስካሁን ሕመምተኛውን ቀዶ ሕክምና እያደረጉ ስም እና ዝና ያተረፉት፣ ዳኅስ ዳኅስ ያለ ደመወዝም የሚያገኙት ጥቂት ዶክተሮች ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ማብቃት አለበት፡፡ እኛስ በምን እናንሳለን፡፡ ሁላችንም የሆስፒታል ሠራተኞች መባላችን ካልቀረ ዕድሉ ሊሰጠን ይገባል፡፡ ለዚህ ነው የጠራናችሁ» በማለት ሰብሳ ቢው ሲናገር አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ፡፡

እነዚያው ጥቂት ዶክተሮች ሃሳብ ለመስጠት እጃቸውን ቢያወጡም የሚሰማቸው አላገኙም፡፡ አንድ በጥበቃነት ሲያገለግሉ የኖሩ ሰውየ ተነሡና፡፡ «ይህንን ላሰባችሁት ዕድሜ ይስጥልን፡፡ ለብዙ ዘመናት ሲያንገበግበን የኖረ ነገር ነው፡፡ እኔ ለምሳሌ ሰላሳ ስምንት ዓመት አገልግያለሁ፡፡ እስካሁን ግን አንድ በሽተኛ አክሜ፤ አንድም መድኃኒት አዝዤ አላውቅም፡፡ ለስሙ ግን የሆስፒታሉ ሠራተኛ ነኝ፡፡ በሽተኞችም እየመጡ "ሐኪም እገሌ የሉም?" ነው የሚሉት፤ ይህ አሠራር ማቆም አለበት» ብለው አስጨበጨቡ፡፡

በዚህ ጊዜ አንደኛው የቀዶ ጥገና ሐኪም በንዴት ጦፈው ተነሡ፡፡ «አራት ደቂቃ ብቻ» አሏቸው ሰብሳቢው፡፡ «ሕክምና ሞያ ነው፡፡ ማኮም ከፈለጋችሁ ተማሩ፡፡ ብዙ ሐኪሞችን ከፈለግን ብዙ የሕክምና ኮሌጆችን መክፈት እንጂ ተሰብስቦ መወሰን አይደለም መፍትሔው፡፡ ሞያ በመማር እና በመልመድ እንጂ እንደ ጠበል በመረጨት አይገኝም፡፡ ችግራችንን ከድጡ ወደ ማጡ እንዳትከቱት» ሊሰሟቸው የፈለጉ ጥቂቶች ናቸው፡፡

«ዋናው ነገር ትምህርት ነው የምትሉት እድሜያችሁን ለማራዘም ነው፡፡ ሕዝብ ካመነብኝ እንኳንስ ሐኪም ሌላም መሆን ይቻላል፡፡ እኔኮ ለዚህ ሆስፒታል ታማኝ ሆኜ ሃያ አምስት ዓመት አገልግዬአለሁ፡፡ ዋናው ለማኅበራችን ያለን ታማኝነት ነው፡፡» አንዲት በጽዳት ሠራተኛነት ያገለገሉ እናት ለንዴቱ በንዴት መልስ ሰጡ፡፡

«እኔ ሃሳብ አለኝ» አሉና አንድ የመዝገብ ቤት ሠራተኛ ተነሡ፡፡ «ካሁን በኋላ አንድ በሽተኛ ሲመጣ በር ተቆልፎ ዶክተሩ ብቻቸውን የሚያነጋግሩበት አሠራር መቅረት አለበት፡፡ ለምንድን ነው ሁላችንም የማንሰማው? ይሄ እኛ እንዳናውቅ የሚደረግ ሜራ ነው፡፡ ስለዚህም እዚሁ አዳራሽ እየመጣ በሽተኛው ይጠየቅ፡፡ ሁላችንም የመመርመር እድሉን እናግኝ፡፡ በሽታው ምን እንደ ሆነ አንድ ዶክተር ብቻውን በአምባገነንነት መወሰንም የለበትም፡፡ እዚሁ አዳራሽ ውስጥ በድምጽ ብልጫ መወሰን አለበት» ተጨበጨበ፡፡

«ተጨማሪ» አሉ የሆስፒታሉ ሾፌር «ላቦራቶሪ የሚባል የሰው ደም የሚጨርስ ነገር መቅረት አለበት፡፡ እኛ እንዳናውቀው እየጫሩ ሐኪሞቹ ይልካሉ፤ እየጫሩ ባለ ላቦራቶሪዎች ይመልሳሉ፡፡ መቅረት አለበት፡፡ ላቦራቶሪ ከሕዝብ ድምፅ አይበልጥም፡፡ ደግሞም ካሁን በኋላ ጥቂት ዶክተሮች ለብቻቸው ቀዶ ጥገና የሚያደርጉበት አሠራር ቀርቶ ማን ቀዶ ጥገና ማድረግ እንዳለበት እዚሁ በስብሰባ መወሰን አለበት» አሁንም ተጨበጨበ፡፡

አምስቱም ዶክተሮች እጃቸውን አወጡ፡፡ «ሥነ ሥርዓት» ይላሉ ደጋግመው፡፡

በስንት መከራ ለአንዱ ተፈቀደላቸው፡፡ «ሕክምና ሞያ ነው፡፡ ሕመምተኛም እዚህ የሚመጣው ባለሞያ ፈልጎ እንጂ ለስብሰባ አይደለም፡፡ ያለ ላቦራቶሪ እንዴት ነው በሽታን ልንለይ የምንችለው? በምን አሠራር ነው ሁላችሁም ልታክሙ የምትችሉት? መግደል ነው እንዴ የምታስቡት፡፡» ሐኪሙ ሳይጨርሱ አንዲት የጤና ረዳት ተነሡና «ይህ ንቀት ነው፡፡ ንቀት ነው፡፡ ዕውቀት ሁለተኛ ነገር ነው፡፡ የመጀመርያው ለሆስፒታሉ የሠራተኞች ማኅበር ታማኞች ነን አይደለንም? ነው፡፡ ቀጣዩ ደግሞ ሕዝብ መርጦናል ወይስ አልመረጠንም ነው፡፡ የቀረው ነገር ፍሬ ከርስኪ ነው» ተሳቀ፤ ተጨበጨበ፡፡

በስብሰባው መጨረሻ በወጣው የአቋም መግለጫ ስድስት ውሳኔዎች ተወሰኑ፡፡

1. ማንኛውም በሽተኛ ወደ ሆስፒታሉ ሲመጣ ወደ ስብሰባው አዳራሽ ገብቶ፣ በግልጽነት፣ በሁሉም ሠራተኞች ፊት እየተጠየቀ እንዲመረመር፤ በድብቅ ዶክተሩ ብቻውን መመርመሩ እንዲቀር

2. ላቦራቶሪ፣ አልትራሳውንድ፣ ራጅ፣ የመሳሰሉት ለብዙኃን አሠራር ስለማይመቹ እንዲቀሩ፡፡ ደግሞም ከመላው ሠራተኛ ድምጽ እነርሱ አይበልጡም

3. ማንኛውም በሽተኛ ምን እንዳመመው በድምፅ ብልጫ እንዲወሰን

4. ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገውን በሽተኛ ማን ቀዶ ጥገና ማድረግ እንዳለበት በድምጽ ብልጫ እንዲወሰን፤ ዶክተሮች እንደማንኛውም ሠራተኛ ድምጽ ካገኙ ያክማሉ፡፡

5. ቀዶ ጥገና አድራጊ ማን ማድረግ እንዳለበት ሲወሰን መጀመርያ ለሠራተኛ ማኅበሩ ያለው ታማኝነት፣ ቀጥሎ ከዚህ በፊት ዕድሉን ያላገኘ መሆኑ፣ እንዲታይ

6. ቀዶ ጥገና አድራጊዎች ከልዩ ልዩ የሆስፒታሉ ክፍሎች ያላቸው ተዋጽዖ እንዲመጣጠን

ተጨበጨበ፡፡

የመጀመርያው በሽተኛ ይግባ ተባለ፡፡ በሽተኛዋ ተጠሩ፡፡ «ወ/ሮ ሀገሬ ይግቡ» ወ/ሮ ሀገሬ ገቡ፡፡ በተሰብሳቢው መካከል አልፈው መድረክ ላይ ተቀመጡ፡፡ ቀድሞ ከሚያውቁት ስለተለየባቸው ግራ ገባቸው፡፡ ሰብሳቢው ጥያቄ ጀመረ፡፡

«ምንዎን ነው የሚያምዎት?»

«ራሴን»

«ከጀመረዎ ምን ያህል ጊዜ ነው»

«ብዙ ዓመት ሆኖታል»

«ዕረፍት ያደርጋሉ»

«አዬ ልጄ ምን ዕረፍት አለኝ»

«ይበቃል» ተባሉ፡፡

«በሉ በሽታቸው ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ላይ ሃሳብ ስጡና በድምፅ እንወስን» አሉ ሰብሳቢው፡፡

«ጨጓራ ነው» «የለም ኩላሊት ነው» «የለም የለም ጉበት ነው» «ፈጽሞ፣ ይህማ መጋኛ ነው» «የለም ደንቃራ ተደርጎባቸው ሳይሆን አይቀርም» ሃሳቦቹ ከያቅጣጫው መጡ፡፡ አሁንም ዶክተሮቹ እየተነሡ ጮኹ፡፡ ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል ነውና ሰሚ አላገ ኙም፡፡ «በሽታ እንዴት በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፤ በቂ ምርመራ ተደርጎ፣ አስፈላጊ የሆኑ ላቦራቶሪ፣ የአልትራ ሳውንድ፣ የመሳሰሉት ውጤቶች ሳይታዩ እንዴት ብዙ ሰው ስለተናገረ ብቻ ሊወሰን ይችላል፡፡ ለምን ታማሚውን እንገድለዋለን» ማን ይስማ፡፡

«ድምፅ ስጡ» ተባለ፡፡

ከአምስት ተቃውሞ በቀር በብዙኃኑ ድምፅ «በሽታው ኩላሊት ነው» ተብሎ ተወሰነ፡፡ ሕመምተኛዋ ወ/ሮ ሀገሬ ተቃወሙ «እኔ ኩላሊቴን ደኅና ነኝ፡፡ ተውኝ እባካችሁ፡፡ እን ዲያውም መታከም አልፈልግም፡፡ ይቅርብኝ እንዲሁ ብኖር ይሻለኛል፡፡ "ትሻልን ሰድጂ ትብስን አመጣሁ" አሉ አያቴ፡፡ በቃኝ አልፈልግም» ተንገበገቡ፡፡

«የለም የለም፤ ይህንን ያህል ጊዜያችንን አባክነውማ አልታከምም ማለት አይችሉም፡፡ አሁንማ ድምፅ ተሰጥቶ፣ ተወስኖ፣ የግድ ነው፤ ይታከማሉ» ሰብሳቢው ተቆጣ፡፡

«ቀዶ ጥገና ያስፈልገዋል አያስፈልገውም?» ሰብሳቢው ጠየቀ፡፡ ከአምስት ተቃውሞ በስተቀር «ያስፈልገዋል ተብሎ ተወሰነ»

«እሺ ማን ቀዶ ጥገና ያድርግ» ሰብሳቢው መጠየቅ ሲጀምር አንዱ ዶክተር ዘለው ተነሡ «ኧረ ስለ ፈጠራችሁ፤ ሰው መቀለጃ አይደለም፡፡ እስቲ ይዋል ይደር በሉ»

ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል በመሆኑ የሰማቸው የለም፡፡

ጥቆማዎች ቀረቡ፡፡ በመጨረሻም የሆስፒታሉ አትክልተኛ ሆነው ለሠላሳ ዓመታት ያገለገሉትና አሁን ዓይናቸውን የጋረዳቸው አቶ እንዳለ ተመረጡ፡፡ ጭብጨባው አስተጋባ፡፡

አቶ እንዳለ ወደ መድረኩ ሲወጡ «ወ/ሮ ሀገሬ ይቅርብኝ አልታከምም» እያሉ ይጮኻሉ፡፡ ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል መሆኑ የገባቸው አልመሰለኝም፡፡

«ለዚህ ዕድል በመመረጤ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ፡፡ እናንተ ካመናችሁብኝ ገና ብዙ አፐሬሽን አደርጋለሁ፡፡ ዋናው መማር ሳይሆን መመረጥ ነው፡፡ የተማሩ ብዙዎች የመሚመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ በሉ በሽተኛዋን እዚህ ጠረጴዛ ላይ አስተኙና ዓይኔን ጋረድ ስላደረገኝ ቢላዋውንና መቀሱን አስይዙኝ፡፡ ደግሞም ኩላሊት የት እንደሚገኝ በእጄ አስጨብጡኝ፤ የቀረውን ነገር ለኔ ተውት»

ዶክተሮች ሊከላከሉ ይታገላሉ፤ ወ/ሮ ሀገሬ ይጮኻሉ፤ ይህ ግን 171ኛው ሆስፒታል በመሆኑ የሚናገር እንጂ የሚሰማ አላገኙም፡፡

31. [ኤልዛቤል ከታሪክ አንድ ገጽ](#) **:**

ታሪክ ራሱን ይደግማል ይባላል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉ ምሳሌዎች በአንድ ወቅት ብቻ ተፈጽመው የቀሩ ታሪኮች አይደሉም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በየዘመናቱ የሚከሰቱ የቤተ ክርስቲያን ጉዞ አካላት ናቸው፡ ፡ እነዚህ ለክፉም ሆነ ለበጎ ምሳሌ ሆነው የተጻፉ ታሪኮች፣ ቤተ ክርስቲያንን የመከራ እና የደስታ ዘመናት ተከትለው ይፈጸማሉ፡፡ የዮሐንስ ራእይን ለመተርጎም ከተጻፉ ከግሪክ እና ሶርያ የጥንታውያን መዛግብት ያገኘሁትን ይህንን ትርጓሜ እስኪ ተመልከቱት፡፡

ነገር ግን አንተን የምነቅፍበት ነገር አለኝ፡፡ ሳትሆን ራሰዋን ነቢይት ነኝ የምትለውን አገልጋዮቼንም ለጣዖት የተሠዋውን እንዲበሉ እና እንዲሴሰኑ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያቺን ሴት ኤልዛቤልን ዝም ብለሃታልና (ራእይ 2÷20)

ኤልዛቤል ማናት?

በብሉይ ኪዳን: በብሉይ ኪዳን የአክአብ ሚስት፣ የሲዶናዊው የኤትበኣል ልጅ ናት (1ኛነገሥ.16-31)፡፡ ባልዋን አክአብን የበኣልን ጣዖት እንዲያመልከና ክፉ ሥራ እነዲሠራ ትገፋፋው የነበረች እርሷ ነች፡፡ በእሥራኤል አምልኮ ባዕድ እንዲስፋፋ ያደረግችና ኤልያስን ያሳደደችው ኤልዛቤል ነበረች፡፡ በቤተ መንግሥቷ አራት መቶ የበኣል፣ አራት መቶ ሃምሳ የአሸራህ ነቢያትን ትመግባቸው ነበር (1ኛ ነገሥ.18-19)፡፡ ባልዋ አክአብ የየዋሑን ሰው የናቡቴን የወይን

እርሻ ለመውሰድ አስቦ ናቡቴ ርስቴን አልሸጥም ባለው ጊዜ ተናደደ። አልዛቤልም ይህንን አይታ ናቡቴን በግፍ አስገደለችው። እርሻውንም ቀማችው (1ኛ ነገሥ.21÷1-19)።

በሐዲስ ኪዳን: በዮሐንስ ራእይ አልዛቤልን የተጠቀሰችውን የትያጥሮኗን ኤልዛቤል በተመለከተ ለቃውንት ልዩ ልዩ ሐተታ አቅርበዋል።

የመጀመርያው ሐተታ ኤልዛቤል የተባለችው የጳጳሱ ሚስት ናት የሚለው የሶርያን እና የግሪክ ጥንታዊ መዛግብት መሠረት ያደረገው ትርጉም ነው። በእነዚህ መዛግበት «ሚስትህን ኤልዛቤልን» ይላል። ይህች የጳጳሱ ሚስት የጥንቷን ኤልዛቤል መንገድ ተከትላ አምልኮ ጣዖትን እና ዝሙትን እያስፋፋች ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነግሣ ትኖር ነበር። በነገራችን ላይ እስከ ሦስተኛው መክዘ መጨረሻ ድረስ ጳጳሳት ሚስት ያገቡ ነበር። ይህች የጳጳሱ ሚስት ቤተ ክርስቲያኒቱን ተረከበቻት። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳይ በእርሷ በኩል ብቻ ነበር የሚያልፈው። ደግሞም ምግባረ ብልሹ እና ሕይወቷ በዝሙት የተነከረ በመሆኑ ምእመናኑን ለሥነ ምግባር ብልሹነት አጋለጠቻቸው። ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሚመጡ አሕዛብም የርሷን ምግባር በማየት «ክርስትናማ እንዲህ ከሆነ» ማለት ጀመሩ።

ሊቀ ጳጳሱ ይህንን ሁሉ ክፉ ሥራ እያዩ በቸልታ ያልፏት ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ መደፈር እና የምእመናኑ ሕይወት አላሳሰባቸውም። በዚህም ምክንያት «ዝም ብለሃታልና» ተብለው ተገሠጹ። ቅዱስ ኤጲፋንዮስን የመሳሰሉ ሌሎች መተርጉማን ደግሞ በትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትኖር የነበረች፣ ክርስቲያን መስላ ጳጳሱን ያታለለችና ብዙ ክርስቲያኖች ከዝሙት ጋር የተቀላቀለውን አምልኮ ባዕድ ችግር የለውም ብለው እንዲቀበሉት ያደረገች ኃይለኛ ሴት ናት ይላሉ። እንደ ኤጲፋንዮስ ሐተታ ይህች ሴት ሀብታም እና ኃይለኛ፣ በዘመኗም በዘርዋ የምትመካ የልዑላን ቤተሰብ ነበረች። ክርስቲያን ነኝ ብላ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብትጠጋም አምልኮ ባዕዷን እና ዝሙቷን አላቆመችም ነበር፡ ፡ በዚህ ጠባይዋም ለጳጳሱም ሆነ ለብዙ ምእመናን መሰናከያ ሆነች።

የኤልዛቤል ፍጻሜ

እግዚአብሔር ታጋሽ ነው። ለሰው የንስሐ ዕድል ሳይሰጥ አይቀጣም። አሁንም ለዚያች ክፉ ለኤልዛቤል የንስሐ ዕድል ሰጥቷት ነበር። ነገር ግን አልተጠቀመችበትም። በመሆኑም የሚመጣባቸውን ቁጣ ነገራቸው። አስቀድሞ ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን፣ የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ የሥራው ያስረከበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን፣ የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዐመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሰፍት ይሆንባቸዋል» በማለት እንዳስተማረ (ሮሜ 2÷4–8)።

የብሉይ ኪዳኗ ኤልዛቤል ከስሕተቷ ልትመለስ ባለመቻሏ የኢዩ ሠራዊት በክፉ ሞት እንድትሞት፣ ለቀብርም ሬሳዋ እንዳይገኝ አድርጓታል (2ኛ ነገሥ.9÷30–37)። ሰባዎቹ የእርሷ እና የአክዓብ ልጆችም በሰይፍ ተገድለዋል (2ኛ ነገሥ.10÷1–11)። በዚሁ አንፃርም የሐዲሷ ኤልዛቤልም «እርሷም ትቀጣለች ልጆቿም ይቀጣሉ» ተብሏል።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከኤልዛቤል ያድናት።

32. ጤፍ እና እንጀራ

በኢትዮጵያውያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ታላቅ ቦታ ካላቸው ትውፊታውያን ምግቦቻችን መካከል እንጀራ አንዱ ነው፡፡ እንጀራ ለኢትዮጵያውያን ምግባቸው ብቻ ሳይሆን የባሕላቸው፣ የርእዮተ ዓለማቸው፣ የታሪካቸው፣ የማንነታቸው እና የሕይወ ታቸው መገለጫም ነው፡፡ ኑሮውን ለማሳካት ውጣ ውረዱ የከበደው ወገን

እንጀራ በሰማይ እኔ በእግሬ ሆኜ

ኣልደርሰበት ኣልኩኝ ባክኜ ባክኜ- በማለት ኑሮን እንጀራ ብሎ ሲጠራው፡፡ በበጋ እህሉን ጨርሶ ክረምትን በቀጠና ያሳልፍ የነበረው የጥንቱ ገበሬ ደግሞ የችግሩን ስፋት

እኛስ ይህችን ክረምት ወጣናት በመላ

በኩርማን እንጀራ ጎመን ተጠቅልላ- ብሎ ነበር የሚገልጠው፡፡

ሽማግሌዎቻችን ሕይወትን እንጀራ ብለው ይጠሯትና ሕይወቱ የተቃና የተሳካ እን ዲሆን የሚፈልጉትን «እንጀራ ይውጣልህ» ብለው ይመርቁታል፡፡ እኛም «የዕለት እን ጀራ ስጠን» ብለን እንጸልያለን፡፡

ትውፊታዊው እንጀራ ክብ ነው፡፡ መጋገርያውም ምጣድም ሆነ ማቅረቢያው ሞሰብም ክብ ናቸው፡፡ የጥንት ቤቶቻችን፣ ቤተ መንግሥቶቻችን እና አብያተ መቅደሶቻችንም በአብዛኛው ክቦች ናቸው፡፡ «ቤተ ንጉሥ ቅርጽ» ይባላሉ፡፡ ሰፈዱም፣ ድስቱም፣ ሞሰበ ወርቁም፣ ሙዳዩም፣ አውድማው፣ ክምሩ፣ ጎተራው፣ ክብ ናቸው፡፡ ምናልባት የእንጀ ራችን ተጽእኖ ይሆን በእነርሱ ላይ ያረፈው? የሚለው ጥናት የሚፈልግ ይመስለኛል፡፡

ኢትዮጵያውያን ዓለም ክብ ናት ብለው ያምኑ ከነበሩት ቀደምት ሕዝቦች መካከል ይመስሉኛል፡፡ በ13ኛው መክዘ መጻፉን የሚናገረውና በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘው /እኔ ከዐሥር ዓመት በፊት ነበር ያነበብኩት/ መጽሐፈ ማስያስ «ምድር ጋን ትመስላለች» ይላል፡፡ የጋን ቅርጽ ያለውን ሞላላ የክበብ ቅርጽ ላስተዋለ የደራሲው ሃሳብ ከዘመናዊው ሃሳብ ጋር ያለውን አንድነት ይገነዘባል፡፡ ኢትዮጵያውያን ዓለም ክብ ናት ብለው ያምኑ እንደነበር የሚያሳየን ሌላው ሥዕላዊ ማስረጃ ደግሞ የቅድስት ሥላሴን ሥዕል ሲስሉ ሥላሴ ዓለማትን በእጃቸው እንደያዙ ለማመልከት ይጠቀሙ የነበሩት ዓለምን ክብ አድርገው ሥለው በሥላሴ እጅ በማስያዝ ነው፡፡

ጥንታውያኑ ሊቃውንት ሰባቱ ሰማያትን ሲስሉ እንኳን በሰባት ክበቦች እያደረጉ ነበር የሚያመለክቷቸው፡፡ በጥንታውያን ሥዕሎቻችንም የሰዎችን መልክ በክበብ ቅርጽ ተስለው ነው የምናገኛቸው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ነገሥታቱ ራሳቸውን የዓለም ገዥዎች አድርገው በሚቆጥሩበት ዘመን ከነገሥታቱ ቀለበት ላይ ለገዥነታቸው ምልክት የምትቀመጠው ሉል እንኳን ክብ ነበረች፡፡

የእንጀራችን ክብነቱ ከባሕላችን እና አስተሳሰባችን ጋር መስተጋብር አለው፡፡ ኢትዮጵ ያውያን ተሰባስበው በአንድነት የመመገብ ባሕል አላቸው፡፡ እንደ አሁኑ እየተቆረሰ መቅረብ ከመጀመሩ በፊት ደግሞ ሁሉም በየደረጃው እና በየመደቡ ሰብሰብ ብሎ ነው የሚቀርበው፡፡ ለማዕድ የሚቀርቡ ሰዎች ለምግቡ የሚኖራቸው ርቀት ተመሳሳይ

እንዲሆን ይመስለኛል እንጀራችን ክብ የሆነው፡፡ በክብ ነገር ዙርያ የሚቀመጡ ሰዎች የትም አቅጣጫ ላይ ቢቀመጡ ለዚያ ነገር የሚኖራቸው ቀረቤታ እኩል ነውና፡፡ በተለይም የወጡን በመካከል መቀመጥ ስናየው ከየትም አቅጣጫ የሚቆርስ ሰው ለወጡ እኩል ተሳታፊነት ይኖረዋል፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን ክብ የሆነውን እንጀራ ከየትኛውም አቅጣጫ የተቀመጡ ሰዎች እየቆረሱ ሲመገቡት በስተ መጨረሻ መካከለኛው ነጥብ ላይ እጆቻቸው ይገናኛሉ፡፡ ይህም የአንድነትን እና የመቀራረብን ብሎም የመፋቀርን ስሜት ያመጣል፡፡ ጉርሻ ትልቅ ሥፍራ በያዘበት በቀደመው ባሕላችን ውስጥ ክቡ እንጀራ አስፈላጊ ነበር፡፡ የሚጎራረሱት ሰዎች በክቡ እንጀራ ዙርያ ሲቀመጡ ወደየትኛውም ጎራሽ ይደርሳሉ፡፡ ከአንዱ አቅጣጫ ወደሌላው አቅጣጫ ለመጎራረስም ከአራት መዓዝኑ ይልቅ ክቡ አመቺ ነው፡፡
ክብ ነገር ይበልጥ የመቀራረብን እና የመወያየትን ስሜት ስለሚፈጥር በሚል ሃሳብ ነበር የአርሴናሉ አሠልጣኝ አርሴን ቬንገር ጃፓንን ጎብኝተው ከተመለሱ በኋላ አራት መዓዝን ሆነው ተሠርተው የነበሩትን የኤምሬትስ ስታዲዮም የመልበሻ፣ የመታጠቢያ እና የመዝናኛ ቦታዎች እንደገና አስፈርሰው የክበብ ቅርጽ እንዲኖራቸው ያስደረጉት፡፡ ለአመጋገባችን ብቻ ሳይሆን ወጋዊ ለሆነው ባሕላችንም የእንጀራችን ቅርጽ ስምሙ ነው፡፡ ክብ ሠርቶ ወግን እየሰለቁ ለመመገብ እና ምግቡ ካለቀም በኋላ በዚያው ለመቀጠል የሞሰቡም ሆነ የእንጀራው ቅርጽ ማኅበራዊ መስተጋብርን የሚፈጥር ነው፡፡

የኢትዮጵያውያን ሕይወት ከእንጀራ ጋር የተያያዘ መሆኑን ከሚያሳዩን ነገሮች አንዱ የጤፍ አመጣጥ ራሱን የቻለ ትውፊታዊ ታሪክ ያለው መሆኑ ነው፡፡ አንድ ነገር በሕዝብ ሕይወት ውስጥ ቦታ ሲኖረውና ከሕዝቡ ባሕል ጋር የተዋሐደ ሲሆን የየት መጣ አፈ ታሪክ እና ትውፊት ባለቤት ይሆናል፡፡ እንጀራም የዚህ ባለቤት ነው፡፡
በትግርኛ ‘ጣፍ’፣ ‘በኦሮምኛ ‘ጣፊ’ በአማርኛ ‘ጤፍ’ እየተባለ ለሚጠራው ለእንጀራ አባቱ የሆነውን ጤፍ አመጣጥ በተመለከተ ታሪክ ነገሥታችን የመዘገበው አፈ ታሪክ እንዲህ ይላል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመት አካባቢ አንዲት ልጃገረድ ነበ ረች፡፡ ይህች ልጃገረድ አንዲት ሴት ልጅ ከሰው፣ አንድ ዘንዶ ደግሞ ከዘንዶ ወለደች፡፡ ዘንዶውም ሰውን ሁሉ እያሳደደ ይበላ ጀመር፡፡ ሕዝቡም እጎቱን አማላጅ አድርገው ኢጋቦስ ለተባለው ለዚህ ዘንዶ በየጊዜው ሊገብሩለት፣ እርሱም እያሳደደ መብላቱን ሊተው ተዋዋሉና ዕርቀ ሰላም ወረደ፡፡
አራት መቶ ዓመታት ያህል በዚህ ሁኔታ እንደኖሩ ገብጋቦ ወይም አንጋቦ የተባለ ሰው ከሐማሴን መጣ፡፡ የሕዝቡን መከራም ተመለከተ፡፡ ለምን ትገብሩለታላችሁ? ቢላቸውም ያለበለዚያ ይጨርሰናል፡፡ ለመገበር የተገደድነውም ለመግደል ቢያቅተን ነው አሉት፡፡ አንተ ግን ብትገድለው ገጥችን ትሆናለህ ብለው ቃል ገቡለት፡፡ እርሱም አጋቦስ የተባለው ዘንዶ ከሚተኛበት ቦታ ሄዶ ሰባት ዙር አጥር በደረቅ እንጨት አሳጠረ፡፡ ከዚያም በአራት መዓዝን እሳት ለቀቀበት፡፡ አጋቦስ የተባለውም ዘንዶ ሙቀት ተሰምቶት ቢነሣ ዙርያውን በእሳት ተከብቧል፡፡ ዘንዶው ብርቱ ስለነበር እንደምንም እሳቱን እያለፈ እስከ ሰባተኛው አጥር ደርሶ ነበር፡፡

ነገር ግን የእሳቱ ወላፈን እና ጭስ መፈናፈኛ ባሳጣው ጊዜ ገብጋቦ ጋሻ እና ጦር ይዞ ወይንም እንደ አንዳንዶቹ መጥረቢያውን አንሥቶ ጦርነት ገጠመውና መሐል አናቱን ፈለጠው፡፡ ከተፈለጠው የዘንዶ ጭንቅላትም ደም እና እዥ መሬት ላይ ፈሰሰ፡፡ ያም ደም እና እዥ የፈሰሰበት መሬት ዕለቱኑ ዝናም ቢዘንብበት በቦታው ላይ ጤፍ በቀለ፡፡ ዘንዶውንም እጎቱ አልቅሳ ቀበረችው፡፡ የተቀበረበትም ሥፍራ «ተመን ዜውዖ» ተብሎ በአኩሰም ምዕራብ እስከ ዛሬ

አለ ይባላል፡፡ አንጋቦ ግዱርን፣ ግዱር ሰባትሶን፣ ሰባትሶ ተዋስያን፣ ተዋስያ ማኸዳን ወይንም ንግሥት ሳባን ወለዱ ይለናል ታሪክ ነገሥታችን፡፡ የጤፍን ታሪክ ከንግሥተ ሳባ ታሪክ ሲያስ ቀድመው፡፡

ጤፍ በኢትዮጵያውያን አፈ ታሪክ ውስጥ ይህንን ያህል ቦታ ያለው፣ ለአመጣጡ ራሱን የቻለ የየት መጣ ታሪክ የሚተረከለት ባለ መዓርግ ምግብ ነው፡፡ የሚገርመው ግን ጤፍ ተገኘ የሚሉበት መንገድ ቢለያይም ሳይንቲስቶቹም ጤፍ ተገኘ የሚሉት በሰሜን ኢትዮጵያ ከ4000 እስከ 1000 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር «ጎብረ ብእር» በሚለው አንደኛ መጽሐፉ ዓይነቶቹን እስከ 32 የሚያደርስለት ጤፍ፣ ከ1800 እስከ 2100 ሜትር ከፍታ፣ ከ450 እስከ 550 ሚሊ ሜትር በሚደርስ ዝናብ፤ከ10 እስከ 27 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በሚሆን ሙቀት ይበቅላል፡፡

ጤፍ ዛሬ ዛሬ ለብዙ ኢትዮጵያውያን የእህል ውድነት ማሳያ ነው፡፡ እህል ተወደደ ማለት ጤፍ ተወደደ፣ እህል ረከሰ ማለትም ጤፍ ረከሰ ማለት ነውና፡፡ ዐፄ ምኒልክም ዛሬ የአድአ በርጋ ማኛ ጤፍ የሚባለውን የጤፍ ዓይነት ከደቡብ ጎንደር ስማዳ ጋይንት አስመጥተው እንዲበቅል ያስደረጉት ቤተ መንግሥቱም ያለ ጥሩ ጤፍ አልሆን ብሏቸው መሆን አለበት፡፡ በሀገሩ እያለ «ስይት» ጤፍ ይባል የነበረው ነጭ ጤፍ ከስማዳ እየመጣ አላረካቸው ቢል ተመሳሳይ አፈር እና አየር አፈላልገው አድአ ላይ ስለዘሩት ይሄው ዛሬ አድአ በርጋ የነጭ ጤፍ ሀገር ሆነ፤ ስይት የሚለው ስሙ ተቀይሮም ማኛ ተባለ ይሉናል ሟቹ መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ «አማርኛ በአማርኛ መፍቻ መዝገበ ቃላት» በተሰኘ ያልታተመ መጽሐፋቸው፡፡

እንጀራ ፍቅር የሚያስይዝ ምግብ ይመስለኛል፡፡ ከጎረቤታችን ኬንያ እስከ አሜሪካ ባሉ የኢትዮጵያውያን ምግብ ቤቶች የሚመገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች በዋናነት የሚመርጡት እንጀራ መመገብን ነው፡፡ ኬንያ በአንድ ምግብ ቤት የምትሠራ ወጣት «በጣም የሚገር መው ነገር አንድ ጊዜ እንጀራን የቀመሰ የውጭ ሀገር ሰው ከዚያ በኋላ ከምግብ ቤታችን አይጠፋም» ብላኛለች፡፡ ይህንን ነገር ይበልጥ ያየሁት ኢየሩሳሌም ነው፡፡ የትንሣኤን በዓል ለማክበር በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን ገዳም የሚሰባሰቡ ኢትዮጵያውያን ከዚሁ ተዘጋጅቶ የሚሄድ የትንሣኤ ድግስ አላቸው፡፡ በፋሲካ ዋዜማ እኩለ ሌሊት፣ ቅዳሴው ካለቀ በኋላ በገዳሙ ግቢ ውስጥ ራት ይበላል፡፡ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ፍልስጥኤማውያን በጉጉት ከሚጠ ብቋቸው ቀናት አንዱ ኢትዮጵያውያን ትንሣኤን የሚያከብሩባት ይህቺ ሌሊት ናት፡፡
ፍልስጥኤማውያኑ ወደ ዴር ሡልጣን ገዳም በዚያች ሌሊት የሚመጡት ትንሣኤን ከኛ ጋር ለማክበር አይደለም፡፡ ለምን እንደሚመጡ ምክንያቱን የምታውቁት ከዴር ሡልጣን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ካለቀ በኋላ ዘግይታችሁ ከወጣችሁ ነው፡፡ እንጀራው እና ወጡ አልቆ ይጠብቃችኋል፡፡ ምነው? ስትሉ መልሱ አንድ ነው፡፡ በዚያች ሌሊት በጉጉት ሲጠባበቁ ያደሩት ፍልስጥኤማውያን ዓመት ሙሉ የጓጉለትን እንጀራ ለማግኘት ተሻም ተው ጨርሰውታል፡፡ እንጀራ እንኳን እኛን ምዕራባውያንን እና ፍልስጥኤማውያንን እንኳን በፍቅር ጥሏቸዋል፡፡

አይ የእንጀራ ነገር፡፡

33. በሰይጣን እጅ የወደቀ ቅርስ

ከአርባ ዓመት በፊት በተመሠረተው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ገብታችሁ ወደ ዋናው ሕንፃ ስትዘልቁ፣ በስተ ግራ በኩል አንድ ታሪካዊ፣ ግን ደግሞ ብዙም ተመልካች የሌለው ቅርስ ታያላችሁ፡፡ ሦስት ሥዕሎች ጎን ለጎን በግድግዳው ላይ ተለጥፈዋል፡፡

ሥዕሎቹን የሳሏቸው ታዋቂው ሰዓሊ ሜትር አርቲስት ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ መሆናቸውን በሥዕሉ ላይ ባሠፈሩት ፊርማ ማወቅ ይቻላል፡፡ የተሳሉት ደግሞ የዛሬ አርባ ዓመት በ1962 ዓም ነው፡፡

የመጀመርያው ሥዕል ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሕመምተኞችን ሲጎበኙ የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ሥዕል ደግሞ ሆስፒታሉ ሲከፈት፣ ከሆስፒታሉ በላይ ከንፉ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነ መልአክ፤ በመካከል ላይም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የሆስፒታሉን መከፈት ሲያበሥሩ፤ ሕዝቡም ለሕክምና ወደ ሆስፒታሉ ሲሄድ የሚያሳይ ነው፡፡

ሦስተኛው ሥዕል ግን በቦታው የለም፡፡

አሳዛኙ ነገርም የሚጀምረው ከዚህ ነው፡፡

ሥዕሉን የሚያውቁት የሆስፒታሉ ባለሞያዎች እንደነገሩኝ ከሆነ ሦስተኛው ሥዕል ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አረጋውያንን ሲያለብሱ የሚያሳይ ሥዕል ነበረ፡፡ ይህ ሥዕል ንጉሠ ነገሥቱን አምርሮ በሚጠላው በደርግ ዘመን እንኳን ከቦታው ማንም አልነካውም ነበር፡፡ ከስድስት ወር በፊት ግን ማንም ሳያውቅ ሥዕሉ በድንገት ተሠወረ፡፡

የት ገባ? ተብሎ ተፈለገ፣ተፈለገ፣ ሊገኝ ግን አልቻለም፡፡ ምናልባት የጥንት ቅርስ ዘራፊዎች ሰርቀውት ይሆናል የሚል ጥርጣሬ በሆስፒታሉ ኃላፊዎች ዘንድ አደረ፡፡ ነገር ግን የተፈራው ነገር አልነበረም፡፡

ሥዕሉ በሆስፒታሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ተጨመዳድዶ ወድቆ ተገኘ፡፡ የሆስፒታሉን ኃላፊዎች የገረማቸው ሁለት ነገር ነው፡፡ መጀመርያ ይህንን አድራጎት የፈጸመው ሰው ለብዙ ሰዓታት ያንን ሥዕል ሲፍቅ እንዴት አንድ ሰው እንኳን አላየውም? ሁለተኛ ደግሞ እንዴት ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሊጥለው ቻለ? እነዚህን ነገሮች ዛሬ ድረስም መመለስ አልተቻለም፡፡

እኔ ግን በሰይጣን እጅ የወደቀ ቅርስ ብየዋለሁ፡፡ ይህ ሰው ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ይጠላቸው ይሆናል፤ በርሳቸው ዘመንም ግፍ ተፈጽሞበት ይሆናል፡፡ ይህንን ስሜቱን ግን ቅርስ በማጥፋት አይደለም መበቀል የሚችለው፡፡ ክፉ ተግባር ዳግም እንዳይፈጸም በማድረግ እንጂ፡፡

ቅርስ የምንወዳቸውን ሰዎች ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡ ክፉ ታሪክም ቢሆን ቅርስ አለው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የግራኝን ካባ ያስቀመጠችው ስለምትወድደው አይደለም፡፡ ታሪክ ስለሆነ እንጂ፡፡

እንደኔ እንደኔ የሌኒን ሐውልትም መፍረስ አልነበረበትም፡፡ ልጆቻችንን ዓላምን ስለበጠበጠው ሌኒን ስለሚባል ሰው በተረት ከምንነግራቸው ሐውልቱን እያሳየን ብንነግራቸው ይበልጥ ይገባቸው ነበር፡፡

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የነበረውን የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥዕል የገነጠለውን ሰው ሰይጣናዊ ሃሳብ የምንቃወመው እና ለሌሎች መሰሎቹም ትምህርት የምንሰጠው ያንን ሥዕል መልሰን በቦታው ከሰቀልነው ብቻ ነው።።

የሆስፒታሉ ምንጮች እንደነገሩኝ ከሆነ ሜዲካል ዳይሬክተሩ ዶክተር መስፍን ሥዕሉን ለማስጠገን ሎሬት አፈወርቅ ተክሌን አነጋግረዋቸው ነበር።። ነገር ግን ሊጠገን የሚችለው በብሔራዊ ሙዝየም ብቻ መሆኑን ነግረዋቸዋል።።

ሙያው ወይንም ገንዘቡ ያላችሁ፤ የቅርስ ተቆርቋሪዎች እባካችሁ ይህንን በሰይጣን እጅ የወደቀ ቅርስ እንታደገው።።

34. በአንድ ሱቅ ታዛ ሥር

ሲ ኤም ሲ፣ ከሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት፣መንገዱን ተሻገርኩና፣ ቆምኩ።። ዓላማየ ሰው መጠበቅ ነበርና ሲዘገይብኝ ጊዜ ጋዜጣ ገዛሁና ከፀሐዩ ለማምለጥ ወደ አንድ ሱቅ ታዛ ተጠጋሁ።።

በሱቁ ውስጥ አንዲት ሴት እና አንድ ወንድ ቆመዋል።። ከውጭ ደግሞ አንድ ሌላ ሰው የሱቁን መስኮት ተደግፎ ወደ ውስጥ ጫቱን እየቃመ ያወራቸዋል።። ከዚያ ደግሞ አንድ ደንበኛቸው መጣ።።

«አንተ ፔጅ ከማድረግ ውጭ አታውቅም እንዴ? ምናለ አንዳንድ ቀን እንኳን ብትደውል» አለው በሱቁ ውስጥ ያለው ሰው በወዳጅነት ስሜት።።

«ካርድ ስላልሞላሁኮ ነው» አለው ትከሻውን በመስኮቱ ዘልቆ በትከሻው እየገጨ።።

«ያደላቸው መንፈስ ይሞላሉ፤ አንተ የሃያ አምስት ብር ካርድ መሙላት ያቅትሃል?» አለችው በሱቁ ውስጥ ያለችው ልጅ።። ሁሉም ሳቁ።።

«ሲያቀብጠኝ ትናንት ኳስ አያለሁ ብዬ ገንዘቤን ጨረስኩ» አለ የመስኮቱን መደገፊያ እየደበደበ።።

«ቤትህ አታይም ምን ሌላ ቦታ ወሰደህ?» አለችው ሻጯ

«የተመታ ኳስ እናቀብላለን ትላላችሁ አሉ።። »

«ማን»

«እዚያ በትልቅ ስክሪን የምታዩት ናችኋ።። ኳስ ተመትቶ ፊት ለፊት ሲመጣ ወደ እናንተ የመጣ መስሏችሁ ልታቀብሉ ትነሣላችሁ አሉ።።»

«የዓለም ዋንጫ አይደለምኮ ሰበታ ወርጄ ነው» አለ እንግዳው ከሚወርድበት ትችት ለመራቅ ብሎ።።

ሰበታ ሜዳ ላይ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ደደቢት መጫወታቸውንና በጨዋታውም ችግር መፈጠሩን ሰምቼ ነበር፡፡ ይህ ሰው የሚያወራው ይህንን መሆን አለበት፡፡

«ዳኛ በቴስታ ሲመታ ለማየት ነው የሄድከው» አለና የሱቁን መደገፊያ ተደግፎ ጫት የሚያመነዥከው ሰው ሳቀበት፡፡

«ኳስ በቴስታ መትተው ጎል ማግባት ሲያቅታቸው ዳኛ በቴስታ መማታት ጀመሩ፡፡ እግር ኳስ እና ቦክስ ተቀላቅሎባቸዋል»

«እንኳንም በዓለም ዋንጫ አልተሳተፍን» አለች ሴትዮዋ፡፡

«እንዴት?» አላት ሱቁ ውስጥ አብሯት የቆመው ሻጭ፡፡

«ዳኛውን ሁሉ በቴስታ እየመቱ ሀገሪቱን ጭራሽ ከእግር ኳስ ያስባርሯት ነበራ»

«እኔኮ የማይገባኝ ሰው በዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ በማስረዳት፣በመከራከር እና በሕግ መሥመር በመሄድ ሃሳቡን ያራምዳል እንጂ እንዴት በኃይል ያምናል፡፡» በሱቁ ውስጥ ያለው ሰው ነበር ይህንን የተናገረው፡፡

እንግዳው ሰውዬ እጆቹን አወናጨፈና «ባካችሁ እርስሱን ተውት የኢትዮጵያ ኳስ እንደሆነ አያልፍለትም፡፡ ምን እንደ ተባለ ታውቃላችሁ፡፡»
«ደግሞ ምን ተባለ? አታመጣው የለህ» አለ ጫቱን የሚቅመው ሰው፡፡

«ኢትዮጵያ፣ኬንያ፣ዑጋንዳ እና ቻይና ለዓለም ዋንጫ የሚበቁበትን ዘመን ለመጠየቅ ወደ አንድ ጠቢብ ዘንድ ሄዱ አሉ፡፡ ኬንያ ጠየቀች፡፡ ከሃያ ዓመት በኋላ የባለች፡፡ ዑጋንዳ ጠየቀች፡፡ ከአሥር ዓመት በኋላ ተባለች፡፡ ቻይና ጠየቀች ከአምስ ዓመት በኋላ ተባለች፡፡ በመጨረሻ ኢትዮጵያ ጠየቀች፡፡ ያን ጊዜ ጠቢቡ መልስ መስጠቱን አቆመና አለቀሰ ይባላል፡፡

ያን ጊዜ ኢትዮጵያ ገረማትና «ለምን አለቀሱ» አለችው ጠቢቡን «የተጨዋቾቻችሁ ጠባይ እና የፌዴሬሽናችሁ አሠራር ዘመኑን ለማየት ስለ ጋረደኝ ነው» አለ ይባላል፡፡

«አታመጣው የለህ፤ ለመሆኑ ያ ነገር ዋጋው ወረደ ወይስ እንደ ወጣ ነው» አለው ወንዱ ባለ ሱቅ፡፡

«አንተ ደግሞ እዚህ ሀገር ላይ የሚወርድ ባለ ሥልጣን እንጂ የሚወርድ ዋጋ አይተህ ታውቃለህ? ይልቅስ አሁኑኑ ብትገዛ ይሻልሃል» አለው እየሳቀ፡፡ «አንዱ ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? መኪና ልገዛ ሄጄ አሁንኮ ገበያው ቀንሷልና ትንሽ ቀንስልኝ ስለው እዚህ ሀገር የሚቀንስ ነገር የለም፤ የሚቀንሰው ፍቅር ብቻ ነው አለኝ እውነቱን ነው፡፡

«ያ ጓደኛህ ሊሄድ ነው አሉ?»
«የት?»

«አሜሪካ ነዋ»

«አልሰማሁም፤ ማን ነገረህ?»

«ራሱ ነው የነገረኝ»

«እርሱንኮ ስትሰማው ቫቱን እየቀነስክ መሆን አለበት»

«እንዴት?»

«ትንሽ ይሰጣላ፤ በቫት ነው ያለ ቫት ብለህ ማጣራት አለብህ»

/ይህ ነገር እኔንም ገረመኝ:: እውነትምኮ አንዳንድ ነገሮችን ከቫት ጋር እና ያለ ቫት መሆናቸውን ማጣራት ያስፈልጋል:: አንዳንዱኮ 15 % እየጨመሩ ሊያወሩ ይችላሉ:: እናም ዋጋውን ከቫቱ ለይቶ መሰማት ያስፈልጋል/

«እውነትህን ነው፤ እርሱኮ ሁል ጊዜ ማማረር ነው የሚወድደው፤ እንደ እርሱኮ ኢትዮጵያ ሲያል ናት:: ጨለምተኛ ነው» ጫት ቃሚው ነው ይህንን የሚለው::

«እዚህ ሀገር ሰው ሆኖ ከመኖር አሜሪካ ሄዶ ውሻ ሆኖ መኖር ይሻላል ካለኝ ወዲህ ጠልቼዋለሁ::» አለች ልጂቱ::

«ተይው ባክሽ እዚህ በየሜዳው መጸዳዳት ለምዶ፣ አሜሪካ ገብቶ እንደ ቡችላ በፖፖ ተቀመጥ ሲባል ምን ሊል ነው?» በእንግዳው ንግግር ሁሉም ሳቁ::

«እኔኮ የማይገባኝ ነገር እዚያ ሀገር ደርሰው የሚመጡት አትምጡ ይቅርባችሁ ማለት ነው የሚወዱት:: ታድያ እነርሱ ለምን ጠቅልለው አይመጡም:: እኛን አትምጡ ብለው እነርሱ ይሄዳሉ:: »

«እሱና ይኼ ተቃራኒ ናቸው» አለች ልጂቱ በግራ እጇ ጫት ቃሚውን እየጠቆመች:: «ይሄ ለራሱ ያለ ኢትዮጵያ አገር የለም:: ገነት ያለችው ኢትዮጵያ ነው:: ሰው ለምን ሀገሩን ለቅቆ ይሄዳል፤ ምናምን ይላል:: ያኛው አገር አያሳየኝ ይላል:: እኔስ ጠይም ሰው አማረኝ»

«እኔ አለሁልሽ አይደል እንዴ?» አላት ሱቁ ውስጥ ያለው ጎልማሳ::

«እኔ መች የሰው ጠይም ፈለግኩ፤ የሃሳብ ጠይም እንጂ»

«ደግሞ የሃሳብ ምን ጠይም አለው» አለ ጫት ቃሚው ሰው ጢሙን እያፍተለተለ::

«አለው እንጂ:: ጥቁርም ያልሆነ፣ ነጭም ያልሆነ ሃሳብማ አለ:: የጥቁሩንም ንጣት፣ የነጩንም ጥቁረት የሚያሳይ ጠይም ሃሳብማ አለ:: ስለ ጥቁሩ ጥቁረት፤ ስለ ነጩ ንጣት ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ገጽታቸውን የሚያሳይ ጽንፈኛ ያልሆነ ጠይም ሃሳብማ አለ::»

«አፌ ቁርጥ ይበልልሽ የኔ ፈላስፋ፤ በስሕተት ነው አንቺ ሸቀጥ ሻጭ የሆንሺው፤ መጽሐፍ ሻጭ ነበር መሆን የነበረብሽ» አለ ባለ ጫቱ እየሳቀ::

/ ጠይም ሰው አማረኝ? አባባሏን ወደድኩላት:: ጽንፍ በበዛበት ቦታ ጠይም ያምራል:: እኔም ብዙ ቦታ ወይ ነጭ አለያም ጥቁር ነው የሚያጋጥመኝ፤ መሐል ቦታ ቆመው ሁለቱንም አይተው ሊገልጡ የሚችሉ ጠይሞች ያስፈልጉናል::/

በዚህ መሐል አንድ የሰማይ ስባሪ የሚያህል ሰው ወደ ሱቁ ታዛ ገባ፡፡ ከዚያም ሲጋራ ጠየቀ፡፡ ሰውየው መስኮቱን ሲደገፍ ሁሉም መስኮቱን ለቀቁለት፡፡ ሰውዬውም ብቻውን መስኮቱን ሞላው፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ በእጁ ዳቦ ይገምጣል፡፡

ሰውዬው ሲጋራውን ገዝቶ እንደሄደ ጫት ቃሚው ሰውዬ «ይሄ ሰው ግን የዘመዶቹን ሁሉ ኪሎ በአደራ አስቀምጦ መሆን አለበት» አለ ሰውዬው የሄደበትን መንገድ በጎሪጥ እያየ፡፡

«ባክህ ሲርበው ከራሱ ሥጋ እየበላ ነው፡፡»

«በምግብ እህል ራስን መቻል ማለት ይህሄ ነዋ» ዘሁንም ተሳሳቁ፡፡

እንደ ሰውዬው ሲጋራ ሊገዛ የፈለገ ደንበኛ ወፍራሙ ሰውዬ እልፍ ከማለቱ መጣ፡፡

«ሳቢ እስኪ» አላት ልጅቱን፡፡

«እዚህ ቤት ዛሬ ተቃራኒ ብቻ ነው እንዴ የሚመጣው» አለች ልጅቱ እየተንፈ ቀፈቀች፡፡

«እንዴት ማን መጣ ደግሞ» ሲጋራ ገዥው ጠየቀ፡፡

«ቅድም ለምድር ለሰማይ የከበደ ሰው መጥቶ ሱቁን ዘጋው፤ አሁን ደግሞ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ሽቦ የመሰለ ሰው መጥቶ ልብስ ልናሰጣበት ነበር፡፡»

«ያ ሰውዬ የሆነውን ታውቂያለሽ?»

«ምን ሆነ ደግሞ? ቀጭኔዎች ቀንታችሁበት ነው?» ልጅቱ መለሰችለት፡፡
«ላይተር ስጭኝና እነግርሻለሁ» ላይተሩን አውጥታ ለኮሰችለት፡፡ እኔም ጢሱ አላስቀምጠኝ ሲል ፈቀቅ አልኩ፡፡
«አንድ ጊዜ» አለ በሲጋራው ጢስ ክብ እየሠራ፡፡ «ሰውዬው በሬ አርዶ ቅርጫ ሊያከፋፍል ይነሣል፡፡ በሬውን ከካራ ገዝቶ በሌሊት ለማረድ አራጅ ይነጋገራል፡፡ ሌሊት አስራ አንድ ሰዓት ከአራጁ ጋር ይነሣና ወደ ቅርጫ ቦታው ይሄዳል፡፡ እዚያ እንደ ደደረሰ ለካስ አራጁ ሌሊት ሲቀመቅም አድሮ አንጎበሩ አልለቀቀውም፡፡ በሬውን ለመጣል አናቱ አካባቢ በትክክል ሳይወጋው ይቀርና በሬው መልሶ ይነሣል፡፡ በዚህ ጊዜ ይሄ ወፍራም ሰውዬ ተዋረድኩ ይልና የበሬውን ሁለት ቀንዶች ጥርቅም አድርጎ ይይዛል፡፡ በሁለት እጁ ቀንዱን ጥርቅም አድርጎ እንደያዘ እንደምንም ታግሎ በሬውን ይጥለዋል፡፡ በሬው መሬት እንደ ወደቀ ወፍራሙ ሰውዬ እየጮኸ «እረደው ቶሎ እረደው» ይለዋል አራጁን፡፡ አራጁ ግን ቢላዋውን እያፋጨ ዝም ብሎ በሬውን ይዞረዋል፡፡ ወፍራሙ ሰውዬ «ኧረ እባክህ እረደው ደከመኝ» ይለዋል አንጎበሩ ያልለቀቀው አራጅ በሬውን እየዞረ ቢላዋውን ያፋጫል፡፡

በዚህ መካከል አንድ ጓደኛው ይደርሳል፡፡ በሬ ከሥር ወፍራሙ ሰውዬ ከላይ አንደሆኑ፡፡ የጓደኛውን መምጣት ሲያይ ወፍራሙ ሰውዬ «ኧረ እባክህ እረደው በለው» ይለዋል፡፡ ጓደኛውም አራጁን «እረደው እንጂ ለምን

ትዞረዋለህ?» ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ አራጁም «እኔኮ ከሁለቱ በሬው የትኛው እንደሆነ መለየት አቅቶኝ ነው» አለው ይባላል፡፡ »

«ይኼ አንድ ሲጋራ ያሸልማል» ብሎ ጫት ቃሚው እየሳቀ ጋበዘው፡፡

እኔም የቀጠርኩት ሰው መጣና ቀጣዩን ሳልሰማ ጥያቸው ሄድኩ፡፡

35. **ማረፊያ**

ሰሞኑን ከዓለም ዋንጫው ጋር በተያያዘ የአንድ የጀርመን ዓሣ ስም ተደጋግሞ ይነሣ ነበር፡፡ ይህ ዓሣ (ኦክቶፐስ) በምግብ የተሞሉ ሳጥኖች የተወዳዳሪ አገሮችን ባንዴራ ይዘው ይሰጡትና አንዱን ይከፍታል፡፡ የከፈተው ሳጥን ላይ ያለውን ባንዴራ የሚያውለበልበውም ሀገር ያሸንፋል፡፡ የፈረንጅ ጥንቆላ ማለት ነው፡፡

ይህንን መሠረት አድርጎ የተቀለደውን የአዲስ አበባ ቀልድ ልንገራችሁ፡፡

እንደ ጀርመኑ ዓሣ አሸናፊውን ሊናገር ይችላል የተባለ የኢትዮጵያ ውሻ የስፔን እና የሆላንድ ባንዴራ የታሠረባቸው ሁለት ሙዳ ሥጋዎች ቀረቡለት፡፡ እንደ አቅራቢዎቹ ግምት የበላው ሥጋ ላይ ያለውን ባንዴራ የሚያውለበልበው ሀገር ያሸንፋል ለማለት ነው፡፡ ታድያ የሀገሬ ውሻ ምኑን ሞኝ ነው፡፡ የስፔንንም የሆላንድንም ባንዴራ የታሠረባቸውን ሙዳ ሥጋዎች ጥርቅም አድርጎ በላቸው አሉ፡፡

በዚህም የተነሣ ከማንኛውም መዝናናት በፊት ሆድ መሙላት አለበት ተባለ አሉ፡፡

36. **ስላላደረግከልኝ ነገር አመሰግንሃለሁ**

እነሆ ታክሲ ይገፍ ከሲ ኤም ሲ ወደ መገናኛ ለመሄድ መንገድ ዳር ቆሜ ነው፡፡ እነዳጋጣሚ አንዲት ዲ ኤክስ መኪና ከፊቴ ቆመች፡፡ የምታሽከረክረው ልጅ በእጇ እንድገባ ጠቆመችኝ፡፡ «ስታስተምር ስለማውቅህ ነው» አለችኝ፡፡ አመሰግኜ ጋቢና ተቀመጥኩ፡፡ የተቀመጥኩበት ወንበር ላይ በመስተዋት የተለበጠ ጥቅስ ነበረበት፡፡ መስተዋቱ የተያያዘበት ፍሬሙ በአበባ ያጌጠ ነው፡፡ ምናልባት ለሰው ልትሰጠው ያዘጋጀችው መሆን አለበት፡፡ እንዳጋጣሚ ጥቅሱን አንሥቼ ከኋላ ወንበር ላይ ሳደርገው «ስላላደረግከልኝ ነገር ሁሉ አመሰግንሃለሁ» ይላል፡፡

የጻፈው ሰው ስሕተት ሠርቷል፡፡ መሆን የነበረበት «ስላደረግከልኝ ሁሉ» ነው፡፡ በስሕተት አንድ ተጨማሪ «ላ» አስገብቶበታል፡፡ ልንገራት ወይስ ልተወው እያልኩ አመነታሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን ስሕተት ላታስተውለው ትችላለች ብዬ ስላሰብኩ መንገሩን መረጥኩ፡፡ «ጥቅሱን የጻፈልሽ ሰው ሳይሳሳት አይቀርም» አልኳት ቀስ ብዬ፡፡ «እውነትክን ነው» አለችና አንድ እጇን ወደ ኋላ ልካ ጥቅሱን ወደ አምጥታ አየችው፡፡ «የቱ ጋ ነው ባክህ የተሳሳተው» አለችኝ፡፡

«ስላደረግክልኝ ለማለት ፈልጎ ስላደረግክልኝ ብሎታል» አልኳት በጣቴ ፊደሉን እያሳየሁ፡፡ «እርሱን ነው እንዴ፤ አይ ፈልጌው ነው» አለች ጥቀሱን ወደ ቦታው እየመለሰች፡፡

«ስላላደረግክልኝ የሚለውን ነው የፈለግሽው?»
«አዎ፤ አይባልም እንዴ»
«ሰምቼ አላውቅም»
«ለሌላ ሰው ላይሠራ ይችላል፡፡ ለኔ ግን ይሠራል»
«እንደዚህ የሚል ጥቅስ ግን ያለ አይመስለኝም»
«ይህ ከሕይወት መጽሐፍ የተገኘ ጥቅስ ነው» አለችና ፈገግ አለች፡፡
«የቱ ነው ደግሞ የሕይወት መጽሐፍ?»
«እያንዳንዱ ሰው የየራሱ የሕይወት መጽሐፍ አለው፡፡ በዚያ መጽሐፍም በሕይወቱ ያገኛቸው ነገሮች ተመዝግበዋል፡፡ በዚያ መጽሐፍ በሕይወት ተፈትነው የነጠሩ ምርጥ ምርጥ ጥቅሶች ይገኛሉ»
«ፈላስፋ ነገር ሳትሆኚ አትቀሪም»
«አንተም የሕይወት መጽሐፍህን ካነበብከው፤ ፈላስፋ መሆንህ አይቀርም፡፡»
«ግን ለምንድን ነው ስላላደረግክልኝ ሁሉ አመሰግንሃለሁ ያልሽው»
አየህ እያንዳንዱ ጥቅስ ከጀርባው የሚጠቀስ ታሪክ አለው፡፡ ታኩን ካላወቅከው ጥቅሱ በደንብ አይገባህም»
«እስኪ በደንብ እንዲገባኝ ታሪኩን ንገሪኝ»
«እንዲህ በቀላሉ ያልቃል ብለህ ነው»
«አንድ ቦታ አቁመን ለምን አትነግሪኝም»
«ይህንን ያህል ያስፈልግሃል?»
«በጣም አጓጓኝ፤ ስላላደረግክልኝ ሁሉ አመሰግንሃለሁ የሚል ሰምቼ አላውቅማ»
መገናኛ ስንደርስ ወደ አንድ ጥግ አቆመች፡፡ እናም እንዲህ ነገረችኝ፡፡

እንደ እኔ ውጭ ሀገር መሄድ የሚወድ ሰው አልነበረም፡፡ ከቻልኩ እንደ ሰው ቪዛ አግኚቼ ካልቻልኩም እንደ በርበሬ እና ሽሮ ተፈጭቼ አሜሪካ መሄድ አለብኝ ብዬ ቁርጥ ሃሳብ ነበረኝ፡፡ ያውም ደግሞ አሜሪካ ገብቼ ዜጋ መሆን ነው የምፈልገው፡፡እዚህ ሀገር መማር፣ መሥራት፣ መኖር ፈጽሞ አልቻልኩም፡፡ ሕልሜም እውኔም አሜሪካ ነው፡፡ ስለ ጤንነቴ ከሚጠይቀኝ ሰው ይልቅ ስለ አሜሪካ የሚነግረኝ ሰው ነበር የምወ ድደው፡፡ ያ በጣም የሚወድደኝ እና የምወድደው አጎቴን እንኳን አስቀይሜዋለሁ፡፡ እርሱ ዜግነቱን የሚለውጥ ሰው ደመኛው ነው፡፡ ከወንድሞቼ እና እኅቶቼ ጋር ምነው ምንስ ቢሆን እንዴት ዜግነት ይቀየራል ?እያለ ይጣላል፡፡ እኔ ደግሞ ካልቀየርኩ ሞቼ እገኛለሁ ብዬ ተነሣሁ፡፡

ቤተ ሰቦቼ ቢሉኝ ቢሠሩኝ ይህንን ሕልም መተው ስላልቻልኩ አለ በሚባለው መንገድ ሁሉ እኔን አሜሪካ ለመላክ ሞከሩ፡፡ ከአጎቴ በቀር፡፡ አንድን ነገር ሙጭጭ ስትልበት ጥምም ነው የሚልብህ፡፡ ለጓደኞቼ የተሳካው መንገድ ሁሉ ለእኔ ጠመመ፡፡ ሌላው ቀርቶ ኬንያ ሄጄ ፕሮሰስ ጥበቃ ሦስት ዓመት ተቀመጥኩ፡፡ ጠብ የሚል ነገር አልነበረም፡፡

የኬንያው አልሳካ ሲል ዑጋንዳ ገባሁ፡፡ እዚያ እንዲያውም የተሻለ ነገር ማየት ችዬ ነበር፡፡ አንድ ፕሮሰስ ገዝቼ አንድ ስድስት ወር ጠበቅኩና ተሳካ፡፡ ለኢንተርቪው ተጠርቼ ስገባ ሰውነቴ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ የማውቀውን ነገር እንኳን መናገር አቃተኝ፡፡ የኔ መውደቅ ሳያንስ ባለ ፕሮሰሱንም አዘጋሁበት፡፡

እንደገና አገሬ ገብቼ ሌላ ነገር ጀመርኩ፡፡ ዲቪ ገዝቻለሁ፤ ፎርጂድ ፓስፖርት ለማሠራት ሞክሬያለሁ፤ ለባዛር እና ለኤግዚቢሽን በሚል ቪዛ ለማሠራት ገንዘብ ከሰከሻለሁ፡፡ ብቻ ተወው፤ ጓደኞቼ «ዋልያ» እያሉ ይቀልዱብኛል፡፡ እንደ ዋልያ ከሀገሬ ውጭ እንድኖር አልተፈቀደልኝማ፡፡ ያልተሳልኩት ታቦት፤ ያልሄድኩበት ጠበል፣ ያላማከርኩት ባሕታዊ፣ ያልከፈልኩበት ኤምባሲ የለም፡፡ ሁሉም ጭጭ ምጭጭ አሉ፡፡

ሲጨንቀኝ ከእግዚአብሔር ጋር ተጣላሁ፡፡ ባይኖር ነው እንጂ ቢኖርማ እንዴት ይህንን ሁሉ ጸሎት፤ ይህንን ሁሉ ሥዕለት አይሰማም፤ ቢያዳላ ነው እንጂ ባያዳላማ ለሌሎች ያደረገውን ለእኔ ማድረግ እንዴት ያቅተዋል ብዬ ተቀየምኩት፡፡

ቀና ብዬ ባየው ሰማዩ ቀለለኝ
አላህን ሠፈራ ወሰዱት መሰለኝ- ያለውን ወሎዬ ታስታውሰዋለህ፡፡ በ1977 ከድርቁ በኋላ ነበር እንዲህ ያለው፡፡ እኔም እንዲያ ነው የሆነብኝ፡፡

አንዲ እንደኔ የጨነቃትም

አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል - ብላለች አሉ፡፡

በመጨረሻ በኑሮዬ ተስፋ ቆረጥኩና ከማይሆኑ ልጆች ጋር ገጠምኩ፡፡ የሕይወቴ መመርያ መቃም፣መጠጣት፣ መጨፈር ሆነ፡፡ ተያይዘን ከከተማ እንወጣለን፡፡ እንቅማለን እንጠጣለን፡፡ ከዚያም ሊደረግ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን፡፡ ላይፍ እንቀጫለን፡፡

እናቴ አዘነችብኝ፡፡ ውጭ ያሉት ወንድሞቼ እና እኅቶቼም እየደወሉ ሊመክሩኝ ሞከሩ፡፡ ማን ሊሰማቸው፡፡ አኅቴማ ዘወትር ኅዘን ብቻ ሆነ ሥራው፡፡ ዘመዶቼ ሁሉ ለምክር ተሰለፉ፡፡ እነርሱ ሊመክሩኝ ባሰቡ ቁጥር እኔ ከእነርሱ ራቅሁ፡፡ በኋላ ላይ አኅቴን «እንደዚያ ስሆን እያየሽኝ ለምን ነበር እንደ ሌሎቹ ያልመከርከኝ» ብዬ ጠይቄው ነበር፡፡ ያለኝን አልረሳውም፡፡ «ሰው በኑሮው ተስፋ በቆረጠበት ሰዓት፣ ሰው ጥፋትን እያወቀ በሚሠራበት ሰዓት፣ ጸሎት እንጂ ምክር አይመልሰውም» ነበር ያለኝ፡፡

አንድ ሁለት ዓመት በዚህ ሁኔታ ከቀጠልኩ በኋላ ደግሞ እርሱም ሰለቸኝ፡፡ ጓደኞቼን ሁሉ ዘጋኋቸው፡፡ በሬን ዘግቼ ቤቴ መዋል ጀመርኩ፡፡ አሁን እናቴ ይበልጥ ጨነቃት፡፡ ልጇን ምን አስነኩብኝ ማለት ጀመረች፡፡ ውጭ መውጣት አስጠላኝ፡፡ ሙዚቃ እና ፊልም ከፍቼ ቤት ውስጥ መዋል፣ ማደር ጀመርኩ፡፡

አንድ ቀን ምን እንደነካኝ አላውቅም በድንገት ተነሥቼ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ሄድኩ። ተሳለምኩና እዚያው ቁጭ አልኩ። የተቀመጥኩት ከዋናው የግቢው በር አጠገብ ነበር። አንድ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰማኛል። ድምፁን ወደምሰማበት ዘወር ስል አንድ ልጅ በትንሽ ቴፕ ነበር የሚያሰማው። ሄጄ ጠየቅኩትና በአሥር ብር ሸጠልኝ። የሕይወቴ ለውጥ ያኔ ተጀመረ።

ቤቴ ገብቼ እየደጋገምኩ አዳመጥኩት። ውስጤን ነበር የነካው። በነጋታው ወደ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ሄጄ ሌሎች ሁለት ካሴቶች ከልጁ ገዛሁ። ልጁ ሌላ ካሴት ከፈለግሽ ብሎ አንድ ሱቅ ጠቆመኝ። እዚያ ሄጄ ሌሎች ሁለት ጨመርኩ።

በትምህርቱ ውስጥ ራሴን ነበር የማየው። ውስጤን ነበር የምመረምረው። መንገዴን ቁልጭ አድርጎ አሳየኝ። እናም ከፈጣሪ ጋር መሟገቴን ተውኩ። ውጭ ስለመሄድ ማለሜን ተውኩ። ለብዙ ሰዓታት ከራሴ ጋር ከተሟገትኩ በኋላ ከስድስት ዓመት በፊት ወደ ተውኩት ትምህርቴ ተመለስኩ። ያኔ ቢዝነስ አስተዳደር የሚባል ትምህርት ጀምሬ አንድ ሴሚስተር እንደተማርኩ ነበር ውጭ ውጭ የሚል ዛር ለክፎኝ ያቋረጥኩት።

እናቴ ማመን አልቻለችም። ቤተ ሰቦቼ ሁሉ ተገረሙ፣ ግን ደግሞ ይመለስባታል ብለው ፈርተው የምላቸውን ከመፈጸም ውጭ ሊናገሩኝ አልደፈሩም።

ላሳጥርለህና ትምህርቴን ላጠናቅቅ አንድ ወር ያህል ሲቀረኝ አጎቴ አስጠራኝ። ቅድም እንዳልኩህ በጣም ነበር የሚወደኝ። እንዲያውም እናቴ ቤት ከኖርኩበት ዘመን እርሱ ቤት የኖርኩበት ዘመን ይበልጥ ነበር። ልጅ ስላልነበረው በእርሱ ስም ነበር የምጠራው። የእኔ ሕይወት በጣም ነበር የሚያሳስበው። በዚያ ላይ የደም ብዛት በሽታ አለበት። የኔን እንደዚያ መሆን ሰምቶ ለብዙ ቀናት አልጋ ላይ መዋሉን ሰምቻለሁ። ርግጠኛ ነኝ የመለሰኝ የርሱ ጸሎት ነው።

እግዚአብሔር ሲወድድህ የሆነ ቦታ ስለአንተ የሚጨነቁ ሰዎች ይሰጥሃል። ጸሎታቸው የሚደርስላቸው፣ጩኸታቸው የሚሰማላቸው ሰዎች ያዘጋጅልሃል። ላታውቃቸው ወይንም ላትገምታቸው ትችል ይሆናል። ግን ስለሚወድድህ ያዘጋጅልሃል።

እቤቱ ስደርስ እናቴ፣ አባቴ፣ ሌላው አጎቴ እና ሁለት አክስቶቼ፣ ከውጭ የመጡ ሁለት ወንድሞቼ እና የአጎቴ የንስሐ አባት ሳሎን ተቀምጠዋል። ሊመክሩኝ ነው ብዬ ፈራሁ። ይገርምሃል አንዳች የሕይወትክን መሥመር በተስፋ መቁረጥ ስትስት ምክር ትጠላለህ። እኔም እንደዚያ ሆኜ ነበር። አሁን ደግሞ ተለውጫለሁ ምን ፈልገው ነው ? እያልኩ ገባሁ።

የሁሉም ዓይን እኔ ጋ ማረፉን ሲቆጠቁጠኝ ይታወቀኛል። ካህኑ ጸሎት አደረሱ። ከዚያም አጎቴ ከተቀመጠበት ተደላደለ። «እንደምታውቁት እኔ ልጅ የለኝም፤ ባለቤቴም ከሞተች ሦስት ዓመት አለፋት። እንግዲህ የሚቀረኝ ሞቴን መጠበቅ ነው» እንዲህ ሲናገር ሳላስበው እንባዬ ከዓይኔ ይፈስ ነበር። «አሁን የጠራኋችሁ ሀብቴን ሁሉ ለልጄ ማውረሴን ለመንገር ነው። ያለችኝ ልጅ እርሷ ብቻ ናት።» አልቻልኩም ተነሥቼ ተጠመጠምኩበት። ተያይዘን ተላቀስን። ካህኑ ነበር ያላቀቁን።

«እንደምታውቁት አንድ ቃል ነበረኝ፡፡ የእኔን ሀብት የሚወርሰው ሀገሩን ለቅቆ ያልሄደው ኢትዮጵያዊው ልጅ ነው፡፡ ከድሮ ጀምሮ ቦታችሁን እንጂ ዜግነታችሁን አትለውጡ እላችሁ ነበር፡፡ መቼም የእኛ እና የናንተ አስተሳሰብ ይለያያል፡፡ ከእርሷ በቀር ሁላችሁም ሄዳችሁ፡፡ ሁሉም ልጆች ዜግነታቸውን ቀየሩ፡፡ ነገሩ በዚህ ጉዳይ ከልጆቼ ብቻ ሳይሆን ከወንድሞቼም ጋር አልተስማማሁም፡፡

እንደኔ ቃል ከዚህ ሀገር ያልወጣችው ብቸኛ ተስፋዬ እርሷ ናት፡፡ እርሷንም የናንተ ዛር ለክፏት ካልሄድኩ ብላ ነበር፡ ፡ የእግዜር ነገር አሥሮ ያዘልኝ እንጂ»

የአጎቴን ፋብሪካ እና ሱፐር ማርኬት ወረስኩ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ወደ አንድ ገዳም ሄድኩና የእግዚአብሔርን ሥራ ለብቻዬ አሰብ ነበር፡፡ እኔ ልሄድበት የፈለግኩትን እና እግዚአብሔር የመረጠልኝን መንገድ እያሰላሰልኩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ንግግር የማይገልጠው ምስጋና አጋጥሞህ ያውቃል? ዝምታ ብቻ የሚገልጠው፡፡ እኔ እግዚአብሔርን ለማመስገን ንግግር አለቀብኝና ዝምታን መረጥኩ፡፡ አንድ ገዳም ሄጄ ቀኑን በሙሉ ዝም ብዬ እውል ነበር፡፡ እይውልህ ትናንት በመከራ ያላገኘኋቸውን ቪዛዎች ዛሬ በክብር ሄጄ እወስዳቸዋለሁ፡፡ ዛሬ አሜሪካ ካልኖርኩ አልልም፡፡ የምሄደው ለሌላ ጉዳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሀገሬ እንድሠራ፣ እንድከበር፣ ፈለገ፡፡ እኔ ደግሞ በሰው አገር መከራ ካልተቀበልኩ አልኩት፡፡ በግድ ጠምዝዞ ወደ ተሻለው መንገድ ወሰደኝ፡፡

ዮሴፍን ታስታውሰዋለህ፡፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ዮሴፍ የግብፅ ንጉሥ እንዲሆን ነው፡፡ የዮሴፍ ፍላጎት ደግሞ ቶሎ ከእሥር ቤት ለመውጣት ነው፡፡ ዮሴፍ በሰው በኩል ከእሥር ሊወጣ ሞከረ፡፡ እግዚአብሔር ግን በእሥራቱ ላይ ሁለት ዓመት ጨመረበት፡፡ አሁን ለዮሴፍ ከእሥራቱ ራሱ በመረጠው መንገድ መውጣቱ ነበር ጥሩ? የዚያን ጊዜ ፍላጎቱን እግዚአብሔር ቢፈጽምለት ነበር ጥሩ ? እንኳንም አላደረገው፡፡ እንኳነም አልፈጸመለት፡፡ የዮሴፍ ዕቅድ ቢፈጸም ኖሮ ያንን የመሰለ ተአምር፣ያንን የመሰለ ታሪክ የት ይገኝ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ በመዶሻ የሚፈረከስ ድንጋይ አለ፡፡ እምቢ ካለ ግን በድማሚት ይመታል፡፡ የኔ ልብ እምቢ አለ፡፡ ስለዚህ በድማሚት ተመትቶም ቢሆን ተመለሰ፡፡ ርግጠኛ ነኝ በሄድኩበት የኃጢአት መንገድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጥበቃው ነበር፡፡ ፍላጎቴን አልከለከለኝም፤ ነገር ግን ለክፉ አልሰጠኝም፡፡ እግዚአብሔር እና አጎቴ ተግባብተዋል፡፡ እኔ እና እግዚአብሔር ግን አልተግባባንም ነበር፡፡ እኔ ከእግዚአብሔር ጋር ለመግባባት ይህንን ሁሉ መንገድ መሄድ ነበረብኝ፡፡

እስኪ አስበው፡፡ የለመንኩትን ቢያደርገው ኖሮ፤ አሜሪካ ሄጄ አንድ ሱፐር ማርኬት እቀጠር ነበር፤ ወይንም የአንድ ፓርኪንግ ሠራተኛ እሆን ነበር፡፡ ምንም እንኳን ይህ በራሱ መጥፎ ባይሆንም እግዚአብሔር ግን ይህንን አልፈለገም፡፡ ከእኛ ይልቅ ለኛ ያውቃልና፡፡ እኛ ከመረጥነው እርሱ የመረጠው ይበልጣልና፡፡ የጠየቅኩትን ከለከለና የመረጠልኝን ሰጠኝ፡፡ እኛ የሚያምረንን፣ እርሱ ግን የሚያምርብንን፤ እኛ የምንፈልገውን፣ እርሱ ግን የሚያስፈልገንን ያደርግልናል፡ :

ለዚህ ነው «ስላላደረግልኝ ሁሉ አመሰግንሃለሁ» የሚል ጥቅስ ያስጻፍኩት፡፡ ዛሬ ላይ እቆምና «እንኳንም የጠየቅኩህን አልሰጠህኝ፤ እንኳንም የለመኩህን አላደረግከው፤ እንኳንም እምቢ አልከኝ፤» እለዋለሁ፡፡

ሰለያት

«ለርእስዬ እም ርእስዬ እስመ አንተ ትቀርቦ» አልኩ፡፡ «ለእራሴ ከእራሴ ይልቅ አንተ ትቀርበዋለህ» ማለት ነው፡፡

ይህ የእርሷ ታሪክ ግን ከስድስት ዓመታት በፊት የተፈጸመ ሌላ ታሪክ አስታወሰኝ፡፡

35. ሰው በቁሙ ሐውልት ለምን ያሠራል?

በዓለም ላይ የሕዝቦቻቸውን ድምፅ የማይሰሙ እና ራሳቸው ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ መሪዎች ባሉባቸው ሀገሮች አንድ የተለመደ ክፉ ተግባር አለ፡፡ መሪዎቹ በቁማቸው ሐውልቶቻቸውን ያሠራሉ፡፡ መንገዱን፣ ሕንፃውን፣ ስታዲዮሙን፣ ት\ቤቱን፣ ሆስፒታሉን ሁሉ በስማቸው ይሰይሙታል፡፡ በየሄዱበት ስለ እነርሱ ብቻ ይነገራል፣ ይዘመራል፣ ይጻፋል፡፡ ሀገሪቱ የአንድ ሰው ንብረት እስክትመስል ድረስ፡፡

የኢራቁ ሳዳም ሁሴን፣ የሰሜን ኮርያው ኪም ኤል ሱንግ፣ የኮንጎው ሞቡቱ ሴሴሴኮ፣ የኢትዮጵያው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ የቻይናው ማኦ ሴቱንግ፣ የሊቢያው መሐመድ ጋዳፊ የቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻችን ናቸው፡፡

ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች በቁማቸው እያሉ በሚሊዮን ዶላሮችን አውጥተው ሐውልቶቻቸውን መሥራት ለምን ፈለጉ? ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር እንኳን ያላደረገውን፣ በግል ገንዘባቸው የሠሩት ይመስል ሁሉን ነገር ለምን በስማቸው ይጠሩታል? ሕዝባቸው ገንዘብ ስለተረፈው ነው? ወይስ ሕዝባቸው በጣም ስለሚወድዳቸው በናንተ ስም ካልሆነ ታንቀን እንሞታለን ስላላቸው ነው?

የእነዚህ ሰዎች ትልቁ ችግራቸው ከውጭ ሳይሆን ከውስጣቸው የሚመነጭ ነው፡፡ ምንም እንኳን በዙርያቸው የሚገኙ «ራት አግባዎቻቸው» (የአቡነ ጎርጎርዮስ ቋንቋ ነው) ሲያወድሷቸው ቢውሉ እነርሱ ግን በዘመናቸው በጎ እንዳልሠሩ ያውቁታል፡፡ እነዚህ በዙር ያቸው ሆነው እናንተ ካሌላችሁ ዓለም የለችም እያሉ የሚነግሯቸው «ካህናተ ደብተራ» (ቤተ መንግሥትን ተጠግተው ነገሥታቱ ሕግ እንዲጥሱ፣ቅዱሳኑ ከነገሥታቱ እንዲጣሉ ያደርጉ የነበሩ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ካህናት) እንደሚሉት ሳይሆን ሕዝቡ «ንቀልልን» እያለ እንደሚጸልይ ይረዱታል፡፡

እነዚህ አምባ ገነኖች ከሞቱ በኋላ እንኳንስ ሥራቸው ዝክረ ሥራቸው ሁሉ እንደሚረሳ፣ እንደሚመዘበር እና ግብዐተ መሬቱ አብሯቸው እንደሚፈጸም ነፍሳቸው ትነግራ ቸዋለች፡፡ ነፍስን ማታለል አይቻልምና፡፡ ከነፍስ ጠባያት አንዱ ዐዋቂነት ነው፡፡ ዐዋቂት ነፍስን ከውጭም ከውስጥም የሚመጣ ከንቱ ውዳሴ፣ የሐሰት ሪፖርት፣ የማስመሰያ ተኩስ እና የማታለያ ስሜት አያታልላትም፡፡ እርሷ ምንጊዜም ትክክለኛውን ነገር ብቻ ትረዳለች፡፡

እነዚህ ሰዎች ወደ ቤታቸው ሲገቡ፤ አልጋቸው ላይ ሲወጡ፣ መጸዳጃ ቤት ሲቀመጡ፣ ወይንም በሌላ መንገድ ለብቻቸው የሚሆኑበት አጋጣሚ ሲፈጠር ነፍሳቸው እውነታውን ታረዳቸዋለች፡፡

እናም ከሞቱ በኋላ ለእነርሱ ሐውልት የሚያቆም፣ መንገድ በስማቸው የሚሰይም፣ በየዓመቱ በዓላቸውን የሚያከብር፣ ዝክረ ታሪካቸውን የሚያስታውስ ትውልድ እንደ ማይኖር ይገባቸዋል። ጅብ ለምን ሌሊት ይሄዳል ቢሉ ቀን የሚሠራውን ስለሚያውቅ ነው እንደሚባለው።

እነዚህ ሰዎች ዘመናቸው ከሞቱ በኋላ እንደማትቀጥል ያውቋታል። ኃይላቸው ሲደክም ጀንበራቸው እንደምትጠልቅ ተረድተውታል። እናም ሲሞቱ ሐውልት እንደ ማይቆ ምላቸው ስሚያውቁት በቁማቸው ሐውልታቸውን ማቆም ይፈልጋሉ። ይህ ሐውልታቸው ከሞቱ በኋላ እንደማይኖር ቢያውቁት እንኳን በቁም ተዝካራቸውን ማውጣት ይመርጣሉ።

ከሞቱ በኋላ ሥራቸው እንደሚቀጥል ያወቁ ቅዱሳን፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣ መሪዎች፣ ደራስያን፣ ሰዓልያን፣ አርበኞች ለፈጣሪያቸው፣ ለሕዝባቸው እና ለሀገራቸው ስለሚያከ ናውኑት በጎ ሥራ እንጂ ስለሚዘከረው ስማቸው አይጨነቁም፡ ፡ ከበጎ ሥራ በላይረዥ ዘመን የሚኖር ሐውልት እንደሌለ ያውቃሉ። ስለሚዘከረው ስማቸው ሳይሆን ስለሚጠቀመው ሕዝባቸው ይጨነቃሉ። ስለ እነርሱ ስም ሳይሆን ስለ ሃይማኖታቸው፣ ሀገራቸው፣ ሕዝባቸው የክብር ስም ይጨነቃሉ።

በጣም በሚገርም ሁኔታ ሐውልታቸውን ራሳቸው ካቆሙ ሰዎች ይልቅ ሐውልታቸውን ተተኪው ትውልድ ያቆመላቸው ሰዎች እስከ ዛሬ ይታወሳሉ፣ ይከበራሉ። ዐፄ ምኒሊክ ባቡር ሲያስገቡ፣ ስልክ ሲያስመጡ፣ መንገድ ሲያሠሩ፣ ት/ቤት ሲያስገነቡ፣ ሆስፒታል ሲያቆሙ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲያስተክሉ ኖሩ። ለዚህ በጎ ሥራቸው ከሞቱ በኋላ ትውልዱ «እምዬ ምኒሊክ» እያለ የማይጠፋ ስም ሰጣቸው። ሐውልታቸውን አቆመላቸው። በ1984 ዓም አካባቢ የመንግሥትን ለውጥ ተጠቅመው ጥቂት እበላ ባዮች ሐውልታቸውን እናወርዳለን ብለው ሲነሡ ሕዝብ እንደ አራስ ነበር ተቆጥቶ፣ እንደ ንብ መንጋ ተቆጭቶ ነበር የተነሣባቸው።

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አበው የእግዚአብሔር ስም እንዲከብር፣ የቀደሙት አባቶቻቸው ስም እንዲዘከር እንጂ ስለራሳቸው ስም ተጨንቀው አያውቁም ነበር። አብርሃ እና አጽብሐ በራሳቸው ስም ቤተ ክርስቲያን አልሠሩም፡ ፡ የኋላ ሰዎች ግን መልካሙን ሥራቸውን አይተው በስማቸው ታቦት ቀረጹላቸው።

ሐውልት በቁም መሥራት የክብር መለኪያ፣ የሥራ ማሳያ ቢሆን ኖሮ ከአንድ ወጥ ዐለት አሥራ አንድ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ያነፀው ቅዱስ ላሊበላ ቢያንስ አንድ ሐውልት ለራሱ ባቆመ ነበር። እርሱ የፈጣሪው ስም የሚሠራበትን ሠራ። ፈጣሪውም የላሊበላ ስም የሚጠራበትን መታሰቢያ አደረገለት። ይኼው በዕለተ ገና ስሙ ለዘለዓለም ሲዘከር ይኖራል። የራሳቸውን ሐውልት ለመሥራት የሚጨነቁት እንደ ላሊበላ ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡት አምኃ የሌላቸው ናቸው።

ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ደብረ አስቦ ዋሻ ገብተው ሲጋደሉ በስማቸው ገዳም አልገደሙም። ያነፁት በእመቤታችን ስም የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን ነው። በስማቸው ታቦት የተቀረጸው፣ ቤተ ክርስቲያን የታነፀው ካረፉ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። እርሳቸው 500 ዓመታት ሊዘልቅ የሚችል የቁም ሐውልት ስለ መሥራት አልተጨነቁም። ከጽድቅ በላይ ምን ሐውልት አለና። ዛሬ ግን ስማቸው ከ500 ዓመታት በላይ ተሻግሮ በመላው ዓለም ይጠራል።

ከጎንደር ነገሥታት ሁሉ አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን በማሠራት፣ ገዳማትን በመገደም፣ ለብዙዎቹ ነገሥታት አንጋሽ እና ጠባቂ በመሆን እቴጌ ምንትዋብን የሚስተካከላት የለም፡፡ ናርጋ ሥላሴ፣ ክብራን ገብርኤል እና የጎንደርዋ ቁስቋም ደብር እስከ ዛሬም ታሪክዋን በህያውነት ይመሰክሩላታል፡፡ በዲፕሎማሲው፣ በኪነ ሕንፃው፣ በሥነ ጽሑፉ፣ በሥነ ሥዕሉ እና በትርጓሜ መጻሕፍቱ ሁሉ ከእርሷ በኋላ ማንም ያልተካውን ሥራ ሠርታለች፡፡

ለዚህ ሁሉ ሥራዋ ግን ሐውልት አላቆመችም፤ ስለ እርሷ የምናገኘው ሥዕል እንኳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ሥር በተማኅጽኖ ሰግዳ፣ እመቤታችንን ከፍ፣ ራስዋን ዝቅ ያደረገችበትን የትኅትና ሥዕሏን ነው፡፡ እርስዋ በትኅትና ዝቅ ብትልም፣ በጎ ሥራዋ ግን ከሦስት መቶ ዓመታትም በኋላ ከትውልዶች በላይ ከፍ ብሎ ማነነቷን ይመሰክራል፡፡

የራሽያ ኮሚኒስት መሪዎች ስማቸውን ከዘመናት በላይ ለማስጠራት ሲሉ ከተማውን ሁሉ በስማቸው ጠርተውት ነበር፡ ፡ በየመንገዱ ሐውልታቸው ቆሞ ነበር፡፡ ፎቶዎቻቸው ዓይን እስኪያሰለቹ ድረስ በመላ ሀገሪቱ ተሰቅለው ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከሰባ ዓመታት በላይ መዝለቅ አልቻሉም፡፡ ዛሬ በስማቸው የጠሯቸው ከተሞች ተቀይረዋል፤ ሐውልቶቻቸው ፈርሰዋል፣ ፎቶዎቻቸው የዕቃ መጠቅለያ ሆነዋል፡፡ ዝክረ ስማቸውም ተረስቷል፡፡ የሚያስታውሰውም ካለ በበጎ አያነሣውም፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገርሙኝ ነገሮች አንዱ የተፈሪ መኮንን ት/ቤት ጉዳይ ነው፡፡ ያንን ት/ቤት ደርግ መጣና «እንጦጦ አጠቃላይ» ብሎ ሰየመው፡፡ እስካሁን ግን የትኛ ውንም ባለታክሲ «እንጦጦ አጠቃላይ ውሰደኝ» ብትሉት እንጦጦ ተራራ ይወስዳችሁ ይሆናል እንጂ ተፈሪ መኮንን ት/ቤት አይወስዳችሁም፡፡ መንግሥት ቢቀይረው እንኳን ሕዝቡ አልተቀበለውም ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነው «ስድስት ኪሎ፣ ተፈሪ መኮንን» እያለ ታክሲው የሚጠራው፡፡

ይህ ነገር አንድ ቁም ነገር እንድናስታውስ ያደርገናል፡፡ ሐውልትን እድሜ የሚሰጠው ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መልስ፡፡ አንድን መታሰቢያ ረዥም ዘመን እንዲኖር የሚያደርገው የተሠራበት ቁሳቁስ አይደለም፡፡ በሕዝቡ ዘንድ ያለው ቅቡልነት እንጂ፡፡ እንደ ሳዳም ሐውልት በውድ ዋጋ የተሠራ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ዛሬ የለም፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ መንግሥት ያልሰየማቸው ሕዝቡ ግን ለመታሰቢያነት የሚጠራቸው ስንት አካባቢዎች፣ መንገዶች፣ አደባባዮች አሉ፡፡ መንግሥት ያለ ሕዝቡ ተቀባይነት ሐውልት ያቆመለት ማርክስ ግን ሐውልቱን ከነመኖሩ የሚያስታውሰው የለም፡፡ ጥቁር አንበሳ አጠገብ ያለው የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሐውልትም ተረስቷል፡፡

ዛሬ ዛሬ ይህንን በመገንዘብ የፖለቲካ መሪዎች እንኳን በቁም ሐውልት ማቆምን እየተውት መጥተዋል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎችን እዚህ ላይ ማንሣት እፈልጋለሁ፡፡ እስከዛሬ ድረስ በትግል ለተሠው ቀደምቶቻቸው እንጂ በሕይወት ላሉት መሪዎቻቸው ሐውልት ሲያቆሙ አላየንም፡፡ በአንድ ወቅት የኤች አይ ቪ ምርመራ ማድረግ አለማድ ረጋቸውን የተጠየቁት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ምርመራ ማድረጋቸውን ነገር ግን የምርመራውን ውጤት ለገበያ እንዳላቀረቡት ተናገሩ፡፡ እርሳቸው «ለገበያ ማቅረብ» ብለው የጠሩት በየአደባባዩ ቢል ቦርድ እያሠሩ መለጠፍን ነበር፡፡

ምነው ዘመናችን መንፈሳውያን መሪዎች ከፖለቲካ መሪዎች በአመክንዮ እና በሰብእና የሚያንሡበት ሆነብን?

36. የአንድ አባት ምክር

በአንድ ወቅት በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ተገኚቼ ነበር፡፡ በዚያ ገዳም የሚኖሩ አባት የነገሩኝ ነገር ለሕይወት መመርያ የሚሆን ነው፡፡ አሁን ከደረስንበት ወቅት ጋር የሚሄድ ነውና ላካፍላችሁ፡፡ በወቅቱ እንደ ዛሬው በቤተ ክርስቲያን ላይ የፈተና ማዕበል ተነሥቶ ነበር፡፡ ያ ወቅት የፖለቲካው ማዕበልም እጅግ ያየለበት ጊዜ ነው፡፡ አንዳንዶቻችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንሰጠው አገልግሎት ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ምንስ ለውጥ ያመጣል? ችግሩ እንደሆነ እየባሰው እንጂ እየተሻለው አልሄደም፤ ታድያ ጊዜያችንን፣ ገንዘባችንን እና ዕውቀታችንን ዝም ብለን እየከሰከስን ይሆን? አሁን የኛ ልፋት የክፉ ሰዎችን ክፋት ለመሸፈን እና በክፋታቸው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ካልሆነ በቀር ችግሩን ይፈታዋል? ወዘተ፣ ወዘተ፣ ጥያቄዎች ይነሡ ነበር፡፡ ያን ጊዜ እኒህ አባት እንዲህ አሉን:- «ብዙ ልጆችን የወለደች የምትወድደው ባሏ የሞተባት አንዲት እናት ነበረች፡፡ ቤተ ዘመዶቿ ምንም ሳይራሩ ያለ ፍላጎቷ ለአንድ ክፉ ባል አጋቧት፡፡ ይህ ባል ግዴለሽ፣ ገንዘብ ወዳድ፣ ጠጥቶ ከመስከር፣ በልቶ ከመጥገብ፣ በስተቀር ሌላ ሞያ የለውም፡፡ ሲወጣ ሲገባ ይደበድባታል፡፡ እንጨት ሽጣ፣ ኩበት ለቅማ፣ እንጀራ ጋግራ፣ ጠላ ጠምቃ ያጠራቀመቻትን ገንዘብ ነጥቆ ይወስድባታል፡፡ ለዘመዶቹም ይበትነዋል፡፡ የት ትሂድ? የሠፈሩ ሕግ፣ ባህሉ እና ልማዱ፣ በሙሉ የእርሷን ሮሮ እና ልመና የሚሰማ አልሆነም፡፡ እርሱን እንደ ሕጋዊ ባልዋ ነው የሚቆጥሩት፡፡ የት ሂዳ መከራዋን ትናገር፡፡ የትስ ሂዳ ከችግሩ ትገላገል?

ይህ ክፉ ባልዋ እርሷን ብቻ ሳይሆን ልጆቿንም ያሰቃያቸው ነበር፡፡ እነርሱም በዚያ ቤት ውስጥ መከራውን እና ስቃዩን፣ ረሃቡን እና ጭቅጭቁን እየሰሙ መኖር መረራቸው፡፡ በዚያ ቤት ሰላም ጠፋ፡፡ ፍቅር ጠፋ፡፡ ምንጊዜም የሚሰማው ክፉ ነገር እና ልብ የሚያደማ ነገር ሆነ፡፡ ሰው ሁሉ ስለዚያ ቤት ያወራል፡፡ መንገድ ላይ ሲያገኟቸው ስለ ቤታቸው ይጠይቃቸዋል፡፡ እነርሱም በሃፍረት ይሸማቀቃሉ፡፡ ስለዚህም እናታቸውን ጥለው ወደ ሌላ ቦታ መሄድና ስለዚያ ቤት ከማያስቡበት እና ከማይሰሙበት ቦታ መድረስ ፈለጉ፡፡ የሚችሉትን ያህል እየሠሩ፣ ለራሳቸው የሚበቃቸውን እየኖሩ፣ መከራውን መገላገል እና እፎይ ብለው መኖር አሰኛቸው፡፡ ታድያ ይህንን ሃሳባቸውን ለአንድ ሽማግሌ ጠቢብ ሰው ነግረው ገንዘብ እና ሃሳብ እንዲሰጣቸው ፈለጉ፡፡ ሄደውም አማከሩት፡፡ ያም ሽማግሌ ሃሳባቸውን ሁሉ ከሰማ በኋላ እንዲህ አላቸው፡፡ «ልጆቼ ልክ ናችሁ ሩቅ ሀገር ሄዳችሁ፣ የምትችሉትን ያህል እየሠራችሁ፣ የራሳችሁን ኑሮ በመኖር ችግሩን ሁሉ መርሳት እና መገላገል ትችላላችሁ፡፡ ምን ያስጨንቃችኋል? ቤት ያለው እዚህ ብቻ ነው እንዴ? ሀገርስ ያለው እዚህ ብቻ ነው እንዴ? ግን አንድ ነገር አስቡ፡፡ እንዲህ ማድረጋችሁ ራሳችሁን ብቻ ከችግሩ ታወጣላችሁ እንጂ ችግሩን አትፈቱትም፤ እናንተ ችግሩን ትረሳላችሁ እንጂ ችግሩን አታስወግዱትም፡፡

«ደግሞም የእንጀራ አባታችሁ እናታችሁን የበደለውን ያህል እናንተም ትበድሏታላችሁ፡፡ እስኪ አስቡት ለዚህች ለእናታችሁ ከእናንተ በቀር የደስታዋ ምንጭ ማን ነው? ሁሉም ነገርዋ የሚያሳዝን እና የሚያስመርር ነው፡፡ እናንተ ግን የደስታዋ ምንጮች ናችሁ፡፡ የእንጀራ አባታችሁ እናታችሁን ያሳዝናታል፤ የእናንተ ጥላችኋት መሄድም ያሳዝናታል፤ እርሱ ብቻዋን እንድትለፋ ትቷታል፤ እናንተ ጥላችኋት ስትሄዱም ያለ አጋዥ ትተዋታላችሁ፤ እርሱ በመስረቅ ዘረፋት፣ እናንተም ባለ መስጠት ዘረፋችኋት፤ ታድያ ከእርሱ በምን ተሻላችሁ? እናንተኮ ያሰባችሁት ለእናታችሁ ሳይሆን ለራሳችሁ ነው፡፡ እናታችሁ ስለተቸገረች አይደለም ያዘናችሁት፣ ችግሩ እናንተን ስለነካ ነው፤ እናታችሁ ስለተራበች አይደለም ያዘናችሁት ረሃቡ ስለነካችሁ ነው፡፡ በእናታችሁ ላይ የደረሰው ችግሳይሆን ስለችግሩ ከየሰው አፍ መስማት ነው የሰለቻችሁ፤ ችግሩን ለመቅረፍ አይደለም መሄድ የፈለጋችሁት፤ ችግሩን ላለማየት እና ላለመስማት ነው፡፡ ከዚያ

ይልቅ ሥራ ሠርታችሁ ገንዘብ አግኙ እና ለእናታችሁ ምግብ ስጧት፤ የሚያስርባትን የእንጀራ አባታችሁን በዚህ ትቃወሙታላችሁ፣ ልብሷን ቀይሩላት፣ የሚያሳርዛትን አባታችሁን በዚህ ትቃወሙታላችሁ፣ ስትታመም አሳክሚት፣ የሚያሳምማትን የእንጀራ አባታችሁን በዚህ ትቃወሙታላችሁ፤ የወግ እቃዎቹን ሰብስቡና አስቀምጡላት፤ዝክረ ታሪኳን ሊያጠፋ የተነሣውን የእንጀራ አባታችሁን በዚህ ትቃወሙታላችሁ፤ እርሱ እያረጀ ሲሄድ እናንተ ግን እያደጋችሁ ነው፡፡ ስለዚህም እየበዛችሁ እና እየመላችሁ ሂዱና ይህንን ቀፍድዶ የያዛትን የመንደሩን ሕግ አስተካክሉት፡ ፡ ምናልባት የእንጀራ አባታችሁ ቢሞት ሌላ የእንጀራ አባት ደግሞ እንዳይተካ፡፡ እንደዚያ ካደረጋችሁ እናንተ የእናታችሁ ልጆች ናችሁ፡፡ ያለ በለዚያ ግን የእንጀራ አባታችሁ ተባባሪዎች ናችሁ፡፡ ሸረሪት ታውቃላችሁ፡፡ ከሰው ቤት ግድግዳ ላይ ድር አድርታ፤ ወልዳ ከብዳ ትኖራለች፡፡ ቤቱ በእሳት ሲያያዝ ግን ከቤቱ ወጥታ ቀድማ የምትሮጥ እርሷ ናት፡፡ ቤቱ የኖርኩበት ነው፡፡ ወግ መዓርግ ያየሁበት ነው፤ እሳቱን በማጥፋት አስተዋጽዖ ማድረግ አለብኝ አትልም፡፡ መሸሸን ብቻ ነው የምትፈልገው፡፡ ለራስዋ ብቻ ነው የምታስበው፡፡ ይህ ከሸረሪትነቷ የመጣ ነው፡፡ እናንተ ግን ሰዎች እንጂ ሸረሪቶች አይደላችሁም፡፡ ሰዎችን እያያችሁ ከሀገራችሁ እና ከቤተ ክርስቲያናችሁ ልትርቁ አትችሉም፡ ፡ አያገባንም ልትሉ አትችሉም፡፡ እሳቱን ማጥፋት ትታችሁ ከእሳት ለማምለጥ ብቻ ልትሮጡ አትችሉም፡፡ ይህንን ካደረጋችሁ ሸረሪቶች እንጂ ሰዎች አይደላችሁም፡፡» አሏቸው

ይህንን ሰምተው ልጆቹ ወደ እናታቸው ተመለሱ:- እስኪ እኔም አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፡፡ የዚህች ሀገር እና የዚህች ቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ፍላጎት ምንድን ነው? ይህች ሀገር እና ይህች ቤተ ክርስቲያን ያለ ረዳት እንዲቀሩ ማድረግ አይደለምን? እናንተም እንተዋት፣ እናቁም፣ እንሸሽ ስትሉ ያለ ረዳት እያስቀራችኋት ነው፡፡ የእነርሱ ፍላጎት ኢትዮጵያን እና ተዋሕዶን ተስፋ ማስቆረጥ አይደለምን? እናንተም ተስፋ ከቆረጣችሁ ተሳካላቸው ማለት ነው፡፡ ልጆቻቸውን እያስመረሩ ማስኮብለል አይደለምን? ከኮበለላችሁ ተሳካላቸው ማለት ነው፡፡ ታሪክን፣ ቅርስን፣ ክብርን፣ ልዕልናን መመዝበር እና ማራከስ አይደለምን? እናንተም ታሪኩን፣ ቅርሱን፣ ባህሉን፣ ክብሩን ርግፍ አድርጋችሁ ትታችሁ በራሳችሁ ዓለም ብቻ ስትቀሩ የእናንት ፍላጎት ሳይሆን የእነርሱ ፍላጎት ተሳካ ማለት ነው፡፡ ታድያ አሁን እናንተ መመለስ ያለባችሁ አንድ ጥያቄ ነው፡፡ የምትፈልጉት የጠላቶቿ ፍላጎት እንዲሳካ ነው ወይስ በመከራ ውስጥ ያለችውና ቀን የጣላት የእናታችሁ ፍላጎት እንዲሳካ ? ምረጡ፡፡ እነሆ ይህ ጥያቄ ሁሌም ይመጣብኛል፡፡

37. ንጉሡ ራቂታቸውን ናቸው

ሁለት እራት አግባ ብልሃተኞች ወደ አንድ ንጉሥ ግቢ ያመሩና ደጅ ይመታሉ፡፡ የግቢው ጠባቂም አቤት ይላል፡፡ እነዚያ ብልሃተኞችም «ለንጉሡ ኃጢአተኛ ሰው የማያየው አዲስ ልብስ ልንሠራ መጥተናል» ይላሉ፡፡ ግቢ ጠባቂውም ሲሮጥ ሄዶ ለንጉሡ ጉዳዩን ያቀርባል፡፡ ንጉሡ ይፈቅዱና ሰዎቹ ገብተው እጅ ነሡ፡፡ «ምን ዓይነት ልብስ ነው የምትሠሩት» አሉ ንጉሡ፡፡ ብልሃተኞቹም «ኃጢአት የሠራ ቀርቶ ያሰበም ሰው ሊያየው የማይችል አዲስ ዓይነት ልብስ ነው» ሲሉ ማብራርያ ሰጡ፡፡ ንጉሡም በነገሩ ተደስተው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ መድበው ልብሱን እንዲሠሩላቸው አዘዙ፡፡

በወርቅ እና በብር የተንቆጠቆጡት፣ ልዩ ድርጎ እና ቤት የተሰጣቸው እነዚያ ብልሃተኞች ቤቱን ዘግተው ሥራ ጀመሩ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ንጉሡ አንዱን ባለሟላቸውን ሥራው የት እንደ ደረሰ እንዲያይላቸውት ላኩት፡፡ ብልሃተኞቹም ተቀብለው አስተናገዱት፡፡ ባለሟሉ ወደ ቤታቸው ሲገባ የሚያየው ነገር አልነበረም፡፡ ባዶ የልብስ መሥሪያ ማሽን፣ ባዶ ጠረጴዛ እና ባዶ አዳራሽ፡፡ ግራ ተጋባ፡፡ ከብልሃተኞቹ አንዱ ወደ ጠረጴዛው አመራና «አዩ ጌታው፤ እጅ ጠባቡ

እያለቀ ነው» አለው ባዶውን ጠረጴዛ እያሳየ፡፡ ባለሟሉ ግን እንኳን እጅ ጠባብ ብጫቂም ጨርቅ በጠረጴዛው ላይ ለማየት አልቻለም፡፡ ነገር ግን «ኃጢአት የሠራ ሰው ልብሱን ማየት አይችልም» ተብሏልና «አላየሁም» ቢል ኃጢአት ስለ ሠራህ ነው የሚለው እንጂ የሚያምነው ስለሌለ «በጣም የሚገርም እጅ ጠባብ ነው፡፡ መቼም ንጉሣችን ሲያዩት ይደሰታሉ» ብሎ ራሱን እየነቀነቀ አደነቀ፡፡ በልቡ ግን ግራ እንደተጋባ ነበር፡፡

«ንጉሥ የሚያምረውን እንጂ የሚያምርበትን፣ ንጉሥ የሚፈልገውን እንጂ የሚያስፈልገውን አይነግሩትም» ይባላልና ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመልሶ ለንጉሡ «እጅግ የሚገርም፣ ዓይን ያላየው ጆሮም ያልሰማው ልዩ የሆነ እጅ ጠባብ ተሠርቷል፡፡» ሲል ሪፖርቱን አቀረበ፡፡ አሁንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ንጉሡ ሌላ ባለሟላቸውን ላኩት፡፡ ያም ባለሟል ወደ ብልሃተኞቹ ቤት ገብቶ አካባቢውን ሲያይ ደነገጠ፡፡ እንኳን የተሰፋ ልብስ የተዘረጋ ክር የለም፡፡ ነገር ግን የቀድሞው ባለሟል አየሁ ብሎ ይሄኛው አላየሁም ቢል ከጓደኛው ማነሱ ነው፡፡ ብልሃተኞቹም ወደ ጠረጴዛው ወስደው «እጅ ጠባቡ ይህንን ይመስላል፤ ሱሪው ደግሞ በመሰፋት ላይ ነው፡፡ የሚቀረን ጫማው ነው» እያሉ ማስጎብኘት ቀጠሉ፡፡

ባለሟሉ እንኳንስ አዲስ የተሠራ እጅ ጠባብና የተሰፋ ሱሪ ቀርቶ አሮጌ ልብስ እንኳን እንኳን ለማየት አልታደለም፡፡ ነገር ግን ኃጢአተኛ ከሚባል «እንደ ዘመኑ ይኖሩ እንደ ንጉሡ ይናገሩ» ነውና «ይህንን ነገር ለማየት በመታደሌ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ፡፡ ይህንን ነገር ለማየት ፈልገው ያላዩ ስንት አሉ፡፡ በሥራችሁ ንጉሡ እንደሚደሰቱ ርግጠኛ ነኝ» ብሎ አመስግኗቸው ወጣ፡፡ በልቡ ግን «እነዚህ ሰዎች ያሾፋሉ እንዴ፤ ምን ዓይነት ነገር ነው እየሠሩ ያሉት» እያለ ያጉተመትም ነበር፡፡ ለንጉሡም ድንቅ ነገር ማየቱን ከዚያኛው አስበልጦ አንቆለጳጵሶ አቀረበ፡፡

በመጨረሻ ራሳቸው ንጉሡ የሥራውን ማለቅ ለማየት ከባለሟሎቻቸው ጋር መጡ፡፡ እነዚያም ብልሃተኞች እንደተለመደው ወገባቸውን አሥረው ማስጎብኘት ጀመሩ፡፡ «ይሄ እጅ ጠባቡ፣ ይሄ ሱሪው፣ ይሄ ካባው፣ ይሄ ጫማው ነው» እያሉ ያሳያሉ፡፡ ንጉሡ ምንም ነገር ለማየት አልቻሉም፡፡ ነገር ግን የእርሳቸው ባለሟሎች አየን ብለው እያወሩ እርሳቸው አላየሁም ቢሉ ራሳቸውን ማስገመት ነው፡፡ ሕዝቡስ ምን ይላል? ደግሞም ዋናው ነገር እርሳቸው አየሁ ማለታቸው እንጂ ማየታቸው አይደለም፡፡ ይህንን ሁሉ አስበው «በሕይወቴ ላየው የምፈልገውን ነገር ነው ያየሁት፡፡ በነገሥታት ታሪክ እንደዚህ ያለ ልብስ መልበሱ የተነገረለት ንጉሥ የለም፡፡ ልዩ የሆነ ሽልማት ይዘጋጅላችኋል» ብለው አድናቆታቸውን ገለጡ፡፡ አጅበዋቸው የመጡትም ምንም ነገር ለማየት ባይችሉም ኃጢአተኛ እንዳይባሉ ሲሉ አደነቁ፤ አመሰገኑ፡፡

«ንጉሥ ሆይ» አለ አንደኛው ብልሃተኛ «ሕዝቡ ሁሉ በዐዋጅ ተጠርቶ ይህንን ልብስ ለብሰው ማየት አለበት»፡፡ የንጉሡም ባለሟሎች «እውነት ነው፤ ይህንን መሰሉ ልብስማ የቤት ልብስ አይሆንም» ብለው እያዳነቁ ሃሳቡን ደገፉት፡፡ ንጉሡም ተስማሙ፡፡

ዐዋጅ ታወጀ፡፡ «ንጉሡ ኃጢአት የሠራ ሰው ሊያየው የማይችል ልብስ ስላሠሩ እንዲህ ባለ ቀን፣ እንዲህ ባለ ቦታ፣ በዚህ ሰዓት ወጥታችሁ እንድታዩ» ተባለ፡፡ በተባለውም ቀን ሕዝቡ ጉድ ለማየት ግልብጥ ብሎ ወጣ፡፡ ንጉሡም ወደ ብልሃተኞቹ ዘንድ መጡ፡፡ ሁለቱ ጓደኞች እየተረዳዱ ንጉሡን ማልበስ ቀጠሉ፡፡ እነዚያ ብልሃተኞች ንጉሡ የለበሱትን ልብስ ሙልጭ አድርገው አውልቀው «አሁን ሱሪውን፣ አሁን እጅ ጠባቡን፣ አሁን ካባውን» እያሉ አለበሷቸው፡፡

ንጉሡም እየሳቁ፣ፈገግ እያሉ፤ በዙርያቸው የተሰለፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ልብሱን ለበሱ ተባለ፡፡ ንጉሡም በልባቸው «ራቁቴን ሊያስኬዱኝ ነው እንዴ?» ይላሉ፡፡ ግን አይናገሩትም፡፡ ተከታዮቻቸውም «እኒህ ሰውዬ ሊያብዱ ነው እንዴ፤ ራቁታቸውን ናቸውኮ» ይላሉ ግን አይናገሩትም፡፡ አፍ እና ልብ እንደ ተለያዩ ንጉሡ ለብሰው ጨረሱ ተባለ፡፡

ከዚያም ሠረገላው ቀረበና ንጉሡ በትረ መንግሥት ጨብጠው ቆሙ፡፡ ባለሟሎቻቸውም ሰግደው አጨበጨቡ፡፡ ከዚያም ሠረገላ ነጅው እንደ ዛሬ ንጉሡን ራቁታቸውን አይቷቸው ስለማያውቅ ሳቅ እያፈነው ሠረገላውን መንዳት ጀመረ፡፡ ወደ አደባባዩም ወጡ፡፡ ሕዝቡ ሁሉ አጨበጨበ፡፡ አንዱ ለጓደኛው «ግሩምኮ ነው፤ ከየት አገኙት ባክህ» ይላል፡፡ ኃጢአተኛ እንዳይባል፡፡ በልቡ ግን «በቃ ስምንተኛው ሺ ማለት ይሄ አይደለም እንዴ፡፡ ንጉሥ ራቁቱን ሲሄድ ከማየት በላይ ምን ምልክት አለ» ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ «ተመልከት፣ ተመልከት እጅ ጠባቡ ሲያብረቀርቅ፣ ንጹሕ ሐር እኮ ነው» ይልና በውስጡ ግን «አብደዋል፣ አብደዋል እንጂ፤ ደኅና ዘመድ አጥተዋል» ብሎ ያማል፡፡ ሁሉም ራሱን ላለማዋረድ እና ኃጢአተኛ ላለመባል ሲል ያላየውን እንዳየ እያደረገ ይጨዋወታል፡፡ በልቡ ግን ግማሹ ይስቃል፣ ግማሹ ያፍራል፣ ግማሹ ይራገማል፣ ቀሪውም ያማል፡፡

ንጉሡም ከሕዝቡ የሚቀርብላቸውን ልክ የሌለው ሙገሳ እየሰሙ፤ የባለሟሎቻቸውን ውዳሴ እያዳመጡ ሰውነታቸው በሙሉ ጥርስ በጥርስ ሆነ፡፡ በውስጣቸው ግን ብርዱ አላስቆም አላቸው፡፡ ነፋሱ ይቀጠቅጣቸው ጀመር፡፡ «ምን ዓይነት ሞኝ ብሆን ነው የነዚያን አጭበርባሪዎች ምክር የሰማሁት፤ አሁን የውስጤን ብናገር ማን ያምነኛል» ይሉ ነበር፡ ፡

በዚህ መካከል እናቱን ተከትሎ የመጣ አንድ ሕፃን ልጅ «እማዬ፣ እማዬ እይ፣ ንጉሡኮ ራቁታቸውን ናቸው» አለና ጮኸ፡፡ በዙርያው የነበሩ ሁሉ «ዝም በል፤ ይሄ ገና ከልጅነቱ ኃጢአት የወረሰው፡፡ ምን የዛሬ ዘመን ልጆች እንዲህ ያለው ግሩም ነገር አይታያቸሁ፡፡ ዝም በል፤ የተረገመ» እያሉ ተረባረቡበት፡፡ እናቱም አፈሩ፡፡ በዚህ ሰዓት ካፊያ እየጣለ ነበር፡፡ ንጉሡ ግን ፈገግታቸው እየጨመረ፣ ስቃያቸውም እያየለ ሄደ፡፡ ያ ሕፃን ልጅ ከእናቱ እጅ አፈትልኮ ወጣና ሠረገላውን እየተከተለ «ኧረ ንጉሡ ራቁታ ቸውን፤ ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን» እያለ መጮኽ ቀጠለ፡፡ ሕዝቡም በኃጢአተኛነቱ እያዘነበት፣ ርግማኑንም እያዥጎ ደኅደበት፣ ዝናሙም እያየለ፣ ንጉሡም እንደቆሙ ትእይንቱ ቀጠለ፡፡

ሕዝቡ ያጨበጭባል፣ ባለሟሎችም እንጀራቸው ነውና ሕዝቡ እንዲያጨበጭብ ያስተባብራሉ፡፡ ቀራቢዎቻቸው እጅ ያውለበልባሉ፤ ንጉሡም የሚቀርብላቸውን ሁሉ በደስታ ይቀበላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡም ያማል፡፡ በዚህ ዘመን መፈጠሩን ይረግማል፡፡ በንጉሡ እብደት ይናደዳል፣ ይዝታል፡፡ ባለሟሎቻቸውም በውስጣቸው አፍረዋል፡፡ በነዚያ ሁለት ብልሃተኞች ድርጊት ተበሳጭተዋል፡፡ እንዲህ ባለው ዘመን ባለሟል በመሆናቸው ራሳቸውን ይረግማሉ፤ ዘመኑንም ይረግማሉ፣ በውስጣቸውም ያማሉ፡፡ ግን ምኑንም አይናገሩትም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ሥራቸው ነውና ሳያጨበጭብ ቆሞ የሚያዩትን ሰው «አጨብጭብ፣ ኃጢአተኛ!´ እያሉ ይቆጣሉ፡፡

ብርዱ እየከፋ፣ ዝናሙ እየጨመረ መጣ፡፡ ንጉሡም ጥርሳቸውን እያፋጩ፣ ሰውነታቸው በብርድ እየተርገፈገፈ፣ ብርዱ አጥንታቸው ድረስ እየሠረሠራቸውም ቢሆን ከመሳቅና፣ ፈገግ ከማለት፣በደስታ እጃቸውን ለሕዝቡ ከማንሣትና ራሳቸውን ከመነቅነቅ አልተቆጠቡም፡፡ ያ ሕፃን ልጅ ብቻ ከኋላ ከኋላ እየተከተለ «ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው፣

ኧረ ንጉሡ ራቁታቸውን ናቸው» እያለ ይጮኻል፡፡ በርሱ ላይ የሚደርሰው ርግማኑና ቁጣውም አሁንም እንደ ቀጠለ ነው፡፡

በመጨረሻ ግን ንጉሡ አልቻሉም፡፡ ብርዱ እና ዝናቡ ከዐቅማቸው በላይ ሆነ፡፡ ሰውነታቸው መርገፍገፍ፣ ጥርሳቸውም እንደ ገጠር ወፍጮ መፋጨት ጀመረ፡፡ ውጫዊ ማስመሰያ ውስጥን ሸፍኖ መቆየት የሚችለው ጥቂት ጊዜ ነውና ንጉሡም የውስጣቸው ሕመም እንደልብ ፈገግ ለማለት እና ደስተኛ ለመምሰል አላስቻላቸውም፡፡ የሆነውን ሳይሆን እንዲሆን የሚፈልጉትን ተቀብሎ መዝለቅ አይቻልም፡፡ ሽል ከሆነ ይገፋል፣ ቂጣ ከሆነ ይጠፋል፡፡

በድንገት ንጉሡ ሠረገላ ነጅውን «አቁም!» ብለው በቁጣ ተናገሩት፡፡ እርሱም ሳቁ ወደ ድንጋጤ ተለወጠበትና አቆመ፡ ፡ «ያ ሕፃን ልጅ ብቻ ነው እውነተኛ፡፡ አዎን እውነት ነው እኔ ራቁቴን ነኝ፡፡ ሁላችሁም ውሸታችሁን ነው፡፡ እኔም ውሸቴን ነው» አሉና ተቀመጡ፡፡ ባለሟሎቻቸውም የቀድሞ ካባቸውን ሰጧቸው፡፡

አንዳንዶቹ ባለሟሎች «እኛ ምን እናድርግ ራሳቸው ናቸው ለዚህ የበቁት» አሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ «ጥፋተኞቹ እኛ ሳንሆን ያኔ ተልከው ያላዩትን እንዳዩ አድርገው የተናገሩት ናቸው» ብለው ወቀሱ፡፡ የቀሩትም «ሰሚ አጥተን ነው እንጂ ኧረ እኛስ ተናግረን ነበር» ብለዋል፡፡ ከሕዝቡም አንዳንዶቹ «አላልኳችሁም፣ እኔ ቀድሞም ተናግሬ ነበር» ያሉ አሉ፡፡ «ድሮም ነገሩ አላማረኝም ነበር» ያሉም ነበሩ፡፡

አንደኛው ሰውዬ ደግሞ ሁሉንም ያስደነቀ ነገር ተናገረ፡፡

«ለዚያ ሕፃን ልጅ ንጉሡ ራቁታቸውን መሆናቸውን የነገርኩትኮ እኔ ነኝ» ሲል፡፡

እነዚያ ሁለት ብልሃተኞች ግን ብራቸውን ይዘው የት እንደ ደረሱ እስካሁን አልታወቀም፡፡

38. [የብርጭቆው ወይስ የምንጩ ውኃ]

በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ኩሬ ብቻ ነበረ፡፡ የሀገሩም ሰዎች ውኃ የሚጠጡት ከዚያ ኩሬ ነው፡፡ አንድ ቀን የሀገሩ ሽማግሌዎች ለድግስ ተሰብስበው እያለ ውኃ ተቀዳ፡፡ ውኃው ግን ቆሻሻ ነበረ፡፡ ተጋባዦቹ በተቀዳላቸው ውኃ ተበሳጩና ሌላ ውኃ እንዲቀዳላቸው ጠየቁ፡፡ ነገር ግን በድጋሚ የተቀዳው ውኃም ቆሻሻ ነበረ፡፡ በዚህ ጊዜ ተጋበዦቹ በሃሳብ ለሁለት ተከፈለ፡፡ አንዳንዱ ችግሩ ከብርጭቆው ነውና ብርጭቆው መቀየር አለበት አለ፡፡ ሌላው ደግሞ የለም ሌላ ውኃ እንደገና መቀዳት አለበት አሉ፡፡

ክርክሩ እያየለ በመሄዱ ሁለቱም ነገሮች እንዲደረጉ ተወሰነ፡፡ ብርጭቆውም ተቀየረ፤ ውኃውም እንደገና ተቀዳ፡፡ ነገር ግን አሁንም ውኃው ንጹሕ ሊሆን አልቻለም፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ጠቢብ አዛውንት አንድ ሃሳብ አመጡ፡፡ «እስኪ ውኃው የሚቀዳበት ኩሬ ይታይ» ሲሉ፡፡

እርሳቸው የሰጡትን ሃሳብ ተከትሎ ኩሬው ታየ፡፡ እውነትም ኩሬው ቆሸሾ ነበር፡፡ እኒያ ሽማግሌም «ውኃ እየቀያየርን ስንቀዳ፣ ብርጭቆም ስንቀይር የኖርነው እንዴው በከንቱ ነው፡፡ ችግሩ ከብርጭቆውም፣ ከተቀዳውም ውኃ አልነበረም፡ ፡ ችግሩ ከምንጩ ነበር» አሉ፡፡ ከዚያም የመንደሯ ሰዎች ተሰብስበው በመውረድ ኩሬውን ከልዩ ልዩ አቅጣጫ መጥተው ካበላሹት ቆሻሻዎች አጸዱት፡፡ የመንደርዋም ነዋሪ ንጹሕ ውኃ መጠጣት ጀመረ ይባላል፡፡

ይህ ታሪክ ከቤተ ክህነታችን ታሪክ ጋር ይመሳሰላል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክህነት ያጋጠመውን ፈተና በተመለከተ ከምእመናንም ሆነ ከተቆርቋሪ ወገኖች ሁለት ዓይነት መፍትሔዎች ይሰማሉ፡፡ የመጀመርያው ችግር ፈጠሩ የምንላቸውን ሰዎች በሌሎች ሰዎች መተካት መፍትሔ ነው የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የቤተ ክርስቲያንዋን ሕንፃዎች፣ቢሮዎች፣ መኪናዎች፣ ወዘተ መቀየር ችግሩን ይፈታል ብሎ የሚያምን ነው፡፡

የሰዎች መለዋወጥ ችግሮችን በመጠኑም ቢሆን አይፈታም ተብሎ አይታመንም፡፡ ከዚህም በላይ የተሻ ሰዎች ለተሻለ ዕድገት የእመርታ መሠረቶችም ይሆናሉ፡፡ ወይንም ደግሞ ዕድገቱን በማፋጠን፣ተፈላጊውን ለውጥ በማቀላጠፍ እና ውጤቱን በማስቀጠል ከፍተኛ ሚናም ይኖራቸዋል፡፡

ነገር ግን የግለሰቦች መለዋወጥ ብቻውን የቤተ ክህነቱን ችግር አይፈታም፡፡ ሕመሙን በመጠኑ ይቀንሰው ካልሆነ በስተቀር፡፡

አንዳንድ ወገኖች የቤተ ክህነቱን ችግሮች ከሥር ከመሠረታቸው ስለማናያቸው አሁን የተፈጠሩ ወይንም በተወሰኑ ግለሰቦች ምክንያት የተከሰቱ፤ ያለበለዚያም ደግሞ እንግዴ ክስተት አድርገን እናያቸዋለን፡፡ ብዙዎቹ ፈተናዎች ግን ዛሬ ተባብሰው፣ ወይንም መኖራቸውን ራሳቸው በራሳቸው ገልጠው፣ ያለበለዚያም እኛ ለማወቅ ችለን ይሆናሉ እንጂ እዚያው ቤተ ክህነቱ ውስጥ ተወልደው ያደጉ ናቸው፡፡

ለምሳሌ ቁልፍ ፈተናዎቻችን የሆኑት ዘረኛነት፣ ፖለቲካዊ ጥገኛነት እና ያልተስተካከለ አሠራር ዛሬ የተጀመሩ ነገሮች አይደሉም፡፡

በቤተ ክህነቱ ታሪክ የሸዋ፣ የጎጃም፣ የጎንደር፣ የትግሬ እየተባሉ የሚነገርላቸው ዘመናት አሉ፡፡ እነዚህ ዘመናት ያለ ሃፍረት ሲነገሩ ስንሰማ ዘረኛነት ሥር ሰድዶ የኖረ ፈተና እንጂ ዛሬ የመጣ ወረርሽኝ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡ አልፎ አልፎ እንደነ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልእ ያሉ አበው ከንፍሮ መካከል እንዳመለጠች ጥሬ ይህንን ፈተና ቢያልፉትም ብዙዎች ግን «እገሌ ያገሬ ሰው ስለሆነ» እያሉ በኩራት መናገርን፣ መመካትን እና መጠቀምን ያለ መሸማቀቅ ሲተገብሩት ኖረዋል፡፡

በውጭ ሀገር እየኖረ ይህንን እቃወማለሁ የሚለው ወገኔም ቢሆን ቤተ ክርስቲያኑን በታቦቱ ስም ከመጥራት ይልቅ በወንዙ እና በጎጡ መጥራት የሚቀናው ነው፡፡ «የነ እገሌ ቤተ ክርስቲያን» የሚባል ኑፋቄም፣ ዕብደትም የሆነ አመለካከት እንደልቡ እጁን ከትቶ የሚጓዘው እዚያው ባሕር ማዶ ነው፡፡

አንዳንዱም ቢሆን እነ እገሌ የሚያደርጉትን የሚቃወመው የርሱ ወገኖች ስላልሆኑ እንጂ ተግባሩ ስሕተት ስለሆነ አይደለም፡፡ ያለበለዚያማ «እነ እገሌ እዚያኛው ቤተ ክርስቲያን ሞልተውታል» እያሉ እያማረሩ ለራስ ወገን እና አመለካከት ብቻ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ማነፅ መች ይኖር ነበር፡፡ አንዳንዴ እንዲያውም ጥፋቱን ለምን እኛ አላጠፋነውም የሚባል ሁሉ ይመስላል፡፡ ከዚያም ባስ ሲል የአንዳንዶቻችን እምነት «የጎመን ምንቸት ውጣ የሥጋ ምንቸት ግባ» ዓይነት ነው፡፡

ፖለቲካውን መንተራሱንም ቢሆን ከጥንት ለምደነው የመጣን ነው፡፡ ቤተ ክህነቱ ከቤተ መንግሥቱ ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ መኖሩ ጠቅሞታል? ወይስ ጎድቶታል? በሚለው ላይ እንወያይ ካልሆነ በቀር አብረው አልሠሩም ማለት ግን

አይቻልም፡፡ በርግጥ አንዳንዶቹ ይህንን ክስተት የኢትየጵያ ብቸኛ ክስተት እያደረጉ ሊያወግዙበት ይነሣሉ፡፡ ነገር ግን ቤተ ክህነቱ ቤተ መንግሥቱን ተጠቅሞ ለሀገር ፣ለወገን፣ ለወንጌል መስፋፋት እና ለድኅነት የሚጠቅም ሥራ እስከሠራ ድረስ ለምን አብራችሁ ሆናችሁ ተብሎ ሊወቀስ አይችልም፡፡ ከጥንቶቹ የነአብጋርን እና የነቆስጠንጢኖስን፣ ከሀገራችን የነአብርሃ እና አጽብሃ፣ የነካሌብን እና የነ ገብረ መስቀልን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ነገር ግን ቤተ ክህነቱ በቤተ መንግሥቱ አሉታዊ ተጽዕኖ ውስጥ ወድቆ መለካዊ /ፈቃድ ፈጻሚ/ ከሆነ ግን ችግር ነው፡፡ ትናንትም ሆነ ዛሬ በዘመናዊው ዓለም ቤተ መንግሥቱን በማቅናትም ሆነ በማገዝ፣የቤተ መንግሥቱንም እገዛ በመጠቀም የሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ የሩሲያን፣ የአርመንያን፣ የግሪክን አብያተ ክርስቲያናት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በሀገራችንም በንጉሡም፣ በደርግም ሆነ በኢሕአዴግ ዘመን ቤተ ክህነቱ ከቤተ መንግሥቱ ጋር ሠርቷል፡፡ ሁለቱም ተከባብረው እና ተጠባብቀው፣ ነጻነታቸውን ጠብቀው እና ተረዳድተው እስከ ሠሩ ድረስ ሁለቱም ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ሲፈርስ ግን ወይ ሁለቱም አለያም ቢያንስ አንዱ ይጎዳሉ፡፡

እስካን ባሉኝ መረጃዎች ከቤተ ክህነት ውጭ በሆኑ ጸሐፍት ለፖለቲካ እና ለዘር በነበራቸው አመለካከት የተደነቁት ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው፡፡ በዘመናቸው የነበሩ የደርግ አባላት በጻፏቸው መጻሕፍት ይህ አቋማቸው በአድናቆት ተዘክሯል፡፡ ለምሳሌ «ነበር» በተሰኘው የዘነበ ፈለቀ ክፍል ሁለት መጽሐፍ ላይ «ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ብጹእ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደራሴ የመሆን ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ በብዙ ልመናና ማግባባት «እሺ እንዳላችሁ ይሁን» ከአሉ በኋላ የእጩ ተመራጭነት ቅፅ እንዲሞሉ ተሰጥቷቸው በመጠይቁ መሠረት በማከናወን ላይ እንዳሉ «ብሔረሰብ» የሚል ረድፍ ላይ እንደደረሱ «አልፈልግም ያልኳችሁ ለዚህ ነው፡፡ እኔ በየትም ቦታ፤ በማንኛውም ጊዜ የምወክለው ሃይማኖቴንና ምእመናንን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ወኪል የመሆን ተልዕኮ የለኝም፤ እንዲኖረኝም አልፈልግም፡፡» ብለው በማንኛውም ሁናቴ የፖለቲካ ወጋግራ መሆን እንደማይሹ በጠንካራ አንደበት ተናገሩ፡፡በቅጹም ላይ ሳይፈርሙበት «ያውላችሁ» ብለው ሊሄዱ ተነሡ፡፡ «ኧረ ግድ የለም ይተውት ብጹዕ አባታችን» ተብለው ያመኑበትን ብቻ በቅፁም ላይ አስፍረው ያላመኑበትን ትተው ፈረሙ» ይላል፡፡ ገጽ 107

ቤተ ክርስቲያን በግብጻውያን ጳጳሳት መመራቷ የራሱ የሆነ ጥቅም እና ጉዳት ነበረው፡፡ ከጉዳቱ አንዱ ጠንካራ፣ በዘመናት የተፈተነ እና ሥር የያዘ ቤተ ክህነት እንዳይኖረን ማድረጉ ነው፡፡ የቤተ ክህነቱን ሥራ ነገሥታቱ እና ግብፃውያን ጳጳሳቱ ከካህናተ ደብተራ ጋር ብቻ በመሆን ማከናወናቸው የቤተ ክርስቲያንዋን እድሜ ግማሽ እንኳን ያለው ቤተ ክህነት እንዳይኖረን አድርጓል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ ብቸኛ የትምህርት ተቋም በነበረች ጊዜ ለራስዋም ሆነ ለሀገሪቱ የሚሆን የተማረ የሰው ኃይል ታመረት ነበር፡፡ ለቅዳሴው፣ ለማኅሌቱ፣ ለአቋቋሙ፣ ለሰዓታቱ፣ ለትርጓሜው፣ ለቅኔው፣ለድጓው የሚሆን የሰው ኃይል ራስዋ በራስዋ ታወጣ ነበር፡፡ ቤተ ክህነት በዘመናዊ መንገድ ሲቋቋም ግን የሕግ ጉዳይ፣የሂሳብ ጉዳይ፣የሥራ አመራር ጉዳይ፣ የመዝገብ አያያዝ ጉዳይ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ጉዳይ ጉዳዮቿ ሆኑ፡፡

ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማቀድ፤ አዲት ማድረግ፣ ሕንፃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማሠራት እና ማስተዳደር፤ ዘመናዊ ት/ቤቶችን ማቋቋም እና ማስተዳዳር፣ የጤና ተቋማትን ማቋቋም እና ማስተዳደር፣ የንግድ ቦታዎችን ማስተዳደር ወዘተ ተጨማሪ ሥራዎቿ ሆኑ።

ነገር ግን ለእነዚህ ተግባራት የሚሆን የሰው ኃይል ማምረቻ የላትም። ከሚያመርቱ ተቋማትም አትወስድም። በሚሊዮን ብሮች ታንቀሳቅሳለች፤ በበቂ የሰው ኃይል የተደራጀ የፋይናንስ መምሪያ ግን የላትም። ሌላው ቀርቶ «ፒች ትሪ አካውንቲንግ» እንኳን እንደ ናፈቃት ሊቀር ነው። አንዱ ደብር ገንዘብ ላይ ይተኛል፣ ሌላው ደብር ጧፍ ይለምናል። ተመሳሳይ ሞያ ያላቸው አገልጋዮች በቦታ መለያየት ብቻ የሰማይ እና የምድር ያህል ርቀት ያለው ደሞዝ ያገኛሉ።

የ35000 አብያተ ክርስቲያናት የሕግ ጉዳይ ይመለከታታል፤ ነገር ግን በቂ የሰው ኃይል የያዘ የሕግ መምሪያ የላትም። ስንት በፒ ኤች ዲ፣ ስንት በዲግሪ? ስንት በዲፕሎማ የተማረ፤ የራስዋንም የሕግ ሥርዓት የጠነቀቀ ባለሞያ አሠማርታለች? ቢባል መልሱ ከባድ ነው።

ብዙ ሕንፃዎች ታስገነባለች፣ አንድ ክፍለ ከተማ እንኳን ያለውን የግንባታ ባለሞያ የላትም። አያሌ ዘመናዊ ት/ቤቶች በሥርዋ አሉ፤ ነገር ግን የትምህርት ሚኒስቴር በሥርዋ የላትም፤ አያሌ የጤና ተቋማት አሏት፣ ነገር ግን የጤና ቢሮ አላደራጀቻም፤ ብዙ ይጠበቅባታል፣ ነገር ግን ቢያንስ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የላትም። ከ45 ሚሊዮን በላይ ምእመን አላት፤ ነገር ግን ከ3000 በላይ የሚታተሙ መጽሔት እና ጋዜጦች የሏትም፤ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መመለሱ እና ደቀ መዛሙርትን ማፍራቱ እሰየው የሚያሰኝ ቢሆንም አደረጃጀቱ ግን አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሚያስፈልጋት የሰው ኃይል አንፃር ባለመቃኘቱ ችግርዋን ሊቀርፍላት አልቻለም። ለምሳሌ ያህል ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲን መንፈሳዊ እና ዓለማዊ/secular/ ኮርሶችን እንዲሰጥ አድርጎ ማዋቀር ይቻል ነበር። በአንድ በኩል ነገረ መለኮትን በሌላ በኩል አስተዳደርን፣ ሕግን፣ የሂሳብ አያያዝን፣ የቅርስ አጠባበቅን፣ አንትሮፖሎጂን፣ ፊሎሎጂን፣ የኮምፒውተር ሳይንስን፣ ታሪክን፣ ኢኮኖሚክስን እና ሌሎችን የተማረ፤ በሁለት በኩል የተሳለ የሰው ኃይል እንዲያፈራ ቢደረግ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን የት በደረሰች ነበር።

እነ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ፣ እነ መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬ፣እነ አለቃ አያሌው፣ እነ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን፣ እና ሌሎቹም በዕውቀት እና በሕይወት ያስጌጧት ቤተ ክህነት ዛሬ ለጋዜጠኛ መልስ ለመስጠት የሚበቃ ሰው እያጣች መምጣቷ የደረሰችበትን ደረጃ ያሳያል። አንድ በዘመድ የተቀጠረ ጨዋ ሰው በአንድ የቤተ ክህነት ስብሰባ ላይ ንግግር ያደርጋል አሉ። ሊቁ ደግሞ ከኋላው ተቀምጠዋል። የርሱ ደመወዝ 1500 ብር፣ የርሳቸው ደመወዝ 400 ብር ነው። በንግግሩ መጽሐፍ ጠቀስኩ ይልና ግእዙን ይሰባብረዋል። ሊቁ አላስችላቸው ብሎ «ምናለ መጀመርያ ብትማር» ይሉታል። እርሱም ዘወር ብሎ «ብማርማ ኖሮ እንደርስዎ በ400 ብር ደመወዝ መቅረቴ ነበር» አላቸው አሉ።

የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ እንኳን የመንግሥት መ/ቤቶችን አሠራር ለማስተካከል ስንት ጊዜ ማሻሻያ ተደርጓል፤ መዋቅር ተቀይሯል፣ ቢፒ አር እና ካይዘን ተተግብሯል። ቤተ ክህነት ግን መዋቅሯን ለማስጠናት፣ ለማሻሻል፣ እንደ ቢ ፒ አር እና ካይዘን የመሳሰሉ የአሠራር ማሻሻያ መንገዶችን ለመተግበር አልሞከረችም። ቢያንስ ሩቅ ሳትሄድ ከመንግሥት እንኳን መማር አልቻለችም።

እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት ሥር የሰደደ እና ከትናንት ጀምሮ የተያያዘ የአሠራር ችግር መኖሩን ነው፡፡ ዛሬ የምናየው የአሠራር ችግር የእነዚህ ሁሉ ትብትቦች ውጤት ነው፡፡

እናም እነዚህ በሽታዎች በአጠቃላይ መልኩ የሚፈታ፣ ምንጫቸውን የሚያስተካክል ነገር ካልመጣ በቀር፣ እንደኔ እምነት ሰዎችን በመቀያየር ብቻ የቤተ ክህነቱን አሠራር ውጤታማ እና ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመጥን ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ታድያ መፍትሔው ምንድን ነው?

እንደኔ እንደኔ የቤተ ክህነትን ችግሮች ለመፍታት ቁልፍ መፍትሔዎች **አራት «መ»ዎች** ናቸው፡፡

1/***መረዳት፡*** የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉዞ፣ የነበረባትን ፈተና እና የቤተ ክህነቱን የችግር ምንጮች በሚገባ መረዳት ማለት ነው፡፡ ከስሜታዊነት፣ ከወገንተኛነት እና ለእኔ ይድላኝ ከሚሉ ስሜቶች ርቀን፤ ችግሩን በሚገባ መገንዘብ አለብን፡፡ ችግሩን በሚገባ ካልተረዳን፤ የቤተ ክህነትን እና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት እና ልዩነት ካልተገነዘብን፤ የምንሰጠው መፍትሔ «እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውን እንዳትነ ቅሉት» የተባለውን የወንጌል ሕግ የሚያፈርስ ይሆናል፡፡

2/መሳተፍ፡ የቤተ ክርስቲያንን ፈተናዎች በምኞት እና በቅን ሃሳብ፣ በቁጭት እና በመብከንከን ብቻ መፍታት አይቻልም፡፡ ራስን የመፍትሔው አካል ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ከምኞት እና ከንዴት ያለፈ ተግባር ያሻል፡፡ በእግር ኳስ ሜዳ ዋንጫ በተመልካች ድጋፍ እና ፍላጎት አይመጣም፡፡ በተጨዋቾች ጥንካሬ እና ተጋድሎ እንጂ፡፡ ዋንጫ በተመልካች ድጋፍ የሚመጣ ቢሆን ኖሮ የዘንድሮውን የዓለም ዋንጫ መውሰድ የነበረባት ደቡብ አፍሪካ ነበረች፡፡

በክርስትና ጉዞም ያለ ክርስቲያኖች ሱታፌ የሚፈታ ችግር የለም፡፡ አንዳንዶች የሚፈልጉት ነገር እንዲሁ እንዲመጣ ይሻሉ፡፡ አንዳንዶችም የተወሰኑት ሰዎች በሚያደርጉት ተጋድሎ እየተደሰቱ ይቀመጣሉ፡፡ ሌሎችም እናንተ ለምን እንዲህ አታደርጉም? ለምን እንዲህ ወይንም እንዲያ አይደረግም? እያሉ ስለጠየቁ ድርሻቸውን የተወጡ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ ግን መፍትሔ አያመጣም፡፡ እያንዳንዳችን የምንችለውን ስናደርግ እንጂ፡፡

አንዳንዶቻችን ደግሞ «አሁን የኔ ብቻ መሮጥ፣ መጋደል፣ መፍጨርጨር ምን ለውጥ ሊያመጣ ነው? እነ እገሌ እና እነ እገሌ ዝም ብለው፣ እነ እገሌ የተውትን እኔ ምን አለፋኝ? አሁን ለመሆኑ እኔን ማን ከሰው ሊቆጥረኝ ነው?» ይላሉ፡፡ አንድ ነገር እናስብ፡፡ በማቴ 25 ላይ ጌታችን በዳግም ምጽአት ይጠይቃቸዋል የተባሉትን ጥያቄዎች እናስብ፡፡ «ተርቤ ለምን አላበላኸኝም?» አለ እንጂ «ረሃብን ከምድረ ገጽ ለምን አላጠፋህም?» አላለም፡፡ «ታሥሬ ለምን አልጠየቅኸኝም?» አለ እንጂ «እሥር ቤቶችን ለምን አላጠፋህም?» አላለም፡፡ ይህ ምን ያሳየናል? የዐቅማችንን ማድረጋችንን እንጂ ጠቅላላውን ችግር መፍታታችንን እግዚአብሔር አይጠይቅም ማለት ነው፡፡ ችግሩን መፍታት መቻል እና ለመፍትሔው አስተዋጽዖ ማድረግ ይለያያሉ፡፡ ለመፍትሔው መነሣት የኛ፤ ችግሩንም መፍታት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፡፡

3/***መሠዋት***፡ ክርስትና በመስቀል ላይ የተመሠረተ ነውና ያለ መሥዋዕትነት ሊጓዝ አይችልም፡፡ ከመስቀል የወረደ ክርስትናም ክርስትና አይሆንም፡፡ ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ለመክፈል ካልተዘጋጀን፤ ምንም ዓይነት ችግርን አንፈታም፡፡ የምናጣው ክብር፣ ዝና፣ ስም፣ ገንዘብ፣ ሥልጣን መኖር አለበት፡፡ መሸነፍን መቀበል አለብን፡፡ ይህ ነው ሰማዕትነት፡፡ ጌታችን ተሸንፎ አሸነፈ፡፡ እኛስ? ክንፍ ለማግኘት እግርን ማጣት ያስፈልጋልኮ፤ እኛስ?

ብዙዎቻችን ምናችንም እንዲነካ አንፈልግም፡፡ በሚጋደሉ ሰዎች ላይ ግን እንፈርዳለን፡፡ ጥቂት መሥዋ ዕትነትም ለመክፈል ዝግጁ አይደለንም፤ ብዙ ሃሳቦችን ግን እንሰነዝራለን፡፡ እነ እገሌን እንዲሠው እንነተ ጉታለን፤ እኛ ግን የእሳቱ ጢስ እንኳን እንዲነካን አንሻም፡፡ ቀደምት ኢትዮጵያውያን አበው «ሰማዕትነት አያምልጥህ» ይሉ ነበር፤ የአሁኖቹ ደግሞ «ሰማዕትነት አይድረስብህ» ነው የምንለው፡፡ ዋንጫው ከተገኘ «አለንበት» እንላለን፤ ዋንጫው ከጠፋ ግን «እኔ የለሁበትም» ነው መልሳችን፡፡ ታድያ እንዴት መፍትሔ ይገኛል፡፡ ለመሆኑ በተጋድሎ እንጂ በስብሰባ የተሸነፈ ሰይጣን አለ? በሰማዕትነት እንጂ በሃሳብ ብዛት ድል የተደረገ ፈተና አለ?

መሥዋዕትነቱን ከባድ የሚያደርገው ከቤተ ክርስቲያን ችግር የሚያተርፉ ወገኖች ስላሉ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ችግሩን ይፈልጉታል፡፡ በችግሩ ቤተ ክርስቲያን ብትጎዳም እነርሱ ያተርፉሉና፡፡ ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን አንድ ከሆነች «የላይ ፈሪ የታች ፈሪ» እያሉ የሚያምታቱ ሰዎች ቦታ ያጣሉ፤ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርዋ ከተጠናከረ ያለ ዕውቀት እና ያለ ዐቅም በዝምድና ብቻ ውጭ መውጣት ይቀራል፤ ያለ ችሎታ እና ያለ በቂ ሕይወት መመንኮስ ይቀራል፣ ክህነት መቀበል ይቀራል፣ መሾም ይቀራል፣ የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ሥርዓት ከተስተካከለ መዝረፍ ይቀራል፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ከጠነከረ እዚህም እዚያም ቤተ ክርስቲያን መክፈትና ገንዘብ መሰብሰብ ይቀራል፤ ያለ ችሎታ እና ብቃት ጵጵና ማግኘት ይቀራል፤ ስለዚህም ችግሩ እንዲቀጥል ይፈለጋል፡፡

እስኪ ተመልከቱ ቀድሞ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ተአምር ሰምተው ነበር የሚመለሱት፤ እምነቱ፣ ጠበሉ፣ ገድሉ፣ ድርሳኑ ያደረጉትን ተአምር ይሰማሉ፡፡ እኛ ግን ምንድን ነው የምንሰማው? ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ እገሌ እና እገሌ ተደባደቡ፣ ተለያዩ፣ እንዲህ እና እንዲያ ተባባሉ፣ እንዲህ ያለ ሥርዓት ፈረሰ፤ እንዲህ ያለ ኑፋቄ ተሰጠ፡፡ ጆሮዎቻችንኮ በጎ ነገር ናፈቃቸው፤ ይህ እንዲመጣ ግን ተጋድሎ እና ሰማዕትነት የግድ ይላል፡፡ «እንበለ መከራ ኢይትረከብ ጸጋ» ነውና፡፡ ያለ ሕማማት ፋሲካ የለም፡፡

4/***መንፈሳዊነት***፡ የመጨረሻው፣ ግን ወሳኙ ነገር ነው፡፡ መንፈሳውያን በሌሉበት ቦታ መንፈሳዊ ነገር መፍትሔ አያገኝም፡፡ መንፈሳዊነት ማለት የሃይማኖትን ትምህርት ማወቅ፤ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፤ የቃል ጸሎትን መሸምደድ፣ የቤተ ክርስቲያንን መዓርጋት መያዝ፤ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ማገልገል ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ መንፈሳዊነትን የሚያጎለብቱ ነገሮች እንጂ በራሳቸው መንፈሳዊነት አይደሉም፡፡

መንፈሳዊነት ኑሮ ነው፤ አመለካከት ነው፤ ሕይወት ነው፤ ቅኝት ነው፡፡ መንፈሳዊነት በፈሪሃ እግዚአብሔር ተቃኝቶ፤ በቃለ እግዚአብሔር ተመርቶ፤ መንፈሳዊን ጥበብ ገንዘብ አድርጎ ውስጥን መለወጥ ነው፡፡

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በምንም መንገድ ካልፈራ፤ ቃለ እግዚአብሔርን ከተለማመደው፤ የማያምንባቸውን ነገሮች ለሥነ ሥርዓት ሲል ብቻ የሚያደርግ ከሆነ፤ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ነገር ከስሕተቱ ካላቆመው፤

«እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር» ከሚባልበት ደረጃ ደርሷል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው የተአምራት ቅጣት እንጂ ምክር እና ተግሣጽ አይመልሰውም፡፡

በመሆኑም የሳኦልን ኃጢአት የሚመክት የዳዊት መንፈሳዊነት፤ የኤልዛቤልን ኃጢአት የሚመክት የኤልያስ መንፈሳዊነት፤ የድርጣድስን ኃጢአት የሚመክት የጎርጎርዮስ መንፈሳዊነት፤ የብርክልያን ኃጢአት የሚመክት የዮሐንስ አፈወርቅ መንፈሳዊነት፤ የግራዚያኒን ኃጢአት የሚመክት የአቡነ ጴጥሮስ መንፈሳዊነት፤ ያስፈልጋል፡፡

አንድ የጥንት አባት «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቁ ችግር የሚፈጠረው መንፈሳውያን ያልሆኑ ሰዎች መንፈሳዊ ሥራ ሲሠሩ ነው» ብሎ ነበር፡፡ ያልመነኑ ሰዎች ከመነኮሱ፤ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ከቀሰሱ፤ እግዚአብሔርን የማያውቁት ሰዎች ካስተማሩ፤ ደመወዝ፣ቤት እና መኪና የሚያጓጓቸው ሰዎች ከጳጳሱ፤ ፍትፍት ያልሰለቻቸው ሰዎች ባሕታውያን ከሆኑ፤ የዘር ዛር ያልለቀቃቸው ሰዎች የሁሉ አባት ከተባሉ፤ከራሳቸው ጋር ያልታረቁ ሰዎች ለታራቂነት እና አስታራቂነት ከተቀመጡ፤ መንፈሳዊነት ሽታውም ጠፍቷል ማለት ነው፡፡

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ለመንፈሳዊ ችግሮች የታክቲክ እና የቴክኒክ እንጂ የመንፈስ መፍትሔ ስንፈልግ የማንገኘው፡፡

አንዳንድ ጊዜኮ እኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለን፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ከእኛ ውስጥ ወጥታለች፤ እኛ በክርስትና ውስጥ ነን፤ ክርስትና ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤እኛ በክህነቱ ልብስ ውስጥ ነን፤ ክህነቱ ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤ እኛ በስብከቱ ቀሚስ ውስጥ ነን፤ ስብከቱ ግን ከውስጣችን ወጥቷል፡፡ እኛ በገዳም እንኖራለን፤ ገዳማዊ ሕይወት ግን በኛ ውስጥ የለም፡፡ ለአንዳንዶቻችን ጵጵስና ፕሮፌሽን ነው፤ ቅስና ፕሮፌሽን ነው፣ ሰባኪነት ፕሮፌሽን ነው፤ ምንኩስና ፕሮፌሽን ነው፤ዝማሬ ፕሮፌሽን ነው፣ እንደ ጥብቅና፣ እንደ ንግድ፣ እንደ ሕክምና፣ እንደ ጋዜጠኛነት፣ እንደ ምሕንድስና፣ የእንጀራ ማግኛ ሞያ፡፡ ታድያ እንዴት መንፈሳውያን መሆን ይቻላል?

በመጽሐፈ መነኮሳት እንደ ተጻፈው በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆነው እንደ ቤተ ክህነት የሚኖሩ፣ በቤተ ክህነትም ሆነው እንደ ቤተ መንግሥት የሚኖሩ ነበሩ፤ አሉ፡፡ ይሁዳ በአካል ከክርስቶስ ጋር ነበር፤ ልቡ ግን ከነ ሊቀ ካህናት ቀያፋ ጋር ጌታን ለመስቀል ያድማል፤ ማርያም እንተ እፍረት በአካል ከአመንዝሮች ጋር ነበረች፤ ልቧ ግን ከርስቶስን ይፈልግ ነበርና ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፡፡ ይሁዳም ልቡ ወዳለበት ሄደ፤ ማርያምም ልቧ ወደ ነበረበት መጣች፡፡ ለመሆኑ ከሁለቱ ሰዎች መንፈሳዊው ማን ነበር?

በአንድ ወቅት አንድ አባት የተናገሩትን እዚህ ላይ ማንሣት ያስፈልጋል፡፡ ለስብሰባ ወደ አንድ መንግሥታዊ ድርጅት ሄጄ ከባለሥልጣናት ጋር ተሰብስቤ ነበር፡፡ በስብሰባው መካከል አንደኛው ባለ ሥልጣን በግእዝ ሲጠቅስ ሰማሁት፤ ተገረምኩ፡፡ ስብሰባው ሲያበቃ ጠብቄ ያንን ሰው «አንተ የቤተ ክህነት ሰው ነህ እንዴ? ቅድም አንድ ነገር ስትናገር ሰምቼሃለሁ» አልኩት፡፡ ሰውዬውም «አዎ ነኝ፤ ምነው ገረመዎት እንዴ» አለኝ፡፡ «የቤተ ክህነት ሰው እንዲህ ባለ ሥፍራ ይኖራል ብዬ አልገምትም ነበር?» ብዬ መለስኩለት፡፡ እርሱም «አባቴ የቤተ ክህነት ሰውኮ በየቦታው አለ፡፡ የቤተ ክህነት ሰው የሌለው ቤተ ክህነት ውስጥ ብቻ ነው» አለኝ ብለው ነገሩን፡፡

ዋናው መፍትሔው ይሄው ነው፡፡ የቤተ ክህነት ሰው በቤተ ክህነት እንዲያገለግል ማድረግ፡፡

እኔ በቀጣይ ማከሰኞ የማቀርባቸው **ሃያ ዝርዝር የመፍትሔ ሀሳቦች** አሉ፡፡ የእናንተንም አስቡበት፡፡ ጊዜው አንድ ልብ ሆነን ለአንዲት እምነት የምንነሣበት ነውና፡፡
ቤተ ክርስቲያን በግብጻውያን ጳጳሳት መመራቷ የራሱ የሆነ ጥቅም እና ጉዳት ነበረው፡፡ ከጉዳቱ አንዱ ጠንካራ፣ በዘመናት የተፈተነ እና ሥር የያዘ ቤተ ክህነት እንዳይኖረን ማድረጉ ነው፡፡ የቤተ ክህነቱን ሥራ ነገሥታቱ እና ግብፃውያን ጳጳሳቱ ከካህናተ ደብተራ ጋር ብቻ በመሆን ማከናወናቸው የቤተ ክርስቲያንዋን እድሜ ግማሽ እንኳን ያለው ቤተ ክህነት እንዳይኖረን አድርጓል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ ብቸኛ የትምህርት ተቋም በነበረች ጊዜ ለራስዋም ሆነ ለሀገሪቱ የሚሆን የተማረ የሰው ኃይል ታመረት ነበር፡፡ ለቅዳሴው፣ ለማኅሌቱ፣ ለአቋቋሙ፣ ለሰዓታቱ፣ ለትርጓሜው፣ ለቅኔው፣ለድጓው የሚሆን የሰው ኃይል ራስዋ በራስዋ ታወጣ ነበር፡፡ ቤተ ክህነት በዘመናዊ መንገድ ሲቋቋም ግን የሕግ ጉዳይ፣የሂሳብ ጉዳይ፣የሥራ አመራር ጉዳይ፣ የመዝገብ አያያዝ ጉዳይ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ጉዳይ ጉዳዮቿ ሆኑ፡፡

ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ማቀድ፤ አዲት ማድረግ፣ ሕንፃዎችን በዘመናዊ መንገድ ማሠራት እና ማስተዳደር፤ ዘመናዊ ት/ቤቶችን ማቋቋም እና ማስተዳደር፣ የጤና ተቋማትን ማቋቋም እና ማስተዳደር፣ የንግድ ቦታዎችን ማስተዳደር ወዘተ ተጨማሪ ሥራዎቿ ሆኑ፡፡

ነገር ግን ለእነዚህ ተግባራት የሚሆን የሰው ኃይል ማምረቻ የላትም፡፡ ከሚያመርቱ ተቋማትም አትወስድም፡፡ በሚሊዮን ብሮች ታንቀሳቅሳለች፤ በበቂ የሰው ኃይል የተደራጀ የፋይናንስ መምሪያ ግን የላትም፡፡ ሌላው ቀርቶ «ፒች ትሪ አካውንቲንግ» እንኳን እንደ ናፈቃት ሊቀር ነው፡፡ አንዱ ደብር ገንዘብ ላይ ይተኛል፣ ሌላው ደብር ጧፍ ይለምናል፡፡ ተመሳሳይ ሞያ ያላቸው አገልጋዮች በቦታ መለያየት ብቻ የሰማይ እና የምድር ያህል ርቀት ያለው ደሞዝ ያገኛሉ፡፡

የ35000 አብያተ ክርስቲያናት የሕግ ጉዳይ ይመለከታታል፤ ነገር ግን በቂ የሰው ኃይል የያዘ የሕግ መምሪያ የላትም፡፡ ስንት በፒ ኤች ዲ፣ ስንት በዲግሪ? ስንት በዲፕሎማ የተማረ፤ የራስዋንም የሕግ ሥርዓት የጠነቀቀ ባለሞያ አሠማርታለች? ቢባል መልሱ ከባድ ነው፡፡

ብዙ ሕንፃዎች ታስገነባለች፣ አንድ ክፍለ ከተማ እንኳን ያለውን የግንባታ ባለሞያ የላትም፡፡ አያሌ ዘመናዊ ት/ቤቶች በሥርዋ አሉ፤ ነገር ግን የትምህርት ሚኒስቴር በሥርዋ የላትም፤ አያሌ የጤና ተቋማት አሏት፣ ነገር ግን የጤና ቢሮ አላደራጀቻም፤ ብዙ ይጠበቅባታል፣ ነገር ግን ቢያንስ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የላትም፡፡ ከ45 ሚሊዮን በላይ ምእመን አላት፤ ነገር ግን ከ3000 በላይ የሚታተሙ መጽሔት እና ጋዜጦች የሏትም፤

የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መመለሱ እና ደቀ መዛሙርትን ማፍራቱ እሰየው የሚያሰኝ ቢሆንም አደረጃጀቱ ግን አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሚያስፈልጋት የሰው ኃይል አንፃር ባለመቃኘቱ ችግርዋን ሊቀርፍላት አልቻለም፡፡ ለምሳሌ ያህል ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲን መንፈሳዊ እና ዓለማዊ/secular/ ኮርሶችን እንዲሰጥ አድርጎ ማዋቀር ይቻል ነበር፡፡ በአንድ በኩል ነገረ መለኮትን በሌላ በኩል አስተዳደርን፣ ሕግን፣ የሂሳብ አያያዝን፣ የቅርስ አጠባበቅን፣ አንትሮፖሎጂን፣ ፊሎሎጂን፣ የኮምፒውተር ሳይንስን፣ ታሪክን፣ ኢኮኖሚክስን

እና ሌሎችን የተማረ፤ በሁለት በኩል የተሳለ የሰው ኃይል እንዲያፈራ ቢደረግ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን የት በደረሰች ነበር፡፡

እነ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ፣ እነ መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬ፣እነ አለቃ አያሌው፣ እነ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን፣ እና ሌሎቹም በዕውቀት እና በሕይወት ያስጌጧት ቤተ ክህነት ዛሬ ለጋዜጠኛ መልስ ለመስጠት የሚበቃ ሰው እያጣች መምጣቷ የደረሰችበትን ደረጃ ያሳያል፡፡ አንድ በዘመድ የተቀጠረ ጨዋ ሰው በአንድ የቤተ ክህነት ስብሰባ ላይ ንግግር ያደርጋል አሉ፡፡ ሊቁ ደግሞ ከኋላው ተቀምጠዋል፡፡ የርሱ ደመወዝ 1500 ብር፣ የርሳቸው ደመወዝ 400 ብር ነው፡፡ በንግግሩ መጽሐፍ ጠቀስኩ ይልና ግእዙን ይሰባብረዋል፡፡ ሊቁ አላስችላቸው ብሎ «ምናለ መጀመርያ ብትማር» ይሉታል፡፡ እርሱም ዘወር ብሎ «ብማርማ ኖሮ እንደርስዎ በ400 ብር ደመወዝ መቅረቴ ነበር» አላቸው አሉ፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ እንኳን የመንግሥት መ/ቤቶችን አሠራር ለማስተካከል ስንት ጊዜ ማሻሻያ ተደርጓል፤ መዋቅር ተቀይሯል፣ ቢፒ አር እና ካይዘን ተተግብሯል፡፡ ቤተ ክህነት ግን መዋቅሯን ለማስጠናት፣ ለማሻሻል፣ እንደ ቢ ፒ አር እና ካይዘን የመሳሰሉ የአሠራር ማሻሻያ መንገዶችን ለመተግበር አልሞከረችም፡፡ ቢያንስ ሩቅ ሳትሄድ ከመንግሥት እንኳን መማር አልቻለችም፡፡

እነዚህ ሁሉ የሚያመለክቱት ሥር የሰደደ እና ከትናንት ጀምሮ የተያያዘ የአሠራር ችግር መኖሩን ነው፡፡ ዛሬ የምናየው የአሠራር ችግር የእነዚህ ሁሉ ትብትቦች ውጤት ነው፡፡

እናም እነዚህ በሽታዎች በአጠቃላይ መልኩ የሚፈታ፣ ምንጫቸውን የሚያስተካክል ነገር ካልመጣ በቀር፣ እንደኔ እምነት ሰዎችን በመቀያየር ብቻ የቤተ ክህነቱን አሠራር ውጤታማ እና ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመጥን ማድረግ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ታድያ መፍትሔው ምንድን ነው?

እንደኔ እንደኔ የቤተ ክህነትን ችግሮች ለመፍታት ቁልፍ መፍትሔዎች **አራት «መ»ዎች** ናቸው፡፡

1/**መረዳት፡** የቤተ ክርስቲያኒቱን ጉዞ፣ የነበረባትን ፈተና እና የቤተ ክህነቱን የችግር ምንጮች በሚገባ መረዳት ማለት ነው፡፡ ከስሜታዊነት፣ ከወገንተኛነት እና ለእኔ ይድላኝ ከሚሉ ስሜቶች ርቀን፤ ችግሩን በሚገባ መገንዘብ አለብን፡፡ ችግሩን በሚገባ ካልተረዳን፤ የቤተ ክህነትን እና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት እና ልዩነት ካልተገነዘብን፤ የምንሰጠው መፍትሔ «እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውን እንዳትነ ቅሉት» የተባለውን የወንጌል ሕግ የሚያፈርስ ይሆናል፡፡

2/መሳተፍ፡ የቤተ ክርስቲያንን ፈተናዎች በምኞት እና በቅን ሃሳብ፣ በቁጭት እና በመብከንከን ብቻ መፍታት አይቻልም፡፡ ራስን የመፍትሔው አካል ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ከምኞት እና ከንዴት ያለፈ ተግባር ያሻል፡፡ በእግር ኳስ ሜዳ ዋንጫ በተመልካች ድጋፍ እና ፍላጎት አይመጣም፡፡ በተጨዋቾች ጥንካሬ እና ተጋድሎ እንጂ፡፡ ዋንጫ በተመልካች ድጋፍ የሚመጣ ቢሆን ኖሮ የዘንድሮውን የዓለም ዋንጫ መውሰድ የነበረባት ደቡብ አፍሪካ ነበረች፡፡

በክርስትና ጉዞም ያለ ክርስቲያኖች ሱታፌ የሚፈታ ችግር የለም፡፡ አንዳንዶች የሚፈልጉት ነገር እንዲሁ እንዲመጣ ይሻሉ፡፡ አንዳንዶችም የተወሰኑት ሰዎች በሚያደርጉት ተጋድሎ እየተደሰቱ ይቀመጣሉ፡፡ ሌሎችም እናንተ ለምን እንዲህ አታደርጉም? ለምን እንዲህ ወይንም እንዲያ አይደረግም? እያሉ ስለጠየቁ ድርሻቸውን የተወጡ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ ግን መፍትሔ አያመጣም፡፡ እያንዳንዳችን የምንችለውን ስናደርግ እንጂ፡፡

አንዳንዶቻችን ደግሞ «አሁን የኔ ብቻ መሮጥ፣ መጋደል፣ መፍጨርጨር ምን ለውጥ ሊያመጣ ነው? እነ እገሌ እና እነ እገሌ ዝም ብለው፣ እነ እገሌ የተውትን እኔ ምን አለፋኝ? አሁን ለመሆኑ እኔን ማን ከሰው ሊቆጥረኝ ነው?» ይላሉ፡፡ አንድ ነገር እናስብ፡፡ በማቴ 25 ላይ ጌታችን በዳግም ምጽአት ይጠይቃቸዋል የተባሉትን ጥያቄዎች እናስብ፡፡ «ተርቤ ለምን አላበላኸኝም?» አለ እንጂ «ረሃብን ከምድረ ገጽ ለምን አላጠፋህም?» አላለም፡፡ «ታሥሬ ለምን አልጠየቅኸኝም?» አለ እንጂ «እሥር ቤቶችን ለምን አላጠፋህም?» አላለም፡፡ ይህ ምን ያሳየናል? የዐቅማችንን ማድረጋችንን እንጂ ጠቅላላውን ችግር መፍታታችንን እግዚአብሔር አይጠይቅም ማለት ነው፡፡ ችግሩን መፍታት መቻል እና ለመፍትሔው አስተዋጽዖ ማድረግ ይለያያሉ፡፡ ለመፍትሔው መነሣት የኛ፤ ችግሩንም መፍታት የእግዚአብሔር ድርሻ ነው፡፡

3/***መሠዋት***፡ ክርስትና በመስቀል ላይ የተመሠረተ ነውና ያለ መሥዋዕትነት ሊጓዝ አይችልም፡፡ ከመስቀል የወረደ ክርስትናም ክርስትና አይሆንም፡፡ ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ለመክፈል ካልተዘጋጀን፤ ምንም ዓይነት ችግርን አንፈታም፡፡ የምናጣው ክብር፣ ዝና፣ ስም፣ ገንዘብ፣ ሥልጣን መኖር አለበት፡፡ መሸነፍን መቀበል አለብን፡፡ ይህ ነው ሰማዕትነት፡፡ ጌታችን ተሸንፎ አሸነፈ፡፡ እኛስ? ከንፍ ለማግኘት እግርን ማጣት ያስፈልጋልኮ፤ እኛስ?

ብዙዎቻችን ምናችንም እንዲነካ አንፈልግም፡፡ በሚጋደሉ ሰዎች ላይ ግን እንፈርዳለን፡፡ ጥቂት መሥዋ ዕትነትም ለመክፈል ዝግጁ አይደለንም፤ ብዙ ሃሳቦችን ግን እንሰነዝራለን፡፡ እነ እገሌን እንዲሠው እንጎተ ጉታለን፤ እኛ ግን የእሳቱ ጢስ እንኳን እንዲነካን አንሻም፡፡ ቀደምት ኢትዮጵያውያን አበው «ሰማዕትነት አያምልጥህ» ይሉ ነበር፤ የአሁኖቹ ደግሞ «ሰማዕትነት አይድረስብህ» ነው የምንለው፡፡ ዋንጫው ከተገኘ «አለንበት» እንላለን፤ ዋንጫው ከጠፋ ግን «እኔ የለሁበትም» ነው መልሳችን፡፡ ታድያ እንዴት መፍትሔ ይገኛል፡፡ ለመሆኑ በተጋድሎ እንጂ በስብሰባ የተሸነፈ ሰይጣን አለ? በሰማዕትነት እንጂ በሃሳብ ብዛት ድል የተደረገ ፈተና አለ?

መሥዋዕትነቱን ከባድ የሚያደርገው ከቤተ ክርስቲያን ችግር የሚያተርፉ ወገኖች ስላሉ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ችግሩን ይፈልጉታል፡፡ በችግሩ ቤተ ክርስቲያን ብትጎዳም እነርሱ ያተርፉሉና፡፡ ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን አንድ ከሆነች «የላይ ፈሪ የታች ፈሪ» እያሉ የሚያምታቱ ሰዎች ቦታ ያጣሉ፤ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርዋ ከተጠናከረ ያለ ዕውቀት እና ያለ ዐቅም በዝምድና ብቻ ውጭ መውጣት ይቀራል፤ ያለ ችሎታ እና ያለ በቂ ሕይወት መመንኮስ ይቀራል፣ ክህነት መቀበል ይቀራል፣ መሾም ይቀራል፣ የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ሥርዓት ከተስተካከለ መዝረፍ ይቀራል፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ከጠነከረ እዚህም እዚያም ቤተ ክርስቲያን መክፈትና ገንዘብ መሰብሰብ ይቀራል፤ ያለ ችሎታ እና ብቃት ጵጵና ማግኘት ይቀራል፤ ስለዚህም ችግሩ እንዲቀጥል ይፈለጋል፡፡

እስኪ ተመልከቱ ቀድሞ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ተአምር ሰምተው ነበር የሚመለሱት፤ እምነቱ፣ ጠበሉ፣ ገድሉ፣ ድርሳኑ ያደረጉትን ተአምር ይሰማሉ፡፡ እኛ ግን ምንድን ነው የምንሰማው? ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ እገሌ

እና እገሌ ተደባደቡ፣ ተለያዩ፣ እንዲህ እና እንዲያ ተባባሉ፣ እንዲህ ያለ ሥርዓት ፈረሰ፤ እንዲህ ያለ ኑፋቄ ተሰጠ፡፡ ጆሮዎቻችንኮ በጎ ነገር ናፈቃቸው፤ ይህ እንዲመጣ ግን ተጋድሎ እና ሰማዕትነት የግድ ይላል፡፡ «እንበለ መከራ ኢይትረከብ ጸጋ» ነውና፡፡ ያለ ሕማማት ፋሲካ የለም፡፡

4/***መንፈሳዊነት***፡ የመጨረሻው፣ ግን ወሳኙ ነገር ነው፡፡ መንፈሳውያን በሌሉበት ቦታ መንፈሳዊ ነገር መፍትሔ አያገኝም፡፡ መንፈሳዊነት ማለት የሃይማኖትን ትምህርት ማወቅ፤ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፤ የቃል ጸሎትን መሸምደድ፣ የቤተ ክርስቲያንን መዓርጋት መያዝ፤ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ማገልገል ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ መንፈሳዊነትን የሚያጎለብቱ ነገሮች እንጂ በራሳቸው መንፈሳዊነት አይደሉም፡፡
መንፈሳዊነት ኑሮ ነው፤ አመለካከት ነው፤ ሕይወት ነው፤ ቅኝት ነው፡፡ መንፈሳዊነት በፈሪሃ እግዚአብሔር ተቃኝቶ፤ በቃለ እግዚአብሔር ተመርቶ፤ መንፈሳዊን ጥበብ ገንዘብ አድርጎ ውስጥን መለወጥ ነው፡፡

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በምንም መንገድ ካልፈራ፤ ቃለ እግዚአብሔርን ከተለማመደው፤ የማያምንባቸውን ነገሮች ለሥነ ሥርዓት ሲል ብቻ የሚያደርግ ከሆነ፤ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ነገር ከስሕተቱ ካላቆመው፤ «እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር» ከሚባልበት ደረጃ ደርሷል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው የተአምራት ቅጣት እንጂ ምክር እና ተግሣጽ አይመልሰውም፡፡

በመሆኑም የሳኦልን ኃጢአት የሚመክት የዳዊት መንፈሳዊነት፤ የኤልዛቤልን ኃጢአት የሚመክት የኤልያስ መንፈሳዊነት፤ የድርጣድስን ኃጢአት የሚመክት የጎርጎርዮስ መንፈሳዊነት፤ የብርክልያን ኃጢአት የሚመክት የዮሐንስ አፈወርቅ መንፈሳዊነት፤ የግራዚያኒን ኃጢአት የሚመክት የአቡነ ጴጥሮስ መንፈሳዊነት፤ ያስፈልጋል፡፡

አንድ የጥንት አባት «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቁ ችግር የሚፈጠረው መንፈሳውያን ያልሆኑ ሰዎች መንፈሳዊ ሥራ ሲሠሩ ነው» ብሎ ነበር፡፡ ያልመነኑ ሰዎች ከመነኮሱ፤ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ከቀሰሱ፤ እግዚአብሔርን የማያውቁት ሰዎች ካስተማሩ፤ ደመወዝ፣ቤት እና መኪና የሚያጓጓቸው ሰዎች ከጳጳሱ፤ ፍትፍት ያልሰለቻቸው ሰዎች ባሕታውያን ከሆኑ፤ የዘር ዛር ያልለቀቃቸው ሰዎች የሁሉ አባት ከተባሉ፤ከራሳቸው ጋር ያልታረቁ ሰዎች ለታራቂነት እና አስታራቂነት ከተቀመጡ፤ መንፈሳዊነት ሽታውም ጠፍቷል ማለት ነው፡፡

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ለመንፈሳዊ ችግሮች የታከቲክ እና የቴክኒክ እንጂ የመንፈስ መፍትሔ ስንፈልግ የማንገኘው፡፡

አንዳንድ ጊዜኮ እኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለን፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ከእኛ ውስጥ ወጥታለች፤ እኛ በክርስትና ውስጥ ነን፤ ክርስትና ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤እኛ በክህነቱ ልብስ ውስጥ ነን፤ ክህነቱ ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤ እኛ በስብከቱ ቀሚስ ውስጥ ነን፤ ስብከቱ ግን ከውስጣችን ወጥቷል፡፡ እኛ በገዳም እንኖራለን፤ ገዳማዊ ሕይወት ግን በኛ ውስጥ የለም፡፡ ለአንዳንዶቻችን ጵጵስና ፕሮፌሽን ነው፤ ቅስና ፕሮፌሽን ነው፣ ሰባኪነት ፕሮፌሽን ነው፤ ምንኩስና ፕሮፌሽን ነው፤ዝማሬ ፕሮፌሽን ነው፣ እንደ ጥብቅና፣ እንደ ንግድ፣ እንደ ሕክምና፣ እንደ ጋዜጠኛነት፣ እንደ ምሕንድስና፣ የእንጀራ ማግኛ ሞያ፡፡ ታድያ እንዴት መንፈሳውያን መሆን ይቻላል?

በመጽሐፈ መነኮሳት እንደ ተጻፈው በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆነው እንደ ቤተ ክህነት የሚኖሩ፣ በቤተ ክህነትም ሆነው እንደ ቤተ መንግሥት የሚኖሩ ነበሩ፤ አሉ። ይሁዳ በአካል ከክርስቶስ ጋር ነበር፤ ልቡ ግን ከነ ሊቀ ካህናት ቀያፋ ጋር ጌታን ለመስቀል ያድማል፤ ማርያም እንተ እፍረት በአካል ከአመንዝሮች ጋር ነበረች፤ ልቧ ግን ክርስቶስን ይፈልግ ነበርና ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። ይሁዳም ልቡ ወዳለበት ሄደ፤ ማርያምም ልቧ ወደ ነበረበት መጣች። ለመሆኑ ከሁለቱ ሰዎች መንፈሳዊው ማን ነበር?

በአንድ ወቅት አንድ አባት የተናገሩትን እዚህ ላይ ማንሣት ያስፈልጋል። ለስብሰባ ወደ አንድ መንግሥታዊ ድርጅት ሄጄ ከባለሥልጣናት ጋር ተሰብስቤ ነበር። በስብሰባው መካከል አንደኛው ባለ ሥልጣን በግእዝ ሲጠቅስ ሰማሁት፤ ተገረምኩ። ስብሰባው ሲያበቃ ጠብቄ ያንን ሰው «አንተ የቤተ ክህነት ሰው ነህ እንዴ? ቅድም አንድ ነገር ስትናገር ሰምቼሃለሁ» አልኩት። ሰውዬውም «አዎ ነኝ፤ ምነው ገረመዎት እንዴ» አለኝ። «የቤተ ክህነት ሰው እንዲህ ባለ ሥፍራ ይኖራል ብዬ አልገምትም ነበር?» ብዬ መለስኩለት። እርሱም «አባቴ የቤተ ክህነት ሰውኮ በየቦታው አለ። የቤተ ክህነት ሰው የሌለው ቤተ ክህነት ውስጥ ብቻ ነው» አለኝ ብለው ነገሩን።

ዋናው መፍትሔው ይሄው ነው። የቤተ ክህነት ሰው በቤተ ክህነት እንዲያገለግል ማድረግ፡

[የመፍትሔ ሃሳቦች](#)

ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች

ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ምን ዓይነት መፍትሔ ነው?

በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክህነቱ አሠራር ሥርዓትን እየለቀቀ የመጣበት ጊዜ ነው። እንደ ዖዝያን ለምጽም ግንባር ላይ ወጥቷል። ንጉሡ ዖዝያን በእግዚአብሔር ላይ በሠራው የድፍረት ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር በለምጽ መታው፡ መጀመርያ ለምጹ በሰውነቱ ላይ ብቻ ስለነበረ በቀሚስ እና ካባ፣ በወርቀ ዘቦ እና በብር ዝርግፍ ሸፈነው። ኃጢአቱ እየባሰ ሲመጣ ግን ለምጹ ግንባሩ ላይ ወጣ። እርሱም ኃጢአቱን በንስሐ ከማስወገድ ይልቅ ለምጹን በሻሽ ለመሸፈን ሞከረ። ለተወሰነ ጊዜም ተሳካለት። በደሉ እና ግፉ እየባሰ በመምጣቱ ግን ለምጹ ሻሹ ላይ ወጣ። ከዚህ በኋላ ለመሸፈን አልቻለም።

አሁን አሁን ነገራችን እንደ ዖዝያን ለምጽ ሊሸፈንበት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ራሱ ችግሩም «አለሁ፣አለሁ» ብሏል። የለህም ብንለውም ራሱን በራሱ ያስመሰክራል።

በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል የሚሉ ሁሉ በመነጋገር ላይ ናቸው። መፍትሔም ይሰነዝራሉ። የመፍትሔ አቅጣጫዎቻቸውን ስናይ ሁለት መልክ አላቸው። ተሐድሶ/reform/ ትንሣኤ /renaissance/ ።

ተሐድሶ

ይህንን መንገድ የሚመርጡት አካላት በቤተ ክርስቲያን ላይ ሥር ነቀል አብዮት መምጣት አለበት ይላሉ። ይህ አብዮት ዶግማዋን፣ ቀኖናዋን፣ትውፊቷን፣ ቅዳሴዋን፣ ጸሎቷን፣ ገዳማዊ ሕይወቷን፣ ወዘተ የሚመለከት ነው ባይ ናቸው። እነርሱ የሚያቀነቅኑት መንገድ ከ500 ዓመታት ጀምሮ ምዕራብ አውሮፓውያን እና አሜሪካውያን በካቶሊክ ቤተ

ክርስቲያን ላይ ያቀነቀኑት መንገድ ነው፡፡ በወቅቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደርዋ ላይ ይታይ በነበረው የሞራል ውድቀት፣ብኩንነት፣ አምባገነንነት፣ ሥርዓት አልበኝነት እና ዓለማዊነት ምክንያት ሕዝቡ ተማረረ፡፡ የወሰደው መፍትሔ ግን ችግርን በችግር የሚተካ ሆነ፡፡ የካቶሊክን ማንኛውንም አስተምሕሮ በመቃወምና በማፍረስ ሌላ ዓይነት አስተምህሮ ተካ፡፡ ከዚያም አልፎ ክርስትናን ርግፍ አድርጎ እስከ መተው ደረሰ፡፡

ተሐድሶ ውጤቱ ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም ነባርዋን ቤተ ክርስቲያን አፍርሶ በለዘብተኛነት በኩል ወደ ጽንፈኛ ዓለማዊነት ያደርሳታልና፡፡ ተሐድሶ መነኮሳት አጠፉ ብሎ ምንኩስና ሕይወትን ለማጥፋት ይነሣል፤ ጳጳሳት አጠፉ ብሎ ጵጵስናን ለማስቀረት ይጥራል፤ በአንዳንድ ቀሳውስት ችግር ቅዳሴን ያስቀራል፤ በሰባክያን ጥፋት ስብከት ይቅር ይላል፤ በተንዛዛ ድግስ ምክንያት ዝክር አያስፈልግም ይላል፤ በአጠቃላይ የሥነ ምግባር ችግሮችን ከመሠረተ እምነት ጋር ይቀላቅላቸውና ቤተ ክርስቲያንን ከመሠረቷ ይንዳታል፡፡

«መነሣት»

ይህ የመፍትሔ አቅጣጫ የሚነሣው በክርስትና ሕይወት መዳከም፣ መዛል እና ዓላማን መሳት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ከበጎች ጋር ተኩላዎች፣ ከስንዴ ጋር እንክርዳድ ሊቀላቀል ይችላል ከሚለው ነው፡፡ በመሆኑም የደከመውን ማጽናት፣ የላሉትን ማጠንከር፣ የተቀላቀሉትን መለየት፣ የተረሱትን ማስታወስ፣ የተበላሹትን ማስተካከል ይገባል ነው፡፡ በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ጥንት ክብርዋ መመለስ ማለት ነው፡፡

ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡

የመጀመርያው አብርሖት ነው፡፡ ሕዝቡ በትምህርት መንገዱ እንዲበራለት ማድረግ፡፡ የቤተ ክርስቲያኑን ማንነት፣ መሠረተ እምነቷን፣ ታሪኳን፣ ሥርዓቷን ያጋጠማትንም ፈተና ዐውቆ፤ ራሱንም የቤተ ክርስቲያን አካል ማድረግ አለበት፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተፈተነች ስንል ራሳችን ተፈተንን ማለታችን ነው፡፡ መከራ ገጠማት ስንል መከራ ገጠመን ማለታችን ነው፡፡ እየተነጋገርን ያለነው ከኛ ውጭ ስለሆነ አካል አይደለም ብሎ ማመን አለበት፡፡ ያላወቀ፣ ያላመነ እና ያልቆረጠን ሕዝብ ለትንሣኤ ማዘጋጀት ከባድ ነው፡፡ አስቀድሞ ሕማማትን ለማለፍ የሚያስችል ብቃት ይጠይቃልና፡፡

ሁለተኛው መዋቅራዊ ሽግግር /structural transformation/ ነው፡፡ መዋቅራዊ ሽግግር ማለት ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ጥንት ክብርዋ የሚመልስ ደረጃውን የጠበቀ እና ዘመኑን የሚዋጅ አሠራር፣ መዋቅር፣ አስተሳሰብ መመሥረት ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ክህነቱ ሳይሆን አሰጣጡ እና አኗኗሩ፤ ጵጵስናው ሳይሆን አሰጣጡ እና አሠራሩ፤ ምንኩስናው ሳይሆን አሰጣጡ፣ አነዋወሩ፤ ብሕትውናው ሳይሆን አነዋወሩ፤ ቅዱሳት መጻሕፍቱ ሳይሆኑ አገባባቸው፤ የቤተ ክርስቲያን ናቸው ተብሎ የሚመዘኑበት መመዘኛ፣ አተረጓጎማቸው፣ ለምን ለምን ጥቅም እንደሚውሉ፤ በዓላቱ ሳይሆኑ፣ ብዛታቸው፣ አከባበራቸው፣ ድንጋጌያቸው፤ ሲኖዶሱ ሳይሆን አሠራሩ፣አወቃቀሩ፤ ወዘተ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ማለት ነው፡፡

መዋቅራዊ ሽግግር ሆ ተብሎ በአብዮት አይመጣም፡፡ አስቀድሞ ችግሩን በመረዳት፣ ከዚያም የችግሩን አንኳር /center of gravity/ በመለየት፣ ከዚያም ደረጃ በደረጃ በመፍታት የሚመጣ ነው፡፡ መግባባትን፣ለአንድ ዓላማ መነሣትን እና ሁሉ ዐቀፍነትን ይጠይቃል፡፡

ለቤተ ክርስቲያን ትንሣኤዋን እንጂ መለወጧን ለማምጣት የምንሠራ ከሆነ በክርስቶስ መሠረት ላይ ሳይሆን በኛ ፍላጎት ላይ የተመሠረተች ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት እየሞከርን ነው ማለት ነው፡፡

እናም እኔ የመፍትሔ ሃሳቦችን የምሰነዝረው ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ተሐድሶ ሳይሆን ትንሣኤ ነው፡፡ በምእመናኑ ሕይወት እና ጉዞ፣ በአባቶች ሕይወት እና ጉዞ፣ በገዳማት ሕይወት እና ዐቅም፣ በአብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር እና ዐቅም፣ በቤተ ክህነቱ አስተዳደር፣መንፈሳዊ ሕይወት እና አሠራር ላይ ዝለት አለ፤ ድክመት አለ፤ የዓላማ መሳት አለ፡፡ ስለዚህም መነሣሣት፣ ወደ ጥንቱ መመለስ እና እንደገና ቀና ማለት ያስፈልጋል በሚለው እምነት ነው፡፡

1 ጉዳዬ ብሎ መጸለይ

ብዙ ጊዜ ስለ ቤተ ክርስቲያን ፈተና ሲነገር ብዙዎቻችን እንጸልይ እንላለን፡፡ ልክ ነው፡፡ ያለ ጸሎት እና ጾም ሰይጣን አይወጣም፡፡ እኛ ግን ይህንን የምንለው አንድም ለማምለጫ፣ አንድም ለምዶብን፣ አንድም መቼም ማንም አያየንም ብለን ነው፡፡ እስኪ ስንቶቻችን ደረታችንን እየደቃን እንደ ራሔል እናለቅሳለን? እስኪ ስንቶ ቻችን ከልባችን እንደ ዳዊት ተዋርደን እግዚአብሔርን ጠየቅነው? የምንጸልየውም ጸሎት የፎርማሊቲ ጸሎት ነው፡፡ ቀድሞ ከምንጸልይበት መንገድ የጨመርነው አንዳች ነገር የለም፡፡

በእውነት የቤተ ክርስቲያንን ትንሣኤ ማየት ከፈለግን ግን ቀልዳችንን አቁመን ለጸሎት እንነሣ፡፡ ለራሳችን ሱባኤ እንግባ፣ ራሳችንን በምንችለው መንገድ እናዋርድ፤ ይህንን ጉዳይ ሳንረሳ እናስበው፡፡

በየገዳማቱ ለሚገኙት አበውም ችግሩን ከማስረዳት ጋር ጸልዩ እንበላቸው፡፡ ባለ ማቋረጥ መባ እየላክን እግዚአብሔርን እንዲማልዱ እናድርግ፡፡ እናቶቻችንንም እንንገራቸው፡፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን እና ሀገር ተጠብቃ የምትኖረው በየዋሐን እናቶች ጸሎት ነው፡፡ የእናቶች ጸሎት እንደ ራሔል በቶሎ ይሰማልና ለጉዳዩ እንዲያስቡበት፣ እንዲያዝኑ በትና እንዲያለቅሱበት እናድርግ፡፡

ብጹአን አበውም በውይይት እና በስብሰባ ችግሩን ለመፍታት ካልቻላችሁ ሌላውን ነገር ትታችሁ ወደ ጸሎቱ ፊታችሁን አዙሩ፡፡

2 ከቲፎዞነት መውጣት

በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ጥብቅና ልንቆም የሚገባው ወገንተኛም ልሆን የሚገባው ለቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ይህም ማለት ለዶግማዋ፣ለሥርዓቷ እና ለትውፊቷ ማለት ነው፡፡ ስለ ሰዎች የምንነጋገረው ከእነዚህ ነገሮች አንፃር መሆን አለበት፡፡ እኛ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን በኩል አገኘናቸው እንጂ ቤተ ክርስቲያንን በሰዎች በኩል አላገኘናትም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርኮችን፣ ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ ሊቃውንትን፣ ሰባክያንን፣ መዘምራንን አፈራች እንጂ እነርሱ አላስገኟትም፡፡ በመሆኑም የሰዎች እና የቡድኖች ቲፎዞ በመሆን ዶግማዋን ፣ሥርዓቷን እና ትውፊቷን ከማፍረስ መቆጠብ አለብን፡፡

ሰውን መውደድ፣ ማድነቅ እና ማክበር መልካም እና ክርስቲያናዊ ምግባርም ነው፡፡ ያ ማለት ግን ክፉ ሥራውን መውደድ፣ማድነቅ እና ማክበር ማለት አይደለም፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ለንስጥሮስ በጻፈው ደብዳቤ «ንስጥሮስ ሆይ አንተን

እወድድሃለሁ፤ ኑፋቄህን ግን እጠላለሁ» ያለውን መርሳት የለብንም፡፡ እገሌ የሀገሬ ልጅ ነው፣ ውለታው አለብኝ፤ የኔን ፖለቲካ ያራምዳል፣ ይወደኛል፣ ይጠቅመኛል፣ አብሮ አደጌ ነው ወዘተ እያልን ጥፋታቸውን በዝምታ ያለፍናቸው ሰዎች ተቀምጠን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ እንዳንችል አድርገውናል፡፡

ታላቁ አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ለኢያሱ ወልደ ነዌ በአንፃረ ኢያሪኮ በተገለጠ ጊዜ ኢያሱ «ከኛ ወገን ነህ ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን?» ሲል ጠይቆት ነበር፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ግን የወገንተኛነትን ጥያቄ አልመለሰም፡፡ «እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ» ነበር ያለው፡፡ «የእግዚአብሔር ከሆነው ጋር ነኝ» ማለቱ ነበር፡፡ በመሆኑም መመዘኛችን ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ ማን ነው? የሚለው እንጂ የኔ ወገን ማን ነው? የሚለው መሆን የለበትም፡፡

በሌላም በኩል እኛ የክርስቶስ ነን ማለትን መልመድ አለብን፡፡ የአቡነ እገሌ፣ የቄስ እገሌ፣ የአባ እገሌ፣ የባሕታዊ እገሌ፣ የሰባኪ እገሌ፣የዘማሪ እገሌ፣ የማኅበረ እገሌ፣አይደለንም፡፡ የጎንደር፣ የጎጃም፣ የትግሬ፣ የወሎ፣ የሸዋ፣ የወለጋ፣ የሲዳሞ፣ የከፋ፣ የሐረር፣ የባሌ፣ የጉሙዝ፣ የአፋር አይደለንም፡፡ እኛ የክርስቶስ ነን፡፡ የክርስቶስ ከሆኑት ጋርም አብረን እንቆማለን፡፡ የሚያገናኙን ሃይማኖት እንጂ ዘር፣ፖለቲካ፣ ወንዝ፣ ተራራ፣ አብሮ አደግነት፣ ጉርብትና፣ አይደለም ብለን ለራሳችን ማሳመን እና መቁረጥ አለብን፡፡

ቲፎዞነት ጭፍን ድጋፍ እና ተቃውሞን ያመጣል፡፡ ነገሮችን በሰከነ መንፈስ፣ በሕግ እና በሥርዓት አንፃር፣ከታሪክ እና ከቅዱሳት መጻሕፍት አንፃር፣ ከተጠየቅ እና ከማስረጃ አንፃር ከመገምገምና አቋም ከመያዝ ይልቅ እነማን አሉበት? እነማን ተናገሩ? ወገኖቼ ናቸው አይደሉም? በሚል መመዘኛ ብቻ ወደ መቃወምና መደገፍ ይወስደናል፡፡ ተፍጻሜተ ሰማዕት ቅዱስ ጴጥሮስ የመከረውን ትቶ አኪላስ አርዮስን ለመሾም የበቃው አብረው የተማሩ የትምህርት ቤት ጓደኞች በመሆናቸው ከሕጉ ዝምድናው በልጦበት ነበር፡፡ ነገር ግን አኪላስም በመንበሩ አልሰነበተም፣ ለቤተ ክርስቲያንም ነቀርሳ አተረፈላት፡፡ ቲፎዞነትም ውጤቱ ይኼው ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዳዊትን እና የዮናታንን ወዳጅነት እናስብ፡፡ ዮናታን የንጉሡ የሳኦል ልጅ ነው፡፡ አባቱ ቢሞት ወራሽ ነው፡፡ ዳዊት ደግሞ መንበሩን ይወርሳል የተባለ ሰው ነው፡፡ ዮናታን የአባቱ ቲፎዞ ሆኖ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ከመጋጨት ይልቅ እግዚአብሔር አብሮት ከሆነው ከዳዊት ጋር መሆንን መረጠ፡፡ በሥጋ፣ በዝምድና እና በጥቅም ሳኦል ይሻለው ነበር፡፡ ዳዊት የአባቱን መንበር እንደሚወስድ እያወቀ እንኳን ሥልጣን ሳያጓጓው ለእውነት መቆምን መረጠ፡፡

ግሪኮች ዲዮስቆሮስ ያለ ሕግ ሲባረር እና ሃይማኖት በኬልቄዶን ስትፈርስ የሮም ቲፎዞ ሆነው አጨበጨቡ፡፡ ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ግን እነርሱ ራሳቸው ከሮም ተለዩ፡፡ መጀመርያውኑ ከቲፎዞነት ይልቅ ለሃይማኖት ቢያደሉ ኖሮ ይህ ሁሉ ባልደረሰ ነበር፡፡

3 መንገር

ብዙ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ላይ በደረሰው ፈተና ያዝናሉ፡፡ የቤተ ክህነቱን መመሰቃቀል እያዩ ይናደዳሉ፡፡ ሚዲያው እና ወሬው ሁሉ ስለሚወድዷት ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ዘመኑን ይኮንናሉ፡፡ አሁን ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ኃላፊነት ላለባቸው አካላት መንገር ያስፈልጋል፡፡ ፓትርያርኩን፣ ጳጳሳቱን፣ መነኮሳቱን፣ ቀሳውስቱን፣ የሚቀርቡ ምእመናን አሉ፡፡ እነዚህ ምእመናን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የሚያውቁትን እና የሚሰሙትን መንገር ይገባቸዋል፡፡

ወደ አባቶች ዘንድ መባውን እና ፍትፍቱን ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንንም ነገር መውሰድ አለባቸው፡፡ ምእመናኑ ምን ያህል ምሬት ላይ እንደ ደረሱ፤ ሁኔታው ካልታረመና በዚሁ ከቀጠለ መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ማስረዳት አለባቸው፡፡ አባቶችን ማማት መፍትሔ አያመጣም፡፡ እነርሱ በሌሉበት ማውገዝ እነርሱ ባሉበት አቦ አቦ ማለት ውጤት አላመጣም፡፡ የምንወዳቸው ከሆነ እንንገራቸው፡፡ እናሳስባቸው፡፡ መስተዋት እንሁናቸው፡፡

ለኛ ለልጆቻችሁ ፈተና ሆናችሁን፤ ስለ እናንተ ክፉ መስማት ሰለቸን፤ ልጆቻችን እየጠየቁን ነው፤ ለምን ዝም ትላላችሁ እያልን ለመፍትሔ እንዲነሡ መቀስቀስ ይገባናል፡፡ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ሺኖዳ እና በአንድ ሌላ ጳጳስ መካከል ልዩነት ተፈጠረና ቤተ ክርስቲያኒቱ አደጋ ላይ ወደቀች፡፡ ሁለቱ አበው በየራሳቸው መንገድ እየሄዱ መሥመሩ ተበላሸ፡፡ በዚህ ጊዜ ምእመናኑ መክረው ተነሡ፡፡

አንድ ቀን ሁለቱ አበው በየራሳቸው ወደ ቅዳሴ ሲገቡ ምእመናኑ በር ላይ ጠበቋቸው፡፡ እርስ በርሳችሁ ተጣልታችሁ አትቀድሱም፤ እኛም አናስቀድስም፤ መጀመርያ ታረቁ፤ አሉ፡፡ ሁለቱም ለጊዜው እምቢ አሉ፡፡ ምእመናኑን ካልታረቃችሁ ብለው መሬት ላይ ወደቁ፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም አባቶች ቀርበው ይቅር ተባባሉ፡፡ ከዚያም አብረው ቀደሱ፡፡

ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ ያሉትን አበው የሚቀርቡ እናቶች እና ሽማግሌዎች፣ ባለ ሀብቶች እና ባለሞያዎች አሉ፡፡ እነዚህ አካላት አባቶቻችን የቤተ ክርስቲያንን ችግር እንዲፈቱ መጠየቅ አለባቸው፡፡ እናንተ የሰላም እና የፍቅር አርአያ ካልሆናችሁ፣ ችግር በመፍታት እና ስሕተትን በማረም አርአያ ካልሆናችሁ፤ የእድገት እና የብልጽግና አርአያ ካልሆናችሁ፣ ተወያይቶ የመስማማት እና የመግባባት አርአያ ካልሆናችሁ፣ ግብረ ሰላሙን ለምን እናመጣለን? ማለት አለባቸው፡፡

4 ከዚህ በኋላ ሹመት ቢቆም

የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ለ10 ሚሊዮን ክርስቲያኖች ከ50 በላይ ጳጳሳት ሲኖሯት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን ከ45 ሚሊዮን ለሆነው ሕዝቧ ጳጳሳቷ ከአርባ አይበልጡም፡፡ እናም ገና አባት ያላገኘ ሕዝብ መኖሩ የማይካድ ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን አስቸኳይ መፍትሔ ከሚያሻቸው ነገሮች አንዱ የሲመት አሰጣጥ ጉዳይ ነው፡፡ ከሲመተ ዲቁና እስከ ጵጵስና ከሕገ ቤተ ክርስቲያንን አንፃር ችግሮች መኖራቸውን በየጊዜው የተካሄዱ የአጠቃላይ የሰበካ ጉባኤያት የአቋም መግለጫዎች ሁሉ ይናገራሉ፡፡ በሲኖዶስም በተደጋጋሚ ተነሥቷል፡፡ ነገር ግን እርምት አልተሰጠውም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዲያቆናትን፣ካህናትን እና መነኮሳትን ሠፍራ ቆጥራ አታውቃቸውም፡፡ እያንዳንዱ አባት ክህነት የሚሰጠው በተለያየ መመዘኛ ነው፡፡ የክህነቱ መታወቂያ በቀላሉ ፎርጅድ ሊሠራ የሚችል ነው፡፡ አበው ክህነት የሰጡትን ሰው ስለማይመዘግቡት ለማን ምን እንደሰጡት አያስታውሱትም፡፡ አንዳንዶች ፈትነው ይሰጣሉ፤ አንዳንዶች በዕውቂያ ያደርጉታል፡፡ አንዳንዶች በአደባባይ አንዳንዶች በድብቅ፡፡ አንዳ ንዶቹ በሀገረ ስብከታቸው፤ አንዳንዶቹ ከቀኖና ውጭ ያለ ሀገረ ስብከታቸው፡፡

የምንኩስናውም እንደዚሁ ነው፡፡ ዋልድባ የመነኮሰውን መርካቶ ከመነኮሰው መለየት አልተቻለም፡፡ ገዳማቱ የታወቀ መዝገብ የላቸውም፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዳታ ቤዝ የለም፡፡ የምንኩስናው መታወቂያ በቀላሉ ፎርጅድ ሊሠራ ይችላል፡ ፡ እነማን የማመንኮስ ሥልጣን እንዳላቸው በትክክል ተለይቶ አይታወቅም፡፡

በመሆኑም እነዚህን መሰል ችግሮችን በአስቸኳይ መቅረፍ ካልተቻለ ያለ ሕግ የመነኮሱ፣ ያለ ሥርዓት የተካኑ ሰዎች ወደ ትልቁ መዓርግ ወደ ጵጵስና መድረሳቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ክብር የሚነካና የማይሽር ቁስል ጥሎ የሚያልፍ ነው፡፡ በመሆኑም ሲኖዶሱ ይህንን ችግር እስኪፈታ ድረስ ሲመተ ጵጵስና ለጊዜው መቆም አለበት፡፡

አሁን አሁን ለሲመተ ጵጵስና ከሃይማኖት እና ምግባር፣ ከዕውቀት እና ችሎታም ሌላ ሌሎች መተያያዎች እየመጡ ነው፡፡ የወርቁ ቁልፍ ሁሉንም በር እየከፈተው ነው፡፡ እናም ቤተ ክርስቲያን ያሏት ችግሮች ይበቋታል፡፡ ሌላ ችግር መጨመር የለባትም፡፡ መጀመርያ አሁን ያለው ችግር ይፈታ፡፡

አራት ኪሎ ቆሞ ለሚያይ ወደዚህ ትልቅ መዓርግ ለመምጣት በእጅ እና በእግራቸው የሚፋጠኑትን ሰዎች መታዘብ ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ እንደ ተመራቂ ተማሪ «ልሾም ነው» እያሉ ያስወራሉ፡፡ ሌሎቹም ልብሱን ገዝተው ቀናቸውን ይጠብቃሉ፡፡ እንዴው አሁን ይሄ የጤና ነው?

5 **መንግሥት ተገቢውን ሥራ መሥራት አለበት**

ልዩ ልዩ መዋቅሮችን በማስተካከል፤ ቢ ፒ አርን በመተግበር፤ በሥልጠና እና በሞያ ማሻሻያ፤ አያሌ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሻሽለዋል፡፡ ቀበሌ እንኳን ተሻሽሎ ወረፋ እና ቢሮክራሲ ብርቅ ሆኗል፡፡ እስካሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ምንም ዓይነት አስተዳደራዊ መሻሻል ያልነካው ቤተ ክህነትን ነው፡፡

ቤተ ክህነቱ አሁን ያለበት ደረጃ ለሀገሪቱ ደረጃ የሚመጥን አይደለም፡፡ ሲሆን እንደ ጥንቱ ከሀገሪቱ እድገት ቀድሞ መምራት ነበረበት፡፡ ካልሆነ ደግሞ በእኩል መሄድ፡፡ ለዚህ ደግሞ ሀገሪቱን የሚመራው መንግሥት ኃላፊነት አለበት፡፡

በመጀመርያ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሀገሪቱ አካል በመሆንዋ፤ እንደገናም የሀገሪቱ አንጺ መገለጫ በመሆንዋ፤ ከዚህም በተጨማሪ በሀገሪቱ ታሪክም ሆነ ሥሪት ውስጥ የማይተካ ሚና ስላላት ለመንግሥት የቤተ ክርስቲያን ነገር ሊገድደው ይገባል፡፡ በርግጥ መግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ ሕግ ያግደዋል፡፡ በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት ማለት ግን ትክክለኛ ትርጉም ያስፈልገዋል፡፡

ገንዘብ ሲመዘበር፣ የአገልጋዮች መብት ሲነካ፣ ሕግ እና አስተዳደር ሲጠፋ፣ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ ተግባር ሲፈጸም ዝም ብሎ ማየት ጣልቃ አለመግባት አይመስለኝም፡፡

ቤተ ክርስቲያኒቱ ደረጃውን የጠበቀ የሠራተኛ አስተዳደር እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ አሠራር እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ የፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖራት፤ ደረጃውን የጠበቀ መዋቅር እንዲኖራት ማስገደድም፤ ማበረታታትም፣ መርዳትም ይገባዋል፡፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን በተፈለገው መጠን ካልተራመደች ከግማሽ በላይ የሆነችው ኢትዮጵያ እንዳልተራመደች ይቆጠራል፡፡

ለምሳሌ የእምነት ተቋማት ከቀረጥ ነጻ ቢሆኑም በውጭ አዲተር የተመሰከረለትና ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ ሪፖርት ከማቅረብ ግን ነጻ መሆን የለባቸውም፡፡ ገንዘቡ የሕዝብ ገንዘብ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ ደግሞ ለትክክለኛው ተግባር እንጂ ሀገርን እና ሕዝብን ለሚጎዳ ተግባር መዋል የለበትም፡፡ ይህም የሚረጋገጠው በአሠራር ነው፡፡ በአብዛኛው የዐለም ሀገሮች የእምነት ተቋማት ከቀረጥ እና ግብር ነጻ ናቸው፡፡ ነገር ግን የሂሳብ ሪፖርት የማስገባት ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህ ደግሞ ሕዝቡ ነጻ የሆነ እና የታመነ ሪፖርት የማግኘት መብቱን ያረጋግጥለታል፡፡

6 አለመተባበር

ምሰጉን ነው በክፉዎች መንገድ ያልሄደ

በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ

በታጥኣንም መንገድ ያልሄደ /መዝ1 ፣1/

አንድ ሰው ችግሩን መፍታት ካቃተው ቢያንስ የችግሩ አካል ከመሆን መራቅ አለበት፡፡ ዛፎቹ ተሰብስበው መጥረቢያ ጨረሰን ብለው ተመካከሩ ይባላል፡፡ ብዙዎቹ ዛፎች መጥረቢያ ይቃጠል፣ ገደል ይጨመር፣ ይታሠር ወዘተ እያሉ ሃሳብ ሰጡ፡፡ አንድ ሽማግሌ ዛፍ ግን «ለመጥረቢያ እጀታ ሆነን ራሳችንን ያስጨረስን እኛ ነን አሉ ይባላል፡፡ አሁንም ለችግሩ መባባስ የምእመናንም አስተዋጽዖ አለበት፡፡

መነኮሳቱ በገዳም እንዳይጸኑ ከተማ እናመጣቸዋለን፤ አጉራ ዘለል ባሕታውያንን ተከትለን መሥመር እናስወጣቸዋለን፤ ገንዘባችንን ጥቅም ላይ በማይውልበት ቦታ እናፈስሳለን፡፡ በየአጥቢያችን የሰበካ ጉባኤያቱ ሲፈርሱ እና ሲዳከሙ ዝም እንላለን፡፡ ሪርት ቢቀርብ ባይቀርብ ግድ የለንም፡፡ የልማት ሕንፃ መሠራቱን እንጂ እንዴት ጨረታ ወጣ? እንዴት ኮንትራክተሩ ተመረጠ? እንዴት ሕንፃው ተከራየ? አንጠይቅም፡፡ ግን በየቤቱ እናማለን፡፡

ገንዘብ መስጠታችንን እንጂ በትክክል መስጠታችንን በተግባርም መዋሉን አንጠይቅም፡፡ ደረሰኝ አለመቀበል ትኅትና የሚመስለን፤ ሽጉጥ ኤድርጎ መስጠት ከከንቱ ውዳሴ መራቅ የሚመስለን ብዙዎች ነን፡፡ ነግር ግን በቤተ ክርስቲያን ጥፋት እየተባበርን ነው፡፡

በአንዳንድ አጥቢያዎች ጧፍ እና ሻማ የአይጥ መዋያ ነው፤ ሌሎቹ ደግሞ በጉሎ ዘይት ይቀድሳሉ፤ በአንዳንድ አጥቢያዎች ልብሰ ተክህኖውን ቤት ጠብቦታል፣ ሌሎቹ ደግሞ በሴት ቀሚስ ይቀድሳሉ፤ በአንዳንድ አጥቢያ ብሩ ሞልቶ ተርፎ ለመኪና ይዋጣል፤ ሌሎቹ ለካህናት ደመወዝ የሚከፍሉት አጥተዋል፤ እኛ ደግሞ ላለው ይጨመርለታል ብለን በብኩንነት ላይ እንጨምራለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ አድባራት ከመጠን በላይ በሰው ኃይል ተጨናንቀዋል፡፡ በአንድ ደብር ትንሹ የሰው ኃይል ሰማንያ ሲሆን ከፍተኛው 300 ነው፡፡ አንዳንድ የአዲስ አበባ አድባራት አገልጋዮች ሰሞነኛነት ሳይደርሳቸው ዓመት ይሞላቸዋል፡፡ ሌላ ቦታ እየሠሩ ለደመወዝ ብቻ የሚመጡም አሉ፡፡ በእነዚህም ላይ ደጀ ጠኚ እየተባለ በየጊዜው ይመደብባቸዋል፡፡ ለምን? ነው ጥያቄው፡፡

በአዲስ አበባ የተከማቸ ገንዘብ አለ፡፡ ስለዚህም ሥጋ ባለበት አሞሮች ይሰባሰባሉ በተባለው መሠረት ሁሉም ወደ አዲስ አበባ ይጎርፋል፡፡ አምስቱ አእማደ ምሥጢር፣ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እና አሥሩን ትእዛዛት እየተጠየቀ ይገባል፡፡ ከዚህም ከፍ ካለ ባለ ሠላሳ፣ ባለ ስድሳ እና ባለ መቶ ፍሬ መሆኑን አይተው ያስገቡታል፡፡

መንግሥት በፌዴሬሽን ምክር ቤት አማካይነት በሚያወጣው ቀመር መሠረት የሀገሪቱን ሀብት ያመጣጥናል፡፡ ቤተ ክህነት ግን ይህንን ማድረግ አልቻለችም፡፡ በርግጥ አንዳንድ ሀገረ ስብከቶች የበጀት ድጎማ ያገኛሉ፡፡ ያ ግን ሊያመጣጥነው አለቻለም፡፡ አንድ የገጠር ካህን አሥር ብር ሲከፈለው፤ አንድ የአዲስ አበባ ካህን አማካይ ደመወዝ ግን አንድ ሺ ብር ነው፡፡ በመካከል ያለው ክፍተት ከሰማይ እና ከምድርም ይሰፋል፡፡

ቤተ ክህነቱ ይህንን እስኪያመጣጥን ድረስ እኛ ማመጣጠን አለብን፡፡ ለምንድን ነው ገንዘባችንን ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት፣ ለተጎዱ ገዳማት እና አድባራት፣ እንዲሁም ለተረሱት የአብነት ት/ቤቶች የማና ውለው? ለምንድን ነው ውጤት በሚያመጣበት ቦታ የማናፈስሰው? ተቀብለው አቡነ ዘበሰማያት ለሚደ ግሙ ምስኪን ካህናት ለምን አንሰጥም?

8 እኔም አጥፍቻለሁ ብሎ መጀመር

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለደረሰባት ፈተና ተጠያቂ የማይሆን የቤተ ክርስቲያን ልጅ የለም፡፡ ምናልባት የጥፋቱ ደረጃ ይለያይ ካልሆነ በቀር፡፡ አንዳንዶቹ በቀጥታ ሌሎቹ በተዘዋዋሪ፤ አንዳንዶቹ ስሕተት በመፈጸም ሌሎቹ ስሕተት ሲፈጸም ዝም በማለት፤ አንዳንዶቹ እኔ የለሁበትም በማለት፣ ሌሎቹ እኔን ካልነካኸ ብለን፤ አንዳንዶቹ ለዕለት ጥቅም፣ ሌሎቹ ለወገንተኛነት፤ ሲባል ለፈጸምናቸው ስሕተቶች መጸጸት አለብን፡፡ ስሕተት መሥራትም ሆነ ሲሠራ በቸልታ ማየት ሁለቱም ያስጠይቃል፡፡ በሉቃስ 10 በተጻፈው የሩኅሩኁ ሳምራዊ ታሪክ ላይ ካህኑ እና ሌዋዊው የተወቀሱት «ኣይተው ገለል ብለው በማለፋቸው» ነው፡፡

አሁን እንደሚታየው ነገሮችን በጥቂት ሰዎች ላይ ብቻ በመጠቆም እጅን ከደሙ ለመታጠብ መሞከር መፍትሔ ሳይሆን ችግር ይወልዳል፡፡ አንዳንዶቻችንም በአጋጣሚ ከሥልጣኑ ቦታ ዘወር በማለታችን የተነሣ የማንጠየቅ ይመስለናል፡፡ ዘወር ብሎ ሲታይ ግን እኛም በቦታው ሳለን እንዲሁ ነበርን፡፡ ልዩነቱ የአንዳንዶች ተሰምቷል የአንዳንዶች አልተሰማም፡፡ የአንዳንዶች ብሷል፣ የአንዳንዶች አልባሰም፡፡ እናም በመጀመርያ ራሳችንን ነጻ እናውጣ፡፡ በንስሐ፣ በመጸጸት፣ ለተሻለም ተግባር በመነሣት፡፡

ዛሬ በቤተ ክህነቱ ለሚታየው ነገር በቤተ ክህነቱ ውስጥ በአንድም በሌላም ያለፉት ሁሉ ይጠየቁበታል፡፡ በዕንቁላሉ ጊዜ ቀጥተውት ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ባልመጣ ነበር፡፡ ምእመናንም ጠለቅ ብለን ቤተ ክርስቲ ያናችንን ከማየት ይልቅ ተሳልሞ በመሄድ ብቻ ስለተውናት ዛሬ ተጠያቂነት የሌለበት አሠራር እንዲሰፍን አደረግን፡፡ ታቦቱንም የሀገሬ ታቦት፣ ጳጳሱንም የሀገሬ ጳጳስ፣ ቄሱንም የሀገሬ ቄስ፣ እያልን ወንዛ ወንዙን ከመሄድ አልፈን «የሃይማኖቴ፣ የቤተ ክርስቲያኔ» ስለማንል ይህ ሁሉ ነገር መጣ፡፡ ቤተ ክህነቱን ርቀነው «እንደ ፍጥርጥሩ ይሁን» ብለን ስለተውነው የሚገባቸው ቀሩና የማይገባቸው ገቡበት፡፡ እናም ከተጠያቂነት አናመልጥም፡፡

ሰባክያን እና መዘምራንም ብንሆን ለዕለት እንጀራችን እና ክብራችን እንጂ ለቤተ ክርስቲያናችን ተቆረቁረን የድርሻችንን ስላልተወጣን፤ ዓይተን እንዳላየን፣ ሰምተን እንዳልሰማን በማለፋችን ይህ ሁሉ መጣ፡፡

አሁን «እኔም አለሁበት» ብለን መነሣት አለብን፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ ከራሳችን እንጀምር፡፡

9 ማኅበራት የሚጠበቅባቸውን ይሥሩ

በቤተ ክርስቲያን ሥር ነን ብለው የተቋቋሙ ልዩ ልዩ ማኅበራት አሉ፡፡ ለጉዞ፣ ነዳያንን ለማብላት፣ ገዳማትን ለመርዳት፣ ለጽዋ፣ ለስብከተ ወንጌል ወዘተ እየተባለ አያሌ ማኅበራት ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህ ማኅበራት ድምፃቸውን ማሰማት ያለባቸው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ሥርዓት ሲጠፋ፣ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ኑፋቄ ሲሰበክ፣ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ያልሆነ ነገር በቤተ ክርስቲያን ሲሠራ፣ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ሥፍራ ሲቆም፣ የሲኖዶሱን ሥልጣን መበለቶች ሲረከቡት ዝም ካሉ መቼ ሊናገሩ ነው፡፡

መጽሔቶቻቸው እና ጋዜጦቻቸው «አቡነ እገሌ ዐረፉ፣ ይህ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፣ ኢየሱስ ከናዝሬት ወደ ገሊላ ሄደ» ለማለት ከሆነ የተቋቋሙት ይህንን የሚሠራ ስላለ ቢያስረክቡት መልካም ነው፡፡ እኔ ጉዞ ካደረግኩ፣ ነዳያንን ካበላሁ፣ ዝክር ከዘከርኩ ሌላው አያገባኝም የሚሉ ማኅበራትም ካሉ ሁሉም የሚኖረው ይህች ቤተ ክርስቲያን ስትኖር መሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡

በተለይም ለቤተ ክህነቱ ቅርብ የሆኑ፣ ብዙ የሰው ኃይል ያላቸው፣ ቅዱስ ሲኖዶስም ኃላፊነት የሰጣቸው ማኅበራት በዝምታቸው ቤተ ክርስቲያንን መጉዳት የለባቸውም፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት ምን ማድረግ እንዳለበት፣ አባቶች ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ የቤተ ክህነቱ አገልጋዮች ምን ማድረግ እንዳ ለባቸው፣ ምእመናን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ መስጠት ይገባቸዋል፡፡ አሁን ሰዓቱ ስለ ቤተ ክርስቲያን ህልውና እንጂ ስለራሳቸው ህልውና የሚያስቡበት ጊዜ አይደለም፡፡

10 ሰባክያን እና መዘምራን የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው

ሕዝቡ ወንጌል ያስተምራሉ፣ወንጌል ይዘምራሉ ብሎ ቦታ የሰጠን አገልጋዮች ለካሴት ሽያጭ እና ለመድረክ ታይታ መሯሯጣችንን ትተን ለቤተ ክርስቲያን መቆም አለብን፡፡ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብለን ነገረ ቤተ ክርስቲያንን ትተን ለራሳችን ብንሯሯጥ ታሪክም ፈጣሪም ይጠይቀናል፡፡ ስምም፣ ክብርም፣ ገንዘብም ያገኘነው በዚህች ቤተ ክርስቲያን መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡

በመጀመርያ ራሳችንን ከችግሩ ነጻ እናድርግ፡፡ ከችግር ፈጣሪዎቹ ጋር መሰለፋችንን እናቁም፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የሚጠበቅብንን እናድርግ፡፡ አንዳንዶቻችን የአስተሳሰብ ችሎታችን፣ የችግር አረዳድ ዐቅማችን እና የኃላፊነት ስሜታችን የስማችንን ያህል አይደለም፡፡ ስማችን እንደ 12ኛ ክፍል፣ ተግባራችን እንደ ሦስተኛ ክፍል ነው፡፡ የማንበብ፣ የመረዳት፣ የመገምገም፣ የማጥናትና ወስኖ የመነሣት ችግሮች አሉብን፡፡

የሚጮኽ ሞንታርቦ፣ የደመቀ ጉባኤ፣ እልልታ የበዛበት መዝሙር የአገልግሎታችን መጨረሻ ሆኗል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን የትናንት እና የዛሬ ሁኔታ ሰከን ብለን አንገመግምም፡፡

በየጊዜው በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካ «የአገልጋይ ጎበረት» እየተባለ ሰዎች ይሰባሰባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከመተማማት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አብሮ ከመብላት በቀር ያስገኘነው ውጤት ግን የለም፡፡ እንዴው ለመሆኑ ግን ተጠራቀምን ወይስ ተሰባሰብን? መሰባሰብኮ የሃሳብ፣ የእምነት እና የግብ አንድነትን ይፈልጋል፡፡ መጠራቀም ግን እንደ ነዳይ ቋጠሮ ከየቦታው መጥቶ በአንድ ቦታ መቀመጥን ብቻ ይፈልጋል፡፡

አጀንዳችንስ ምንድን ነው? በመዝሙር ስለመረዳዳት፣ በመድረክ ስለመረዳዳት፣ አንዱ ሌላውን ስለማጀብ፣ ከዚህ አያልፍም፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በጥናት በተመረኮዘ ሁኔታ ተነጋግረን እናውቃለን? ወስነንስ እናውቃለን? ለውሳኔያችንስ ተገዝተን እናውቃለን?

ሕዝቡ እየበሰለ እኛ ባለንበት እየረገጥን ከሆነ ቀድሞን ይሄዳል፡፡ ተቀምጦ ስለሰማን የቀደምነው እንዳይ መስለን፡፡ ስለ ክብረ ወንጌል፣ ስለ ክብረ ቤተ ክርስቲያን ብሎ እንጂ ከምናውቀው በላይ ያውቃል፣ ከምንነግረው በላይም ይሰማል፤ ደግሞም ይታዘባል፡፡

ስለዚህም በእውነት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከሆንን የልጅነት ስሜታችንን ትተን ለቤተ ክርስቲያን እንነሣ፤ ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃ Apologists የምንሆንበት ዘመን ዛሬ ነው፡፡

ሰዎቹ ለራሳቸው ሐውልት መሥራታቸው ሳያንስ «ሐውልት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የተደገፈ ነው» ብለው ሲያስተምሩ፣ በየጋዜጣው ሲጽፉ እና መጽሐፍ ሲበትኑ ዝም ነው ያልነው፡፡ ጥብቅናችን የት ላይ ነው፡፡ ተሐድሶዎች ገድላቱን እና ቅዳሴያቱን ሲያብጠለጥሉ ዝም አልን፣ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ሥፍራ ስናይ ዝም አልን፤ ታድያ ድርሻችን ምንድን ነው፡፡ ናቡከደነፆር ሕልም አይቶ ሲጠፋው መተተኞቹን፣ አስማተኞቹን እና ኮከብ ቆጣሪዎቹን ሰብስቦ «ሕልሙንም ትርጉሙንም አምጡ» አላቸው፡፡ እነርሱ ግን አልቻሉም፡፡ በዚህ ጊዜ ያላቸውን መተርጉማን ሲነግሩን «ፈረስ አይደላችሁ አልጋልባችሁ፣ በሬ አይደላችሁ አላርስባችሁ፣ ለዚህ ጊዜ ካልሆናችሁኝ ምን ታደርጉልኛላችሁ» ብሎ አስወጣቸው ይላሉ፡፡ የኛም ዕጣ ፈንታ ይኼው እንዳይሆን፡፡

11 ችግሩን ከውስጥ መፍታት

አንዳንዶች የተወሰኑ ሰዎች ተጋድለው ችግሩን እንዲፈቱ ይፈልጋሉ፡፡ እነርሱ ግን ችግሩ ከተፈታ በኋላ ተጠርተው ቦታውን መያዝ ያምራቸዋል፡፡ አንዳንድ ከቤተ ክርስቲያን መሥመር ያፈነገጡ ሰዎች «ችግሩ ሲስተካከል እንመለሳለን» ይላሉ፡፡ ጥያቄው ማን ሲያስተካክለው? የሚል ነው፡፡ ችግሩ ሲስተካከልማ እንኳን ክርስቲያኖች ሙስሊሞችስ ይመጡ የለም ወይ? አሁን ቤተ ክርስቲያን ተጫውቶ ዋንጫ የሚያመጣ እንጂ ዙርያ ከብቦ የሚያጨበጭብ ተመልካች አትፈልግም፡፡

አሁን በቤተ ክህነቱ የምናየው ችግር እንዲፈታ ከፈለግን የሥጋ ሥራችን ያመጣብንን ልዩነት ትተን አንድ ሆነን እንሰለፍ፡፡ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ እንጋደል፡፡ መጀመርያ ቤተኛ እንሁንና የልጅነት መብታችንን እንጠይቅ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በውስጧ ያልነበሩ፣ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ብቅ የሚሉ ሰዎች ጤና ሰጥተዋት አያውቁም፡፡

ለቤተ ክርስቲያን የምንቆረቆር ከሆነ «ገለልተኛ» «ስደተኛ» «መጻተኛ» እያልን የምናዜመውን አራተኛ እና አምስተኛ ዜማ ትተን፣ ያገባናል ብለን ቤታችንን እንረከብ፡፡ ከውጭ ሆነን ችግሩ እንዲፈታ ከምንመኝ ይልቅ ወደ ውስጥ ገብተን ከሚጋደሉት ጋር አብረን ሆነን እንጋደል፡፡

12 ሊቃውንት ድምፃቸው ይሰማ

ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እና ሥነ ምግባርን የሚመለከቱ ጉዳዮች እየመጡ ነው፡፡ ችግሮቹ ዓይን አውጥተው ራሳቸው እየተናገሩ ነው፡፡ እንዲህ ባለ ጊዜ የሃይማኖት ጦር ሰብቀው፣ የዕውቀት ዘገር ነቅንቀው፣ የጥበዐት ዝናር ታጥቀው ብቅ የሚሉ ሊቃውንት ያስፈልጋሉ፡፡ አሁን ጥያቄው «እውነት ወይንም ውሸት በል» የሚል ነው፡፡ ምእመናን መልሱን ይፈልጋሉ፡፡ ሊቃውንት ደግሞ መልሱን መናገር አለባቸው፡፡

በተለይም ከአቡነ ቴዎፍሎስ እስከ አሁን ያለው ታሪክ ግልጽ መልስ ይጠይቃል፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስ እንዴት ተገደሉ? በዚያ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ቅዱስ ሲኖዶስ በወቅቱ ምን አለ? አቡነ መርቆሬዎስ እንዴት ወረዱ? ቅዱስ ሲኖዶስ እንዴት ወሰነ? ምክንያቱ ምን ነበር? አቡነ ጳውሎስ እንዴት ተሾሙ? አመራረጡ እንዴት ነበር? መልስ የሚፈልጉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እዚህም እዚያም ከሚረጩ ነገሮች ያለፈ ግልጽ እና እውነት ነገር የመነገሪያ ጊዜው አሁን ነው፡፡ በተለይም ሁለቱ ፓትር ያርኮች በሕይወት እያሉ፣ ራሳቸው መልስ ለመስጠት በሚችሉበት ጊዜ ሊቃውንቱ መናገር፣ መጻፍ አለባቸው፡፡ በሞት ከተቀደምን ሐሜት ይሆንብናል፡፡

በሌላም በኩል በምንኩስና፣ በክህነት፣ በጵጵስና አሰጣጥ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ አሠራር፣ በቤተ ክህነቱ መንፈሳዊ ጉዞ ወዘተ የሚታዩትን ነገሮች ከቅዱሳት መጻሕፍት አንፃር አስተያይቶ መናገር፣ ማሳየት እና ማረም ከእናንተ ይጠበቃል፡፡

13 የሰበካ ጉባኤ አመራሮች የድርሻቸውን ይወጡ

የየአጥቢያው ገንዘብ ሲመዘበር፣ ተገቢ ላልሆነ ነገር ሲውል፣ ምስኪን ካህናት ደመወዝ አልበቃ ብሏቸው ልጆቻቸውን የሚያበሉት እና የሚያስተምሩበት ሲያጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥይት የማይበሳው መኪና ለመግዛት ሚሊዮኖች ከየአጥቢያው ሲዋጣ የአጥቢያ ሰበካ ጉባኤ አባላት ዝም ማለት የለባቸውም፡፡

ቢያንስ ሦስት ነገሮች ማድረግ አለባቸው፡፡

የመጀመርያው ለምን ብለው መጠየቅ አለባቸው፡፡ በስብሰባቸው ያልወሰኑት ነገር ሲፈጸም ምንም ማድረግ አንችልም ብለው መተው የለባቸውም፡፡ ሁለተኛም መረጃ መያዝ አለባቸው ነገ በምርመራ ሊጣራ ይችላልና ተገቢውን ዶክመንት መያዝ ያስፈልጋል፡፡ እየባሰ ሲመጣ ደግሞ ለምእመናኑ፣ ለፀረ ሙስና ኮሚሽን እና ለሚመለከታቸው አካላት መግለጽ አለባቸው፡፡

እስኪ የሙዳየ ምጽዋቱን ሳጥን ይቁጠሩት? ስንት ሙዳየ ምጽዋት የደብሩ ስንትስ የግለሰቦች አለ? እስኪ የሕንፃውን አከረያየት እና የኪራይ መጠን ይጠይቁ? እስኪ የንዋያተ ቅድሳቱን መጠን እና አድራሻ ይመርምሩ? የቻሉትን ያስተካክሉ ያልቻሉትን ግን አቤት ይበሉ፡፡ ዝም ብሎ መቀመጥ ግን በስሕተቱ መስማማት ነው፡፡

14 ብጹአን አበው ራሳቸውን ቢያዩ

አባግዐ ቤተ ክርስቶስን እንዲያስማሩ የተሾሙት አበው ምን ያህል የተሠማሩበትን እንደፈጸሙ ራሳቸውን ቢያዩት፡፡ ጥፋቱን ሁሉ በአንድ ሰው ላይ አላከኮ መቀመጥ ራስን ብቻ ነው የሚያሳምነው፡፡ ለመሆኑ የየራሱን ሐውልት በልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቆመ አለ? ችግሩን መፍታት ለምን ከራስ አይጀመርም፡፡ ቀኖና ያላፈረሰ አለ? የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሆነው አሜሪካ ሲኖዶስ የማያውቃት፣ ሲኖዶስንም የማታውቅ የየራሳቸው የግል ቤተ ክርስቲያን ያላቸው ጳጳሳት የሉም? በሰው ሀገረ ስብከት ገብተው ክህነት የሚሰጡ አባቶች የሉም? በሰው ሀገረ ስብከት ገብተው ቤተ ክርስቲያን የሚባርኩ አባቶች የሉም? የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንብረት ነው እየተባለ የሚታወቀው ሁሉ በርግጥ የቤተ ክርስቲያንዋ ነው? የመኳንንት እና የመበለቶች እጅ የለበትም? ታድያ ማን ማንን ያማል? ማንስ ማንን ይወቅሳል? ማንስ በማን ይፈርዳል?

የዘመድ አሠራር በየሀገረ ስብከቱ የለም? ለመሆኑ ከወንዛችን ሰው ውጭ እናምናለን? እስኪ ሾፌሮቻችን ይታዩ? በየሀገረ ስብከቱ ብክነት የለም? በየሠፈሩ የቤት ሐውልት አላቆምንም? ከጥቂት አበው በስተቀር ከዚህ ነጻ የሚሆን ይገኛል? ታድያ ራሳችንን ሳናጸዳ እንዴት ሰውን ለመውቀስ ሞራል ይኖረናል? ለዝምታችንም አንዱ ምክንያት ይኼው ነው፡፡

እስኪ ጽዳቱን ከቤታችን እንጀምረው፡፡ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ልናየው የምንፈልገውን ዓይነት አሠራር በሀገረ ስብከታችን፣ በኮሌጆቻችን እና በመምሪያዎቻችን እንጀምረው፡፡ ለመሆኑ በየሀገረ ስብከቱ ይሂዱልን የሚባሉ አበው ለምን እየበከቱ መጡ? ዘመኑስ ይምጡልን ከሚለው ይሂዱልን ወደሚለው ለምን ተቀየረ?

ምንም እንኳን እናንተን ለመውቀስ ሥልጣን ባይኖረንም፣ ይቅር በሉኝና ለቤተ ክርስቲያን ሲባል መጀመርያ በየቤቱ ያለው ችግር ይፈታ፡፡ እያንዳንዱ አካባቢውን ቢያጸዳ ከተማዋ ትጸዳለች ይባል የለ፡፡ ከዚያ በአንድነት ሆኖ የዋናውን ቤት ችግር መፍታት ይቻላል፡፡

15 የመዝሙር ቤቶች የድርሻቸውን ይወጡ

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከሙዚቃ ቤቶች ይልቅ የመዝሙር ቤቶች በዝተዋል፡፡ ታክሲዎችን እና ካፍቴርያዎችን ያጨናነቁት ዘፈኖች ቀንሰዋል፡፡ በአንድ በኩል መልካም ውጤት ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ መሥመሩን ከሳተ አደገኛ ነው፡፡ መዝሙሮቹን እና ስብከቶቹን መርምሮ ማሳለፍ እና ማረም የቤተ ክህነቱ ድርሻ ነበር፡፡ ነገር ግን ከቁም ነገር አልጣፈውም፡፡ እኛም የተከፈተ ቤት አገኘንና እንደ ልብ ተዘልለን ተቀመጥን፡፡ የሚገባንን ሳይሆን የምንፈልገውን እየሠራን፡፡ የሚያጸድቀንን ሳይሆን የሚያዋጣንን ብቻ እያሳታምን፡፡ ሃይማኖት ያለውን ትተን ገበያ ያለውን እያሠራጨን፡፡ ሥርዓት መር መሆን ሲገባን ገበያ መር ሆነን፡፡

ለምን ግን ቤተ ክርስቲያንን አብረን እንጎዳታለን? እንዴት ከጉዳቷ እናተርፋለን? ለኢንሹራንስ ሲሉ ወላጆቻቸውን እንደሚገድሉ ክፉ ልጆች እንዴት ለገንዘብ ስንል ከሚጥሏት ጋር እንተባበራለን?

ለምን እኛ የምንችለውን አናደርግም? በምዕራቡ ዓለም የሙያ ማኅበራት ደረጃ ያወጣሉ፣ ሥርዓት ያስይዛሉ፣ ባለሞያ ፈትነው ፈቃድ ይሰጣሉ፣ ሞያውን ይቆጣጠራሉ፡፡ እኛስ ታድያ አንድነት ፈጥረን፣ ሊቃውንቱን መድበን፣ ደመወዛቸውን ሰጥተን የምናወጣቸውን ብናስመረምር እና ብናሳርም ምን አለ? ለማንም ብለን አይደለም፤ ለነፍሳችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ስንል፡፡

ቤተ ክህነቱ ኃላፊነቱን አልተወጣም ብለን እንዴት እኛም ኃላፊነት የጎደለው ሥራ እንሠራለን? ቤተ ክርስቲያን እኮ አደረጃጀት እንጂ ሊቃውንት አላጣችም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እስኪሠራ በመቃኞ እንደ ሚቀደሰው ሁሉ ዋናው ቤተ ክህነት እስኪሠራ እኛ ለመቃኞ የሚሆን አሠራር ብንዘረጋ ምናለበት? ማን ያውቃል እግዚአብሔር በጎ ኅሊና ችንን፣ ለሥርዓት ተገዥነታችንን፣ ለእውነት ያለንን ትጋት አይቶ መፍትሔውን ይሰጠን ይሆናል፡፡

16 ሁሉም ወደ የበኣቱ ይመለስ

የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሰው ሁሉ በቤተ ክርስቲያናዊ በኣት ብቻ መገናኘት አለበት፡፡ ምንም እንኳን በሃይማኖት ምክንያት፣ በሀገር ፍቅር ስሜት፣ ለታሪክ ባላቸው ክብር እና ፍቅር፣ ለበጎ ነገር ባላቸው ቅንዐት፣ ወዘተ ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመርዳት ቢመጡ፣ በኣታቸው ግን ክርስትና መሆን አለበት፡፡

በዘር፣ በፖለቲካ፣ በጥቅም፣ በሥልጣን እና በፍቅረ ሲመት ተነሣሥተው የራሳቸውን አጀንዳ በቤተ ክርስቲያን ላይ ለመጫን እና የቤተ ክርስቲያንን ችግር ለአጀንዳቸው ማቀጣጠያ ለማድረግ የሚነሡትን ኃይሎች ግን «ወደየበኣታችሁ ተመለሱ» ማለት ያስፈልጋል፡፡

አንዳንዶች የቤተ ክህነቱን ችግር የፖለቲካ አጀንዳቸው ማንፀባረቂያ፣ ሌሎች የዘር አጀንዳቸውን ማቅረቢያ፣ ሌሎችም የሹመት ፍላጎታቸውን ማንገሻ ሊያደርጉት አሰፍስፈዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ በጥብርያዶስ ባሕር እንደ ተገኙት አምስት ገበያ ሕዝብ ናቸው፡፡ እነዚያ መልኩን ለማየት፣ ምግብ ለመብላት፣ ለመፈወስ፣ ተአምር ለማየት፣ ወሬ ለመቃረም፣ ሮማውያንን ገልብጦ ለመንገሥ፣ ሥልጣን ለማግኘት ወዘተ ተሰብስበው ነበር፡፡ በትክክለኛው ዓላማ የተሰባሰቡት ከ120 አይበልጡም ነበር፡፡

ጌታችን በአይሁድ እጅ ሲያዝ ግን የበሉበትን ወጭት ሰብረው፣ ያገኙትን ፈውስ ረስተው፣ ያዩትን ተአምራት ዘንግተው፣ የተማሩትን ትምህርት ትተው «ስቅሎ፣ ስቅሎ» እያሉ ነው የጮኹት፡፡ ሁሉም የየራሳቸው አጀንዳ አልሳካ ሲላቸው መልሰው በጠላትነት ተሰለፉ፡፡

አሁንም ለየራሳቸው ዓላማ ሲሉ ችግሩን የሚያቀጣጥሉ፣ የሚያራግቡ እና ባለቤት መስለው የሚታዩትን «ወደ በኣታችሁ ተመለሱ» እንበላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አጀንዳ ከመጋራት ይልቅ፣ ቤተ ክርስቲያን የእነርሱን አጀንዳ እንድትጋራ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን አይሠሩም፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ለእነርሱ እንድትሠራ ይፈልጋሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን አይጠቅሟትም፤ ቤተ ክርስቲያንን ግን መጠቀሚያ ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ እናም እባካችሁ «ወደየበኣታችሁ ተመለሱ»፡፡

17 የሚሠሩትን ማገዝ

የቤተ ክርስቲያንን ጉዳት ዝም ብለው ማየት አቅቷቸው፣ ክርስትናቸውም አስገድዷቸው የሚችሉትን የሚያደርጉ አካላት አሉ፡፡ በግለሰብም ሆነ በማኅበር ደረጃ ተነሥተው ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት፣ ለአብነት ት/ቤቶች መጠናከረ፣ ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት መቀጠል፣ የሚተጉ ወገኖች አሉ፡፡ እነዚህን አካላት ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ጽርሐ ጽዮን ዘተዋሕዶ ማኅበር ያሉትን፣ የመኖርያ ቦታቸውን ቀንሰው ለገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሰባክያን ማሠልጠኛ የነኑትን፤ እንደ ደጆቸሽ አይዘጉ ያሉትን፣ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን አገልግሎት ለማስቀጠል የሚደክሙትን፤ እንደ ደቡብ ኦሞ አብያተ ክርስቲያናት መርጃ ማኅበር ያሉትን፣ ወደ ክርስትና ያልመጡ ወገኖችን ለማገልገል የተነሡትን፤ እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት፣ገዳማት እና አድባራትን ለመርዳት እንዲሁም ቅርስ እና ታሪክን ለመጠበቅ የተነሡትን፤እንደ ማኅበረ ሰላም፣ የመዝሙርን አገልግሎት ሥርዓትን በጠበቀ መንገድ ለማስፋፋት የሚተጉትን፤ሌሎችንም በስም ያልተጠቀሱትን በማገዝ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይዳከም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ ዛሬ የሰንበት ት/ቤቶች በኮሌጅ ደረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ኮርሶችን እየሰጡ ነው፡፡ እንደ ዓምደ ሃይማኖት ሰሰንበት ት/ቤት ያሉት ደግሞ በተልዕኮ ትምህርት እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጅምሮች ማደግ አለባቸው፡፡ ትናንትና ሁለት ኮምፒውተር ይዘው የጀመሩ ማዕከላት ኮሌጅ ሲባሉ አራት እና አምስት መቶ ደቀ መዝሙር የሚያሠለጥኑት፣ የመማርያ መጻሕፍትን የሚያዘጋጁት ሰንበት ት/ቤቶቻችን ወደ ኮሌጅ ደረጃ የማያድጉት ለምንድን ነው?

ቀዳማይ፣ ካልኣይ፣ ሣልሳይ፣ ራብኣይ የሚለው ኮርስ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ ዓመት ተብሎ ለምን አይሰጥም? በውኑ የቀጣዩ ትውልድ ልጆች አሁን እኛ በተማርንበት መንገድ ይማራሉ? ታድያ ሰንበት ት/ቤቶቻችንን ካሁኑ ለምን አናዘጋጃቸውም?

በአንድ በኩል ሊቃውንቱ ተተኪውን ትውልድ የሚያስተምሩበት ዕድል ያገኛሉ፤ በሌላም በኩል በተልዕኮ ትምህርት በውጭ ያሉትን ምእመናን ማዳረስ ይቻላል፤ እንደ ገናም ደግሞ አንድ የሰንበት ተማሪ እድሜ ልኩን ሥላሴ ስንት ናቸው? እየተባለ ሲማር ከሚኖር ዕድገት ያለው ትምህርት ለማግኘት ይረዳዋል። እናም እስኪ በየዐቅማችን እንጀምረው። ነገን ዛሬ እንትከል።

18 ለትልቁ ስንል ትንንሾችን መተው

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ በዶግማ እና በትውፊት ላይ ካልሆነ በቀር በአሠራር፣ በይትበሃል፣ በጊዜያዊ ጠብ፣ በልጅነት ስሜት እና ባለ መረዳዳት የተፈጠሩትን ልዩነቶች ለቤተ ክርስቲያን ሲባል ማስማማት እና ይቅር መባባል ያስፈልጋል።

አንድ ዓይነት ዓላማ፣ እምነት እና ራእይ እያላቸው እርስ በርሳቸው የማይስማሙ አገልጋዮች፣ ማኅበራት እና ቡድኖች አሉ። እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ የሚፎካከሩ፤ አንዱ አንዱን ከመርዳት ይልቅ መገፋፋትን የሚወድዱ፤ ተባብሮ ከመሥራት ይልቅ በየፊናቸው መሮጥን የሚመርጡ አሉ። ይህ ግን ማብቂያው አሁን ነው። የማይስማሙት ተስማምተው ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠቁ መስማማት የሚገባን እንዴት እንለያያለን። አሠራር ልዩ ልዩ ነው፤ ሃይማኖት ግን አንድ ነው። ሁላችንም የግድ አንድ ዓይነት ሰዎች የአንድ ማኅበርም አባላት መሆን አይጠበቅብንም፤ ነገር ግን ተግባብተን መሥራት ይጠበቅብናል። ትንንሽ ልዩነቶችን ሳንፈታ ትልቁን ችግር መፍታት አንችለም።

ለመነጋገር፣ ለመግባባት እና ተባብሮ ለመሥራት እንነሣ። አባላቱም ብንሆን ዝም ብለን በአመራሮቹ አንመራ። ከእነ እገሌ ጋር ለምን አብረን አንሠራም? ለምን አንረዳዳም? ለምን ሥራ አንካፈልም? ለምን ልምድ አንለዋወጥም? ለምን እንተማማለን? ለምን እንራራቃለን? ብለን እንጠይቅ። በእውነት ቤተ ክርስቲያናችንን የምንወድድ ከሆነ ተዋድደን በአንድነት እንቁመላት።

19 እንወያይ

ሐሜቱን እናቁም፤ አሁን እንወያይ። ምንተ ንግበር? እንበል። ጊዜው የተግባር ነው። በየአለንበት ሃሳብ እንለዋወጥ። አንዱ ሌላውን ይቀስቅስ። የተኛ እንዳይኖር አስተውሉ። በየጉባኤያቱ መብል እና መጠጥ ይቀነስ፣መዝሙር አይብዛ፤ እንመካከር። እንወያይ። የተግባር ዕቅድ እናውጣ። እየተነጋገርን አንርሳ። ቀስቃሽም አንፈልግ።

ለመሆኑ ስለ ቤተ ክርስቲያን ለማሰብ እና ለመወያየት አንዳች አስደንጋጭ ዜና መስማት አለብን? እስከ ዛሬ የሰማነው አይበቃንም? ሰንበት ት/ቤቶች ከሰንበት ት/ቤቶች፤ ማኅበራት ከማኅበራት፤ አገልጋዮች ከአገልጋዮች፣ አባቶች ከአባቶች

እንነጋገር፤ አጀንዳችን ቤተ ክርስቲያን ትሁን፡፡ ለማማት አይደለም፤ ለተግባር፡፡ ለአፍ ጅምናስቲክ አይደለም፤ ለተጋድሎ፡፡ ወሬ ለማሟሟቅ አይደለም፤ ለቁጭት፡፡ የራስዋ እያረረባት የሰው ታማስላለች እንደሚባለው አሁን ሌሎች ነገሮችን ለጊዜው ጋብ አድርገን ወደ ራሳችን እንመለስ፡፡

20 ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ

በኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ /ኤድስን ለመግታት ከተነሡት አካላት መካከል ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩት ወገኖች ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ይዘውት የተነሡት መሪ ቃልም «ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ» የሚለው ነው፡፡ እኛም ይህ የምንሰማው ችግር ሁሉ ለልጆቻችን መተላለፍ የለበትም፡፡ ይህንን ከታሪክ መጻሕፍት ብቻ ያንብቡት፡፡ «ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ» ብለን እንነሣ፡፡ ሁላችንም ለራሳችን ቃል እንግባ፡፡

«ይህ ችግር ወደ ትውልድ እንዳይሸጋገር በእግዚአብሔር ኣጋዥነት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ ትውልድ ይዳን በኔ ይብቃ፡፡»
እግዚአብሔር ቤተ ክስቲያናችንን ይጠብቅ፡፡ አሜን፡፡

እነሆ በቀጣዮቹ ቀናት ይህ ብሎግ የእናንተን የመፍትሔ ሃሳቦች ያስተናግዳል፡፡ በተሰጡት ላይ መጨመር፣ ማሻሻል፤ መቃወምም ሆነ የድጋፍ ሃሳብ መስጠት ይቻላል፡፡ በተቻለ መጠን ሃሳቦቻችን ከግለሰቦች ይልቅ ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ፤ ከምሲጋናና ጥላቻ ይልቅም ሃሳብ ላይ ያነጣጥሩ፡፡

39. ቅኝ አልተገዛንም?

አባት ሁልጊዜ ለልጁ ስለ ሀገሩ ታሪክ እና ወግ ይነግረዋል፡፡ በተለይም አንድ ነገር ደጋግሞ ያነሣለት ነበር፡፡ «ኢትዮጵያ ከሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች ተለይታ ቅኝ ያልተገዛች፣ራስዋን ችላ የኖረች ሀገር ናት፡፡ የራስዋ ፊደል፣ የራስዋ የዘመን አቆጣጠር፣ የራስዋ ባሕል ያላት ናት» ይለዋል፡፡ አንድ ቀን ታድያ ልጁ ጥያቄ አነሣ፡፡ «ኢትዮጵያ ግን በእውነት ቅኝ አልተገዛችም?» የሚል፡፡ እናም አባቱን መሞገት ጀመረ፡፡

«አባዬ ግን በእውነት ኢትዮጵያ በአውሮፓውያን ቅኝ አልተገዛችም? ወይስ ለሞራሌ ብለህ ነው ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች ሀገር ናት እያልክ የምትነግረኝ» አለው ልጁ፡፡ አባትዬውም ደንግጦ «ምነው ልጄ ምን አዲስ ነገር ተገኘ? ይህኮ እኔ የፈጠርኩት አይደለም፡፡ ዓለም በሙሉ የሚያውቀው እውነት ነው፡፡ የትኛውንም መጽሐፍ አገላብጥ፣ የትኛውንም ሊቅ ጠይቅ፣ ይህንኑ ብቻ ይነግሩሃል» አለው፡፡ ልጁም «ይህ ከሆነማ ሆኗል ተብሎ የሚታሰበውና የሚታየው ነገር ይለያያል» አለው፡፡

«እንዴት ማለት» አለ አባት፡፡

«ኢትዮጵያ ቅኝ አለመገዛቷ ሆኗል ተብሎ የሚታሰበው ነገር ነው፤ የሚታየው ነገር ግን ቅኝ ተገዝታ የኖረች ብቻ ሳይሆን አሁንም ቅኝ እየተገዛች መሆንዋን የሚያሳይ ነው»

አባት ግራ ገብቶት ልጁን ትኩር ብሎ አየው፡፡ «መቼም የዛሬ ልጆች ተፈላሳሚዎች ናችሁ፡፡ የማታመጡት ነገር የላችሁም፡፡ እኛ አሜን ብለን የተቀበልነውን ነገር ሁሉ መጠራጠር አመላችሁ ሆኗል፡፡ ምን አግኝተህ ነው ይህንን ያልከው?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ለምሳሌ በቀደም ዕለት እኔና አንተ እዚያ ቢሮ ሄድን፡፡ ታስታውሳለህ?» አለው ልጁ፡፡ «አዎ እና ምን ተፈጠረ?» አለው አባት፡፡

«በር ላይ የተፈጠረውን ታስታውሰዋለህ?» ልጁ መልሶ ጠየቀ፡፡

«ምን ተፈጠረ? ተፈተሽን ገባን፡፡ አለቀ» አለው አባት፡፡

«በጣም ጥሩ እኔ እና አንተ ተፈትሸን ገባን፡፡ ከእኛ አጠገብ የነበረው ፈረንጅ ግን ሰላምታ ብቻ ቀርቦለት ገባ፤ ለምን? እኔ እና አንተ ግብር ከፋይ የዚህች ሀገር ዜጎች ነን፡፡ እኔ እና አንተ አጥንታቸውን ከስከሰው፣ ደማቸውን አፈሰሱ እያልን ዘወትር የምናነሣቸው አባቶቻችን ልጆች ነን፡፡ ነገር ግን እኛ አንታመንም፤ ስለዚህ ተፈተሽን፡፡ ፈረንጁ ግን ታማኝ ነው፤ እናም ሳይፈተሽ በጥሩ ፈገግታ ገባ፡፡ እኛ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለን እንጠረጠራለን፤ ፈረንጁ ግን ንጹሕ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ «ሆሆ» አለ አባት፡፡ «እና ይሄ ከቅኝ ግዛት ጋር ምን አገናኘው?»

«ቆይ ቆይ ታገሠኝ፡፡ እዚያ ቢሮ ብቻ አይደለምኮ፡፡ ታላላቅ በዓላት ሲከበሩ በየአደባባዩ ሐበሻ ሆነህ ፎቶ ግራፍ ላንሣ፣ ፊልም ልቅረጽ ብትል ጠባቂው አያሳልፍህም፡፡ ፈቃጁም በመከራ ነው የሚፈቅድልህ፡፡ እርሱም ቢሆን ዘመድ ካገኘህ፡ ፡ ፈረንጅ ከሆንክ ግን መልክህ ብቻ ይበ ቃል፡፡ የፈለግከውን ብትቀርጽ፣ የፈለግከውን ብታነሣ ማን ጠያቂ አለህ፡፡ እስኪ ወደ ታሪካዊ ቦታዎች ሂድ፤ ለሐበሻ ያልተፈቀዱ ቦታዎች ለፈረንጅ ክፍት ናቸው፡፡ አንተ የማታገኘውን መረጃ ፈረንጅ በቀላሉ ያገኘዋል፡፡

«አንቱ ከውጭ ሀገር የመጣ ጊዜ ትዝ ይልሃል? ምሳ ሊጋብዘን እዚያ ሆቴል ገባን፡፡ እኔ መጀመርያውኑም እንዲህ ያሉ ፈረንጅ የሚያዘወትራቸው ሆቴሎች መሄዱን አልፈለግኩትም ነበር፡፡ ደግሞም ተናግሬያለሁ፡፡ ግን ከሄድን በኋላ ያልኩት ነው የደረሰው፡፡

«ምን ተፈጠረ፤ ነበርኩ አይደለም እንዴ?»

«አዎ ነበርክ፡፡ ነገር ግን አንተ ቅኝ ግዛትን መሬት ላይ ነው የምትፈልገው፤ እኔ ደግሞ ሰው ላይ፡፡ አንተ ስለ ድንበር የምታስበው በምዕራብ፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን፣ በደቡብ እያልክ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ድንበሩን ከመካከላችን ነው የምፈልገው፡፡

«እኛ ነበርን ወደ ሆቴሉ ቀድመን የገባንው፡፡ ወንበር ይዘን የተቀመጥነው፡፡ ነገር ግን አስተናጋጆቹ ሁሉ ፈረንጆቹን ለማስተናገድ ነበር ሽር ጉድ የሚሉት፡፡ እኛ ተቀምጠን ከኋላችን የመጡት ፈረንጆች ቀድመው ተስተናገዱ፡፡ አጎቴ ነገሩ ስላልገባውና የአስተናጋጆቹ ንዝህላልነት ብቻ ስለመሰለው ከራሱ ሀገር ጋር አወዳድሮ ተናደደ፡፡ በኋላም በመከራ ነው የታዘዙን፡፡ የሚገርመው ነገር የምግብ ዝርዝሩን ሳየው አንድም ኢትዮጵያዊ ምግብ አላገኘሁም፡፡ ለኔ አልገረመኝም፡፡ እዚያ ቤት የሚጠበቀው ፈረንጅ እንጂ ሐበሻ አይደለም፡፡ አንተም እንድትሄድ የሚጠበቅብህ ፈርንጀህ ነው፡፡ ተወው ምግቡን፡፡ ምግቡ የተጻፈበት ቋንቋ እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ብቻ ነው፡፡ አንዳች የሀገርህ ቋንቋ የለውም፡፡ ከምግብ ዝርዝሩ ውስጥ ምን የሚል የእንግሊዝኛ ቃል እንዳየሁ ታውቃለህ?

«ምን አየህ ደግሞ? ዛሬ ለጉድ ነው መቼም አመጣጥህ» አለው አባቱ እየጓጓ፡፡

«ታንግ ኤንድ ሰንበር ይልልሃል ምግቡ»

«ታንግ ኤንድ ሰንበር ደግሞ ምንድን ነው?»

«እይውልህ ምላስ እና ሰንበር የሚለውን ለመግለጥ ነዋ፡፡ ምግቡን ሲያፈረንጁት እኮ ነው፡፡ ምናለ መጀመርያ በአማርኛ፣ ከዚያም ስሙን በእንግሊዝኛ፣ ቀጥሎ ስለ ምግቡ ባሕል እና ይዘት መጠነኛ ማብራርያ ቢሰጡ፡፡ አይ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ፡፡

«ቋንቋ አለን ግን አንጽፍበትም፡፡ ቁጥር አለን ግን አናስብበትም፤ ባሕል አለን ግን አንኮራበትም፡፡ እስኪ ቻይናን እያት፡ ፡ መላውን ዓለም በቻይና ምግብ ቤት ስታጥለቀልቀው፡፡ የሠራተኞቹ አለባበስ፤ የምግብ ቤቱ ስም፤ ስሙ የተጻፈበት ቋንቋ፤ የምግቦቹ ስያሜ፣ ስያሜያቸው የተጻፈበት ቋንቋ፣ ግድግዳው ላይ የተጻፈው እና የተሳለው ነገር፣ የሚቀርብበት ዕቃ ምኑ ቅጡ ቤጂንግ ያለህ ነው የሚመስልህ፡፡ «እስኪ ዘመዶችህን እያቸው አባዬ፤ ኢትዮጵያዊውን ስምኮ ድራሹን እያጠፉት ነው፡፡ በግእዝ፣ በአማርኛ፣ በትግርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በወላይትኛ፣ በሲዳምኛ ስሞች መጠራት እየቀረኮ ነው፡፡ የአሁኑ ዘመን የስም ፍልስፍና ቢቻል የልጆችህ ስም ከአራት ፊደል ያልበለጠ፣ ለቁልምጫ የሚያመች እና ያልተለመደ ይሁን የሚል ነው፡፡ ይህ አይደለም ግን ችግሩ፡፡ እነዚህን ነገሮች ለማሟላት እየተረባረብን ያለነው የፈረንጅ ስሞች ላይ ነው፡፡ ልክ ቅኝ የተገዙ አፍሪካውያን የሀገራቸውን ነባር ስሞች እየዘነጉ በቅኝ ገዥዎቹ ስሞች እንደተጠሩት እኛም ያንን መንገድ ሳንወረር እየተከተልነው ነው፡፡

«የነገው ትውልድ የሚወጣባቸውን ትምህርት ቤቶችንስ ታያለህ? የሚያስተዋውቁትኮ ብቁ ኢትዮጵያዊ መምህር አለን ብለው ሳይሆን አንዳች ፈረንጅ እኛ ትምህርት ቤት ያስተምራል እያሉና እርሱን በቴሌቭዥን እያሳዩ ነው፡፡ ምን ያድርጉ ይህ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ ይህንን ነው የሚወደው፡፡ ማንዴላ ለነጻነት የተደረገ ረዥሙ ጉዞ በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ አስተናጋጆቹን እና ፓይለቶቹን ኢትዮጵያውያን ሆነው ሲያገኟቸው የተሰማቸውን ስሜት ይህ ቅኝ ያልተገዛ ሕዝብ አያውቀውም፡፡

«እስኪ የትምህርት ቤቶቹን ስሞች እይ፤ አጸደ ሕፃናቱም፣ አዳዲስ የግል ኮሌጆቹም በአብዛኛውኮ ኢትዮጵያዊ ስም የላቸውም፡፡ እነዚህ ሦስት ሺ ዓመት በነጻነት ኖረች በምትባል ሀገር የተከፈቱ፣ እነዚህ ፈረንጆች ሳይደፍሯት በነጻነት ኖረች ተብሎ በሚዘመርላት ሀገር የሚያስተምሩ፣ እነዚህ ቅኝ ሳንገዛ ድንበራችንን አስከብረን ኖርን እያሉ ልጆቿ በሚፎክሩላት ሀገር ያሉት ትምህርት ቤቶች ፈረንጅኛ ስያሜን በፈረንጅኛ ካልሰጡ ያደጉ አይመስላቸውምኮ፡፡ ከሀበሻ

ገና ይልቅ የፈረንጅ ክሪስማስ የሚያከብሩት ትምህርት ቤቶቻችን በርግጥም ቅኝ ግዛት ያልነካን መሆናችንን ይመሰክራሉ፡፡

«የቻይናን፣ የጃፓንን እና የሕንድን ፊልም ያየ ሰው ሰዎቹ ኢትዮጵያውያን ሆነው ቢሠሩት እንኳን የቻይና፣ የሕንድ እና የጃፓን ፊልም መሆኑን ማወቅ ይችላል፡፡ እዚያ የሚያየው ባሕል እና ኑባሬ፣ እዚያ የሚታየው ሥርዓት እና ወግ፣ እዚያ የሚደረገው ድርጊት፣ ሃሳቡ እና አመለካከቱ የቻይና፣ የሕንድ፣ የጃፓን ነው፡፡ እስኪ አባዬ ብዙዎቹን የኛን ሀገር ፊልሞች ተመልከት፡፡ ሰዎቹ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ባናውቅ ኖሮ የኢትዮጵያ ፊልም መሆኑን እንዴት እናውቅ ነበር? ደግነቱ ብዙዎቹን የፊልም ተዋንያን በድራማ እና በቴሌቭዥን ማስታወቂያ አስቀድመን ማወቃችን ጠቀመን እንጂ፣ ተቀጥረው ለሌላ ሀገር የሚሠሩ ነበር የሚመስለን፡፡

«አለባበሱ፣ ቤቱ፣ መኪናው፣ ባሕሉ፣ ጠባዩ፣ ምኑ ነው ኢትዮጵያዊ? ሃሳቡ እንኳን ሳይቀር የፈረንጅ ሃሳብኮ ነው፡፡ ፈረንጅ መንገድ ለመንገድ የሚታኮስ ፊልም ስለ ሠራ እኛም በሰላም ሀገር፤ ለዚያውም ከስንት ዓመታት በኋላ ባገኘናት ቀለበት መንገድ ላይ የሚታኮስ ፊልም መሥራት አለብን? የፍቅር ፊልሞቻችን እንኳን የፈረንጅን የፍቅር ጠባያት ነው የሚያሳዩን፤ ሐበሻ አያፈቅርም? ሐበሻ የፍቅር ዘፈን የለውም? በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሶማልኛ፣ በአፋርኛ ፍቅር የለም? ለመሆኑ ሐበሻ ሃሳብ የለውም፤ ተረት የለውም፤ ጉዳይ የለውም፤ ለፊልም የሚበቃ ኑሮ የለውም፣ ለፊልም የሚበቃ ታሪክ የለውም? ቅኝ ሳንገዛ ሦስት ሺ ዓመት በነጻነት ኖረን፣ ድንበር አስከብረን፣ ለፊልም እንኳን የሚበቃ ነገር እንዴት አላተረፍንም?

«ይሄ ዘርፋፋ ከናቴራ ለብሶ፣ ቀበቶ የሌለው ቦርፋፋ ሱሪ ሶርቶ፣ እንደ ባሕታዊ ሠንሰለት ታጥቆ የሚሄደው የሀገሬ ወጣት እውነት ቅኝ ያልተገዛ ነው? አሜሪካውያን ጥቁሮች ለምን ይህንን ዓይነት ልብስ እንደለበሱ ያውቀዋል? በዚያ የባርነት እና የልዩነት ዘመን ቀበቶ እንዳያደርጉ፣ ዘርፋፋ ልብስ እንዲለብሱ ለምን ይደረግ እንደነበር ይገባዋል? እነማን ከትውልድ ሀገራቸው በሠንሠለት ታሥረው ለባርነት እንደተዳረጉ? እነማንስ በተወሰዱበት ሀገር በሠንሰለት ታሥረው በከባድ የጉልበት ሥራ እንደ ተሰቃዩ ያውቀዋል? እነዚያ ለሦስት መቶ ዓመታት የነበረባቸውን ስቃይ ለማስታወስ ያደርጉታል፤ ሌላውን ባህላቸውን አጥፍተውባቸዋልና ይህንን ባህላቸውን ያጠፋባቸውን ታሪክ በመከራ ይስቡታል፡፡ ታድያ ቅኝ አልተ ገዛም ያልከው ወገኔ ይህንን ሲለብሰውስ ምን ማለቱ ነው?

«እና አባዬ ምናልባት መሬቱ ቅኝ አልተገዛ ይሆናል፡፡ እርሱም ቢሆን ያጠራጥረኛል፡፡ መሬት ማግኘቱ አንዳንዴ ከሀገሬ ሰዎች ይልቅ ለውጮቹ ሲቀናቸው አያለሁና፡፡ የርሱም አመለካከት ተቀይሮ ይሆናል፡፡ እኛ ሰዎቹ ግን ልባችን ቅኝ የተገዛ ይመስለኛል፡፡ ይልቅ ሆኗል ብለን በምናስበውና በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ማስተዋል እንጀምር፡፡ ምናልባት እየሆነ ያለው ሆኗል ብለን ከምናስበው የተለየ እንዳይሆን፡፡»

አባት ትኩር ብሎ ነበር ልጁን የሚያየው፡፡ እርሱም በልጁ ላይ ሆኗል ብሎ የሚያስበውና እየሆነ ያለው ተለያይቶበት፡ ፡

37. ***መታረቅ ወይስ መታረቅ*** **:-** ሰሞኑን የሁላችንንም ተስፋ ከፍ ከፍ አድርጎ የነበረ ነገር ሲጨልም አይተናል፡፡

በአባቶች መካከል የተፈጠረው መለያየት በዕርቅ ሊፈታ ነው ተባለ፡፡ ሽማግሌዎች ተሰባሰቡ ተባለ፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ እና በዝርወት ያሉት አበውም ፈቃደኛ ሆኑ ተባለ፡፡ ቀን ተቆረጠ ተባለ፡፡ ከአዲስ አበባ የተወከሉ ልኡካን አሜሪካ ገቡ ተባለ፡፡ አዲስ አበባ ከሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ተመድበው አሜሪካ የሚገኙት ሊቃነ ጳጳሳት ሳያውቁት እና ሳይሳተፉበት ሽማግሌዎች ተቀበሏቸው ተባለ፡፡ በሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ሳይሆን ሆቴል ዐረፉ ተባለ፡፡ አንዳንድ ሽማግሌዎች ራሳቸው እዚህ ከነበሩት አበው ጋር አይስማሙ ነበር ተባለ፡፡ ዳላስ አውሮፕላን ማረፊያ የደረሰውን ልኡክ ለመቀበል በነበረው መርሐ ግብር ላይ ፍቅር ሳይሆን መቃቃሩ በግልጽ ታይቶ ነበር ተባለ፡፡

ሽማግሌዎቹ ምሥጢር ላለማውጣት ተማምለዋል ተባለ፡፡ ዋናው መፍትሔ ነገሩን ከባለቤቱ ሕዝብ መደበቅ ነው ተባለ፡፡ ከአዲስ አበባ ልኡካን አንዱ ከኛ ጋር ሊነጋገር አይችልም ብለው አሜሪካ ያሉት አባቶች አቋም ያዙ ተባለ፡፡ ሽማግሌዎቹ እያግባቡ ነው ተባለ፡፡ ይህ ከልኡካኑ አንዱ የሆነ ሰው ይቅርታ መጠየቅ አለበት ተባለ፡፡ በመጨረሻም እርቁ ሳይጀመር ተጠናቀቀ ተባለ፡፡ ከዚያም መግለጫ ወጣ፡፡ እኛም አነበብን፡፡

ብዙዎቹን ነገሮች ተባለ «ተባለ» እያልኩ የምዘረዝረው እርቁ ለምን አስፈለገ? ዓላማው ምንድን ነው? ሽማግሌዎቹ እነማን ናቸው? እንዴት ተሰባሰቡ ወይም ተመረጡ? ከዚህ በፊት ያላቸው ችሎታ እና ልምድ ምንድን ነው? እነማን ተወከሉ? ውይይቱ የት እና መቼ ይጀመራል? በምን በምን ጉዳዮች ሊነጋገሩ ወሰኑ? ወዘተ ለሚሉት ጥያቄዎች በተባራሪ ከሚሰሙት ነገሮች በስተቀር እኔ ባይ አካል ምንም ነገር ለማለት ስላልደፈረ ነው፡፡

ምክንያቱም ቦታው የሚዲያ አሠራር እና ጥቅም የማይታወቅበት፤ ነገሮች ከሕዝብ ተነጥለው የሚሠሩበት አሜሪካ ነውና፡፡

እኔ ግን አንድ ነገር እጠይቃለሁ፡፡ ለመሆኑ እነዚህ አካላት መታረቅ ነው መታረቅ ያለባቸው? መታረቅ የሚለው ቃል ሲጠብቅ እና ሲላላ ትርጉሙ ይለያያል፡፡ ሲጠብቅ «መቃናት፣ መገራት፣ መስተካከል፣ መታረም፣» ማለት ነው፡፡ ሲላላ ደግሞ «መስማማት፣ መግባባት፣ ይቅር መባባል» ማለት ይሆናል፡፡

እኔ ግን መጀመርያ መገራት፣ መቃናት፣ መስተካከል፣ መታረም ይቀድማል ባይ ነኝ፡፡ ይህ ቢኖር ኖሮ ስንት የተለፋበት ዕርቅ ባልፈረሰ ነበር፡፡

መጀመርያ መታረቅ የሚያስፈልጋቸው እንዲህ ያለውን ነገር ለመሸምገል የሚነሱ አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በመንፈሳዊነት እና በአካሄድ መታረቅ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ይህ ሽምግልና ሲጀመር ራሳቸው ሽማግሌዎቹም ሆኑ ሕዝቡ ጸሎት እንዲያደርጉ መነገር ነበረበት፡፡ የፍቅር ጠላት የሆነውን ሰይጣን ያለ ጸሎት ማስወጣት ይቻላል ብሎ ማሰብ የወንጌሉን ቃል ማስተሐቀር ነው፡፡ ዓላማቸውን ገልጠው «እኛም ሱባኤ ይዘናል እናንተም ጸልዩልን» ቢሉን ኖሮ ከመካከላችን እግዚአብሔር የሚሰማው አንድ ሰው ባልጠፋ፤ የዚህም ሰው ጸሎት የተወያዮቹን ልብ ባስተካከለው ነበር፡፡ ከዚህም ታልፎ ጸሎት ሕይወታቸው ወደ ሆኑ ገዳማውያን አበው መባውን በመላክ በጸሎት አስቡን መባል አለበት፡፡ በፍቅር እስከ መቃብር የፊታውራሪ አሰጌን እና የፊታውራሪ መሸሻን ለጦርነት የደረሰ ጠብ ያበረደው የዲማ ጊዮርጊስ እና የብቸና ጊዮርጊስ ካህናት ጸሎት እና ልመና መሆኑን ሊቁ ሐዲስ ዓለማየሁ ነግረውን ነበረ፡፡ መቼም ሁለቱ

ተወያዮች ከፊታውራሪ መሸሻ እና ከፊታውራሪ አሰጌ የተሻለ ዕውቀት እና መንፈሳዊነት አይጠፋባቸውም፡፡ ነገር ግን ፍቅር እስከ መቃብር የተጻፈውና የታተመው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ስለሆነ ለነማንዴላ እንጂ ለኛ ዕርቅ አይጠቅምም፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በአሠራር መታረቅ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ሽምግልና ወይ ባህላዊውን አለያም ዘመናዊውን የሽምግልና አካሄድ ያለ በለዚያም ሁለቱንም መያዝ አለበት፡፡ በባህላዊው ሽምግልና የሚፈሩ እና የሚታፈሩ ሽማግሌዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ተው ቢሉ የሚሰሙ፣ ቢራገሙ የሚያደርሱ፣ ቢናገሩ የሚያሳምኑ ሽማግሌዎች፡፡ እኔ እንዳየሁት ግን አሁን ተጀምሮ የነበረውን ውይይት ያስተባበሩት ሽማግሌዎች ከአንድ እና ሁለት ሰዎች በቀር ይሄ ያንሳቸው ነበር፡፡

በዘመናዊው የሽምግልና አካሄድ ደግሞ የቴክኒክ ኮሚቴ እና አማካሪዎች ያስፈልጋሉ፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴው ሽምግልናው ከመደረጉ በፊት ቦታውን፣ ተወያዮችን፣ አጀንዳዎችን፣ አካሄዶችን፣ ችግር ቢያጋጥም የመፍቻ መንገዶችን፣ ወዘተ ቀድሞ በሚገባ የሚሠራ የባለሞያዎች ቡድን ነው፡፡ በዕርቅ እና ድርድር ጉዳዮች ልምድ ያካበቱ፣ መፍትሔ ማመንጨት የሚችሉ ባለሞያዎች ይካተቱበታል፡፡ እነዚህ ባለሞያዎች ከሁለቱም ወገን አማካሪዎች ጋር በመሆን መንገዱን እንደ ዮሐንስ ይጠርጉታል፡፡

አማካሪዎቹ ተወያዮቹን ወክለው በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ቀደም ብለው ይነጋገራሉ፤ የሚያስማሙትን እና የሚያለያዩትን ይለያሉ፤ ከቤተ ክርስቲያን ሕግ እና ሥርዓት፣ ከታሪካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች አንፃር ነገሮችን ይገመግማሉ፡፡ የማስማሚያ ሃሳብም ያመነጫሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ዋናዎቹ ተወያዮች ሲመጡ እነርሱ አማካሪ በመሆን ውይይቱን ያሣልጣሉ፡፡

ሌላው መታረቅ የሚገባቸው ተወያዮቹ ናቸው፡፡ አባቶች ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩ ናቸው፤ ለመንጋው ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው፤ ሌሎችን ያስታርቃሉ ተብለው የሚጠበቁ ናቸው፤ በዕድሜም ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ በዕውቀትም የበለጸጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት እና ውይይቱ እንዲሳካ የቻሉትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው፡፡

አሁን እንደታየው ግን በሁለቱም ተወያዮች ዘንድ ያልታረቁ ነገሮች ነበሩ፡፡

ከአዲስ አበባ የመጡት ተወያዮች እዚያ ለሚገኘው ሕዝብ ምንም አልነገሩትም፡፡ በተባራሪ ከሰማው ነገር በቀር፡፡ ጉዳዩን የቤተ ክህነቱ ሰዎች እንኳን ጥርት ባለ መልኩ አያውቁትም፡፡ እዚህ አሜሪካ ያሉት ሊቃነ ጳጳሳትም በዌብ ሳይት እና ሀገር ቤት በመደወል ከሰሙት በስተቀር በመዋቅሩ መሠረት አልተነገራቸውም፡፡ የሂደቱ አካልም አልነበሩም፡፡ «ባለቤት ያቃለለውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም» ይባላል፡፡ ቤት ውስጥ የቀሩት ልጆች እየተናቁ፣ ከቤት ወጠተዋል የተባሉትን ለማምጣት የሚደረግ ውይይት እንዴት ውጤታማ ይሆናል?

በአሜሪካ ከነበሩት አባቶችም ያልታረቀ ነገር ነበር፡፡

በመጀመርያ ደረጃ ልኡካኑን በተመለከተ ማለቅ ያለበት መጀመርያ ነው፡፡ በሌላም በኩል አንድ አካል ወኪሉን ከላከ እርሱኑ ተቀብሎ መነጋገር ይቻል ነበር፡፡ በመግለጫው ላይ የቀረበው ስሞታ ቀድሞ ሊያልቅ ይገባው የነበረ እንጂ የውይይቱ ማፍረሻ መሆን አልነበረበትም፡፡ ለመሆኑ አንደኛው ወገን ስለሌላው ወገን ሲጽፍ፣ ሲናገር፣ ሲያወግዝ አልኖረም እንዴ) ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው መግለጫ፣ በጻፈው ጽሑፍ እና በወሰነው ውሳኔኮ ሁሉም አበው አሉበት፡፡ እዚህ ያሉት አባቶችም ሲጽፉ፣ ሲያወግዙ ነው የኖሩት፡፡ እንዴት አንድ ሰው ብቻ የጉዳዩ ባለቤት ሊሆን ቻለ?

በሌላስ በኩል መለያየት፣ መወጋገዝ፣ መጻጻፍ እና መተቻቸት ባይኖር ኖሮ የዕርቅ ውይይትስ ያስፈልግ ነበር? የተጋደሉ፤ የተታኮሱ፤ የተጨፋጨፉ ሰዎችኮ በፖለቲካው መድረክ ተወያይተዋል፤ ታርቀዋል፡፡ እንኳንስ የሃይማኖት ሰዎች፡፡ ደግሞስ መንፈሳዊ ሰው ይቅርታ ልጠይቅ ይላል እንጂ እገሌ ይቅርታ ይጠይቀኝ ማለት የጀመረው ከመቼ ወዲህ ነው? ይቅር በለው የሚል እንጂ ይቅርታ እንዲጠይቅህ አስደርገው የሚል ወንጌል ተጻፈ እንዴ?

እስከ ዛሬ በታሪክ እንደታየው በመንበር ላይ የተቀመጠ እና ሥልጣኑን የተቆናጠጠ አካል ነበር ምክንያት እየፈጠረ ዕርቅን እና ውይይትን የሚያደናቅፈው፡፡ አሁን ግን ያኛው ወገን ለእምቢታ ቸኮለ፡፡ ብዙ ሰዎች የደነቃቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ዕርቁን መደገፉ፣ አሜሪካ ድረስ ልዑካን ልኮ ለመነጋገር መፍቀዱ ነበር፡፡ ይህንን መልካም ዕድል ተጠቅሞ፤ ፈተናዎችን ሁሉ በመቋቋም ለቤተ ክርስቲያን አንዳች ጠቃሚ ነገር መሥራት እዚህ ያሉት አበው ድርሻ ነበር፡፡ ግን አልታደልንም፡፡

ሌላው ቀርቶ ነገሩን በዓለማዊ መንገድ ካየነው ከአዲስ አበባ አሜሪካ ድረስ መመጣት አልነበረበትም፡፡ ወይይቱ በአማካይ ቦታ መሆን ነበረበት፡፡ ነገር ግን ችግሩ ወዳለበት ቦታ ያኛው አካል መምጣቱ በራሱ አንድ ሊደነቅ የሚገባው ርምጃ ነበረ፡፡ «እናንተ ኬንያ ኑና እንወያይ» ከሚለው ትዕቢት ይልቅ «ያላችሁበት መጥተን እንወያይ» ማለቱ አዲስ ጅምር ነበር፡፡ ምናለበት እንደ በላዔ ሰብእ ጠብታ ነገር ስናገኝ እንደ ሰይጣን ከመድፋት፣ እንደ ድንግል ማርያም ጥላችንን ብንጥልበት እና ሚዛን እንዲደፋ ብናደርገው?

አንዳንድ አካላት የችግሮችን መኖር ይፈልጓቸዋል፡፡ ጭር ሲል አይወዱም፡፡ በችግሩ እያመካኙ የፖለቲካ ሂሳብ መሥራት፤ ገንዘብ መሰብሰብ እና ድጋፍ መሰብሰብ ለምደዋል፡፡ ችግሩ ከተፈታ የመታገያ አጀንዳ እናጣለን ብለው ይፈራሉ፡፡ ውይይቱ ሊካሄድ ነው በተባለበት ሰሞንና በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ የሚሰሙ ድምፆች ነበሩ፡፡ ትላልቅ የሚባሉ አባቶች ሳይቀሩ ለምን ውይይት ይደረጋል? እያሉ ጫና ሲያሳድሩ ነበር፡፡ የአሜሪካው ልኡካን ይህንን ጫና መቋቋም የቻሉ አይመስለኝም፡፡ ይህ ልብ ቀድሞ መታረቅ ነበረበት፡፡ ምንም እንኳን በቂ መረጃ ባለማግኘቱ ሊወቀስ ባይችልም፤ ሕዝቡ በተባራሪ የሰማውን በመያዝ አይዟችሁ በርቱ፤ ከጎናችሁ ነን፤ ይህ እና ያ ሃሳብ አለን እያለ ማበረታታት ነበረበት፡፡ መጸለይ ነበረበት፡፡ ሽማግ ሌዎቹንም የት ደረሰ? እያለ በግድም ቢሆን መጠየቅ ነበረበት፡፡

አሠራራቸውን እንዲያስተካከሉ እርማት መስጠት ነበረበት፡፡ ልኡካኑ ላይ ጫና ማሳደር ነበረበት፡፡ እንዴት በተልካሻ ምክንያት ይህንን ትልቅ ዳቦ ሊጥ ታደርጋላችሁ? ብሎ መቆጣት ነበረበት፡፡ ዋንጫ እንዲመጣ ከመጫወት ይልቅ ዋንጫ እንዲመጣ የመጠበቅ አካሄድ እስከ ዛሬም አላዋጣን፤ ዛሬም አላዋጣን፡፡ ቀድሞ መታረቅ የነበረበት አንዱ ነገር ይህ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ሳይታረቁ ዕርቁ ተጀመረና፤ እንደተጀመረ አለቀ ተባለ፡፡ ከዚያም መግለጫ ወጣ ተባለ፤ ለመግለጫውም መልስ ተሰጠው ተባለ፡፡ ሕዝቡም የሚያወራበት አጀንዳ አገኘ ተባለ፡፡ ችግራችንም ይቀጥላል ተባለ፡፡

38. **[ኑ እንፍጠር](#)**

ግሪኮች እንዲህ ይላሉ፡፡

በድሮ ዘመን የአቴና ሰዎች መልካም መሪዎችን በማጣታቸው ምክንያት ይማረሩ ነበር፡፡ አንድ ቀን ወደ ኦሊምፐስ ተራራ ወጥተው የአማልክት ንጉሥ የሆነውን ዜውስን ለመኑት፡፡ «እባክህ ከመንደራችን እስከ ሀገራችን ድረስ ባሉት ቦታዎች በመልካም የሚያስተዳድሩ መሪዎችን ስጠን» አሉት፡፡ ዜውስም «ፊንቄያውያን መጥተው ይግዟችሁን?» ሲል ጠየቃቸው አቴናውያንም «አንፈልግም» አሉ፡፡ «ካርታጎዎች መጥተው ይግዟችሁን?» አላቸው ዜውስ አሁንም «በቅኝ መገዛት አንፈልግም» አሉ፡፡ እንደገናም «ሮማውያንን አምጥቼ በላያችሁ ልሹምባችሁን?» ሲል ጠየቃቸው፡፡ አቴናውያን በዚህም ሊሰማሙ አልቻሉም፡፡

ዜውስ ባቢሎናውያንን፣ ፋርሶችን፣ ኬጢያውያንን እና ጢሮሳውያንን አምጥቶ በአቴና አውራጃዎች ለመሾም ፈቃዳቸውን ጠየቃቸው፡፡ አቴናውያን ግን ፈጽሞ አይሆንም አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዜውስ «ታድያ ከየት አምጥቼ ነው መልካም መሪዎችን የምሰጣችሁ?» ሲል ጠየቃቸው፡፡ «ከመካከላችን ስጠን» ብለው መለሱለት፡፡ በዚህ ጊዜ ዜውስ አዝኖ እንዲህ አላቸው፡፡ «ጥሩ በሬ ለማግኘት ጥሩ ጥጃ፣ ጥሩ ጠቦትም ለማግኘት ጥሩ ግልገል፣ ጥሩ ወፍ ለማግኘት ጥሩ ጫጩት፣ ጥሩ ዶሮም ለማግኘት ጥሩ ዕንቁላል ያስፈልጋል፡፡ እናንተ በመልካም ያላሳደጋችኋቸውን ልጆች እኔ እንዴት አድርጌ በመልካም እሾማቸዋለሁ፡፡ እኔ ሰውን ፈጠርኩ፤ መሪዎቻችሁን ግን እናንተ ፍጠሩ፡፡»

መሪን ማን ይፈጥረዋል?

ፓርቲ? ድርጅት? ትግል? ሰላማዊ ሰልፍ? ንግግር? ምርጫ? ወይስ ሌላ? እንደ ዜውስ ምክር ከሆነ ሕዝብን አምላክ፣ መሪን ግን ሕዝብ ይፈጥረዋል፡፡ መሪዎች የሕዝቡ ሥዕሎች ናቸው፡፡ ከተወለዱበት ቀን እስከ ተሾሙበት ቀን ድረስ በማኅበረሰቡ መካከል ሲኖሩ ሕዝቡ በአንድም በሌላም መልኩ የሳለባቸውን ሥዕል ነው በሥልጣን ወንበር ላይ ሆነው የሚያሳዩን፡፡ መሪዎቻችን የተረቶቻችን፣ የዘፈኖቻችን፣ የአባባሎቻችን፣ የእምነቶቻችን፣ አመለካከቶቻችን፣ የአኗኗራችን የአበላላችን እና የአጠጣጣችን ውጤቶች ናቸው፡፡

ወላጅ ሳሎን ሲመገብ ጓዳ ውስጥ ግቡ ይባሉ ከነበሩ ልጆች ግልጽነትን መጠበቅ፣ ከወላ ጆቻቸው ጋር በአንድም ጉዳይ ሳይወያዩ እና በሃሳብ ልዕልና ለውሳኔ ሳይበቁ ከሚያድጉ ልጆች ተወያይቶ መግባባትን እና ከኃይል እና ከሥልጣን ይልቅ በሃሳብ ልዕልና መተ ማመንን መጠበቅ፣ ልጅ እና ፊት አይበርደውም እየተባሉ ከሚያድጉ ልጆች መካከል የሕፃናትን መብት የሚያከብሩ መሪዎች መመኘት፤

ወላጆቻቸው ችግሮቻቸውን ተነጋግረው፣ተከራክረው እና ጊዜ ወስደው ከመፍታት ይልቅ በትንሽ በትልቁ ሲደባደቡ እና ሲፋቱ እያዩ ካደጉ ልጆች መካከል የክርክር እና የውይይት ባሕል ያለው፣ ልዩነቱን ኣቻችሎ የሚኖር፣ ጊዜ ወስዶ ችግሮችን የሚፈታ እና በትንሽ በትልቁ ፓርቲውን ጥሎ የማይወጣ መሪ መጠበቅ፣ ሴቷ ልጅ በቤት ሥራ ስትዳፋ እያየ እርሱ ሲራገጥ ከሚውል ልጅ መካከል የጾታ እኩልነትን የሚያሰፍን መሪ መሻት፣ ከየቢሮው እና ከየፋብሪካው፣ ከመንግሥት ካዝና እና ከቤተ እምነት ሙዳየ ምጽዋት፣ ከግብር እና ከቀረጥ፣ በተመነተፈ ገንዘብ ከሚያድግ ልጅ መካከል የሀገሩን ገንዘብ የማይበላ መሪ መፈለግ፣

በቤተሰቡ መካከል በሚነገሩ አባባሎች እና ተረቶች፣ ስድቦች እና ርግማኖች አንዱ ብሔረሰብ ከሌላው ተለይቶ ሲሳቅበት እና ሲቀለድበት፣ሲተረትበት እና ሲሾፍበት፣ ሲናቅ እና ሲንቋሸሽ እየሰማ ያደገን ልጅ አድገህ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት የምታሰፍን መሪ ሁን ብሎ ያለ ዐቅሙ ማሸከም፣ አስተማሪውን እያንጓጠጠ፣ እየተደባደበ እና በትምህርት ሰዓቱ እየቀለደ የሚያድግን ልጅ ማይምነትን ከሀገር የምታጠፋ መሪ ሁን ማለት፣ ታናናሽ ወንድሞቹን እና እኅቶቹን እያንቆራጠጠ፣ የሠፈር ሴቶችን መቆሚያ መቀመጫ እያሳጣ፣ ለምን ቀና ብላችሁ ኣያችሁኝ ብሎ የሸሚዙን እጅጌ እየሰበሰበ ያደገን ልጅ ዴሞክራሲያዊ መሪ እንዲሆን መመኘት ያልዘሩትን ማጨድ ነው።።

በሀገራችን ጀግንነት ስለሚደነቅ፣ ጀግናም ስለሚከበር፣አንበሳ እና ኣጋዝን፣ ነብር እና ዝሆን መግደል ስለሚያሸልም፣ በባሕላዊው ትምህርት ፈረስ ጉግስ እና ጦር ውርወራ፣ ሽመል ስንዘራ እና ጋሻ ምከታ፣ ውኃ ዋና እና ዝላይ ከልጅነት ጀምሮ ይሰጥ ስለነበር ሀገራችን ኣያሌ የጦር ሜዳ ጀግኖችን ኣፍርታለች።። በጠላት ላይ አስደናቂ ድል የሚቀዳጁ፣ ድንበራቸውን ለአፍታም የማያስደፍሩ፣ ጀግንነት ከነጭ እና ቀይ የደም ሴላቸው ጋር ሦስተኛ ሕዋስ የሆነላቸው አርበኞችን ኣፍርታለች።። ነገር ግን የአመራር፣ የአስተዳደር እና የአሠራር ጀግኖችን፣ የዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብት ጀግኖችን፣ የክርክር እና የውይይት ጀግኖችን ገና አላፈራችም።። የመቻቻል አና የመደማመጥ፣ ተቃራኒን ሃሳብ፣ የማንደስትበትን ውሳኔ፣ የምንጠላውን አመለካከት እንደ በጎ የሚቀበሉ መሪዎችን ገና አላገኘችም።። አንድ ሰው እንዳለው «ኮምፒውተሩ ባልተጫነበት ሶፍት ዌር ሊሠራ ኣይችልም»።።

ለመሆኑ፤ ከሠፈር እድር እስከ ቤተ መንግሥት፣ ከቀበሌ እስከ ፓርላማ፣ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ የምትፈልጋቸውን ዓይነት መሪዎች ለማፍራት የሚያስችል ዘፈን፣ ተረት፣ አባባል፣ ጨዋታ፣ ብሂል፣ ወግ፣ ባሕል፣ ሥርዓት አለንን? እንደ ኢትዮጵያ ባለች ሚዲያ እና ንባብ፣ ትምህርት እና ለዘመናዊ ሥልጣኔ መጋለጥ ውሱን በሆነባት ሀገር፤ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ከአካባቢያዊ ባሕላቸው እና ወጋቸው ጋር ነው በሚያሳልፉባት፤ ካነበቡት መጽሐፍ የሰሙት ተረት፣ ከተማሩት ትምህርት የበሉት ድግስ፣ ከተከታተሉት ሚዲያ የዋሉበት ጨዋታ፣ ካገኙት ሥልጠና ያመሹበት የልቅሶ ድንኳን በሚበዛበት ማኅበረሰብ ውስጥ፤ ኅብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን መሪዎች ለመፍጠር የሚያስችል ባሕል አለውን?

አባቱ አንድም ቀን ጋዜጣ ሲያነብ ያላየው፣ እንዲያነብም ያላደረገው፣ በቤታቸው ውስጥ ከትምህርት መጻሕፍት በቀር ሌላ መጽሐፍ ሲገዛ አይተው የማያውቁ፣ እናቶች ከብበው ቡና ላይ፣ አባቶች ከበበው ጠጅ ቤት እና ልቅሶ ቤት ሲያውካኩ እንጂ መጽሐፍ ሲያነብቡ፣ ባነበቡት እና በተረዱት ነገርም ሲከራከሩ ያልሰማን ልጅ፣ ነገ አድጎ ስለ ፕሬስ ነጻነት ዘብ ይቆማል የሚለው ማን ደፋር ነው? ስሞቻችን እንኳን «በለው ፣ቁረጠው፣ ፍለጠው፣ አንቆራጥጠው፣ ግዛቸው፣ ዋኻባቸው»፣ በሆኑበት ሀገር፣ መሪነትን ሲያስብ ጉልበትን የማያስብ መሪ ከየት እናመጣለን?

ቤተሰቦቻችን፣ እድሮቻችን፣ ዕቁቦቻችን፣ የትምህርት ክፍሎቻችን፣ የጽዋ ማኅበሮቻችን፣ ሰንበቴዎቻችን፣ መጅሊሶቻችን፣የእምነት ተቋሞቻችን፣ የወጣት እና የሴት ማኅበሮቻችን፣ የሞያ እና የሲቪክ ማኅበሮቻችን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶቻችን፣ ምን ዓይነት መሪዎች አሏቸው? ስለ ፓርላማው እና ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለ ካቢኔው እና ስለ ምክር ቤቱ ከመነጋገራችን በፊት በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ታላቁን ቦታ ስለ ሚይዙት ስለ እነዚህ ተቋማት አሠራር፣ አመራር፣ የመሪዎች አመራረጥ፣ ድምጽ አሰጣጥ እስኪ እንነጋገር፡፡

ለመሆኑ በዕድር እና በዕቁብ የምረጡኝ ዘመቻ አለ? በየትምህርት ቤቱ የክፍል ኃላፊን ስም ጠሪ መምህር ይመርጠዋል፣ ወይስ ሃሳቡን አቅርቦ ብትመርጡኝ ለክፍላችን እንዲህ እና እንዲያ አደርጋለሁ ብሎ ተማሪው ይመርጠዋል? ለመሆኑስ በክፍል ኃላፊ ምርጫ ተማሪዎች በኮሮጆ ውስጥ ድምጽ ይሰጣሉ? በእድር እና በዕቁብ ሊቀመንበር እና ሰብሳቢ ምርጫ ጊዜ ድምጽ እንዴት ነው የሚሰጠው፣ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ፣ ግልጽ እና የማይጭበረበር ነው?

የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች፣ ዲኖች፣ የዲፓርትመንት ሊቃነ መናብርት ሃሳባቸውን አቅርበው፣ ምረጡን ብለው፣ ተወዳድረው፣ የምረጡን ዘመቻ አድርገው፣ ተከራክረው በድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ተመርጠው የሚመሩበት ዘመን መቼ ነው የሚመጣው? ተማሪዎችስ የተማሪ ምክር ቤቶችን መሪዎች፣ የፓርላማ አባላት በሚመረጡበት ሥርዓት የሚመርጡት እና ለወደፊቱ የፖለቲካ እና የመሪነት ሕይወታቸው ልምድ የሚቀስሙት መቼ ነው?

ታድያ እነዚህን ሁሉ እንደዋዛ ዘልለን የሀገር መሪ ከየት እናገኛለን፡፡ ዜውስ እንዳለው እኛ ያልፈጠርነውን መሪ ፈጣሪ ከየት ያመጣዋል? ከአፍሪካ? ከአውሮፓ? ከአሜሪካ? ከቻይና? ወይስ ከላቲን አሜሪካ? ለምን መንደራችንን በተገቢው መንገድ ከማስተዳደር አንጀምርም፡፡ በኮንዶሚኒየም ሕንፃዎች፣ በሪል እስቴት መንደሮች፣ በአፓርትመንቶች፣ ግልጽ ምርጫን፣ አንዳች የለውጥ ዕቅድ ይዞ ተመርጦ መሥራትን፣ በየጊዜው ሪፖርት ማድረግን፣ ተሰብስበን ሥራን መገምገምን፣ በሚገባ የሠራውን መሸለምን፣ በሚሰጠን አካባቢያዊ ኃላፊነት ያለ ቸልታ ማገልገልን ለምን እንጀምረውም? መሪዎችን ለምን አንፈጥርም? መሪነት ፓርላማ ከገቡ፣ ከተሾሙ እና ሥልጣን ከያዙ በኋላ እንዴት ይጀመራል? ሰዎች እየመሩ ቆይተው ወደ ሥልጣን መምጣት አለባቸው እንጂ ወደ ሥልጣን መጥተው መሪነትን መማር የለባቸውም፡፡

የዕድሩ ሙሴ ከተመረጡ ስንት ጊዜያቸው ነው? ሥልጣናቸውስ ገደብ አለው? የዕቁቡ ዳኛ ለስንት ዓመት ነው በዓመት አንድ ዕጣ በነፃ እየበሉ የሚኖሩት? የሥልጣናቸው ገደብ እስከ መቼ ነው? የሰበካ ጉባኤው ምክትል ሊቀ መንበር፣ የአካባቢው መጅሊስ ሊቀ መንበር፣ የወጣቶች ማኅበር ሰብሳቢው፣ የሴቶች ማኅበር ሊቀ መንበር፣ የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት፣ የኮሚኒቲው ሰብሳቢ፣ የቦርዱ ሊቀ መንበር፣ የኮሚቴው ሊቀ መንበር፣ የክለቡ ፕሬዚዳንት፣ የድርጅቱ ፕሬዚዳንት፣ የሥልጣናቸው ገደብ ይታወቃል? እዚያ ቦታስ ከተቀመጡ ስንት ጊዜ ሆናቸው? የሚተካቸው ሰው ስላጡ ነው? እርሳቸው ተቀብተው ነው የተቀመጡት? ለመሆኑስ እንዴት እንደሚቆዩ እያሰቡ ነው የሚኖሩት ወይስ ጥሩ ሥራ ሠርተው እንዴት ለሌላው እንደ ሚያስረክቡ? ታድያ በጊዜ ገደብ ሥልጣን ላይ የሚወጡ፣ ጊዜያቸው ሲደርስ ሪፖርታቸውን አቅርበውና የሚገባቸውን ሠርተው ወንበራቸውን ለሌላው የሚያስረክቡ መሪዎች ከየት ነው የምናገኘው? ከመካከላችን ያልፈጠርናቸውን ከየት እናስመጣ?

ኑ በየአካባቢያችን የነገ መሪዎቻችንን እንፍጠር፡፡ ሕዝብ ነው መሪውን በአርአያው እና በአምሳሉ የሚፈጥረው፡፡ መሪ በአንድ ቀን ምርጫ፣ በአንድ ሰሞን ንግግር ኣይፈጠርም፤ መሪ በሂደት የሚገኝ ነው፡፡ ባሕሩ ያልያዘውን ዐሣ መረቡ አያጠምደውም፡፡ ኩርንችት ተዘርቶ በለስ፣ እሾህ ተዘርቶም ወይን የሚያበቅል መሬት የለም፡፡

39. [«ጨለማን ዘወትር ከመውቀስ ቁራጭ ሻማ መለኮስ »]

በዲ. ዮሐንስ መኮንን

ለውድ የዲያቆን ዳንኤል ብሎግ ታዳሚዎች

እንኳን ለጦመ ፍልሰታ በሰላም አደረሳችሁ ሱባኤው የግል እና የቤተክርስቲያናችን ችግሮቻችንን መፍቻ ያድርግልን፡፡

ወንድማችን ዲ.ን ዳንኤል ብዙዎቻችን ፈራ ተባ ስንልበት የነበረውን የቤተ ክህነቱን ጉዳይ ለአደባባይ አብቅቶታል፡፡ ምንም እንኳን ሰው ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ቢሆንም!! ለውይይት ክፍት ለማድረግ ቀዳሚውን ሰማዕትነት (ምስክርነት) ከመውሰዱም ሌላ በበኩሉ የታዩትን የመፍትሔ ሀሳቦች ሰንዝሯል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በርካታ አርቶዶክሳውያን ወጣት ምሁራን የመጀመሪያ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲገሪ ማሟያ ጥናታቸውን በቤተ ክርስቲያን ዙርያ ማድረግ እየተለመደ መጥቷል፡፡ አንድ ወዳጄ ታዲያ ጥናቱን በቤተ ክርስቲኒቱ ዙሪያ ማድረግ ፈልጎ የመነሻ ችግር (statement of the problem) ማግኘት ይቸገረው እና ፕሮፌሰሩ ዘንድ በመሄድ የገጠመውን ችግር ይነገራቸዋል፡፡ መምህሩም «እንዴት የመነሻ ችግር ታጣለህ? ቤተክስቲያን ማለት በራሱ ችግር አይደለም ወይ?» በማለት መልሰውለታል፡፡ አሁን አሁን ከችግሮቹ ብዛት፣ ስፋት እና ጥልቀት የተነሳ «ቤተ ክህነት» ማለት «ችግር» የማለት ያህል ሆኗል፡፡

• በዲ.ን ዳንኤል ሐሳቦች ላይ ተጨማሪ አስተያየቶች

ወንድማችን ዲ.ን ዳንኤል ባቀረበው የቤተክህነቱ ችግሮች ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፡፡ ነገር ግን በእኔ አተያይ ችግሮቹን እንጂ ጥልቀታቸውን (magnitude of the problem) አላሳየንም፡፡

የቀረቡት ችግሮች ጥቅል በመሆናቸው ግለሰባዊና ተቋማዊ ጉዳዮችን መለየት አላስቻለንም

ዳንኤል ያቀረባቸው አብዛኞቹ የመፍትሔ ሃሳቦችም የወል በመሆናቸው እኔ ባይ ተጠያቂ ባለቤት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

የመፍትሔ ሃሳቦቹም ዝርዝር የአፈጻጸም መርሐግብር ሊዘጋጅላቸው በሚችል መልኩ መሰናዳት ይኖርባቸዋል፡፡

በግል የታዩኝ የመፍትሔ ሃሳቦች

- ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከወሰንን ፤

- ከሃገር ውስጥ እና ከሃገር ውጭ ከሚገኙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ምሁራን፣ ምእመናን የተውጣጣ የችግሮቹን ዓይነታቸውን እና ጥልቀታቸውን (magnitude of the problem) የሚጠና እና የመፍትሔ ሃሳቦችን የሚያሰባስብ ጉባኤ (council) ብናቋቁም፡፡ ጉባኤውም ቤጊዜው የደረሰበትን ለምእመናን የሚያሳውቅበት መንገድ መቀየስ፡፡

- ሙሉ ጊዜያቸውን ለዚሁ ሥራ ማዋል፣ ማስተባበር እና መምራት የሚችሉ የሰው ኃይል እና ቁሳቁስን ማደራጀት፡፡

- ችግሮቹን በቅደም ተከተል መፍታት የሚያስችለን የአገልግሎት መዋጮ (levis fund) የሚሰበሰብበትን እና በአግባቡ ገንዘቡን የታለመለት ጉዳይ ላይ ብቻ ወጪ መደረጉን የምንቆጣጠርበትን መንገድ መቀየስ፡፡

- የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በመለየት የሚያስፈልገንን የሰው እና የቁሳቁስ ልክ ብናዘጋጅ

- ዕቅዶችን የመፈፀሚያ ዝርዝር ቅደም ተከተል እና የሥራ ክፍፍል (manual) ማዘጋጀት

ይህንን ማድረግ ካልቻልን ችግሩን ከመተረክ አልፎ የተጨበጠ ሥራ ሳንሠራ እንቀራለን፡፡

«ጨለማን ዘወትር ከመውቀስ ቁራጭ ሻማ መለኮስ »

ከአዘጋጁ

ሴሎች አንባብያንም አስተያየቶቻችሁን እና የመፍትሔ ሃሳቦቻችሁን ሠንዝሩ፡፡ እየበሉ እየጠጡ ዝም .....

[ሕዝቤ ዕውቀት በማጣት ጠፋ (ሆሴዕ 4፣6)]

ሰሎሞን ይሼይሰ - ሚኒሶታ

እንደ እኔ እምነት የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ከውጭ ሆኖ መፍታት አይቻልም፡፡ ውኃን ከውኃ ውጭ መዋኘት እንደማይቻለው ሁሉ፡፡ በውስጡ ያሉ አገልጋዮች ችግሩን ተረድተው የመፍትሔው አካል መሆን አለባቸው፡፡ እኛ ከውጭ ያለነው ድጋፍ ሰጭ ነው ልንሆን የምንችለው፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የሚገኙ ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ ካህናት፣ ሰባክያን፣ ዘማርያን እና የሰበካ ጉባኤ አመራሮች ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን ያሉ ችግሮች እንዲቀጥሉ የሚፈልጉ አይደሉም። የችግሩ ተዋንያን ጥቂቶች ተጠቂዎች ግን ብዙዎች ናቸው። በመሆኑም የመጀመርያው ነገር ዕውቀቱን እና ንቃቱን መፍጠር መሆን አለበት።

በመሆኑም የሚከተሉትን ነገሮችን መጠቆም እወዳለሁ።

1 ለንስሐ አባቶቻችን እና ለሰበካ ጉባኤያት ኮፒ እያደረግን ብንሰጣቸው እና ብናወያያቸው።

2 ይበልጥ ደግሞ ገንዘባችንን አሰባስበን እነዚህን ጽሑፎች በመጽሐፍ መልክ አሳትመን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አባቶች እና አገልጋዮች እንዲደርሳቸው ብናደርግ

ይህ ጎትመት ደግሞ በቀላሉ እንዲዳረስ ከፈለግን የጎትመቱን ወጭ እኛ በመሸፈን በነጻ ወይንም በርካሽ እንዲያገኙት ብናደርግ ጥሩ ነው።

3 የመንግሥት አካላት እነዚህን ሃሳቦች እንዲያገኟቸው መንገዶችን ብናመቻች። እንደኔ ሃሳብ የመንግሥት አካላት ሁሉ ችግሩን ይፈልጉታል ተብሎ መታመን የለበትም። ከባለሥልጣናትም ኮ የቤተ ክርስቲያን ነገር የሚያሳስባቸው ይኖራሉ።

4 ሚዲያዎችም እነዚህን ሃሳቦች እንዲያንፀባርቁና ከእነዚህም የተሻሉ ሃሳቦችን እንዲያቀርቡ ብናበረታታቸው።

እንደእኔ እንደእኔ...

ሲሎንዲስ ዘአውሮፓ

የዲ. ዳንኤል የመፍትሔ ሃሳቦች መንፈሳዊ ምክርንና ተግባራዊ አካሄዶችን ያካተቱ ነበሩ፤ለዚያም ነው አንዳንዶቹ ጥቅል የሚሆኑት።ዲ. ዮሐንስ ያነሳሀቸው ነጥቦችና አካሄዶች ለዘላቂ መፍትሔ የሚበጁ ተግባራዊ አካሄዶች ናቸው። አሁንም ግን ከእነዚህ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውና ወደ ተጠቀሱት መንገዶች የሚያመጡ ጅምሮች ያስፈልጉናል፤ አለበለዚያ አሁንም የምንቆመው ጥቅል (abstract) የሆኑ ዕቅዶች ላይ ነው

ለምሳሌ 'እንዲህ ብናደርግ' ተብለው ለተጠቀሱት አሳማኝ መፍትሔዎች ኃላፊነቱን ወስዶ የሚሰራው አካል አሁንም ግልጽ አይደለም

እንደእኔ እንደእኔ...

1.የቤተ ክህነቱን አሰራር የከለለው መጋረጃ መከፈት አለበት

የሚነሱት የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ ለመወያየትም ሆነ ለመስራት ከምዕመናን ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክህነትም ተነሳሽነት መኖር፣እንዲኖርም መሰራት አለበት።ለዚህ ደግሞ አስተዳደራዊ አካሄዶችን የሰወረው መጋረጃ መከፈት አለበት። በሌላው ዘንድ የጠፋውንና ምዕመኑ የያዘውን ፈሪሃ እግዚአብሔርና መንፈሳዊነት ተጠቅመው የቤተ ክህነቱ መጋረጃ እንደ መቅደስ መጋረጃ እንዲታይ የሚፈልጉ ሐናንያውያን አሉ። በየአጥቢያው የሚመረጡ የሰበካ ጉባኤ አባላት የምዕመኑ ተወካይ ናቸውና ቢያንስ አበይት የቤተ ክርስትያን አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን አውቀው ለምዕመኑ እንዲያሳውቁ ብሎም ልዩ ውሳኔዎች ሲሰጡ እንዲገኙና እንዲሳተፉ መደረግ አለበት።እንደአማራጭ ቤተ ክህነቱ በየ2 ወይም 3 ወሩ የሚያወጣው አስተዳደራዊ የጎትመት ውጤት፣ለምዕመኑ በመረጃ የሚደርስበትና አስተያየት የሚቀበልበት ድረ ገጽ መክፈት..የመሳሰሉ ጅምሮች ሲፈጸሙ ግልጽ ወደሆነና ለውይይት ወደሚያመች መንገድ ይወስዱናል። እናም እንደ አንድ የቤተ ክርስትያን ምዕመን አስተዳደራዊ አካሄዶችን የማወቅና የመሳተፍ ድርሻችንን ልናስጠብቅ ይገባል ባይ ነኝ፤ ለጊዜው ይህን ጥያቄ ልናነሳ ልንወያይ የምንችለው በየቤተ ክርስትያኑ በሚገኘው የሰበካ ጉባኤ በኩል ነው...መቀሳቀስና መንቀሳቀስ ያስፈልጋል

2.መሪነቱን ይዞ የሚያስፈጽመውን አካል መወሰን

በምዕመኑ የሚነሱትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለቤተ ክህነት የሚያደርስና መልሱንም የሚያሳውቅ ጉዳዩን ጀማሪ አካል ያስፈልጋል(በመጠኑ ተጠቅሷል)።እስካሁን ባለው መዋቅር ይህ አካል ከቤተ ክርስትያን አሰራር ውስጥ ያለ መሆን ካለበት ሊሆን የሚችለው ብቸኛ አካል ማኅበረ ቅዱሳን ነው።ነገር ግን እርሱም እስካሁን ወደ ሁሉም ምዕመን እንደሚፈለገው የደረሰ አካል ኣይደለም፤ጥቂት የማይባል ሰውም ለጊዜው በተሳሳተ መልኩ ተረድቶታል። እኔ ይህን አካሄድ ብመርጥም ሌላው አማራጭ ምዕመናንን ማዕከል ያደረገ ጎብረት መመስረት ነው፤እንዴት ይመስረትና ከቤተ ክህነቱ ጋር ችግሮችን መወያየት እንዴት ይጀምር የሚሉት ከዚህኛው አማራጭ ጋር የሚመጡ ጥያቄዎች ናቸው...በዚህም ሆነ በዚያ ይህ አስተዳደራዊ ችግር ይመለከተናል፤የሚበደለው ከቤተ ክርስትያን የምናገኘው መንፈሳዊ አገልግሎትም ነው፤የሚባክነው ንብረታችን ነው...ይህንንም አካል የመወሰን ወይም የማቋቋም ሙሉ ነጻነት አለን፣የተሸፋፈነ አስተዳደራዊ ውሳኔና አሠራር ማብቃት አለበት

3.እንደሚመለከተን ማመንና መሳተፍ

ይሄ አስተዳደራዊ ችግር አረም ነው፣ስንዴውን አያጠፋም ግን ምግቡን ይሻማል።

የቤ.ክንን አስተምህሮ ለጊዜው አይቀይር ይሆናል የእኛን ጉዞ ግን ይፈታተናል፤ባላት አቅም ሁሉንም ወደበረቱ እንዳትሰበስብ አቅሟን ያዳክማል ንብረቷን ያባክናል።ወንድሞቼ ዘመኑ ተቀይሯል፤አሁን ድንጋዩን ካላነሱ ከመቃብር መጠራት የለም።ድርሻ አለን፤በትዕቢት ሳይሆን በመንፈሳዊ ቅንዓት የምንወጣው።በመልካሙ ጊዜ አባቶቻችንም በየዋሃት ተመላሰሱ፤እረኞቹም ቢያንስ ሰውን ፈሩ። ስለቤተክርስትያን ጉዳይ ሲነሳ እንደሦስተኛ ወገን ከውጪ ከመመልከትና ከማማት ወጥተን ባለው አጋጣሚ ሁሉ ያመንንበትን መናገር መስራት አለብን።ቢያንስ በሰንበተ ክርስቲያን ቤ.ክ ስንሳለም ወደፊት ልናይ ስለምንችለው ዝብርቅርቅ ለልጆቻችን ምንድንነው የምንነግረው? ችግሩ የበለጠ ሲከፋኮ እንደምዕራቡ ዓለም እያንዳንዳችንን ከቤቱ ሊገፋ ይታገላል. .በቤታችን!?

አንድ እህቴ ያጋጠማትን ጠቅሼ ላብቃ...ታክሲ ላይ በአጋጣሚ አጠገቧ የተቀመጠ ሰው ነው፤በምኞት የተንገላታ የሚመስል።ታክሲው በቤ.ክ አጠገብ ሲያልፍ ስትሳለም ያይና ስለ ቤ.ክ ጨዋታ ይጀምራል።

ወሬው መሐል ላይ እንዲህ አላት

'በዚህ ዘመንኮ ቢዝነስ ያለው ቤ.ክ ነው፤እኔን ውሰጅ በቅርቡ ...ሀገር ቤ.ክንን ወክዬ ሄጄ ነበር ሌላውን ቢዝነስ ተይውና ክፍያው እራሱ ነፍስ ነው።አንቺ ብቻ የምትቀርቢው ሰው ይኑርሽ አሪፍ አሪፍ ቦታ እየተወከልሽ ትላኪያለሽ...' ሌላም ሌላም ዝርዝርና ተራው ምዕመን የማያውቃቸው የአስተዳደር ጉዳዮችን መዘክዘክ ቀጠለ። የሚወራልዎት እርስዎ ቢሆኑ ምን ያደርጋሉ?ለመፍትሄው ካልሰራን የዚህ ዓይነት ሰዎች ናቸው ተራበተው በሽታቸውን የሚያዛምቱት፤እኛንና ቤተክርስትያንን ወክለው በአደባባይ የሚቆሙት!

አምላክ ቅዱሳን በማይመረመር ጥበቡ ወደመፍትሔ ይምራን፤ድርሻችንን የምናውቅበትና የምንወጣበት ማስተዋል ያድለን፣ለበጎ ሥራ ያስተባብረን።

[መጀመሪያ መሰማማት ብንጀምር]

ዲያቆን መሐሪ ገብረ ማርቆስ

የእነዚህ ሁሉ መፍትሔ ሐሳቦች መነሻ መሆን ያለበት መጀመሪያ መሰማማት ስንጀምር ይመስለኛል። የተማረው የቤተክርስቲያን ትውልድ ማድረግ መጀመር ያለበት ነገር መጀመሪያ ማድመጥ ነው- መጽሐፍ ለማድመጥ የፈጠናችሁ ለመናገር የዘገያችሁ ሁኑ እንዲል።

የትኛውንም ችግር ለመፍታት መጀመሪያ ችግሩ ምን እንደሆነ በአግባቡ መረዳት አለብን። ከዚያ ያን ችግር ለመፍታት "ምን ምን ጥሬ ሀብቶች አሉን?" ብለን መጠየቅ ይገባናል። ከዚህ በኋላ ነው ከብዙ አማራጭ መፍትሔዎች መካከል በጥቂት ቤዛ የተሻለ ስኬት የምናገኝበትን መምረጥ የምንችለው። ይህንን ለማድረግ መጀመሪያ የዚህ ትውልድ አባላት መደማመጥ ያለብን ይመስለኛል።

ምን እናድምጥ?

መጀመሪያ በዚህ ረገድ የተሠሩ ጥናቶችን እናገላብጥ። አልተሠሩ እንደሆነም ማኅበረ ቅዱሳን የምርምር ወጪያቸውን በከፊልም ሆነ በሙሉ ሸፍኖ አጥኚዎች ችግሩን ከሥሩ እንዲያጠኑት ይደረግ። የተሠሩትም ሆኑ ወደፊት የሚሠሩት ጥናቶችም ለሰፊው ሕዝብ የሚደርስበት መንገድ ይመቻች። ጥናቶቹና ውጤቶቻቸው በየደረጃው ካለው የተማረ ሰው አንሥቶ እስከ እያንዳንዷ መበለት ቤት የሚገቡበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልገናል።

ለዚህም ከኢንተርኔት እስከ የቡናላይ ወሬ ያሉ ስትራቴጂዎች አገልግሎት ላይ ይውላሉ። በዚህም ችግሩ የአባ ጳውሎስና የአባ መርቆሬዎስ ወይም የእበላባዮችና የግብር አግቢዎቻቸው ብቻ ሳይሆን የነገውን ትውልድ አምላክ

የሚነሣ፣ ቤተክርስቲያን የሚያሳጣ፣ ቅርስ የሚነፍግ፣ ማንነትን የሚያጥል፣ ተነቅሎ መጣል ያለበት መራራ ሳንክ መሆኑን እንዲሰማው ማድረግ የሚቻል ይመስለኛል። የኛ ጥረት መሆን ያለበት ሰዎቹ እንዲሰማቸው ማድረግ ሳይሆን ያለውን መረጃ ማሳወቅ ነው። የችግሩ ምሬት በራሱ የማንንም ስሜት ሳይቆነጥጥ (ባያንገሸግሽ እንኳ) አይቀርምና።

ይህ የማሳወቅ ተግባር መፍትሔውን ወደማሰብ መምራቱ አይቀሬ ነው። መፍትሔዎቹንም ከቀደሙትም፣ ከካህናቱም፣ ከምእመናኑም ማድመጥ ተገቢ ይሆናል። ከዚያ በኋላ የተሻለውንና በአመክንዮ የተደገፈውን መፍትሔ አጽድቆ ወደ ተግባር መግባት ይቻላል። የትግበራው አካላት የሚሆኑት ሁሉም የቤተክርስቲያኗ ልጆችም የመፍትሔውም ምንጮች ስለሆኑም ሁሉም በባለቤትነት ስሜት ሥራውን ሊያከናውን ይችላል የሚል እምነት አለኝ።
:

ነገሮች ቀላል ይናሉ ብሎ መገመት ሞኝነት ይመስለኛል- በተለይ ሲጀመር። ግን በእግዚአብሔር ይቻላል። አትርሱ! የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰልፍ ነው። እግዚአብሔርም ብቻውን አልተሰለፈም። ጌዴዎንም ብቻውን አላሸነፈም።

[እናንተም አትራቁን ቅረቡን]

አባተ ከአዲስ አበባ

ለዲያቆን ዳንኤል ክብረት

አንዳንድ የብሎጉ አንባብያን በሰጡት ሃሳብ መሠረት ጽሑፎቹን ፕሪንት አድርጌ ለአምስት ብጹአን አባቶች አንብቤላቸው ነበር። በጣም ነው የተደሰቱት። በተለይ አንደኛው አባት «ልጆቻችን እንዲህ ማሰብ ከጀመሩ የመፍትሔው ቀን ቀርቧል ማለት ነው» አሉ።

እኔ እንዳየሁት ሁሉም ልብ ውስጥ ቁጭት ይታያል። ቤተ ክርስቲያን ችግር ላይ መሆንዋን አምስቱም ሲናገሩ ነበር። አንደኛው አባትም «እስኪ መንገዱን አሳዩን፣ ምናልባትኮ ለኛ ያልታየን ለልጆች ይታያቸው ይሆናል። ከሌሎች አባቶች ጋር ሆነን እናነሣዋለን» ብለዋል።

ይበልጥ ያነሡት ነገር ደግሞ ታትሞ ለቤተ ክህነት ሰዎች እና ለሌሎች አባቶች ለመን ግሥትም አካላት ቢደርስ ብለዋል። በየሄድንበት የምእመናኑ ዓይን ይጋረዳፍ፤ ጥያቄ ይጠይቁናል፤ መልሱን ግን አብረን ነው መፈለግ ያለብን። ብለዋል።

«እናንተም አትራቁን ቅረቡን፣በግላችንም ቢሆን አወያዩን፤ ፈተናው የሁላችንም ነውና ተረዳድተን የሚቻለውን እናድርግ። ጳጳስ የሆንነውኮ ይህች ቤተ ክርስቲያን በመኖርዋ ነው፤ የተከበርነው በዚህች ቤተ ክርስቲያን ነው። ዐቅም ጠፍቶ እንጂ ማን ከፉዋን ይመኛል» ብለዋል።

ለሌሎች አባቶችም እንዳነብላቸው ነግረውኛል። ዕድሉን ካገኘሁ ያሉኝን እነግርሃለሁ።

ከንፈራችንን መጠን ብቻ እንዳንተወው

ከአቤል ቀዳማዊ

የቤተ ክህነቱ ችግር እስከነ መፍትሄው መስታወት ሆነህ አሳይተኸናል። አልታደልንምና ብዙውን ግዜ ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበት ነባራዊ ሁኔታ ሲነገር ሚስጥራችን በአደባባይ ወጣ የሚል ተቃውሞ ከብዙዎች ይሰማል። ተቃዋሚዎቹ የራሳቸው የሆነ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል፤ አንድም ጥቅመኞች ጥቅማቸው እንዳይነካ በሌላም እውነተኛ ተቆርቋሪዎች በግንዛቤ እጥረት።

እንግዲህ በዚህ ከሁለት ዓመት ወዲህ በአንተው አገላለጽ የቤተ ክህነቱ ችግር " እንደ ዖዝያን ለምጽ ሊሸፈንበት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል" ብለሀል። በዚም ምክንያት ያገባኛል የሚሉ አካላትም መነጋገር ጀምረዋል። ይህ አሁን ለእይታ ያበቃኸው የቤተ ክህነቱ ችግር እስከነ መፍትሔው እንደ "ደራሽ ውሃ" ሐውልቱ ሲቆም አይመስለኝም። ብዙ ዓመታት ያጠናኸው ጥናት መሆኑን በሚገባ ያስታውቃል።

አሁንም ፍራቻዬ ይህ ሀሳብ ከንፈራችንን መጠን ብቻ እንዳተወው እሰጋለሁ። ብዙውን ግዜ አብዛኛውን የእኛ ማሕበረሰብ ማለትም ኢትዮጵያውያን ችግሮቻችን ትዝ የሚሉን ዘማሪው ሲያዜመው፣ ሰባኪው ሲሰብከው፣ ገጣሚው ሲገጥመው፣ ዘፋኙ ሲዘፍነው እና ጸሐፊው ሲጽፈው ብቻ ነው። በዘማሪያን፣ በገጣሚያን፣ በሰባኪያን እና በደራሲያን ችግሮቻችን ሰምተን ከንፈራችን በመምጠ ከማዘን ውጪ ችግሮቻችን በዘለቄታው እንዲፈቱ የራስ ጥረት አናደርግም።

አሁንም አንተ ያቀረብካቸው የመፍትሄ ሀሳቦች በአጠቃላይ ለባለ ድርሻው በቀጥታ እንዲደርስ ምን እናድርግ? እዚህ ላይ ባለ ድርሻ ያልኳቸው በጠቅላላ የተዋሕዶ እምነት ተካታዮች ናቸው። ይህ የአንተ ብሎግ ምን አልባት በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ የእምነቱ ተከታዮች ያዩት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፤በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩት የእምነቱ ተካታዮች ግን ብሎጉን የማየት እድል አያገኙም። ሥለዚህ እንዴት ይህ ሀሳብ ለሚሊዮኖቹ ባለ ድሻዎች ይድረስ?

፩. በቀጥታ ሕዝባዊ ስልጠናዎች ማዘጋጀት ሥልጠናው ማን ያዘጋጀው? ቢባል፤ በሀገራችን ውስጥ እና ከሀገራችንም ውጪ ብዙ ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ማኅበራት አሉ። እነዚህ ማኅበራት ጉባኤያት እና ሕዝባዊ ስልጠናዎች የመስጠት አቅም አላቸው። አንተ በስም የጠቀስካቸው ማኅበራት እያንዳንዳቸው የሥራ አስፈጻሚ አካላት እንዳላቸው እርግጥ ነው። በመሆኑም ይህ የቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ በሥም ለጠቀስካቸው እና ለሌሎቹም በሥም ላልተጠቀሱትም ማኅበራት የሥራ አስፈጻሚ እና ለሥራ አመራር አካላት እንዲደርሳቸው ቢደረግ ።

ለእነዚህ የሥራ አስፈጻሚ አካላት ሀሳቡስ "ማን ያቅርበው"? እኔ እንደሚመስለኝ ከእያንዳንዱ ማኅበራት የሥራ አስፈጻሚ አካላት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው ይሄንን ጽሑፍ ያየዋል ብዬ እገምታለሁ፤ አንብቦም እንደ ማንኛውም የችግሩ ተካፍይ "ምን ላድርግ"? ብሎ ራሱን እንደሚጠይቅ እርግጠኛ ነኝ። ታድያ ይህ ጽሑፍ ያየ እና የሰማ ለቤተ

ክርስቲያን ህልውና ቆሜያለሁ የሚል የትኛውም ማኅበር የሥራ አስፈጻሚ አካል ከሌሎቻችን በተለየ ሁኔታ የበለጠ ኃላፊነት ይኖርበታል ብዬም አምናለሁ። ኃላፊነቱም ለሌሎቹ ላልሰሙና ላላዩ የማኅበሩ አባላት እና የእምነቱ ተከታዮች የሚደርስበት ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

ሥለዚህ ይህ በዚህ በእኛ ዘመን በይፋ ለውይይት እየቀረበ ያለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ነቀርሳ ያልዘመነ አስተዳደር በዘለቄታው እንዲቀረፍ ወንድማችን ያነሳቸው የመፍትሄ ሀሳቦች የማኅበራት የሥራ አስፈጻሚ አካላት እና የሥራ አመራር ተወያይተውበት የማወያየት ግዴታ አለባቸው ብዬ አምናለሁ።

፪. ሰንበት ት/ቤቶች እንደ አንድ ሥራ በእቅድ ቢይዙት። ይህንን አንተ ያቀረብከልን የመፍትሄ ሃሳብ ያነበቡ የሰንበት ት/ቤት አባላት በይበልጥ ደግሞ የሰንበት ት/ቤት አመራር አካላት በእቅድ ተይዞ በየ አጥቢያቸው ተወያይተውበት ለሌሎችም የሚዳረስበት ሁኔታ ቢያመቻቹ ለምሳሌ ጽሑፉ አባዝተው በየ አጥቢያቸው ቢያሰራጩ።

፫. የሰማ ቢያሰማ ያነበበም ቢያስነብብ ይህ የአንተ ብሎግ የሚያነብ ሰው ብዛት ፭ ሺህ ቢሆን እያንዳንዱ ሰው ለአንደ ጽሑፉ ላልደረሰው ሰው እንኳ ቢያስነብብ የአንባቢው ቁጥር ወደ ፴ ሺህ ያሳድገዋል። ስለዚህ እያንዳንዱ ይህ የመፍትሄ ሃሳብ ያነበበ ቢያንሰ ይህ ጽሁፍ ላልደረሰው ለአንድ ሰው የማስነብብ ኀላፊነት ቢወስድ። ሌላው ደግሞ በየ አለንበት ቦታ ሆነን አንድም፣ ሁለትም፣ ሶስትም ሆነን በዚህ በቀረብው የመፍሄ ሃሳብ ላይ ውይይት ብንጀምር እና ለተፈጻሚነቱም የግል ጥረት እናድርግ ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ይጠብቅልን!!! አሜን

[ኳሱን አትንኩብን]

በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ የጀመርነውን ውይይት ለማሰቢያ ጊዜ እናገኝ ዘንድ ለጊዜው ዐረፍ እንበልና ማከሰኞ ደግሞ የሌሎቻችሁን አስተያየት በመጨመር እንመለሳለን።። ለዛሬው ለማረፊያ እነሆ።።
«ወጣቱ በአውሮፓ እግር ኳስ ነፍሱ ሊወጣ ነው።። የሀገሩን እግር ኳስ እና የሀገሩን ጉዳዮች ከመከታተል ይልቅ በእን ግሊዝ፣ በጣልያን እና በስፔይን የእግር ኳስ ተጨዋቾች ልቡ ተነድፏል።። ሚዲያዎችም ቢሆኑ እንዴው ለአመል ያህል የሀገራችንን ኳስ ነካ ነካ ያደርጉና እጥፍጥፍ ብለው ወደ አውሮፓ ይሻገራሉ» እያላችሁ ታሙናላችሁ አሉ።።

ወገኞች ናችሁ እንዴው።። የጨዋታውን ዓይነት፣ የግቡን ልዩነት፣ የታክቲክ እና የቴክኒኩን ነገር ተውት ይቅር ግዴለም።። የተጨዋቾቹን ዝና እና ታዋቂነት፣ የሚያሳዩትን ምትሐት ተውት ኣይነሣ ግዴለም።። አሁን እኛ ሀገር በእግር የሚመታ ኳስ እንጂ እግር ኳስ አለ ይባላል? እንኳን የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽንን ከመሠረቱት ሦስት ሀገሮች አንዱ ልንመስል እግር ኳስ ከአውሮፕላን ተወርውሮ የነጠረባት ሀገር እንመስላለን? ለመሆኑ እኛ ሀገር ስለ ተጨዋቹ እና ስለ ጨዋታው ከሚነገረው በላይ ስለ ቡድኖቹ ሽኩቻ እና ስለ ፌዴሬሽኑ ውዝግብ የሚነገረው አይበልጥም?

«ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንቢያው ቁጢጥ» ሲባል አልሰማችሁም።። ኳሱ መከራ እያየ፣ እኛ ማን ሥልጣን ላይ ይውጣ የሚለው ነው የሚያወዛግበን።። መጀመርያ ኳሱ ሲኖር እኮ ነው ፌዴሬሽን እና የፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት

የሚያስፈልገው፡፡ «ጥርስ የላት ትወቀር አማራት» አሉ፡፡ የኢትዮጵያን እግር ኳስ አሁን ካለበት ደረጃ ለማድረስ እኮ ግዴለሽነት እና ክፋት እንጂ ፌዴሬሽን አያስፈልግም ነበር፡፡

ስንት ዋንጫ እየሳሙ፣ስንት ውጤት እያመጡ፣ ስንት ታሪክ እየሠሩ ዓለምን የሚያናውጡ ቡድኖች ያሏቸው ፌዴሬሽኖች ሳይወዛገቡ እኛ ፊፋ ድረስ ሄደን እንካሰሳለን፡፡ «ቅቤ አንጣሪዋ ተቀምጣ ጎመን ቀንጣሺን ምች መታት» አሉ ወይዘሮ ዘርፌ፡፡ ፊፋስ ቢሆን «ማስረጃችሁን አምጡ፣ የፊፋ ሕግ አልተከበረም፣ መተዳደርያው ተጥሷል» እያለ ያለ ደረጃችን ደረጃ ከሚሰጠን መጀመርያ እስኪ ስታዲዮም ገብቼ ስትጫወቱ ልያችሁ፣ እስኪ ቡድኖቻችሁ እንዴት እንደተደራጁ አሳዩኝ፣ እስኪ ስንት ስታዲዮም ገነባችሁ፣ እስኪ ቢሮአችሁ እንዴት እንደ ተደራጀ ልይ» ቢል ኖሮ ውዝግቡ ይህንን ያህል ዘመን ሞች ይፈጅ ነበር፡፡ በሌለ ነገር እኮ ነው መከራ የምናየው፡፡

«ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ» የተባለው ደረሰና ለምንድን ነው ኳሳችሁ የማያድገው? ተብለው ሲጠየቁ «ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስ ስለሚያይ ከስታዲዮም ስለ ጠፋ ነው፡፡ ስለዚህም የአውሮፓ ጨዋታ የማይታይበትን መንገድ እንፈልጋለን» አሉ አሉ፡፡ ለሠራነው ስሕተት ራሳችንን ተጠያቂ የምናደርግበት፣ ይህ ነገር ሊከሰት የቻለው ምን ስሕተት ስለሠራሁ ነው? ብለን የምንጠይቅበት ዘመን መቼ ይሆን የሚመጣው፡፡ እንዴው እድሜ ልካችንን ለችግራችን ሁሉ ውጫዊ ምክንያት እንደፈለግን ልንኖር ነው?

የጤፍ ነጋዴ ፓስታ በብዛት ስለተመረተ ገበያ ጠፋብኝ ብሎ ያውቃል? የቢራ ፋብሪካ እዚህም እዚያም ቢከፈት የሀገሬ ጠጅ ቤቶች መች ንቅንቅ አሉ፡፡ እነ ገደል ግቡ፣ እነ ውስኪ ለምኔ፣ ጠጅ ቤት ይሄው ጢም እንዳሉ ናቸው፡፡ ሌላውን ተውት የሀገሬ ሰው በፊልሞቹ ላይ የሚሰጠውን ያንን ሁሉ ትችት እየሰማ እንኳን፣ «ሰው በዐቅሙ ነው የሚጸድቀው» ብሎ ከውጭ ሀገር ፊልሞች እኩል እንዲያውም በላይ፣ የሀገሩን ፊልም እያየ አይደለም እንዴ?

ለመሆኑ ሕዝቡ የአውሮፓ እግር ኳስን ለምን እንደሚወድደው ያውቁታል፡፡ የጨዋታውን ጣዕም እና የቡድኖቹን የብቃት ደረጃ አላነሣውም፡፡ እንዳላስጎመጃቸው ብዬ፡፡ ኧረ ሌላ ሌላውን፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ አንድ ቡድን፣ ተጨዋች፣ የቡድን አሰላለፍ፣ የአሠልጣኞች ሁኔታ፣ የክለብ ባለቤቶች እንቅስቃሴ፣ የገቢ እና ወጭ ጉዳይ ለማውራት መረጃ ይገኛል? የተጠናከረ ዌብ ሳይት ያለው ቡድን አለ? የተደራጀ ሙዝየም ያለው ቡድን አለ? የአንድ ተጨዋች ታሪክ፣ ያገባቸው ግቦች፣ መቼ እንዳገባ፣ የት ላይ እንዳገባ? በመዝገብ ይያዛል? በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ በዛሬው ዕለት የዛሬ ሠላሳ ዓመት ምን ተደርጓል? ተብሎ ቢጠየቅ መልስ ያለው ክለብ እና ፌዴሬሽን አለን?

በሐሜት ከሚነገረው በዘለለ የተጠናቀረ፣ሁሉም ሊያውቀው የሚችል እና የሰሚውን ልቡና ሊያረካ የሚችል መረጃ አለ? ስለ አውሮፓ ቡድኖች፣ ፌዴሬሽኖች፣ ተጨዋቾች፣ አሠልጣኞች እኮ ከሚፈለገው በላይ የመረጃ ጎረፍ ይፈስሳል፡፡ ምን በሉ፣ ምን ጠጡ፣ የት ዋሉ፣ የጫማ ቁጥራቸው ስንት ነው፣ የቤተሰባቸው ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ፣ በደቂቃ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡ «የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም» ሲባል አልሰማችሁም፣ ታድያ የማናውቀውን እግር ኳሳችንን እንዴት እንውደደው፡፡

አንዳንድ ባለሥልጣናት እኮ መረጃ መስጠት የሚመስላቸው ጋዜጠኛ ጠርተው የሚያስቡትን እና የሚፈልጉትን መናገር ነው፡፡ ይሄኮ ሃሳብን መግለጥ እንጂ መረጃ መስጠት አይደለም፡፡ መረጃ መስጠት ማለትማ መረጃ መሰብሰብ፣ ሊገኝ በሚችልበት ቦታ እና መንገድ ማስቀመጥ፣ በልዩ ልዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ወደ

ተጠቃሚዎቹ ማድረስ ነው፡፡ ደግሞምኮ እኛ የምንፈልገውን እና የምንወደውን ብቻ እንዲታወቅ የምናደርግ ከሆነ መረጃ መስጠት ሳይሆን ዕንቁልልጮሽ ነው የሚሆነው፡፡

ደግሞስ መረጃ ቢኖርስ ነጻነቱ የት ይገኛል፡፡ የአውሮፓ እግር ኳስን እኮ ብንፈልግ ስለ ተጨዋቹ ፣ብንፈልግ ስለ አሠልጣኙ፣ ብንፈልግ ስለ ክለቡ ባለቤት፣ ብንፈልግ ስለ ቡድኑ ገቢ እና ወጭ፣ ብንፈልግ ስለ ፌዴሬሽኑ የዕለት ውሎ ስንተች፣ ስንተነትን፣ ስንከራከር ብንወል ማን ተቆጭ አለን፡፡ ጋዜጠኞቹ እንኳን ዘና ብለው መዘገብ የሚችሉት የሀገሪቱን ዘገባ ጨርሰው ሜዲትራንያንን ሲሻገሩ ነው፡፡ የሚቆጣቸው ፌዴሬሽን፣ የሚያስፈራራቸው ባለሀብት፣ የሚሰድባቸው ደጋፊ፣ የሚዝትባቸው ክለብ የለ፡፡ እኛ ሀገርኮ ኳሱ ለትንታኔ አይመች፣ የኳሱም ሰዎች ለትንታኔ አይመቹ፡፡

ስለ ጊዮርጊስ ከተቸህ «ፀረ ጊዮርጊስ» ትባልና መቆሚያ መቀመጫ ታጣለህ፡፡ ስለ ቡና ከተናገርክ «ፀረ ቡና» ትባልና ምስህ ዱላ ይሆናል፡፡ እንኳንስ ስትተቸው ስታመሰግነው እንኳን «ሦስት ጊዜ ምስጋና አንዱ ለነገር ነው»ብሎ በሚጠራጠርህ ሰው መካከል ሆነህ እንዴት ነው ስለ ሀገራችን ክለቦች የምትጨነቀውና የምትደግፈው፡፡ «ድጋፍ ተቃውሞን ካልፈቀደ፣ እንጀራ እርሾን ካልወሰደ» ምን ያደርጉልናል፡፡

ሁለት የአውሮፓ ኃያላን ቡድኖች ከመጋጠማቸው በፊት እዚህ አዲስ አበባ ሆነን አሰላለፋቸውን እናውቀዋለን፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማን ለማን እንደተሰለፈ በግልጽ ይታወቃል? በዛሬ ጨዋታ ለአርሴናል የተሰለፈው በቀጣዩ ጨዋታ አሠልጣኙ እንኳን ሳይሰማ ለማንቸስተር እየተሰለፈ መከራ አየንኮ፡፡ እዚህ አዲስ አበባ ሆነን የተጨዋቾች የዝውውር መስኮት ሲከፈት ማን ወደ የትኛው ቡድን ሊሄድ እንደሚችል በግምትም፣ በፍንጭም፣ በመረጃም እንናገራለን፡፡ መሄድ አለበት፣ የለበትም እያልን እንከራከራለን፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም መስክ ማን ወደ የትኛው ቡድን ለመቀላቀል እንዳሰበ፣ እነማን ማንን እንዳስፈረሙ፣ ማን ከነማን ጋር ለመፈራረም ውስጥ ውስጡን እየመከረ እንደሆነ ማወቅ፣ ካወቁስ በኋላ ሃሳብ መስጠት ይቻላል? ይኼው ስንቶቹ መቼ እንደ ተነጋገሩና፣ መቼ ሃሳባቸውን እንደቀየሩ ሳናውቀው ለሌላ ቡድን ሲጫወቱ አገኘናቸው አይደል እንዴ፡፡ አንዳንዶቹም ጭራሽ የነበሩበትን ቡድን ለቅቀው፣ እንዲያውም አብረዋቸው ከተጫወቱት ጋር ተጋጭተው፣ የሌላ ቡድን አሠልጣኝ ሲሆኑ ያየናቸው በድንገት ነው፡፡ የአውሮፓ ኳስ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ ለመገመት በቻልን፣ ከተቻለም ፍንጭ ባገኘን ነበር፡

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንንም ሳይፈሩና ሳይሰቀቁ እንደ ልብ ሊያወሩበት እና ሊከራከሩበት የሚችሉት ጉዳይ የአውሮፓ ኳስ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ ብንደግፍ፣ ብንቃወም፣ የደገፍነውን ቡድን ዓርማ ብናውለበልብ፣ ማልያውን ብንለብስ፤ ስለ እያንዳንዱ ነገር እያነሳን ብንፈልጥ ብንቆርጥ ማን ተቆጭ አለን፡፡ እና እንደዚህ በነጻነት የሚወራ ጉዳይ ከየት ይገኛል ጃል፡፡ አቦ ተውና፡፡

ደጋፊም ተቃዋሚም መሆን እዚህ ሀገር ዕዳ ነው፡፡ የመንግሥት ደጋፊ ነኝ ካልክ ገልማጭህ ብዙ ነው፡፡ ተቃዋሚም ነኝ ካልክ የሚያጉረጠርጥብህ በዚያው ልክ ነው፡፡ የአንዱን ማልያ መልበስ ቀርቶ ልትገዛ ስታገላብጥ ከታየህ መከራ ነው፡፡ እንኳንስ ስለ ተጨዋቾቹ አንሥቶ ለመነጋገር እና ለመተቸት ይቅር እና በቴሌቭዥን ሲቀርቡ እንኳን እነርሱን

ትኩር ብለህ ካየህ አንዱ «ምን ታፈጣለህ?» ይልሃል ሌላው ደግሞ «ምነው ሙድ ያዝኽሳ» ብሎ ይተርብሃል፡፡ በአውሮፓ ኳስ ግን፣ ብትደግፉ ተለጣፊ፣ ብትቃወሙ አደናቃፊ የሚላችሁ የለም፡፡

ደግሞስ ደጋፊ እና ተቃዋሚ በአንድ አዳራሽ የሚሰበሰብበት ይህንን የመሰለ ነገር ከየት ይገኛል፡፡ ከመተራረብ፣ ከመተቻቸት ያለፈ ሌላ ነገር የለ፡፡ ርግጥ ነው እግር ኳሱን በፖለቲካው መንገድ ለማስኬድ የሚፈልጉት አንዳንዶች ብጥብጥ እያነሡ ተቸግረን ነበር፡፡ አሁን ግን ጋብ ብለዋል፡፡ በኳስኮ በዚህኛው ጨዋታ ካሸነፋችሁ እየጨፈራችሁ ቤታችሁ ትገባላችሁ፣ አንድ ሳምንት ትተነትናላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ለቀጣዩ ጨዋታ መዘጋጀት ነው፡፡ ትናንት አሸነፋችሁ ማለት ነገም ታሸንፋላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ብትሸነፉም ለጊዜው ትናደዱና እንደ ገና ለማሸነፍ መሥራት ነው፡፡ ቴክኒክ እና ታክቲክ መቀየር፣ ሥልጠናውን ማጠናከር ብቻ ነው፡፡ ትናንት ለምን እንዲህ ሆነ ብሎ ሙዝዝ ማለት የለም፡፡ ሌላ ሌላውንማ ሲያሸንፍና ሲሸነፍ ምን እንደሚመስል አየነውኮ፡፡

ኧረ ለመሆኑ የአውሮፓ ኳስ ባይኖር ስለ ምን እናወራ ነበር፡፡ ሰው ቋንቋ ኖሮት እንዴት ሳያወራ ይኖራል? ምሳ ሲበላ፣ ሻሂ ሲጠጣ፣ ቡና ሲፈላ፣ በታክሲ እና በአውቶቡስ ሲኬድ ታድያ ምን ይወራ? ሁሉም ነገር ፖለቲካ በሆነበት ጊዜ ታድያ ምን እናውራ፡፡ ጤፍ ተወደደ ፖለቲካ ነው፣ጤፍ ረከሰም ፖለቲካ ነው፡፡ ሀገራችን አደገች ማለት ፖለቲካ ነው፣ ሀገራችን ወደ ኋላ ቀረች ማለትም ፖለቲካ ነው፡፡ እገሌ ተሳሰቷል ማለት ፖለቲካ ነው፣ልክ ነው ብሎ መናገርም ፖለቲካ ነው፡፡ ታድያ ምን እንበል?

ምን እባል ይሆን? ማን ሰምቶኝ ይሆን? ተብሎ በሚወራበት በዚህ ጊዜ እንደ ልብ የሚወራ ነገር ማግኘት ቀላል ይመቻል እንዴ! እኛ ተመልካቾች በሂደት አንድ የጥናት ውጤት አግኝተናል፡፡ ቢያንስ ስለ አውሮፓ እግር ኳስ ስታወራ የትኛውም የፓርቲ አባል እንደማይቆጣ፡፡ አውሮፓውያን ኢትዮጵያውያን ቢሆኑ ኖሮኮ በስፔን ቡድን ላይ ትችት ስትሰነዝር የስፔን ኤምባሲ፣ በእንግሊዝ ቡድን ላይ ስትወርድበት የእንግሊዝ ኤምባሲ፣ የጣልያንን ቡድን ስታነሣ ጣልያን ኤምባሲ አያስቀምጡንም ነበር፡፡ አቦ እንኳን ኢትዮጵያውያን አልሆናችሁ፤ ተመችታችሁናል፡፡

የሆስፒታል ቫይረስ

በሕክምና እና በሕክምና ባለሞያዎች ዘንድ ካሉት ሥጋቶች መካከል አንደኛው በሆስፒታል ውስጥ ሆስፒታሉን ለምደው እና ወድደው፤ የሚኖሩት ቫይረሶች ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ቫይረሶች በተለያዩ ሕመምተኞች አማካኝነት ወደ ሆስፒታሉ ይመጡና እዚያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመላመድ፣ የሚረጩትን መድኃኒቶች፣ ኬሚካሎች እና የማጽጃ ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ በመቋቋም ኑሯቸውን በሕክምና ተቋሙ ውስጥ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የተነሣ የሕክምና ባለሞያዎችን እንዲሁም ታካሚዎችን ያጠቃሉ፡፡

እንደዚህ ዓይነቶቹ ቫይረሶች መከላከያዎችንም ሆነ መድኃኒቶቹን ስለተለማማዱቸው እነርሱን በማከም ማሸነፍም ሆነ ማድከም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሕክምናው ባለበት በዚያው በሆስፒታሉ ውስጥ ስለሚኖሩም ራሳቸውን እያባዙ እና እንደነርሱው ሕክምናውን የሚቋቋሙ መሰሎቻቸውን እያበራከቱ በመሄድ፣ የሕክምና ማዕከል ተብሎ የተቋቋመውን አካል የማይድኑ በሽታዎች ማምረቻ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ ቫይረሶች ለረዥም ጊዜ ከቆዩና በቶሎ ካልተነቃባቸው፣ የሕክምና ማዕከሉን ይቆጣጠሩታል። መፍትሔውንም ውስብስብና ከዐቅም በላይ ያደርጉታል። ሆስፒታሉን እስከማስቀየር፤ እስከማቃጠል፣ እስከማፍረስ እና እስከማዘጋት ይደርሳሉ።

በመንፈሳዊ እና በፖለቲካ ተቋሞቻችን ውስጥ ከምናያቸው አልፈቱ ካሉን ችግሮች መካከል አንደኛው የሆስፒታል ቫይረስ ችግር ነው።

ደግነት፣ ቅንነት፣ ትጎትና፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ መከባበር፣ ይቅርታ፣ ለጋስነት፣ ራስን መግዛት፣ ይነግሥባቸዋል ተብለው በሚጠበቁት መንፈሳዊ ተቋሞቻችን ውስጥ ትዕቢት፣ጠማማነት፣እኔን ብቻ ይድላኝ ማለት፣ብጥብጥ፣ መናናቅ፣ ቂም በቀል፣ ስስት፣ አፍቅሮ ንዋይ፣ ነግሦባቸው እናያለን። ለሌሎች አርአያ ይሆናሉ፤ ማኅበረሰቡን በሞራል ሕጎች እና በሥነ ምግባር ይታደጋሉ ተብለው ተስፋ ሲደረግባቸው እነርሱ ራሳቸው የሥነ ምግባር ብልሹነት መገለጫ ቦታዎች ይሆናሉ።

ለሀገሪቱ ዕድገት እና ብልጽግና፣ መሻሻል እና ብርታት፣ አርአያዎች እና ሞተሮች፣ ብቁ እና ታታሪ፣ በሥነ ምግባር የታነፀ እና ሕግ አክባሪ ዜጋ ፈጣሪዎች ሲባሉ የሙስና እና የብልሹ አሠራሮች፣ የኋላ ቀር ቢሮክራሲ እና የአምባገነንነት ምሳሌዎች፣ የሀገሪቱንም እድገት ጎታቾች ሆነው ይታያሉ። ለምን?

የሆስፒታል ቫይረስ አለ ማለት ነው። ሰይጣን መንኩሶ፣ ቀስሶ፣ ደቁኖ፣ ሰባኪ ሆኖ፣ ቅኔ ተምሮ፣ ጸጉሩን አስረዝሞ፣ ሼህ እና ቃዲ፣ ዑለማ ሆኖ፤ ፓስተር እና ወንጌላዊ፣ ዘማሪ እና ነቢይ፣ አገልጋይ እና አስመላኪ፣ ሆኖ ራሱ በቦታው ተቅምጧል ማለት ነው። ስለዚህም ሌሎችን ያድናል ተብሎ ተስፋ የተሰጠው ተቋም ራሱ የበሽታዎቹ መነሻ/ የቫይረሶቹ መኖርያ ሆኗል ማለት ነው።

ሌላ ቦታ ያለው ቫይረስ መድኃኒት የሚፈራ፣ በመድኃኒትም የሚጠቃ፣ በመድኃኒትም የሚድን ነው። ሆስፒታል ውስጥ የሚኖር ቫይረስ ግን ምንም አይፈራም። ተለማምዶታላ። አንዳንድ ጊዜ ምእመናን ምንም ያህል ቢያጠፉ እና ቢበድሉ፣ ቢሳሳቱ እና ኃጢአት ቢሠሩም መገሠጽ፣ ማስተማር፣ ማስፈራራት፣ የፈጣሪን ስም ጠርቶ መመለስ፣ ቃለ መጽሐፍ ጠቅሶ ልባቸውን መስበር ቀላል ነው። እነርሱ ጋር ያለው ቫይረስ በመድኃኒት ሊታከም፣ ሊድን ወይንም ሊዳከም የሚችል ነው።

አሁን የቸገረን ሆስፒታል ውስጥ ያለው ቫይረስ ነው። ትምህርት፣ ጸሎት፣ መቅሰፍት፣ ተግሣጽ፣ ድርሳን እና ተአምር፣ ትንቢት እና መገለጥ፣ ቁርዐን እና ዱአ፣ ባህታዊ እና ልሣን ተናጋሪ፣ ሊፈራ የማይችል። ጠበል የለመደ ሆኖብን ነው የተቸገርነው። እግዚአብሔርን የማያውቁ የእግዚአብሔር ሰዎች በዝተው ነው የተሰቃየነው። ለቤተ እምነት ቅርብ ለፈጣሪ ግን ሩቅ የሆኑ አካላት ናቸው ሊድኑ ያልቻሉት።

አትስረቅ የሚለው አካል ከሰረቀ፣ አታመንዝር ያለውም ካመነዘረ፤ ተፋቀሩ ያሉት ከተጣሉ፣ አንድ ሁኑ የሚሉት ከተከፋፈሉ፤ ሁላችን የአንድ የፈጣሪ ልጆች ነን የሚሉት በዘር እና በንሣ ከተባሉ፤ የመነኑትን የሥልጣን ጥም ከያዛቸው፤ ሞተዋል የተባሉት የየራሳቸውን ቪላ ከገነቡ፤ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ የያዙት የቢሮውን ቁልፍ ከዘጉ፤ ሌላ ልሳን እንናገራለን እያሉ የሕዝቡን ልሣን ካላዳመጡ፤ የነገው ትንቢት ተገለጠልን እያሉ የዛሬው ችግር

ከጠፋቸው፤ በሽተኞችን እንፈውሳለን እያሉ እነርሱ ራሳቸው የማይፈወሱ በሽተኞች ከሆኑ፤ እንግዲህ «ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡታል፣ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡታል» የተባለው ደርሷል ማለት ነው።

ፖለቲካችንም ተመሳሳይ ቫይረስ እያጠቃው ነው።

ሕዝቡን በርእዮተ ዓለም አንቅተው ያሰልፋሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው ርእዮተ ዓለም ከሌላቸው፤ ሕዝቡን አደራጅተው እና መንገድ አሳይተው ወደ ዕድገት እና ብልጽግና ያደርሱታል ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው መደራጀት እና መንቃት አቅቷቸው መንገድ ከጠፋባቸው፤ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ያደርጉታል ተብለው ተስፋ ሲጣልባቸው እነርሱ ለራሳቸው ሥልጣን ብቻ የሚያስቡ ከሆኑ፤ ለሌላው ያስረዳሉ፣ ያሳውቃሉ፣ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው የድርጅታቸውን ፕሮግራም፣ ሕግ እና መመርያ ማወቅ እና መተግበር ሲሳናቸው፤ የተወዳደሩበት ዓላማ እና የሚሠሩት ሥራ ሲለያይ፤ የሆስፒታሉ ቫይረስ አለ ማለት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊው የፖለቲካ አካሄድ ከተጀመረ ጀምሮ ሥርዓታት ቢለዋወጡ እንኳን ያልጠፉ ችግሮች ግን አሉ። የደጋፊውም ሆነ የተቃዋሚው፣ ያለፈውም ሆነ የመጣው፣ የሚጋሯቸው ተመሳሳይ በሽታዎች አሉ። ከአዲሱ ትውልድ ይልቅ በነባሮቹ ማመን፤ የተወሰኑትን ብቻ የፖለቲካ ተዋንያን ማድረግ፣ በየጊዜው መለያየት እና መሰነጣጠቅ፤ ለችግሮች ምንጊዜም የውጭ ተጠያቂን መፈለግ፤ የማይጨበጥ እና የማይዳሰስ ጠላት መፍጠር፤ ከተሳትፎ ይልቅ ቲፎዞነትን መምረጥ፣ ከአመክንዮ ይልቅ ስሜትን ማዳመጥ፣ ከመሠረተ ሃሳቦች ይልቅ ግለሰቦችን መከተል፤ የፖለቲካ አካሄዶችን ከግላዊ ጥቅም አንፃር መመዘን፤ ስሕተትን መቀበል እንደ ውርደት ማየት፤ ራስን ብቻ ማዳመጥ።

እነዚህ እና ሌሎች መሰሎቻቸው የፖለቲካውን ሆስፒታል ተላምደውት እየኖሩ ያሉ ቫይረሶች ናቸው። ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተላምደው፣ መሰሎቻቸውንም ተከተው ተቀምጠዋል። የሚመጡ መከላከ ያዎችም ሆኑ መድኃኒቶች ሊያጠፏቸው አልቻሉም። ሆስፒታሉ ውስጥ ከመኖራቸው የተነሣ እነርሱ ራሳቸው የሆስፒታሉ አካላት ሆነዋልና። እዚህም እዚያም ቢኬድ፣ ይህኛውንም ሆነ ያኛውን አካል ብናይ ይቃወማቸዋል፣ እዋጋቸዋለሁ ይላል፣ ይምላል፣ ይገዘታልሃሃ ነገር ግን ራሱ የቸግሩ እንጂ የመፍትሔው አካል ስላልሆነ አያከማቸውም።

እዚህኛው ፓርቲ ውስጥ እንዲህ እና እንዲያ አለ፣ ይህኛው አካሄድ በዚህ እና በዚያ ምክንያት አያስኬድም ብሎ የተሻለ ነገር ሊፈጥር፣ ሌላ አካሄድ ሊያሳይ እንደ አዲስ ይደራጅና ሳያስበው ያንኑ ስሕተት ይወርሰዋል። ምክንያቱም እነዚህ ችግሮች እንደ ሆስፒታሉ ቫይረስ ቋንቋችንን፣ አሠራራችንን፣ባህላችንን፣ ሕጎቻችንን፣ መመርያዎቻችንን፣ ውሳኔዎቻችንን ተለማምደዋቸዋል።

ባለፈው ሥርዓት ሕዝብ ሁሉ የሚያውቀው አንድ አባባል ነበር። በሀገሪቱ ውስጥ ኮሚቴዎች በዙ ተብሎ ምክክር ተደረገ። በመጨረሻም ተመካካሪዎች በአንድ ሃሳብ ላይ ተስማማሙ ይባላል። ኮሚቴዎችን አጥንቶ የሚቀንስ ሌላ ኮሚቴ ይቋቋም። እነዚህ ሰዎች ኮሚቴን እንቀንሳለን ብለው ሌላ ተጨማሪ ኮሚቴ እንዲያቋቁሙ ያደረጋቸው ቫይረሱ ነው። ይህ ችግር ዛሬም እንኳን አልለቀን ስላለ በየመሥሪያ ቤቱ፣ድርጅቱ፣ ማኅበራቱ፣ ወዘተ አንዳች ችግር ተፈጠረ፣ ሕዝብ ተማረረ፣ አሠራር ተበላሸ፣ ተብሎ ሲጠየቅ እንደ መጀመርያ እና ዋና መፍትሔ ተደርጎ የሚቆጠረው

ኮሚቴ ማቋቋም ነው፡፡ ያለ ኮሚቴ ማሰብ እና መሥራት የሚቻል አይመስለንም፡፡ ለምን? የሆስፒታሉ ቫይረስ መፍትሔውን ስለለመደው ችግሩን መፍትሔ እያደረገው ይኖራል፡፡

እዚህ ሲያትል ያሉ ሰዎች የነገሩኝን ላውጋችሁ፡፡ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ተዳከመ፡፡ አዳዲሱ ትውልድ ራቀው፣ ነባሮቹ አመራሮች መሥራት አልቻሉም ተባለ፡፡ አመራሩን በአዲስ ለመተካት፤ በተለይም አዲሱን ትውልድ ቦታ ለመስጠት፤ ወጣቶች ገብተው እንዲይዙት ለማድረግ በየቦታው፣ በየሬዲዮው፣ በየጋዜጣው ተደሰኮረና ስብሰባ ተጠራ፡፡ ይሄው ሃሳብም በስብሰባው ቦታ ይበልጥ ተንፀባረቀ፡፡ በመጨረሻ ምርጫ ተደረገ፡፡ የሚገርመው ግን የተመረጡት በሙሉ ሽማግሌዎች፣ ደጃዝማች፣ ባሻ፣ ሻለቃ፣ የተሰኙ½ ብለው ብለው ያልተሳካላቸው ሰዎች ሆኑ፡፡ የተባለው እና የሆነው ነገር ሊገጣጠም አልቻለም፡፡ ይሄ የሆስፒታል ቫይረስ መች በፉከራ ብቻ ይጠፋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን በርእዮተ ዓለም የተለያየን ነን ይሉና በአደረጃጀት ግን ተመሳሳይ ናቸው፤ በድብቅነት፣ በአመራረጥ፣ ከውጭ ለመጣ ነገር በሚሰጡት ልዩ ቦታ፣ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ትናንት ያልተሳካላቸው ሰዎች ለአሥራ ሁለተኛ እና አሥራ ሦስተኛ ጊዜ መሪነትን የሚሞክሩበት፤ ያጠፉ ሰዎች የሚሸለሙበት ፖለቲካዊ አካሄድ የሁሉም ጠባይ ነው፡፡ ሃሳባቸውን ከመናገር አልፈው ለመጻፍ የማይ ወድዱ፤ ራሳቸውን በራሳቸው ለመተቸት የማይደፍሩ፤ አጠቃላይ ፖለቲካዊ አካሄዱን፣ አስተሳሰቡን፣ ለመለወጥ ከመሥራት ይልቅ ለምርጫ ብቻ የሚሠሩ ፓርቲዎችን መመሥረት ተመሳሳዩ ጠባይ ነው፡፡ በትክክል ቢታይ፣ ፕሮግራማቸው ቢመረመር፣ ዘጠና ስድስቱ የሀገራችን ፓርቲዎች ከአራት እና አምስት አይበልጡም ነበር፡፡ ዘጠና ስድስት ያደረጓቸው ርእዮታቸውና ፕሮግራማቸው ሳይሆን መሪዎቻቸው እና ቲፎዞዎቻቸው ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ መድኃኒት የማያስለቅቀው የሆስፒታል ቫይረስ ነው፡፡

የሆስፒታልን ቫይረስ በተለመደው የሕክምና መንገድ እና አሠራር ማጥፋት፣ ማዳከም እና ማላቀቅ አይቻልም፡፡ ሆስፒታሉን ከመድኃኒቶቹ በላይ ያውቀዋልና፡፡ እርሱኮ በሕክምና በለሞያዎቹ፣ በመድኃኒት መሣርያዎቹ፣ በአልጋዎቹ እና ግድግዳዎቹ፣ በፋርማሲዎቹ እና ላቦራቶሪዎቹ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ስለዚህም ሆስፒታሉ ሙሉ በሙሉ በእነዚህ ቫይረሶች ተወርሮ ሥራ ከማቆሙ በፊት ከተለመዱት የተለየ፤ አዲስ እና መሠረታዊ የሆነ መፍትሔ መምጣት አለበት፡፡ ሕክምናው ሐኪሞቹን፣ መሣርያዎቹን፣ አልጋዎቹን፣ ቤቱን ከማከም መጀመር አለበት፡፡

ይህ ጽሑፍ ባለፈው ቅዳሜ በሮዝ መጽሔት የወጣ ነው

«መንግሥት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም» ምን ማለት ነው?

ኃይለ ገብርኤል - ከአራት ኪሎ

የተከበራችሁ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆችና የዲ/ን ዳንኤል የጡመራ-መድረክ እድምተኞች ሰላመ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን።

ባለፉት ሳምንታት ወንድማችን ዲ/ን ዳንኤል በቤተ ክህነቱ ውስጥ ያሉትን፣የብዙዎቻችንን አንገት ያስደፉትንና አብዛኛው ምእመን በሆዱ ይዞ ዘወትር የሚያርበትንና የሚያለቅስበትን የቤታችንን ጉድ ዝምታ መፍትሔ አይደለም በማለት ብቻውን ነጥሮ ወጥቶ ከብዙ በጥቂቱ ለእኛ በሚገባን መልኩ ነግሮናል። ችግሮቹን ከመዘርዘር ባሻገርም መፈትሔ ሊያመጡ ይችላሉ ብሎ ያመነባቸውን ነጥቦችንም በግልፅ አመላክቷል።

እየበሉ እየጠጡ ዝም..... የሚለው የአበው ምሳሌ አንድም በኔ እንዳይተረት አንድም እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነቴ የድርሻዬን መወጣት ስላለብኝ እነሆ በውስጤ ያለውን እናገር ዘንድ ጀመርኩ።

ዲ/ን ዳንኤል እንዳመለከተው በአሁኑ ወቅት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ይመለከተኛል የሚሉ ሁሉ በመነጋገር ላይ ናቸው፡፡ መፍትሔም ይሰነዝራሉ፡፡ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩም የሚሰነዘሩት የመፍትሔ አቅጣጫዎች ሁለት መልክ አላቸው ***ተሐድሶ እና ትንሣኤ***። ተሐድሶ ተብዬው ለተፈጠረው ችግር በአንድም በሌላ ተጠያቂ እና ቢሳካለት ለቤተ ክርስቲያን ውድቀት ዘወትር የሚተጋ እንጂ ለሰላሟና አንድነቷ ተጨናቂ አይደለም። ስለዚህም በእኔ እምነት የመፍትሔው አቅጣጫ አንድና ብቸኛ ሲሆን እርሱም ***ትንሣኤ*** ነው። የትንሣኤን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉና በዲ/ን ዳንኤል የተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ደግሞ **አብርሖትና መዋቅራዊ ሽግግር** ናቸው። እነዚህ ሁለት መንገዶች መልካምነታቸው ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ ረዘም ያለ ጊዜን የሚጠይቁና የተራበነውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት በቅርቡ ላይመልሱልን ይችላሉ ብዬ ሰጋሁ።

ስለዚህም እንደኔ አመለካከት ከአብርሖትና ከመዋቅራዊው ሽግግር ጎን ለጎን መንግስት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ጠንከር ያለ ጫና ማሳደር ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ።

ይህ እምነቴ ግን መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም መባሉን ሳልሰማ ቀርቼ አይደለም። ከመስማትም አልፌ አንብቤዋለሁ ስለሆነም እስቲ ስለዚህ ጉዳይ የሚሰማኝን ልሰንዝር።

ሁላችንም እንደምናውቀው መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ይህም መሰረቱ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሁለት አንቀፅ ፲፩ ላይ የሰፈረው ነው። ይኸውም የሚከተለው ነው።

አንቀፅ ፲፩ (የመንግስትና የሃይማኖት መለያየት)

1. መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።

2. መንግስታዊ ሃይማኖት የለም።

3. መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም።

መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት ግን ምን ማለት ነው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እኮ የሀገሪቱ ብቸኛ የትምህርት ተቋም በነበረች ጊዜ ለራስዋም ሆነ ለሀገሪቱ የሚሆኑ፣ ምግባራቸው የቀና፣ አንደበተ ርቱዕ፣ በሰውና በእግዚአብሐር ዘንድ የተከበሩ፣ ሀገራችን ዛሬ ለደረሰችበት ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የሆኑ፣ በዓለማዊና መንፈሳዊ ዕውቀታቸው በሁለቱም ጎን እንደተሳለ ሰይፍ የሆኑ ሊቅና ሊቀ ሊቃውንትን በጥራት ስታመርት የኖረች ናት። ይቺ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን ለማፍራት፣ የዕለት ተዕለት መንፈሳዊና ማሕበራዊ ተግባሮቿን ለማከናወን፣ ለቅዳሴው፣ ለማኅሌቱ፣ ለአቋቋሙ፣ ለሰዓታቱ፣ ለትርጓሜው፣ ለቅኔው፣ለድጓው የሚሆን የሰው ኃይል ራስዋ በራስዋ ማንንም ሳትለምንና ሳታስቸግር መሰረቷ

በሆነው በልዑል እግዚአብሔር እርዳታ እና ዘወትር ደከመኝና ሰለቸኝ በማይሉና ለዓለም ሙት በሆኑ ልጆቿ ድካምና ጥረት ስታወጣ የኖረችና አሁንም በማውጣት ላይ የምትገኝ ናት።

ይህንን የተቀደሰ ተግባሯንም በሃገራችን ላይ በተለያዩ ዘመናት ስልጣን ጨብጠው ከነበሩ መንግስታት ጋር በመከባበርና በመረዳዳት እየሰራች ነፃነቷን ጠብቃ እነሆ በኢሕአዴግ ዘመነ መንግስት ላይ እንገኛለን። ታድያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሰረቷ ፅኑ፣ተግባሯ መልካም፣ አላማዋና ግቧ እንደ ፀሐይ ጮራ ግልፅ፣ ፍሬዋም ለሀገራችን ሐዝቦችና መንግስትም ጭምር ጣፋጭ ሆኖ ሳለ መንግስታችን የህጎች ሁሉ የበላይ በሆነው በህገ መንግስቱ ላይ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም በማለት በግልፅ ያሰቀመጠበት ምክንያት ምንድነው?

በእኔ አመለካከት መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ማለት፤

1. በተለያዩ የሹመት እርከን ላይ ያሉ የቤተክርስትያን አገልጋዮች ሹመታቸውና የመሿሚያው መስፈርት የሚወጣውና የሚፀድቀው በህገ ቤተ ክርስቲያን እንጂ በመንግስት አይደለም።

2. መንግስት በህገ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጁን በማስገባት ሰባቱን የአዋጅ አፅዋማት በዙ ብሎ መቀነስ አሊያም

አነሱ ብሎ መጨመር አይችልም።

3. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ያሬድ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጧትን ሶስቱን የዜማ አይነቶች

መንግስት እኔን ደስ አላሰኙኝም በማለት በማናቸውም መንገድ ማሻሻል ወይም መቀየር ፈፅሞ አይችልም አያስበውምም።

4. መንግስት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስርዓተ ቅዳሴ ጣልቃ በመግባት

ሀ. የፀሎተ ቅዳሴው ሰዓት ረዝሟልና አሳጥሩ ወይም አጠሯልና አስረዝሙ፣

ለ. ስትቀድሱ እንዲህና እንዲያ እያላችሁ ቀድሱ፣

ሐ. በሳምንት ይሔን ያህል በወርና በዓመትም ይህንና ያን ያህል ጊዜ ብቻ ቀድሱ፣

መ. ፀሎተ ቅዳሴ በእነዚህ ቀናት እንጂ በዚህና በዛኛው ቀን መፈፀም የለበትም፣

ሠ. በፀሎተ ቅዳሴ ጊዜ ተገኝተው ማስቀደስ ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እነ እገሌ እንጂ እነ እገሌ አይችሉም፣

ረ. በፀሎተ ቅዳሴ ጊዜ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገኘት ያለባቸውን የካህናትና የዲያቆናት እንዲሁም የምዕመኑ ቁጥር ይሄን ያህል ብቻ መሆን አለበት፣ ወዘተ... ብሎ መወሰን አይችልም።

5. መንግስት በቤተ ክርስቲያን ሙዳየ ምፅዋት ውስጥ ምዕመናንና ምዕመናት መጨመር ያለባቸው የገንዘብ መጠን

ቢያንስ ቢያንስ ይሔን ያህል ጣራው ደግሞ ይሄ ነው ብሎ ተመን ማውጣት አይችልም።

6. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በምትመራበት ቅዱስ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ዓስርቱን ትዕዛዛት 9 ወይም ፲ ማድረግ፣ እንዲሁም አምስቱን አዕማደ ሚስጥራት 4 ወይም 6 ማድረግ፣ሰባቱን ሚስጥራተ ቤተ ክርስቲያንም 6 ወይም 8 ማድረግ አይችልም።

7. መንግስት በሚስጥረ ቁርባንም ያገባኛል በማለት ቅዱስ ቁርባንን መቀበል የሚችሉት ምዕመናንና ምዕመናት ሊያሟሉ ከሚጠበቅባቸው መንፈሳዊ መስፈርት በተጨማሪ ዲፕሎማና ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል፣ በፖለቲካ አመለካከታቸውም ጀርባቸው እየተጠና መሆን አለበት ብሎ መደንገግ ፈፅሞ አይችልም።

8. ምዕመናንና ምዕመናት ፀሎት ለማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበትን ሰዓት፣ የሚፀልዩትን የፀሎት አይነት፣

የሚያነቡትን የፀሎት መፅሐፍ ዓይነት፣በፀሎት ሰዓት ስለሚኖራቸው እንቅስቃሴ መወሰን አይችልም።

9. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ህልውናዋን ይበልጥ በማጠናከርና ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በምታደርገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን እንዳትወጣና ለታሪክና ለትውልድ የሚተላለፉ አበይት የሥራ ክንውኖቿንም እንዳታስመዘግብ መንግስት በአንድም በሌላ መንገድ እንቅፋት መሆን ወይም መፍጠር የለበትም።

10. ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትናንት የነበረች ዛሬም ያለች ነገም የምትኖር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ናትና ወቅቱ የሚጠይቀውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በሚገባ መወጣት ትችል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች የምታከናውናቸውን ክንዋኔዎች መንግስት ለእርሱ በሚመቸው መልኩ መቃኘት አይችልም።

ወዘተ... ማለት ነው እንጂ፤

1ኛ. ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ምንጭ ሆና የኖረች ቤተ ክርስቲያን መሆኗን፣

2ኛ. ከጥንት ጀምሮ ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንደበቱን የሚፈታው መሠረታዊ የቋንቋና የሥነ ጽሕፈት ዕውቀት የሚያገኘው ከዚች ቤተ ክርስቲያን መሆኑን፣

3ኛ. ዘመናዊው ትምህርት በሀገሪቱ እስከተዘረጋበት ቅርብ ጊዜ ድረስ ጠቅላላው የትምህርት ቁልፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ እጅ ተይዞ የነበረ መሆኑን፣

4ኛ. የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቱ ብዙ ሊቃውንትን ሲያበረክቱ የኖሩ መሆኑንና አያበረከቱም መሆናቸውን

በመዘንጋትና እጇን አመድ አፋሽ በማድረግ ህፃናት በጥሩ ሰነ-ምግባር እንዲያድጉ፣ ብሔርና ብሔረሰቦች ተከባብረውና ተዋድደው እንዲኖሩ፣ በተለያዩ የመንግስት የኃላፊነት ቦታ ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለስራቸውና ለህሊናቸው ታማኝ እንዲሆኑ፣ ምእመኑ ቀኑን ሙሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲውል፣ ምእመኑ በመንግስት አካላት በደል ቢደርስበት እንኳን ስሜታዊ ባለመሆንና ትዕግስትን ገንዘቡ በማድረግ ችግሮችን በህጋዊ መንገድ እንዲፈታ ከዚህም ካለፈ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ብሶቱንና መበደሉን ለእግዚአብሔር እንዲያሳውቅ፣ ወዘተ… በማስተማርና በመምከር ለሀገራችን ሕዝቦች እና ለመንግስትም ጭምር የዋለችውን ውለታ በመርሳት

1ኛ. ለብዙዎች ዓለማዊና መንፈሳዊ ጥበብን ዘወትር ሲመግቡ የኖሩትና በመመገብም ላይ የሚገኙት የቤተ ክርስቲያን ጡቶች እና እጆች በአጉራ ዘለል ግለሰቦች ሲነከሱ፣

2ኛ. ህዝበ ክርስቲያኑ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲውል ከዕለት ጉርሱ ቀነሶ በሙዳየ ምፅዋት የጨመረው ገንዘብ ሲመዘበር፣

3ኛ. ምዕመኑን በንፁህ ልቦና እና መልካም ኣርዓያነት የሚያገለግሉ አገልጋዮች መብት ሲነካ፣

4ኛ. ለዘመናት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትተዳደርበት የነበረው ሕግ እና አስተዳደር ሲጠፋ፣

5ኛ. በቅድስት ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ የሚያበላሽ ተግባር ሲፈጸም፣

6ኛ. ጥንታዊቷና ሓዋርያዊቷ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሕዝቦቿ ሰላምና ፍቅር ዘወትር የሚያለቅሱት አገልጋዮቿ እየተገፉ በምትካቸው በቤተ ክርስቲያን ችግር የሚያተርፉ ሆዳቸው አምላካቸው በሆኑ ግለሰቦች ስትወረር፣

7ኛ. በቅድስት ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ኣይደለም ለቤተ ክርስቲያን ለሌላም የሚተረፍ መንፈሳዊ ጥበብና እውቀት ባለቤት የሆኑ አባቶች እያሉ የመንፈሳዊነትን ትርጉም እንኳን በቅጡ የማያውቁ ግለሰቦች ያልተገባቸውን መነፈሳዊ ስራ እንሰራለን እያሉ ሲያበላሹት፣

8ኛ. በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ቦታዎች ቦታውን የማይመጥን መንፈሳዊነትና ዕውቀት የሌላቸው ገለሰቦች ተቀምጠው ህዝበ ክርስቲያኑ ከቦታው ሊያገኘው የሚገባውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳያገኝ ሲደረግ፣ 9ኛ. በቤተ ክህነቱ ውስጥ ተቀምጠው ለሚያጠፉት ጥፋት ተጠያቂ ላለመሆን ራሳቸውን በአንድም በሌላ መንገድ ከመንግስት አካላት ጋር በማቆራኘት መንግስትን ለጥፋታቸው መሸፈኛና ተባባሪ በማድረግ ዘወትር በጥፋት ላይ ጥፋትን የሚጨምሩ፣ መንፈሳዊነትን ለዓለማዊ ጥቅም የሸጡ፣ የቤተ ክርስቲያንን ህግና ስርዓት ሲቆርጡና ሲቀጥሉ የሚውሉ፣ የክህነት ካባ የለበሱ ነገርግን ክህነት በውስጣቸው የሌለ፣ ክርስቲያን ነን የሚሉ የክርስቲያን ምግባር የሌላቸውና ህዝበ ክርስቲያኑን ከመንግስት ጋር ለማጋጨት ሌት ተቀን የሚተጉ ግለሰቦች ሲበራከቱ፣

ነዐኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ለእምነታቸው ያላቸውን ክብርና ለቤተክርስቲያናቸው ያላቸው መንፈሳዊ ቅንዓት እስከ መስዋዕትነት መሆኑን እያወቁ ምእመኑ ከልጅነቱ ጀምሮ በውስጡ ያደገውን ጨዋነት፣ ህግ አክባሪነት፣ ሰላም ወዳድነት፣ ሆደ ሰፊነትና መንፈሳዊ ትዕግስትን በመፈታተን በውስጣቸው ሸሽገው ለያዙት ርካሽ ዓላማ መጠቀሚያ ለማድረግ ሲሯሯጡ፣መንግስት በቸልታ ማየት አለበት ማለት አይደለም፡፡

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት ሲደፈርስ አስችሎት በቸልታ ማየት አለበት ማለት አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ለማቃጠል የሚለኮሰው እሳት መንግስት እርሱንም እንደማይምረው ጠንቅቆ ያውቀዋል።

ስለዚህ የተከበራችሁ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የተፈጠረውንና የብዙዎቻችንን አንገት ያስደፋውን ችግር በጊዜያዊ ማሰታገሻ ሳይሆን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከነ ሰንኮፉ ለማስወገድ መንግስት ኃላፊነቱን ሊወጣበት ስለሚችልበት መንገድና ሊወስዳቸው ስለሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች በግልፅ እንነጋገር።

“የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር ያከናውንልናል እኛ ባሪያዎቹም ነስተን እንሰራለን” ነህምያ 2፡20

ቸር ያሰማን።
[የኛን ችግር እኛ እንፍታው]

ዲያቆን መሐሪ ገብረማርቆስ

እንደሚመስለኝ እኚህ ኃይለ ገብርኤል የሚባሉ ሰው ችግራችን የገባቸው አይመስለኝም፡፡ የችግራችን አንዱ ምንጭ እኮ ኃላፊነትን ከመቀበል ይልቅ “እንትና ይሥራው፡፡ ወይም እነ እንቶኔ ይከውኑት፡፡ እኔ የልጆች አሳዳጊ፣ የሽማግሎች ጧሪ፣ የእድር ዳኛ፣ የዕቁብ ጸሐፊ ወዘተ. ነኝ፡፡” እያልን መሸሻችን ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ችግር እንዲህ ሰማይ እንዲሰቀል ያደረጉት እነማን ናቸውና? ነገሥታቱና የእነርሱ ፈቃድ ፈጻሚዎች ካህናተ ደብተራ አይደሉምን፡፡ የቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ላደመጠው ዛሬም ይናገራል፡፡ ያድምጡት፡፡

በመሠረቱ “የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ነገሥታት መፍታት አለባቸው፡፡” የሚል አስተምህሮ ከየት የተገኘ እንደሆነ አይገባኝም- ነገሥታት አስተዳዳሪዎች (በውድ ወይንም በግድ ሊሆን ይችላል) እንጂ ወንጌል ሰባኪነት ዐቢይ ግብራቸው አይደለምና፡፡ አሁን ያለንበት ችግር ሁሉ ትልቁ መነሻው ጳጳሳት የዘወትር የነገሥታት ግብር በላተኞች፣ ነገሥታት የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ሆነው ሕዝቡን እግዚአብሔርንና ሕገ እግዚአብሔርን በማስተማር ማበልጸግ ቀርቶ እንደ ገባር መመልከት ሥር ሰድዶ በመኖሩ አይደለምን? ጳጳሳቱ በዋናነት የነገሥታቱን፣ ነገሥታቱም በዋናነት የጳጳሳቱን (የቤተ ክርስቲያኗን አላልኩም!) ጥቅም በማስጠበቅ ባተሌ ሆነው ወንጌል መስበክ ተዘንግታ፣ ሕዝቡ ችላ ተብሎ በመኖሩ አይደለምን? ቤተ ክርስቲያንን ግን ቤተ ክርስቲያን ያሰኛት መሠረታዊው ነገር በክርስቶስ

ደም የከበሩ ልጆች መኖራቸው ነበር፡፡ የትኛው መልእክት ነው ለነገሥታት የተጻፈው? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለድኾች ወንጌልን በመስበክ እንጂ ነገሥታትን በማባበል አይታወቅም፡፡

ሕገመንግሥቱን ለመተንተን በሞከሩበት ረገድ ደግሞ ይህን ተመልከቻለሁ፡፡ አንደኛ ይህች እኔና በእኔ እድሜ ያሉ ወጣቶች የተረከብናት ሀገር ኢትዮጵያ እንደምትባል ብቻ ሳይሆን በውስጧ ክርስቲያኖችም፣ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችም በሰላም የሚኖሩባት፣ ልዩ ልዩ ቋንቋችን የሚናገሩ ነገዶች ከነየራሳቸው ታሪክ፣ ባህልና ሥነ ጽሑፍ ጋር ተፈቃቅደው ያሉባት ሀገር ናት እንጂ ነገሥታቱ ጠፍጥፈው የፈጠሯትና ቤተ ክርስቲያኗ ብቻዋን በትምህርት እየቀረጸች ያሳደገቻቸው ሕዝቦች ያሉባት ሀገር አይደለችም፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ሕዝቦች መንግሥት የእነዚህን ሁሉ ሕዝቦች መሠረታዊ ሰብአዊ ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ያደርጋል እንጂ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ሃይማኖታዊ ጉዳይ እየገባ ችግሮችን የመፍታት ታሪካዊም ኅሊናዊም ግዴታም ሆነ መብት የለውም፡፡

የችግሮቻችንን መነሻዎች ከዲያቆን ዳንኤል ክብረት ጽሑፍ እንዳስተዋልሁት በወረስነው የአድርባይነት (ዛሬን ልኑር ስለነገ አያገባኝም ባይነትን እና እነእንቶኔ ይወጡትን ይጠቀልላል፡፡) ባህልና በመንፈሳዊው ቦታ ላይ የምናየው የመንፈሳዊነት ድርቅ ላይ የሚያጠነጥኑ ሆነው ይታዩኛል፡፡ በመሆኑም መፍትሔው ያለው እኛው እጅ እንጂ ነገሥታቱ ዘንድ አይደለም፡፡ ነገሥታቱማ Athnatius from CA እንዳለው እኛን የሚመለከቱን እንደጅሎች ቤተ ክርስቲያንንም የሚመለከቱት ብልሆች የሚመሯት በሥነ ምግባር የታነጹ ዜጎችን (ዜጋ ማለት በነገራችን ላይ የድሮ ትርጉሙ ገባር ማለት ነበር፡፡) የምታፈራ የጅሎች መሰባሰቢያ ተቋም አድርገው ነው፡፡ መብታቸው ነው፡፡ እራሳችንን አስተባብረን ለበጎ ነገሮቻችንና ለመልካም ነገዎቻችን መቆም እስካልቻልን ድረስ በማቴሪያሊስቶች ዘንድ እንከፎች ተደርጎ ከመቆጠር አንድንም፡፡

ዛሬ ለእነዚህ ሰዎች ችግራችንን ፍቱልን ብሎ ማቅረብና መብት መስጠት ነገ በቤተ ክርስቲያናችን እንደ ልጅነታቸው ሳይሆን እንደ ንግሥናቸው እንዳሻቸው እንዲያዙ መብት መስጠት ነው፡፡ ወገን ነገሮችን ከነገው ትውልድ ጋር እናስባቸው እንጂ! ቁጭ ብሎ የሰቀሉት ኮ ቆሞ ለማውረድ ይከብዳል፡፡ “ከታሪካችን የምንማረው ከታሪክ አለመማራችንን ነው” ይላል ፈላስፋ፡፡ አሜሪካ ዛሬ መያዣ መጨበጫ ያሳጧትን ጽንፈኞች የኮሚዩኒስቱን ወገን ያዳከሙልኛል ብላ በፈቃዷ እንዳደራጀቻቸው ልብ በሉ፡፡ ነገሥታት ቤተ ክርስቲያንን ከጠቀሙት ይልቅ የጎዷት እጅግ ይበዛል፡፡ ታሪኳን ተመልከቱ፡፡

የቤተ ክርስቲያን ችግር መነሻው እኛው ዘንድ ነው መፍትሔውም መመንጨት ያለበት ከእኛው ቤተ ክርስቲያኗን ተጠግተን ከምንኖር ሰዎች ነው፡፡ ወደነገሥታቱ እንመለስ ካልን መፍትሔንም ከእነርሱ ከጠበቅን አለቀ ዐደቱን ሰብረን መውጣት አንችልም፡፡ ይልቅ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባቱን ሕገመንግሥታዊ አቋም እንጠቀምበትና ሰላማዊና ጥበብን በተሞላ መንገድ ቤተ ክህነቱን ከሸፈነው የኃጢኣት አቧራ እናጽዳው፡፡ መንግሥት የሚፈልገው አካባቢያዊው ሰላም እንዳይናጋ ብቻ ነው፡፡ ፖሊሲዎቹን እስካልነቀነቅንበት ንቅናቄያችንን አይጠላውም፡፡

እናስተውል!!!!

ባርባራ እና ስቴፈን

አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን የዕለት ተዕለት ተግባራት የሚያጋጥሙንን ነገሮች ካስተዋልናቸው በትምህርት ቤት የማናገኛቸውን ዕውቀቶች እንገበይባቸዋለን፡፡ መደበኛውን ሥራችንን እንኳን ቢሆን በማዳመጥ እና በፍቅር ከሠራነው ለዕድሜ ልክ የሚሆኑ ዕውቀቶችን እግረ መንገዳችንን እናገኛለን፡፡ አንዲት አሜሪካዊት ነርስን ያጋጠማት ነገርም እንደዋዛ ነበር ሕይወቷን የቀየረው፡፡

አንድ ቀን አንድ ሽማግሌ ታካሚ ሰው ከነርሷ ፊት ለፊት ተቀምጠው አሁንም አሁንም ይቁነጠነጡ ነበር፡፡ አሁንም አሁንም ደጋግመው ሰዓታቸውን ያያሉ፡፡ ነርሷ ገረማትና ረጋ ብለው ሕክምናቸውን እንዲከታተሉ ነገረቻቸው፡፡ ሃሳቧን ተቀብለው ለጥቂት ሰኮንዶች ረጋ ቢሉም አሁንም የቀደመ ነገራቸው ተመለሰ፡፡

«ለምንድን ነው ይህንን ያህል ያልተረጋጉት? ያጋጠመዎ ችግር አለ?» አለቻቸው፡፡

«ፈጽሞ፤ ምንም ዓይነት ችግር አላጋጠመኝም»

«ታድያ ለምን ይቁነጠነጣሉ፤ መረጋጋትኮ አልቻሉም» አለቻቸው፡፡

«ይቅርታ» አሉና አንገታቸውን ደፋ አደረጉ፡፡ ነገር ግን ወዲያውኑ ሰዓታቸውን ደግመው ተመለከቱት፡፡

«ሐኪሙን ለማግኘት የቸኮሉበት ምክንያት አለ?» አለቻቸው ነርሷ የሰውዬው ሁኔታ እንግዳ ሆኖባት፡፡

«አዎ፤ በቶሎ እርሳቸው ጋር ቀርቤ ብጨርስ ጥሩ ነው» አሏት፡፡

«ሌላ ሐኪም ጋር ቀጠሮ ይዘዋል» አለቻቸው፡፡

«ፈጽሞ፤ ሌላ ሐኪም ጋርስ ቀጠሮ የለኝም» አሉ ታካሚው፡፡

«ታድያ ወዴት ለመሄድ ነው ይህንን ያህል የቸኮሉት፡፡»

«ከባለቤቴ ጋር አምስት ሰዓት ላይ ቀጠሮ አለኝ» አሉ ታካሚው፡፡

«አ፤ ከባለቤትዎ ጋር ከሆነማ ነገሩ ቀላል ነው፤ ማስረዳትም ይችላሉ፤ ባለቤትዎም ቢሆኑኮ የርስዎን ታክመው መዳን ይፈልጉታል፡፡ እናም እባክዎ አሁን በቂ ጊዜ ስለ ሌለዎ ይደውሉላቸውና አንድ አሥራ አምስት ደቂቃ እንደሚያረፍዱ ይንገሯቸው» አለች ነፍሷ እፎይታ እየተሰማት፡፡

«ባለቤቴ ጋር መደወል አልችልም፡፡ እርሷ ብደውልላትም መደወሌን አታውቅም፤ መደወሌንም አታስታውስም» አሉ በኀዘን ስሜት፡፡

«እንዴ ለምን?» አለች ነርሷ አሁን እንደገና ግራ እየተጋባች፡፡

«እርሷ ታምማለች፡፡ ያለችውም በአረጋውያን መጦርያ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አታስታውሰውም፡፡ አልዛይመር የተባለው በሽታ በጣም አጥቅቷታል፡፡» አሉና ታካሚው ሰዓታቸውን ተመለከቱ፡፡

«ታድያ በዚህ ዓይነት እርስዎንስ ያስታውሱዎታል እንዴ?» አለች ነርሷ በተሰበረ ልብ፡፡

«የኔ ልጅ እርሷኮ እኔንም አታስታውሰኝም፡፡ ፈጽማ ረስታኛለች» አሉ ታካሚው፡፡

«ማንነትዎን አያስታውሱዎትም፤ አያውቁዎትም ማለት ነው?»

«አዎ አታውቀኝም፡፡ የምታስታውሰው ነገርም የላትም፤ ፈጽማ ረስታኛለች፤ የምገዛላትን፤ የማደርግላትን ነገር ሁሉ ረስታዋለች፡፡ እኔ አሁን ማን እንደሆንኩ አታውቅም»

«ታድያ እንደዚህ የማያስታውሱዎ ከሆነ ለምን ቸኮሉ?» ለእርሳቸውኮ አምስት ሰዓትም ሆነ ሰባት ሰዓት ያው ነው፡፡ በሉ ቀስ ብለው ሕክምናዎን ጨርሰው ይሂዱ» አለች ነርሷ ነገሩን በማቅለል፡፡

«የለም የኔ ልጅ፤ እንደዚያ አይደለም፡፡ እኔ እርሷጋ ዘወትር እሑድ በአምስት ሰዓት መሄድን አስለምጃለሁ፡፡ ከርሷ ጋር በዚህ ሰዓት ቀጠሮ አለኝ፡፡ ብታውቀውም ባታውቀውም፤ ብታስታውሰውም ባታስታውሰውም ቀጠሮዬ ግን አይቀርም፡፡ ዋናው ነገር የርሷ ማስታወስ አይደለም ልጄ፤ የኔ ማክበር ነው፡፡ ይህ ለእኔ እና ለእርሷ ፍቅር ከሚከፈሉት መሥዋዕትነቶች አንዱ ነው፡፡ እርሷ አታውቀኝም፤ እኔ ግን አውቃታለሁ፡፡ ትናንት እንደዚህ አልነበረችም፡፡ እኔ የትናንትናዋን ሚስቴን ነው የማስታውሰው፡፡ ስለዚህ በሰዓቱ መሄድ አለብኝ፡፡

«ያኔ አታዬኝም፤ አትሰማብኝም ብዬ ምንም ነገር ተደብቄያት አድርጌ አላውቅም ነበር፡፡ ዛሬም አታውቅም ብዬ ምንም ነገር ላደርግ አልፈልግም፡፡ በሰው አለማወቅ መጠቀም ይበልጥ አላዋቂነት ነው ልጄ፡፡»

«ለመሆኑ ካላስታወሱዎት አሁን ሂደው ምን ያደርጋሉ?» አለች ነርሷ የኒህን አስገራሚ ሰው የኑሮ ምሥጢር ለማወቅ ጓጉታ፡፡

«ልብሷን እቀይርላታለሁ፤ የቤቷን አበባ እቀይራለሁ፡፡ ወደ ውጭ አወጣትና ብታስታው ሰውም ባታስታውሰውም ዝም ብዬ በዚህ ሳምንት የሆነውን ነገር አወራታለሁ፤ ያለፈውን ትዝታ እያነሣሁ አጫውታታለሁ፡፡ ብትስቅም፣ ባትስቅም አንዳንድ ጊዜ ቀልድ እነግራታለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አጫጭር ታሪኮችን አነብላታለሁ፡፡ ይህ ሁሉ ድሮ ደኅና እያለች የማደርግላት ነው፡፡ አንዳችም አላጓድልባትም፡፡ አየሽ ልጄ፣ እኔ ያኔ ስንጋባ ቃል የገባሁት ለሚስቴ እንዲህ እና እንዲያ አደርግላታለሁ ብዬ እንጂ እርሷ እንዲህ እና እንዲያ ታደርግልኛለች ብዬ አይደለም፡፡ ይህንን

ቃል የገባችው እርሷ ናት፡፡ እርሷ ደግሞ እስከ ምትችል ድረስ ይህንን ነገር አክብራ ፈጽማለች፡፡ አሁን ግን አትችልም፡፡ እኔ ግን ቃል የገባሁትን መፈጸም እችላለሁ፡፡ ስለዚህ ለምን አስቀርባታለሁ፡፡ አንቺ ለምን የራስሽን አታደርጊም? ያንቺን ጥሩነት እና መጥፎነት ለምን ሰዎች ይወስኑልሻል? አንቺ ራስሽ መወሰን አትችይም?»

«አምስት ደቂቃዎን ብቻ ልውሰድብዎት፤ ይህንን ሁሉ እንደሚያደርጉላቸው ውለታዎን የማያስቡልዎ ከሆነ፤ ከርሳቸውም አንዳች ምላሽ የማያገኙ ከሆነ፤ ምን ይሁነኝ ብለው ይደክማሉ?» አለች ነርሷ አገጯን በመዳፏ ደግፋ፡፡

«እኔ ለሚስቴ አንዳች ነገር የማደርገው ውለታ ፍለጋ ብዬ አይደለም፡፡ የኔ ደስታ ሳደርግ እንጂ ሲደረግልኝ የሚገኝ አይደለም፤ በመስጠት እንጂ በመቀበል አይገኝም፤ በመሞት እንጂ በመግደል አይገኝም፤ እኛ አብረን ለመኖር ተስማማን፤ ቃል ገባን እንጂ፤ በደኅንነታችን ጊዜ ብቻ አብረን ለመሥራት ኮንትራት አልተፈራረምንም፡፡ ለኔ በደኑ ጊዜም ሚስቴ፣ ናት በክፉው ጊዜም ሚስቴ ናት፡፡ ሳትታመምም ሚስቴ ናት፤ ታምማም ሚስቴ ናት፡፡ ሌላው ቀርቶ ስትሞትም ሚስቴ ናት፡፡ እርሷ ብታልፍም እኔ ግን ትዝታዋን አግብቼው እቀጥላለሁ፡፡ ከዚያም ደግሞ በሞት እከተላታለሁ፡፡ ስለሚቀጥለው ዓለም አላውቅም፡፡ ከቻልኩ ግን እዚያም ብትሆን ሚስቴ ናት፡፡ እኔ ባልዋ ስሆን ለርሷ የባልነት ግዴታዬን ለማድረግ እንጂ ከርሷ ለመቀበል አይደለም፡፡ እርሷም የርሷን ለማድረግ እንጂ ከኔ ለመቀበል አይደለም፡፡ ልጇ ከሰጡሽ ተቀበይ እንጂ ለመቀበል ግን ስትይ ግን አትስጭ፡፡ አሁን ይብቃኝና እባክሽን ሐኪሙ ጋር ቶሎ አገናኝኝና ልሂድ፡፡» አሉ ታካሚው አሁንም ሰዓታቸውን እያዩ፡፡ ነርሷ ተገረመች፡፡

«ካላስቸገርኩዎ እባክዎን የባለቤትዎን ስም ይንገሩኝ» አለች ነርሷ በሶፍት ዓይኖቿን እየጠረገች፡፡

«ባለቤቴ ባርባራ ትባላለች፤ የኔ ከመዝገቡ ላይ አለልሽ» አሏት፡፡

«አዎ ሚስተር ስቴፈን» አለችና ማወቋን ገለጠችላቸው፡፡

ቀዳሚው ታካሚ ከሐኪሙ ጋ ለመውጣት ሲዘገዩ እኒህኛው ታካሚ ተነሡና ሄዱ፡፡ «እባክዎን ቆዩ» ለማለት ነርሷ ልብ አልቀረላትም፡፡

ነርሷ ፈቃድ ወሰደችና ለአሥራ አምስት ቀናት ያህል ቤቷ ተቀመጠች፡፡ እኒያ አረጋዊ ታካሚ የነገሯትን ነገር ደግማ ደጋግማ አምሰለሰለችው፡፡ በእርሳቸው ሕይወት ውስጥ ያለውን መመርያ መረመረችው፡፡ ከራስዋም ጋር ለማዛመድ ሞከረች፡፡ በአሥራ አምስተኛው ቀን አንድ ሃሳብ መጣላት፡፡ ሰዎች በራሳቸው ተነሣሽነት ከማንም ዋጋ እና ውለታ ሳይጠብቁ በጎ ነገርን እንዲያደርጉ የሚያበረታታ፤ የሚያስተባብር እና የሚያስተምር ተቋም መመሥረት፡፡

እጅግ ብዙ ሰዎችን በዚህ ዓላማ ያሰለፈ አንድ ትልቅ ተቋም መሠረተች «ባርባራ እና ስቴፈን» ይባላል፡፡

ይህንን ታሪክ ሳነብብ ብዙ ነገሮች ታወሱኝ፡፡ አንተ እንዲህ የማታደርግ ከሆነ እኔም እንዲህ አደርጋለሁ ብለው በእልህ ዥዋዥዌ የሚጫወቱ ባል እና ሚስት፡፡ ከእገሊት ጋር ስለሄደ ከእገሌ ጋር ሄጂ ልኩን እሰጠዋለሁ ብለው የሚጠዛጠዙ ፍቅረኞች፡፡ ሌላው ሰው ቀጠሮ ስለማያከብር የኛ ቀጠሮ ማክበር ምን ዋጋ አለው ብለው አርፋጅ የሆኑ

ሰዎች፡፡ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ እንደሚባለው ሌላው ሰው እየዘረፈ የኔ ሐቀኛ መሆን ምን ዋጋ አለው ብለው ራሳቸውን በሌሎች ምክንያት ያበላሹ ሰዎች፡፡

ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ትኩረት ካልሰጡት እኔ ምን አግብቶኝ እጨነቃለሁ ብለው የተማሪዎቻቸው ቸልተኛነት የተጋባባቸው መምህራን፡፡ የሠፈሩ ሰው ቆሻሻ የትም እየጣለ እኔ ብቻዬን ብጠነቀቅ ምን ዋጋ አለው ብለው እነርሱም ከበራቸው ላይ ቆሻሻ መከመር የጀመሩ ሰዎች፡፡

እገሌ ከኔ ሠርግ አልመጣም ብለው ከሰው ሠርግ የቀሩ፤ እገሌ ልቅሶ ሳይደርሰኝ ቀረ ብለው ከሰው ልቅሶ የቀሩ፡፡ እገሌ ታምሜ አልጠየቀኝም ብለው ሲታመም በመቅረት ብድር የሚመልሱ ሰዎች፤ እገሌ ሰላም አላለኝምና ሰላም አልለውም ብለው ሰላምታ ያቆሙ ሰዎች፤ ሌሎቹም ሌሎቹም፡፡

እገሌ አስቀይሞኛልና ከዕድር ከማኅበር ተለይቻለሁ፤ እገሌ እንደምጠብቀው አልሆነልኝምና ከዛሬ ጀምሮ አልመጣም፡፡ ከመንግሥት ጋር ተጣልቻለሁና ከንግዲህ ለሀገሬ አንዳች በጎ ነገር አልሠራም፡፡ ፓትርያርኩ ሊሰሙ አልቻሉምና ከንግዲህ ስደተኛ፣ ገለልተኛ፣ ቁሪተኛ፣ ስሞተኛ ሆኛለሁ፡፡ እነ እገሌ ለምሠራው ሥራ፣ለምሰጠው አገልግሎት፣ለማደርገው አስተዋጽዖ ግምት አልሰጡትምና ትቼዋለሁ፤ የምንለውን ሰዎች ሚስተር ስቴፋን ቢሰሙ ምን ይሉ ይሆን?

እኒያ ታካሚ ሽማግሌ እንዳሉት ለምን ይሆን ግን የኛን ማንነት ሰዎች የሚወስኑት? ፀሐይ ትወጣለች፤ ነገር ግን እኛ እንድንሞቃት አስባ አይደለም፡፡ እርሷ ግን ምንጊዜም ትወጣለች፡፡ ነፋሱም ይነፍሳል፤ እኛ እህል ብናበራይበትም ባናበራይበትም ይነፍሳል፡፡ መሬት በፀሐይ ዙርያ ትዞራለች፤ በብርሃኑ እና በጨለማው ጊዜ ሰዎች ቢጠቀሙም ባይጠቀሙም ትዞራለች፡፡ እነዚህ ሁሉ የእነርሱን ድርሻ ይወጣሉ እንጂ የኛን ምላሽ አስበው አይለወጡም፡፡

ታድያ እኛ ምነዋ!

ችግር ነን መፍትሔ ?

ሁለት መኪኖችን ብቻ አጨናንቃ የምታሳልፍ መንገድ ነበረች፡፡ ሁለቱ መኪኖች ሲተላለፉ ጎንና ጎናቸው ሊነካካ ለጥቂት ብቻ ነው የሚያመልጡት፡፡ ነገር ግን ሾፌሮቹ ሁሉ ለምደውታልና በቀላሉ ፈገግ እያሉ ይተላለፋሉ፡፡

አንድ ቀን አንድ ለምድር ለሰማይ የከበደ ወፍራም የትራፊክ ፖሊስ መሐል መንገድ ላይ ቆሞ በግራ እና በቀኝ የሚተላለፉትን ተሽከርካሪዎች «እለፉ እለፉ» ይላል፡፡ መኪኖቹ መተላለፍ ስላልቻሉ ከሚሄደው የሚቆመው በዛ፡፡ በተለይማ ትልልቆቹ የጭነት መኪኖች መተላለፍ አልቻሉም፡፡ የትራፊክ ፖሊሱ ግራ ገባው፡፡ ከዚያ በፊት ምንም እንኳን መንገዱ ጠባብ ቢሆንም እንደዚያ ቀን ያለ መጨናነቅ ግን ታይቶ አይታወቅም፡፡ መኪኖቹ ቀስ ይሉ ይሆናል እንጂ አይቆሙም፡፡

«ዛሬ ምን ተፈጠረ፣ ምን ዓይነት ሾፌሮች ናቸው ደግሞ ዛሬ የመጡት፣ ምን ዓይነት የተረገመ ቀን ነው» እያለ ያማርራል፡፡ በሾፌሮቹ እና በመኪኖቹም ላይ ይቆጣል፡፡ አልቻለም እንጂ እየሳበ ሊያሳልፋቸውም ይፈልጋል፡፡ «የኔ አባት በአንድ እጁ መቶ መኪና ያቆማል» ብላ አንዲት ሕፃን ልጅ ለጓደኞቿ ነገረቻቸው አሉ፡፡ «እንዴ ምን ዓይነት ስፖርተኛ ቢሆን ነው?» ብለው ቢጠይቋት «አይ ስፖርተኛ አይደለም የትራፊክ ፖሊስ ነው» አለች እየተባለ የሚነገረው ለርሱ ነው እያሉ ይሳሳቃሉ፡፡

የትራፊክ ፖሊሱ የትራፊክ መጨናነቁ የመጣበት ምክንያት አልተገለጠለትም፡፡ ምንም እንኳን መንገዱ አስቸጋሪ፣ መሠራት ሲገባው ሳይሠራ የኖረ፣ እንኳን ሁለት መኪኖችን አንድን መኪና በደንብ የማያሳልፍ ቢሆንም የዛሬው መጨናነቅ ግን ለየት ያለበት ምክንያት ግን አልተገለጠለትም፡፡

እየቆየ መናደድ እና ክፉ ቃል መናገር ጀመረ፡፡ ሾፌሮቹን ጮኸባቸው «ዛሬ ምንድን ነው የኾናችሁት?» እያለ አፈጠጠባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሾፌር በመስኮቱ ብቅ ብሎ «ወንድሜ አንዱ ችግርኮ አንተው ነህ» አለው፡፡ የትራፊክ ፖሊሱ ከጠዋት ጀምሮ የለፋው ድካሙ ትዝ አለውና «እንዴት ይህንን ሁሉ ስደክም እያየህ ችግሩ አንተም ነህ ትለኛለህ?» አለው፡፡ ሾፌሩም፡፡ «በዚህ በጠባብ መንገድ ተራራ የምታህል ሰውዬ ስትጨመርበት በምን እንለፍ፡፡ አንተኮ መፍትሔ የሰጠህ መስሎሃል እንጂ ችግር እያበባስክ ነው፡፡ እስኪ ከመንገዱ ወጣ በልና የሚሆነውን እየው» አለው፡፡

የትራፊክ ፖሊሱ ለተወሰነ ጊዜ ሲያቅማማ ከቆየ በኋላ ከመንገዱ መሐል ወጣ፡፡ ያን ጊዜ ሲጨናነቁ የነበሩት መኪኖች እንደ ቀድሟቸው መተላለፍ ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳን የመንገዱ ችግር እንዳለ ቢሆንም የቆሙት መኪኖች ግን መንቀሳቀስ ቻሉ፡፡

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መንገድ ላይ የቆምን ሰዎችም ይህንን ጥያቄ መጠየቅ አለብን፡፡ እኛ ለቤተ ክርስቲያን ችግሮች መፍትሔ አመጣን ወይስ እኛው ራሳችን ችግሮች ሆንን?

ኢትዮጵያውያን አበው ጵጵስና አይሾሙ በሚል በኋላ የመጣ ሕግ ምክንያት ዘ17 ጳጳሳትን ከግብጽ አመጣን፡፡ ቋንቋችንን አያውቁም፣ ከሀገሪቱ ስፋት አንፃርም በቂ አይደሉም፣ ደግሞስ ኢትዮጵያ ከማን አንሳ ነው ሰዎቿ ብቁ አይደለም የሚባሉት? ብለን ከግብጻውያን ጋር ተከራክረን ጵጵናን አመጣን ::

ይህንን ለማየት ብዙ አበው ወደዱ ግን አላዩም፣ የኛ ዓይኖች ግን ንዑዳን ከቡራን ናቸው፤ ኢትዮጵያን አበው ኢትዮጵያውያንን ሲሾሙ፤ ሕዝቡም በየአካባቢው ጳጳሳትን ሲያገኝ ተመልክተዋልና፡፡

ግን ግብፃውያን ይሾሙበት ከነበረው ዘመን ምን ያህል ለውጥ አመጣን? ምን ያህል ስብከተ ወንጌልን አሰፋፋን? ምን ያህል በየገጠሩ ደረስን? ምን ያህል አዳዲስ ሕዝቦችን ለወንጌል ጠራን? ምን ያህሉ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ተምረው፣ አምነው፣ ተጠምቀው፣ ተክነው፣ ጳጵሰው ለማየት በቃን?

የክህነት እና የምንኩስና አሰጣጡ ከግብፃውያን ዘመን ይልቅ የተሻለ ሆነ? የራሳችን ሲኖዶስ በስንት የቀኖና ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ወሰነ? ስንት ያረፉ ቅዱሳን በሲኖዶሳችን «ቅዱስ» ተብለው ተወሰነላቸው፡፡ መጻሕፍት ተቆጥረው

ተሰፍረው በሲኖዶሱ ጸደቁጥ ዛሬ የራሳችን ሲኖዶስ እያለን «ዓሣ ይበላል አይበላም? ስቅለት በማርያም ዕለት ሲውል ይሰገዳል አይሰገድም» የሚሉት እንኳን ውሳኔ አጥተው እያጨቃጨቁን አይደለም»

የቤተ ክህነቱ አሠራር የሀገር ልጆች ሲይዙት ምን ያህል ተቀላጠፈ» ግብጽ ድረስ ከመሄድ አዲስ አበባ ድረስ መምጣት ቀላል ሆነ» ለግብጻውያን ይገበር የነበረው ወርቅ እና ብር ቀርቶልናልን» የጵጵስናው መዓርግስ ከግብጻውያኑ ዘመን ይልቅ ዛሬ ይበልጥ በሕዝቡ ዘንድ ተከበረን»

የጵጵስና ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ችግር ሆነ ወይስ መፍትሔ»

ወንጌል በሚገባ አልተሰበከም፣ የጥንቱ አካሄድ አያስኬድም፣ በአዲስ ጉልበት እና በአዲስ መንገድ ሕዝቡን ማስተማር አለብን ብለን አያሌ «ሰባክያን» ተነሣን፡፡ ነጠላም፣ ጋቢም፣ ቀሚስም፣ ወይባም፣ ካፖርትም ደርበን በየመድረኩ ቆምን፡፡ ከመሐል ከተማ እስከ ዳር ሀገር፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ባሕር ማዶ ዞርን፡፡ ሕዝቡም እሰይ ሰባክያን አገኘን፣ ቃለ እግዚአብሔርን ተማርን፣ ሃይማኖታችንንም ዐወቅን ብሎ ደስ አለው፡፡

ለመሆኑ ከዚህ ሁሉ በኋላ ሕዝቡ ቆራቢ ሆነ? በመናፍቃን መወሰዱ ቀረ? ባዕድ አምልኮ ቀረ? ገባው ወይስ ተደናገረ? ቲፎዞ ነው ወይስ ደቀ መዝሙር ያፈራነው? ለመሆኑ በኛ ዘመን ስንቶቹ ዐፄ ካሌቦች ሥልጣናቸውን ትተው መነኑ? ስንቶቹ አቡነ ሳሙኤሎች ተነሥተው በአንበሳ እየሄዱ አስተማሩ? ስንቶቹ ክፍለ ዮሐንሶች በዕውቀት ከበሰሉ በኋላ መነኑ? ስንቶቹ ላሊበላዎች አዲስ ተአምር ሠሩ? ስንት እግዚእ ኃረያ እና ጸጋ ዘአብ ተገኙ? ምንድን ነው ያፈራነው ፍሬ?

እኛ ባልነበርን ጊዜ ዘንዶ ይረግጡ፣ አንበሳ ይረግጡ፣ በደመና ይወጡ የነበሩት ቅዱሳን በስብከተ ወንጌሉ ዘመን የት ሄዱ?

ሕዝቡ ጥቅስ ዐወቀ፤ ዐውቆ ግን ምን አደረገ? ማይክራፎኑ አደገ፣ የስብከቱ መድረክ ጨመረ፣ የሰባኪው ቀሚስ ተለወጠ፣ የሰባኪው የኑሮ ሁኔታ ተለወጠ፣ ትምህርቱ ከብራና ወደ ዲቪዲ ተሻሻለ፣ ከዶግማ ትምህርት ወደ ቀልዳ ቀልድ ተቀየረ፣ ሰውን ከማዳን ሰውን ወደ ማስደሰት ተሸጋገረ፣ የተማሩ ሊቃውንት ያልተማረውን ሰው ማስተማራቸው ቀርቶ ያልተማርን ሰባክያን ያልተማረውን ሰው ማስተማር ጀመርን፡፡

የማይጾም የሚጾመውን፣ የማይጸልይ የሚጸልየውን፣ የማያስቀድስ የሚያስቀድሰውን ወደ ሚያስተምርበት ዘመን ደረስን፤ ሕዝቡን ከቤተ ክርስቲያን ወደ አዳራሽ፣ ገድል እና ተአምር ከመስማት ቀልድ እና ጨዋታ ወደመስማት አሸጋገርነው፡፡ እኛ ባልነበርንበት ዘመን ምንም ያልሆነ ሕዝብ ሰባክያን በዙ በሚባልበት ዘመን በአሥር ዓመት ውስጥ ፴% ቀነሰ፡፡ የክርስቶስ ተከታዮች አናፈራለን ብለን የእገሌ ተከታይ አፍርተን አረፍነው፤ ከቤተ ክርስቲያኑ ቁጥር ይልቅ በኛ ዘመን ጫት ቤቱ በለጠ፡፡

ታድያ እኛ አሁን ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ችግር ነን ወይስ መፍትሔ?

«ነይ ነይ እምዬ ማርያም» እየተባለ የተዘመረው መዝሙር አይበቃም ብለን ተነሣን፡፡ መናፍቃን ሕዝቡን በመዝሙር ከሚወስዱት በመዝሙር እናስቀረው ተባለ፡፡ ዘማርያን መጡ፣ የብስ ረገጡ፡፡ መዝሙር አወጡ፡፡ ካሴት አስቀረጡ፡፡ በየሦስት ቀኑ አንድ የመዝሙር ካሴት እስከመውጣት ደረሰ፡፡ መዝሙር ከጠፋበት ዘመን ተነሥተን መዝሙር የበዛበት ዘመን ላይ ደረስን፡፡ ቤቱ፣ ሻሂ ቤቱ፣ ታክሲው፣ የቤት መኪናው፣ ጫት ቤቱ ሁሉ መዝሙር በመዝሙር ሆነ፡፡

ሕዝቡም በቋንቋችን፣ የሚገባን መዝሙር አገኘን ብሎ ደስ አለው፡፡ ዘማርያኑም «በምስጋና ምድሪቱን ከደንናት» ብለው ተኩራሩ፡፡

ለመሆኑ የያሬድ ዜማ ይበልጥ ታወቀ ወይስ ጠፋ? በመዝሙር በኩል መናፍቃንን ተከላከልን ወይስ አስገባን? ድምፃዊው በዛ ወይስ ዘማሪው? መዝሙር አገልግሎት ሆነ ወይስ ሥራ? ዝማሬ ጽደቅ ሆነ ወይስ ሞያ? ሕዝቡን ከዘፈን አመጣነው ወይስ ከቅዳሴ አስወጣነው? የዘማርያኑ ኑሮ ነው ወይስ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ነው የተለወጠው? ሕዝቡ መንፈሳዊ መዝሙር ነው የሚገዛው ወይስ በእናቱ ዘፈን በአባቱ መዝሙር የሆነ? ሕዝቡን ወደ ጸጥታ ወደብ ወሰድነው ወይስ አጨቃጨቅነው? አስማማነው ወይስ አለያየነው? የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አስፋፋን ወይስ የራሳችንን አመለካከት? ታድያ እኛ ለቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ችግር ነን ወይስ መፍትሔ?

ነዳያንን ለማብላት፣ ገዳማትን ለመጎብኘት፣ ገዳማትን ለመርዳት፣ጽዋ ለመጠጣት፣ ስብከተ ወንጌል ለማስፋት፣ የሞያ እገዛ ለማድረግ፣ ወዘተ ተብሎ ማኅበራት እንደ እንጉዳይ ወጡ፡፡ ሕፃኑ፣ ወጣቱ፣ ሽማግሌው፣ ወንዱ፣ ሴቱ ማኅበርተኛ ሆነ፡፡ አንድ አልበቃ ብሎ አንድ ሰው ሁለት ሦስት ማኅበር ገባ፡፡

ቤተ ክህነቱ በሚገባ አልሠራም፣ ገዳማት አድባራቱ ተጎድተዋል፣ መዘምራን ተለያይተዋል፣ ሰባክያን ተራርቀዋል፣ እየተባለ የማኅበር ዓይነት መጣ፡፡ ሌላው ቀርቶ በየበኣታቸው ይጸልያሉ የሚባሉት ባሕታውያንም ማኅበር አቋቁመናል አሉ፡፡ በሰማይ የሚበሩ፣ በምድር የሚሽከረከሩ፣ በባሕር የሚኖሩ ሁሉ ማኅበር መሠረቱ፡፡ የተማሩ፣ ያልተማሩ፣ ለመማር ያላሰቡ ማኅበር ኖራቸው፡፡

ቤተ ክህነቱ ተረሳ፡፡ ሁሉም በየራሱ መሮጥ ጀመረ፡፡ ዋናው ሞተር እንዲሠራ እናደርጋለን ብለው የተቋቋሙ ማኅበራት ለራሳቸው ሞተር ሆኑ፡፡ ቤተ ክህነትም ሳያውቃቸው፣ ቤተ ክህነቱንም ሳያውቁት ቀጠሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ዋናው ችግር አይመለከተንም ብለው ማሉ፡፡ ዕንቅርቱን ትተው ንቅሳቱ ላይ አተኮሩ፡፡ ገበተው ከመሥራት ይልቅ ወጥተው መተቸትን መረጡ፡፡

እንደ ዘመነ መሳፍንት ሁሉም በየራሳቸው ነው የሚጓዙት፡፡ ለመተባበር፣ ለመነጋገር፣ አይፈልጉም፤ አያስቡምም፡፡ በአንድ መንገድ እየተጓዙ ይገፋፉሉ፡፡ አንድ ቦታ እየሠሩ፣ ይነጣጠቃሉ፡፡ ብዙዎቹ ማኅተም እንጂ ራእይ የላቸውም፡፡ አባል እንጂ ዓላማ ይጎድላቸዋል፡፡ የትኛውን ገዳም እንደሚረዱ እንጂ የትኛውን ችግር እንደሚፈቱ አያውቁም፡፡

ሕዝቡ እነርሱን ተስፋ አድርጎ እንዲቀመጥ አደረጉት፡፡ ለጥያቄዎች መልስ፣ ለችግሮች መፍትሔ፣ ለጨለማው ብርሃን ከእነርሱ ይጠብቃል፡፡ እነርሱ ደግሞ «ሀ- ራስክን አድን» ብለው በራሳቸው አጀንዳ ተጠምደዋል፡፡ «ቤተ ክርስቲያናችን» ማለት ትተው «ማኅበራችን» ማለት ጀምረዋል፡፡ «የቤተ ክርስ ቲያናችን ልጅ» መባሉ ቀርቶ «የማኅበራችን ልጅ» ሆኗል ቋንቋቸው፡፡

ቤተ ክህነቱን ያስተካክላሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ቤተ ክህነቶች ሆነዋል፡፡ አሠራርን ያስተካክላሉ ሲባሉ እነርሱ ራሳቸው በተወሳሰበ፣ ግልጽነት በጎደለው እና ኋላ ቀር በሆነ አሠራር ተተብትበዋል፡፡ የገንዘብ አያያዛቸው፣ የርዳታ አሰጣጣቸው፣ የአባላት አመዘጋገባቸው፣ የሪፖርት አቀራረባቸው፣ የፋይል አያያዛቸው፣ የዶክመንት አደረጃጀታቸው፣ የስብሰባ አካሄዳቸው ከቤተ ክህነቱ የባሰ ሆነዋል፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተገላገሉትን ቢሮክራሲ እነርሱ ወሰዱት፡፡ ለጉባኤ እና ለድግስ ብሎም ሞቅታ ላለበት ተግባር እንጂ ለአገልግሎት የሰነፉ አባላት መናኸርያ እየሆኑ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ፈተና ማኅበራት ካልነበሩበት ዘመን ይልቅ በበዙበት ዘመን ብሷል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ቦታ የያዙት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ሐውልት መቆም የጀመረው፣ የፎቶ ፖስተር በዐውደ ምሕረት የተሰቀለው፤ የቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ትምህርት በዐውደ ምሕረት መሰጠት የጀመረው፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ተዳክሞ ግለሰቦች ቦታውን መያዝ የጀመሩት በማኅበራት ዘመን ነው፡፡

አንጀቴ ተቆርጦ ከሆዴ ከወጣ

ከንግዲህ ሐኪሙ ምን ሊቀጥል መጣ

አንድ ሰው የችግሩም የመፍትሔውም አካል መሆን አይችልም፡፡ መጀመርያ የችግሩ አካል ከመሆን መላቀቅ መቻል አለበት፡፡ አንድ ሐኪም ለአንድ በሽተኛ መድኃኒት የሚያዝዘው እንዲያድነው ወይንም እነዲያሸለው እንጂ እንዲገድለው መሆን የለበትም፡፡ ቀዶ ጥገና ያደረገ ሐኪም ቀጥሎ ኢንፌክሽን እንዳይከተል መከላከልም አለበት፡፡

በደርግ ዘመን ኮሚቴ በዝቷል ይቀነስ ሲባል ኮሚቴ የሚቀንስ ሌላ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነ እየተባለ የሚተረተው ቀልድ ቀልድ ብቻ አይደለም፡፡ የተሰጠው መፍትሔ ችግሩን የሚጨምር እንጂ የሚፈታ አለመሆኑን የሚያሳይም ነው፡፡

አሁንም የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለመፍታት ተብለው የመጡ መፍትሔዎች እና የተቋቋሙ አካላት በራሳቸው መታየት አለባቸው፡፡ በርግጥ እነዚህ መንገዶች እና አካላት ችግር ጨምረዋል ወይስ መፍትሔ አምጥተዋል? እነርሱ ራሳቸውም ራሳቸውን ማየት አለባቸው፡፡ ምንድን ነው ያመጣነው ለውጥ? ካለመ ኖራችን መኖራችን ምን ይጠቅማል? የቆምነው በትክክለኛው መንገድ ላይ ነውን? ብለን መጠየቅ አለ ብን፡፡ እስኪ 2003 ዓም ከመምጣቱ ወይንም ከማለፉ በፊት ከላይ የተጠቀስነው አካላት ራሳችንን እንመርምር፤ በተለይም አመራሮቹ ወይምን ዋና ዋናዎቹ አሁን የምንሄድበትን መንገድ ከወቅቱ ችግሮች እና ተግዳሮቶች አንፃር እንመዝነው፤ ከዚያም ችግር ሳይሆን መፍትሔ የሚያደርገንን አቅጣጫ እንተልም፡፡ ያለበለዚያ ግን ምንን ምን ቢመራው ሁለቱም ወደ ገደል ይሄዳሉ የተባለው ይፈጸምብናል፡፡